፭ ለሰውዮው ፡ አትታዩው ። በተኛም ፡ ጊዜ ፡ የሚተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ተመልከቺ ÷ ገብተ ሽም ፡ እግሩን ፡ ግለጪ ÷ ተጋደሚም ፡ የምታ ፮ ደርጊውንም ፡ እርሱ ፡ ይነግርሽል ። ሩትም ፡ — የተናገርሽኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለቻት ። ፯ ወደ ፡ አውድማውም ፡ ወረደች ÷ እማት ዋም ፡ ያዘዘቻትን ፡ ሁሉ ፡ አደረገች ። በሌዝም ፡ ፰ ከበላና ፡ ከጠጣ ፡ ሰውነቱንም ፡ ደስ ፡ ካሰኘ ፡ በኋላ ÷ በእህሉ ፡ ክምር ፡ አጠገብ ፡ ሊተኛ ፡ ሄደ ፡ ሩትም ፡ በቀስታ ፡ መጣች ÷ እግሩንም ፡ ፱ ገልጣ ፡ ተኛች ። መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ደንገጠ ÷ ዘወርም ፡ አለ ፤ እነ ሆም ÷ እንዲት ፡ ሴት ፡ በእግርጌው ፡ ተኝታ ፲ ነበረች ። እርሱም ፡ — ማን ፡ ነሽ ? አለ ። እርስ ዋም ፡ — እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ሩት ፡ ነኝ ፡ ዋርሳዉ ፡ ነህና ፡ ልብስህን ፡ በባሪያህ ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ፡ አለችው ። ፲ በሌዝም ፡ አለት ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ የተባረክሽ ፡ ውኂ ፤ በለጠጋም ፡ ድህም ፡ ብለሽ ፡ ጉበዛዝትን ፡ አልተከተልሽምና ፡ ከፊ ፲፩ ተኛው ፡ ይልቅ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ቸርነት ፡ አድርገሻል ። አሁንም ÷ ልጄ ፡ ሆይ ÷ አትፍሪ ፡ በአገሬ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ምግባረ ፡ መል ፲፪ ካም ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ሆንሽ ፡ ያውቃሉና ፡ ይሁን ፡ እው ንን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደርግልሻለሁ ። የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ መሆኔ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፲፫ ከእኔ ፡ የቀረበ ፡ ዘመድ ፡ አለ ። ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ አደሪ ፡ ነገም ፡ እርሱ ፡ ዋርሳ ፡ መሆን ፡ ቢወድድ ፡ መልካም ፡ ነው ÷ ዋርሳ ፡ ይሁን ፤ ዋርሳ ፡ ቢሆን ፡ በይወድድ ፡ ግን ÷ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፤ እኔ ፡ ዋርሳ ፡ እሆንሻለሁ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ተኚ ። ፲፬ እስኪነጋም ፡ በእግርጌው ፡ ተኛች ፡ በሌዝም ፡ — ሴት ፡ መደ ፡ አውድማው ፡ እንደ ፡ መጣች ፡ ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ገና ፲፭ ስውና ፡ ሰው ፡ ላይተያይ ፡ ተነግች ። እር ሱም ፡ — የለበስሽውን ፡ ኩታ ፡ አምጥተሽ ፡ ያዢው ፡ አላት ፤ በያዘችም ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰፈረሳት ፡ አሸከማትም ። ፲፮ እርሱም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ሄደ ። ወደ ፡ አማ ትዋም ፡ መጣች ÷ እማትዋም ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ÷ እንዴት ፡ ነሽ ? አለቻት ፡ እርስዋም ፡ ሰውዮው ፲፯ ያደረገላትን ፡ ሁሉ ፡ ነገረቻት ። ወደ ፡ አማ ትሽ ፡ ባዶ ፡ እጅሽን ፡ አትሂጂ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፲፰ ስድስት ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰጠኝ ፡ አለቻት ። እር ስዋም ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ÷ ሰውዮው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዛሬ ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ አያርፍምና ፡ ፍጻ ሜው ፡ እስኪ ፡ታወቅ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ በዪ ፡ አለች ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ በሌዝም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ በር ፡ አደሰሰይ ፡ ወጥቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ። እነሆም ÷ በሌዝ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ይናገር ፡ የነበረው ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ሲያልፍ ፡ በሌዝ ፡ — እንተ ፡ ቀርበህ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፤ አለው ። እርሱም ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ተቀ ፪ መጠ ። በሌዝም ፡ ከከተማይቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ ጠርቶ ፡ — በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ተቀመጡ ። በሌዝም ፡ ፫ የቅርብ ፡ ዘመዱን ፡ — ከሞዓብ ፡ ምድር ፡ የተመ ለሰችው ፡ ኑኃሚን ፡ የወንድማችንን ፡ የአቤሜ ሌክን ፡ ጢንዶ ፡ ትሸጣለች ። እኔም ፡ በዚህ ፡ ፬ በተቀመጡት ፡ በሕዝቤ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ እንድትገዛው ፡ አስታውቅህ ፡ ዘንድ ፡ አሰብሁ ። መቤዠት ፡ ብትወድድ ፡ ተቤዠው ፡ መቤዠት ፡ በተወድድ ፡ ግን ፡ ከእንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መራሽ ፡ የለምና ÷ እኔም ፡ ከእንተ ፡ ፭ቀኋ ፡ ነኝና ፡ እንዳ ውቀው ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። እርሱም ፡ — እቤዠ ዋለሁ ፡ አለው ። በሌዝም ፡ — እርሻውን ፡ ከኑ ፮ ኃሚን ፡ እጅ ፡ በምትገዛበት ፡ ቀን ÷ ለሞተው ፡ በርስቱ ፡ ስሙን ፡ እንድታስነሣለት ፡ ከም ዋቹ ፡ ሚስት ፡ ከሞኣስዊቱ ፡ ከሩት ፡ ደግሞ ፡ ትገዛለህ ፡ አለ ። የቅርብ ፡ ዘመዱም ፡ — የራሴን ፡ ርስት ፡ ፯ እንዳላበላሽ ፡ መቤዠት ፡ አልችልም ፤ እኔ ፡ መቤዠቱን ፡ አልችልምና ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡ መቤ ዠቱን ፡ ውሰደው ፡ አለ ።

፰ በጥንት ፡ ጊዜም ÷ ማንም ፡ ቢሸጥ ፡ ቢለው ጥም ፡ ነገሩን ፡ ለማጽናት ፡ ሰው ፡ ጫማውን ፡ እንዲያወልቅ ፡ ለባልንጀራውም ፡ እንዲሰጠው ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በእ ፱ስራኤል ፡ ምስክር ፡ ነበረ ። የቅርብ ፡ ዘመዱም ፡ በሌዝን ፡ — አንተ ፡ ግዛው ፡ አለው ፡ ጫማው ፲ንም ፡ አወለቀ ። በሌዝም ፡ ሽማግሌዎችንና ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ — ለአቢሜሌክና ፡ ለኬሌዎን ፡ ለመሐሎንም ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ከኑኃሚን ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ገዛሁ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ። ደግሞም ፡ የምዋቹ ፡ ስም ፡ ከወንድ ፲፩ ሞቹ ፡ መካከል ፡ ከእገሩም ፡ ደጅ ፡ እንዳይጠፋ ፡ የምዋቹን ፡ ስም ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ እንዳስነሣ ፡ የመሐሎንን ፡ ሚስት ፡ ሞዓባዊቱን ፡ ሩትን ፡ ሚስት ፡ ተገቢኝ ፡ ዘንድ ፡ መሰይሁት ፤ እና ንተም ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ፡ አላቸው ። ፲፪ በከተማይቱ ፡ በር ፡ እደበሰይም ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ — እኛ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤ እግዚአብሔር ፡ ይሠችን ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ የም ገባውን ፡ ሴት ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ እንደ ፡ ሁለቱ ፡ እንደ ፡ ራሔልና ፡ እንደ ፡ ልያ ፡ ያድርጋት ፡ አንተም ፡ በኤፍራታ ፡ በለ ጠጋ ፡ ሁን ÷ ስምህም ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ይጠራ ። ፲፫ ቤትህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚህች ፡ ቈንጆ ፡ ከሚ ሰጥህ ፡ ዘር ፡ ትዕማር ፡ ለይሁዳ ፡ እንደ ፡ ወለደ ችው ፡ እንደ ፡ ቁፌስ ፡ ቤት ፡ ይሁን ፡ አሉት ።

፲፬ በሌዝም ፡ ሩትን ፡ ወሰደ ÷ ሚስትም ፡ ሆነ ችው ። ደረሰባትም ÷ እግዚአብሔርም ፡ ፅንስ ፡ ሰጣት ÷ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ። ሴቶችም ፡ ኑኃሚንን ፡ — ዛሬ ፡ ዋርሳ ፡ ያላሳሣሽ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ይጠረክ ፡ ስሙም ፡ በእስራኤል ፡ ይጠራ ። ፲፭ ከበበችም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ለእንቺ ፡ ከምትሻል ፡ ከምትወድድሽ ፡ ምራት ፡ ተወል ዶአልና ፡ ለውኑትሽን ፡ ያሳደሰዋል ÷ በእርጅና ፲፮ ሽም ፡ ይመግብሻል ፡ አሉአት ። ኑኃሚንም ፡ ልጁን ፡ አቅፋችውም ÷ ሞግዚትም ፡ ሆነችው ። ሰቶችም ፡ ጎረቤቶችዋ ፡ ለኑኃሚን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደላት ፡ አሏት ፡ ስሙንም ፡ ኢዮቤድ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ። ፲፯ እርሱም ፡ የዳዊት ፡ አባት ፡ የእሴይ ፡ አባት ፡ ነው ። ፲፰ የፋሬስም ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ፋሬስ ፡ ኤስሮምን ፡ ወለደ ÷ ኤስሮምም ፡ አራምን ፡ ፲፱ ወለደ ÷ አራምም ፡ አሚናዳብን ፡ ወለደ ÷ አሚ ፳ ናዳብም ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ÷ ነአሶንም ፡ ሰል ሞንን ፡ ወለደ ÷ ሰልሞንም ፡ በዔዝን ፡ ወለደ ÷ ፳፩ በዔዝም ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ÷ ኢዮቤድም ፡ ፳፪ እሴይን ፡ ወለደ ÷ እሴይም ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ።

(እርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ።)

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ከአርማ ቴም ፡ መሌፋ ፡ የሆነ ፡ ሰሙ ፡ ሕልቃና ፡ የተባለ ፡ ኤፍሬማዊ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ እርሱም ፡ የኢ.ያሬም ፪ ኤል ፡ ልጅ ፡ የኢ.ሪኮ ፡ ልጅ ፡ የቶሑ ፡ ልጅ ፡ የናሲብ ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ሁለትም ፡ ሚስቶች ፫ ነበሩት ፡ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ሐና ፡ የሁለተኛዪ ቱም ፡ ስም ፡ ፍናና ፡ ነበረ ፡ ለፍናናም ፡ ልጆች ፬ ነበሩአት ÷ ለሐና ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አልነበራትም ። ፭ ያም ፡ ሰው ፡ በሌሙ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ለሠራ ዊት ፡ ጌታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ከከተማው ፡ በየዓመቱ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። የእግ ዚአብሔርም ፡ ካህናት ፡ ሁለቱ ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡ ፮ እፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ። ሕልቃና ፡ የሚሠዋበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜም ፡ ለሚስቱ ፡ ለፍናና ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ ፯ እድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ሰጣቸው ። ሐናንም ፡ ይመ ድድ ፡ ነበርና ፡ ለሐና ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ሰጣት ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ማኅፀን ፰ ዋን ፡ ዘግቶ ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡ ማኅፀ ንዋን ፡ ዘግቶ ፡ ነበርና ፡ ጣውንትዋ ፡ ታስቈጣት ፡ ታበሳጫትም ፡ ነበር ። በየዓመቱም ፡ እንዲህ ፱ በደረገ ፡ ጊዜ ፡ እርስዋም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምትወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ታበሳጫት ፡ ነበር ። ሐናም ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ÷ እንዳችም ፡ እትቀም ፲ ስም ፡ ነበር ። በልዋም ፡ ሕልቃና ፡ — ሐና ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ ? ለምንስ ፡ እትቀም ሽም ? ለምንስ ፡ ልብሽ ፡ ያዝንብሻል ? እኔስ ፡ ከአሥር ፡ ልጆች ፡ እልሻልሽምን ? አላት ።

፱ በሴሎ ፡ ከበሉና ፡ ከጠጡ ፡ በኋላም ፡ ሐና ፡ ተነሣች ። ከዙኮ ፡ ዔሊ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መቃን ፡ አጠገብ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ፲ ተቀምጦ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ በልብዋ ፡ ትመ ረር ፡ ነበር ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ጸሰየች ÷ ፲፩ ጽኑ ፡ ልቅሶም ፡ አለቀሰች ። እርስዋም ፡ — አቤቱ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ÷ የባሪያህን ፡ መዋረድ ፡ ተመልከተህ ፡ ብታስበኝ ፤ አንተም ፡ በትረሰ ፡ ለባሪያህም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ብትሰጥ ÷ ዕድሜውን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጠዋ ለሁ ÷ ምላጭም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አይደርስም ፡ ብላ ፡ ስእለት ፡ ተሰለች ።

፲፪ ጸሎትዋንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሰ ፵ች ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ አፍዋን ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። ፲፫ ሐናም ፡ በልብዋ ፡ ትናገር ፡ ነበር ፤ ድምፅዋም ፡ ሳይሰማ ፡ ከንፈርዋን ፡ ታንቀሳቅስ ፡ ነበር ፤ ፵ ዔሊም ፡ እንደ ፡ ሰከረች ፡ ቈጠራት ። ዔሊም ፡ — ስከርሽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? የወይን ፡ ጠጅ ፲፭ ሽን ፡ ከእንቺ ፡ አርቂው ፡ አላት ። ሐናም ፡ — ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አይደለም ÷ እኔስ ፡ ልብዋ ፡ ያዘ ንበት ፡ ሴት ፡ ነኝ ፤ ጠጅና ፡ ሌላ ፡ የሚያሰክር ፡ ነገር ፡ አልጠጣሁም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ በእግዚአብ ፲፮ ሔር ፡ ፊት ፡ ነፍሴን ፡ አፈሰስሁ ፤ ጎስኔና ፡ ጭን ቀቴ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ተናግሬ ፲፯ አለሁና ፡ ባሪያህን ፡ እንደ ፡ ምናምንቴ ፡ ሴት ፡ አት ቍጠረኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ። ዔሊም ፡ — በደ ኅና ፡ ሂጂ ÷ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የለመን ፲፰ ሽውን ፡ ልመና ፡ ይስጥሽ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ። እርስዋም ፡ — በሪያህ ፡ በዓይንህ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለች ። ሴቲቱም ፡ መንገድዋን ፡ ሄደች ፡ በላችም ÷ ፊትዋም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አዘ ንተኛ ፡ መሰሉ ፡ አልታየም ።

፲፱ ማልደው ፡ ተነሥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰገዱ ÷ ተመልሰውም ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ መጡ ። ሕልቃናም ፡ ሚስ ቱን ፡ ሐናን ፡ አወቃት ÷ እግዚአብሔርም ፡ አሰበት ፡ የመሰነበዋም ፡ ወራት ፡ ከሰፈ ፡ በኋላ ፡ ሐና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ። እርስዋም ፡ — ከእግዚአብሔር ፡ ለምኜዋለሁ ፡ ስትል ፡ ሰሙኤል ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

፳ ሰውዮውም ፡ ሕልቃና ፡ ነዜት ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ፳፩ ጋር ፡ የዓመቱን ፡ መሥዋዕትና ፡ ስእለቱን ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ። ሐና ፡ ፳፪ ግን ፡ አልወጣችም ÷ ባልዋንም ፡ — ሕፃኑ ፡ ጡት ፡ እስኪ ፡ ተው ፡ ድረስ ፡ እቀመጣለሁ ፡ ከዚ ያም ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ÷ ለዘላለም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እመጣዋለሁ ፡ አለችው ። ባልዋም ፡ ሕልቃና ፡ — ፳፫ በዓይንሽ ፡ ደስ ፡ ያሰኘሽን ፡ አድርጊ ፡ ጡትም ፡ እስኪ ተው ፡ ድረስ ፡ ተቀመጪ ። ብቻ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ቃሉን ፡ ያጽና ፡ አለት ። ሴቲቱም ፡ ልጅዋን ፡ እያጠባች ፡ ጡት ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ በዚትዋ ፡ ተቀመጠች ። ጡትም ፡ በተው ፡ ጊዜ ፡ ፳፬ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ እርሱንና ፡ አንድ ፡ የሦስት ፡

ዓመት ፡ ወደፈን ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዳቁት ፡ አንድ ፡ አቁማዳ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አመጣችው ፡ ሕፃኑም ፡ ገና ፡ ታናሽ ፡ ነበረ ።
፳፭ ወይፈኑንም ፡ አረዱ ፡ ሕፃኑንም ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡
፳፮ አመጡት ። እርስዋም ፡ አለች ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በሕያው ፡ ነፍስህ ፡ እምሳስሁ ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመጸለይ ፡ በዚህ ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ቆማ ፡ የነበረች ፡ ሴት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፳፯ ስለዚህ ፡ ሕፃን ፡ ጸለይሁ ፤ እግዚአብሔርም ፡
፳፰ የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ሰጥቶኛል ። እኔም ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥቼዋለሁ ፡ ዕድሜውን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ሐናም ፡ ስትጸልይ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፡ —
ልቤ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸና ፡
ቀንዴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡
አፌ ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ተከፈተ ፡
በማዳንህ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።
፪ እንደ ፡ እግዚአብሬ ፡ ቅዱስ ፡ የለምና ፡
እንደ ፡ አምላክንህም ፡ ጻድቅ ፡ የለምና ፡
ከአንተ ፡ በቀር ፡ ቅዱስ ፡ የለም ።
፫ አትታበዩ ፡ በኩራትም ፡ አትናገሩ ፡
እግዚአብሔር ፡ አዋቂ ፡ ነውና ፡
እግዚአብሔርም ፡ ሥራውን ፡ የሚመዝን ፡ ነውና ፡
ከአፋችሁ ፡ የኵራት ፡ ነገር ፡ አይውጣ ።
፬ የኃያላንን ፡ ቀስት ፡ ሰብሮአል ፡
ደከሞችም ፡ በኃይል ፡ ታጥቀዋል ።
፭ ጠግበው ፡ የነበሩ ፡ እንጀራ ፡ አጡ ፡
ተርበው ፡ የነበሩ ፡ ከራብ ፡ ዐርፈዋል ፡
መከኒቱ ፡ ሰባት ፡ ወልዳለችና ፡
ብዙም ፡ የወለዶችው ፡ ደክማለች ።
፮ እግዚአብሔር ፡ ይገድላል ፡ ያድናልም ፡
ወደ ፡ ሲኤል ፡ ያወርዳል ፡ ያወጣል ።
፯ እግዚአብሔር ፡ ድሀ ፡ ያደርጋል ፡ ባለጠጋም ፡ ያደርጋል ፡
ያዋርዳል ፡ ደግሞም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።
፰ ከሕዝቡ ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ ያስቀምጣቸው ፡ ዘንድ ፡
የክብርንም ፡ ዙፋን ፡ ያወርሰቸው ፡ ዘንድ ፡
ችግረኛውን ፡ ከመሬት ፡ ያስነሣል ፡
ምስኪኑንም ፡ ከጉድፍ ፡ ያስነሣል ፡
የምድር ፡ መሠረቶች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ናቸውና ፡
በእነርሱ ፡ ላይም ፡ ዓለምን ፡ አደረገ ።
፱ እርሱ ፡ የቅዱሳኑን ፡ እግር ፡ ይጠብቃል ፡
ኃጥኣን ፡ ግን ፡ ገሃም ፡ ብለው ፡ በጨለማ ፡ ይቀመጣሉ ፡
ሰው ፡ በኃይሉ ፡ አይበረታምና ።
፲ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ የሚጣሉ ፡ ይደቅ

ቃሉ ፡
በሰማይም ፡ ያንጐደጕድባቸዋል ፡
እግዚአብሔር ፡ አስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡
ይፈርዳል ፤
ለንጉሡም ፡ ኃይል ፡ ይሰጣል ፡
የመሲሑንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

፲፩ ሕልቃናም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ሄደ ፤ ብላቴናውም ፡ በካህኑ ፡ በዔሊ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግል ፡ ነበር ።
፲፪ የዔሊ ም ፡ ልጆች ፡ ምናምንቴዎች ፡ ነበሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ።
፲፫ የካህናትም ፡ ልማድ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መሥዋዕት ፡ ሲያቀርብ ፡ ሥጋው ፡ በተቀቀለ ፡ ጊዜ ፡ የካህኑ ፡ ሱሌ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ፡ በእጁም ፡ ሦስት ፡ ጣት ፡ ያለው ፡ ሜንሶ ፡ ነበረ ፤
፲፬ ወደ ፡ ድስቱም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ምንቸቱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አፍላሉ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቶፋው ፡ ይሰድደው ፡ ነበር ፤ ሜንሶውም ፡ ያወጣውን ፡ ሁሉ ፡ ካህኑ ፡ ለእርሱ ፡ ይወስደው ፡ ነበር ። ወደዚያም ፡ በመጡት ፡ በእስራኤላውያን ፡ ላይ ፡ በሴሎ ፡ እንዲህ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።
፲፭ ደግሞም ፡ ስቡን ፡ ሰያቃጥሉ ፡ የካህኑ ፡ ሱሌ ፡ መጥቶ ፡ የሚሠዋውን ፡ ሰው ፡— ጥሬውን ፡ እንጂ ፡ የተቀቀለውን ፡ ሥጋ ፡ ከእንቀ ፡ አይወስድምና ፡ እጠብስለት ፡ ዘንድ ፡ ለካህኑ ፡ ሥጋ ፡ ስጠኝ ፡ ይለው ፡ ነበር ።
፲፮ ሰውዮውም ፡— አስቀድሞ ፡ ስቡን ፡ ያቃጥሉት ፡ ኋላም ፡ ሰውነትህ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘትን ፡ ትወስዳለህ ፡ ቢሉው ፡ አርሱ ፡— አይሆንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ስጠኝ ፡ እንጂም ፡ ብትል ፡ በግድ ፡ እወስደዋለሁ ፡ ይለው ፡ ነበር ።
፲፯ ሰዎቹም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍርባን ፡ ይንቁ ፡ ነበርና ፡ የጉበዛዝቱ ፡ ኃጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ።
፲፰ ሰሙኤል ፡ ግን ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሰሰ ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ ሰብሶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያገለግል ፡ ነበር ።
፲፱ እናቱም ፡ ታናሽ ፡ መደረቢያ ፡ ሠራችለት ፡ በየዓመቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ለመሥዋት ፡ ከባልዋ ፡ ጋር ፡ ስትወጣ ፡ ታመጣለት ፡ ነበር ።
፳ ዔሊም ፡ ሕልቃናንና ፡ ሚስቱን ፡— ለእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ተሰለችው ፡ ስጦታ ፡ ፋንታ ፡ ከዚህች ፡ ሴት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘር ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ ባረካቸው ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ።
፳፩ እግዚአብሔርም ፡ ሐናን ፡ አሰበ ፡ ፀነሰ ፡ ሦስት ፡ ወንዶችና ፡ ሁለትም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለደች ። ብላቴናውም ፡ ሰሙኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አደገ ።
፳፪ ዔሊም ፡ እጅግ ፡ አረጀ ፡ ልጆቹም ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ሁሉ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጅ ፡ ከሚያገለግሉት ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተኙ ፡ በማ ፡ እርሱም ፡ አሳትው ፡— ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ሰምቻለሁና ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔ

ርን ፡ ሕዝብ ፡ ኃጢአተኛ ፡ በማድረጋችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የደረሰኝ ፡ ወሬ ፡ መልካም ፡ አይደለ
፳፫ ምና ፡ ይህ ፡ አይሆንም ። ሰውስ ፡ ሰውን ፡ ቢበድል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድበታል ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እግዚአብሬን ፡ ቢበድል ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የሚለምን ፡ ማን ፡ ነው ? እነርሱ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊገድላቸው ፡ ወድዶአልና ፡ የአባታ
፳፬ ቸውን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ። ብላቴናውም ፡ ሰሙኤል ፡ እያደገ ፡ ሄደ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ በሰውም ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ እያገኘ ፡ ሄደ ።
፳፭ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡ መጥቶ ፡ አለው ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በግብጽ ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ ባሪያ ፡ ሰሰ ፡ ለአባ
፳፮ ትህ ፡ ቤት ፡ ተገለጥሁ ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ካህን ፡ ይሆንኝ ፡ ዘንድ ፡ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ዕጣንንም ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ ኤፉድንም ፡ በፊቴ ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ ለአባ ፡ መረጥሁት ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ የእሰት ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ ሰሰ ፡ ምግብ ፡ ለአባትህ ፡ ቤት ፡
፳፰ ሰጠሁ ። በማደሪያዬ ፡ ያቀርቡት ፡ ዘንድ ፡ ያዛ ዝሁትን ፡ መሥዋዕቴንና ፡ ቍርባኔን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ረገጣችሁ ? እንድትወፍሩም ፡ የእስ ራኤልን ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በመ ብላታችሁ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ልጆችህን ፡ ሰምን ፡
፳፱ አከበርህ ? ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእውነት ፡ ቤትህ ፡ የአባትህም ፡ ቤት ፡ ለዘላለም ፡ በፊቴ ፡ እንዲኖር ፡ ተናግሬአለሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ያከበሩኝን ፡ እከ ብራለሁና ፡ የናቁኝም ፡ ይናቃሉና ፡ ይህ ፡ እይ
፴፩ ዞንልኝም ። እነሆ ፡ ለቤትህ ፡ ኀይማሌ ፡ እንዳ ይገኝ ፡ ክንድህን ፡ የአባትህንም ፡ ቤት ፡ ክንድ ፡
፴፪ የምሰብርበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ። በእስራኤል ፡ በረከት ፡ ሁሉ ፡ በማደሪያዬ ፡ ጠላትህን ፡ ታያ ለህ ፡ በቤትህም ፡ ለዘላለም ፡ ኀይማሌ ፡ አይገ
፴፫ ኝም ። ከመሠዊያዬ ፡ ያልተቈረጠ ፡ ልጅህ ፡ ቢገኝ ፡ ዓይንህን ፡ ያፈዝዝዋል ፡ ነፍስህንም ፡ ያሰ ዝናል ፡ ከቤትህም ፡ የሚወለዱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
፴፬ በጕልማኒነት ፡ ይሞታሉ ። ይህ ፡ በሁለቱ ፡ ልጆችህ ፡ በአፍኒንና ፡ በፊንሐስ ፡ ላይ ፡ የሚመጣ ፡ ለአንተ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ሁለቱ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡
፴፭ ይሞታሉ ። የታመነም ፡ ካህን ፡ ለእኔ ፡ አሰኘሳለሁ ፡ በልቤም ፡ በነፍሴም ፡ እንዳለ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ፤ እኔም ፡ የታመነ ፡ ቤት ፡ አሠራለታ ለሁ ፡ ዘመኑን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ በቀባሁት ፡ ሰው ፡
፴፮ ፊት ፡ ይሄዳል ። ከቤትህም ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ይመጣል ፡ በፊቱም ፡ ሰግዶ ፡— ቍራሽ ፡ እን ጀራ ፡ እበላ ፡ ዘንድ ፡ ከክህናት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሰማ ፡ እባክህ ፡ ስደደኝ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ አንድ ፡ እንጀራም ፡ ይለምናል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ብላቴናውም ፡ ሰሙኤል ፡ በዔሊ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግል ፡ ነበር ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡

ያሰኘውን ፡ ያድርግ ፡ አለ ።

፲፱ ሳሙኤልም ፡ አደገ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከአ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ ከቃሉም ፡ አንዳች ፡ በም
፳ ድር ፡ ላይ ፡ አይወድቅም ፡ ነበር ። አስራኤልም ፡
ሁሉ ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ድረስ ፡ ሰሙ
ኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ያሆን ፡ ዘንድ ፡
፳፩ የታመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀ ። እግዚአብሔ
ርም ፡ ደግሞ ፡ በሴሎ ፡ ተገለጠ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለሳሙኤል ፡
በሴሎ ፡ ይገለጥ ፡ ነበር ። የሳሙኤልም ፡ ቃል ፡
ለአስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ይረሰ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ አስራኤልም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋር ፡
ሊዋጉ ፡ ወጡ ፡ በአቤንኤዘር ፡ አጠገብ ፡ ሰፈሩ ፡
፪ ፍልስጥኤማውያንም ፡ በአፌቅ ፡ ሰፈሩ ። ፍል
ስጥኤማውያንም ፡ በአስራኤል ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ፡
ሰልፉም ፡ በተመደበ ፡ ጊዜ ፡ አስራኤል ፡ በፍል
ስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ተመቱ ፡ ጦርነት ፡ በተ
ደረገበትም ፡ ሰፍራ ፡ ከአስራኤል ፡ አራት ፡ ሺህ ፡
፫ የሚያህሉ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ። ሕዝቡም ፡ ወደ ፡
ሰፈር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የአስራኤል ፡ ሽማግሌ
ዎች ፡ — ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍልስጥኤማ
ውያን ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መታን ? በመከከለ
ችን ፡ እንዳጄድ ፡ ከጠላቶቻችንም ፡ እጅ ፡ እን
ዳያድነን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡
፬ ታቦት ፡ ከሴሎ ፡ እናምጣ ፡ አሉ ። ሕዝቡም ፡
ወደ ፡ ሴሎ ፡ ላኩ ፡ በኪሩቤልም ፡ ላይ ፡ የሚቀ
መጠውን ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔ
ርንሥቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ አመጡ ፡
ሁለቱም ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ጋር ፡
በዚያ ፡ ነበሩ ።

፭ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡
ወደ ፡ ሰፈር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ታላቅ ፡ አልልታ ፡ አደረጉ ፡ ምድሪቱም ፡ አስተ
፮ ጋበች ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ የአልልታውን ፡
ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ — በዕብራውያን ፡ ሰፈር ፡
ያለው ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ የአልልታ ፡ ድምፅ ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? አሉ ። የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡
፯ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ አስተዋሉ ። ፍልስ
ጥኤማውያንም ፡ ፈርተው ፡ — እግዚአብሔ ፡
ወደ ፡ ሰፈር ፡ መጥቶአል ፡ አሉ ። ደግሞም ፡
እንዲህ ፡ አሉ ፡ — ወዮልን ፤ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡
፰ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አልሆነም ። ወዮልን ፤ ከእነ
ዚህ ፡ ከኃያላን ፡ አማልክት ፡ እጅ ፡ ማን ፡ ያድን
ናል ? እነዚህ ፡ አማልክት ፡ ግብጻውያንን ፡ በም
ድረ ፡ በዳ ፡ በልቁ ፡ በልዩ ፡ መቅሠፍት ፡ የመቱ ፡
፱ ናቸው ። እናንተ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሆይ ፡ ጽ
እዘአችሁ ፡ ጐብዙ ፡ እናንተ ፡ በሪያዎች ፡ እን
ዳይረ ጋችኋቸው ፡ ዕብራውያን ፡ በሪያዎች ፡ እን
፲ ዳያደርጉአችሁ ፡ ጐብዙ ፡ ተዋጉ ። ፍልስጥኤ
ማውያንም ፡ ተዋጉ ፡ እስራኤልም ፡ ተመቱ ፡
ሁሉም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ሸሹ ፡
እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ግድያ ፡ ሆነ ፡ ከአስራኤልም ፡
፲፩ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ እግረኞች ፡ ወደቁ ። የእግዚአብ
ሔርም ፡ ታቦት ፡ ተማረከች ፡ ሁለቱም ፡ የዔሊ ፡
ልጆች ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ ሞቱ ።

፲፪ በዚያም ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የብንያም ፡ ሰው ፡ ከሰ
ልፍ ፡ አየበረረ ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡ በራሱም ፡
፲፫ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ መጣ ። በመ
ጣም ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡
ልቡ ፡ ተናውጦ ፡ ነበርና ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ በወ
ንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ሰው
ዮውም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ገብቶ ፡ በወረ ፡
፲፬ ጊዜ ፡ ከተማይቱ ፡ ሁሉ ፡ ተጮኾአልቻች ።
ዔሊም ፡ የጩኸቱን ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ —
፲፭ ይህ ፡ ጫጫታ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። ሰውዮ
ውም ፡ ፈጥኖ ፡ መጣና ፡ ለዔሊ ፡ ነገረው ።
ዔሊም ፡ የዘጠና ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፡
፲፮ ነበረ ፡ ዓይኖቹም ፡ ማየት ፡ አስከ ፡ ጨናቸው ።
ሰውዮውም ፡ ለዔሊ ፡ እኔ ፡ ከሰልፍ ፡ የመጣሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ዛሬም ፡ ከሰልፍ ፡
፲፯ ኰበለልሁ ፡ አለ ። እርሱም ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ፡
ነገሩስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? አለው ። መልእክተ
ኛውም ፡ መልሶ ፡ — አስራኤል ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡
ፊት ፡ ሸሹ ፤ ደግሞ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
ግድያ ፡ ሆኖአል ፡ ሁለቱም ፡ ልጆችህ ፡ አፍኒ
ንና ፡ ፊንሐስ ፡ ሞተዋል ፡ የእግዚአብሔርም ፡
፲፰ ታቦት ፡ ተማርካለች ፡ አለ ። ሰውዮውም ፡ ስለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡
በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ ከወንበሩ ፡ ወደቀ ፡
እርሱ ፡ ሸምግሎ ፡ ደንዝዞም ፡ ነበርና ፡ አንገቱ ፡
ተሰብሮ ፡ ሞተ ። እርሱም ፡ በአስራኤል ፡ ላይ ፡
አርባ ፡ ዓመት ፡ ፈረጅ ፡ ነበረ ።

፲፱ ምራቱም ፡ የፊንሐስ ፡ ሚስት ፡ አርግዛ ፡ ልት
ወልድ ፡ ተቃርባ ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርም ፡
ታቦት ፡ ተማረከች ፡ አንዳ ፡ ተማረከች ፡ እማትዋና ፡ ቢል
ዋም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ምጥ ፡
ደርሶባት ፡ ነበርና ፡ ተንበርክክ ፡ መለደች ። ወደ ፡
፳ ሞትም ፡ በቀረበች ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉት ፡
ሴቶች ፡ — ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወልደሻልና ፡ አትፍሪ ፡
አሉአት ። እርስዋ ፡ ግን ፡ አልመለሰችላቸውም ፤
፳፩ በልብዋም ፡ አላኖረችውም ። እርስዋም ፡ የአ
ግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ስለ ፡ ተማረከች ፡ ስለ ፡
አማትዋና ፡ ስለ ፡ ባልዋም ፡ — ክብር ፡ ከእስራ
ኤል ፡ ለቀቀ ፡ ስትል ፡ የሕፃኑን ፡ ስም ፡ — ኢ.ክ
በድ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ። እርስዋም ፡ — የእግዚ ፳፪
አብሔር ፡ ታቦት ፡ ተማርካለችና ፡ ክብር ፡ ከአ
ስራኤል ፡ ለቀቀ ፡ አለች ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡
፪ ታቦት ፡ ወሰዱ ፡ ከአቤንኤዘርም ፡ ወደ ፡ አዛጦን ፡
፫ ይዘውት ፡ መጡ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ዳጎን ፡
ቤት ፡ አገቡት ፡ በዳጎንም ፡ አጠገብ ፡ አኖሩት ።
፬ በነጋውም ፡ የአዛጦን ፡ ሰዎች ፡ ማለዱ ፡ እነ
፭ ሆም ፡ ዳጎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ በግምባሩ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ፡ ዳጎን
ንም ፡ አንሥተው ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ መለሱት ።
፮ በነጋውም ፡ ማለዱ ፡ እነሆም ፡ ዳጎን ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግ
ምባሩ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ፡ የዳጎንም ፡ ራስ ፡ እጆ
ቹም ፡ ተቈርጠው ፡ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወድ
ቀው ፡ ነበር ፤ የዳጎንም ፡ ደረት ፡ ብቻውን ፡
፯ ቀርቶ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ የዳጎን ፡ ካህናት ፡
ወደ ፡ ዳጎንም ፡ ቤት ፡ የሚገቡት ፡ ሁሉ ፡ በእዛ
ጦን ፡ ያለውን ፡ የዳጎንን ፡ መድረክ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ድረስ ፡ አይረግጡም ።

፯ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በእዛጦን ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ ከባደች ፡ አጠፋቸውም ፡ አዛጦንንና ፡
፯ ድንበራቸውንም ፡ በአበጭ ፡ መታቸው ። የአ
ዛጦንም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ አንደ ፡ ሆነ ፡ በዩ ፡
ጊዜ ፡ — እጁ ፡ በእኛና ፡ በአምላክችን ፡ በዳጎን ፡
ላይ ፡ ጠንክራለችና ፡ የአስራኤል ፡ እምላክ ፡
፰ ታቦት ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አይቀመጥ ፡ አሉ ። ልከ
ውም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ ሰበሰቡና ፡ — በአስራኤል ፡ አም
ላክ ፡ ታቦት ፡ ምን ፡ እናድርግ ? አሉ ። እነር
ሱም ፡ — የአስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡
ጌት ፡ ይዙር ፡ ብለው ፡ መለሱ ። የአስራኤል
ንም ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ወደዚያ ፡ ተሸከሙት ።
፱ ከተሸከሙትም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡
በታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ በከተማይቱ ፡ ላይ ፡ ሆነች ፤
ከታናሹም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ የከተማይ
ቱን ፡ ሰዎች ፡ መታ ፡ አብጭም ፡ መጣባቸው ።
፲ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ አስቀሎና ፡
ሰደዱት ። የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ አስ
ቀሎና ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አስቀሎናውያን ፡ —
እኛንና ፡ ሕዝበችንን ፡ ሊገድሉ ፡ የአስራኤልን ፡
አምላክ ፡ ታቦት ፡ አመጡብን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።
፲፩ በከተማይቱ ፡ ሁሉ ፡ የሞት ፡ ድንጋጤ ፡ ነበርና ፡
የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በዚያ ፡ እጅግ ፡ ከብዳ ፡
ነበረችና ፡ ልክው ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለ
ቆች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ — የእስራኤልን ፡ አም
ላክ ፡ ታቦት ፡ ይደዱ ፡ እኛንና ፡ ሕዝቦችንን ፡ እን
ዳይገድል ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይመለስ ፡ አሉ ።
፲፪ ያልሞቱትም ፡ ሰዎች ፡ በእብጭ ፡ ተመቱ ፡ የከ
ተማይቱም ፡ ዋይታ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በፍልስጥኤማው
፪ ያን ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ። ፍልስጥኤማ
ውያንም ፡ ካህናትንና ፡ ምዋርተኞችን ፡ ጠር
ተው ፡ — በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ ምን ፡
እናድርግ ? ወደ ፡ ስፍራውስ ፡ በምን ፡ እንስ
፫ ደድው ? አስታውቁን ፡ አሉ ። እነርሱም ፡ —
የአስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ብትሰድዱ ፡
የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ መልሱለት ፡ እንጂ ፡ በዶ
ውን ፡ አትሰደዱት ፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ትፈወ
ሳላችሁ ፡ እጁም ፡ ከእናንተ ፡ አለመራቁ ፡ ስለ ፡
ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃላችሁ ፡ አሉ ። እነር
ሱም ፡ — ስለ ፡ በደል ፡ መሥዋዕት ፡ የምንመል
ስለት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አሉ ። እነርሱም ፡ እን
ዲህ ፡ አሉ ፡ — አናንተንና ፡ አለቆቻችሁን ፤ ያገ
ኘች ፡ መቅሠፍት ፡ እንዲት ፡ ናትና ፡ እንደ ፡ ፍል
ስጥኤማውያን ፡ አለቆች ፡ ቍጥር ፡ እምስት ፡
የወርቅ ፡ እብጭች ፡ እምስትም ፡ የወርቅ ፡ እይ
ጦች ፡ አቅርቡ ። የእበጭችሁንም ፡ ምሰሉ ፡
፭ ምድራችሁንም ፡ የሚያጠፉትን ፡ የአይጦችን ፡
ምሰሉ ፡ አድርጋችሁ ፡ ለአስራኤል ፡ አምላክ ፡
ክብርን ፡ ስጡ ፡ እጁን ፡ ከእናንተና ፡ ከአማል
ክቶቻችሁ ፡ ከምድራችሁም ፡ ምናልበት ፡ ያቀ
ል ፡ ያሆናል ። ግብጻውያንንና ፡ ፈርዖንም ፡
፮ ልባቸውን ፡ እንዳጸኑ ፡ ልባችሁን ፡ ለምን ፡ ታጸ
ናላችሁ ? እግዚአብሔር ፡ ጎይሉን ፡ ከደረገባ
ቸው ፡ በኋላ ፡ ያወጡአቸው ፡ አይደሉምን ?
እነርሱም ፡ አልሄዱምን ? አሁንም ፡ ወስዳችሁ ፡
፯ እንዲት ፡ ሰረገላ ፡ ሥሩ ፡ የሚያጠቡም ፡ ቀን
በር ፡ ያልተጫነባቸውን ፡ ሁለት ፡ላሞች ፡ በሰ
ረገላ ፡ ጥመዱአቸው ፡ እንበሰቻቸውንም ፡ ለይ
ታችሁ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መልሱአቸው ። የአግዚ
፰ አብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ወስዳችሁ ፡ በሰረገላው ፡
ላይ ፡ እኑሩት ፡ ስለ ፡ በደልም ፡ መሥዋዕት ፡
ያቀረብችሁትን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ በሣጥን ፡
ውስጥ ፡ አድርጋችሁ ፡ በታቦቱ ፡ አጠገብ ፡ አኑ
ሩት ፡ ይሄድም ፡ ዘንድ ፡ ስደዱት ። ተመልከ
፱ ቱም ፡ በድንበሩም ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ቤትሳ
ሚስ ፡ ቢወጣ ፡ ይህን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያደ
ረገብን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እለዚያም ፡ እን
ዳያው ፡ መጥቶብናል ፡ እንጂ ፡ የመታን ፡ የአ
ርሱ ፡ እጅ ፡ እንዳልሆነ ፡ እናውቃለን ።

፲ ሰዎቹም ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ የሚያጠቡትን ፡ ፩
ሁለት ፡ ላሞች ፡ ወሰዱ ፡ በሰረገላም ፡ ጠመዱ
አቸው ፡ እንበሰቻቸውንም ፡ በቤት ፡ ዘጉባ
ቸው ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ የወርቁ ፡ ፲፩
አይጦችና ፡ የእበጭቻቸው ፡ ምሳሌ ፡ ያሉበት ፡
ንም ፡ ሣጥን ፡ በሰረገላው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ። ላሞ ፲፪
ችም ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ወደሚወስደው ፡
መንገድ ፡ አቅንተው ፡ አምቢ ፡ እያሉ ፡ በጉሳ
ናው ፡ ላይ ፡ ሄዱ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡
ግራም ፡ አላሉም ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡
አለቆች ፡ እስከ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ዳተር ፡ ድረስ ፡
በኋላ ፡ በኋላቸው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። የቤትሳ ፲፫
ሚስ ፡ ሰዎችም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ስንዴ ፡
ያጭዱ ፡ ነበር ፤ ዓይናቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድር
ገው ፡ ታቦቱን ፡ አዩ ፡ በማየታቸውም ፡ ደስ ፡
አላቸው ። ሰረገላውም ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚያዊው ፡ ፲፬
ወደ ፡ ኢያሱ ፡ አርሻ ፡ መጣ ፡ ታላቅም ፡ ድን
ጋይ ፡ በነበረባት ፡ በዚያ ፡ ቆመ ፤ የሰረገላው
ንም ፡ እንጨት ፡ ፈልጠው ፡ ላሞቹን ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።
፲፭ ሌዋውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከአ
ርሱ ፡ ጋር ፡ የነበረውንም ፡ የወርቁ ፡ ዕቃ ፡ ያለ
በትን ፡ ሣጥን ፡ አወረዱ ፡ በታላቁም ፡ ድንጋይ ፡

ላይ ፥ እኖሩት ፥ በዚያም ፥ ቀን ፥ የቤትሳሚስ ፥ ሰዎች ፥ ለእግዚአብሔር ፥ የሚቆጠሰውን ፥ መሥዋዕት ፥ አቀረቡ ፥ መሥዋዕትንም ፥ ሠዉ ። ፲፭ ፍልስጥኤማውያንም ፥ አምስቱ ፥ አለቆች ፥ ዙሪት ፥ ጊዜ ፥ ባዩ ፥ ቀን ፥ ወደ ፥ አስቀሮና ፥ ተመለሱ ። ፲፮ ፍልስጥኤማውያን ፥ ለሰ ፥ በደል ፥ መሥዋዕት ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ያቀረቡአቸው ፥ የወርቅ ፥ እብሎች ፥ እነዚህ ፥ ናቸው ፥ አንዲቱ ፥ ለአዛጦን ፥ አንዲቱም ፥ ስጋዝ ፥ አንዲቱም ፥ ለአስቀሎና ፥ አንዲቱ ፥ ለጌት ፥ አንዲቱ ፥ ለአቃሮን ፥ የወጪቱም ፥ እደጠች ፥ ሞጥር ፥ ለአምስቱ ፥ የፍልስጥኤማውያን ፥ አለቆች ፥ እንደ ፥ ነበሩት ፥ ከተሞች ፥ ሁሉ ፥ ቁጥር ፥ እንዲሁ ፥ ነበረ ፥ እነርሱም ፥ አሰከ ፥ ታላቁ ፥ ድንጋይ ፥ የሚደርሱ ፥ ከተሞችና ፥ መንደሮች ፥ ናቸው ። በዚህም ፥ ድንጋይ ፥ ላይ ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ታቦት ፥ አሰቀመጡ ፥ ድንጋይም ፥ እሰከ ፥ ዛሬ ፥ ድረስ ፥ በቤትሳሚሳዊው ፥ በኢያሱ ፥ እርሻ ፥ አለ ።

፲፱ ወደ ፥ እግዚአብሔርም ፥ ታቦት ፥ ውስጥ ፥ ተመልከተዋልና ፥ የቤትሳሚስን ፥ ሰዎች ፥ መታ ፥ በሕዝቡም ፥ ከአምሰት ፥ ሺህ ፥ ሰው ፥ ሰበ ፥ ሰዎችን ፥ መታ ፥ እግዚአብሔርም ፥ ሕዝቡን ፥ በታላቅ ፥ ግዳይ ፥ ሰለ ፥ መታ ፥ ሕዝቡ ፥ አሰቀሰ ። ፳ የቤትሳሚስ ፥ ሰዎች ፥ — በዚህ ፥ በቅዱስ ፥ አምላክ ፥ በእግዚአብሔር ፥ ፊት ፥ መቆም ፥ ማን ፥ ይችላል ? ከእኛስ ፥ ወዋቶ ፥ ወደ ፥ ማን ፥ ይሄዳል ? አሉ ። ፳፩ በቂርያትይዓሪምም ፥ ወደ ፥ ተቀመጡት ፥ ሰዎች ፥ መልክተኞች ፥ ልከው ፥ — ፍልስጥኤማውያን ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ታቦት ፥ መልሰዋል ፥ ወርዳችሁም ፥ ወደ ፥ እናንተ ፥ አውጡት ፥ አሉ ።

ምዕራፍ ፥ ፯ ።

፩ የቂርያትይዓሪም ፥ ሰዎችም ፥ መጥተው ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ታቦት ፥ አመጡ ፥ በኮረብታውም ፥ ላይ ፥ ወሰስው ፥ ወደ ፥ አሚናዳብ ፥ ቤት ፥ አዛቡት ፥ የእግዚአብሔርንም ፥ ታቦት ፥ እንዲጠብቅ ፥ ልጁን ፥ አልዓዛርን ፥ ቀደሱት ። ፪ ታቦቱም ፥ በቂርያትይዓሪም ፥ ከተቀመጠበት ፥ ቀን ፥ ጀምሮ ፥ ወራቱ ፥ ረዘመ ፥ ዘያ ፥ ዓመትም ፥ ሆነ ፥ የእስራኤልም ፥ ቤት ፥ ሁሉ ፥ አገዖ ፥ እግዚአብሔርን ፥ ተከተለ ።

፫ ሳሙኤልም ፥ የእስራኤልን ፥ ቤት ፥ ሁሉ ፥ — ፐሙሉ ፥ ልባችሁ ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ከተመለሳችሁ ፥ እንግዶችን ፥ አማልክትና ፥ አስታሮትን ፥ ከመካከላችሁ ፥ አርቁ ፥ ልባችሁንም ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ አቅኑ ፥ እርሱንም ፥ ብቻ ፥ አምልኩ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፥ እጅ ፥ ያድናችኋል ፥ ብሎ ፥ ተናገራቸው ። ፬ የእስራኤልም ፥ ልጆች ፥ በአሊምንና ፥ አስታሮትን ፥ አራቁ ፥ እግዚአብሔርንም ፥ ብቻ ፥ አመለኩ ።

፭ ሳሙኤልም ፥ — እስራኤልን ፥ ሁሉ ፥ ወደ ፥ ምጽጳ ፥ ሰብስቡ ፥ ስለ ፥ እናንተም ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ እጸልያለሁ ፥ አለ ። ፮ ወደ ፥ ምጽጳም ፥ ተሰበሰቡ ፥ ውኃም ፥ ቀድተው ፥ በእግዚአብሔር ፥ ፊት ፥ አፈሰሱ ፥ በዚያም ፥ ቀን ፥ ጾሙ ፥ በዚያም ፥ — እግዚአብሔርን ፥ በድለናል ፥ አሉ ። ሳሙኤልም ፥ በእስራኤል ፥ ልጆች ፥ ላይ ፥ በምጽጳ ፥ ፈረደ ። ፯ ፍልስጥኤማውያንም ፥ የእስራኤል ፥ ልጆች ፥ ወደ ፥ ምጽጳ ፥ እንደ ፥ ተሰበሰቡ ፥ በሰሙ ፥ ጊዜ ፥ የፍልስጥኤማውያን ፥ አስቆች ፥ በእስራኤል ፥ ላይ ፥ ወጡ ፥ የእስራኤልም ፥ ልጆች ፥ ሰምተው ፥ ፍልስጥኤማውያንን ፥ ፈሩ ። ፰ የእስራኤልም ፥ ልጆች ፥ ሳሙኤልን ፥ — ከፍልስጥኤማውያን ፥ እጅ ፥ ያድነን ፥ ዘንድ ፥ ወደ ፥ አምላካችን ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ትጸልይልን ፥ ዘንድ ፥ አትታክት ፥ አሉት ። ፱ ሳሙኤልም ፥ አንድ ፥ የሚጠባ ፥ የበግ ፥ ጠቦት ፥ ወስዶ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ፈጽሞ ፥ የሚቃጠል ፥ መሥዋዕት ፥ አድርጎ ፥ አቀረበው ፥ ሳሙኤልም ፥ ስለ ፥ እስራኤል ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ጮኸ ፥ እግዚአብሔርም ፥ ሰማው ። ፲ ሳሙኤልም ፥ የሚቀበለውን ፥ መሥዋዕት ፥ ሲያሳርግ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፥ ከእስራኤል ፥ ጋር ፥ ሊዋጉ ፥ ቀረቡ ፤ እግዚአብሔርም ፥ በዚያች ፥ ቀን ፥ በፍልስጥኤማውያን ፥ ላይ ፥ ታላቅ ፥ ነጐድጓድ ፥ አንጐደጐደ ፥ አስደነገጣቸውም ፥ በእስራኤልም ፥ ፊት ፥ ድል ፥ ተመቱ ። ፲፩ የእስራኤልም ፥ ሰዎች ፥ ከምጽጳ ፥ ወጡ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፥ አሳደዱ ፥ በቤትካር ፥ ታችም ፥ እስኪደርሱ ፥ ድረስ ፥ መቱአቸው ።

፲፪ ሳሙኤልም ፥ አንድ ፥ ድንጋይ ፥ ወሰደ ፥ በምጽጳና ፥ በሸን ፥ መካከል ፥ አኖረው ፥ ስሙንም ፥ — እስከ ፥ አሁን ፥ ድረስ ፥ እግዚአብሔር ፥ ረድቶናል ፥ ሲል ፥ አቤንኤዘር ፥ ብሎ ፥ ጠራው ። ፲፫ ፍልስጥኤማውያንም ፥ ተዋረዱ ፥ ዳግመኛም ፥ ከዚያ ፥ ወዳያ ፥ ወደ ፥ እስራኤል ፥ ድንበር ፥ አልመጡም ፥ በሳሙኤል ፥ ሰዎሚ ፥ ሁሉ ፥ የእግዚአብሔር ፥ እጅ ፥ በፍልስጥኤማውያን ፥ ላይ ፥ ነበረች ። ፲፬ ፍልስጥኤማውያንም ፥ ከአስቀሎና ፥ ጀምሮ ፥ እሰከ ፥ ጌት ፥ ድረስ ፥ ከአስራኤል ፥ የወሰዱአቸው ፥ ከተሞች ፥ ለአስራኤል ፥ ተመለሱ ፥ አስራኤልም ፥ ድንበሩን ፥ ከፍልስጥኤማውያን ፥ እጅ ፥ አዳነ ። በአስራኤልና ፥ በአሞራውያንም ፥ መካከል ፥ ሰላቅ ፥ ነበረ ።

፲፭ ሳሙኤልም ፥ በሰዶሚው ፥ ሁሉ ፥ በእስራኤል ፥ ላይ ፥ ዳኛቸው ፥ ነበር ። ፲፮ በየዓመቱም ፥ ወደ ፥ ቤቴል ፥ ወደ ፥ ጌልገላ ፥ ወደ ፥ ምጽጳም ፥ ይዞር ፥ ነበር ፥ በእነዚያም ፥ ስፍራዎች ፥ ሁሉ ፥ በእስራኤል ፥ ላይ ፥ ዳኛቸው ፥ ነበር ። ፲፯ ቤቱም ፥ በዚያ ፥ ነበረና ፥ ወደ ፥ አርማቴም ፥ ይመለስ ፥ ነበር ፥ በዚያም ፥ በእስራኤል ፥ ላይ ፥ ዳኛቸው ፥ ነበር ። በዚያም ፥ ለእግዚአብሔር ፥ መሠዊያ ፥ ሠራ ።

ምዕራፍ ፥ ፰ ።

፩ እንዲህም ፥ ሆነ ፥ ሳሙኤል ፥ በሸመገለ ፥ ጊዜ ፥ ልጆቹን ፥ በእስራኤል ፥ ላይ ፥ ፈራጆች ፥ አደረጋቸው ። ፪ የበኵር ፥ ልጁም ፥ ስም ፥ ኢዮኤል ፥ የሁለተኛውም ፥ ስም ፥ አብያ ፥ ነበረ ። እነርሱም ፥ በቤርሰባህ ፥ ይፈርዱ ፥ ነበር ። ፫ ልጆቹም ፥ በመንገዱ ፥ አልሄዱም ፥ ነገር ፥ ግን ፥ ረብ ፥ ለማግኘት ፥ ፈቀቅ ፥ አሉ ፥ ጉቦም ፥ እየተቀበሉ ፥ ፍርድን ፥ ያጣምሙ ፥ ነበር ።

፬ የእስራኤልም ፥ ሽማግሌዎች ፥ ሁሉ ፥ ተሰብሰበው ፥ ወደ ፥ ሳሙኤል ፥ ወደ ፥ አርማቴም ፥ መጡና ፥ — እነሆ ፥ አንተ ፥ ሸምግለሃል ፥ ልጆችህም ፥ በመንገድህ ፥ አይሄዱም ፥ አሁንም ፥ እንደ ፥ አሕዛብ ፥ ሁሉ ፥ የሚፈርድልን ፥ ንጉሥ ፥ አድርግልን ፥ አሉት ። ፮ የሚፈርድልንም ፥ ንጉሥ ፥ ስጠን ፥ በሉት ፥ ጊዜ ፥ ነገሩ ፥ ሳሙኤልን ፥ አስከፋው ፥ ሳሙኤልም ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ጸለየ ። ፯ እግዚአብሔርም ፥ ሳሙኤልን ፥ አለው ፥ — በእነርሱ ፥ ላይ ፥ እንዳልነግሥ ፥ እኔን ፥ እንጂ ፥ አንተን ፥ አልናቁምና ፥ ዘሜሉህ ፥ ነገር ፥ ሁሉ ፥ በሕዝቡን ፥ ቃል ፥ ስማ ። ከግብጽ ፥ ከወጣቸው ፥ ቀን ፥ ጀምሮ ፥ እስከ ፥ ዛሬ ፥ ድረስ ፥ እኔን ፥ ትተው ፥ እንግዶች ፥ አማልክት ፥ በማምለካቸው ፥ እንደ ፥ ሠሩት ፥ ሥራ ፥ ሁሉ ፥ እንዲሁ ፥ በእንተ ፥ ደግሞ ፥ ያደርጉብሃል ። አሁንም ፥ ቃላቸውን ፥ ስማ ፥ ነገር ፥ ግን ፥ ጽኑ ፥ ምስክር ፥ መስክርባቸው ፥ በእነርሱም ፥ ላይ ፥ የሚነግሠውን ፥ የንጉሡን ፥ ወግ ፥ ንገራቸው ።

፲ ሳሙኤልም ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ ሁሉ ፥ ንጉሥን ፥ ለጸለጥ ፥ ሕዝብ ፥ ነገራቸው ። ፲፩ እንዲህም ፥ አለ ፥ — በእናንተ ፥ ላይ ፥ የሚነግሠው ፥ የንጉሡ ፥ መገዴ ፥ ይህ ፥ ነው ፥ ወንዶች ፥ ልጆቻችሁን ፥ ወስዶ ፥ ሰረገሎችኅና ፥ ፈረሰኞች ፥ ያደርጋቸዋል ፥ በሰረገሎቹም ፥ ፊት ፥ ያሮጣሉ ፥ ለራሱም ፥ የሻለቆችና ፥ የመቶ ፥ አለቆች ፥ ያደርጋቸዋል ፥ እርሻውንም ፥ የሚያርሱ ፥ አዝመትንም ፥ የሚያጭዱ ፥ የጦር ፥ መሣሪያውንና ፥ የሰረገሎቹንም ፥ ዕቃ ፥ የሚሠሩ ፥ ይሆናሉ ። ፲፪ ሴቶች ፥ ልጆቻችሁንም ፥ ወስደ ፥ ሽቶ ፥ ቀማሚዎችና ፥ ወጥቤቶች ፥ አበዛዎችም ፥ ያደርጋቸዋል ። ፲፫ ከአርሻችሁና ፥ ከወይናችሁም ፥ መልካም ፥ መልካሙን ፥ ወስዶ ፥ ለሎሌዎቹ ፥ ይሰጣቸዋል ። ፲፬ ከዘራችሁና ፥ ከወይናችሁም ፥ አሥራት ፥ ወስዶ ፥ ለሎገደረበቹና ፥ ለሎሌዎቹ ፥ ይሰጣቸዋል ። ፲፭ ሎሌዎቻችሁንና ፥ ገረዶቻችሁን ፥ ከከብቶቻችሁና ፥ ከአህዮቻችሁም ፥ መልካም ፥ መልካሞቹን ፥ ወስዶ ፥ ያሠራቸዋል ። ፲፮ ከበጎቻችሁና ፥ ከፍየሎቻችሁ ፥ አሥራት ፥ ይወሰዳል ፤ እናንተም ፥ ባሪያዎች ፥ ትሆኑታላችሁ ። ፲፯ በዚያም ፥ ቀን ፥ ለእናንተ ፥ ከመረጣችሁት ፥ ከንጉሣችሁ ፥ የተነሣ ፥ ትጮኻላችሁ ፥ በዚያም ፥ ቀን ፥ እግዚአብሔር ፥ አልሰማችሁም ።

፲፱ ሕዝቡ ፥ ግን ፥ የሳሙኤልን ፥ ነገር ፥ ይሰማ ፥ ዘንድ ፥ እንቢ ፥ አለ ፥ — እንዲህ ፥ አይሁን ፥ ንገር ፥ ግን ፥ ንጉሥ ፥ ይሁንልን ፥ እኛም ፥ ደግሞ ፥ እንደ ፥ አሕዛብ ፥ ሁሉ ፥ እንሆናለን ፥ ንጉሣችንም ፥ ይፈርድልናል ፥ በፊታችንም ፥ ወጥቶ ፥ ሰለ ፥ እኛ ፥ ይዋጋል ፥ አሉት ። ፳ ሳሙኤልም ፥ የሕዝቡን ፥ ቃል ፥ ሁሉ ፥ ሰማ ፥ ለእግዚአብሔርም ፥ ተናገረ ። ፳፩ እግዚአብሔርም ፥ ሳሙኤልን ፥ — ቃላቸውን ፥ ስማ ፥ ንጉሥም ፥ አንግሥ ፥ ላቸው ፥ አለው ። ሳሙኤልም ፥ የእስራኤልን ፥ ሰዎች ፥ — እያንዳንዳችሁ ፥ ወደ ፥ ከተማችሁ ፥ ሂዱ ፥ አላቸው ።

ምዕራፍ ፥ ፱ ።

፩ ሰሙ ፥ ቂስ ፥ የተባለ ፥ አንድ ፥ ብንያማዊ ፥ ሰው ፥ ነበረ ፥ እርሱም ፥ የአቢኤል ፥ ልጅ ፥ የጽሮር ፥ ልጅ ፥ የብኩራት ፥ ልጅ ፥ የብንያማዊው ፥ የአፌቅ ፥ ልጅ ፥ ጽኑዕ ፥ ኃያል ፥ ሰው ፥ ነበረ ። ፪ ለእርሱም ፥ ሳአል ፥ የሚባል ፥ የተመረጠ ፥ መልከም ፥ ልጅ ፥ ነበረው ፥ ከእስራኤልም ፥ ልጆች ፥ ከእርሱ ፥ ይልቅ ፥ መልከም ፥ የሆነ ፥ ሰው ፥ አልነበረም ፥ ከሕዝቡም ፥ ሁሉ ፥ ይልቅ ፥ ከትከሻውና ፥ ከዚያም ፥ በላይ ፥ ቁመቱ ፥ ዘለግ ፥ ያለ ፥ ነበረ ። ፫ የሳአልም ፥ አባት ፥ የቂስ ፥ አህዮች ፥ ጠፍተው ፥ ነበር ፥ ቂስም ፥ ልጁን ፥ ሳአልን ፥ — ከብላቴኖቹ ፥ አንዱን ፥ ወስደህ ፥ ተነሣ ፥ አህዮችንም ፥ ሰመሽት ፥ ሂድ ፥ አለው ። በተራራማው ፥ በኤፍሬም ፥ አገርና ፥ በሻሊሻ ፥ አሰፋ ፥ አላገኙአቸውም ፥ በሻዕሊም ፥ ምድርም ፥ አሰፋ ፥ በዚያም ፥ አልነበሩም ፥ በብንያም ፥ ምድርም ፥ አሰፋ ፥ አላገኙአቸውምም ።

፭ ወደ ፥ ጹፍ ፥ ምድር ፥ በመጡ ፥ ጊዜም ፥ ሳአል ፥ ከእርሱ ፥ ጋር ፥ የነበረውን ፥ ብላቴና ፥ — አበቴ ፥ ሰለ ፥ አህዮች ፥ ማሰብ ፥ ትቶ ፥ ሰለ ፥ እኛ ፥ እንዳይጨነቅ ፥ ና ፥ እንመለስ ፥ አለው ። ፮ እርሱም ፥ — እነሆ ፥ አንድ ፥ የእግዚአብሔር ፥ ሰው ፥ በዚህች ፥ ከተማ ፥ አለ ፥ እርሱም ፥ የተከበረ ፥ ሰው ፥ ነው ፥ የሚናገረውም ፥ ሁሉ ፥ በእውነት ፥ ይፈጸማል ፥ አሁን ፥ ወደዚያ ፥ እንሂድ ፥ ምናልባት ፥ የምንሄድበትን ፥ መንገድ ፥ ይነግረናል ፥ አለው ። ፯ ሳአልም ፥ ብላቴናውን ፥ — እነሆ ፥ እንሄዳለን ፥ ነገር ፥ ግን ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ሰው ፥ ምን ፥ እና ፥ መጣለታለን ? እንጀራ ፥ ከከረጢታችን ፥ አልቆ ፥ አልና ፥ እጅ ፥ መንሻም ፥ የለንምና ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ሰው ፥ የምናመጣለት ፥ ምን ፥ አለን ? አለው ። ፰ ብላቴናው ፥ ደግሞ ፥ ሰላል ፥ መልሶ ፥ — እነሆ ፥ በእጄ ፥ የሰቅል ፥ ብር ፥ ሩቡ ፥ አለኝ ፥ እርሱንም ፥ መንገዳችንን ፥ እንዲነግረን ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ሰው ፥ እሰጣለሁ ፥ አለ ። ፱ ዛሬ ፥ ነቢይ ፥ የሚባለው ፥ ቀድሞ ፥ በሰ ፥ ራእይ ፥ ይባል ፥ ነበርና ፥ አሰቀድሞ ፥ በእስራኤል ፥ ዘንድ ፥ ሰው ፥ እግዚአብሔርን ፥ ለመጠየቅ ፥ ሲሄድ ፥ — ኑ ፥ ወደ ፥ ባለ ፥ ራእይ ፥ እንሂድ ፥ ይል ፥ ነበር ። ፲ ሳአልም ፥ ብላቴናውን ፥ — የተናገርኸው ፥ ነገር ፥ መልካም ፥ ነው ፥ ና ፥ እንሂድ ፥ አሰውና ፥ የእግ

ዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወዳሰበት ፡ ኩሎ ፡ ገዲ ። ፲፭፡ በከተማይቱም ፡ ዳግት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ቀንጃ ጅት ፡ ውኃውን ፡ ሊቀዱ ፡ ሲመጡ ፡ አገኙና ፡— በለ ፡ ራእይ ፡ በዚህ ፡ አለ ፡ ወይ ? አሉአቸው ። ፲፮፡ እነርሱም ፡— አዎን ፡ እነሆ ፡ በፊታችሁ ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ መጥቶአልና ፡ ዛሬም ፡ ሕዝቡ ፡ በኩረብታው ፡ ላይ ፡ በሰው ፡ መስገጃ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ አለበቸውና ፡ ፈጥናችሁ ፡ ውጡ ። ወደ ፡ ከተማይቱም ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፡ መሥዋዕቱን ፡ እርሱ ፡ የሚባርክ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እርሱ ፡ ሳይወጣ ፡ ሕዝቡ ፡ ምንም ፡ አይቀምሱ ምና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የተጠሩት ፡ ይበላሉና ፡ ለመብላት ፡ ወደ ፡ ኩረብታው ፡ መስገጃ ፡ ሳይ ወጣ ፡ ታገኙታላችሁ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ታገኙ ታላችሁና ፡ አሁን ፡ ውጡ ፡ አሉአቸው ። ወደ ፲፬፡ ከተማይቱም ፡ ጠጡ ፡ በከተማይቱም ፡ ውስጥ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሳሙኤል ፡ ወደ ፡ ኩረብ ታው ፡ መስገጃ ፡ ለመውጣት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ።

፲፫፡ ገና ፡ ሳኦል ፡ ሳይመጣ ፡ ከእንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳሙኤልን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገልጦለት ፡ ነበር ፡— ነገ ፡ በዚህች ፡ ሰዓት ፡ ከብ ንያም ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እሰድድልሃለሁ ፡ ልቅሶአቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የደረሰ ፡ ሕዝቤን ፡ ተመልክቻለሁና ፡ ለሕዝቤ ፡ ለእስራኤል ፡ አለቃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ትቀባዋለህ ፡ ከፍልስጥኤማው ፲፮፡ ያንም ፡ እጅ ፡ ሕዝቤን ፡ ያድናል ። ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፡ ያነገ ርውህ ፡ ሰው ፡ እነሆ ፡ እርሱም ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፲፯፡ ይጨለጥሳል ፡ አለው ። ሳኦልም ፡ በበሩ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀርቦ ፡— የቤተ ፡ ራእዩ ፡ ቤት ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እበክህ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ፲፰፡ ሳሙኤልም ፡ መልሶ ፡ ሳኦልን ፡— ባለ ፡ ራእዩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ዛሬም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትበላላችሁና ፡ በፈቱ ፡ ወደ ፡ ኩረብታው ፡ መሸገኛ ፡ ውጡ ፡ ነገም ፡ አሰናብትሃለሁ ፡ በልብህም ፡ ያለውን ፲፱፡ ሁሉ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በፊት ፡ የጠፉ ፡ አህዮችህ ፡ ተገኝተዋልና ፡ ልብህን ፡ አኅላልቸው ። የእስራኤል ፡ ምኞት ፡ ለማን ፡ ነው ? ለአንተና ፡ ለአባትህ ፡ ቤት ፡ አይደለምን ? ፳፡ አለው ። ሳኦልም ፡ መልሶ ፡— እኔ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ከሚያንስ ፡ ወገን ፡ የቢንያም ፡ ብንያማዊ ፡ አይደለሁምን ? ወይስ ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ ወገ ኖች ፡ ሁሉ ፡ የሚያንስ ፡ አይደለምን ? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ነገርኸኝ ? አለ ።

፳፩፡ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልንና ፡ ብላቴናውን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ አዳራሽ ፡ አገባቸው ፡ ከመጠሩትም ፡ ሰዎች ፡ ዐበይ ፡ ራስ ፡ አስቀመጣቸው ። የተጠሩትም ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ያህል ፡ ነበሩ ። ሳሙኤልም ፡ ወጥቤ ፳፪፡ ቱን ፡— በእንተ ፡ ዘንድ ፡ አኑረው ፡ ብዬ ፡ የሰ ጠሁህን ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ አምጣ ፡ አለው ። ፳፫፡ ወጥቤቱም ፡ ጭኑንና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የነበረ ውን ፡ አምጥቶ ፡ በሳኦል ፡ ፊት ፡ አኖረው ። ሳሙኤልም ፡— ሕዝቡን ፡ ከሠራዙ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ተወሰንው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለእንተ ፡ ተጠ ብቆአልና ፡ እነሆ ፡ የተቀመጠልህን ፡ በፊትህ ፡ አኑረህ ፡ ብላው ፡ አለ ። ፳፬፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኦል ፡ ከሳሙኤል ፡ ጋር ፡ በላ ። ከኩረብታውም ፡ መሰ ገጃ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ወረዱ ፡ ሳሙኤልም ፡ ለሳኦል ፡ በሰገነቱ ፡ ላይ ፡ መኝታ ፡ አዘጋጀለት ። ፳፭፡ እርሱም ፡ ተኛ ። ማልዶም ፡ ተነሡ ፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳኦልን ፡ ከሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ጠርቶ ፡— ተነሣና ፡ ላሰናብትህ ፡ አሰው ። ሳኦ ልም ፡ ተነሣ ፡ እርሱና ፡ ሳሙኤልም ፡ ሁለቱ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጡ ። እነርሱም ፡ በከተማይቱ ፳፯፡ ዳር ፡ ሲወርዱ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳኦልን ፡— ብላቴና ውን ፡ ወደ ፡ ፊታችን ፡ እንዲያልፍ ፡ እዘዘው ፡ አንተ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አሰማህ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቁም ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡ አለፈ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ሳሙኤልም ፡ የዘይቱን ፡ ብርሌ ፡ ወስዶ ፩፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰው ፡ ሳመውም ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡— በርስቱ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶሃል ። የእግዚአብሔር ንም ፡ ሕገብ ፡ ትገዛለህ ። በዙሪያውም ፡ ካሉ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ታድናቸዋለህ ። ዛሬ ፡ ከእኔ ፡ በተለየህ ፡ ጊዜ ፡ በብንያም ፡ ዳርቻ ፡ በጼ ልጻህ ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በራሔል ፡ መቃብር ፡ አጠ ገብ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ታገኛለህ ፤ እነርሱም ፡— ልትሻቸው ፡ ሄደህ ፡ የነበርህላቸው ፡ አህዮች ፡ ተገኝተዋል ፡ እነሆም ፡ አባትህ ፡ ስለ ፡ አህዮች ፡ ማሰብ ፡ ትቶ ፡— የልጄን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ አደ ርጋለሁ ? እያለ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይጨነቃል ፡ ይሉሃል ። ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፈት ፡ ትሄ ፫፡ ዳለህ ፡ ወደ ፡ ታቦር ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ዛፍ ፡ ትደ ርሳለህ ፡ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ሦስት ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶት ፡ ሁለተኛው ፡ ሦስት ፡ ዳቦ ፡ ሦስተኛውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አዝማሪ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ቤቱል ፡ ሲወጡ ፡ ያገኙሃል ፤ ለሳምታም ፡ ይሰጡሃል ፡ ፬፡ ሁለትም ፡ ዳቦ ፡ ይሰጡሃል ፡ ከእጃቸውም ፡ ትቀ በላለህ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ ሰፍረዉ ፡ ወዳሰበት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮረ ብታ ፡ ትመጣለህ ፡ ወደዚያም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ በደረስህ ፡ ጊዜ ፡ በገናና ፡ ከበሮ ፡ እምዚልታና ፡ መሰንቆ ፡ ደዘሙ ፡ ትንቢት ፡ እየተናገሩ ፡ ከኩረ ብታው ፡ መስገጃ ፡ የሚወርዱ ፡ የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ ያገኙሃል ። ፮፡ የእግዚአብሔርም ፡ መን ፈስ ፡ በኃይል ፡ ይወርድብሃል ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ትንቢት ፡ ትናገራለህ ፤ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ሆነህ ፡ ትለወጣለህ ። ፯፡ እነዚህም ፡ ምልክቶች ፡ በደረሱህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ እጅህ ፡ የምታገኘውን ፡ ሁሉ ፡ አድርግ ። ፰፡ በፊትም ፡ ወደ ፡ ጌልጌላ ፡ ተወርዳለህ ፤ እኔም ፡ እነሆ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እወርዳለሁ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እስክመጣና ፡ የምታደርገውን ፡ እስክነ ግርህ ፡ ድረስ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቆያለህ ።

፱፡ ከሳሙኤልም ፡ ዘንድ ፡ ለመሄድ ፡ ፊቱን ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሌላ ፡ ልብ ፡ ለመ ጠለት ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ምልክቶች ፲፡ ሁሉ ፡ ደረሱለት ። ወደዚያም ፡ ከረብታ ፡ በደ ረሰ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ አገኙት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በኃይል ፡ ወረደ በት ፡ በመካከላቸውም ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። ፲፩፡ ቀድሞም ፡ የሚያውቁት ፡ ሁሉ ፡ ከነቢያት ፡ ጋር ፡ ትንቢት ፡ ሲናገር ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡— የቂስን ፡ ልጅ ፡ ያገኘው ፡ ምንድር ፡ ነው ? በውኑ ፡ ሳኦል ፡ ከነቢያት ፲፪፡ ወገን ፡ ነውን ? ተብባሉ ። ከዚያም ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡— አበታቸውስ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ መለሰ ። ስለዚህም ፡ ለሳኦል ፡ ደግሞ ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ ነውን ? የሚል ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ። ፲፫፡ ትንቢት ፡ መናገሩንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኮረብታው ፡ መስገጃ ፡ መጣ ።

፲፬፡ አጎቱም ፡ ሳኦልንና ፡ ብላቴናውን ፡— ወዴት ፡ ሄዳችሁ ፡ ኖሮአል ? አላቸው ። እርሱም ፡— አህ ዮችን ፡ ልንሻ ፡ ሄደን ፡ ነበር ፤ ባጣናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣን ፡ አለ ። የሳኦ ፲፭፡ ልም ፡ አጎት ፡— ሳሙኤል ፡ የነገረህን ፡ እበክህ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ፲፮፡ ሳኦልም ፡ አጎቱን ፡— አህ ዮች ፡ እንደ ፡ ተገኙ ፡ ገለጠልን ፡ አለው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳሙኤል ፡ የነገረውን ፡ የመንግሥትን ፡ ነገር ፡ አላወራለትም ።

፲፯፡ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፲፰፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ጠራ ። የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣሁ ፡ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፡ ከሚያሰጨንቁአችሁም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ አዳንኋችሁ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ከመከራችሁና ፡ ከሥጋታችሁ ፡ ሁሉ ፡ ያዳ ናችሁን ፡ አምላካችሁን ፡ ንቃችሁ ፡— እንዲህ ፡ አይሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ አንግሥልን ፡ አላችሁት ። አሁንም ፡ በየነገዳችሁና ፡ በየወገና ችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቀርቡ ፡ አለ ፳፡ ቸው ። ሳሙኤልም ፡ የእስራኤልን ፡ ነገዶች ፡ ሁሉ ፡ አቀረበ ፡ ዕጣውም ፡ በብንያም ፡ ነገድ ፳፩፡ ላይ ፡ ወደቀ ። የብንያምንም ፡ ነገድ ፡ በየወገና ቸው ፡ አቀረበ ፡ ዕጣውም ፡ በማጥሪ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። የማጥሪንም ፡ ወገን ፡ በየሰዉ ፡ አቀረበ ፡ ዕጣውም ፡ በቂስ ፡ ልጅ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፳፪፡ ወደቀ ፡ ፈለጉትም ፡ አላገኙትምም ። ከእግዚ አብሔርም ፡— ገና ፡ ወደዚህ ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ አለን ? ብለው ፡ ደግሞ ፡ ጠየቁት ፤ እግዚአብ ሔርም ፡— እነሆ ፡ በዕቃ ፡ መከከል ፡ ተሸሽጎአል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። እንርሱም ፡ ሮጠው ፡ ከዚያ ፡ አመጡት ፡ እርሱም ፡ በሕዝቡ ፡ መከከል ፡ ቆመ ፡ ከሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ከትከሻው ፡ ወደ ፳፫፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁመተ ፡ ረጅም ፡ ነበረ ። ሳሙ

ኤልም ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡— ከሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ የሚመስል ፡ እንደሌለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠውን ፡ ታያላችሁን ? አላቸው ፡ ሕዝ ቡም ፡ ሁሉ ፡— ንጉሥ ፡ ሕያው ፡ ይሁን ፡ እያሉ ፡ አልልታ ፡ አደረገ ።

፳፬፡ ሳሙኤልም ፡ የመንግሥቱን ፡ ወግ ፡ ነገረ ፡ በመጽሐፍም ፡ ጻፈው ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ አኖረው ። ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እየቤታቸው ፡ አሰናበታቸው ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ሄደ ፤ እግዚአብ ሔር ፡ ልባቸውን ፡ የነካ ፡ ኃያላንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሄዱ ። ምናምንቴዎች ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ያድነናል ? ብለው ፡ ናቁት ፡ እጅ ፡ መንሻም ፡ አላመጡለትም ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ አሞ ፩፡ ናዊው ፡ ናዖስ ፡ መጣ ፡ በኢያቢስ ፡ ገለዓድም ፡ ሰፈረ ፡ የኢያቢስም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡— ቃል ፡ ኪዳን ፡ እድርግልን ፡ ዘንድ ፡ እኛም ፡ እንገዛልሃለን ፡ አሉት ። አሞናዊውም ፡ ናዖስ ፡— ቀኜ ፡ ዓይናች ፪፡ ሁን ፡ ሁሉ ፡ በማውጣት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደር ግላችኋለሁ ፡ በእስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ስድብ ፡ አደርጋለሁ ፡ አላቸው ። የኢያቢስም ፡ ሽማግ ፫፡ ሌዎች ፡— ወደ ፡ እስራኤል ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ መል ክተኞችን ፡ እንድንልክ ፡ ሰበት ፡ ቀን ፡ ቆይልን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሚያድነን ፡ በይኖር ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንመጣለን ፡ አሉት ። መልክተኞቹም ፬፡ ሳኦል ፡ ወዳሰበት ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ መጥተው ፡ ያዘን ፡ ነገር ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ ተናገሩ ፡ ሕዝ ቡም ፡ ሁሉ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አለቀሱ ። እነሆም ፡ ሳኦል ፡ በሬዎቹን ፡ ተከ ፭፡ ትሎ ፡ ከእርሻው ፡ መጣ ፡ ሳኦልም ፡— ሕዝቡ ፡ የሚያለቅሰው ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ነው ? አለ ። የኢያቢ ስንም ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡ ነገሩት ።

፮፡ ይህንም ፡ ነገር ፡ በሰማው ፡ ጊዜ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በኃይል ፡ ወረደ ፡ ቊጣውም ፡ እጅግ ፡ ነደደ ። ፯፡ ጥምዱንም ፡ በሬ ዎች ፡ ወስዶ ፡ ቈራረጣቸው ፡ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ በመልክተኞች ፡ እጅ ፡ ሰደደና ፡— ሳኦልንና ፡ ሰሙኤልን ፡ ተከትሎ ፡ የማይወጣ ፡ ሁሉ ፡ በበሬዎቹ ፡ እንዲሁ ፡ ይደ ረግ ፡ አለ ። ድንጋጤም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደቀ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡ ወጡ ። በቤዜቅም ፡ ቈጠራ ፰፡ ቸው ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ። የመጡትንም ፡ መልክተኞች ፡— የኢያቢስ ፡ ገለዓድን ፡ ሰዎች ፡— ነገ ፡ ፀሐይ ፡ በተኰሰ ፡ ጊዜ ፡ ማዳን ፡ ይሆንላችኋል ፡ በሉአቸው ፡ አሉ ፱፡ አቸው ። መልክተኞችም ፡ መጥተው ፡ ለኢያ ቢስ ፡ ሰዎች ፡ ነገሩ ፡ ደስም ፡ አላቸው ። የኢ ፲፡ ያቢስም ፡ ሰዎች ፡— ነገ ፡ እንወጣላችኋለን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛችሁንም ፡ አድርጉብን ፡ አሉ ።

፲፩ በነጋውም ፡ ሳአል ፡ ሕዝቡን ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ አደረገ፤ ፡ ወግሞም ፡ በሌ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ መካከል ፡ ገቡ ፡ ቀትርም ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ አምኖኦውያን ፡ መቱ ፡ የቀሩትም ፡ ተበ ተኑ ፡ ሁለትም ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ አልቀ ሩላቸውም ።

፲፪ ሕዝቡም ፡ ሳሙኤልን ፡— ሳአል ፡ አይንገሥ ብን ፡ ያሉ ፡ እነማና ቸው ፡ አውጡአቸውና ፡ እንግደላቸው ፡ አሉት ። ሳአልም ፡— ዛሬ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በእስራ ኤል ፡ ማዳን ፡ አድርጎአልና ፡ ዛሬ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይሞትም ፡ አለ ።

፲፫ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡— ኑ ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ እንሂድ ፡ በዚያም ፡ መንግሥቱን ፡ እናድስ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ሄዱ ፡ በዚያም ፡ ሳአልን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጌ ልገላ ፡ አነገሡት ። በዚያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፡ በዚ ያም ፡ ሳአልና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ሳሙኤልም ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡ አለ ፡— የነገራችሁኝን ፡ ሁሉ ፡ ሰምቼ ፡ አንግሼላችኋ ለሁ ። አሁንም ፡ እነሆ ፡ ንጉሡ ፡ በፊታችሁ ፡ ይሄዳል ፡ እኔም ፡ አርጅቻለሁ ፡ ሽምግያለሁም ፡ እነሆም ፡ ልጆቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ናቸው ፡ እኔም ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በፊታችሁ ፡ ሄድሁ ። እነሆኝ ፡ በእግዚአሔ ር ና ፡ እርሱ ፡ በቀባው ፡ ፊት ፡ መስክሩብኝ ፡ የማንን ፡ በሬ ፡ ወሰድሁ ? የማንንስ ፡ አህያ ፡ ወሰድሁ ? ማንንስ ፡ ሸንገልሁ ? በማንስ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ አደረግሁ ? ዓይኖቼንስ ፡ ለማሳወር ፡ ከማን ፡ እጅ ፡ ጉቦ ፡ ተቀበልሁ ? እኔም ፡ እመል ስላችኋለሁ ። እነርሱም ፡— አልሸነገልኸንም ፡ ግፍም ፡ አላደረግህብንም ፡ ከሰውም ፡ እጅ ፡ ምንም ፡ አልወሰድህም ፡ አሉ ። እርሱም ፡— በእጄ ፡ ምንም ፡ እንዳላገኛችሁ ፡ እግዚአብሔ ር ና ፡ እርሱ ፡ የቀባው ፡ ዛሬ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡— ምስክር ፡ ነው ፡ አሉ ።

፮ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፡— ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ያላቀ ፡ አባቶቻችሁንም ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። አሁ ንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻ ችሁ ፡ ስላደረገው ፡ ጽድቅ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ፊት ፡ እምዋገታችሁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቁሙ ። ያዕቆብና ፡ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ግብጻውያን ፡ አስጨነቁአቸው ፡ አባቶቻችሁም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ላከ ፡ አባቶቻችሁንም ፡ ከግብጽ ፡ አውጥተው ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ አኖሩአቸው ። አምላካቸውንም ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ረሱ ፡ ለአሰር ፡ ሠራዊትም ፡ አለቃ ፡ ለሲሣራ ፡ እጅ ፡ ለፋሊስዔሌማውያንም ፡ እጅ ፡ ለሞዓብም ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ። እነርሱም ፡— እግዚአብሔርን ፡ ትተን ፡ በኣሌ ምንና ፡ አስታሮ ትን ፡ በማምለካችን ፡ በድለናል ፡ አሁንም ፡ ከጠ ላቶቻችን ፡ እጅ ፡ እደነን ፡ እናመልከህማለን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ። እግዚ አብሔርም ፡ ይሩበአልን ፡ ባርቅንም ፡ ዮፍታ ሔንም ፡ ሰሙኤልንም ፡ ላከ ፡ በዙሪያችሁም ፡ ከሉት ፡ ከጠላቶቻችሁ ፡ እጅ ፡ አዳናችሁ ፡ ተዘል ላችሁም ፡ ተቀመጣችሁ ። የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ናዖስ ፡ እንደ ፡ መጣባችሁ ፡ ባያችሁ ፡ ጊዜ ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሣችሁ ፡ ላለ ፡— እንዲህ ፡ አይሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ያንገሥልን ፡ አላችሁኝ ። አሁንም ፡ የመረጣ ችሁትንና ፡ የፈለጋችሁትን ፡ ንጉሥ ፡ አይ ፡ አነ ሆም ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ፡ አደረገላችሁ ። እግዚአብሔርን ፡ ብትፈሩ ፡ ብታመልኩትም ፡ ቃሉንም ፡ ብትሰሙ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ባታምፁ ፡ እናንተና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ንጉሥ ፡ አምላካችሁን ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ብትከተሉ ፡ መልካም ፡ ይሆንላች ኋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ብታምፁ ፡ በእናንተና ፡ በንጉሣችሁ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ትሆናለች ። አሁንም ፡ ቁሙ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዓይናችሁ ፡ ፊት ፡ ወደሚያደርገው ፡ ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ተመ ልከቱ ። የስንዴ ፡ መከር ፡ ዛሬ ፡ አይደለምን ? ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጮኻለሁ ፡ እርሱም ፡ ነጐድጓድና ፡ ዝናብ ፡ ይልክል ፡ እናንተም ፡ ንጉሥ ፡ በመሰመራችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያደረጋችሁት ፡ ክፋት ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ታያላችሁም ። ሰሙኤ ልም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ። እግዚአ ብሔርም ፡ በዚያን ፡ ቀን ፡ ነጐድጓድና ፡ ዝናብ ፡ ላከ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሰሙኤልን ፡ እጅግ ፡ ፈሩአቸው ።

፲፱ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ሰሙኤልን ፡ ንጉሥ ፡ ዘመ ለመናቸን ፡ በኃጢአታችን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ክፋት ፡ ጨምረናልና ፡ እንዳንሞት ፡ ስለ ፡ በረ ያዎችህ ፡ ወደ ፡ አምላክህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይ ፡ አሉት ። ሰሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፡— አትፍሩ ። በእውነት ፡ ይህን ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ አደረጋችሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍ ጹም ፡ ልባችሁ ፡ አምልኩት ፡ እንጂ ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ፈቀቅ ፡ አትበሉ ። ምና ምንቴ ፡ ነውና ፡ የማይረቡንና ፡ የማያድኑ ፡ ከን ቱን ፡ ነገር ፡ ለመከተል ፡ ፈቀቅ ፡ አትበሉ ። እግ ዚአብሔር ፡ ለእርሱ ፡ ሕዝብ ፡ ያደርጋችሁ ፡ ዘንድ ፡ ወድዶአልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰሙ ፡ ታላቅ ፡ ስሙ ፡ ሕዝቡን ፡ አያተውም ። ደግሞ ፡ መልክውንና ፡ ቅኑን ፡ መንገድ ፡ አስተምራች ኋለሁ ፡ እንጂ ፡ በስ ፡ አናንተ ፡ መጸለይን ፡ በመ ተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አበድል ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ። ብቻ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፡ ያደረገላችሁንም ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አይታችኋ ልና ፡ በፍጹም ፡ ልባችሁ ፡ በእውነት ፡ አምል ኩት ። ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ብትሠሩ ፡ አናንተም ፡ ንጉሣችሁም ፡ ትጠፋላችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ሳአልም ፡ በአሰራ ኤል ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሳአል ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ከእስራኤል ፡ መረጠ ፤ ሁለቱም ፡ ሺህ ፡ በማክ ማስና ፡ በቤቴል ፡ ተራራ ፡ ከሳአል ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፡ አንዱም ፡ ሺህ ፡ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ከዮናታን ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፡ የቀረውንም ፡ ሕዝብ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ አሰናበተ ። ዮናታንም ፡ በና ሲብ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የፍልስጥኤማውያን ን ፡ ጭፍራ ፡ መታ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ያ ሰሙ ፡ ሳአልም ፡— ዕብራውያን ፡ ይስሙ ፡ ብሎ ፡ በእንሩ ፡ ሁሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ።

፬ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ሳአል ፡ የፍልስጥኤማው ያንን ፡ ጭፍራ ፡ እንደ ፡ መታ ፡ ደግሞም ፡ እስ ራኤል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጸየፉ ፡ ሰሙ ፡ ሕዝቡም ፡ ሳአልን ፡ ለመከ ተል ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ተሰበሰቡ ።

፭ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡ ለመ ዋጋት ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ሰረገሎች ፡ ስድ ስትም ፡ ሺህ ፡ ፈረሰኞች ፡ በበሕርም ፡ ዳር ፡ እን ዳለ ፡ አሸዋ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ፡ ወጥተ ውም ፡ ከቤትአዌን ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በማ ክማስ ፡ ሰፈሩ ። ሕዝቡም ፡ ተጨንቀው ፡ ነበ ሩና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ በጭንቀት ፡ እንዳሉ ፡ በዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በዋሻና ፡ በእሾህ ፡ ቊጥቋጦ ፡ በገደልና ፡ በግንብ ፡ በጉድጓድም ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸጉ ። ከዕብራውያንም ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻ ግረው ፡ ወደ ፡ ጋድና ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ምድር ፡ ሄዱ ፡ ሳአል ፡ ግን ፡ ገና ፡ በጌልገላ ፡ ነበረ ፡ ሕዝ ቡም ፡ ሁሉ ፡ ተንቀጥቅጠው ፡ ተከተሉት ።

፰ ሳአልም ፡ ሰሙኤል ፡ እንደ ፡ ቀጠረው ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቆየ ፡ ሰሙኤል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጌል ገላ ፡ አልመጣም ፡ ሕዝቡም ፡ ከእርሱ ፡ ተሰደ ተው ፡ ተበታተኑ ። ሳአልም ፡— የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አም ጡልኝ ፡ አለ ። የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረገ ። የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ማለረግ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሰሙኤል ፡ መጣ ፡ ሳአልም ፡ እንዲመርቀው ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ። ሳሙኤልም ፡— ያደረግኸው ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። ሳአልም ፡— ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ተሰደ ተው ፡ አንደ ፡ ተበታተኑ ፡ አንተም ፡ በቀጠሮው ፡ አንዳልመጣህ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወደ ፡ ማከማስ ፡ አንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አየሁ ፡ በስዚህ ፡— ፍልስጥኤማውያን ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ይወ ርዱብኛል ፡ እኔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምህ ለልስመንሁም ፡ አልሁ ፡ በለዚህም ፡ ሳሌታ ገሥ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረግሁ ፡

አለ ። ሰሙኤልም ፡ ሳአልን ፡— አላባጀህም ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘህን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅህም ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግ ሥትህን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘላለም ፡ አጽን ቆልህ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ መንግሥትህ ፡ አይ ጸናም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንደ ፡ ልቡ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መርጦአል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘ ህን ፡ አልጠበቅህምና ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አዝዞታል ፡ አለው ።

፲፬ ሰሙኤልም ፡ ከጌልገላ ፡ ተነሥቶ ፡ መንገዱን ፡ ሄደ ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ሳአልን ፡ ተከተሉት ፡ ሰልፈኞቹን ፡ ሊገናኙ ፡ ሄዱ ። ከጌልገላም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ጊብዓ ፡ መጡ ፡ ሳአልም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ቈጠረ ፡ ስድስት ፡ መቶም ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ሳአልና ፡ ልጁ ፡ ዮናታንም ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ተቀ መጡ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ በማክማስ ፡ ሰፈሩ ። ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ሰፈር ፡ ማራ ኪዎች ፡ በሦስት ፡ ክፍል ፡ ሆነው ፡ ወጡ ፡ አን ዱም ፡ ክፍል ፡ በዖፍራ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ሦጋል ፡ ምድር ፡ ሄደ ። ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ቤት ሖሮን ፡ መንገድ ፡ ዘረ ፡ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ በበረሀው ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ወደ ፡ ሰቦይም ፡ ሸለቆ ፡ በሚመለከተው ፡ ዘዳሪቻ ፡ መንገድ ፡ ዘረ ።

፲፱ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዕብራውያን ፡ ሰይ ፍና ፡ ጦር ፡ አንዳይሠሩ ፡ ብለው ፡ ነበርና ፡ በአ ስራኤል ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ብረተ ፡ ሠሪ ፡ አልተ ገኘም ። አስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ የማረሻውን ፡ ጫፍና ፡ ማጭዱን ፡ መጥረቢያውንና ፡ መቆፈ ሪያውን ፡ ይስል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤማው ያን ፡ ይወርድ ፡ ነበር ። ለማረሻው ፡ ጫፍና ፡ ለመቆፈሪያው ፡ ዋጋው ፡ የሰቅል ፡ ከር ፡ አጅ ፡ ደቁ ፡ አጅ ፡ ነበረ ። መጥረቢያውንም ፡ ለማሳል ፡ መውጊያውንም ፡ ለማበጀት ፡ ዋጋው ፡ የሰቅል ፡ ከር ፡ አጅ ፡ ፭ዱ ፡ አጅ ፡ ነበረ ። በሰዘህም ፡ በሰ ልፍ ፡ ቀን ፡ በደፍና ፡ ጦር ፡ ከሳአልና ፡ ከዮና ታን ፡ ጋር ፡ በነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ አል ተገኘም ፡ ብቻ ፡ በሳአልና ፡ በልጁ ፡ በዮናታን ፡ ዘንድ ፡ ተገኘ ። የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ ወደ ፡ ማክማስ ፡ መተላለፊያ ፡ ወጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ አንድ ፡ ቀንም ፡ አንዲህ ፡ ሆነ ፡ የሳአል ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ጋሻ ጃግሬውን ፡— ና ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ እንሸፍ ፡ አለው ፡ ለአባቱም ፡ አልነገረውም ። ሳአልም ፡ በመጌዶን ፡ በሰው ፡ በሮማኮ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ በጊብዓ ፡ ዳርቻ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፡ ከእር ሱም ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ የሚያህል ፡ ሰው ፡ ነበረ ። የኢካቦድ ፡ ወንድም ፡ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ የፊንሐስ ፡ ልጅ ፡ የዔሊ ፡ ልጅ ፡ በሉሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከሀን ፡ የሆነ ፡

ኤፍድም ፡ የሰበሰ ፡ አከ ፡ያ ፡ አብሮ ፡ ነበር ፡ ሕዝቡ ፡
፱፡ ዮናታን ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ አላወቁም ። ዮናታንም ፡
ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሰራኖር ፡ ሲሻገርበት ፡
በወደደው ፡ መተላለፊያ ፡ መከከል ፡ በወዲህ ፡
እንድ ፡ ሾጣጣ ፡ በወዲህ ፡ እንድ ፡ ሾጣጣ ፡ ድን
ጋዞች ፡ ነበሩ ። የአንዱም ፡ ስም ፡ በጼጽ ፡ የው
፮፡ ሰተኛውም ፡ ሰም ፡ ሰኔ ፡ ነበረ ። እንዱም ፡
ሾጣጣ ፡ በማከማበ ፡ እንጻር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡
ሁለተኛውም ፡ በጊብዓ ፡ አንጻር ፡ በደቡብ ፡
በኩል ፡ የቆመ ፡ ነበሩ ።
፯፡ ዮናታንም ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውን ፡— ና ፡ ወደ ፡ እነ
ዚህ ፡ ቁላፋን ፡ ሰራኖር ፡ እንሰና ፡ በብዙ ፡ ወይም ፡
በጥቂት ፡ ማዳን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያስቸግረ
ውምና ፡ ምናልበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሠራልን ፡
፰፡ ያሠናል ፡ አለው ። ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡— ልብህ ፡
ያሰኘህን ፡ ሁሉ ፡ አድርግ ፡ እነሆ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡
ነኝ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ልብ ፡ ሁሉ ፡ የአለም ፡ ልብ ፡
፱፡ አገዳሁ ፡ ነው ፡ አለው ። ዮናታንም ፡ አለ ፡— ና
እነሆ ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ እናልፋለን ፡ እንገለጥላቸ
፲፡ ውማለን ፡ እንርሱም ፡— ወደ ፡ እናንተ ፡ እስ
ከንመጣ ፡ ድረስ ፡ ቆዩ ፡ ቢሉን ፡ በስፍራችን ፡
እንቆማለን ፡ ወደ ፡ እንርሱም ፡ እንመጣም ።
፲፩፡ ነገር ፡ ግን ፡— ወደ ፡ እኛ ፡ ውጡ ፡ ቢሉን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአቸዋ
ልና ፡ እንወጣለን ፡ ምልክታችንም ፡ ይህ ፡ ይሆ
፲፪፡ ናል ። ሁለታቸውም ፡ ሰፍልስጥኤማውያን ፡
ሩፍሩ ፡ ተገለጡ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡— እነሆ ፡ ሰብረውይን ፡ ከተሸሸጉበት ፡ ጕድጓድ ፡
ይወጣሉ ፡ አሉ ። የሰራኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ የና
ታንንና ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውን ፡— ወደ ፡ እኛ ፡ ውጡ ፡
እንድ ፡ ነገርም ፡ እናሰያችኋለን ፡ አሉ ። ዮናታ
ንም ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውን ፡— እግዚአብሔር ፡ በእ
ስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአቸዋልና ፡ ተከ
፲፫፡ ተለኝ ፡ አለው ። ዮናታንም ፡ በእጅና ፡ በእ
ግሩ ፡ ወጣ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ ተከትሎው ፡ ፍል
ስጥኤማውያንም ፡ በዮናታን ፡ እጅ ፡ ወደቁ ፡
፲፬፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ ተከትሎ ፡ ገደላቸው ። የዮ
ናታንና ፡ የጋሽ ፡ ጃግሬውም ፡ የመጀመሪያ ፡
ግዳያቸው ፡ በእኔያ ፡ ትልም ፡ እርሻ ፡ መከከል ፡
፲፭፡ ዘያ ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ነበረ ። በሰፈሩም ፡ በእርሻ
ውና ፡ በሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ መከከል ፡ ሽብር ፡
ነበረ ፡ በሰፈሩ ፡ የተቀመጡና ፡ ሰምርከ ፡ የመ
ውት ፡ ተሸበሩ ፡ ምድሪቱም ፡ ተናወጠች ፡ ከአ
ግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ ሆነ ።
፲፮፡ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ያሉ ፡ የሳኦል ፡ ዘበኞችም ፡
ተመለከቱ ፡ እነሆም ፡ ሠራዊቱ ፡ ወዲህና ፡
፲፯፡ ወዲያ ፡ እየተራመሱ ፡ ተበታተኑ ። ሳኦልም ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡— እስኪ ፡
ተቋጠሩ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ የሄደ ፡ ማን ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ተመልከቱ ፡ አላቸው ። በተቋጠሩም ፡ ጊዜ ፡
እነሆ ፡ ዮናታንና ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬው ፡ በዚያ ፡ አል
፲፰፡ ነበሩም ። በዚያም ፡ ቀን ፡ አከ ፡ያ ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ፊት ፡ ኤፍድ ፡ ለብሶ ፡ ነበርና ፡ ሳኦል ፡—
፲፱፡ ኤፍድን ፡ እምጣ ፡ አለው ። ሳኦል ፡ ከክህኑ ፡

ጋር ፡ ስነጋገር ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ሰፈር ፡
ግርግሮታ ፡ እየበዛና ፡ እየጠነከረ ፡ ሄደ ፡ ሳኦ
ልም ፡ ክህኑን ፡— እጅህን ፡ መልስ ፡ አለው ።
ሳኦልና ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ጮ፡
ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ውጊያው ፡ መጡ ፡
እነሆም ፡ የእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ በባልንጀ
ራው ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡
ሆነ ። ቀደሞ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋር ፡ የን ፳፩፡
በሩት ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ከሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ የመ
ጡት ፡ ሰብራውያን ፡ ደግሞ ፡ ከሳኦልና ፡ ከዮና
ታን ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ እስራኤሉያን ፡ ለመ
ሆን ፡ ዘሩ ። ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በተራራ ፳፪፡
ማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ የተሸሸጉት ፡ ሁሉ ፡
ፍልስጥኤማውያን ፡ እንደ ፡ ኰበለሉ ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ሲዋጉአቸው ፡ ተከት
ለው ፡ ገሠገሡ ። እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ፳፫፡
ቀን ፡ እስራኤልን ፡ አዳነ ፡ ውጊያውም ፡ በቤት
አዌን ፡ በኩል ፡ አለፈ ። ከሳኦልም ፡ ጋር ፡ የን
በሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እሥር ፡ ሺህ ፡ የሚያህሉ ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ። ውጊያውም ፡ በተራራማው ፡
በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ተበታትኖ ፡ ነበር ። ፳፬፡
የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተጨነቁ ፡
ሳኦል ፡— ጠላቶቼን ፡ እስከበቀል ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ድረስ ፡ መብል ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡
ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ አምሎአቸው ፡ ነበርና ። ሕዝ ፳፭፡
ቡም ፡ ሁሉ ፡ መብል ፡ አልቀመሱም ። ሕዝ
ቡም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ገቡ ፡ ማርም ፡ በም ፳፮፡
ድር ፡ ላይ ፡ ነበረ ። ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ በገቡ ፡
ጊዜ ፡ እነሆ ፡ የሚፈሰስ ፡ ማር ፡ ነበረ ፡ ሕዝቡ ፡
መሐላውን ፡ ፈርቶ ፡ ነበርና ፡ ማንም ፡ እጁን ፡
ወደ ፡ አፉ ፡ አላደረገም ። ዮናታን ፡ ግን ፡ አባቱ ፳፯፡
ሕዝቡን ፡ በማል ፡ ጊዜ ፡ አልሰማም ፡ ነበር ፡ እር
ሱም ፡ በእጁ ፡ ያለችውን ፡ በትር ፡ ሠደፍዋት ፡
ወደ ፡ ወለላው ፡ ነበረ ፡ እጁንም ፡ ወደ ፡ አፉ ፡
አደረገ ፡ ዓይኑም ፡ በራ ። ከሕዝቡም ፡ አንድ ፡ ፳፰፡
ሰው ፡ መለሰ ፡— አባትህ ፡— ዛሬ ፡ መብል ፡ የሚ
በላ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡
መሐላ ፡ አምሎአቸዋል ፡ አለው ፡ ሕዝቡም ፡
ደከሙ ። ዮናታንም ፡— አባቴ ፡ ምድሪቱን ፡ ፳፱፡
አስቸገረ ፡ ከዚህ ፡ ማር ፡ ዋቂት ፡ ብቀምስስ ፡
ዓይኔ ፡ እንዴ ፡ በራ ፡ እዩ ። ይልቅስ ፡ ሕዝቡ ፡ ፴፡
ከገፍት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ምርኮ ፡ በልተው ፡
ቢሆኑ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ መመታት ፡ ይበ
ልጥ ፡ እልነበረምን ፡? አለ ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ከማክ ፴፩፡
ማስ ፡ እስከ ፡ ኤሎን ፡ ድረስ ፡ መቱአቸው ፡ ሕዝ
ቡም ፡ እጅግ ፡ ደከመ ። ሕዝቡም ፡ ሰምርኮ ፴፪፡
ላይ ፡ በጎችን ፡ በሬዎችንም ፡ ጥጆችንም ፡ መሰ
ደው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አረዱ ፡ ሕዝቡም ፡
ከደሙ ፡ ጋር ፡ ይሉ ። ለሳኦልም ፡— እነሆ ፡ ፴፫፡
ሕዝቡ ፡ ከደሙ ፡ ጋር ፡ በመብላታቸው ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ በደሉ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ሳኦልም ፡—
እጅግ ፡ ተሳስፋችሁ ፡ አሁንም ፡ ትልቅ ፡ ድን
ጋይ ፡ እንከበልላችሁ ፡ አቅርቡልኝ ፡ አላቸው ።

፴፬፡ ሳኦልም ፡— በሕዝቡ ፡ መከከል ፡ አየዘራችሁ ፡— ፡
እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሬውንና ፡ በጉን ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ ያቅርብ ፡ በዚህም ፡ እረዱና ፡ ብሉ ፡ ከደ
ሙም ፡ ጋር ፡ በመብላታችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አትበድሉ ፡ በሉአቸው ፡ አለ ። እያንዳንዱም ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ በሬውን ፡ በዚ
ያች ፡ ሌሊት ፡ አቀረበ ፡ በዚያም ፡ አረደው ።
፴፭፡ ሳኦልም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፡
ይኸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ መጀ
መሪያ ፡ መሠዊያ ፡ ነው ።
፴፮፡ ሳኦልም ፡— ፍልስጥኤማውያንን ፡ በሌሊት ፡
ተከትለን ፡ እስከ ፡ጋ ፡ ድረስ ፡ እንበዝብዛቸው ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ እናስቀርላቸው ፡ አለ ።
እነርሱም ፡— ደስ ፡ የሚያሰኝህን ፡ ሁሉ ፡ አድ
ርግ ፡ አሉት ። ከዚህም ፡— ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንቅረብ ፡ አለ ። ሳኦልም ፡— ፍልስጥ
ኤማውያንን ፡ ልከተልን ፡? በእስራኤልስ ፡ እጅ ፡
አሳልፈህ ፡ ትሰጣቸዋለህን ፡? ብሎ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ጠየቀው ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ አልመ
፴፯፡ ለሰለትም ። ሳኦልም ፡— እናንተ ፡ የሕዝቡ ፡
አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ቅረቡ ፡ ዛሬ ፡ ይህ ፡
ኃጢአት ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቁ ፡ ተመ
፴፰፡ ልከቱም ፡ እስራኤልን ፡ የሚያድን ፡ ሕያው ፡
እግዚአብሔርን ፡ ኃጢአቱ ፡ በልጄ ፡ በዮናታን ፡
ቢሆን ፡ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፡ አለ ። ከሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ አንድ ፡ የመለሰለት ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።
፴፱፡ እስራኤልንም ፡ ሁሉ ፡— እናንተ ፡ በአንድ ፡
ወገን ፡ ሁኑ ፡ እኔና ፡ ልጄ ፡ ዮናታንም ፡ በሌላ ፡
ወገን ፡ እንሆናለን ፡ አሰ ። ሕዝቡም ፡ ሳኦልን ፡—
ደስ ፡ የሚያሰኝህን ፡ አድርግ ፡ አሉት ። ሳኦልም ፡
የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡— ፵፡
እውነትን ፡ ግለጥ ፡ አሰው ። ሳኦልና ፡ ዮናታ
፵፩፡ ንም ፡ ተያዙ ፡ ሕዝቡም ፡ ነጻ ፡ ሆነ ። ሳኦልም ፡—
በእኔና ፡ በልጄ ፡ በዮናታን ፡ መከከል ፡ ዕጣ ፡
ጣሉ ፡ አለ ። ዮናታንም ፡ ተያዘ ።
፵፪፡ ሳኦልም ፡ ዮናታንን ፡— ያደረግኸውን ፡ ንገ
ረኝ ፡ አለው ። ዮናታንም ፡— በእጄ ፡ በለሙ ፡
በበትሬ ፡ ጫፍ ፡ ጥቂት ፡ ማር ፡ በእርግጥ ፡ ቀም
ሽለው ፡ እነሆኝ ፡ እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።
፵፫፡ ሳኦልም ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያድርግ
ብኝ ፡ እንዲሁም ፡ ይጨምርብኝ ፡ ዮናታን ፡
፵፬፡ ሆይ ፡ ፈጽመህ ፡ ትሞታለህ ፡ አለ ። ሕዝቡም ፡
ሳኦልን ፡— በውኑ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
መድኃኒት ፡ ያደረገ ፡ ዮናታን ፡ ይሞታልን ፡?
ይህ ፡ አይሁን ፡ ዛሬ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡
አድርጎአልና ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከራሱ ፡
ጠጕር ፡ እንዳት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድ
ቅም ፡ አሉት ። ሕዝቡም ፡ እንዳይሞት ፡ ዮና
፵፭፡ ታንን ፡ አዳነው ። ሳኦልም ፡ ፍልስጥኤማውያ
ንን ፡ ከመከተል ፡ ተመለሰ ፡ ፍልስጥኤማውያ
ንም ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ሄዱ ።
፵፮፡ ሳኦልም ፡ መንግሥቱን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
አጸና ፡ በዙሪያውም ፡ ከሱት ፡ ከሞላቶቹ ፡
ሁሉ ፡ ጋር ፡ ከሞኣብም ፡ ከአሞንም ፡ ልጆች ፡ ፡

ከኤዶምያስም ፡ ከሱባም ፡ ነገሥታት ፡ ከፍል
ስጥኤማውያንም ፡ ጋር ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። በየሄደ
በትም ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ይነሣ ፡ ነበር ። ፵፯፡ እርሱም ፡
ጀግና ፡ ነበረ ፡ ፡ አማሌቃውያንንም ፡ መታ ፡
አሰራኤልንም ፡ ከዘራፊዎቹ ፡ አድ ፡ አላን ።
የሰአልም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ዮናታን ፡ ፵፱፡
የሱይ ፡ ሚልኪሳ ፡ ነበሩ ። የሁለቱም ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ ሰም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ የታላቂቱ ፡ ስም ፡
ሜሮብ ፡ የታናሺቱም ፡ ስም ፡ ሚልከል ፡ ነበረ ።
የሳኦልም ፡ ሚስት ፡ ስም ፡ የአኪማአስ ፡ ልጅ ፡ ፶፡
አከ ፡ናሆም ፡ ነበረ ፡ የሠራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ስም ፡
የሳኦል ፡ አጎት ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡ ነበረ ።
የሳኦልም ፡ አባት ፡ ቂስ ፡ ነበረ ፡ የአበኔርም ፡ ፶፩፡
አባት ፡ ኔር ፡ የአቢኤል ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።
በሳኦልም ፡ ዕድሜ ፡ ሁሉ ፡ ከፍልስጥኤማው ፶፪፡
ያን ፡ ጋር ፡ ጽኑ ፡ ሙሪ ፡ ነበረ ፡ ሳኦልም ፡
ጽኑ ፡ ወይም ፡ ኃያል ፡ ሰው ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ይሰበሰብ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፡ አሰው ፡— በእግዚ ፩፡
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንድትሆን ፡ እቀ
በህ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ፡ አሁንም ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ ስማ ። የሠራዊት ፪፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እስራ
ኤል ፡ ከግብጽ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አማሌቅ ፡ በመን
ገድ ፡ እየተቃወመ ፡ ያደረገብትን ፡ አብቀላለሁ ።
አሁንም ፡ ሄደህ ፡ አማሌቅን ፡ ምታ ፡ ያላቸው ፫፡
ንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመህ ፡ አጥፋ ፡ አትማራቸውም ፡
ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ ብላቴናውንና ፡ ሕፃኑን ፡ በሬ
ውንና ፡ በጉን ፡ ግመሉንና ፡ አህያውን ፡ ግደል ።
ሳኦልም ፡ ሕዝቡን ፡ ጠርቶ ፡ በኔልጎላ ፡ ቈጠ ፬፡
ራቸው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ እግረኞች ፡ ከይ
ሁዳም ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ሳኦልም ፡ ፭፡
ወደ ፡ አማሌቅ ፡ ከተማ ፡ ወጣ ፡ በሸለቆውም ፡
ውስጥ ፡ ተደበቀ ። ሳኦልም ፡ ቄናውያንን ፡— ተነ ፮፡
ሥታችሁ ፡ ሂዱ ፡ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቸርነት ፡ አድርጋችኋልና ፡
ከአማሌቅ ፡ ጋር ፡ እንዳለጠፋችሁ ፡ ከመከከላ
ቸው ፡ ውረዱ ፡ አላቸው ፡ ቄናውያንም ፡ ከአ
ማሌቃውያን ፡ መከከል ፡ ሄዱ ። ሳኦልም ፡ አማ ፯፡
ሌቃውያንን ፡ ከኤውሳኖ ፡ ጀምሮ ፡ በግብጽ ፡
ፊት ፡ አስከለቸው ፡ አስከ ፡ ሱር ፡ ደረሰ ፡ መታ
ቸው ። የአማሌቅንም ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ ቢሕ ፰፡
ይውዝ ፡ ማረከው ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡
ስለት ፡ ፈጽም ፡ አጠፋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳኦ ፱፡
ልና ፡ ሕዝቡ ፡ ለአጋግ ፡ ለተመረጡትም ፡ በጎ
ችና ፡ በሬዎች ፡ ሰሰቡትም ፡ ጥጆችና ፡ ጠቦቶች ፡
ለመልከሞቹም ፡ ሁሉ ፡ ራሩላቸው ፡ ፈጽሞ ፡
ሊያጠፉአቸውም ፡ አልወደዱም ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ምናምንቴንና ፡ የተናቀውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡
አጠፉት ።
የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡— ሳኦል ፡ እንን ፲፡
ከመከተል ፡ ተመልሰአልና ፡ ትእዛዜንም ፡ አል

ፈጸመምና ፡ ስላነገሥኍት ፡ ተጸጸትሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣ ። ሳሙኤልም ፡ ተቈጣ ፡ ሌሊቱንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ። ሳሙኤልም ፡ በነጋውም ፡ ሳኦልን ፡ ሊመ ገናኘት ፡ ማለደ ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቀርሜ ሎስ ፡ መጣ ፡ እነሆም ፡ የመታሰቢያ ፡ ዓምድ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ዙሮ ፡ አለፈ ፡ ወደ ፡ ጌልገላም ፡ ወረደ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ለሳሙኤል ፡ ደረሰለት ። ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጣ ፡ ‘ሳኦልም ፡— አንተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተባረክህ ፡ ሁን ፡ የእ ግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፈጽሚአለሁ ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡— ይህ ፡ ዘጅሮቤ ፡ የምሰ ማው ፡ የበጎች ፡ ጩኸትና ፡ የበሬዎች ፡ ግሣት ፡ ምን ድር ፡ ነው ? አለ ። ሳኦልም ፡— ሕዝቡ ፡ ለእምላ ክህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዉአቸው ፡ ዘንድ ፡ መልከሞቹን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ አድነዋቸዋ ልና ፡ ከአማሌቃውያን ፡ እምጥተዋቸዋል ፡ የቀ ሩትንም ፡ ፈጽመን ፡ አጠፋን ፡ አለው ። ሳሙ ኤልም ፡ ሳኦልን ፡— ቆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የነገረኝን ፡ ልንገርህ ፡ አለው ፡ እር ሱም ፡— ተናገር ፡ አለው ።

ሳሙኤልም ፡ አለ ፡— በነያንህ ፡ ምንም ፡ ታናሽ ፡ ብትሆን ፡ ለእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ አለቃ ፡ አልሆንህምን ? እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀባህ ። እግዚአ ብሔርም ፡— ሂደህ ፡ ኃጢአተኞቹን ፡ አማሌቃ ውያንን ፡ ፈጽመህ ፡ አጥፋቸው ፡ እስኪጠፉም ፡ ድረስ ፡ ውጋቸው ፡ ብሎ ፡ በመንገድ ፡ ላከህ ። ለምርኮ ፡ ሳስተህ ፡ ሰምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማህም ? ሰምንስ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረግህ ? ሳኦልም ፡ ሳሙ ኤልን ፡— የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምቻለሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በላከኝ ፡ መንገድ ፡ ሄጄአለሁ ፡ የአማሌቅን ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ አምጥቻለሁ ። አማሌቃውያንንም ፡ ፈጽሜ ፡ አጥፍቻለሁ ። ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ለእምላክህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጌ ልገላ ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፡ ከእርሙ ፡ የተመረጡ ትን ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ከምርኮው ፡ ወሰዱ ። እለው ። ሳሙኤልም ፡— በውኑ ፡ የእግዚአብ ሔርን ፡ ቃል ፡ በመስማት ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚታዘዝለ ፡ በሚታረድ ፡ መሥዋዕት ፡ ደስ ፡ ይሰዋልን ? እነሆ ፡ መታ ዘዝ ፡ ከመሥዋዕት ፡ ማዳመጥም ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ ስብ ፡ ከማቅረብ ፡ ይበልጣል ። ዓመፅኝ ነት ፡ እንደ ፡ ምዋርተኛ ፡ ኃጢአት ፡ አልከኝን ትም ፡ ጣዖትንና ፡ ተራፊምን ፡ እንደ ፡ ማም ለክ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ንቀሃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ፡ እንዳትሆን ፡ ናቀህ ፡ አለ ።

ሳኦልም ፡ ሳሙኤልን ፡— ሕዝቡን ፡ ስለ ፈራሁ ፡ ቃላቸውንም ፡ ስለ ፡ ሰማሁ ፡ የእግዚአ ብሔርን ፡ ትእዛዝና ፡ የእንተን ፡ ቃል ፡ በመተላ ለፍ ፡ በድያለሁ ። አሁንም ፡ እበክህ ፡ ኃጢአ ቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ አሰ ግድ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ተመለስ ፡ አለው ። ሳሙ ኤልም ፡ ሳኦልን ፡— የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ንቀሃልና ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንዳትሆን ፡ ንቆሃልና ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ አልመለስም ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ ሊሄድ ፡ ዘወር ፡ በለ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦል ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ያዘ ፡ ተቀደደም ። ሳሙኤልም ፡— እግዚአብ ሔር ፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ዛሬ ፡ ከእ ንተ ፡ ቀደዳት ፡ ከእንተም ፡ ለሚሻል ፡ ለጎረ ቤትህ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣት ። የእስራኤል ፡ ኃይል ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የሚጸጸት ፡ እይደለምና ፡ እሱዋ ኽም ፡ እይጸጸትምም ፡ አለው ። እርሱም ፡— በድያለሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በሕዝቤ ፡ ሽማግሌ ዎች ፡ ፊትና ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ አብከህ ፡ አክ ብረኝ ፡ ለአምላክህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሰ ግድ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ተመለስ ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ ከሳኦል ፡ በኋላ ፡ ተመለሰ ፡ ሳኦ ልም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰገደ ።

ሳሙኤልም ፡— የአማሌቅን ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ እምጡልኝ ፡ አለ ። አጋግም ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጣ ። አጋግም ፡— በውኑ ፡ ሞት ፡ እንደዚህ ፡ መራራ ፡ ነውን ? አለ ። ሳሙኤ ልም ፡— ሰይፍህ ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ አልበ ፡ እን ዳደረገቻቸው ፡ እንዲሁ ፡ እናትህ ፡ በሴቶች ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ ትሆናለች ፡ አለ ፡ ሳሙ ኤልም ፡ አጋግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጌ ልገላ ፡ ቈራረጠው ።

ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ሄደ ፡ ሳኦ ልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ወጣ ። ሳሙ ኤልም ፡ እስከ ፡ ሞተበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሳኦልን ፡ ለማየት ፡ ዳግመኛ ፡ አልሄደም ። ሳሙኤልም ፡ ለሳኦል ፡ አሰቀሰ ። እግዚአብሔርም ፡ በእስራ ኤል ፡ ላይ ፡ ሳኦልን ፡ ስላነገሠ ፡ ተጸጸተ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፡— በእስራ ኤል ፡ ላይ ፡ እንዳይነግሥ ፡ ስናቅሁት ፡ ለሳኦል ፡ የምታለቅስለት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? በቀንድህ ፡ ዘይቱን ፡ ሞልተህ ፡ ሂድ ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ንጉሥ ፡ አዘጋጅቻለሁና ፡ ወደ ፡ እሴይ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ እልክሃለሁ ፡ አለው ። ሳሙኤ ልም ፡— እንዴት ፡ እሄዳለሁ ? ሳኦል ፡ ቢሰማ ፡ ይገድለኛል ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፡— አን ዲት ፡ ጊደር ፡ ይዘህ ፡ ሂድና ፡— በእግዚአብሔር ፡ አመጣ ፡ ዘንድ ፡ መጣሁ ፡ በል ። እሴይንም ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ጥራው ። የምታደርገው ንም ፡ አስታውቅሃለሁ ፡ የምነግርህንም ፡ ቅባ ልኝ ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ አደረገ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔ ምም ፡ መጣ ። የአገሩም ፡ ሽማግሌዎች ፡ እየ ተንቀጠቀጡ ፡ ሊገናኙት ፡ መጡና ፡— የመ ጣኸው ፡ ለደኅንነት ፡ ነውን ? አሉት ። እር ሱም ፡— ስደኅንነት ፡ ነው ፡ ስእግዚአብሔር ፡ አመጣ ፡ ዘንድ ፡ መጣው ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ፡ ከእ ኔም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ኑ ፡ አለ ። እሴ ይንና ፡ ልጆቹንም ፡ ቀደሰቸው ፡ ወደ ፡ መሥዋ ዕቱም ፡ ጠራቸው ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤል ያብ ፡ ተመልክቶ ፡— በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀባው ፡ በፊቱ ፡ ነው ፡ አለ ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሳሙኤልን ፡— ፊቱን ፡ የቋመቱንም ፡ ዘለ ግታ ፡ እትይ ፡ ሰው ፡ እንዲያይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያይምና ፡ ናቅሁት ፡ ሰው ፡ ፊትን ፡ ያያል ፡ ኣግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልብን ፡ ያያል ፡ አለው ። እሴይም ፡ አሚናዳብን ፡ ጠርቶ ፡ በሳሙኤል ፡ ፊት ፡ አሳለፈው ። እርሱም ፡— ይህን ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልመረጠውም ፡ አለ ። እሴ ይም ፡ ሣማን ፡ አሳለፈው ። እርሱም ፡— ይህን ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልመረጠውም ፡ አለ ። እሴይም ፡ ከልጆቹ ፡ ሰበተን ፡ በሳሙኤል ፡ ፊት ፡ አሳለፋቸው ። ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፡— እግዚ አብሔር ፡ እነዚህን ፡ አልመረጠም ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፡— የቀረ ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አለህን ? አለው ። እርሱም ፡— ታናሹ ፡ ገና ፡ ቀርቶአል ፡ እነሆም ፡ በጎችን ፡ ይጠብቃል ፡ አለ ። ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፡— እርሱ ፡ እስኪ መጣ ፡ ድረስ ፡ እንረፍቅምና ፡ ልከህ ፡ አስመጣው ፡ አለው ። ልከም ፡ አስመጣው ፡ እርሱም ፡ ቀይ ፡ ዓይኑም ፡ የተዋበ ፡ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔርም ፡— ይህ ፡ ነውና ፡ ተነሥተህ ፡ ቅባው ፡ አለ ። ሳሙኤልም ፡ የዘይቱን ፡ ቀንድ ፡ ወስዶ ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ቀባው ። የእ ግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ በኃይል ፡ መጣ ። ሳሙኤልም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ሄደ ።

የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከሳኦል ፡ ፈቀ ፡ ክቶም ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አሠቃየው ። የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡— እነሆ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያሠቃይሃል ፡ በገና ፡ መልከም ፡ እድርጎ ፡ የሚ መታ ፡ ሰው ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ በፊት ፡ የሚቆሙትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ይዘዝ ፡ ከእግዚ አብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ከፉ ፡ መንፈስ ፡ በሆነብህ ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ ሲመታ ፡ እንተ ፡ ደኅና ፡ ትሆናለህ ፡ እሱ ት ። ሳኦልም ፡ ባሪያዎቹን ፡— መልካም ፡ እድርጎ ፡ በገና ፡ መምታት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ፈልጋችሁ ፡ እምጡልኝ ፡ አላቸው ። ከብላቴኖ ቹም ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፡— እነሆ ፡ መልክም ፡ እድርጎ ፡ በገና ፡ የሚመታ ፡ የቤተ ፡ ልሔሚዊ ውን ፡ የእሴይን ፡ ልጅ ፡ እይቻለሁ ፡ እርሱም ፡ ጽኑዕ ፡ ኃያል ፡ ነው ፡ በነገርም ፡ ብልህ ፡ መል ኩም ፡ ያማረ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ እሴይ ፡ መል ክተኞች ፡ ልከ ፡— ከበጎች ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ልጅህን ፡ ዳዊትን ፡ ላክልኝ ፡ አለ ። እሴይም ፡ እንጀራና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አቁማዳ ፡ የተጫነ ፡ አህያ ፡ የፍየልም ፡ ጠቦት ፡ መስዶ ፡ በእጁ ፡ በዳ ዊት ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ላከ ። ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጣ ፡ በፊቱም ፡ ቆመ ፡ እጅግም ፡ ወደ ደው ፡ ሳኦልንም ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬው ፡ ሆነ ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ እሴይ ፡— በኃይል ፡ ምገስ ፡ እግ ኝቶልና ፡ ዳዊት ፡ በፊቴ ፡ እበክህ ፡ ይቁም ፡ ብሎ ፡ ላከ ። እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ በገና ፡ ይዞ ፡ በእጁ ፡ ይመታ ፡ ነበር ፡ ሳኦልንም ፡ ደስ ፡ ያሰኘው ፡ ያሰርፈውም ፡ ነበር ። ክፉ ፡ መንፈስም ፡ ከእርሱ ፡ ይርቅ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሞኙሮቻቸውን ፡ በይ ሁዳ ፡ በለው ፡ በሰኰት ፡ አከማቹ ፡ በሰኰትና ፡ በዓዜቃ ፡ መካከል ፡ በኤፌስደሚም ፡ ሰፈሩ ። ሳኦልና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ተከማቹ ፡ በዔላ ፡ ሸለቆም ፡ ሰፈሩ ፡ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋር ፡ ሊዋጉ ፡ ተሰለፉ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ በአ ንድ ፡ ወገን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ። እስራኤልም ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፡ በመከከላቸውም ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ። ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ሰፈር ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ጎልያድ ፡ ቁመቱም ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ከስን ዝር ፡ የሆነ ፡ ዋነኛ ፡ ጀግና ፡ መጣ ። በራሱም ፡ የናስ ፡ ኮር ፡ ደፍቶ ፡ ነበር ። ጥሩርም ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፡ የጥሩሮም ፡ ሚዛን ፡ እምስት ፡ ሺህ ፡ ሰቅል ፡ ናስ ፡ ነበረ ። በእግሮቹም ፡ ላይ ፡ የናስ ፡ ገምበሌ ፡ ነበረ ። የናስም ፡ ጭሬ ፡ በትከሻው ፡ ላይ ፡ ነበረ ። የጦሩም ፡ የሰ ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ ነበረ ፡ የጦሩም ፡ ሚዝን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ብረት ፡ ነበረ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ በፊቱ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ቆሞ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ጭፍሮች ፡ ጮኸ ፡— ለሰልፍ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ወጣችሁ ? እኔ ፡ ፍልስ ዔኤማዊ ፡ አናንተም ፡ የሳኦል ፡ ባሪያዎች ፡ አይ ደላችሁምን ? ለእናንተ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ምረጡ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ይውረድ ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ሊዋጋ ፡ ቢችል ፡ ቢገድለኝም ፡ ሰ ባሪያዎች ፡ እንሆናችኋለን ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ባሸንፈው ፡ ብገድለውም ፡ አናንተ ፡ ባሪያዎች ፡ ትሆኑናላችሁ ፡ ለእኛም ፡ ትገዛላችሁ ፡ አለ ። ፍልስጥኤማዊውም ፡— ዛሬ ፡ የእስራኤል ፡ ጭፍሮች ፡ ተገዳደርኳቸው ፡ እንዋጋ ፡ ዘንድ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ ስጡኝ ፡ አለ ። ሳኦልና ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚላ ቸውን ፡ የፍልስጥኤማዊውን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፡ ደነገጡም ።

ዳዊትም ፡ የዚያ ፡ የኤፍራታዊው ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡ ያም ፡ ሰው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ስሙም ፡ እሴይ ፡ ነበረ ፡ ስንኀትም ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ በሳኦልም ፡ ዘመን ፡ በዕድሚ ፡ እርጅና ፡ ሸምግሎም ፡ ነበር ። የእሴይም ፡ ሦስቱ ፡ ታላላቆች ፡ ልጆቹ ፡ ሳኦልን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ሰልፉ ፡ ሄዱ ። ነበር ፡ ወደ ፡ ሰልፉም ፡ የሄዱት ፡ የሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ታላቁ ፡

ኤልያብ ፡ ሁለተኛውም ፡ አሚናዳብ ፡ ሦስተኛ
፲፪ ውም ፡ ሣማ ፡ ነበረ ። ዳዊት ፡ የሁሉ ፡ ታናሽ ፡ ነበረ ፤ ሦስቱም ፡ ታላላቆች ፡ ሳኦልን ፡ ተከተ
፲፫ ለው ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ የእባቱን ፡ በጎች ፡ ሰመ ጠበቅ ፡ ከሳኦል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡
፲፬ ይመላለስ ፡ ነበር ። ፍልስጥኤማዊውም ፡ ጥዋ ትና ፡ ማታ ፡ ይቀርብ ፡ እርባ ፡ ቀንም ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

፲፭ እሴይም ፡ ልጁን ፡ ዳዊትን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦— ከዚህ ፡ ከተጠበሰው ፡ እሸት ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ እነዚህንም ፡ እሥር ፡ አንጀራዎች ፡ ለወንድሞችህ ፡ ውሰድ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩም ፡ ወደ፡
፲፯ ወንድሞችህ ፡ ፈጥነህ ፡ እድርሰላቸው ፡ ይህንም ፡ አሥሩን ፡ አይብ ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ውሰዳቸው ፡ የወንድሞችህንም ፡ ደኅንነት ፡ ጠይቅ ፡ ወሬአ ፡ ቸውንም ፡ አምጣልኝ ። ሳኦልና ፡ እነርሱ ፡ የእ ስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከፍልስጥኤማው ያን ፡ ጋር ፡ እየተዋጉ ፡ በኤላ ፡ ሸለቆ ፡ ነበሩ ።
፲፰ ዳዊትም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፡ በጎቹንም ፡ ለጠባቂ ፡ ተው ፡ አሌይም ፡ ያዘዘውን ፡ ይዘ ፡ ሄደ ። ዌና ራውም ፡ ተሰልፎ ፡ ሲወጣ ፡ ሰለልፍም ፡ ሲጮኽ፡ በሰረገሎች ፡ ወደ ፡ ተከበበው ፡ ሰፈር ፡ መጣ ።
፲፱ እስራኤልና ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ለፊት፡
፳ ተሰላልፈው ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ ዕቃውን ፡ በዕቃ ፡ ጠባቂው ፡ እጅ ፡ አኖረው ፡ ወደ ፡ ሠራ ዊቱም ፡ ሮጠ ፡ የወንድሞቹንም ፡ ደኅንነት ፡ ጠየቀ ። እርሱም ፡ ሲነጋገራቸው ፡ እነሆ ፡ ጎል
፳፩ ያድ ፡ የተበሰው ፡ ያ ፡ ዋነኛ ፡ ጀግና ፡ ፍልስጥኤ ማዊ ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፡ የተናገረውንም ፡
፳፪ ቃል ፡ ተናገረ ፤ ዳዊትም ፡ ሰማ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰውዮውን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ፡
፳፫ ፈርተው ፡ ከእርሱ ፡ ሸሹ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡— ይህን ፡ የወጣውን ፡ ሰው ፡ እያችሁ ትን ? በእውነት ፡ እስራኤልን ፡ ሊገዳደር ፡ ወጣ፡ የሚገድለውንም ፡ ሰው ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ባለ ጠጋ ፡ ያደርገዋል ፡ ልጁንም ፡ ይድርለታል ፡ ያባቱንም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ፡
፳፭ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ያወጣቸዋል ፡ አሉ ። ዳዊትም ፡ በአጠገቡ ፡ ለቆሙት ፡ ሰዎች ፡— ይህን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ለሚገድል ፡ ከእስራኤልም ፡ ተግዳሮትን ፡ ለሚያርቅ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይደረግለታል ? የአያውን ፡ አምላክ ፡ ሙናፍቆች ፡ የሚገዳደር ፡ ይህ ፡ ያልተገረዘ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ማን ፡ ነው ?
፳፯ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ሕዝቡም ፡— ለሚገድ ለው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግለታል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ መለሱለት ።

፳፰ ታላቅ ፡ ወንድሙም ፡ ኤልያብ ፡ ከሰዎች ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ሰማ ፡ የኤልያብም ፡ ቍጣ ፡ በዳ ዊት ፡ ላይ ፡ ነድዶ ፡— ስምን ፡ ወደዚህ ፡ ወረ ድህ ? እነዚያንስ ፡ ጥቂቶች ፡ በጎች ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ለማን ፡ ተውሃቸው ? እኔ ፡ ሁራትህንና ፡ የልጣህን ፡ ክፋት ፡ እውቃለሁና ፡ ሰልፉን ፡ ለማ ፳፱ የት ፡ መጥተሃል ፡ አለው ። ዳዊትም ፡— እኔ ፡ ምን ፡ እደረግሁ ? ይህ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እያደለ ፴ ምን ? አለ ። ዳዊትም ፡ ከእርሱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ዘወር ፡ አለ ፥ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፤ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ መለሱለት ።

፴፩ ዳዊትም ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፥ ሰውሉ ልም ፡ ነገሩት ፤ ወደ ፡ እርሱም ፡ አስጠራው ።
፴፪ ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፡— ስለ ፡ እርሱ ፡ የማንም ፡ ልብ ፡ አያውደቅ ፤ አኔ ፡ ባሪያህ ፡ ሄጀ ፡ ያንን ፡
፴፫ ፍልስጥኤማዊ ፡ እወጋዋለሁ ፡ አለው ። ሳኦ ልም ፡ ዳዊትን ፡— አንተ ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ነህና ፥ እርሱም ፡ ከብላቴንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ጦረኛ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ለመውጋት ፡ ትሄድ ፡
፴፬ ዘንድ ፡ አትችልም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ሳኦ ልን ፡ አለው ፡— አኔ ፡ ባሪያህ ፡ የአባቴን ፡ በጎች ፡ በጠብቅ ፡ እንበሳና ፡ ድብ ፡ ይመጣ ፡ ነስር ፥ ከመ ንጋውም ፡ ጠቦት ፡ ይወስድ ፡ ነበር ። በኋላ ፡
፴፭ ውም ፡ እከተለውና ፡ አመታው ፡ ነበር ፥ ከአ ፉም ፡ አስጥለው ፡ ነበር ፤ በተነሣብኝም ፡ ጊዜ ፡ ጦርጮውን ፡ ይዤ ፡ አመታውና ፡ እገድለው ፡ ነበር ። አኔ ፡ ባሪያህ ፡ እንበሳና ፡ ድብ ፡ መታው ፡
፴፮ ይህም ፡ ያልተገረዘው ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ የሕያ ውን ፡ አምላክ ፡ ጭፍሮች ፡ ተገዳድሯልና ፡ ከእነርሱ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይሆናል ። ዳዊትም ፡—
፴፯ ከእንበሳና ፡ ከድብ ፡ እጅ ፡ ያስጣለኝ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከዚህ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ እጅ ፡ ያስጥለ ኛል ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡— ሂድ ፡ እግዚ አብሔርም ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፡ አለው ።
፴፰ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ የገዘ ፡ ራሱን ፡ ልብስ ፡ አለ በሰው ፡ ሰራሱም ፡ ላይ ፡ የናስ ፡ ቊር ፡ ደቆ ሰት ፡ ጥሩርም ፡ አለበሰው ። ዳዊትም ፡ ሰይፉን ፡
፴፱ በልብሱ ፡ ላይ ፡ ታጠቀ ፡ ዋናም ፡ አልፈተነው ፡ ምና ፡ መሄድ ፡ ምክረ ። ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፡— አልፈተንሁትምና ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መሄድ ፡ አልችልም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አወለቀ ። በት
፵ ራንም ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ፡ ከወንዝም ፡ እምሰት ፡ ድብልብል ፡ ድንጋዮችን ፡ መረጠ ፡ በእረኛ ፡ ኮረጀውም ፡ ዘኪሱ ፡ ከተታቸው ፡ ወንጭፍሮ ፡ በእጁ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ቀረበ ።

፵፩ ፍልስጥኤማዊውም ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ቀረበ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ በፊቱ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።
፵፪ ጎልያድም ፡ ዳዊትን ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ አየው ፡ ቀይ ፡ ብላቴና ፡ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነበረና ፡
፵፫ ናቀው ። ፍልስጥኤማዊውም ፡ ዳዊትን ፡— በትር ፡ ይዘህ ፡ የምትመጣብኝ ፡ አኔ ፡ ውሻ ፡ ነኝን ? አለው ። ፍልስጥኤማዊውም ፡ በአምላ ኩ ፡ ስም ፡ ዳዊትን ፡ ረገመው ። ፍልስጥኤማዊ
፵፬ ውም ፡ ዳዊትን ፡— ወደ ፡ አኔ ፡ ና ፥ ሥጋህንም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ አሰጣ ለሁ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡
፵፭ አለው ፡— አንተ ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ ጭሬም ፡ ይዘህ ፡ ትመጣብኛለህ ፤ አኔ ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ በተገዳደር ኸው ፡ በእስራኤል ፡ ጭፍሮች ፡ አምላክ ፡ ስም ፡

ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ዳዊትም ፡ ሰለኤል ፡ መናገሩን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የዮናታን ፡ ነፍስ ፡ በዳዊት ፡ ነፍስ ፡ ታሰ
፪ ረች ፥ ዮናታንም ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ወደደው ። ሳኦ ፫ ልም ፡ ቀን ፡ ለኦል ፡ ወሰደው ፥ ወደ ፡ አባ ቱም ፡ ቤት ፡ ያመልሰው ፡ ዘንድ ፡ እልተወውም ።
፬ ዮናታንም ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ስለ ፡ ወደደው ፡ ከዳ ፭ ዊት ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ። ዮናታንም ፡ የለበሰውን ፡ ካባ ፡ አውልቆ ፡ እርሱንና ፡ ልብ ሱን ፡ ሰይፉንም ፡ ቀስቱንም ፡ መታጠቂያው ንም ፡ ለዳዊት ፡ ሸለመው ። ዳዊትም ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ሰደደው ፡ ሁሉ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፥ አስተው ሎም ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ሳኦልም ፡ በጦረኞች ፡ ላይ ፡ ሾመው ፡ ይሆም ፡ በሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ዓይ ንና ፡ በሳኦል ፡ በሪያዎች ፡ ዓይን ፡ መልከም ፡ ነበረ ።

፮ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ዳዊት ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ገድሎ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ከያዘመሩና ፡ እየዘ ፈኑ ፡ አልልም ፡ እያሉ ፡ ከበሮና ፡ አታሞ ፡ ይዘው ፡ ንጉሡን ፡ ሳኦልን ፡ ሊቀበሉ ፡ ሴቶች ፡ ከእስራ ኤል ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ወጡ ። ሴቶችም ፡— ፯ ሳኦል ፡ ሺህ ፥ ዳዊትም ፡ እልፍ ፡ ገደለ ፡ እያሉ ፡ እየተቀባበሉ ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡ እጅግ ፡ ፰ ተቈጣ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡ እስከ ፉው ፡ እርሱም ፡— ለዳዊት ፡ እልና ፡ ሰጡት ፥ ለእኔ ፡ ግን ፡ ሺህ ፡ ብቻ ፡ ሰጡኝ ፤ ከመንግሥት ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ቀረ በት ? አለ ። ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡ ተመቅኝቶ ፡ ተመለከተው ።

፱ በነጋውም ፡ ሳኦል ፡ ከፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያዘው ፥ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። ዳዊትም ፡ በየቀኑ ፡ ያደርግ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በእጁ ፡ በገና ፡ ይመታ ፡ ነበር ። ፲ ሳኦ ልም ፡ ጦሩን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡— ዳዊትን ፡ ከግንቡ ፡ ጋር ፡ አጣብቂ ፡ እመታዋ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ። ዳዊትም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ ዘወር ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፡ ከእ ፲፩ ርሱ ፡ ጋር ፡ በለ ፡ ነበረ ፡ ከሰለልም ፡ ሰሰ ፡ ተሰየ ፡ ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡ ፈራው ። በሰዚህም ፡ ሳኦል ፡ ፲፪ ከእርሱ ፡ አራቀው ፥ የሺህ ፡ አለቃም ፡ አደረ ገው ፤ ሕዝቡም ፡ ፊት ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ በእከሌ ፡ ሁሉ ፡ አስተውሎ ፡ ያደ ፲፫ ርግ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ። ሳኦልም ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፲፬ አየቶ ፡ እጅግ ፡ ፈራው ። ነገር ፡ ግን ፡ በፊታ ፲፭ ቸው ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እስራኤ ልና ፡ ይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ ዳዊትን ፡ ወደዱ ።

፲፮ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡— ታላቂቱ ፡ ኤሊ ፡ ሚሮብ ፡ እኅቷ ፡ እርስዋን ፡ አድርልሃለሁ ፤ ብቻ ፡ ቀል ጣፋ ፡ ልጅ ፡ ሁንልኝ ፥ ስለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጦርነት ፡ ተጋደል ፡ አለው ። ሳኦልም ፡— የፍል ስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ትሁን ፡

እንኂ ፡ የእኔ ፡ እጅ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እትሁን ፡ ይል ፡ ነበር ። ዳሞትም ፡ ሳኦልን ፡ — ስንሥሥ ፡ እማች ፡ እሠን ፡ ዘንጀ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ? ሰው ነቲስ ፡ ምንድር ፡ ናት ፡ የእዘቲስ ፡ ወገን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አሰው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ሜርብ ፡ ዳሞትን ፡ የምታገበበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ለመሓላታቸው ፡ ለእስድሪኤል ፡ ተሳረች ። የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሚልክል ፡ ዳሞትን ፡ ወደደች ፡ ይሠም ፡ ወረ ፡ ስሳኦል ፡ ደረሰለት ፡ ነገሩም ፡ ደስ ፡ አሰኘው ። ሳኦልም ፡ — ወጥመደ ፡ ትሠነው ፡ ዘንደ ፡ የዩ ልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ትሠን ፡ ዘንድ ፡ እርስዋን ፡ እድርሰታለሁ ፡ አለ ፡ ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ — ዘሬ ፡ ሁለተኛ ፡ እማች ፡ ትሠንኛለህ ፡ አለው ።

ሳኦልም ፡ በሪያዎቹን ፡ — እነሆ ፡ ንጉሥ ፡ እጅግ ፡ ወድዶሃል ፡ በሪያዎቹም ፡ ሁሉ ፡ ወድ ደውሃል ፡ አሁንም ፡ ስንጉሥ ፡ እማች ፡ ሁን ፡ ብላችሁ ፡ በስውር ፡ ሰዳሞት ፡ ነገሩት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። የሳኦልም ፡ ሰሪያዎች ፡ ደዘን ፡ ቃል ፡ በዳሞት ፡ ጆሮ ፡ ተናገሩ ፡ ዳሞትም ፡ — እኔ ፡ ድዘ ፡ የተጠቃውም ፡ ሰው ፡ ሰሆን ፡ ስንጉሥ ፡ እማች ፡ እሠን ፡ ዘንድ ፡ ስእናንተ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ይመስላችኋልን ? አለ ። የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡ — ዳሞት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ ይጥለው ፡ ዘንድ ፡ አሰበ ፡ — የንጉሥን ፡ ጠላቶች ፡ ይበቀል ፡ ዘንድ ፡ ከመቶ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሸለፈት ፡ ዘቀር ፡ ንጉሥ ፡ ማኤ ፡ አይሻም ፡ ብላችሁ ፡ ሰዳሞት ፡ ነገሩት ፡ አላቸው ። የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡ ደዘን ፡ ቃል ፡ ሰዳሞት ፡ ነገሩት ፡ ስንጉሥም ፡ እማች ፡ ደሆን ፡ ዘንድ ፡ ዳሞትን ፡ ደስ ፡ አሰኘው ። ዳሞትና ፡ ሰምቹም ፡ ተነሥተው ፡ ጌዱ ፡ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ መቶ ፡ ሰምች ፡ ገደሉ ፡ ዳሞትም ፡ ስንጉሥ ፡ እማች ፡ ደሆን ፡ ዘንድ ፡ ሰሰበቸውን ፡ እሥጥዶ ፡ በቀጥራቸው ፡ ልክ ፡ ስንጉሡ ፡ ሰጠ ። ሳኦልም ፡ ልጁን ፡ ሚልክልን ፡ ጻረሰት ። ሳኦልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዳሞት ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አየ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ወደዱት ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ እጥብቆ ፈራው ፡ ሳኦልም ፡ ፅድሚውን ፡ ሁሉ ፡ ስዳሞት ፡ ጠሳት ፡ ሆነ ።

የፍልስጥኤማውያንም ፡ አሰቆች ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፡ በወጡም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከሳኦል ፡ በሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ዳሞት ፡ እስተውሙ ፡ ያደርግ ፡ ነበርና ፡ ስሙ ፡ እጅግ ፡ ተጠርቶ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

ሳኦልም ፡ ለልጁ ፡ ለዮናታንና ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ዳሞትን ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ነገራቸው ። የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ግን ፡ ዳሞትን ፡ እጅግ ፡ ደወድድ ፡ ነበር ። ዮናታንም ፡ — አቡቴ ፡ ሳኦል ፡ ሊገድልህ ፡ ፈልጎአል ፡ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ስነገው ፡ ተጠንቅቀህ ፡ ተሸሸግ ፡ ዘሸሸግ ፡ ሰአልም ፡ ያደ ተቀመጥ ፡ አእም ፡ እወጣለሁ ፡ አንተም ፡ ብሰ ነበት ፡ እርሻ ፡ ባለብቱ ፡ አጠገብ ፡ አቆማለሁ ። ስሰ አል ፡ እንተም ፡ ከአባቴ ፡ ጋር ፡ እንገገራለሁ ፡ የሰንውንም ፡ አይቹ ፡ እነግርንሰሐ ፡ ብሎ ፡ ለዳሞት ፡ ነገረው ። ዮናታንም ፡ ሰአባቱ ፡ ሰሳአል — እርሱ ፡ አልበደለህምና ፡ ሥራውም ፡ ለአንተ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ሠኖአልና ፡ ንጉሡ ፡ ባሪያውን ፡ ዳሞትን ፡ አይበድለው ፡ ነፍሱንም ፡ በእጁ ፡ ጥሎ ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ገደስ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ መድኃኒት ፡ አደረገ ፡ አንተም ፡ አይተህ ፡ ደስ ፡ አለህ ፡ በከንቱ ፡ ዳሞትን ፡ በመግደል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ላይ ፡ ትበደላለህ ? ብሎ ፡ በስ ፡ ዳሞት ፡ መልካም ፡ ተናገረ ።

ሳኦልም ፡ የዮናታንን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡ ሳኦልም ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ዳሞት ፡ አይገደልም ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ ጠርቶ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡ ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ አመጣው ፡ እንደ ፡ ቀድሞውም ፡ በፊቱ ፡ ነበረ ።

ደግሞም ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ፡ ዳሞትም ፡ ወጥቶ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፡ ታላቅ ፡ ግዳይም ፡ ገደላቸው ፡ ዘፊቱ ። ሸሹ ። ሳኦልም ፡ ጦሩን ፡ ይዘ ፡ በዜቱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሰሰ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያዘው ። ዳሞትም ፡ በእጁ ፡ በገና ፡ ደመታ ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ ከግንብ ፡ ጋር ፡ ያጣብቀው ፡ ዘንድ ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ፡ ዳሞትም ፡ ከሳኦል ፡ ፊት ፡ ዘወር ፡ አለ ፡ ጦሩም ፡ በግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ተተከለ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ዳሞት ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ ጠብቀው ፡ በነጋው ፡ እንዲገድሉት ፡ መልእክተኞችን ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ቤት ፡ ላከ ፡ ሚስቱም ፡ ሜልክል — በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ነፍስህን ፡ ካላጸንህ ፡ ነገ ፡ ትገደላለህ ፡ ብላ ፡ ነገረችው ። ሜልክልም ፡ ዳሞትን ፡ በመስኮት ፡ አወረደችው ፡ ሄደም ፡ ሸሽቶም ፡ አመለጠ ። ሜልክልም ፡ ተራፊሙን ፡ ወሰደ ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ አኖረችው ፡ ፀራቡኔውም ፡ ጉንጉን ፡ የፍየል ፡ ጠጉር ፡ አደረገች ፡ በልብሱም ፡ ከደነችው ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ እንዲያመጡት ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፡ እር ስሞም ፡ — ታምሞአል ፡ አስቻቸው ። ሳኦልም ፡ — እኒደልው ፡ ዘንድ ፡ ዳሞትን ፡ ነኝ ፡ አልጋው ፡ አምጡልኝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ሰደደ ። መልእክተኞቹም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ተራፊሙን ፡ በአልጋው ፡ ላይ ፡ እገኙ ፡ በፀራቡኔውም ፡ ጕንጉን ፡ የፍየል ፡ ጠጉር ፡ ነበረ ። ሳኦልም ፡ ሜልክልን ፡ — ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አድርገሽ ፡ አታለልሽኝ ? ጠላቴን ፡ አስኰበለሽ ፡ ሸው ፡ አለት ። ሜልክልም ፡ ሰሳአል ፡ — እርሱ ፡ — አውጥተሽ ፡ ስደኚኝ ፡ አስዚያም ፡ እገድልሻለሁ ፡ አሰኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

ዳሞትም ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ፡ ወደ ፡ አርማቴምም ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣ ፡ ሳኦልም ፡ ያደ

ረገበትን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡ እርሱና ፡ ሳሙኤልም ፡ ሄዱ ፡ በነዋትዘራማም ፡ ተቀመጡ ። ሳኦልም ፡ — ዳሞት ፡ እንህ ፡ በእርማቴም ፡ አገር ፡ በነዋትዘራማ ፡ ተቀምጠአል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ። ሳኦልም ፡ ዳሞትን ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ። የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ ትንቢት ፡ ሲናገሩ ፡ ሳሙኤልም ፡ አሰቃቸው ፡ ሠኖ ፡ ሲቆም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በሳኦል ፡ መልእክተኞች ፡ ላይ ፡ ወረደ ፡ እነርሱም ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ጀመር ። ሳኦልም ፡ ያንን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሌሎች ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ፡ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ። ሳኦልም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ምስተኛ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ፡ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ። የሳኦልም ፡ ቊጣ ፡ ነደደ ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ መጣ ፡ በሚኬኩም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ የውኃ ፡ ጕድጓድ ፡ ደረሰ ። ሳሙኤልና ፡ ዳሞት ፡ የት ፡ ናቸው ? ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ እንድ ፡ ሰውም ፡ — እነሆ ፡ በአርማቴም ፡ አገር ፡ በነዋትዘራማ ፡ ናቸው ፡ አሰው ። ወደ ፡ አርማቴምም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ነዋትዘራማ ፡ ሄደ ። የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በእርሱ ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ፡ እርሱም ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ አርማቴምም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ነዋትዘራማ ፡ አስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ትንቢት ፡ ይናገር ፡ ነበር ። ልብሱንም ፡ አወለቀ ፡ በሳሙኤልም ፡ ፊት ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ ራቁቱንም ፡ ወድቆ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ሁሉ ፡ ተጋደመ ። ስለዚህ ፡ — ሳኦል ፡ ደግሞ ፡ ከነቢያት ፡ መከከል ፡ ነውን ? ይበባሉ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ዳሞትም ፡ ከአርማቴም ፡ አገር ፡ ከነዋትዘራማ ፡ ሸሽ ፡ ወደ ፡ ዮናታንም ፡ መጥቶ ፡ — ምን ፡ አደረግሁ ? አኔንስ ፡ ስመግደል ፡ የሚፈልግ ፡ በአባትህ ፡ ፊት ፡ ጠማምነቴና ፡ ኃጢአቴ ፡ ምን ፡ ድር ፡ ነው ? ብሎ ፡ ተናገረው ። ዮናታንም ፡ — ይህንስ ፡ ያርቀው ፡ አትሞትም ፡ እነሆ ፡ አባቴ ፡ አስቀድሞ ፡ ለእኔ ፡ ሳይገልጥ ፡ ትልቅም ፡ ትንሽም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ አያደርግም ፡ አሰቴስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስምን ፡ ይሰውረኛል ? እንዲህ ፡ አይደለም ፡ አለው ። ዳሞትም ፡ — እኔ ፡ በፊትህ ፡ ሞገስ ፡ እንዳገኘሁ ፡ አባትህ ፡ በእኩንት ፡ ያውቃል ፡ እርሱም ፡ — ዮናታን ፡ እንዳያዝንብኝ ፡ አይወደውም ፡ ይላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ! በሕያው ፡ ነፍስህም ፡ እምላለሁ ! በእኔና ፡ በሞት ፡ መከከል ፡ እንድ ፡ እርምጃ ፡ ያህል ፡ ቀርቶአል ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ — ነፍስህ ፡ የወደደችውን ፡ ሁሉ ፡ እደር ፡ ግልሃለሁ ፡ አሰው ። ዳሞትም ፡ ዮናታንን ፡ አለው ፡ — እነሆ ፡ ነገ ፡ መባቻ ፡ ነው ፡ በንጉሥም ፡ አብገብ ፡ ሰምሳ ፡ አልቀመጥም ፡ አስከ ፡ ምስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በሙሳ ፡ በሜዳ ፡ እንደ ፡ ሸሸግ ፡ አሰናብትኝ ። አባትህም ፡ በጠፋኝ ፡ ጊዜ ፡ በቢያ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ የንሞት ፡ መሥዋዕት ፡ አሰቸውና ፡ ዳሞት ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ፈጥኖ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ አጽንቶ ፡ ለምኖኛል ፡ በስው ። እርሱም ፡ መል ካም ፡ ነው ፡ ቢል ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ደኅንነት ፡ ይሆንልኛል ፡ ቢቈጣ ፡ ግን ፡ ክፋት ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቈረጠች ፡ እወቅ ። እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከእኔን ፡ ከባሪያህ ፡ ጋር ፡ አድርገሃልና ፡ ለባሪያህ ፡ ቸርነት ፡ አድርግ ። በደል ፡ ግን ፡ ቢገኝብኝ ፡ እንተ ፡ ግደለኝ ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ አባትህ ፡ ታደርሰኛለህ ? ዮናታንም ፡ — ይህ ፡ ከእንተ ፡ ይራቅ ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ክፋት ፡ በሳይህ ፡ እንደ ፡ ተቈረጠች ፡ ያወቅሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልነግርህም ፡ ? አለ ። ዳሞትም ፡ ዮናታንን ፡ — አባትህ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የነገረህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ይንግረኛል ? አለው ። ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ — ና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ እንውጣ ፡ አለው ። ሁለቱም ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጡ ።

ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ አለው ፡ — የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ይሁን ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባቴን ፡ መርምሬ ፡ እነሆ ፡ በዳሞት ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ ቢያስብ ፡ ልኬ ፡ አነልኖልሃለሁ ፡ አባቴም ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ ክፉት ፡ ማድረግ ፡ ቢወድድ ፡ እኔም ፡ ብላስታውቅህ ፡ በደህና ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ ባላሰናብትህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በየሩታን ፡ ይሁን ፡ ያድርግ ፡ ይሁንም ፡ ያጨመር ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከአባቴ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ። እኔም ፡ እንዳልሞት ፡ በሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ አድርግልኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዳዊትን ፡ ጠላቶች ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከምድር ፡ ባጠፋቸው ፡ ጊዜ ፡ ስዘላለም ፡ ቸርነትህን ፡ ከቤቱ ፡ አታርቀው ። ዮናታንም ፡ — እግዚአብሔር ፡ ከዳዊት ፡ ጠላቶች ፡ እጅ ፡ ይፈልገው ፡ ብሎ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ። ዮናታንም ፡ ዳሞትን ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ይወድደው ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማሰሰት ።

ዮናታንም ፡ አለው ፡ — ነገ ፡ መባቻ ፡ ነው ፡ መቀመጫህም ፡ ባዶ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛልና ፡ ትታሰበለህ ። ምስት ፡ ቀንም ፡ ያህል ፡ ቆይ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድ ፡ ትንሥሥ ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ተሸሸግህበት ፡ ስፍራ ፡ ሂድ ፡ በኤዜል ፡ ድንጋይም ፡ አጠገብ ፡ ቆይ ። እኔም ፡ በዓላማ ፡ ላይ ፡ እወረውራለሁ ፡ ብዙ ፡ ምስት ፡ ፍላጻዎችን ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ እወረውራለሁ ። እነሆም ፡ ሂድ ፡ ፍላጻዎችን ፡ ፈልግ ፡ ብዙ ፡ ብላቴናውን ፡ እልክሞለሁ ፡ ብላቴናውንም ፡ — እነሆ ፡ ፍላጻው ፡ ከእንተ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ ይሰኸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ና ፡ ያልሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ እግዚአብሔርን ! ለእንተ ፡ ደኅንነት ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ የለብህም ። ብላቴናውን ፡ ግን ፡ — እሠ ፡ ፍላጻው ፡ ከእንተ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ያል

ሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰናብቶሃ
ልና ፡ መንገድህን ፡ ሂድ ። አንተና ፡ እኔም ፣
ስለ ፡ ተነጋገርነው ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘ
ላለም ፡ በመከከላችን ፡ ምስክር ፡ ነው ።
፳፪ ፡ ዳዊትም ፡ በሚጼው ፡ ተሸሸገ ፤ መብቻም ፡
በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ግብር ፡ ለመብላት ፡ ተቀ
፳፫ ፡ መጠ ። ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ በግ
ንቡ ፡ አጠገብ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ዮና
ታንም ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፡ አበኔርም ፡ በሳኦል ፡ አጠ
ገብ ፡ ተቀመጠ ፤ የዳዊትም ፡ ስፍራ ፡ በዶውን ፡
፳፬ ፡ ነበረ ። ሳኔልም ፡ — እንድ ፡ ነገር ፡ ሆኖአል ፡
ንጹሕም ፡ አይደለም ፤ በእውነት ፡ ንጹሕ ፡
አይደለም ፡ ብሎ ፡ አሰበአልና ፣ በዚያን ፡ ቀን ፡
፳፭ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም ። ከመባቻም ፡ በኋላ ፡
በማግሥቱ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ የዳዊት ፡ ስፍራ ፡
በዶውን ፡ ነበረ ፣ ሳኔልም ፡ ልጁን ፡ ዮናታንን ፡ —
የአሴይ ፡ ልጅ ፡ ትናንትና ፡ ወይም ፡ ዛሬ ፡ ማብር ፡
ሊበላ ፡ ያልመጣ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ? አለው ።
፳፮ ፡ ዮናታንም ፡ ለሳኔል ፡ — ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
ልሔም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ አጽንቶ ፡ ለመነኝ ፡
፳፯ ፡ እርሱም ፡ — ዘመዶቹ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መሥ
ዋዕት ፡ አላቸውና ፡ ወንድሜም ፡ ጠርቶኛልና ፡
አሁክህ ፡ አሰናብተኝ ፡ አሁንም ፡ በዓይኖችህ ፡
ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልሂድና ፡ ወን
ድሞቼን ፡ ልይ ፡ አለ ፡ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡
ሰደቃ ፡ አልመጣም ፡ ብሎ ፡ መሰሰለት ።
፳፱ ፡ የሳኔልም ፡ ቊጣ ፡ በዮናታን ፡ ላይ ፡ ነደደና ፡ —
አንተ ፡ የጠማማ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የአሴይን ፡
ልጅ ፡ ለአንተ ፡ ማፈርያ ፡ ለእናትህም ፡ ኀፍረት ፡
ሥጋ ፡ ማፈርያ ፡ እንደ ፡ መረጥህ ፡ አኔ ፡ አላው
፴ ፡ ቅምን ? የአሰይም ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ቢሕ
ይወት ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ አንተና ፡
መንግሥትህ ፡ እትጸኑም ፡ አሁንም ፡ የሞት ፡
ልጅ ፡ ነውና ፡ ልከህ ፡ አስመጣልኝ ፡ አለው ።
፴፩ ፡ ዮናታንም ፡ ለአበቱ ፡ ለሳኔል ፡ — ስለ ፡ ምን ፡
ይሞታል ? ያደረገውስ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብሎ ፡
፴፪ ፡ መለሰለት ። ሳኔልም ፡ ሊወጋው ፡ ጦሩን ፡ ወረ
ወረበት ፡ ዮናታንም ፡ አበቱ ፡ ዳዊትን ፡ ፈጽሞ ፡
፴፫ ፡ ሊገድለው ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ አወቀ ። አበቱ ፡
ዳዊትን ፡ ስለሳፈረው ፡ ዮናታን ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡
አዝኖአልና ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ከሰደቃው ፡
ተነሣ ፡ በመቢቻውም ፡ በሁለተኛ ፡ ቀን ፡ ግብር ፡
አልበላም ።
፴፬ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በነጋው ፡ ዮናታን ፡ ከዳዊት ፡
ጋር ፡ ወደ ፡ ተቃጠረበት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡
ወጣ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡
፴፭ ፡ ነበረ ። ብላቴናውንም ፡ — ሮጠህ ፡ የምወረው
ራቸውን ፡ ፍላጻዎች ፡ ፈልግልኝ ፡ አለው ።
ብላቴናውም ፡ በሮጠ ፡ ጊዜ ፡ ፍላጻውን ፡ ወደ ፡
፴፮ ፡ ማዶ ፡ ወረወረው ። ብላቴናውም ፡ ዮናታን ፡
ፍላጻውን ፡ ወደ ፡ ወረወረበት ፡ ስፍራ ፡ በመጣ ፡
ጊዜ ፡ ዮናታን ፡ — ፍላጻው ፡ ከአንተ ፡ ወዲያ ፡
፴፯ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ብላቴናው ፡ ጮኸ ። ዮና
ታንም ፡ ደግሞ ፡ — ቶሎ ፡ ፍጠን ፡ አትቆይ ፡

ብሎ ፡ ወደ ፡ ብላቴናው ፡ ጮኸ ፡ የዮናታንም ፡
ብላቴና ፡ ፍላጻዎቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡
መጣ ። ዮናታንና ፡ ዳዊት ፡ ብቻ ፡ ነገሩን ፡ ፴፱
ያውቁ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ብላቴናው ፡ ምንም ፡
አያውቅም ፡ ነበር ። ዮናታንም ፡ መሣርያውን ፡ ፵
ለብላቴናው ፡ በጥቶ ፡ — ወደ ፡ ከተማ ፡ ውሰድ ፡
አለው ። ብላቴናውም ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ፵፩
ከስፍራው ፡ በደቡብ ፡ አጠገብ ፡ ተነሣ ፡ በምድ
ርም ፡ ላይ ፡ በግምባሩ ፡ ተደፋ ፡ ሦስት ፡ ጊዜም ፡
ለሰላምታ ፡ ሰገደ ፤ እየተላቀሱም ፡ እርስ ፡ በእ
ርሳቸው ፡ ተሳለሙ ፡ ይልቁንም ፡ ዳዊት ፡ እጅግ ፡
አለቀሰ ። ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፡ — በደኅና ፡ ፵፪
ሂድ ፤ እነሆ ፡ እኛ ፡ ሁለታችን ፡ በእኔና ፡ በአ
ንተ ፡ በዘሬና ፡ በዘርህ ፡ መካከል ፡ ለዘላለም ፡
እግዚአብሔር ፡ ይሁን ፡ ብሰን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ ተማምለናል ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ሄደ ፡ ዮናታንም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ ፩
ወደ ፡ ኖብ ፡ መጣ ፣ አቢሜሌክም ፡ እየተንቀጠ
ቀጠ ፡ ዳዊትን ፡ ሊገናኘው ፡ መጣና ፡ — ስለ ፡
ምን ፡ አንተ ፡ ብቻህን ፡ ነህ ? ከአንተስ ፡ ጋር ፡
ስለ ፡ ምን ፡ ማንም ፡ የለም ? አለው ። ዳዊትም ፡ ፪
ካህኑን ፡ አቢሜሌክን ፡ — የተላከህበትን ፡ ነገ
ርና ፡ የሰጠሁህን ፡ ትእዛዝ ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፡
ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አዝዘኛል ፡ ስለዚ
ህም ፡ ብላቴኖቹን ፡ እንዲህ ፡ በሰ ፡ ስፍራ ፡ ተው
ኋቸው ። አሁንስ ፡ በእጅህ ፡ ምን ፡ አለ ? አም ፫
ስት ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ የተገኘውን ፡ ለእጄ ፡
ስጠኝ ፡ አለው ። ካህኑም ፡ ለዳዊት ፡ መልሶ ፡ — ፬
ሁሉ ፡ የሚበላው ፡ እንጀራ ፡ የለኝም ፡ ነገር ፡
ግን ፡ የተቀደሰ ፡ እንጀራ ፡ አለ ፤ ብላቴኖቹ ፡ ከሴ
ቶች ፡ ንጹሐን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ መብላት ፡ ይቻ
ላል ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ለካህኑ ፡ መልሶ ፡ — ፭
በእውነት ፡ ከወጣን ፡ ጀምረን ፡ እኛ ፡ ሰውነታ
ችንን ፡ ከሴቶች ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጠብቀናል ፤
የብላቴኖችም ፡ ዕቃ ፡ የተቀደሰች ፡ ናት ፤ ስለ
ዚህ ፡ ዛሬ ፡ ዕቃቸው ፡ የተቀደሰች ፡ በመሆንዋ ፡
እንጀራው ፡ እንደሚበላ ፡ እንጀራ ፡ ይሆናል ፡
አለው ። ካህኑም ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ትኩስ ፡ ፮
እንጀራ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ከተነሣው ፡ ከገጹ ፡ ኅብስት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡
እንጀራ ፡ አልነበረምና ፡ የተቀደሰውን ፡ እን
ጀራ ፡ ሰጠው ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ክሳሌል ፡ በሬያዎች ፡ አንድ ፯
በው ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፊት ፡ ተገኝቶ ፡
ነበር) ስሙም ፡ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ ነበረ ፡
ለሳኔል ፡ የእረኞቹ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ። ዳዊትም ፡ ፰
አቢሜሌክን ፡ — የንጉሥ ፡ ጉዳይ ፡ ስላስቸኰ
ለኝ ፡ ሰይፌንና ፡ መሣርያዬን ፡ አላመጣሁምና ፡
በእንተ ፡ ዘንድ ፡ ጦር ፡ ወይም ፡ ሰይፍ ፡ አለ ፡
ወይ ? አለው ። ካህኑም ፡ — በኤላ ፡ ሸለቆ ፡ የገደ ፱
ልኸው ፡ የፍልስጥኤማዊው ፡ የጎልያድ ፡ ሰይፍ ፡

እነሆ ፡ በመጐናጸፊያ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ከዚህ ፡
ከኤፉዱ ፡ በኋላ ፡ አለ ፡ ተወደደውም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ውሰደው ፡ ሌላ ፡ ከዚህ ፡ የለም ፡ አለ ።
ዳዊትም ፡ — እንደ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ የለምና ፡ እር
ሱን ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።
፲ ፡ ዳዊትም ፡ ተነሣ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኤልን ፡
ፈርቶ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ጌትም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አን
፲፩ ፡ ኩስ ፡ ሄደ ። የአንኩስ ፡ ባሪያዎችም ፡ — ይህ ፡
ዳዊት ፡ የአገሩ ፡ ንጉሥ ፡ አይደለምን ? ሳኤል ፡
ሺህ ፡ ዳዊትም ፡ እልፍ ፡ ገደለ ፡ ብለው ፡ ሴቶች ፡
በዘፈን ፡ የዘመሩለት ፡ እርሱ ፡ አይደለምን ?
፲፪ ፡ አሉት ። ዳዊትም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በልቡ ፡
አኖረ ፡ የጌትንም ፡ ንጉሥ ፡ አንኩስን ፡ እጅግ ፡
፲፫ ፡ ፈራ ። በፊታቸውም ፡ አእምሮውን ፡ ሰወጠ ፡
በያዙትም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ ሆነ ፡ በበ
ራም ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ተንፈራፈረ ፡ ልጋጉም ፡
በጢሙ ፡ ላይ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ። አንኩስም ፡
፲፬ ፡ በሪያዎቹን ፡ — እነሆ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እብድ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ አይታችኋል ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
፲፭ ፡ አመጣችሁት ? በፊቴ ፡ ያብድ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡
ያመጣችሁት ፡ እብድ ፡ ጠፍቶብኝ ፡ ነውን ? እን
ዲህ ፡ ያለውስ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ይገባልን ? አለ
ቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ ተነሣ ፡ ወደ ፡ ዓዶላም ፡ ፩
ዋሻ ፡ ኩበለል ፡ ወንድሞቹና ፡ የአባቱ ፡ ቤተ ፡
ሰብ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
፪ ፡ ወደዚያ ፡ ወረዱ ። የተጨነቀም ፡ ሁሉ ፡ ብድ
ርም ፡ ያሰበት ፡ ሁሉ ፡ የተከፋም ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ ተከማቸ ፡ እርሱም ፡ በላያቸው ፡
አለቃ ፡ ሆነ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አራት ፡ መቶ ፡
የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።
፫ ፡ ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ በሞዓብ ፡ ምድር ፡ ወዳለ ፡
ችው ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ሄደ ፤ የሞዓብንም ፡
ንጉሥ ፡ — እግዚአብሔር ፡ የሚያደርግልኝን ፡
እስከማውቅ ፡ ድረስ ፡ አባቴና ፡ እናቴ ፡ ከእንተ ፡
ጋር ፡ ይቆዩ ፡ ዘንድ ፡ እሰምንሃለሁ ፡ አለው ።
፬ ፡ በሞዓብም ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ አመጣቸው ፡ ዳዊ
ትም ፡ በአምባ ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ወራት ፡
፭ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ። ነቢዩ ፡
ጋድም ፡ ዳዊትን ፡ — ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡
ምድር ፡ ሂድ ፡ እንጂ ፡ በአምባው ፡ ውስጥ ፡ አት
ቀመጥ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡
ሔሬት ፡ ዱር ፡ መጣ ።
፮ ፡ ሳኤልም ፡ ዳዊትና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡
አንደ ፡ ተገለጡ ፡ ሰማ ። ሳኤልም ፡ በጌብዓ ፡ በአ
ጣጥ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ በከረብታው ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ በእጁም ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ነበር ፡ ባሪያዎቹም ፡
፯ ፡ ሁሉ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆመው ፡ ነበር ። ሳኤልም ፡
በአጠገቡ ፡ የቆሙትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ — ብንያማ
ውያን ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ስሙ ፡ በውኑ ፡ የእ
ሴይ ፡ ልጅ ፡ እርሻና ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ለሁላችሁ ፡
ይሰጣችኋልን ? ሁላችሁንስ ፡ ሽለቆችና ፡ የመቶ ፡
አለቆች ፡ ያደርጋችኋልን ? ሁላችሁ ፡ በላዩ ፡ ፰
ዶልታችሁ ፡ ተነሣችሁብኝ ፡ ልጄ ፡ ከአሴይ ፡
ልጅ ፡ ጋር ፡ ሲማማል ፡ ማንም ፡ አይገልጥልኝም ፡
ከእናንተም ፡ አንድ ፡ ለእኔ ፡ የሚያዝን ፡ የለም ፡
ዛሬም ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ ሁሉ ፡ ልጄ ፡ ባሪያዬን ፡
እንዲያደፍት ፡ ሲያስነሣብኝ ፡ ማንም ፡ አላስታወ
ቀኝም ፡ አላተው ። በሳኤልም ፡ በሪያዎች ፡ አጠ ፱
ገብ ፡ የቆመው ፡ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ መልሶ ፡ —
የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኖብ ፡ ወደ ፡ አኪጦብ ፡ ልጅ ፡
ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ ሲመጣ ፡ አይቼዋለሁ ። እግ ፲
ዚአብሔርንም ፡ ጠየቀለት ፡ ስንቅንም ፡ ሰጠው ፡
የፍልስጥኤማዊውንም ፡ የጎልያድን ፡ ሰይፍ ፡
ሰጠው ፡ አለ ።
ንጉሡም ፡ የአኪጦብን ፡ ልጅ ፡ ካህኑን ፡ አቢ ፲፩
ሜሌክን ፡ በሮጦም ፡ ያሉትን ፡ ከህናት ፡ የአባ
ቱን ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ልከ ፡ አስጠራቸው ፡ ሁላቸ
ውም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጡ ። ሳኤልም ፡ — የአ ፲፪
ኪጦብ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ስማ ፡ አለ ፡
እርሱም ፡ — እነሆኝ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡
መለሰ ። ሳኤልም ፡ — አንተና ፡ የአሴይ ፡ ልጅ ፡ ፲፫
ለምን ፡ ዶለታችሁብኝ ? እንጀራና ፡ በይፍ ፡
ሰጠኸው ፡ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ጠላት ፡
ሆኖ ፡ ይነሣብኝ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡
እርሱ ፡ ጠየቅህለት ፡ አለው ። አቢሜሌክም ፡ ፲፬
መልሶ ፡ ንጉሡን ፡ — ከባሪያዎችህ ፡ ሁሉ ፡ የታ
መነ ፡ ለንጉሥም ፡ አማች ፡ የሆነ ፡ በትእዛዝህ ፡
የሚሄድ ፡ በቤትህም ፡ የከበረ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡
ያለ ፡ ማን ፡ ነው ? በውኑ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ እግዚ ፲፭
አብሔርን ፡ እጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ጀመርሁን ?
ይህ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ፡ እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
እጅግ ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ቢሆን ፡ አላውቅምና ፡
ንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ በእኔ ፡ በባ
ሪያውና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አያኑር ፡
አለ ። ንጉሡም ፡ — አቢሜሌክ ፡ ሆይ ፡ አን ፲፮
ተና ፡ የአባትህ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማችሁ ፡ ትሞ
ታላችሁ ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ በዙሪያው ፡ የቆሙ ፲፯
ትን ፡ እግረኞች ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡
እጅ ፡ ከዳዊት ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ሰተብለላውንም ፡
ሲያውቁ ፡ በጆሮዬ ፡ አልገለጡምና ፡ ዘራችሁ ፡
ግደሉአቸው ፡ አላቸው ። የንጉሡ ፡ በሪያዎች ፡
ግን ፡ እጃቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡
ላይ ፡ ይዘረጉ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አሉ ። ንጉሡም ፲፰
ዶይቅን ፡ — አንተ ፡ ዙረህ ፡ በካህናቱ ፡ ላይ ፡ ውደ
ቀበቸው ፡ አለው ። ኤዶማዊውም ፡ ዶይቅ ፡
ዙሮ ፡ በካህናቱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡
የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ የለበሱትን ፡ ሰማንያ ፡ አም
ስት ፡ ሰዎች ፡ ገደለ ። የካህናቱንም ፡ ከተማ ፲፱
ኖብን ፡ በስይፍ ፡ ስለት ፡ መታ ፡ ወንዶችንና ፡
ሴቶችንም ፡ ብላቴኖችንና ፡ ጡት ፡ የሚጠቡ ፡
ትን ፡ በሬዎችንና ፡ አህዮችንም ፡ በጎችንም ፡
በስይፍ ፡ ስለት ፡ ገደለ ።
ከአኪጦብም ፡ ልጅ ፡ ከአቢሜሌክ ፡ ልጆች ፡ ፳
ስሙ ፡ አብያታር ፡ የሚባል ፡ አንዱ ፡ ልጅ ፡ አም
ልጦ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ሸሸ ። አብያታርም ፡ ሳኤል ፡ ፳፩

የእግዚአብሔርን ፡ ከሀናት ፡ እንደ ፡ ፈጀ ፡ ሰዳ
ሽ፪፡ ሞት ፡ ነገረው ። ዳዊት ፡ አብያታርን ፡— ኤዶማ
ዊው ፡ ዶይቅ ፡ በዚያ ፡ መኖሩን ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡—
ለሳኦል ፡ በእርግጥ ፡ ይነግራል ፡ ብዬ ፡ በዚያው ፡
ቀን ፡ እውቂዋለሁ ፡ ለእበትህ ፡ ቤት ፡ ነፍስ ፡
ሁሉ ፡ የጥፋታቸው ፡ ምክንያት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
ሽ፫፡ ነፍሴን ፡ የሚፈልግ ፡ የእንተን ፡ ነፍስ ፡ ይፈል
ጋልና ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ተጠብቀህ ፡ ትኖራለ
ህና ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥ ፡ አትፍራ ፡ አሰው ።

ምዕራፍ ፡ ሽር ።

፩፡ ለዳዊትም ፡— እነሆ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡
ቅዒላን ፡ ይወጋሉ ፡ አውድማውንም ፡ ይዘር
፪፡ ፋሉ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ደረሰው ። ዳዊትም ፡—
ልሂድን ? እነዚህንስ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ልም
ታን ? ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፡ እግዚ
አብሔርም ፡ ዳዊትን ፡— ሂድ ፡ ፍልስጥኤማው
፫፡ ያንን ፡ ምታ ፡ ቅዒላንም ፡ እድን ፡ አሰው ። የዳ
ዊትም ፡ ሰዎች ፡— እነሆ ፡ በዚህ ፡ በይሁዳ ፡
መቀመጥ ፡ እንፈራለን ፡ ይልቁንስ ፡ በፍልስጥ
ኤማውያን ፡ ጭፍሮች ፡ ላይ ፡ ወይ ፡ ቅዒላ ፡ ብን
፬፡ ሄድ ፡ እንዴት ፡ ነው ? አሉት ። ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፡ እግዚአብሔርም ፡
መልሶ ፡— ፍልስጥኤማውያንን ፡ በእጅህ ፡ አሳ
ልፌ ፡ እሰጣለሁና ፡ ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡
፭፡ ውረድ ፡ አለው ። ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወደ ፡
ቅዒላ ፡ ሄዱ ፡ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋር ፡
ተዋጉ ፡ እንስሶቻቸውንም ፡ ማረኩ ፡ በታላ
ቅም ፡ አገዳደል ፡ ገደሉአቸው ። ዳዊትም ፡ በቅ
ዒላ ፡ የሚኖሩትን ፡ አዳነ ።

፮፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ የአቢሜሉክ ፡ ልጅ ፡ አብ
ያታር ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ በኩበለሰ ፡
፯፡ ጊዜ ፡ ኤፉዱን ፡ ይዘ ፡ ወረዶ ፡ ነበር ። ሳኤልም ፡
ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሰማ ፡ ሳኤ
ልም ፡— መዝጊያና ፡ መወርወሪያ ፡ ወዳለበት ፡
ከተማ ፡ ገብቶ ፡ ተገኝቶአልና ፡ እግዚአብሔር ፡
፰፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፡ አሰ ። ሳኤልም ፡
ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ወረደው ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡
ና ፡ ሰዎቹንም ፡ ይከብቡ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡
፱፡ ሁሉ ፡ አዘዘ ። ዳዊትም ፡ ሳኤል ፡ ክፉን ፡ እንዳ
ሰበበት ፡ አወቀ ፡ ከሀኑን ፡ አብያታርንም ፡—
፲፡ ኤፉዱን ፡ ወደዚህ ፡ አምጣ ፡ አሰው ።ዳዊትም ፡—
የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡ በእኔ ፡ ምክን
ያት ፡ ከተማይቱን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ሳኤል ፡ ወደ ፡
፲፩፡ ቅዒላ ፡ ሊመጣ ፡ እንደሚፈልግ ፡ እኔ ፡ ብረያህ ፡
ፈጽሚ ፡ ሰምቻለሁ ። የቅዒላ ፡ ሰዎች ፡ በእጁ ፡
እሳልፈው ፡ ይሰጡኛልን ? በረያህስ ፡ እንደ ፡
ሰማ ፡ ሳኤል ፡ በውኑ ፡ ይመርዳልን ? የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ አቤቱ ፡ እንድትነግረኝ ፡ እለምንሃ
ሰው ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፡— ይወርዳል ፡
፲፪፡ አለ ። ዳዊትም ፡— የቅዒላ ፡ ሰዎች ፡ እኔንና ፡
ሰዎቼን ፡ በሳኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡኛ
ልን ? አለ ። እግዚአብሔርም ፡— አሳልፈው ፡
፲፫፡ ይሰጡአችኋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ዳዊትና ፡ ለድ
ስት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፡
ከቅዒላ ፡ ወጡ ። መሄድም ፡ ወደሚችሉበት ፡
ሄዱ ። ሳኤልም ፡ ዳዊት ፡ ከቅዒላ ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡
ሰማ ፡ ስለዚህም ፡ ከመውጣት ፡ ቀረ ።

፲፬፡ ዳዊትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በእምባ ፡ ውስጥ ፡
ደኖር ፡ ነበር ። ከዘፍ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ባለው ፡
በተራራማው ፡ አገር ፡ ተቀመጠ ፡ ሳኤልም ፡
ሁልጊዜ ፡ ይፈልገው ፡ ነበር ። እግዚአብሔር ፡
፲፭፡ ግን ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠውም ። ዳዊ
ትም ፡ ሳኤል ፡ ነፍሱን ፡ ሊፈልግ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡
አየ ፡ ዳዊትም ፡ በዘፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በየሸው ፡
ውስጥ ፡ ደኖር ፡ ነበር ። የሳኤልም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡
፲፮፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጥሻው ፡ ውስጥ ፡
ሄደ ፡ እጁንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጽንቶ ፡—
፲፯፡ የእዙ ፡ የሳኤል ፡ እድ ፡ አታገኝህምና ፡ አትፍራ ፡
አንተም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትሆና
ለህ ፡ አኔም ፡ ከአንተ ፡ በታች ፡ ሁለተኛ ፡ እሆ
ናለሁ ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ አባቴ ፡ ሳኤል ፡ ያው
፲፰፡ ቃል ፡ አሰው ። ሁለቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ። ዳዊትም ፡ በጥ
ሻው ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ፡ ዮናታንም ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ ሄደ ።

፲፱፡ የዘፍ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ሳኤል ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡
መጥተው ፡— እነሆ ፡ ዳዊት ፡ በየሴሞን ፡ ይሁዋ
በኩል ፡ በኤኬላ ፡ ከረጋታ ፡ ላይ ፡ በጥሻ ፡ ውስጥ ፡
ባሉት ፡ አምበሎች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡
የለምን ? አሁንም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ትወርድ ፡
፳፡ ዘንድ ፡ ነፍስህ ፡ እንደ ፡ ወደደች ፡ ውረድ ፡ በን
ጉሥም ፡ እጅ ፡ እርሱን ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡
እኛ ፡ አሰን ፡ አሉት ። ሳኤልም ፡ አለ ፡— እና ፡
ንተ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ አዝናችኋልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡
፳፩፡ ዘንድ ፡ የተባረክችሁ ፡ ሁኑ ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡
ሂዱ ፡ እርሱም ፡ እሮሮ ፡ ተንኰለኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ሰምቻለሁና ፡ አጥብቃችሁ ፡ ፈልጉት ፡ እግ
ሩም ፡ የሚሄድበትን ፡ ስፍራ ፡ እዩና ፡ እወቁ ፡
፳፪፡ በዚያ ፡ ያየውንም ፡ ሰው ፡ እግኝ ። እርሱ ፡
የሚደበቅበትንና ፡ የሚሸሸግበትን ፡ ስፍራ ፡
እየና ፡ እወቁ ፡ በእርግጥም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመ
ለሱ ፡ እኔም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እሄዳለሁ ፡ ብም
፳፫፡ ድርም ፡ ውስጥ ፡ ቢሸሸግ ፡ በይሁዳ ፡ አእላፋት ፡
ሁሉ ፡ መከከል ፡ እፈልገዋለሁ ።

፳፬፡ እነዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ከሳኤል ፡ በፊት ፡
ወደ ፡ ዚፍ ፡ ሄዱ ፡ ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ ግን ፡ በየሴ
ሞን ፡ ይሁዋ ፡ በኩል ፡ በኤረባ ፡ በማያን ፡ ምድረ ፡
፳፭፡ በዳ ፡ ነበሩ ። ሳኤልና ፡ ሰዎቹም ፡ ሊፈልጉት ፡
ሄዱ ፡ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዓለቱ ፡
ወርዶ ፡ በማያን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተቀመጠ ፡ ሳኤ
ልም ፡ ያንን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊትን ፡ በማያን ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ አሳደደው ። ሳኤልም ፡ በተራ
፳፮፡ ራው ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ሄደ ፡ ዳዊትና ፡ ሰዎ
ቹም ፡ በተራራው ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሄዱ ።
ሳኤልና ፡ ሰዎቹም ፡ ዳዊትንና ፡ ሰዎቹን ፡ ለመ
ያዝ ፡ ከብበዋቸው ፡ ነበርና ፡ ዳዊት ፡ ከሳኤል ፡
፳፯፡ ፊት ፡ ያመልጥ ፡ ዘንድ ፡ ፈጠነ ። መደ ፡ ሳኤልም ፡

መልእክተኛ ፡ መጥቶ ፡— ፍልስጥኤማውያን ፡
እነሩን ፡ ወርረውታልና ፡ ፈጥነህ ፡ ና ፡ አለው ።
ሽ፰፡ ሳኤልም ፡ ዳዊትን ፡ ማለደድ ፡ ትቶ ፡ ተመሰሰ ፡
ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋር ፡ ሊዋጋ ፡ ሄደ ። ስለ
ዚህ ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የማምሰጥ ፡ ዓለት ፡
ሽ፱፡ ተበለ ። ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ በዓይንጋዲ ፡
አምባዎች ፡ ተቀመጠ ።

ምዕራፍ ፡ ሽ፬ ።

፩፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ሳኤል ፡ ፍልስጥኤማውያ
ንን ፡ ከማሳደድ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡
ዳዊት ፡ በዓይንጋዲ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አለ ፡ የሚል ፡
፪፡ ወሬ ፡ ደረሰለት ። ሳኤልም ፡ ከእስራኤል ፡ ሁሉ ፡
የተመረጡትን ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ፡
ዳዊትንና ፡ ሰዎቹንም ፡ ለመፈለግ ፡ የበረዘ ፡ ፍየ
፫፡ ሎች ፡ መደ ፡ ነበሩባቸው ፡ ዓሰቶች ፡ ሄደ ። በመ
ንገድም ፡ አጠገብ ፡ ወዳሉት ፡ የበጎች ፡ ማደሪ
ያዎች ፡ መጣ ፡ በዚያም ፡ ዋሻ ፡ ነበረ ፡ ሳኤልም ፡
ወገቡን ፡ ይሸከር ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ገባ ። ዳዊ
፬፡ ትና ፡ ሰዎቹም ፡ ከዋሻው ፡ በውስጠኛው ፡ ቦታ ፡
ተቀምጠው ፡ ነበር ። የዳዊትም ፡ ሰዎች ፡—
እነሆ ፡ ጠላትህን ፡ በእጅህ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠ
ዋሰሁ ፡ በዓይንህም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝህን ፡ ታደ
ርግበታለህ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የነገርህ ፡
ቀን ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ አሉት ። ዳዊትም ፡
ተነሥቶ ፡ የሳኤልን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ዘርፍ ፡ በቀ
፭፡ ስታ ፡ ቈረጠ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡
የሳኤልን ፡ የልብሱን ፡ ዘርፍ ፡ ስለ ፡ ቈረጠ ፡ የዳ
፮፡ ዊት ፡ ልብ ፡ በጎዘነ ፡ ተመታ ። ሰዎቹንም ፡—
እግዚአብሔር ፡ የቀባው ፡ ነውና ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በቀባው ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ
ውን ፡ ነገር ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እጀንም ፡ እጥል
በት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ያርቀው ፡
፯፡ አላቸው ። ዳዊትም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ሰዎቹን ፡
ከሰከላቸው ፡ በሳኤልም ፡ ላይ ፡ ይነሡ ፡ ዘንድ ፡
አልተዋቸውም ፡ ሳኤልም ፡ ከዋሻው ፡ ተነሥቶ ፡
መንገዱን ፡ ሄደ ።

፰፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ ተነሣ ፡
ከዋሻውም ፡ ወጣ ፡ ከሳኤልም ፡ በኋላ ፡— ጌታዬ ፡
ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፡ ሳኤልም ፡ ወደ ፡
ኋላው ፡ ተመለከተ ፡ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡
፱፡ ተጐንብሶ ፡ እጅ ፡ ነሣ ። ዳዊትም ፡ ሳኤልን ፡
አለው ፡— እነሆ ፡ ዳዊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይሻብ
ሃል ፡ የሚሉህን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ለምን ፡ ትሰማ
፲፡ ሰህ ? እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በዋሻው ፡ ውስጥ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠህ ፡ ዓይ
ንህ ፡ አይታለች ፡ አንተንም ፡ እንድንደልህ ፡
ሰዎች ፡ ተናገሩኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡— በእግዚአብ
ሔር ፡ የተቀባ ፡ ነውና ፡ እጄን ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡
፲፩፡ አልዘረጋም ፡ ብዬ ፡ ራራሁልህ ። ደግሞም ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ የልብስህ ፡ ዘርፍ ፡ በእጄ ፡ እንዳለ ፡
ተመልከተህ ፡ እወቅ ፡ የልብስህንም ፡ ዘርፍ ፡
በቈረጥሁ ፡ ጊዜ ፡ አልገደልሁህም ፡ ስለዚህም ፡
በእጄ ፡ ክፋትና ፡ በደል ፡ እንደሌለ ፡ አንተም ፡

ነፍሴን ፡ ልትወስድ ፡ ምንም ፡ ብታሳድደኝ ፡ እን
ዳልበደልሁህ ፡ ተመልከተህ ፡ እወቅ ። እግዚ
፲፪፡ አብሔር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መከከል ፡ ይፍረድ ፡
እግዚአብሔርም ፡ አንተን ፡ ይበቀልልኝ ፡ እጄ ፡
ግን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ አትሆንም ። በጥንት ፡
፲፫፡ ምሳሌ ፡— ከኃጢአተኞች ፡ ኃጢአት ፡ ይወ
ጣል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ እጄ ፡ ግን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡
አትሆንም ። የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ማንን ፡ ሰማ
፲፬፡ ሰይድ ፡ መጥቶአል ? እንተስ ፡ ማንን ፡ ታሳድዳ
ለህ ? የሞተ ፡ ውሻን ፡ ወይስ ፡ ቁንጫን ፡ ታሳድ
ዳለህን ? እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳኛ ፡
፲፭፡ ይሁን ፡ በእኔና ፡ በእንተም ፡ መከከል ፡ ይፍ
ረድ ፡ አይቶም ፡ ይምዋገትልኝ ፡ ከእጅህም ፡
ያድነኝ ።

፲፮፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሰባ
ለል ፡ መናገር ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሳኤል ፡— ልጄ ፡
ሆይ ፡ ዳዊት ፡ ይህ ፡ ድምፅህ ፡ ነውን ? አለ ፡
ሳኤልም ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።
፲፯፡ ዳዊትን ፡ አሰው ፡— እኔ ፡ ክፉ ፡ በመለስሁልህ ፡
ፋንታ ፡ በጎ ፡ መልሰህልኛልና ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡
ይልቅ ፡ ጻድቅ ፡ ነህ ። እግዚአብሔርም ፡ በእ
፲፰፡ ጅህ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶኝ ፡ ሳለ ፡ አልገደልኸኝ
ምና ፡ ለእኔ ፡ መልካም ፡ እንዳደረግህልኝ ፡
አንተ ፡ ዛሬ ፡ አሳየኸኝ ። ጠላቱን ፡ አግኝቶ ፡
፲፱፡ በመልካም ፡ መንገድ ፡ ሸኝቶ ፡ የሚሰድድ ፡
ማን ፡ ነው ? ስለዚህ ፡ ለእኔ ፡ ስለደረግኸው ፡
ቸርነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመልስልህ ። አሁ
፳፡ ንም ፡ እነሆ ፡ እንተ ፡ በእርግጥ ፡ ንጉሥ ፡ እንድ
ትሆን ፡ የእስራኤልም ፡ መንግሥት ፡ በእጅህ ፡
እንድትጸና ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ። አሁን ፡ እንግ
፳፩፡ ዲህ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ዘራን ፡ እንዳትቈርጥ ፡ ከአ
ባቴም ፡ ቤት ፡ ስሜን ፡ እንዳታጠፋው ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ማልልኝ ። ዳዊትም ፡ ለሳኦል ፡
፳፪፡ ማለለት ። ሳኤልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ዳዊትና ፡
ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ ወጡ ።

ምዕራፍ ፡ ሽ፭ ።

፩፡ ሰሙኤልም ፡ ሞተ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡
ተሰብሰበው ፡ አለቀሱለት ። በአርማቴምም ፡
በቤቱ ፡ ቀበሩት ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡
ፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወረደ ።

፪፡ በማደንም ፡ የተቀመጠ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡
ከብቶቹም ፡ በቀርሜሎስ ፡ ነበረ ፡ እጅግም ፡ ታላቅ ፡
ሰው ፡ ነበረ ። ለእርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ በጎ
ችና ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ፍየሎች ፡ ነበሩት ። በቀር
፫፡ ሜሎስም ፡ በጎቹን ፡ ይሸልት ፡ ነበር ። የሰውዮ
ውም ፡ ሰም ፡ ናባል ፡ የሚስቱም ፡ ሰም ፡ አቢ
ግያ ፡ ነበረ ፡ የሴቲቱም ፡ አእምሮ ፡ ታላቅ ፡
መልክም ፡ የተዋበ ፡ ነበረ ፡ ሰውዮው ፡ ግን ፡
፬፡ ባለጌ ፡ ነበረ ፡ ግብሩም ፡ ክፋ ፡ ነበረ ፡ ከከሌብም ፡
ወገን ፡ ነበረ ። ዳዊትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሰሰ ፡—
፭፡ ናባል ፡ በጎቹን ፡ ይሸልታል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡
ሰማ ። ዳዊትም ፡ አሥር ፡ ጕልማሶች ፡ ላከ ፡ ለጕ
፮፡ ልማሶችም ፡ አሰ ፡— ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ወጥታ

ችሁ ፡ ወደ ፡ ናባል ፡ ሂዱ ÷ በስሜም ፡ ስለ ፡
፭፡ ሰላም ፡ ጠይቁት ፡ እንዲህም ፡ በሉት ፡— በደ
ኅንነት ፡ ኑር ÷ ለአንተና ፡ ለቤትህም ፡ ለአንተም ፡
፮፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ። እውንም ፡ በጎ
ችህን ፡ እንድትሸልት ፡ ሰምቻለሁ ፡ እረኞች
ዘንድ ፡ ነበርህ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ÷ ከቶ ፡ አልበደል
ናቸውም ፡ በቀርሜሎስም ፡ ዘመንህ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡
፰፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከመንጋው ፡ አንዳች ፡ አልጐደ
ለባቸውም ። ጕልማሶችህን ፡ ወይቃቸው ፡
እነርሱም ፡ ይነግሩሃል ፡ አሁንም ፡ እንግዲህ ፡
ዘመልከም ፡ ቀን ፡ መጥተንብሃልና ፡ ጕልማሶች ፡
በፊትህ ፡ ሞገስ ፡ ያግኙ ፡ በእጅህም ፡ ከተገ
ኘው ፡ ለባሪያዎችህና ፡ ለልጅህ ፡ ለዳዊት ÷ እስ
ከዘ ፡ ስጥ ።

፱፡ የዳዊትም ፡ ጕልማሶች ፡ መጡ ÷ ይህንም ፡
ቃል ፡ ሁሉ ፡ በዳዊት ፡ ስም ፡ ለናባል ፡ ነግረው ፡
፲፡ ዝም ፡ አሉ ። ናባልም ፡ ለዳዊት ፡ ሰረያዎች ፡— ዳ
ዊት ፡ ማን ፡ ነው ? የእሴይስ ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ነው ?
እያንዳንዳቸው ፡ ከጌቶቻቸው ፡ የኰበለሉ ፡ ባሪያ
፲፩፡ ዎች ፡ ዛሬ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እንጀራዬንና ፡
የወይን ፡ ጠጀን ፡ ለሸላቾቼም ፡ ያረድሁትን ፡
ሥጋ ፡ ወስጀ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ለማላ
ውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ አሰማስኩን ? ብሎ ፡ መሰሰ
፲፪፡ ሳቸው ። የዳዊትም ፡ ጕልማሶች ፡ ዞረው ፡ በመ
ጡበት ፡ መንገድ ፡ ተመለሱ ÷ መጥተውም ፡
፲፫፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ። ዳዊትም ፡
ሰዎቹን ፡— ሁላችሁ ፡ ሰይፋችሁን ፡ ታጠቁ ፡
አላቸው ። ሁሉም ፡ ሰይፋቸውን ፡ ታጠቁ ÷
ዳዊትም ፡ ሰይፉን ፡ ታጠቀ ፡ አራት ፡ መቶ ፡
ሰዎችም ፡ ዳዊትን ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ÷ ሁለት ፡
መቶውም ፡ በሰቃው ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።

፲፬፡ ዝብላቴኖቹ ፡ አንዱ ፡ ለናባል ፡ ሚስት ፡ ለአ
ቢግያ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራት ፡— እነሆ ÷
ዳዊት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳለ ፡ ጌታችንን ፡ ሊሰ
ርከው ፡ መልእክተኞች ፡ ላከ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሰደበ
፲፭፡ ቸው ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡
እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበሩ ፡ አልበደሉንምም ÷
ከእነርሱም ፡ በጅንበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በም
ድረ ፡ በዳ ፡ ሳለን ፡ እንዳች ፡ አልጠፋብንም ፡
፲፮፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ መንጋውን ፡ በጠበቅን
በት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አጥር ፡
፲፯፡ ሆነውን ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ በጌታችንና ፡ በቤቱ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዲመጣ ፡ ተወሬጠ
አልና ÷ እርሱ ፡ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ማንም ፡ ሊናገረው ፡ አይችልምና ፡ የምታደር
ጊውን ፡ ተመልከቺና ፡ እወቂ ።

፲፰፡ አቢግያም ፡ ፈጥና ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ እንጀራ ÷
ሁለት ፡ አቁማዳ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ÷ አምስትም ፡
የተዘጋጁ ፡ በጎች ÷ አምስትም ፡ መስፈሪያ ፡
ጥብስ ፡ እሸት ÷ አንድ ፡ መቶ ፡ ዘለላ ፡ ዘቢብ ÷
ሁለት ፡ መቶም ፡ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ ወሰደች ÷ ለአ
፲፱፡ ህዮችም ፡ ሳይ ፡ አስጫነች ። ለብላቴኖችዋም ፡— አስቀድማችሁ ፡ በፊቴ ፡ ሂዱ ÷ እነሆም ÷ እከተ
ላችኋለሁ ፡ አለች ። ይህንም ፡ ስበልዋ ፡ ለናባል ፡

አልነገረችውም ። እርስዋም ፡ በአህያዋ ፡ ላይ ፡ ሸ፡
ተቀምጣ ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ በተሰወረ ፡ ስፍራ ፡
ስወረደች ፡ ጊዜ ÷ እነሆ ÷ ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ ወደ ፡
እርስዋ ፡ መጡ ። እርስዋም ፡ ተገናኘቻቸው ።
ዳዊትም ፡— ለዚህ ፡ ሰው ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ ሸ፩፡
እንድ ፡ ነገር ፡ እንዳደጠፋበት ፡ በእውነት ፡ ከጣ
ቱን ፡ ሁሉ ፡ ስምድረ ፡ በዳ ፡ ስከንቱ ፡ ጠበቅሁ ÷
እርሱም ፡ ስለ ፡ በጎነቱ ፡ ክፋት ፡ መለሰልኝ ።
ስእርሱም ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ጥዦት ፡ ሸ፪፡
ድረስ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ስኀኒ ፡ ብተው ÷ እግዚ
አብሔር ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያድርግ ፡
እንዲህም ፡ ይጨምር ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

አቢግያም ፡ ዳዊትን ፡ ስየች ፡ ጊዜ ፡ ከአህያዋ ፡ ሸ፫፡
ላይ ፡ ፈጥና ፡ ወረደች ÷ በዳዊትም ፡ ፊት ፡ በግ
ምባርዋ ፡ ወደቀች ÷ በምድርም ፡ ላይ ፡ እጅ ፡
ነሣች ። በእግሩም ፡ ላይ ፡ ወደቀች ÷ እንዲህም ፡
አለች ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ ይህ ፡ ኀጢአት ፡ በእኔ ፡
ላይ ፡ ይሁን ፡ እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ስጀርህ ፡ ልናገር ÷ ሸ፬፡
የስሪያዘንም ፡ ቃል ፡ አድምጥ ። በዚህ ፡ ምና
ምንቴ ፡ ሰው ፡ በናባል ፡ ላይ ፡ ጌታዬ ፡ ልቡን ፡
እንዳይጥል ፡ እስምናለሁ ፡ እንደ ፡ ስሙ ፡ እን
ዲሁ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ስሙ ፡ ናባል ፡ ነው ÷ ስን
ፍናም ፡ አድሮበታል ፡ እኔ ፡ ስሪያህ ፡ ግን ፡ ከአ
ንተ ፡ የተላኩትን ፡ የጌታዬን ፡ ጕልማሶች ፡
አላየሁም ። አውንም ÷ ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ ሕያው ፡
እግዚአብሔርን ፣ በሕያው ፡ ነፍስህም ፡ እምሳ
ስህ ፣ ወደ ፡ ደም ፡ እንዳትገባ ÷ እጅህም ፡ ራስህን ፡
እንዳታድን ፡ የከለከለህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡
አውንም ፡ ጠላቶችህና ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡
የሚሹ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ናባል ፡ ይሁኑ ። አውንም ፡ ሸ፮፡
ባሪያህ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ ያመጣችው ፡ ይህ ፡ መተ
ያያ ፡ ጌታዬን ፡ ለሚከተሉ ፡ ጕልማሶች ፡ ይሰጥ ።
የእግዚአብሔርን ፡ ጦርነት ፡ ስጦምትዋጋ ፡ እግ ሸ፯፡
ዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ ለጌታዬ ፡ የታመነ ፡
ቤት ፡ ይሠራልና ፡ የአንተ ፡ የሰረያህን ፡ ኀጢአት ÷
አስክህ ÷ ይቅር ፡ በል ፣ በዘመንህም ፡ ሁሉ ፡
ክፋት ፡ አይገኝብህም ። ያሰድያህ ፡ ዘንድ ፡ ሸ፰፡
ነፍስህንም ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ቢነሣ ፡ የጌታዬ ፡
ነፍስ ፡ በሕያዎን ፡ ጠኅን ፡ በእምላክህ ፡ ስእግዚ
አብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታሰረች ፡ ትሆናለች ፡ የጠ
ላቶችህንም ፡ ነፍስ ፡ ከወንጭፍ ፡ እንደሚጣል ፡
እንዲሁ ፡ ይጥላታል ። እግዚአብሔርም ፡ ለጌ
ታዬ ፡ የተናገረውን ፡ ቸርነት ፡ ሁሉ ፡ ባደረገልህ ፡
ጊዜ ÷ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ አስቃ ፡ አድርጎ ፡ ሸ፱፡
ባስነሣህ ፡ ጊዜ ÷ አንተ ፡ በከንቱ ፡ ደም ፡ እንዳ
ላፈሰስህ ÷ ወገዛ ፡ እጅህም ፡ እንዳልተነሰህ ፡
ይህ ፡ ዕንቅፋትና ፡ የሕሊና ፡ ጸጸት ፡ በጌታዬ ፡
እይሆንልህም ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስጌታዬ ፡
በጎ ፡ ስደረገልህ ፡ ጊዜ ÷ ባሪያህን ፡ አስብ ።

ዳዊትም ፡ አቢግያን ፡ አላት ፡— ዛሬ ፡ እኔን ፡ ሸ፲፡
ለመገናኘት ፡ እንቺን ፡ የሰደደ ፡ የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ። ወደ ፡
ደም ፡ እንዳልሄድ ÷ በእጅም ፡ በቀል ፡ እንዳላ
ደርግ ፡ ዛሬ ፡ የከለከለኝ ፡ አስምሮሽ ፡ የተመሰ

ገን ፡ ይሁን ÷ እንቺም ፡ የተመሰገንሽ ፡ ሁኚ ። ሸ፲፩፡
ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ እንዳላደርግብሽ ፡ የከለከለኝ ፡
የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፣
እኔን ፡ ለመገናኘት ፡ ፈጥነሽ ፡ በልመጣሽ ፡ ኖሮ ÷
እስከ፡ነጋ ፡ ድረስ ፡ ስናባል ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡
ሸ፲፪፡ በንኳ ፡ ባልቀረውም ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ ያመ
ጣችውን ፡ ከእጅዋ ፡ ተቀብሎ ፡— ወደ፡ሰላ ፡ ወደ ፡
ቤትሽ ፡ ሂጂ ፡ እነሆ ÷ ቃልሽን ፡ ሰማሁ ÷ ፊት ፡
ሽንም ፡ አከበርሁ ፡ አላት ።

አቢግያም ፡ ወደ ፡ ናባል ፡ መጣች ፡ እነሆም ÷ ሸ፲፫፡
በቤቱ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ግብዣ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡
ያደርግ ፡ ነበር ፡ ናባልም ፡ እጅግ ፡ ሰክሮ ፡ ነበ
ርና ፡ ልቡ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ነበር ፡ ስለዚህም ፡
እስከ፡ነጋ ፡ ድረስ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ሸ፲፬፡
ነገር ፡ አልነገረችውም ፡ ነበር ። በነጋውም ፡
የጠጁ ፡ ስክር ፡ ከናባል ፡ በለፈ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡
ይህን ፡ ነገር ፡ ነገረችው ፡ ልቡም ፡ ስውስጡ ፡
ሞተ ÷ እንደ ፡ ድንጋይም ፡ ሆነ ፡ ከአሥር ፡ ሸ፲፭፡
ቀንም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናባልን ፡ ቀሠ
ፈው ፡ አርሱም ፡ ሞተ ።

ዳዊትም ፡ ናባል ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡
ጊዜ ፡— ከናባል ፡ እጅ ፡ የስድቤን ፡ ፍርድ ፡
የፈረደልኝ ÷ ባሪያውንም ፡ ከክፋት ፡ የጠበቀ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፣ እግዚአብሔርም ፡
የናባልን ፡ ክፋት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መለሰ ፡ አለ ። ሸ፲፮፡
ዳዊትም ፡ ልከ ፡ ያገባት ፡ ዘንድ ፡ አቢግያን ፡
ተነጋገራት ። የዳዊትም ፡ ስሪያዎች ፡ ወደ ፡
ቀር ፡ ዩራስ ፡ ወደ ፡ አቢግያ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡— ሸ፲፯፡
ዳዊት ፡ ያገበኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እንቺ ፡ ልከናል ፡
ብለው ፡ ነገሩአት ። ተነሥታም ፡ በግምባርዋ ፡
ወድቃ ፡ እሮ ፡ ነሣችና ፡— እነሆ ÷ እኔ ፡ ገረድህ ፡
የጌታዬን ፡ ሱሌዎች ፡ እግር ፡ ሊጥብ ፡ ዘንድ ፡ ሸ፲፰፡
አገልጋይ ፡ ነኝ ፡ አለች ። አቢግያም ፡ ፈጥና ፡
ተነሣች ፡ በአህያም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠች ÷ አም
ስቱም ፡ ገረዶችዋ ፡ ተከተሉአት ፡ የዳዊትንም ፡
መልእክተኞች ፡ ተከትላ ፡ ሄደች ÷ ሚስትም ፡
ሆነችው ።

ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ ኢይዝራኤላዊቱን ፡ አኪ ሸ፲፱፡
ናሆምን ፡ ወሰደ ፡ ሁለቱም ፡ ሚስቶች ፡ ሆኑለት ።
ሳኦል ፡ ግን ፡ የዳዊትን ፡ ሚስት ፡ ልጁን ፡ ሜል ሸ፳፡
ኮልን ፡ አገሩ ፡ ጋሊም ፡ ለነበረው ፡ ለሴላ ፡ ልጅ ፡
ስፈልጢ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ሽ፭ ።

የዚፍ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ፩፡
መጥተው ፡— እነሆ ÷ ዳዊት ፡ በየሺሞን ፡ ፊት ፡
ስፈት ፡ ስለው ፡ በኤኬላ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ ተሸ
ሽጎአል ፡ አሉት ። ሳኦልም ፡ ተነሥቶ ፡ ዳዊትን ፡
በዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሸ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡
የተመረጡ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡
ዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወረደ ። ሳኦልም ፡ ለየሴ ፪፡
ሞን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በኤኬላ ፡ ኮረብታ ፡
ላይ ፡ ሰመንገዱ ፡ አጠገብ ፡ ሰፈረ ። ዳዊትም ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ÷ ሳኦ
ልም ፡ በስተ ፡ ኋላው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
እንደ ፡ መጣ ፡ አየ ። ዳዊትም ፡ ሰላዮች ፡ ሰደዶ ÷ ፫፡
ሳኦልም ፡ ወደዚህ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በእርግጥ ፡
አመቀ ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ፬፡
ሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ መጣ ፡ ሳኦልና ፡ የሠራዊቱ ፡
አለቃ ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርም ፡ የተኙበትን ፡
ስፍራ ፡ አየ ፡ ሳኦልም ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡
ነበር ፡ ሕዝቡም ፡ በዙሪያው ፡ ሰፍሮ ፡ ነበር ።

ዳዊትም ፡ ኬጢያዊውን ፡ አቢሜሌክንና ፡ ፭፡
የጽሩያን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብን ፡ ወንድም ፡ አቢ
ሳን ፡— ወደ ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡
የሚወርድ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡
አቢሳም ፡— እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አወርዳለሁ ፡
አለ ። ዳዊትና ፡ አቢሳም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ በሌ ፮፡
ሊት ፡ መጡ ፡ እነሆም ÷ ሳኦል ፡ ጦሩ ፡ በራሱ ፡
አጠገብ ፡ በምድር ፡ ተተክሰ ፡ ጠለፈሩ ፡ ውስጥ ፡
ተኝቶ ፡ ነበር ፡ አበኔርና ፡ ሕዝቡም ፡ በዙሪያው ፡
ተኝተው ፡ ነበር ። አቢሳም ፡ ዳዊትን ፡— ዛሬ ፡ ፯፡
እግዚአብሔር ፡ ጠላትህን ፡ በእጅህ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጥቶታል ፡ አሁንም ፡ እኔ ፡ ስመር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ከምድር ፡ ጋር ፡ ሳጣብቀው ÷ ሁለተኛም ፡ አያ
ዳግምም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አቢሳን ፡— እግ ፰፡
ዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ የሚዘረጋ ፡
ንጹሕ ፡ አይሆንምና ፡ አትግደለው ፡ አለው ።
ደግሞም ፡ ዳዊት ፡— ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፣ ፱፡
እግዚአብሔር ፡ ይመታዋል ÷ ወይም ፡ ቀኑ ፡
ደርሶ ፡ ይሞታል ÷ ወይም ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡
ወርዶ ፡ ይገደላል ፡ አል ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፲፡
በቀበው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ስዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ከእኔ ፡ ያርቀው ፡ አሁንም ፡ በራሱ ፡
አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጦርና ፡ የውኃውን ፡ መን
ቀል ፡ ይዘህ ፡ እንሂድ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ በሰ ፲፩፡
አል ፡ ራስ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ ጦርና ፡ የው
ኃውን ፡ መንቀል ፡ ወሰደ ፡ ግንም ፡ ሰያይ ፡ ሳያ
ውቅም ፡ ጌሩ ፡ ከእግዚአብሔም ፡ ዘንድ ፡
ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ወድቆባቸው ፡ ነበርና ፡
ሁሉ ፡ ተኝተው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የነቃ ፡ አልነበ
ረም ።

ዳዊትም ፡ ወደዚያ ፡ ተሻገረ ፡ ስተራራውም ፡ ፲፫፡
ራስ ፡ ላይ ፡ ርቆ ፡ ቆመ ፡ በመካከላቸውም ፡ ሰፊ ፡
ስፍራ ፡ ነበረ ። ዳዊትም ፡ ለሕዝቡና ፡ ለኔር ፡ ፲፬፡
ልጅ ፡ ለአበኔር ፡— አበኔር ፡ ሆይ ÷ አትመል
ስምን ? ብሎ ፡ ጮኸ ። አበኔርም ፡ መልሶ ፡— ስን
ጉሥ ፡ የምትጮኸው ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነህ ? አለ ። ፲፭፡
ዳዊትም ፡ አበኔርን ፡— አንተ ፡ ጕልማሳ ፡ አይደ
ስህምን ? በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አንተን ፡ የሚ
መስል ፡ ማን ፡ ነው ? ጌታህን ፡ ንጉሡን ፡ ስመ
ግደል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ ነበርና ፡ ጌታህን ፣
ንጉሡን ፡ የማትጠብቅ ፡ በለ ፡ ምን ፡ ነው ? ይህ ፡ ፲፮፡
ያደረግኸው ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔር ! እናንተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የቀበውን ፡ ጌታችሁን ፡ አልጠበቃችሁ
ምና ፡ ሞት ፡ ይገበቸኋል ፡ አሁንም ፡ የንጉሡ ፡
ጦርና ፡ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ የነበረው ፡ የውኃው ፡

መንቀል ፡ የት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልክት ፡ አለው ።

፲፯ ሳኦልም ፡ የዳዊት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቆ ፡— ልጄ ፡ ዳዊት ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ድምፅህ ፡ ነውን ? አለው ። ዳዊትም ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ድምፄ ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞ ፡ አለ ፡— ፲፰ ጌታዬ ፡ ባሪያውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያሳድዳል ? ምን ፡ አደረግሁ ፡ ምንስ ፡ ክፋት ፡ በእጄ ፡ ላይ ፡ ተገኘብኝ ? አሁንም ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የእኔን ፡ የባሪያህን ፡ ቃል ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ እሰ ፲፱ ምንሃለሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አስነሥ ፡ ቶህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቁርበንን ፡ ይቀበል ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ቢሆኑ ፡— ሂድ ፡ ሌሎችን ፡ አማ ልክት ፡ አምልክ ፡ ብለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ እንዳልቀመጥ ፡ ዛሬ ፡ ዋሉውኛልና ፡ ፳ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርጉማን ፡ ይሁኑ ። አሁንም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ቆቅን ፡ እንደ ሚሻ ፡ የአሰራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነፍሴን ፡ ለመሻት ፡ ወጥቶአልና ፡ ደሜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርቆ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይፍሰስ ።

፳፩ ሳኦልም ፡— በድያለሁ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ዳዊት ፡ ተመለስ ፡ ዛሬ ፡ ነፍሴ ፡ በዋይንህ ፡ ፊት ፡ ከብራ ለችና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክፉ ፡ አላደርግብህም ፡ እነሆ ፡ ሰንፍና ፡ አድርጌአለሁ ፡ እጅግ ፡ ብዙም ፡ ፳፪ ስቻለሁ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ መልሶ ፡ አለ ፡— የን ጉሥ ፡ ጦር ፡ እነሆ ፡ ከብላቴኖችም ፡ አንድ ፡ ፳፫ ይምጣና ፡ ይውሰዳት ። ዛሬም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶህ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ አዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ አል ወደደሁምና ፡ ለሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እንደ ፡ ጽድቁና ፡ እንደ ፡ እምነቱ ፡ ፍዳ ፳፬ ውን ፡ ይከፈለው ። ነፍስህም ፡ ዛሬ ፡ በዋይኔ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ከበረች ፡ እንዲሁ ፡ ነፍሴ ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ ዓይን ፡ ፊት ፡ ትከበር ። ዘመክ ፳፭ ራም ፡ ሁሉ ፡ ያድነኝ ። ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡— ልጄ ፡ ዳዊት ፡ ሆይ ፡ ሩጭክ ፡ ሁን ፡ ማድረግን ፡ ታደር ጋለህ ። መቻልንም ፡ ትችላለህ ፡ አለው ። ዳዊ ትም ፡ መንገዱን ፡ ሄደ ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ስፍ ራው ፡ ተመለሰ ።

ምዕራፍ ፳፯ ።

፩ ዳዊትም ፡ በልቡ ፡— አንድ ፡ ቀን ፡ በሳኦል ፡ እጅ ፡ እጠፋለሁ ፡ ወይ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ምድር ፡ ከመሸሽ ፡ በቀር ፡ የሚሻለኝ ፡ የለም ፡ ሳኦልም ፡ በእስራኤል ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ መሻት ፡ ይተዋል ፥ እንዲሁም ፡ ከእጁ ፡ እድናለሁ ፡ አለ ። ፪ ዳዊትም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ስድስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ንጉሥ ፡ ፫ ወደ ፡ አሜህ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ አሉት ። ዳዊ ትና ፡ ሰዎቹም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከነ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከአንኩስ ፡ ጋር ፡ በጌት ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፡ ከዳ ዊትም ፡ ጋር ፡ ኢይዝራኤላዊቱ ፡ አኪኖሀምና ፡ የቀርሜሎሰዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡ አቢግያ ፬ ሁለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ነበሩ ። ሳኦልም ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ እንደ ፡ ኩበለለ ፡ ሰማ ፡ ከዚያም ፡ ዘኋላ ፡ ደግሞ ፡ አልፈለገውም ።

፭ ዳዊትም ፡ እንኩሰን ፡— በዓይንህ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ በእንዲቱ ፡ ከተማ ፡ የምቀመጥበት ፡ ሰፍራ ፡ ለጠኝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ በንጉሥ ፡ ከተማ ፡ አቀመጣለሁ ፡ አለው ። ፮ በዚያም ፡ ቀን ፡ አንኩስ ፡ ጺቅላግን ፡ ሰጠው ፡ ስለ ዚህም ፡ ጺቅላግ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለይሁዳ ፯ ነገሥታት ፡ ሆነች ። ዳዊትም ፡ በፍልስጥኤማው ያን ፡ አገር ፡ የተቀመጠበት ፡ የነበሰን ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከአራት ፡ ወር ፡ ነበረ ።

፰ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወጥተው ፡ በጌሹራውያ ንና ፡ በገርዛውያን ፡ በአማሌቃውያንም ፡ ላይ ፡ ዘመቱ ፡ እነዚህም ፡ አስከ ፡ ሱር ፡ አስከ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ በሰሙ ፡ አገር ፡ ድሮውኑ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ ምድሪቱን ፡ ፱ መታ ፡ ወንድ ፡ ሆነ ፡ ሴትም ፡ ሆነ ፡ ማንንም ፡ በሕይወት ፡ አልተወም ፡ በጎችንና ፡ ላሞችን ፡ አህያዎችንና ፡ ግመሎችን ፡ ልብስንም ፡ ማረከ ፡ ተመልሶም ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ መጣ ። አንኩ ፲ ስም ፡— ዛሬ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ዘመታችሁ ? አለ ፡ ዳዊትም ፡— በይሁዳ ፡ ደቡብ ፡ በይረሕምኤ ላውያንም ፡ ደቡብ ፡ በቄናውያንም ፡ ደቡብ ፡ ላይ ፡ ዘመትን ፡ አለ ። ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ አደ ፲፩ ረገ ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ በማቂ መኖበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልማዱ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ እንዳይናገሩብን ፡ ብሎ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ወንድም ፡ ሆነ ፡ ሴትም ፡ ሆነ ፡ ማንንም ፡ በሕይወት ፡ አልተወም ። አንኩስም ፡— በእገዙ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፲፪ አጅግ ፡ የተጠላ ፡ ሆኖአል ፡ ስለዚህም ፡ ለዘላ ለም ፡ ባሪያ ፡ ይሆነኛል ፡ ብሎ ፡ ዳዊትን ፡ አመ ነው ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ከእስራ ኤል ፡ ጋር ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሞኖሮጮቻቸውን ፡ ለሰልፍ ፡ ሰበሰቡ ፡ አንኩ ሰም ፡ ዳዊትን ፡— አንተና ፡ ሰዎችህ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እንድትወጡ ፡ በእርግጥ ፡ አወቅ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አንኩስን ፡— አሁን ፪ ፡ ባሪያህ ፡ የሚያደርገውን ፡ ታያለህ ፡ አለው ። አንኩሰም ፡ ዳዊትን ፡— እንግዲህ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ራሴን ፡ ጠባቂ ፡ አደርግሃለሁ ፡ አለው ።

፫ ሳሙኤል ፡ ግን ፡ ሞቶ ፡ ነበር ። እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ አልቅሰውለት ፡ ነበር ። በከተማውም ፡ በአርማቴም ፡ ቀብረውት ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችን ፡ ከም ፬ ድር ፡ አጥፍቶ ፡ ነበር ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ተሰብስበው ፡ መጡ ፡ በሱነምም ፡ ሰፈሩ ፡ ሳኦ ልም ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ። በጊልቦ ፭ ዓም ፡ ሰፈሩ ። ሳኦልም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ። ልቡም ፡ እጅግ ፡ ተንቀጠቀጠ ። ሳኦልም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፡ በሕልም ፡ ወይም ፮ በኡራም ፡ ወይም ፡ በነቢያት ፡ አልመለሰለትም ። ፯ ሳኦልም ፡ ባሪያዎቹን ፡— ወደ ፡ አርሰቃ ፡ ሄጂ ፡ እጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ መናፍስትን ፡ የምትጠራ ፡ ሴት ፡ ፈልጉልኝ ፡ አላቸው ፡ ባሪያዎቹም ፡— እነሆ ፡ መናፍስትን ፡ የምትጠራ ፡ እንዲት ፡ ሴት ፡ በዓይንዶር ፡ አለች ፡ አሉት ።

፰ ሳኦልም ፡ መልኩን ፡ ለውጦ ፡ ሌላ ፡ ልብስም ፡ ለብሶ ፡ ሄደ ፡ ሁለትም ፡ ሰዎች ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። በሴሊትም ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ መጡ ። እር ሱም ፡— እስከሽ ፡ በመናፍስት ፡ አምዋቸኝ ፱ ልኝ ፡ የምልሽንም ፡ አስነሽልኝ ፡ አላት ። ሴቲ ቱም ፡— እነሆ ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠን ቋዮችን ፡ ከምድር ፡ እንዳጠፋ ፡ ሳኦል ፡ ያደረገ ውን ፡ ታውቃለህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እኔን ፡ ሰማስገደል ፲ ወጥመድ ፡ ለነፍሴ ፡ ታደርጋለህ ፡ አለችው ። ሳኦ ልም ፡— ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ቅጣት ፡ አያገኝሽም ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፲፩ ፡ ማለላት ። ሴቲቱም ፡— ማንን ፡ ላስነሣልህ ? አለች ፡ እርሱም ፡— ሳሙኤልን ፡ አስነሽልኝ ፡ አለ ። ፲፪ ሴቲቱም ፡ ሳሙኤልን ፡ በየች ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸች ፡ ሴቲቱም ፡ ሳኦልን ፡— አንተ ፡ ሳኦል ፡ ስትሆን ፡ ለምን ፡ አታለልኸኝ ? ብላ ፡ ፲፫ ተናገረችው ። ንጉሡም ፡— አትፍራ ፡ ያየሽው ፡ ምንድር ፡ ነው ? አላት ። ሴቲቱም ፡ ሳኦልን ፡— አማልክት ፡ ከምድር ፡ ሲወጡ ፡ አየሁ ፡ አለችው ። ፲፬ አርሱም ፡— መልኩ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? አላት ። እርስዋም ፡— ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ወጣ ፡ መጐናጸፊያም ፡ ተጐናጽፎአል ፡ አለች ። ሳኦ ልም ፡ ሰሙኤልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀ ፡ በፊ ቱም ፡ ተንበረበረ ፡ ዘምድርም ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

፲፭ ሰሙኤልም ፡ ሳኦልን ፡— ለምን ፡ አወክበኝ ? ሰምንስ ፡ አስነሣኝ ? አለው ። ሳኦልም ፡ መልሶ ፡— ፍልስጥኤማውያን ፡ ይወጉኛልና ፡ እጅግ ፡ ተጨንቄአለሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከእኔ ፡ ርቆአል ፡ በነቢያት ፡ ወይም ፡ በሕልም ፡ አልመለ ሰልኝም ፡ ስለዚህም ፡ የማደርገውን ፡ ታስታ ፲፮ ውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠራሁህ ፡ አለው ። ሰሙኤ ልም ፡ አለ ፡— እግዚአብሔር ፡ ከሥራህ ፡ ጠላ ፲፯ ትም ፡ ከሠንህ ፡ ለምን ፡ ትጠይቀኛለህ ? እግዚ አብሔርም ፡ በቃሉ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አድርጎ አል ፡ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥትህን ፡ ከእ ጅህ ፡ ነጥቆ ፡ ለጎረቤትህ ፡ ለዳዊት ፡ ሰጥቶታል ። ፲፰ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማህምና ፡ በአ ማሌቅም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ቍጣውን ፡ አላ ደረግህምና ፡ ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፲፱ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አድርጎብሃል ። እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ በፍልስጥኤማው ያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡ ነገም ፡ አንተና ፡ ልጆችህ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትሆናላችሁ ፡ እግዚአ ብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራ ፡ ደግሞ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ። ፳ ሳኦልም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በቁመቱ ፡ ሙሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ከሰሙኤልም ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ሁሉ ፡ አንጀራ ፡ አልበላምና ፡ ኃይል ፡ አልቀረለትም ። ሴቲቱም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፳፩ መጣች ። እጅግም ፡ ደንግጦ ፡ አንደ ፡ ነበረ ፡ አያት ፡— እነሆ ፡ አገልጋይህ ፡ ቃልህን ፡ ሰማሁ ፡ ነፍሴንም ፡ በእጄ ፡ ጣልሁ ። የነገርሽኝንም ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ የባሪያህን ፡ ቃል ፡ አንድትሰማ ፡ አለም ፳፪ ንሃለሁ ። በፊትህም ፡ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ ላኑር ልህ ፡ በመንገድም ፡ ስትሄድ ፡ ትበረታ ፡ ዘንድ ፡ ብላ ፡ አለችው ። እርሱ ፡ ግን ፡— አልበላም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሪያዎቹና ፡ ሴቲቱ ፡ አስገደዱት ። ቃላቸውንም ፡ ሰማ ፡ ከም ድርም ፡ ተነሥቶ ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ፳፫ ለሴቲቱም ፡ ማሰፊያ ፡ አንበሳ ፡ ነበራት ፡ ፈጥና ፡ አረደችው ፡ ዱቄቱንም ፡ ወስዳ ፡ ለወሰችው ፡ ቂጣም ፡ አንጀራ ፡ አድርጋ ፡ ጋገረችው ። በሳኦ ፳፬ ልና ፡ በባሪያዎቹም ፡ ፊት ፡ አቀረበችው ፡ በል ተውም ፡ ተነሡ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ሄዱ ።

ምዕራፍ ፳፱ ።

፩ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሞኖሮጮቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ሰበሰቡ ፡ እስራኤላውያንም ፡ በኢይዝራኤል ፡ ባለው ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ አጠ ገብ ፡ ሰፈሩ ። የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቆች ፪ በመቶ ፡ በመቶ ፡ በሺህ ፡ በሺህ ፡ እየሆኑ ፡ ያልፉ ፡ ነበር ፡ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ከእንኩስ ፡ ጋር ፫ በኋለኛው ፡ ሞኖፍራ ፡ በኩል ፡ ያልፉ ፡ ነበር ። የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቆች ፡— እነዚህ ፡ ዕብራውያን ፡ በዚህ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፡ አሉ ፡ እንኩሰም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለቆች ፡— ይህ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የሳኦል ፡ በሪያ ፡ ዳዊት ፡ አይደለምን ? እርሱም ፡ በእነዚህ ፡ ቀኖች ፡ በእነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ከተጠጋበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ አላገኘሁበትም ፡ አላቸው ። ፬ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ ተቆጥ ፭ ተው ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ በሰቀመጥኸው ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ይመለስ ፡ በስልቆ ፡ ውስጥ ፡ ጠላት ፡ እንዳይሆንን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ አይውረድ ፡ ከጌታው ፡ ጋር ፡ በምን ፡ ይታረቃል ? የእነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ራሰ ፡ በመቀረጥ ፡ አይደለ ምን ? ወይስ ፡ ሴቶች ፡— ሳኦል ፡ ሺህ ፡ ገደለ ፡ ዳዊት ፡ አልፍ ፡ ገደለ ፡ ብለው ፡ በዘፈን ፡ የዘመ ሩለት ፡ ይህ ፡ ዳዊት ፡ አይደለምን ? አሉት ።

፮ አንኩስም ፡ ዳዊትን ፡ ጠርቶ ፡— ሕያው ፡ እግ ዚአብሔርን ! አንተ ፡ ቅን ፡ ነህ ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ በሞፍራው ፡ ከኩል ፡ መውጣትህና ፡ መግባ ትህ ፡ በፊቴ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ከመጣህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አንዳች ፡ ክፋት ፡ አላገኘሁብህም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአለቆች ፡ ዘንድ ፡ አልተወደድህም ። አሁንም ፡ ተመል ሰህ ፡ በደኅና ፡ ሂድ ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡

አለቆች ፡ ዓይን ፡ ክፋት ፡ እታድርግ ፡ አለው ።
፳ ዳዊትም ፡ አንኩስን ፡— ምን ፡ አድርጌአለሁ ?
ጌኤስ ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ጠላቶች ፡ ጋር ፡
እንዳልዋጋ ፡ በፊትህ ፡ ከተቀመጥሁ ፡ ጀምሬ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእኔ ፡ በባሪያህ ፡ ምን ፡ አግ
፳፩ ኝተህብኛል ? አለው ። አንኩስም ፡ መልሶ ፡
ዳዊትን ፡— እንደ ፡ አምላክ ፡ መልእክተኛ ፡ በዓ
ይኔ ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ሠንህ ፡ አውቃ
ለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለ
ቆች ፡— ከእኛ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ አይወጣም ፡
፳፪ አሉ ። አሁንም ፡ አንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡
የመጡ ፡ የጌታህ ፡ ባሪያዎች ፡ ማልዳችሁ ፡
ተነሡ ፡ ሲነጋም ፡ ተነሥታችሁ ፡ ሂዱ ፡ አለው ።
፳፫ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ማልደው ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ ይመለሱ ፡
ዘንድ ፡ ተነሡ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወደ ፡
ኢይዝራኤል ፡ ወጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ። ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጺቅላግ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አማ
ሌቃውያን ፡ በደቡብ ፡ አገርና ፡ በጺቅላግ ፡ ላይ ፡
ዘምተው ፡ ነበር ። ጺቅላግንም ፡ መትተው ፡
፪ በእሳት ፡ አቃጥለዋት ፡ ነበር ፡ ሴቶቹንና ፡ በው
ስጥዋም ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ ከታናሽ ፡ እስከ ፡
ታላቅ ፡ ድረስ ፡ ማርከው ፡ ነበር ። ሁሉንም ፡
ወስደው ፡ መንገዳቸውን ፡ ሄዱ ። እንጂ ፡ አን
፫ ድስ ፡ እንኳ ፡ አልገደሉም ፡ ነበር ። ዳዊትና ፡
ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡
በእሳት ፡ ተቃጥላ ፡ ሚስቶቻቸውም ፡ ወንዶ
ችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ ተማርከው ፡
፬ አገኙ ። ዳዊት ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡
ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ለማልቀስ ፡
፭ ኃይል ፡ እስኪያጡ ፡ ድረስ ፡ አለቀሱ ። የዳዊ
ትም ፡ ሁለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ኢይዝራኤላዊቲቱ ፡ አኪ
ናሆምና ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡
፮ የነበረችው ፡ አቢግያ ፡ ተማርከው ፡ ነበር ። ስለ ፡
ወንዶችና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ የሕዝቡ ፡
ሁሉ ፡ ልብ ፡ ተቈጥቶ ፡ ነበርና ፡ ሕዝቡ ፡ ሊወ
ግሩት ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ ዳዊት ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ፡
ዳዊት ፡ ግን ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ልቡን ፡ አበረታ ።
፯ ዳዊትም ፡ የአቢሚሌክን ፡ ልጅ ፡ ካህኑን ፡ አብ
ያታርን ፡— ኤፉዱን ፡ አቅርብልኝ ፡ አለው ፡ አብ
፰ ያታርም ፡ ኤፉዱን ፡ ለዳዊት ፡ አቀረበለት ። ዳዊ
ትም ፡— የእነዚህን ፡ ሠራዊት ፡ ፍለጋ ፡ ልከተ
ልን ? አገኛቸዋለሁን ? ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ጠየቀ ። እርሱም ፡— ታገኛቸዋለህና ፡ ፈጽመ
ህም ፡ ምርኮውን ፡ ትመልሳለህና ፡ ፍለጋቸውን ፡
፱ ተከተል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ዳዊትም ፡ ከእር
ሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡
ሄዱ ። እስከ ፡ በዞር ፡ ወንዝ ፡ ድረስም ፡ መጡ ፡
፲ ከእነርሱም ፡ የቀሩት ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ። ዳዊ
ትም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ አራት ፡ መቶ ፡
ሰዎች ፡ አሳደዱ ። ሁለቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡
የበዞር ፡ ወንዝን ፡ መሻገር ፡ ደክመዋልና ፡ በኋላ ፡
ቀሩ ።
፲፩ በበረሀውም ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ግብጻዊ ፡ አግኝ
ተው ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፡ እንጀራም ፡
፲፪ ሰጡትና ፡ በላ ። ውኃንም ፡ አጠጡት ፡ ከበለሱም ፡
ጥፍጥፍ ፡ ቂራሞና ፡ ሁለት ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡
ሰጡት ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንጀራ ፡
አልበላም ፡ ውኃንም ፡ አልጠጣም ፡ ነበርና ። በበላ ፡
፲፫ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተመለሰች ። ዳዊ
ትም ፡— አንተ ፡ የማን ፡ ነህ ? ከወዴት ፡ መጣህ ?
አለው ። እርሱም ፡— እኔ ፡ የአማሌቃዊ ፡ ባሪያ ፡
ግብጻዊ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ፡ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በፊት ፡
፲፬ ታምሜ ፡ ነበርና ፡ ጌታዬ ፡ ጥሎኝ ፡ ሄደ ። እኛም ፡
በክሊታውያን ፡ ደቡብ ፡ በይሁዳም ፡ ምድር ፡
በክሌብም ፡ ደቡብ ፡ ላይ ፡ ዘመትን ፡ ጺቅላግ
፲፭ ንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠልናት ፡ አለ ። ዳዊትም ፡—
ወደ ፡ እነዚያ ፡ ሠራዊት ፡ ዘንድ ፡ ልትመራኝ ፡
ትወድዳለህን ? አለው ፡ እርሱም ፡— እንዳትገ
ድለኝ ፡ ለጌታዬም ፡ እጅ ፡ አሳልፈህ ፡ እንዳትሰ
ጠኝ ፡ በእምላክ ፡ ማልልኝ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እነ
ዚያ ፡ ሠራዊት ፡ እመራሃለሁ ፡ አለ ።
፲፮ ወደ ፡ ታችም ፡ እንዳወርድ ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡
እነሆ ፡ ከፍልስጥኤማውያንና ፡ ከይሁዳ ፡ ምድር ፡
ከወሰዱት ፡ ከብዙ ፡ ምርኮ ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡
በልተው ፡ ጠጥተውም ፡ የበዓልም ፡ ቀን ፡ አድ
ርገው ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡ ነበር ።
፲፯ ዳዊትም ፡ ከማታ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማግሥቱ ፡
ማታ ፡ ድረስ ፡ መታቸው ፡ ከእነርሱም ፡ በግመል ፡
ተቀምጠው ፡ ከሸሹ ፡ ከአራት ፡ መቶ ፡ ጕልማ
ሶች ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ አመለጠ ፡ የለም ። ዳዊ
፲፰ ትም ፡ አማሌቃውያን ፡ የወሰዱትን ፡ ሁሉ ፡ አስ
ጣላቸው ፡ ሁለቱንም ፡ ሚስቶቹን ፡ አዳነ ። ከወ
ንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከወሰዱትም ፡
ምርኮ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅም ፡ ሆነ ፡ ታናሽም ፡ ሆነ ፡
ምንም ፡ የጐደለባቸው ፡ የለም ፡ ዳዊትም ፡
፲፱ ሁሉን ፡ አስጣለ ። ዳዊትም ፡ የበጉንና ፡ የላሙን ፡
፳ መንጋ ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ፡ ከራሱም ፡ ከብት ፡ ፊት ፡
እየነዳ ፡— ይህ ፡ የዳዊት ፡ ምርኮ ፡ ነው ፡ አለ ።
፳፩ ዳዊትም ፡ ደክመው ፡ ዳዊትን ፡ ይከተሉት ፡
ዘንድ ፡ ወዳልቻሉ ፡ በቦዞር ፡ ወንዝ ፡ ወዳስቀ
ራቸው ፡ ወደ ፡ ሁለቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ መጣ ፡
እነርሱም ፡ ዳዊትን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሕዝብ ፡ ሊቀበሉ ፡ ወጡ ። ዳዊትም ፡ ወደ ፡
ሕዝቡ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ደኅንነታቸውን ፡ ጠየቀ ።
፳፪ ከዳዊትም ፡ ጋር ፡ ከሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ክፉዎቹና ፡
ምናምንቴዎቹ ፡ ሁሉ ፡— እነዚህ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
አልመጡምና ፡ እየራሳቸው ፡ ሚስቶቻቸው
ንና ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ይሂዱ ፡ እንጂ ፡
ከስጣልነው ፡ ምርኮ ፡ ምንም ፡ አንሰጣቸውም ፡
፳፫ አሉ ። ዳዊትም ፡— ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ የጠበ
ቀን ፡ በእኛም ፡ ላይ ፡ የመጣውን ፡ ጭፍራ ፡ በእጃ
ችን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰ
ጠን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አታድርጉ ፡ ይህንስ ፡ ነገር ፡
፳፬ ማን ፡ ይሰማችኋል ? ነገር ፡ ግን ፡ የተዋጉትና ፡
ዕቃውን ፡ የጠበቁት ፡ እየል ፡ ፈንታ ፡ እኩል ፡
፳፭ ይሆናል ። አንደኑት ፡ ይከፈላሉ ፡ አለ ። ከዚ
ያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡
ለእስራኤል ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡ አደረገው ።
፳፮ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ጺቅላግ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ለዘመዶቹ ፡ ለይሁዳ ፡ ሽማግሌዎች ፡— እነሆ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ምርኮ ፡ በረከትን ፡
ተቀበሉ ፡ ብሎ ፡ ከምርኮው ፡ ሰደደላቸው ።
፳፯ በቤቴል ፡ ለነበሩ ፡ በራሞት ፡ ለደቡብ ፡ ለነ
፳፰ በሩ ፡ በየቲር ፡ ለነበሩ ፡ በአሮዔር ፡ ለነበሩ ፡
በሚፍሞት ፡ ለነበሩ ፡ በኤሽትሞዓ ፡ ለነበሩ ፡
፳፱ በቀርሜሎስ ፡ ለነበሩ ፡ በዩረሕምኤላውያንና ፡
በቄኔውያን ፡ ከተሞችም ፡ ለነበሩ ፡ በሔርማ ፡
፴ ለነበሩ ፡ በቦራሣን ፡ ለነበሩ ፡ በዓታክ ፡ ለነበሩ ፡
፴፩ በኬብሮን ፡ ለነበሩ ፡ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ በተ
መላለሱበት ፡ ስፍራ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ላከ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

፩ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡
ተዋጉ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በፍልስጥኤ
ማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ። ተወግተውም ፡ በጊል
፪ ቦዓ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወደቁ ። ፍልስጥኤማውያ
ንም ፡ ሳኦልንና ፡ ልጆቹን ፡ በእግር ፡ በእግራቸው ፡
፫ ተከትለው ፡ አባረሩአቸው ። ፍልስጥኤማውያ
ንም ፡ የሳኦልን ፡ ልጆች ፡ ዮናታንንና ፡ አሚና
፬ ዳብን ፡ ሚልኪሳንም ፡ ገደሉ ። ሰልፍም ፡ በሳ
አል ፡ ላይ ፡ ጠነከረ ። ቀስተኞችም ፡ አገኙት ፡
፭ እርሱም ፡ ከቀስተኞቹ ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ተጨ
፮ ነቀ ። ሳኦልም ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውን ፡— እነዚህ ፡
ቈላፋን ፡ መጥተው ፡ እንዳይወጉኝና ፡ እንዳይ

ሳለቁብኝ ፡ ሰይፍህን ፡ መዝዘህ ፡ ውጋኝ ፡ አለው ።
ጋሻ ፡ ጃግሬው ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፈርቶ ፡ ነበርና ፡
እንቢ ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ሰይፉን ፡ ወስዶ ፡ በላዩ ፡
፭ ወደቀ ። ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ ሳኦል ፡ እንደ ፡
ሞተ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በሰይፉ ፡
፮ ላይ ፡ ወደቀ ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሞተ ። በዚ
ያም ፡ ቀን ፡ ሳኦል ፡ ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ ጋሻ ፡
ጃግሬውም ፡ ሰዎቹም ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።
፯ በሸለቆውም ፡ ማዶና ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡
የነበሩ ፡ እስራኤላውያን ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡
እንደ ፡ ሸሹ ፡ ሳኦልና ፡ ልጆቹም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡
ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከተሞቹን ፡ ለቅቀው ፡ ሸሹ ፡ ፍልስ
ጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ ተቀመጡባቸው ።
፰ በማግሥቱም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ የሞቱትን ፡
ለመግፈፍ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦልና ፡ ሦስቱ ፡
ልጆቹ ፡ በጊልቦዓ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡
አገኙአቸው ። የሳኦልንም ፡ ራስ ፡ ቈርጠው ፡
፱ የጦር ፡ ዕቃውን ፡ ገፍፈው ፡ ለጣዖታቱ ፡ መቅ
ደስ ፡ ለሕዝቡም ፡ የምስራች ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰደዱ ።
፲ የጦር ፡ ዕቃውንም ፡ በአስታሮት ፡ መቅደስ ፡
ውስጥ ፡ አኖሩት ፡ ሬሳውንም ፡ በቤትሳን ፡ ቅጥር ፡
፲፩ ላይ ፡ አንጠለጠሉት ። ፍልስጥኤማውያንም ፡
በሳአል ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ የኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡
፲፪ ሰዎች ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጀግኖች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ተነሥተው ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሄዱ ። የሳኦል
ንም ፡ የልጆቹንም ፡ ሬሳ ፡ ከቤትሳን ፡
ቅጥር ፡ ላይ ፡ አወረዱ ፡ ወደ ፡ ኢያቢስም ፡
መጡ ። በዚያም ፡ አቃጠሉት ። አጥንታቸው
፲፫ ንም ፡ ወሰዱ ። በኢያቢስም ፡ ባለው ፡ በአሣጣ ፡
ዛፍ ፡ በታች ፡ ቀበሩት ። ሰበት ፡ ቀንም ፡ ጸሙ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልእ ።

(እርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልእ ፡ ነው ።)

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ። ሳኦል ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
ዳዊት ፡ አማሌቃውያንን ፡ ከመግደል ፡ ተመልሶ ፡
በጺቅላግ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ተቀመጠ ።
፪ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ እነሆ ፡ ከሳኦል ፡ ሰፈር ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡ በራሱም ፡
ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ዳዊትም ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በግምባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።
፫ ዳዊትም ፡— ከወዴት ፡ መጣህ ? አለው ። እር
ሱም ፡— ከእስራኤል ፡ ሰፈር ፡ ኰብልዬ ፡ መጣሁ ፡
፬ አለው ። ዳዊትም ፡— ነገሩ ፡ እንዴ ፡ ሆነ ፡ ንገ
ሆነ ? እስኪ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። እርሱም ፡
መልሶ ፡— ሕዝቡ ፡ ከሰልፉ ፡ ሸሽቶአል ። ከሕ
ዝቡ ፡ ብዙው ፡ ወደቁ ፡ ሞቱም ። ሳኦልና ፡
፭ ልጁም ፡ ዮናታን ፡ ደግሞ ፡ ሞተዋል ፡ አለ ።
፮ ዳዊትም ፡ ወሬኛውን ፡ ጕልማሳ ፡— ሳኦልና ፡
ልጁ ፡ ዮናታን ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በምን ፡ ታው
ቃለህ ? አለው ። ወሬኛውም ፡ ጕልማሳ ፡
፯ አለ ፡— በድንገት ፡ ወደ ፡ ጊልቦዓ ፡ ተራራ ፡
መጣሁ ። እነሆም ፡ ሳኦል ፡ ጦሩን ፡ ተመርኵዞ ፡
ቆሞ ፡ ነበር ። ሰረገሎችና ፡ ፈረሰኞችም ፡ ተከ
፰ ትለው ፡ ደረሱበት ። ወደ ፡ ኋላውም ፡ ዘወር ፡
አለና ፡ አኔን ፡ አይቶ ፡ ጠራኝ ፡ አኔም ፡— እነ
ሆኝ ፡ አልሁ ። እርሱም ፡— አንተ ፡ ማን ፡ ነህ ?
፱ አለኝ ፡ አኔም ፡— አማሌቃዊ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ መለ
ስሁለት ። እርሱም ፡— ሰውነቴ ፡ ዝሎአልና ፡
፲ ደግሞ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ነፍሴ ፡ ገና ፡
ፈጽማ ፡ ሕያው ፡ ናትና ፡ በላዬ ፡ ቆመህ ፡ ግደ
ለኝ ፡ አለኝ ። አኔም ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ አለ ፡
መዳኑን ፡ አይቼ ፡ በላዩ ፡ ቆሜ ፡ ገደልሁት ፡
በራሱም ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ዘውድ ፡ በክን
ዱም ፡ የነበረውን ፡ ቢተዋ ፡ ወሰድሁ ፡ ወደዚ
ህም ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ አመጣሁት ።

፲፭ ዳዊትና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡
፲፮ ሁሉ ፡ ልብሶቻውን ፡ ይዘው ፡ ቀደዱ ። በሰይ
ፍም ፡ ወድቀዋልና ፡ ለሳኦልና ፡ ለልጁ ፡ ለዮና
ታን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ሕዝብ ፡ ለእስራኤ
ልም ፡ ወገን ፡ እንበ ፡ እያፈሰሱ ፡ አለቀሱ ፡ እስከ ፡
፲፯ ማታም ፡ ድረስ ፡ ጾሙ ። ዳዊትም ፡ ወሬኛውን ፡
ጕልማሳ ፡— አንተ ፡ ከወዴት ፡ ነህ ? አለው ፡
እርሱም ፡— እኔ ፡ የመጻተኛው ፡ የአማሌቃ
ዊው ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ዳዊትም ፡—
እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ ለመግደል ፡ እጅህን ፡
፲፰ ስትዘረጋ ፡ ለምን ፡ አልፈራህም ? አለው ። ዳዊ
ትም ፡ ከጕልማሶቹ ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ፡— ወደ ፡
እርሱ ፡ ቅረብና ፡ ውደቅበት ፡ አለው ። እር
፲፱ ሱም ፡ መታው ፡ ሞተም ። ዳዊትም ፡— እግዚ
አብሔር ፡ የቀባውን ፡ እኔ ፡ ገድያለሁ ፡ ብሎ ፡
አፍህ ፡ በላይህ ፡ መስክሮአልና ፡ ደምህ ፡ በራ
ስህ ፡ ላይ ፡ ይሁን ፡ አለው ።
፳ ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ሳኦልና ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡
፳፩ ዮናታን ፡ ይህን ፡ የኀዘን ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘ ። የይሁ
ዳንም ፡ ልጆች ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።
እነሆ ፡ ይህ ፡ በያሻር ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎአል ።
፳፪ የእስራኤል ፡ ክብር ፡ በኮረብቶች ፡ ላይ ፡
ተወግቶ ፡ ሞተ ፤
ኃያላን ፡ እንዴት ፡ ወደቁ !
፳፫ የፍልስጥኤማውያን ፡ ቈነጃጅት ፡ ደስ ፡
እንዳይላቸው ÷
የቈላፋንም ፡ ቈነጃጅት ፡ እልል ፡ እንዳ
ይሉ ÷
በጌት ፡ ውስጥ ፡ አታውሩ ፤
በአስቀሎናም ፡ አደባባይ ፡ የምስራች ፡
አትበሉ ።
፳፬ እናንተ ፡ የጌልቦዓ ፡ ተራሮች ፡ ሆይ ÷
የሳኦል ፡ ጋሻ ፡ በዘይት ፡ እንዳልተቀባ ÷
የኃያላን ፡ ጋሻ ፡ በዚያ ፡ ወድቆአልና ፡
ዝናብና ፡ ጠል ፡ አያውረድባችሁ ÷
ቀሮበንንም ፡ የሚያበቅል ፡ እርሻ ፡ አይሁ
ንባችሁ ።
፳፭ ከሞቱት ፡ ደምና ፡ ከኃያላን ፡ ስብ ፡
የዮናታን ፡ ቀስት ፡ አልተመለሰችም ÷
የሳኦልም ፡ ሰይፍ ፡ በከንቱ ፡ አልተመለ
ሰም ።
፳፮ ሳኦልና ፡ ዮናታን ፡ የተዋደዱና ፡ የተስ
ማሙ ፡ ነበሩ ፤
በሕይወታቸውና ፡ በሞታቸው ፡ አልተለ
ያዩም ፤
ከንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ነበሩ ፤
ከአንበሳም ፡ ይልቅ ፡ ብርቱዎች ፡ ነበሩ ።
፳፯ የእስራኤል ፡ ቈነጃጅት ፡ ሆይ ÷
ቀይ ፡ ሐርና ፡ ጥሩ ፡ ግምጃ ፡ ያለብሳችሁ ፡
ለነበረ ÷
በወርቁዘቦም ፡ ላስጌጣችሁ ፡ ለሳኦል ፡ አል
ቅሱለት ።
፳፰ ኃያላንም ፡ በሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡
ወደቁ !
ዮናታንም ፡ በኮረብቶችህ ፡ ላይ ፡ ወድቆ
አል ።
ወንድሜ ፡ ዮናታን ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ ስለ ፡ ፳፱
አንተ ፡ እጨነቃለሁ ፡
በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ውድህ ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡
ነበረ ፡
ከሴት ፡ ፍቅር ፡ ይልቅ ፡ ፍቅርህ ፡ ለእኔ ፡
ግሩም ፡ ነበረ ።
ኃያላን ፡ እንዴት ፡ ወደቁ ! ፴
የሰልፍም ፡ ዕቃ ፡ እንዴት ፡ ጠፋ !

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡— ከይሁዳ ፡ ከተ ፩
ሞች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ልውጣን ? ብሎ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፡— ውጣ ፡
አለው ። ዳዊትም ፡— ወዴት ፡ ልውጣ ? አለ ።
እርሱም ፡— ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ውጣ ፡ አለው ።
ዳዊትም ፡ ከሁለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ከኢይዝራኤላ ፪
ዊቱ ፡ ከአኪናሆምና ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የና
ባል ፡ ሚስት ፡ ከነበረችው ፡ ከአቢግያ ፡ ጋር ፡
ወደዚያ ፡ ወጣ ። ዳዊትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነ ፫
በሩትን ፡ ሰዎችና ፡ ቤተ ፡ ሰባቸውን ፡ ሁሉ ፡
አመጣ ፡ በኬብሮንም ፡ ከተሞች ፡ ተቀመጡ ።
የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ በይሁዳ ፡ ቤት ፡ ፬
ይነግሥ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ በዚያ ፡ ቀቡት ።
ሳኦልን ፡ የቀበሩት ፡ የኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡
ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ።
ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ፭
መልእክተኞችን ፡ ልከ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡—
እናንተ ፡ ለጌታችሁ ፡ ለሳኦል ፡ ይህን ፡ ቸርነት ፡
አድርጋችኋልና ÷ ቀብራችሁትማልና ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ የተባረካችሁ ፡ ሁኑ ። አሁንም ፡ እግ ፮
ዚአብሔር ፡ ቸርነትንና ፡ እውነትን ፡ ያድርግላ
ችሁ ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ አድርጋችኋልና ፡ እኔ ፡
ደግሞ ፡ ይህን ፡ ቸርነት ፡ እመልስላችኋለሁ ።
አሁንም ፡ ጌታችሁ ፡ ሳኦል ፡ ሞቶአልና ፡ እጃ ፯
ችሁ ፡ ትጽና ÷ እናንተም ፡ ጨክኑ ፤ ዳግም ፡
የይሁዳ ፡ ቤት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አሆን ፡
ዘንድ ፡ ቀብተውኛል ።
የሳኦልም ፡ ጭፍራ ፡ አለቃ ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ ፰
አበኔር ፡ የሳኦልን ፡ ልጅ ፡ ኢያቡስቴን ፡ ወስዶ ፡
ወደ ፡ መሃናይም ፡ አሻገረው ፤ በገለዓድና ፡ ፱
በአሹራውያን ፡ በኢይዝራኤልም ፡ በኤፍራ
ምም ፡ በብንያምም ፡ በእስራኤልም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ አነገሠው ። የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ኢያቡስቴም ፡ ፲
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡
የአርባ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ሁለት ፡ ዓመ
ትም ፡ ነገሠ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ዳዊ
ትን ፡ ተከተለ ። ዳዊትም ፡ በይሁዳ ፡ ቤት ፡ ፲፩
ንግሦ ፡ በኬብሮን ፡ የተቀመጠበት ፡ ዘመን ፡
ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ነበረ ።
የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርና ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ የኢ ፲፪
ያቡስቴ ፡ ባሪያዎች ፡ ከመሃናይም ፡ ወደ ፡ ገባ
ዖን ፡ ወጡ ። የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብና ፡ የዳ ፲፫

ዊት ፡ ባሪያዎች ፡ ወጥተው ፡ በገባዖን ፡ ውኃ ፡
መቆሚያ ፡ አጠገብ ፡ ተገናኝአቸው ፡ በውኃ
ውም ፡ መቆሚያ ፡ በአንዱ ፡ ወገን ፡ እነዚህ ÷ በሌላ
ውም ፡ ወገን ፡ እነዚያ ፡ ሆነው ፡ ተቀመጡ ።
፲፬ አበኔርም ፡ ኢዮአብን ፡— ጕልማሶች ፡ ይነሡ ÷
በፊታችንም ፡ ይቈራቈሱ ፡ አለው ። ኢዮአ
ብም ፡— ይነሡ ፡ አለ ። ለብንያም ፡ ወገንና ፡
ለሳኦል ፡ ልጅ ፡ ለኢያቡስቴ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ÷
ከዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ተቈጥ
፲፭ ረው ፡ ተነሡ ። ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ የወደረ
ኛውን ፡ ራስ ፡ ያዘ ÷ ሰይፉንም ፡ በወደረኛው ፡
ጐን ፡ ሻጠ ÷ ተያይዘውም ፡ ወደቁ ። የዚያም ፡
ስፍራ ፡ ስም ፡ የስለታም ፡ ሰይፍ ፡ እርሻ ፡ ተብሎ ፡
፲፮ ተጠራ ÷ እርሱም ፡ በገባዖን ፡ ነው ። በዚያም ፡
ቀን ፡ ጽኑ ፡ ሰልፍ ፡ ሆነ ፤ በዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡
ፊት ፡ አበኔርና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ተሸነፉ ።
፲፯ በዚያም ፡ ሦስቱ ፡ የጽሩያ ፡ ልጆች ፡ ኢዮአ
ብና ፡ አቢሳ ፡ አሣሄልም ፡ ነበሩ ። አሣሄልም ፡
እንደ ፡ ዱር ፡ ሚዳቋ ፡ በሩጫ ፡ ፈጣን ፡ ነበረ ።
፲፰ አሣሄልም ፡ የአበኔርን ፡ ፍለጋ ፡ ተከታተለ ÷
አበኔርንም ፡ ከማሳደድ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ አላለም ።
፲፱ አበኔርም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተና ፡— አንተ ፡
አሣሄል ፡ ነህን ? አለ ። እርሱም ፡— እኔ ፡ ነኝ ፡
፳ አለ ። አበኔርም ፡— ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡
ግራ ፡ ፈቀቅ ፡ በል ፡ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ያዝ ÷
መሣሪያውንም ፡ ውሰድ ፡ አለው ። አሣሄል ፡
፳፩ ግን ፡ እርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ፈቀቅ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡
፳፪ አንቢ ፡ አለ ። አበኔርም ፡ አሣሄልን ፡— ከም
ድር ፡ ጋር ፡ እንዳላጣብቅህ ፡ እኔን ፡ ከማሳደድ ፡
ፈቀቅ ፡ በል ፤ ወደ ፡ ወንድምህ ፡ ወደ ፡ ኢዮ
አብ ፡ ፊቴን ፡ አቅንቼ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻል
፳፫ ኛል ? አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ ፈቀቅ ፡
ይል ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ አበኔርም ፡ በጦሩ ፡
ጫፍ ፡ ሆዱን ፡ ወጋው ÷ ጦሩም ፡ በኋላው ፡ ወጣ ÷
በዚያም ፡ ስፍራ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ። አሣሄልም ፡
ወድቆ ፡ በሞተበት ፡ ስፍራ ፡ የሚያልፍ ፡ ሁሉ ፡
ይቆም ፡ ነበር ።
፳፭ ኢዮአብና ፡ አቢሳም ፡ አበኔርን ፡ አሳደዱ ፡
በገባዖንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ በጋይ ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ አማ ፡ ኮረብታ ፡
፳፮ ድረስ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ ጠለቀች ። የብንያ
ምም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ አበኔር ፡ ተሰበሰቡ ÷ በአን
፳፯ ድነትም ፡ ሆኑ ÷ በኮረብታም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።
፳፰ አበኔርም ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ጮኸ ፡— ሰይፍ ፡
በውኑ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ያጠፋልን ? ፍጻሜ
ውሱ ፡ መራራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አታውቅምን ?
ሕዝቡ ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ከማሳደድ ፡ ይመ
፳፱ ለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ የማትናገር ፡ እስከ ፡ መቼ ፡
፴ ነው ? አለው ። ኢዮአብም ፡— ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔርን ! ባትናገር ፡ ኖሮ ፡ ሕዝቡ ፡ በጥዋት ፡
ወጥተው ፡ በሄዱ ፡ ነበር ÷ ወንድሞቻቸውንም ፡
፴፩ ማሳደድ ፡ በተዉ ፡ ነበር ፡ አለ ። ኢዮአብም ፡
ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ÷ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ቆመ ÷
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እስራኤልን ፡ አላሳደደም ÷
ሰልፍም ፡ አላደረገም ። አበኔርና ፡ ሰዎቹም ፡ ፴፪
ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ዓረባ ፡ እያለፉ ፡ ሄዱ ፡ ዮርዳ
ኖስንም ፡ ተሻገሩ ÷ ቢትሮንንም ፡ ሁሉ ፡ ከለፉ ፡
በኋላ ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ መጡ ።
ኢዮአብም ፡ አበኔርን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሰ ፡ ፴፫
ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ከዳዊትም ፡ ባሪያ
ዎች ፡ ከአሣሄል ፡ ሌላ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡
ጐደሉ ። የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ከብንያምና ፡ ፴፬
ከአበኔር ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ያህል ፡
ገደሉ ። አሣሄልንም ፡ አንሥተው ፡ በቤተ ፡ ፴፭
ልሔም ፡ በአባቱ ፡ መቃብር ፡ ቀበሩት ። ኢዮአ
ብና ፡ ሰዎቹም ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሄዱ ÷ በኬብ
ሮንም ፡ አነጉ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

በሳኦል ፡ ቤትና ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ፩
ብዙ ፡ ዘመን ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ፤ የዳዊት ፡ ቤት ፡
እየበረታ ÷ የሳኦል ፡ ቤት ፡ ግን ፡ እየደከመ ፡
የሚሄድ ፡ ሆነ ።
ለዳዊትም ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ በኬብሮን ፡ ተወ ፪
ለዱለት ፤ በኵሩም ፡ ከኢይዝራኤላዊቱ ፡ ከአኪ
ናሆም ፡ የተወለደው ፡ አምኖን ፡ ነበረ ። ሁለተ ፫
ኛውም ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡
ከነበረች ፡ ከአቢግያ ፡ የተወለደው ፡ ዳሉአያ ፡
ነበረ ። ሦስተኛውም ፡ ከጌሹር ፡ ንጉሥ ፡ ከተል
ማይ ፡ ልጅ ፡ ከመዓካ ፡ የተወለደው ፡ አቤሴሎም ፡
ነበረ ። አራተኛውም ፡ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶን ፬
ያስ ፡ አምስተኛውም ፡ የአቢጣል ፡ ልጅ ፡ ሰፋጥ
ያስ ፡ ነበረ ። ስድስተኛውም ፡ የዳዊት ፡ ሚስት ፡ ፭
የዔግላ ፡ ልጅ ፡ ይትረኃም ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡
ለዳዊት ፡ በኬብሮን ፡ ተወለዱለት ።
በሳኦል ፡ ቤትና ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ፮
ጦርነት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አበኔር ፡ በሳኦል ፡ ቤት ፡
ይበረታ ፡ ነበር ። ለሳኦልም ፡ የኢዮሄል ፡ ልጅ ፡ ፯
ሪጽፋ ፡ የተባለች ፡ ቁባት ፡ ነበረችው ። ኢያቡ
ስቴም ፡ አበኔርን ፡— ወደ ፡ አባቴ ፡ ቁባት ፡ ለምን ፡
ገባህ ? አለው ። አበኔርም ፡ በኢያቡስቴ ፡ ቃል ፡ ፰
እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እኔ ፡ ለአባ
ትህ ፡ ለሳኦል ፡ ቤት ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዘመዶ
ቹም ፡ ቸርነት ፡ አድርጌአለሁ ÷ አንተንም ፡ ለዳ
ዊት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጠሁም ፡ አንተም ፡
ዛሬ ፡ ከዚህች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ሠራሁት ፡ ኃጢ
አት ፡ ትከሰሰኛለህ ፤ በውኑ ፡ እኔ ፡ የውሻ ፡ ራስ ፡
ነኝን ? መንግሥትን ፡ ከሳኦል ፡ ቤት ፡ ያወጣ ፡ ፱፣፲
ዘንድ ፡ የዳዊትንም ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤልና ፡
በይሁዳ ፡ ከዳን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡
ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለዳዊት ፡ እንደ ፡ ማለለት ፡ እንዲሁ ፡ ክእርሱ ፡
ጋር ፡ በላደርግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአበኔር ፡ ይህን ፡
ያድርግበት ፡ ይህንም ፡ ይጨምርበት ። ኢያቡ ፲፩
ስቴም ፡ አበኔርን ፡ ይፈራው ፡ ነበርና ፡ አንዳች ፡
ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።
አበኔርም ፡ ለዳዊት ፡— ምድሪቱ ፡ ለማን ፡ ፲፪
ናት ? ከእኔ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርግ ÷

እጇም ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ትሠናለች ÷ እስራኤል
ንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እንተ ፡ እመልሰዋለሁ ፡
ብለው ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞች ፡ ሰደ
፲፫፡ ደለት ። ዳዊትም ፡— ይሁን ÷ ከእንተ ፡ ጋር ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርጋለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡
ነገር ፡ ከእንተ ፡ እሻለሁ ፡ ፊቴን ፡ ለማየት ፡ በመ
ጣህ ፡ ጊዜ ÷ የሳኦልን ፡ ልጅ ፡ ሜልክልን ፡ ካላ
፲፬፡ መጣህልኝ ፡ ፊቴን ፡ አታይም ፡ አለ ። ዳዊትም ፡
ወደ ፡ ሳአል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያቡስቴ ፡— በመቶ ፡
ፍልስጥኤማውያን ፡ ሸለፈት ፡ ያጨኋት ፡ ሚስ
ቴን ፡ ሜልክልን ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞ
፲፭፡ ችን ፡ ሰደደ ። ኢያቡስቴም ፡ ልከ ፡ ከሴሳ ፡ ልጅ ፡
፲፮፡ ከጌልዋ ፡ ከፈልጢኤል ፡ ወሰዳት ። በልዋም ፡
እያለቀሰ ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ሄደ ÷ እስከ ፡ ብራ
ቁም ፡ ደረሰ ፡ ተከተላት ። አበኔርም ፡— ሂድ ÷
ተመለስ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ ተመለሰ ።
፲፯፡ አበኔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡— አስ
ቀድሞ ፡ ዳዊት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡
፲፰፡ ዘንድ ፡ ፈልጋችሁ ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡
ስለ ፡ ዳዊት ፡— በባሪያዬ ፡ በዳዊት ፡ እጅ ፡ ሕዝ
ቤን ፡ እስራኤልን ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅና ፡
ከጠላቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ አድናለሁ ፡ ብሎ ፡
ተናግሮአልና ፡ እንግዲህ ፡ አሁን ፡ አድርጉ ፡
፲፱፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። አበኔርም ፡ ደግሞ ፡ በብንያም ፡
ወገን ፡ ጆሮ ፡ ተናገረ ፡ አበኔርም ፡ ደግሞ ፡ በእ
ስራኤልና ፡ በብንያም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡
የነበረውን ፡ ለዳዊት ፡ ሊነግረው ፡ ወደ ፡ ኬብ
፳፡ ሮን ፡ ሄደ ። አበኔርም ፡ ከሀያ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡
ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጣ ። ዳዊትም ፡
፳፩፡ ለአበኔርና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡
ግብዣ ፡ አደረገላቸው ። አበኔርም ፡ ዳዊትን ፡—
ተነሥቼ ፡ ልሂድ ÷ ከእንተ ፡ ጋርም ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ እንዲያደርጉ ÷ ነፍስህም ፡ እንደ ፡ ወደ
ደች ፡ ሁሉን ፡ እንድትገዛ ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡
ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ ልሰብስብ ፡ አለው ። ዳዊ
ትም ፡ አበኔርን ፡ አሰናበተው ÷ በደኅናም ፡ ሄደ ።
፳፪፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የዳዊት ፡ ባሪያዎችና ፡ ኢዮ
አብ ፡ ከዘመቻ ፡ ታላቅ ፡ ምርኮ ፡ ይዘው ፡ መጡ ።
አበኔር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ አሰናብቶት ፡ በደኅና ፡
ሄዶ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በኬብሮን ፡ አልነበረም ።
፳፫፡ ኢዮአብና ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበረ ፡ ጭፍራ ፡
ሁሉ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡— የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡
ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጣ ÷ አሰናበተውም ፡ በደኅና ፡
ውም ፡ ሄደ ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ለኢዮአብ ፡ ነገ
፳፬፡ ሩት ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ገብቶ ፡—
ምን ፡ አደረግህ ? እነሆ ÷ አበኔር ፡ መጥቶልህ ፡
ነበር ፡ በደኅና ፡ እንዲሄድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሰና
፳፭፡ በት ፡ ኸው ? የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡ ያታልልህ ፡
ዘንድ ÷ መውጫህንና ፡ መግቢያህንም ፡ ያውቅ ፡
ዘንድ ÷ የምታደርገውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያስተ
፳፮፡ ውል ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አታውቅምን ?
፳፯፡ አለው ። ኢዮአብም ፡ ከዳዊት ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡
መልእክተኞችን ፡ ከአበኔር ፡ በኋላ ፡ ላከ ፡ ከሴ
ይራም ፡ ጒድጓድም ፡ መለሱት ። ዳዊት ፡ ግን ፡
ይህን ፡ አላወቀም ።
፳፰፡ አበኔርም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡
ኢዮአብ ፡ በበር ፡ ውስጥ ፡ በቂይታ ፡ ይናገረው ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ ወሰደው ፡ በዚያም ፡
ለወንድሙ ፡ ለአሣሄል ፡ ደም ፡ ተበቅሎ ፡ ሆዱን ፡
መታው ፡ ሞተም ። በኋላም ፡ ዳዊት ፡ ይህ ፡
፳፱፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡— ከኔር ፡
ልጅ ፡ ከአበኔር ፡ ደም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ለዘላለም ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ÷ መንግሥቴም ፡
ንጹሕ ፡ ነው ፡ በኢዮአብ ፡ ራስ ፡ ላይና ፡ በአ
፴፡ ባቱ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይምጣበት ፡ በኢዮአ
ብም ፡ ቤት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡
ለምጻም ፡ ወይም ፡ አንካሳ ፡ ወይም ፡ በሰይፍ ፡
የሚወድቅ ፡ ወይም ፡ እንጀራ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡
አይታጣ ፡ አለ ። ኢዮአብና ፡ ወንድሙ ፡ አቢ
፴፩፡ ሳም ፡ በሰልፍ ፡ በገባዖን ፡ ወንድማቸውን ፡ አሣ
ሄልን ፡ ገድሎ ፡ ነበርና ፡ አበኔርን ፡ ገደሉት ።
፴፪፡ ዳዊትም ፡ ኢዮአብንና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበ
ሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡— ልብሳችሁን ፡ ቅደዱ ÷
ማቅም ፡ ልበሱ ÷ በአበኔርም ፡ ፊት ፡ አልቅሱ ፡
አላቸው ። ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ከቃሬዛው ፡ በኋላ ፡
ሄደ ። አበኔርንም ፡ በኬብሮን ፡ ቀበሩት ፡ ንጉ
ሡም ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ በአበኔር ፡
መቃብር ፡ አጠገብ ፡ አለቀሰ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡
አለቀሱ ። ንጉሡም ፡ ለአበኔር ፡—
፴፫፡ አበኔር ፡ ሰነፍ ፡ እንደሚሞት ፡ ይሞታልን ?
፴፬፡ እጅህ ፡ አልታሰረም ÷ እግርህም ፡ በሰንሰ
ለት ፡ አልተያዘም ፡
ሰው ፡ በዓመፀኞች ፡ ፊት ፡ እንደሚወድቅ ፡
አንተ ፡ እንዲሁ ፡ ወደቅህ ፡
ብሎ ፡ የልቅሶ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘለት ። ሕዝቡም ፡
፴፮፡ ሁሉ ፡ ዋይታ ፡ አብዝተው ፡ አለቀሱ ። ሕዝ
ቡም ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ ሳይመሽ ፡ ዳዊትን ፡ እንጀራ ፡
ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ሊጋብዙት ፡ መጡ ፡ ዳዊት ፡
ግን ፡— ፀሐይ ፡ ሳትጠልቅ ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡
ሌላ ፡ ነገር ፡ ብቀምስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡
ያድርግብኝ ÷ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ፡ ብሎ ፡
፴፯፡ ማለ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ተመለከቱ ÷
ደስ ፡ አሰኛቸውም ፡ በሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡
ንጉሥ ፡ ያደረገው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ።
፴፰፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እስራኤልም ፡
ሁሉ ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ የአበኔር ፡ ሞት ፡ ከንጉሡ ፡
ዘንድ ፡ እንዳልሆነ ፡ አወቁ ። ንጉሡም ፡ ባሪያ
፴፱፡ ዎቹን ፡— ዛሬ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መኰን
ንና ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ አታውቁ
ምን ? እኔም ፡ ዛሬ ፡ ምንም ፡ ለመንገሥ ፡ የተቀ
በሁ ፡ ብሆን ፡ ደካማ ፡ ነኝ ፡ እነዚህም ፡ ሰዎች ፡
የጽሩያ ፡ ልጆች ፡ በርትተውብኛል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ክፋት ፡ በሠራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ክፋቱ ፡
ይመልስበት ፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩፡ የሳአልም ፡ ልጅ ፡ ኢያቡስቴ ፡ አበኔር ፡ በኬ
ብሮን ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጁ ፡ ደከ
መች ÷ እስራኤላውያንም ፡ ሁሉ ፡ ደነገጡ ።
፪፡ ለሳአልም ፡ ልጅ ፡ ለኢያቡስቴ ፡ የጭፍራ ፡ አለ
ቆች ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩት ፡ የአን
ዱም ፡ ስም ፡ በዓና ÷ የሁለተኛውም ፡ ስም ፡
ሬካብ ፡ ነበረ ÷ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ የብኤሮ
ታዊው ፡ የሬሞን ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፡ ብኤሮትም ፡
፫፡ ለብንያም ፡ ተቈጥራ ፡ ነበር ። ብኤሮታውያንም ፡
ወደ ፡ ጌቴም ፡ ሸሽተው ፡ ነበር ÷ እስከ ፡ ዛሬም ፡
ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተጠግተው ፡ ነበር ።
፬፡ ለሳአልም ፡ ልጅ ፡ ለዮናታን ፡ አንድ ፡ ሽባ ፡
የሆነ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ። የሳአልና ፡ የዮናታን ፡
ወሬ ፡ ከኢይዝራኤል ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የአም
ስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ÷ ሞግዚቱም ፡ አዝ
ላው ፡ ሸሸች ፡ ፈጥናም ፡ ስትሸሽ ፡ ወድቆ ፡
ሽባ ፡ ሆነ ። ስሙም ፡ ሜምፊቦስቴ ፡ ነበረ ።
፭፡ የብኤሮታዊውም ፡ የሬሞን ፡ ልጆች ፡ ሬካ
ብና ፡ በዓና ፡ ቀኑ ፡ ሲሞቅ ፡ ወደ ፡ ኢያቡስቴ ፡
ቤት ፡ መጡ ፡ እርሱም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ በም
፮፡ ንጣፉ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ። በረኛይቱም ፡
ስንዴ ፡ ታበጥር ፡ ነበር ÷ እንቀላፍታም ፡ ተኛታ ፡
ነበር ፡ ሬካብና ፡ ወንድሙ ፡ በዓናም ፡ በቀስታ ፡
፯፡ ገቡ ። ወደ ፡ ቤትም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡
በእልፍኙ ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡
መቱት ÷ ገደሉትም ፡ ራሱንም ፡ ቈርጠው ፡ ወሰ
ዱት ÷ በዓረባም ፡ መንገድ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡
፰፡ ሄዱ ። የኢያቡስቴንም ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡
ዳዊት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ÷ ንጉሡንም ፡—
ነፍስህን ፡ ይሻ ፡ የነበረው ፡ የጠላትህ ፡ የሳአል ፡
ልጅ ፡ የኢያቡስቴ ፡ ራስ ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ዛሬ ፡ ከሳአልና ፡ ከዘሩ ፡ ለጌታችን ፡ ለን
፱፡ ጉሥ ፡ ተበቀለለት ፡ አሉት ። ዳዊትም ፡ ለብኤ
ሮታዊው ፡ ለሬሞን ፡ ልጆች ፡ ለሬካብና ፡ ለወን
ድሙ ፡ ለበዓና ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡—
፲፡ ነፍሴን ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ ያዳነ ፡ ሕያው ፡ እግዚ
አብሔርን ! መልካም ፡ ወሬ ፡ የያዘ ፡ መስ
፲፩፡ ሎት ፡— እነሆ ÷ ሳአል ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ የነገረኝን ፡
የምስራቹ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሆን ፡ ይገር ፡ በጺቅ
ላግ ፡ ገደልሁት ። ይልቁንስ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡
በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ የገደላችሁ ፡
ትን ፡ እናንተን ፡ ኃጢአተኞችንማ ፡ እንዴት ፡
፲፪፡ ነዋ ? ደሙን ፡ ከእጃችሁ ፡ አልሻውምን ? ከም
ድርም ፡ አላጠፋችሁምን ? ዳዊትም ፡ ጕልማ
ሶቹን ፡ አዘዘ ÷ ገደሉአቸውም ፡ እጃቸውንና ፡
እግራቸውን ፡ ቈርጠው ፡ በኬብሮን ፡ በውኃ ፡
መቆሚያ ፡ አጠገብ ፡ አንጠለጠሉአቸው ። የኢ
ያቡስቴንም ፡ ራስ ፡ ወስደው ፡ በአበኔር ፡ መቃ
ብር ፡ በኬብሮን ፡ ቀበሩት ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩፡ የእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡
ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥተው ፡— እነሆ ÷ እኛ ፡ የአ
ጥንትህ ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋህ ፡ ቍራጭ ፡ ነን ። አስ
፪፡ ቀድሞ ፡ ሳአል ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡
ሳለ ፡ እስራኤልን ፡ የምታወጣና ፡ የምታገባ ፡
አንተ ፡ ነበርህ ፡ እግዚአብሔርም ፡— እንተ ፡
ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ትጠብቃለህ ÷ በእስራ
ኤልም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትሆናለህ ፡ ብሎህ ፡ ነበር ፡
፫፡ አሉት ። የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ፡ ንጉሡ ፡
ዳዊትም ፡ በኬብሮን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አደረገ ፡ በእስራ
ኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ ቀቡት ።
፬፡ ዳዊትም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡
፭፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ÷ አርባ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።
፮፡ በኬብሮን ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ከስድስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በእ
ስራኤል ፡ ሁሉና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡
፯፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።
ንጉሡና ፡ ሰዎቹም ፡ በእገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከተቀ
መጡት ፡ ከኢያቡሳውያን ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡
ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዱ ፡ እነርሱም ፡— ዳዊት ፡
ወደዚህ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ አስበው ፡
ነበርና ፡ ዳዊትን ፡— ዕውሮችንና ፡ እንከሰችን ፡
ከላወጣህ ፡ በቀር ፡ ወደዚህ ፡ አትገባም ፡ አሉት ።
፰፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ አምባይቱን ፡ ጽዮንን ፡ ያዘ ÷
እርስዋም ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ናት ። በዚያም ፡
ቀን ፡ ዳዊት ፡— ኢያቡሳውያንን ፡ የሚመታ ፡
በውኃ ፡ መሄጃው ፡ ይውጣ ፡ የዳዊትም ፡ ነፍስ ፡
የምትጠላቸውን ፡ ዕውሮችንና ፡ እንከሰችን ፡
ያውጣ ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ በምሳሌ ፡— ዕው
ርና ፡ እንካሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አይግቡ ፡ ተባለ ።
፱፡ ዳዊትም ፡ በአምባይቱ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ÷ ፱፡
የዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ። ዳዊትም ፡
ዙሪያዋን ፡ ከሚሎ ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ቀጠ
ራት ። ዳዊትም ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ፡ የሠራዊት ፡
፲፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ነበረ ።
የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡
መልእክተኞችን ፡ የዝግባ ፡ እንጨትንም ፡ እና
ጢዎችንም ፡ ጠራቢዎችንም ፡ ላከ ፡ ለዳዊትም ፡
ቤት ፡ ሠሩለት ። ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእ
፲፪፡ ስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ እንዳጸናው ÷
ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ እስራኤልም ፡ መንግሥቱን ፡
ከፍ ፡ እንዳደረገ ፡ አወቀ ።
ዳዊትም ፡ ከኬብሮን ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ሌሎ
፲፫፡ ቹን ፡ ቁባቶቹንና ፡ ሚስቶቹን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ወሰደ ፡ ለዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ ተወለዱለት ። በኢየሩሳሌምም ፡ የተ
፲፬፡

ወለጶላት ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሳሙስ ÷ ፲፫፡ ሰባብ ÷ ናታን ÷ ሰሎሞን ÷ ኢያቢሐር ፡ ኤሊ ፲፬፡ ሱዓ ÷ ናፌቅ ÷ ያፍያ ÷ ኤሊሳማ ÷ ኤሊዳሄ ፡ ኤሊፋላት ።

፲፭፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዳዊት ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ሰሙ ÷ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሁሉ ፡ ዳዊትን ፡ ሊፈልጉ ፡ ወጡ ፡ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ፲፮፡ ወረደ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ በራ ፲፯፡ ፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ተበትነው ፡ ሰፈሩ ። ዳዊትም ፡ — ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ልውጣን ? በእጃስ ፡ አሳልፈህ ፡ ትሰጣቸዋለህን ? ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፡ ዳዊትን ፡ — ፍልስጥኤማውያንን ፡ በእርግጥ ፡ በእጅህ ፡ አሳ ፲፰፡ ልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁና ፡ ውጣ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ወደ ፡ በኣልፐራሲም ፡ መጣ ÷ በዚያም ፡ መታቸውና ፡ — ውኃ ፡ እንዲያፈርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቼን ፡ በፊቴ ፡ አፈረሳቸው ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ በኣል ፲፱፡ ፐራሲም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ጣዖቶቻቸውንም ፡ በዚያ ፡ ተዉ ÷ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወሰዱአቸው ።

፳፩፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ደግሞ ፡ መጡ ÷ በራ ፳፪፡ ፋይምም ፡ ሸለቆ ፡ ተበትነው ፡ ሰፈሩ ። ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እርሱም ፡ — በኋላ ቸው ፡ ዙረህ ፡ በሾላው ፡ ዛፍ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ፳፫፡ ግጠማቸው ፡ እንጂ ። አትውጣ ። በሾላውም ፡ ዛፍ ፡ ራስ ፡ ውስጥ ፡ የሽውሽውታ ፡ ድምፅ ፡ ስት ሰማ ÷ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፍልስ ጥኤማውያንን ፡ ሠራዊት ፡ ለመምታት ፡ በፊትህ ፡ ወጥቶ ፡ ይሠናልና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቸኮል ፳፬፡ አለው ። ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፡ ከገባዖንም ፡ እስከ ፡ ጌዝር ፡ ድረስ ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ መታ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩፡ ዳዊትም ፡ ዳግም ፡ ከእስራኤል ፡ የተመረጡ ትን ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ሰበሰበ ። ፪፡ ዳዊትና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ካለች ፡ ከበኣል ፡ ተነሥተው ፡ በኪሩብ ፡ ላይ ፡ በተቀመጠ ፡ በሠራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተጠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ ያመጡ ፫፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ በአዲስ ፡ ሰረገላ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፡ በኮረብታውም ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ ከአሚናዳብ ፡ ቤት ፡ አመጡት ፡ የአሚናዳብ ፡ ልጆችም ፡ ዖዛ ፡ እና ፡ አሒዮ ፡ ፬፡ አዲሱን ፡ ሰረገላ ፡ ይነዱ ፡ ነበር ። በኮረብታው ውም ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ ከአሚናዳብ ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ባመጡ ፡ ጊዜ ፡ ፭፡ አሒዮ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። ዳዊትና ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ በቅኔና ፡ በበገና ፡ በመሰንቆም ፡ በከበሮም ፡ በንጋጉትና ፡ በጸናጽል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሙሉ ፡ ኃይላቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።

፮፡ ወደ ፡ ናኮንም ፡ አውድማ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በሬዎቹ ፡ ይፋንኑ ፡ ነበርና ፡ ዖዛ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፯፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ያዘ ። የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በዖዛ ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ድፍረቱ ፡ በዚያው ፡ ቀሠፈው ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ አጠገብ ፡ በዚያው ፡ ሞተ ። እግዚአብሔርም ፡ ዖዛን ፡ ስለ ፡ ሰበረው ፡ ፰፡ ዳዊት ፡ አዘነ ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የዖዛ ፡ ስብራት ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ። ፱፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፲፡ ፈራና ፡— የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ ይመጣል ? አለ ። ዳዊትም ፡ የእግዚ አብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከተማ ፡ ያመጣው ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፡ ዳዊ ፲፩፡ ትም ፡ በጌት ፡ ሰው ፡ በአቢዳራ ፡ ቤት ፡ አገባው ። የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ በጌት ፡ ሰው ፡ በአ ቢዳራ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ተቀመጠ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አቢዳራንና ፡ ቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ባረከ ።

፲፪፡ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ የአቢዳ ራን ፡ ቤትና ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ታቦት ፡ አንደ ፡ ባረከ ፡ ሰማ ። ዳዊትም ፡ ሄዶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከአቢዳራ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከተማ ፡ በደስታ ፡ አመጣው ። ፲፫፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ስድ ስት ፡ አርምጃ ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ በሬና ፡ አንድ ፡ ፍሪዳ ፡ ሠዋ ። ዳዊትም ፡ በሙሉ ፡ ኃይሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይዘፍን ፡ ነበር ፡ ዳዊትም ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ። ፲፬፡ ዳዊትና ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ እየነፉ ፡ የእግዚአ ብሔርን ፡ ታቦት ፡ አመጡ ።

፲፭፡ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከተማ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ሜልክል ፡ በመስኮት ፡ ሆና ፡ ተመለከተች ÷ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሲዘልልና ፡ ሲዘ ፲፮፡ ፍን ፡ አየች ፡ በልብዋም ፡ ናቀችው ። የእግዚ አብሔርንም ፡ ታቦት ፡ አገቡ ÷ ዳዊትም ፡ በተከ ለለት ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በስፍራው ፡ አኖሩት ፡ ዳዊትም ፡ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋ ፲፯፡ ዕትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አሳረገ ። ዳዊ ትም ፡ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ማሳረግ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ በሠራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መረቀ ። ለሕዝ ፲፰፡ ቡም ፡ ሁሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ወገን ፡ ለወንዱም ፡ ለሴቱም ፡ ለእያንዳንዱ ፡ አንዳንድ ፡ እንጀራ ፡ አንዳንድም ፡ የሥጋ ፡ ቍራሬ ፡ አንዳንድም ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥና ፡ አከፋፈለ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

፳፡ ዳዊትም ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ሊመርቅ ፡ ተመለሰ ። ሚ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሜልክል ፡ ዳዊትን ፡ ለመቀ በል ፡ ወጣችና ፡— ምናምንቴዎች ፡ እርቃናቸ ውን ፡ እንደሚገልጡ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡

በባሪያዎቹ ፡ ቈነጃጅት ፡ ፊት ፡ እርቃኑን ፡ በመ ገለጡ ፡ ምንኛ ፡ የተከበረ ፡ ነው ፤ አለችው ። ፳፩፡ ዳዊትም ፡ ሚልክልን ፡— በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘፍኛለሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ በእስራ ኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ከአባትሽና ፡ ከቤቱ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የመረጠኝ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፡ ስለዚህም ፡ በእግዚ ፳፪፡ አብሔር ፡ ፊት ፡ እጫወታለሁ ። አሁንም ፡ ከሆ ንሁት ፡ ይልቅ ፡ የተናቅሁ ፡ እሆናለሁ ÷ በዓይ ንሽም ፡ እዋረዳለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በተናገርሽው ፳፫፡ ቈነጃጅት ፡ ዘንድ ፡ እከብራለሁ ፡ አላት ። የሳኦ ልም ፡ ልጅ ፡ ሚልክል ፡ እስከ ፡ ሞተችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልጅ ፡ አልወለደችም ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ንጉሡ ፡ በቤቱ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዙሪያው ፡ ካሉት ፪፡ ጠላቶቹ ፡ ሁሉ ፡ በሳረፈው ፡ ጊዜ ÷ ንጉሡ ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡— እኔ ፡ ከዝግባ ፡ በተሠራ ፡ ቤት ፡ ተቀምጬአለሁ ÷ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ግን ፡ በመጋረጆች ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፫፡ ተቀመጠ ፡ እይ ፡ አለው ። ናታንም ፡ ንጉ ሡን ፡— እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ሂድ ÷ በልብህም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ አድርግ ፬፡ አለው ። በዚያም ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ናታን ፡ መጣ ፤ እንዲህም ፡ አለው ፡— ፭፡ ሂድ ÷ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ ንገረው ፡— እግዚአ ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የአስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣሁበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በድንኳንና ፡ በማ ደሪያ ፡ እሄድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በቤት ፡ አልተቀ መጥሁምና ፡ አንተ ፡ የምኖርበትን ፡ ቤት ፡ እት ፮፡ ሠራልኝም ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ባለፍሁበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡— ስለ ፡ ምን ፡ ቤትን ፡ ከዝግባ ፡ እንጨት ፡ አልሠራችሁልኝም ? ብዬ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ያጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ከእ ስራኤል ፡ ነገድ ፡ ላዘዝሁት ፡ ለአንዱ ፡ በሙሉ ፡ ፯፡ ተናግሬአለሁን ? አሁንም ፡ ዳዊትን ፡ በሪያዬን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፡— የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— አንተ ፡ መንጋውን ፡ ስትከተል ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፰፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ከበግ ፡ ጥበቃ ፡ ወሰድሁህ ፡ በሄ ድህበትም ፡ ሁሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነበርሁ ÷ ጠላቶችህንም ፡ ሁሉ ፡ ከፊትህ ፡ አጠፋሁ ፡ በም ድርም ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ ታላላቆቹ ፡ ስም ፱፡ ታላቅ ፡ ስም ፡ አደርግልሃለሁ ። ለሕዝቤም ፡ ለእ ስራኤል ፡ ስፍራ ፡ አደርግለታለሁ ÷ እተክለው ፡ ማለሁ ፤ በስፍራውም ፡ ይቀመጣል ÷ ከዚያም ፡ ፲፡ በኋላ ፡ አይናወጥም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ዘመንና ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጆች ፡ እንዳ ፲፩፡ ስነሣሁበት ፡ ጊዜ ፡ ግፈኞች ፡ ተመልሰው ፡ አያ ስጨንቁትም ፡ ከጠላቶችህም ፡ አሳርፍሃለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ ያንግርሃል ። ዕድሜህም ፡ በተፈ ፲፪፡ ጸመ ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶችህም ፡ ጋር ፡ በንቀላፋህ ፡ ጊዜ ÷ ከወገብህ ፡ የሚወጣውን ፡ ዘርህን ፡ ከእንተ ፡ በኋላ ፡ አስነሣለሁ ÷ መንግሥቱንም ፡ አጸናለሁ ። ፲፫፡ እርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፤ የመንግሥቱ ፲፬፡ ንም ፡ ዙፋን ፡ ለዘላለም ፡ አጸናለሁ ። እኔም ፡ አባት ፡ እሆነዋለሁ ÷ እርሱም ፡ ልጅ ፡ ይሆነኛል ፤ ክፉ ፡ ነገርም ፡ ቢያደርግ ÷ ሰው ፡ በሚቀጣበት ፡ በትርና ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መቅጫ ፡ እገሥጸዋ ፲፭፡ ለሁ ፡ ከፊቴም ፡ ከጣልሁት ፡ ከሳኦል ፡ እንዳራ ፲፮፡ ቅሁ ፡ ምሕረቴን ፡ ከእርሱ ፡ አላርቅም ። ቤት ፲፯፡ ሀና ፡ መንግሥትህም ፡ በፊቴ ፡ ለዘላለም ፡ ይጠ ነክራል ÷ ዙፋንህም ፡ ለዘላለም ፡ ይጸናል ። እን ፲፰፡ ደዚህ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህም ፡ ራእይ ፡ ሁሉ ፡ ናታን ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

፲፱፡ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ገባ ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሆይ ÷ እስከዚህ ፡ ያደረስኸኝ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ? ቤቴስ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ጌታዬ ፡ እግ ፳፡ ዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ ይህ ፡ በፊትህ ፡ ጥቂት ፡ ነበረ ፤ ስለ ፡ ባሪያህም ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ለሩቅ ፡ ዘመን ፡ ተናገርህ ! ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ ይህ ፡ የሰው ፡ ሕግ ፡ ነው ። ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ ፳፩፡ አንተ ፡ በባሪያህ ፡ ታውቃለህና ፡ ዳዊትስ ፡ ይናገ ርህ ፡ ዘንድ ፡ የሚጨምረው ፡ ምንድር ፡ ነው ? ለባሪያህም ፡ ታስታውቀው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ቃልህ ፡ ፳፪፡ ምክንያትና ፡ እንደ ፡ ልብህ ፡ አሳብ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደረግህ ። ስለዚህም ÷ አቤቱ ፡ ፳፫፡ አምላኬ ፡ ሆይ ÷ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ የለምና ÷ በጆሮአችንም ፡ እንደ ፡ ሰማን ፡ ሁሉ ፡ ከእንተ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ነህ ። ለእርሱ ፡ ለራሱ ፡ እንዲሆን ፡ ሕዝብን ፡ ይቤዥ ፡ ፳፬፡ ዘንድ ፡ ለእርሱ ፡ ለራሱም ፡ ስም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ÷ በእሕዛብና ፡ በአምላኮቻቸውም ፡ ፊት ፡ ከግብጽ ፡ በተቤዠው ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ተአምራትንና ፡ ድንቅን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሄደለት ፡ እንደ ፡ ሕዝብህ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ያለ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ሕዝብ ፡ አለ ? ሕዝብ ፳፭፡ ህንም ፡ እስራኤልን ፡ ለዘላለም ፡ ሕዝብ ፡ አድ ርገህ ፡ አጽንተኸዋል ፡ አንተም ÷ አቤቱ ፡ አም ላክ ፡ ሆነሃቸዋል ። አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ÷ አሁ ፳፮፡ ንም ፡ ለባሪያህና ፡ ለቤቱ ፡ የተናገርኸውን ፡ ለዘ ላለም ፡ አጽናው ÷ እንደ ፡ ተናገርህም ፡ አድርግ ። ፳፯፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ዘንድ ፡ ስምህ ፡ ለዘላ ለም ፡ ታላቅ ፡ ይሁን ፤ የባሪያህም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ በፊትህ ፡ የጸና ፡ ይሁን ። አቤቱ ፡ የእስ ፳፰፡ ራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡— እኔ ፡ ቤት ፡ እሠራልሃለሁ ፡ ብለህ ፡ ለባሪያህ ፡ ገልጠሃልና ፡ ስለዚህ ፡ ባሪያህ ፡ ይህ ችን ፡ ጸሎት ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ደፈረ ። ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ ፳፱፡ አሁንም ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ ነህ ÷ ቃልህም ፡ እውነት ፡ ነው ÷ ይህንም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለባ ሪያህ ፡ ተናግረሃል ። ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፴፡

ሆይ ÷ አንተ ፣ ተናግረሃልና ፣ አሁን ፣ እንግዲህ ፣ ለዘላለም ፣ በፊትህ ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ የባሪያህን ፣ ቤት ÷ እባክህ ÷ ባርክ ፣ በበረከትህም ፣ የባሪያህ ፣ ቤት ፣ ለዘላለም ፣ ይባረክ ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ ከዚህም ፣ በኋላ ፣ ዳዊት ፣ ፍልስጥኤማውያንን ፣ መታ ÷ አዋረዳቸውም ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፣ እጅ ፣ ሚቴግ ፣ አማ ፣ የተበለችውን ፣ ከተማ ፣ ወሰደ ።

፪ ሞዓብን ፣ መታ ÷ ሞዓባውያንንም ፣ በምድር ፣ ጥሎ ፣ በገመድ ፣ ሰፈራቸው ፤ በሁለትም ፣ ገመድ ፣ ለሞት ፣ በእንድም ፣ ገመድ ፣ ሙሉ ፣ ለሕያውት ፣ ሰፈራቸው ፤ ሞዓባውያንም ፣ ለዳዊት ፣ ገባሮች ፣ ሆኑ ÷ ግብርም ፣ አመጡለት ።

፫ ዳዊትም ፣ ደግሞ ፣ በኤፍራጥስ ፣ ወንዝ ፣ አጠገብ ፣ የነበረውን ፣ ግዛት ፣ መልሶ ፣ ለመያዝ ፣ በሄደ ፣ ጊዜ ፣ የረአብን ፣ ልጅ ፣ የሱባን ፣ ንጉሥ ፣ አድርአዛርን ፣ መታ ። ዳዊትም ፣ ከእርሱ ፣ ሺህ ፣ ሰባት ፣ መቶ ፣ ፈረሰኞች ÷ ሀያ ፣ ሺህም ፣ እግረኞች ፣ ያዘ ፣ ዳዊትም ፣ የሰረገለኛውን ፣ ፈረስ ፣ ሁሉ ፣ ቋንጃ ፣ ቈረጠ ፣ ለመቶ ፣ ሰረገላ ፣ ብቻ ፣ አስቀረ ። ከደማስቆም ፣ ሶርያውያን ፣ የሱባን ፣ ንጉሥ ፣ አድርአዛርን ፣ ሊረዱ ፣ በመጡ ፣ ጊዜ ፣ ዳዊት ፣ ከሶርያውያን ፣ ሀያ ፣ ሁለት ፣ ሺህ ፣ ሰዎች ፣ ገደለ ። ዳዊትም ፣ በደማስቆ ፣ ሶርያ ፣ ጭፍሮች ፣ አኖረ ፣ ሶርያውያንም ፣ ለዳዊት ፣ ዘበኖች ፣ ሆኑ ÷ ግብርም ፣ አመጡለት ፤ እግዚአብሔርም ፣ ዳዊት ፣ በሄደበት ፣ ሁሉ ፣ ድልን ፣ ሰጠው ። ዳዊትም ፣ ለአድርአዛር ፣ ባሪያዎች ፣ የነበሩትን ፣ የወርቅ ፣ ጋሻዎች ፣ ወሰደ ÷ ወደ ፣ ኢየሩሳሌምም ፣ ይዘአቸው ፣ መጣ ። ንጉሡም ፣ ዳዊት ፣ ከአድርአዛር ፣ ከተሞች ፣ ከቤሓሕና ፣ ከቤሮታይ ፣ እጅግ ፣ ብዙ ፣ ናስ ፣ ወሰደ ።

፱ የሐማትም ፣ ንጉሥ ፣ ቶዑ ፣ ዳዊት ፣ የአድርአዛርን ፣ ጭፍራ ፣ ሁሉ ፣ እንደ ፣ መታ ፣ ሰማ ።

፲ ቶዑም ፣ ከአድርአዛር ፣ ጋር ፣ ሁልጊዜ ፣ ይዋጋ ፣ ነበርና ፣ ዳዊት ፣ አድርአዛርን ፣ ድል ፣ ስለ ፣ መታ ፣ ቶዑ ፣ ልጁን ፣ አዶራምን ፣ ደኅንነቱን ፣ ይጠይቅ ፣ ዘንድ ÷ ይመርቀውም ፣ ዘንድ ፣ ወደ ፣ ንጉሥ ፣ ዳዊት ፣ ላከው ፤ እርሱም ፣ የብርና ፣ የወርቅ ፣ የናስም ፣ ዕቃ ፣ ይዞ ፣ መጣ ።

፲፩፣፲፪ ንጉሥ ፣ ዳዊትም ፣ ከሸነፋቸው ፣ ከአሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ ከሶርያ ፣ ከሞዓብም ፣ ከአሞንም ፣ ልጆች ፣ ከፍልስጥኤማውያንም ፣ ከአማሌቅም ፣ ከረአብም ፣ ልጅ ፣ ከሱባ ፣ ንጉሥ ፣ ከአድርአዛር ፣ ምርኮ ፣ ከቀደሰው ፣ ብርና ፣ ወርቅ ፣ ጋር ፣ እነዚህን ፣ ደግሞ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ቀደሰ ።

፲፫ ዳዊትም ፣ በተመለሰ ፣ ጊዜ ፣ ከኤዶምያስ ፣ አሥራ ፣ ስምንት ፣ ሺህ ፣ ሰዎች ፣ በጨው ፣ ሸለቆ ፣ ውስጥ ፣ በመምታቱ ፣ ስሙ ፣ ተጠራ ።

፲፬ በኤዶምያስ ፣ ሁሉ ፣ ጭፍሮች ፣ አኖረ ÷ ኤዶማውያንም ፣ ሁሉ ፣ ለዳዊት ፣ ገባሮች ፣ ሆኑ ፣ እግዚአብሔርም ፣ ዳዊት ፣ በሚሄድበት ፣ ሁሉ ፣ ድልን ፣ ሰጠው ።

፲፭ ዳዊትም ፣ በእስራኤል ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣ ነገሠ ፤ ዳዊትም ፣ ለሕዝቡ ፣ ሁሉ ፣ ፍርድንና ፣ ጽድቅን ፣ አደረገላቸው ።

፲፮ የጽሩያ ፣ ልጅ ፣ ኢዮአብም ፣ የሠራዊት ፣ አለቃ ፣ ነበረ ፣ የአሒሉድም ፣ ልጅ ፣ ኢዮሣፍጥ ፣ ታሪከ ፣ ጸሐፊ ፣ ነበረ ፣

፲፯ የአኪጡብም ፣ ልጅ ፣ ሳዶቅ ÷ የአቢሜሌክም ፣ ልጅ ፣ አብያታር ፣ ካህናት ፣ ነበሩ ፣ ሠራያም ፣ ጸሐፊ ፣ ነበረ ፣

፲፰ የዮዳሄ ፣ ልጅ ፣ በናያስ ፣ በከሊታውያንና ፣ በፈሊታውያን ፣ ላይ ፣ ነበረ ፣ የዳዊትም ፣ ልጆች ፣ አማካሪዎች ፣ ነበሩ ።

ምዕራፍ ፱ ።

፩ ዳዊትም ፦ ስለ ፥ ዮናታን ፣ ቸርነት ፣ አደር ግለት ፣ ዘንድ ፣ ከሳኦል ፣ ቤት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ቀርቶአልን ? አለ ። ከሳኦልም ፣ ቤት ፣ ሲባ ፣ የሚባል ፣ አንድ ፣ ባሪያ ፣ ነበረ ÷ ወደ ፣ ዳዊትም ፣ ጠሩት ፤ ንጉሡም ፦ አንተ ፣ ሲባ ፣ ነህን ? አለው ። እርሱም ፦ አኔ ፣ ባሪያህ ፣ ነኝ ፣ አለ ።

፫ ንጉሡም ፦ የእግዚአብሔርን ፣ ቸርነት ፣ አደርግለት ፣ ዘንድ ፣ ከሳኦል ፣ ቤት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ አልቀረምን ? አለ ። ሲባም ፣ ንጉሡን ፦ እግሩ ፣ ሽባ ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ የዮናታን ፣ ልጅ ፣ አለ ፣ አለው ። ንጉሡም ፦ ወዴት ፣ ነው ? አለው ፣ ሲባም ፣ ንጉሡን ፦ እነሆ ፣ እርሱ ፣ በሎዶባር ፣ በዓሚኤል ፣ ልጅ ፣ በማኪር ፣ ቤት ፣ አለ ፣ አለው ።

፭ ንጉሡም ፣ ዳዊት ፣ ልከ ፣ ከሎዶባር ፣ ከዓሚኤል ፣ ልጅ ፣ ከማኪር ፣ ቤት ፣ አስመጣው ። የሳኦልም ፣ ልጅ ፣ የዮናታን ፣ ልጅ ፣ ሜምፊቦስቴ ፣ ወደ ፣ ዳዊት ፣ መጣ ÷ በግምባሩም ፣ ወድቆ ፣ እጅ ፣ ነሣ ። ዳዊትም ፦ ሜምፊቦስቴ ፣ ሆይ ÷ አለ ፣ እርሱም ፣ እነሆኝ ፣ ባሪያህ ፣ አለ ። ዳዊትም ፦ ስለ ፣ አባትህ ፣ ስለ ፣ ዮናታን ፣ ቸርነት ፣ ፈጽሜ ፣ አደርግልሃለሁና ፣ አትፍራ ፤ የአባትህንም ፣ የሳኦልን ፣ ምድር ፣ ሁሉ ፣ እመልስልሃለሁ ÷ አንተም ፣ ሁልጊዜ ፣ ከገበታዬ ፣ እንጀራ ፣ ትበላለህ ፣ አለው ። እርሱም ፦ የሞተ ፣ ውሻ ፣ ወደምመስል ፣ ወደ ፣ እኔ ፣ የተመለከትህ ፣ እኔ ፣ ባሪያህ ፣ ምንድር ፣ ነኝ ? ብሎ ፣ እጅ ፣ ነሣ ።

፱ ንጉሡም ፣ የሳኦልን ፣ ባሪያ ፣ ሲባን ፣ ጠርቶ ፦ ለሳኦልና ፣ ለቤቱ ፣ ሁሉ ፣ የነበረውን ፣ ሁሉ ፣ ለጌታህ ፣ ልጅ ፣ ሰጥቻለሁ ። አንተና ፣ ልጆችህ ፣ ሎሌዎችህም ፣ ምድሩን ፣ እረሱለት ፣ ለጌታህም ፣ ልጅ ፣ እንጀራ ፣ ይሆነው ፣ ዘንድ ፣ ፍሬውን ፣ አግባ ፣ የጌታህ ፣ ልጅ ፣ ሜምፊቦስቴ ፣ ግን ፣ ሁልጊዜ ፣ ከገበታዬ ፣ ይበላል ፣ አለው ። ለሲባም ፣ አሥራ ፣ አምስት ፣ ልጆችና ፣ ሀያ ፣ ባሪያዎች ፣ ነበሩት ። ሲባም ፣ ንጉሡን ፦ ጌታዬ ፣ ንጉሡ ፣ ባሪያውን ፣ እንዳዘዘ ፣ እንዲሁ ፣ ባሪያህ ፣ ያደርጋል ፣ አለው ። ሜምፊቦስቴም ፣ ከንጉሡ ፣ ልጆች ፣ እንደ ፣ አንዱ ፣ ከዳዊት ፣ ገበታ ፣ ይበላ ፣ ነበር ። ለሚምፊቦስቴም ፣ ሚካ ፣ የተባለ ፣ ታናሽ ፣ ልጅ ፣ ነበረው ። በሲባም ፣ ቤት ፣ ያሉ ፣ ሁሉ ፣ ለሚምፊቦስቴ ፣ ያገለግሉ ፣ ነበር ። ሜምፊቦስቴም ፣ ከንጉሥ ፣ ገበታ ፣ ሁልጊዜ ፣ እየበላ ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ተቀምጦ ፣ ነበር ፤ ሁለት ፣ እግሩም ፣ ሽባ ፣ ነበረ ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የአሞን ፣ ልጆች ፣ ንጉሥ ፣ ሞተ ÷ ልጁም ፣ ሐኖን ፣ በፋንታው ፣ ነገሠ ።

፪ ዳዊትም ፦ አባቱ ፣ ወረታ ፣ እንዳደረገልኝ ፣ እኔ ፣ ለናያስ ፣ ልጅ ፣ ለሐኖን ፣ ቸርነት ፣ አደርጋለሁ ፣ አለ ። ዳዊትም ፣ አባቱ ፣ ስለ ፣ ሞተ ፣ ሊያጽናናው ፣ ባሪያዎቹን ፣ ላከ ፤ የዳዊትም ፣ ባሪያዎች ፣ ወደ ፣ አሞን ፣ ልጆች ፣ አገር ፣ መጡ ።

፫ የአሞንም ፣ ልጆች ፣ አለቆች ፣ ጌታቸውን ፣ ሐኖንን ፦ ዳዊት ፣ አባትህን ፣ አክብሮ ፣ ሊያጽናናህ ፣ ባሪያዎቹን ፣ ወደ ፣ አንተ ፣ የላከ ፣ ይመስልሃልን ? ዳዊትስ ፣ ከተማይቱን ፣ ለመመርመር ፣ ለመሰለል ፣ ለማጥፋትም ፣ ባሪያዎቹን ፣ የላከ ፣ አይደለምን ? አሉት ። ሐኖንም ፣ የዳዊትን ፣ ባሪያዎች ፣ ወስዶ ፣ የጢማቸውን ፣ ግሚስ ፣ ላጨ ÷ ልብሳቸውንም ፣ እስከ ፣ ወገባቸው ፣ ድረስ ፣ ከሁለት ፣ ቀድዶ ፣ ሰደዳቸው ።

፭ ዳዊትም ፣ ይህን ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ሰዎቹ ፣ እጅግ ፣ አፍረው ፣ ነበሩና ፣ ተቀባዮች ፣ ላከ ። ንጉሡም ፦ ጢማችሁ ፣ እስኪያድግ ፣ ድረስ ፣ በኢያሪኮ ፣ ተቀመጡ ÷ ከዚያም ፣ በኋላ ፣ ተመለሱ ፣ አላቸው ።

፮ የአሞን ፣ ልጆች ፣ በዳዊት ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ ተጠሉ ፣ ባዩ ፣ ጊዜ ÷ የአሞን ፣ ልጆች ፣ ልከው ፣ ከሶርያውያን ፣ ከቤትሮዖብና ፣ ከሱባ ፣ ሀያ ፣ ሺህ ፣ እግረኞች ÷ ከመኅካ ፣ ንጉሥም ፣ አንድ ፣ ሺህ ፣ ሰዎች ÷ ከጦብም ፣ አሥራ ፣ ሁለት ፣ ሺህ ፣ ሰዎች ፣ ቀጠሩ ። ዳዊትም ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ኢዮአብንና ፣ የኃያላኑን ፣ ሠራዊት ፣ ሁሉ ፣ ላከ ።

፰ የአሞንም ፣ ልጆች ፣ ወጥተው ፣ በበሩ ፣ መግቢያ ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ ተሰለፉ ፤ የሱባና ፣ የረአብ ፣ ሶርያውያን ÷ የጦብና ፣ የመዓከም ፣ ሰዎች ፣ ለብቻቸው ፣ በሰፊ ፣ ሜዳ ፣ ላይ ፣ ነበሩ ።

፱ ኢዮአብም ፣ በፊትና ፣ በኋላ ፣ ሰልፍ ፣ እንደ ፣ ከበበው ፣ ባየ ፣ ጊዜ ፣ ከእስራኤል ፣ ምርጥ ፣ ምርጡን ፣ ሁሉ ፣ መረጠ ÷ በሶርያውያንም ፣ ፊት ፣ ለሰልፍ ፣ አሰራቸው ።

፲ የቀረውንም ፣ ሕዝብ ፣ በወንድሙ ፣ በአቢሳ ፣ እጅ ፣ አድርጎ ፣ በአሞን ፣ ልጆች ፣ ፊት ፣ ለሰልፍ ፣ አሰራቸው ።

፲፩ ሶርያውያን ፣ ቢበረቱብኝ ፣ ትረዳኛለህ ፣ የአሞን ፣ ልጆች ፣ ቢበረቱብህ ፣ እኔ ፣ መጥቼ ፣ እረዳሃለሁ ።

፲፪ አይዞህ ፣ ስለ ፣ ሕዝባችንና ፣ ስለ ፣ አምላክችንም ፣ ከተሞች ፣ እንበርታ ፤ እግዚአብሔርም ፣ ደስ ፣ ያሰኘውን ፣ ያድርግ ፣ አለ ።

፲፫ ኢዮአብና ፣ ከእርሱም ፣ ጋር ፣ የነበረው ፣ ሕዝብ ፣ ከሶርያውያን ፣ ጋር ፣ ሊዋጉ ፣ ቀረቡ ÷ እነርሱም ፣ ከፊቱ ፣ ሸሹ ።

፲፬ የአሞንም ፣ ልጆች ፣ ሶርያውያን ፣ እንደ ፣ ሸሹ ፣ ባዩ ፣ ጊዜ ፣ እነርሱ ፣ ደግሞ ፣ ከአቢሳ ፣ ፊት ፣ ሸሹ ÷ ወደ ፣ ከተማይቱም ፣ ገቡ ፤ ኢዮአብም ፣ ከአሞን ፣ ልጆች ፣ ተመልሶ ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ መጣ ።

፲፭ ሶርያውያንም ፣ በእስራኤል ፣ ፊት ፣ እንደ ፣ ተሸነፉ ፣ ባዩ ፣ ጊዜ ፣ በአንድነት ፣ ተሰበሰቡ ።

፲፮ አድርአዛርም ፣ ልኮ ፣ በወንዝ ፣ ማዶ ፣ የነበሩትን ፣ ሶርያውያን ፣ አመጣ ፤ ወደ ፣ ኤላምም ፣ መጡ ÷ የአድርአዛርም ፣ ሠራዊት ፣ አለቃ ፣ ሶባክ ፣ በፊታቸው ፣ ነበረ ።

፲፯ ዳዊትም ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ እስራኤልን ፣ ሁሉ ፣ ሰበሰበ ፤ ዮርዳኖስንም ፣ ተሻግሮ ፣ ወደ ፣ ኤላም ፣ መጣ ፤ ሶርያውያንም ፣ በዳዊት ፣ ፊት ፣ ተሰልፈው ፣ ከእርሱ ፣ ጋር ፣ ተዋጉ ።

፲፰ ሶርያውያንም ፣ ከእስራኤል ፣ ፊት ፣ ሸሹ ፤ ዳዊትም ፣ ከሶርያውያን ፣ ሰባት ፣ መቶ ፣ ሰረገለኞች ፣ አርባ ፣ ሺህም ፣ ፈረሰኞች ፣ ገደለ ፤ የሠራዊቱንም ፣ አለቃ ፣ ሶባክን ፣ መታ ÷ እርሱም ፣ በዚያው ፣ ሞተ ።

፲፱ ለአድርአዛርም ፣ የሚገብሩ ፣ ነገሥታት ፣ ሁሉ ፣ በእስራኤል ፣ ፊት ፣ እንደ ፣ ተሸነፉ ፣ ባዩ ፣ ጊዜ ፣ ከእስራኤል ፣ ጋር ፣ ታረቁ ÷ ገበሩላቸውም ። ሶርያውያንም ፣ ከዚያ ፣ ወዲያ ፣ የአሞንን ፣ ልጆች ፣ ይረዱ ፣ ዘንድ ፣ ፈሩ ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ እንዲህም ፣ ሆነ ፣ በዓመቱ ፣ መልወጫ ፣ ነገሥታት ፣ ወደ ፣ ሰልፍ ፣ በሚወጡበት ፣ ጊዜ ÷ ዳዊት ፣ ኢዮአብን ፣ ከእርሱም ፣ ጋር ፣ ባሪያዎቹን ፣ እስራኤልንም ፣ ሁሉ ፣ ሰደደ ። የአሞንንም ፣ ልጆች ፣ አጠፉ ÷ ረባትንም ፣ ከበቡ ፣ ዳዊት ፣ ግን ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ቀርቶ ፣ ነበር ።

፪ እንዲህም ፣ ሆነ ፣ ወደ ፣ ማታ ፣ ጊዜ ፣ ዳዊት ፣ ከምንጣፉ ፣ ተነሣ ÷ በንጉሥም ፣ ቤት ፣ በሰገነት ፣ ላይ ፣ ተመላለሰ ፣ በሰገነቱ ፣ ሳለ ፣ አንዲት ፣ ሴት ፣ ስትታጠብ ፣ አየ ፣ ሴቲቱም ፣ መልከ ፣ መልካም ፣ ነበረች ።

፫ ዳዊትም ፣ ልከ ፣ ስለ ፣ ሴቲቱ ፣ ጠየቀ ፣ አንድ ፣ ሰውም ፦ ይህች ፣ የኤልያብ ፣ ልጅ ፣ የኬጢያዊው ፣ የኦርዮ ፣ ሚስት ፣ ቤርሳቤህ ፣ አይደለችምን ? አለ ። ዳዊትም ፣ መልእክተኞች ፣ ልከ ፣ አስመጣት ፣ ወደ ፣ እርሱም ፣ ገባች ÷ ከርሱንም ፣ ተኛ ፣ ወደ ፣ ቤትዋም ፣ ተመለሰች ።

፭ ሴቲቱም ፣ አረገዘች ÷ ወደ ፣ ዳዊትም ፦ እርግዝ አለሁ ፣ ብላ ፣ ላከችበት ።

፮ ዳዊትም ፣ ወደ ፣ ኢዮአብ ፦ ኬጢያዊውን ፣ አርዮን ፣ ስደድልኝ ፣ ብሎ ፣ ላከ ። ኢዮአብም ፣ አርዮን ፣ ወደ ፣ ዳዊት ፣ ሰደደው ።

፯ አርዮም ፣ ወደ ፣ እርሱ ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ዳዊት ፣ የኢዮአብንና ፣ የሕዝቡን ፣ ደኅንነት ÷ ሰልፉም ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ጠየቀው ።

፰ ዳዊትም ፣ አርዮን ፦ ወደ ፣ ቤትህ ፣ ሂድ ÷ እግርህንም ፣ ታጠብ ፣ አለው ። አርዮም ፣ ከንጉሡ ፣ ቤት ፣ ሲወጣ ፣ ማለፊያ ፣ የንጉሥ ፣ መብል ፣ ተከትሎት ፣ ሄደ ።

፱ አርዮ ፣ ግን ፣ ከጌታው ፣ ባሪያዎች ፣ ሁሉ ፣ ጋር ፣ በንጉሥ ፣ ቤት ፣ ደጅ ፣ ተኛ ፣ ወደ ፣ ቤቱም ፣ አልወረደም ።

፲ አርዮ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ አልሄደም ፣ ብለው ፣ ለዳዊት ፣ ነገሩት ፣ ዳዊትም ፣ አርዮን ፦ አንተ ፣ ከመንገድ ፣ የመጣህ ፣ አይደለምን ? ስለ ፣

ምን ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አልወረድህም ? አለው ።
፲፩ አርዮም ፡ ዳዊትን ፡— ታቦቱና ፡ እስራኤል ፡ ይሁዳም ፡ በጎጆ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ጌታዬ ፡ ኢዮአብና ፡ የጌታዬም ፡ ባሪያዎች ፡ በሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ሰፍረዋል ፤ እኔ ፡ ልበላና ፡ ልጠጣ ፡ ወይስ ፡ ከሚስቴ ፡ ጋር ፡ ልተኛ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ እሄዳለሁን ? በሕይወትህና ፡ በሕያው ፡ ነፍስህ ፡ እምላለሁ ፤ ይህን ፡
፲፪ ነገር ፡ አላደርገውም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አርዮን ፡— ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፡ ነገም ፡ አሰናብትሃለሁ ፡ አለው ። አርዮም ፡ በዚያ ፡ ቀንና ፡ በነጋውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ።
፲፫ ዳዊትም ፡ ጠራው ፡ በፊቱም ፡ በላና ፡ ጠጣ ፡ አሰከረውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡ ከጌታው ፡ ባሪያዎች ፡ ጋር ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አልወረደም ።
፲፬ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ለኢዮአብ ፡ ደብዳቤ ፡
፲፭ ጻፈ ፡ በአርዮም ፡ እጅ ፡ ላከው ። በደብዳቤውም ፡— አርዮን ፡ ጽኑ ፡ ሰልፍ ፡ ባለበት ፡ በፊተኛው ፡ ስፍራ ፡ አቁሙት ፡ ተመትቶም ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ከኋላው ፡ ሽሹ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ።
፲፮ ኢዮአብም ፡ ከተማይቱን ፡ በከበበ ፡ ጊዜ ፡ ጀግኖች ፡ እንዳሉበት ፡ በሚያውቀው ፡ ስፍራ ፡ አርዮን ፡ አቆመው ። የከተማይቱም ፡ ሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ከኢዮአብ ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ፡ ከዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ከሕዝቡ ፡ አንዳንዱ ፡ ወደቁ ፡ ኬጢያዊው ፡ አርዮም ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ።
፲፯ ኢዮአብም ፡ ከተማይቱን ፡ ሲከባ ፡ ልከ ፡ በሰልፍ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።
፲፱ ለመልእክተኛውም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡— የሰልፉን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ነግረህ ፡ በፈጸምህ ፡ ጊዜ ፡— ስትዋጉ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ለምን ፡ ቀረባችሁ ? ከቅጥሩ ፡ በላይ ፡
፳፩ ፍላጻ ፡ እንዲወረወር ፡ አታውቁምን ? የሩቤሼትን ፡ ልጅ ፡ አቤሜሌክን ፡ ማን ፡ ገደለው ? ከቅጥር ፡ ላይ ፡ የወፍጮ ፡ መጅ ፡ ጥላ ፡ በቴቤስ ፡ ላይ ፡ የገደለችው ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አይደለች ፡ ምን ? ስለ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ እንደዚህ ፡ ቀረባችሁ ? ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ ሲቈጣ ፡ ብታይ ፡ አንተ ፡— በሪያህ ፡ ኬጢያዊው ፡ አርዮ ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ፡ በለው ።
፳፪ መልእክተኛውም ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ፡ ኢዮአብም ፡ ያዘዘውን ፡ ሁሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።
፳፫ መልእክተኛውም ፡ ዳዊትን ፡— ሰዎቹ ፡ በረቱብን ፡ ወደ ፡ ሜዳም ፡ ወጡብን ፡ እኛም ፡ ወደቅንባቸው ፡ እስከ ፡ ከተማይቱም ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ተከተልናቸው ።
፳፬ ፍላጻ ፡ የሚወረውሩም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በባሪያዎችህ ፡ ላይ ፡ ወረወሩ ፡ ከንጉሡም ፡ በሪያዎች ፡ አንዳንድ ፡ ሞቱ ፡ ኬጢያዊው ፡ አርዮ ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ፡ አለው ።
፳፭ ዳዊትም ፡ መልእክተኛውን ፡— ሰይፍ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ያን ፡ ያጠፋልና ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በዓይንህ ፡ አይክፋ ፡ ከተማይቱን ፡ የሚወጉትን ፡ አበርታ ፡ አፍርሰትም ፡ ብለህ ፡ ለኢዮአብ ፡ ንገረው ፡ አንተም ፡ አድናው ፡ አለው ።
፳፮ የአርዮም ፡ ሚስት ፡ ባልዋ ፡ አርዮ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ለባልዋ ፡ አለቀሰች ።
፳፯ የልቀሰዋም ፡ ወራት ፡ ሲፈጸም ፡ ዳዊት ፡ ልከ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አስመጣት ፡ ሚስትም ፡ ሆነችው ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደችለት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፋ ፡ ሆነ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

እግዚአብሔርም ፡ ናታንን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ላከ ፡
፩ ወደ ፡ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ አለው ፡— በአንድ ፡ ከተማ ፡ አንዱ ፡ ባለጠጋ ፡ አንዱም ፡ ድሀ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።
፪ ባለጠጋውም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ በግና ፡ ላም ፡ ነበረው ።
፫ ለድሀው ፡ ግን ፡ ከገዛት ፡ አንዲት ፡ ታናሽ ፡ በግ ፡ በቀር ፡ አንዳች ፡ አልነበረውም ፡ አሳደጋትም ፡ ከልጆቹም ፡ ጋር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደገች ። እንጀራውንም ፡ ትበላ ፡ ከዋንጫውም ፡ ትጠጣ ፡ በብብቱም ፡ ትተኛ ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ልጁም ፡ ነበረች ።
፬ ወደ ፡ በሰጠጋውም ፡ እንግዳ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከበጉና ፡ ከላሙ ፡ ወስዶ ፡ ለዚያ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ለመጣው ፡ እንግዳ ፡ ያዘጋጅለት ፡ ዘንድ ፡ ሳሳ ፡ የዚያንም ፡ የድሀውን ፡ ሰው ፡ በግ ፡ ወስዶ ፡ ለዚያ ፡ ለመጣው ፡ ሰው ፡ አዘጋጀ ።
፭ ዳዊትም ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ናታንን ፡— ሕያው ፡ እግዚአብሔር ! ይህን ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ የሞት ፡ ልጅ ፡ ነው ። ይህን ፡ አድርጎአልና ፡ አላዘነምና ፡
፮ ስለ ፡ አንዲቱ ፡ በግ ፡ አራት ፡ ይመልስ ፡ አለው ።
፯ ናታንም ፡ ዳዊትን ፡ አለው ፡— ያ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነህ ። የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ልትሆን ፡ ቀባሁህ ፡ ከሳኦልም ፡ እጅ ፡
፰ አዳንሁህ ፤ የጌታህንም ፡ ቤት ፡ ሰጠሁህ ፡ የጌታህንም ፡ ሚስቶች ፡ በብብትህ ፡ ጣልሁልህ ፡ የእስራኤልንና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ ሰጠሁህ ፡ ይህም ፡ አንሶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ እጨምርልህ ፡ ነበር ።
፱ እሁንስ ፡ በፊቱ ፡ ክፉ ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ አቃለልህ ? ኬጢያዊውን ፡ አርዮን ፡ በሰይፍ ፡ መትተሃል ፡ ሚስቱንም ፡ ለአንተ ፡ ሚስት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ወስደሃል ፡ አርሱንም ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡ ሰይፍ ፡ ገድለሃል ።
፲ ስለዚህም ፡ አቃልለኸኝልና ፡ የኬጢያዊውንም ፡ የአርዮን ፡ ሚስት ፡ ለአንተ ፡ ሚስት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ወስደሃል ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ፡ ከቤትህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አስነሣብሃለሁ ፡ ሚስቶችህንም ፡ በዓይንህ ፡ ፊት ፡ እወስዳለሁ ፡ ለዘመድህም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ በዚህችም ፡ ፀሐይ ፡ ዓይን ፡ ፊት ፡ ከሚስቶችህ ፡ ጋር ፡ ይተኛል ።
፲፩ አንተ ፡ ይህን ፡ በስውር ፡ አድርገኸዋል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፊትና ፡ በፀሐይ ፡ ፊት ፡ አደርገዋለሁ ።
፲፪ ዳዊትም ፡ ናታንን ፡— እግዚአብሔርን ፡ በድያለሁ ፡ አለው ።
ናታንም ፡ ዳዊትን ፡— እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ ኃጢአትህን ፡ አርቆልሃል ፤ አትሞትም ።
፲፫ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ታላቅ ፡ የስድብ ፡ ምክንያት ፡ አድርገሃልና ፡ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ የተወለደልህ ፡ ልጅ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፡ አለው ።
፲፬ ናታንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።
እግዚአብሔርም ፡ የአርዮ ፡ ሚስት ፡ ለዳዊት ፡ የወለደችውን ፡ ሕፃን ፡ ቀሠፈ ፡ እጅግም ፡
፲፭ ታምሞ ፡ ነበር ። ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፤ ዳዊትም ፡ ጾመ ፡ ገብቶም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተኛ ።
፲፮ የቤቱም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተነሥተው ፡ ከምድር ፡ ያነሡት ፡ ዘንድ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሙ ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ።
፲፯ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕፃኑ ፡ ሞተ ። የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡— ሕፃኑ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ብንነግረው ፡ አልሰማንም ፤ ይልቁንስ ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ብንነግረው ፡ እንዴት ፡ ይሆን ? በነፍሱ ፡ ክፉ ፡ ያደርጋል ፡ ብለው ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ይነግሩት ፡
፲፰ ዘንድ ፡ ፈሩ ። ዳዊትም ፡ ባሪያዎቹ ፡ በሹክሹክታ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አወቀ ፡ ዳዊትም ፡ ባሪያዎቹን ፡— ሕፃኑ ፡ ሞቶአል ? አላቸው ። እነርሱም ፡— ሞቶአል ፡ አሉት ።
፲፱ ዳዊትም ፡ ከምድር ፡ ተነሥቶ ፡ ታጠበ ፡ ተቀባም ፡ ልብሱንም ፡ ለወጠ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሰገደ ። ወደ ፡ ቤቱም ፡ መጣ ፡— እንጀራ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፡
፳ በፊቱም ፡ አቀረቡለት ፡ በላም ። በሪያዎቹም ፡— ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ? በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡ ጾመህና ፡ አለቀስህ ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተነሥተህ ፡ እንጀራ ፡ በላህ ፡
፳፩ አሉት ። እርሱም ፡— ሕፃኑ ፡ ሕያው ፡ ሳለ ፡— እግዚአብሔር ፡ ይምረኝ ፡ ሕፃኑም ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ? ብዬ ፡
፳፪ ጾሙ ፡ አለቀስሁም ። አሁን ፡ ግን ፡ ሞቶአል ፡ የምጾመው ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? በውኑ ፡ እንግዲህ ፡ እመልሰው ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኛልን ? እኔ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እሄዳለሁ ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አይመለስም ፡ አለ ።
፳፫ ዳዊትም ፡ ሚስቱን ፡ ቤርሳቤህን ፡ አጽናናት ፡ ወደ ፡ እርስዋም ፡ ገባ ፡ ከእርስዋም ፡ ጋር ፡ ተኛ ፤ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ፡ ስሙንም ፡ ሰሎሞን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። እግዚአብሔርም ፡ ወደደው ፤
፳፬ ደግሞም ፡ በነቢዩ ፡ በናታን ፡ እጅ ፡ ልክ ፡ ስሙን ፡ ሰለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይዲድያ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።
፳፭ ኢዮአብም ፡ የአሞንን ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ ረባትን ፡ ወጋ ፡ የውኃውንም ፡ ከተማ ፡ ያዘ ።
፳፮ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡— ረባትን ፡ ወግቻለሁ ፡ የውኃውንም ፡ ከተማ ፡ ይገርአለሁ ።
፳፯ አሁንም ፡ ከተማይቱን ፡ እንዳልይዝ ፡ በስሜም ፡ እንዳት ፡ ጠራ ፡ የቀረውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰብስብ ፡ ከተማይቱንም ፡ ክብበህ ፡ ያዝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።
፳፰ ዳዊትም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ረባት ፡ ሄደ ፡ ወግቶም ፡ ያዛት ።
፳፱ የንጉሣቸውንም ፡ ዘውድ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ወሰደ ። ክብደቱም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ያህል ፡ ነበር ፡ ክቡር ፡ ዕንቍም ፡ ነበረበት ፡ ዳዊትም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አደረገው ።
፴ ከከተማይቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አወጣ ።
፴፩ በውስጥዋም ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ አውጥቶ ፡ በመጋዝና ፡ በብረት ፡ መቄፈሪያና ፡ በብረት ፡ መጥረቢያ ፡ እንዲሠሩ ፡ አደረጋቸው ፤ የሸክላ ፡ ጡብም ፡ እንዲያቃጥሉ ፡ አደረጋቸው ። በአሞን ፡ ልጆች ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ።
፴፪ ዳዊትም ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ለዳዊት ፡
፩ ልጅ ፡ ለአቤሴሎም ፡ አንዲት ፡ የተዋበች ፡ እኅት ፡ ነበረችው ። ስምዋም ፡ ትዕማር ፡ ነበረ ፤ የዳዊትም ፡ ልጅ ፡ አምኖን ፡ ወደዳት ።
፪ አምኖንም ፡ ከእኅቱ ፡ ከትዕማር ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ተከዘ ፡ ታመመ ። ድንግልም ፡ ነበረችና ፡ እንዳች ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፡ በዓይኑ ፡ ፊት ፡ ጭንቅ ፡ ሆኖበት ፡ ነበር ።
፫ ለአምኖንም ፡ የዳዊት ፡ ወንድም ፡ የሰምዓ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ የሚባል ፡ ወዳጅ ፡ ነበረው ። ኢዮናዳብም ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።
፬ እርሱም ፡— የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ በቀን ፡ እንዲህ ፡ ከሳህ ? አትነግረኝምን ? አለው ። አምኖንም ፡— የወንድሜን ፡ የአቤሴሎምን ፡ እኅት ፡ ትዕማርን ፡ እወድ ፡ ዘንድ ፡ አለው ።
፭ ኢዮናዳብም ፡— ታምመኢአ ፡ ለሁ ፡ ብለህ ፡ በአልጋህ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፤ አባትህም ፡ ሊያይህ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡— እኅቴ ፡ ትዕማር ፡ እንድትመጣና ፡ እኔ ፡ የምበላውን ፡ እንጀራ ፡ እንድትሰጠኝ ፡ መብትንም ፡ እኔ ፡ እያየሁ ፡ እንድታዘጋጅልኝ ፡ ከእጅዋም ፡ እንድበላው ፡ አስ ፡ ምንሃለሁ ፡ በል ፡ አለው ።
፮ እንዲሁም ፡ አምኖን ፡— ታምመኢአ ፡ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ተኛ ፤ ንጉሡም ፡ ሊያየው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡— አምኖን ፡ ንጉሡን ፡— እኅቴ ፡ ትዕማር ፡ እንድትመጣና ፡ እኔ ፡ እያየሁ ፡ ሁለት ፡ እንጐቻ ፡ እንድታደርግልኝ ፡ ከእጅዋም ፡ እንድበላ ፡ አስምንሃለሁ ፡ አለው ።
፯ ዳዊትም ፡— መብልን ፡ ታዘጋጂለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወንድምሽ ፡ ወደ ፡ አምኖን ፡ ቤት ፡ ሂጂ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ወደ ፡ ትዕማር ፡ ቤት ፡ ላከ ።
፰ ትዕማርም ፡ ወደ ፡ ወንድምዋ ፡ ወደ ፡ አምኖን ፡ ቤት ፡ ሄደች ። ተኝቶም ፡ ነበር ፤ ዱቄትም ፡ ወስዳ ፡ ለመሰች ፡ አያየም ፡ እንጐቻ ፡ አደረገች ፡ ገነፈችም ።
፱ ምጣዱንም ፡ ወስዳ ፡ በፊቱ ፡ ገለበጠች ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ።
አምኖም ፡ ሁሉ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አስወጡ ፡ አለ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።
፲ አምኖንም ፡ ትዕማርን ፡— ከእጅሽ ፡ እበላ ፡ ዘንድ ፡ መብሉን ፡ ወደ ፡ እልፍኙ ፡ አግቢው ፡ አላት ፤ ትዕማርም ፡ የሠራችውን ፡ እንጐቻ ፡ ወስዳ ፡ ወንድምዋ ፡

አምኖን ፡ ወዳለበት ፡ አልፍኘ ፡ አገባችው ። ፲፭ መብሉንም ፡ ባቀረበች ፡ ጊዜ ፡ ያዘችኅና ፡— እኅቴ፡ ፲፮ ሆይ ፡ ኑዪ ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ተኚ ፡ አላት ። እርስዋ ፡ መልሳ ፡— ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ አይሆንም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አይገባምና ፡ አታሳፍረኝ ፡ ይህንም ፡ ነውረኛ ፡ ሥራ ፡ ፲፯ አታድርግ ። እኔም ፡ ነውሬን ፡ ወዴት ፡ ልሸከም ? አንተም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከምና ምንቴዎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ትሆናለህ ፡ እንግዲህስ ፡ ለንጉሡ ፡ ንገረው ፡ ። እኔንም ፡ ፲፰ ሆም ፡ አልችው ። ቃልዋን ፡ ግን ፡ አልሰማም ፡ ከእርስዋም ፡ ይልቅ ፡ ብርቱ ፡ ነበረና ፡ በግድ ፡ አስነወራት ። ከእርስዋም ፡ ጋር ፡ ተኛ ።

፲፱ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አምኖን ፡ ፈጽሞ ፡ ጠላት ፡ አስቀድሞም ፡ ከወደዳት ፡ ውድ ፡ ይልቅ ፡ በኋላ ፡ የጠላት ፡ ጥል ፡ በለጠ ። አምኖንም ፡— ተነሥ ፡ ፳ ተሽ ፡ ሂጂ ፡ አላት ። እርስዋም ፡— አይሆንም ፡ ቀድሞ ፡ ከሠራኸው ፡ ክፋት ፡ ይልቅ ፡ እኔን ፡ በማውጣትህ ፡ የበለጠ ፡ ክፋት ፡ ትሠራለህ ፡ ፳፩ አለችው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማትም ። የሚያገለግለውንም ፡ ብላቴና ፡ ጠርቶ ፡— ይህችን ፡ ሴት ፡ ከፊቴ ፡ አስወጥተህ ፡ በሩን ፡ ዝጋባት ፡ ፳፪ አለው ። ብዙ ፡ ኀብር ፡ ያለውንም ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ልብስ ፡ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ደናግሎች ፡ ይለብሱ ፡ ነበርና ። አገልጋዩም ፡ አስወጥቶ ፡ በሩን ፡ ዘጋባት ። ፳፫ ትሰማርም ፡ በራስዋ ፡ ላይ ፡ አመድ ፡ ነስንሳ ፡ ብዙ ፡ ኀብርም ፡ ያለውን ፡ ልብስዋን ፡ ተርትራ ፡ እጅዋንም ፡ በራስዋ ፡ ላይ ፡ ጭና ፡ እየጮኸች ፡ ሄደች ።

፳ ወንድምዋም ፡ አቤሴሎም ፡— ወንድምሽ ፡ አምኖን ፡ ከእንቺ ፡ ጋር ፡ ነበረን ? አኅቴ ፡ ሆይ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ዝም ፡ በዪ ፡ ወንድምሽ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በልብሽ ፡ አትያዢው ፡ አላት ። ትዕማርም ፡ በወንድምዋ ፡ በአቤሴሎም ፡ ቤት ፡ ፳፩ ብቸዋን ፡ ተቀመጠች ። ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ አምኖን ፡ ስለ ፡ ወደደው ፡ የልጁን ፡ የእምኖን ፡ ነፍስ ፡ አላሳዘነም ። ፳፪ አቤሴሎምም ፡ እኅቱን ፡ ትዕማርን ፡ ስላሳፈራት ፡ አምኖንን ፡ ጠልቶታልና ፡ አቤሴሎም ፡ አምኖንን ፡ ክፉም ፡ ሆነ ፡ መልካሙም ፡ አልተናገረውም ።

፳፫ ከሁለት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ በኤፍሬም ፡ አቅራቢያ ፡ ባለችው ፡ በዘላሶር ፡ በጎቹን ፡ አሸለተ ፡ አቤሴሎምም ፡ የንጉሡን ፡ ፳፬ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ። አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥቶ ፡— እነሆ ፡ ባሪያህ ፡ በጎቹን ፡ ያሸልታል ፡ ንጉሡና ፡ ሎሌዎቹ ፡ ከባሪያህ ፡ ፳፭ ጋር ፡ ይሂዱ ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ አቤሴሎምን ፡— ልጄ ፡ ሆይ ፡ እንኩብኖዝሃለንና ፡ ሁላችን ፡ እንመጣ ፡ ዘንድ ፡ አይሆንም ፡ አለው ። የግድም ፡ አለው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ መረቀው ። ፳፮ እንጂ ፡ ለመሄድ ፡ እንቢ ፡ አለ ። አቤሴሎምም ፡— አንተ ፡ እንቢ ፡ ካልህ ፡ ወንድሜ ፡ አምኖን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ እንዲሄድ ፡ አለምንሃለሁ ፡ አለ ። ንጉሡም ፡— ከእንተ ፡ ጋር ፡ ለምን ፡ ይሄዳል ? ፳፯ አለው ። አቤሴሎምም ፡ የግድ ፡ አለው ፡ ። አምኖንንና ፡ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሰደደ ። አቤሴሎምም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ፳፰ ግብዣ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፤ አቤሴሎምም ፡ አገልጋዮቹን ፡— አምኖን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጥቶ ፡ ልቡን ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እዩ ፡— አምኖንን ፡ ግደሉ ፡ ባልኋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ግደሉት ፡ አትፍሩም ፡ ያዘዝኋችሁም ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ በርቱ ፡ ጽኑም ፡ ብሉ ፡ አዘዛቸው ። የአቤሴሎምም ፡ ፳፱ አገልጋዮች ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ በአምኖን ፡ ላይ ፡ አደረጉበት ። የንጉሡም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ተነሥተው ፡ በየበቅሎቻቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ሸሹ ።

፴ ገና ፡ በመንገድ ፡ ሳሉ ፡ ለዳዊት ፡— አቤሴሎም ፡ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ገድሶአል ፡ ከእነርሱም ፡ አንድ ፡ አልቀረም ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ መጣለት ። ንጉሡም ፡ ተነሥቶ ፡ ልብሱን ፡ ፴፩ ቀደደ ። በምድር ፡ ላይም ፡ ወደቀ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ሁሉ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀድደው ፡ በእጠገቡ ፡ ቆሙ ። የዳዊትም ፡ ወንድም ፡ የሳምኅ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡— ጌታዬ ፡ ጕልማሶቹ ፡ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አያስብ ፡ እኅቱን ፡ ትዕማርን ፡ ብግድ ፡ ካስነወራት ፡ ጀምሮ ፡ በአቤሴሎም ፡ ዘንድ ፡ የተቈረጠ ፡ ነገር ፡ ነበረና ፡ ፴፪ የሞተ ፡ አምኖን ፡ ብቻ ፡ ነው ። አሁንም ፡ የሞተ ፡ አምኖን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ሞቱ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ አያኑር ፡ አለው ።

፴፫ አቤሴሎምም ፡ ኩበለለ ። ጕበኛውም ፡ ጕል ማሳ ፡ ዓይኑን ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ እነሆም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በኋላው ፡ በተራራው ፡ አጠገብ ፡ በመንገድ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ። ፴፬ ኢዮናዳብም ፡ ንጉሡ ፡— እነሆ ፡ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ መጥተዋል ፡ ባሪያህ ፡ እንዳለው ፡ እንዲሁ ፡ ሆነአል ፡ አለው ። ፴፭ ተናግሮም ፡ በዛኤረስ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ወዲያው ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ገቡ ። ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አለቀሱ ። ደግሞ ፡ ንጉሡና ፡ ባሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሱ ። ፴፮

አቤሴሎም ፡ ግን ፡ ኩበለሉ ፡ ወደ ፡ ጌሹር ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዓሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ተልማይ ፡ ሄደ ። ዳዊትም ፡ ሁልጊዜ ፡ ለልጁ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ። ፴፯ አቤሴሎም ፡ ኩብሉ ፡ ወደ ፡ ጌሹር ፡ ሄደ ፡ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተቀመጠ ። ፴፰ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ስለ ፡ አምኖን ፡ ሞት ፡ ተጽናንቶ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ናፈቀ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ የንጉሡ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳዘነበለ ፡ አወቀ ። ፪ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ቴቁሔ ፡ ልኮ ፡ ከዚያ ፡ ብልሃተኛ ፡ ሴት ፡ አስመጣና ፡— አልቅሺ ፡ የኀዘንም ፡ ልብስ ፡ ልበሺ ፡ ዘይትም ፡ አትቀቢ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ሰውም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንደምታለቅሺ ፡ ሁኚ ፫ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገብተሽ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ንገሪው ፡ አላት ፤ ኢዮአብም ፡ ቃሉን ፡ በአርስዋ ፡ አፍ ፡ አደረገ ።

፬ እንዲሁም ፡ የቴቁሔይቱ ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ገብታ ፡ በግምበርዋ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቀች ፡ እጅ ፡ ነሥታም ፡— ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አድነኝ ፡ ፭ አለች ። ንጉሡም ፡— ምን ፡ ሆነሽል ? አላት ። እርስዋም ፡ መልሳ ፡ አለች ፡— በእውነት ፡ እኔ ፡ ባሌ ፡ የሞተብኝ ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ ነኝ ። ፮ ለእኔም ፡ ለባሪያህ ፡ ሁለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩኝ ፡ በሜዳም ፡ ተጣሉ ፡ የሚገላግላቸውም ፡ አልነበረም ፡ አንዱም ፡ ሌላውን ፡ መትቶ ፡ ገደለው ። ፯ እነሆም ፡ ዘመዶች ፡ ሁሉ ፡ በባሪያህ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡— ስለ ፡ ገደለው ፡ ስለ ፡ ወንድሙ ፡ ነፍስ ፡ እንገድለው ፡ ዘንድ ፡ ወንድሙን ፡ የገደለውን ፡ አውጪ ፡ አሉኝ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ወራሹን ፡ የቀረውን ፡ መብራቴን ፡ ያጠፋሉ ፡ የባሌን ፡ ስምና ፡ ዘርም ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አያስ ቀሩም ።

፰ ንጉሡም ፡ ሴቲቱን ፡— ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ሂጂ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ አዝዛለሁ ፡ አላት ። ፱ ያቺቱ ፡ ሐይቱም ፡ ሴት ፡ ንጉሡን ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ኃጢአቱ ፡ በእኔና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ይሁን ፤ ንጉሡና ፡ ዙፋኑ ፡ ንጹሕ ፡ ይሁን ፡ አለችው ። ፲ ንጉሡም ፡— የሚናገርሽን ፡ አምጪልኝ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አይነካሽም ፡ አለ ። ፲፩ እርስዋም ፡— ደም ፡ ተበቃዮችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳያጠፉ ፡ ልጄንም ፡ እንዳይገድሉ ፡ ንገሡ ፡ አምላኩን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስብ ፡ አለች ። እርሱም ፡— ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ከልጅሽ ፡ አንድ ፡ ጠጕር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይወድቅም ፡ አለ ።

፲፪ ሴቲቱም ፡— እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፡ አለች ፤ እርሱም ፡— ተናገሪ ፡ አለ ። ፲፫ ሴቲቱም ፡ አለች ፡— በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሰብህ ? ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናግሮ ፡ እልና ፡ ያሰደደውን ፡ ስላላስመለሰ ፡ በደለኛ ፡ ነው ። ፲፬ ሁላችን ፡ እንሞታለን ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰና ፡ እንደማይመለስ ፡ ውኃ ፡ ነን ፤ እግዚአብሔርም ፡ የነፍስን ፡ ጥፋት ፡ አይወድድም ። ነገር ፡ ግን ፡ የተጣለ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይጠፋ ፡ በምክሩ ፡ ያስባል ። ፲፭ አሁንም ፡ ሕዝቡ ፡ ስለሚያስፈራኝ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ እነግረው ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለሁ ፤ እኔም ፡ ባሪያህ ፡— ምናልባት ፡ የእኔን ፡ የባሪያውን ፡ ልመና ፡ ንጉሡ ፡ ያደርግልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለንጉሡ ፡ ልናገር ፤ እርስዋንና ፡ ልጅዋን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከሚሻ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ ባሪያውን ፡ ይሰማል ፡ አልሁ ። ፲፮ እኔም ፡ ባሪያህ ፡— መልካሙንና ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ንጉሡ ፡ ጌታዬ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ነውና ፡ የጌታዬ ፡ የንጉሡ ፡ ቃል ፡ ያጽናናኛል ፡ አምላክህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አልሁ ።

፲፯ ንጉሡም ፡ ለሴቲቱ ፡ መልስ ፡— የምጠይቅሽን ፡ ነገር ፡ አትሰውሪኝ ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ይናገር ፡ አለች ። ፲፰ ንጉሡም ፡— በዚህ ፡ ሁሉ ፡ የኢዮአብ ፡ እጅ ፡ ከእንቺ ፡ ጋር ፡ ነውን ? አላት ። ሴቲቱም ፡ መልሳ ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በሕያው ፡ ነፍስህ ፡ እምላለሁ ! ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ከተናገረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ሊል ፡ የሚችል ፡ የለም ፤ ባሪያህ ፡ ኢዮአብ ፡ እዝዘኛል ። ፲፱ ይህንም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በባሪያህ ፡ አፍ ፡ አደረገው ። ባሪያህ ፡ ኢዮአብ ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ መልክ ፡ እንዲለውጥ ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ጠቢብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንተም ፡ ጌታዬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጠቢብ ፡ ነህ ፡ አለች ።

፳ ንጉሡም ፡ ኢዮአብን ፡— እነሆ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አድርጌአለሁ ፡ እንግዲህ ፡ ሂድና ፡ ብላቴናውን ፡ አቤሴሎምን ፡ መልሰው ፡ አለው ። ፳፩ ኢዮአብም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግምባሩ ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣ ፡ ንጉሡንም ፡ ባረከ ፡ ኢዮአብም ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የባሪያህን ፡ ነገር ፡ አድርገሃልና ፡ በዓይንህ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ እንዳገኘ ፡ ባሪያህ ፡ ዛሬ ፡ አወቀ ፡ አለ ። ፳፪ ኢዮአብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጌሹር ፡ ሄደ ፡ አቤሴሎምንም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይዞ ፡ መጣ ። ፳፫ ንጉሡም ፡— ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፡ ፊቴን ፡ እንዳያይ ፡ አለ ፡ አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ፡ የንጉሡንም ፡ ፊት ፡ አላየም ።

፳፬ በእስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አቤሴሎም ፡ በውበቱ ፡ የተመሰገነ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፡ ከእግሩ ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ ድረስ ፡ ነውር ፡ አልነበረበትም ። ፳፭ ጠጕሩም ፡ ይከብደው ፡ ነበርና ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይቈርጠው ፡ ነበር ፡ ሲቈረጥም ፡ የራሱ ፡ ጠጕር ፡ በንጉሡ ፡ ሚዛን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ያህል ፡ ይመዘን ፡ ነበር ። ፳፮ ለአቤሴሎምም ፡ ሦስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለዱለት ፤ የሴቲቱም ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ትዕማር ፡ ነበረ ፡ ። እርስዋም ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

፳፯ አቤሴሎምም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የንጉሡን ፡ ፊት ፡ ሳያይ ፡ ተቀመጠ ። ፳፰ አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ይልክ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ላከ ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ሊመጣ ፡ አልወደደም ፡ ሁለተኛም ፡ ላከበት ፡ ሊመጣ ፡ ግን ፡ አልወደደም ። ፳፱ ባሪያዎቹንም ፡— በእርሻዬ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ የኢዮአብን ፡ እርሻ ፡ እዩ ፡ በዚያም ፡ ገብስ ፡ አለው ፡ ሂዳችሁ ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉት ፡ አላቸው ። የአቤሴሎምም ፡ ባሪያዎች ፡ እርሻውን ፡ አቃጠሉት ። ፴ አቤሴሎምም ፡

ብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጣና ፡ — ባሪያዎችህ ፡ እርሻዩን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ፴፪ ፡ አቃጠሉት ? አለው ። አቤሴሎምም ፡ ኢዮአብን ፡ መልሶ ፡ — ከጌሹር ፡ ለምን ፡ መጣሁ ? በዚያ ፡ ተቀምጬ ፡ ብሆን ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር ፡ ብለህ ፡ እንድትነግረው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እልክህ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተራዡህ ፤ አሁንም ፡ የንጉሡን ፡ ፊት ፡ ልየ ። ኃጢአት ፡ ቢሆንብኝ ፡ ይግደለኝ ፡ ፴፫ ፡ አለው ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጥቶ ፡ ነገረው ፡ አቤሴሎምንም ፡ ጠራው ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገብቶ ፡ በንጉሥ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በግምባሩ ፡ ተደፋ ። ንጉሡም ፡ አቤሴሎምን ፡ ሳመው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ሰረገላና ፡ ፈረሶች ፡ ፶ሩትም ፡ የሚሮጡ ፡ አምሳ ፡ ሰዎች ፡ ፪ አዘጋጀ ። አቤሴሎምም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ በበሩ ፡ አደባባይ ፡ ይቆም ፡ ነበር ፡ አቤሴሎምም ፡ ከንጉሥ ፡ ለሚሰፈረድ ፡ ጕዳይ ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እየጠራ ፡ — እንት ፡ ከወዴት ፡ ከተማ ፡ ነህ ? ብሎ ፡ ይጠይቅ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ — እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ፫ ፡ ከአንዳቱ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ይመልስ ፡ ነበር ። አቤሴሎምም ፡ — ነገርህ ፡ እውነትና ፡ ቅን ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከንጉሥ ፡ ታገዘ ፡ የሚሰማህ ፡ የለም ፡ ፬ ፡ ይለው ፡ ነበር ። አቤሴሎምም ፡ — ነገርና ፡ ከር ፡ ከር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ቅንም ፡ ፍርድ ፡ እፈርድለት ፡ ዘንድ ፡ በእገር ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡ በሾመኝ ? ይል ፡ ፭ ፡ ነበር ። ሰውም ፡ እጅ ፡ ሊሰግደው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ይይዝና ፡ ይስ ፮ ፡ መው ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ አቤሴሎም ፡ ከንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰማ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በሚመጣ ፡ ሁሉ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ አቤሴሎምም ፡ የእስራኤልን ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ሰረቀ ።

፯ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ንጉሡን ፡ — ለእግዚአብሔር ፡ የተሳልሁትን ፡ ስእለት ፡ ለመስጠት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ፰ ፡ እሄዳለሁ ፡ ልሂድ ። አንተ ፡ ብሪያህ ፡ በሰርያ ፡ ጌሹር ፡ ሳለሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቢመልሰኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርባለሁ ፡ ብዬ ፡ ስእለት ፡ ተስዬ ፡ ነበር ፡ አለው ። ፱ ንጉሡም ፡ — በደኅና ፡ ሂድ ፡ አለው ፡ ተነሥቶም ፡ ፲ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ሄደ ። አቤሴሎምም ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ — የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በሰሚትሁ ፡ ጊዜ ፡ — አቤሴሎም ፡ በኬብሮን ፡ ፲፩ ፡ ነገሠ ፡ በሉ ፡ የሚሉ ፡ ጕበኞች ፡ ላክ ። የተጠሩትም ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋር ፡ በየዋህነት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሄዱ ፡ የሚዘነውንም ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ፲፪ አቤሴሎምም ፡ የዳዊት ፡ መካር ፡ የነበረውን ፡ የጊሎ ፡ ሰው ፡ አኪጦፌልን ፡ ከከተማው ፡ ከጊሎ ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ አስጠራው ። ሴራውም ፡ ጽኑ ፡ ሆነ ፡ ከአቤሴሎምም ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ።

፲፫ ለዳዊትም ፡ — የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋር ፡ ሆኖአል ፡ የሚል ፡ ወሬኛ ፡ መጣለት ። ፲፬ ዳዊትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ሁሉ ፡ — ተነሡ ፡ እንሽሽ ፡ ያለዚያ ፡ ከአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ የሚድን ፡ ከእኛ ፡ የለምና ፡ መዋቶም ፡ እንዳይዘን ፡ ከቀም ፡ እንዳያመጣብን ፡ ከተማይቱንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ እንዳያመታ ፡ ፈጥነናችሁ ፡ እንሂድ ፡ አላቸው ። ፲፭ የንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ ንጉሡን ፡ — እነሆ ፡ ጌታችን ፡ ንጉሡ ፡ የመረጠውን ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ እሺ ፡ ብለን ፡ እናደርጋለን ፡ አሉት ። ፲፮ ንጉሡም ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ወጡ ፡ በዚ ፡ ንጉሡም ፡ አሥሩን ፡ ሴቶች ፡ ቁባቶቹን ፡ ቤቱን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ተወ ። ፲፯ ንጉሡም ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ወጡ ፡ በዜ ፡ ትሜር ፡ ሐቅም ፡ ቆሙ ። ፲፰ ባሪያዎቹም ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ አለፉ ፡ ከለታውያንና ፡ ፈሊታውያንም ፡ ሁሉ ፡ ከጌት ፡ የመጡት ፡ ስድስት ፡ መቶው ፡ ጌታውያን ፡ ሁሉ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አለፉ ።

፲፱ ንጉሡም ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ኢታይን ፡ — ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለምን ፡ መጣህ ? አንተ ፡ ከስፍራህ ፡ የመጣህ ፡ እንግዳና ፡ ስደተኛ ፡ ነህና ፡ ተመለስ ፡ ከንጉሡም ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ ። ፳ የመጣኸው ፡ ትና ንት ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ላዙርህን ? እኔ ፡ ወደምሄድበት ፡ እሄዳለሁ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ተመ ለስ ፡ ወንድሞችህንም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ መልስ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምሕረቱንና ፡ እውነቱን ፡ ያድርግልህ ፡ አለው ። ፳፩ ኢታይም ፡ ለንጉሡ ፡ መልሶ ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በጌታ ዬም ፡ በንጉሡ ፡ ሕይወት ፡ እምላለሁ ፤ በእውነት ፡ ጌታዬ ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ በሞትም ፡ ቢሆን ፡ በሕይወትም ፡ በዚያ ፡ ይሁም ፡ አገ ፡ ባሪያህ ፡ እሆናለሁ ። ፳፪ ዳዊትም ፡ ኢታይን ፡ — ሂድ ፡ ተሻገር ፡ አለው ። የጌት ፡ ሰው ፡ ኢታ ይና ፡ ሰዎቹም ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነ በሩት ፡ ሕፃናት ፡ ሁሉ ፡ ተሻገሩ ። ፳፫ በእገርም ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ አለቀሱ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ተሻገሩ ። ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ የቄድሮንን ፡ ፈፋ ፡ ተሻገረ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ ተሻገሩ ።

፳፬ እነሆም ፡ ደግሞ ፡ ሳዶቅ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሌዋውያን ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከ ዳን ፡ ታቦት ፡ ተሸክመው ፡ መው ፡ የእግዚአብ ሔርንም ፡ ታቦት ፡ አስቀመጡ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ከከተማይቱ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ አብያ ታር ፡ ወጣ ። ፳፭ ንጉሡም ፡ ሳዶቅን ፡ — የእግዚአብሔ ርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መልስ ፤ በእግዚአ ብሔር ፡ ዓይን ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ መልሶ ፡ እርሱንና ፡ ማደሪያውን ፡ ያሳየኛል ። ፳፮ ነገር ፡ ግን ፡ — አልወድድህም ፡ ቢለኝ ፡ እነሆኝ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ያድርግብኝ ፡ አለው ።

፳፯ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅን ፡ — እነሆ ፡ አንተና ፡ ልጅህ ፡ አኪማአስ ፡ የአብያታርም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቻችሁ ፡ በደኅና ፡ ፳፰ ወደ ፡ ከተማ ፡ ተመለሱ ። እኔም ፡ እስክ ናንተ ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ እስኪመጣልኝ ፡ ድረስ ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ መሻገሪያ ፡ እቆያለሁ ፡ አለው ። ፳፱ ሳዶቅም ፡ አብያታርም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መለሱት ፡ በዚያም ፡ ተቀመጡ ።

፴ ዳዊትም ፡ ተከናንቦ ፡ ያለ ፡ ጫማ ፡ እያለቀሰ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወቀበት ፡ ወጣ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ተከናንበው ፡ ፴፩ እያለቀሱ ፡ ወጡ ። አኪጦፌል ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋር ፡ በሴራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፤ ዳዊትም ፡ — አቤቱ ፡ የአኪጦፌልን ፡ ምክር ፡ ስንፍና ፡ አድርገህ ፡ አንድትለውጥ ፡ ፴፪ አለምንሃለሁ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሰገደበት ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አርካዊው ፡ ኩሲ ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡ በራ ሱም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ሊገናኘው ፡ መጣ ። ፴፫ ዳዊትም ፡ አለው ፡ — ከእኔ ፡ ጋር ፡ ብትመጣ ፡ ፴፬ ትከብደኛለህ ፤ ወደ ፡ ከተማ ፡ ግን ፡ ተመልሰህ ፡ ለአቤሴሎም ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ባሪያ ፡ እሆንሃ ለሁ ፤ አስቀድሞ ፡ ለአባትህ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርሁ ፡ እንዲሁ ፡ አሁን ፡ ለአንተ ፡ ባሪያ ፡ እሆ ንሃለሁ ፡ ብትለው ፡ የአኪጦፌልን ፡ ምክር ፡ ከንቱ ፡ ታደርግልኛለህ ። ከህናቴ ፡ ሳዶቅና ፴፭ አብያታርም ፡ በዚያ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ አይደሉ ምን ? ከንጉሡ ፡ ቤትም ፡ የምትሰማውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለካህናቱ ፡ ለሳዶቅና ፡ ለአብያታር ፡ ንገራ ፴፮ ቸው ። እነሆ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማአስና ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ልጆቻቸው ፡ በዚያ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አሉ ፤ የምትሰሙትን ፡ ሁሉ ፴፯ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ላኩልኝ ። ፡ የዳዊትም ፡ ወዳጅ ፡ ኩሲ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መጣ ፡ አቤሴሎምም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ዳዊትም ፡ ከተራራው ፡ ራስ ፡ ዋቂት ፡ ፈቀቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የሜምፊቦስቴ ፡ ባሪያ ፡ ሲባ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ እንጀራ ፡ አንድ ፡ መቶም ፡ ዘለላ ፡ ዘቢብ ፡ አንድ ፡ መቶም ፡ በለስ ፡ አንድ ፡ አቁማዳም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የተጫኑ ፡ ሁለት ፡ አህዮች ፡ አየ ፪ ፡ ነዳ ፡ ተገናኘው ። ንጉሡም ፡ ሲባን ፡ — ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ሲባም ፡ — አህዮቹ ፡ የንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይቀመጡባቸው ፡ ዘንድ ፡ እንጀራውና ፡ በለሱ ፡ ብላቴኖቹ ፡ ይበ ላት ፡ ዘንድ ፡ የወይን ፡ ጠጁም ፡ በበረሀ ፡ የሚደ ክሙት ፡ ይጠጡት ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ ። ፫ ንጉሡም ፡ — የጌታህ ፡ ልጅ ፡ ወዴት ፡ ነው ? አለ ። ሲባም ፡ ንጉሡን ፡ — እነሆ ፡ — የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ የአባቴን ፡ መንግሥት ፡ ይመልስል ኛል ፡ ብሎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጦአል ፡ አለው ። ፬ ንጉሡም ፡ ሲባን ፡ — እነሆ ፡ ለሚም ፊቦስቴ ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ ለእንተ ፡ ይሁን ፡ አለው ። ሲባም ፡ — እጅ ፡ እነሣለሁ ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በፊትህ ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለ ።

፭ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ብሖቁም ፡ መጣ ፤ እነሆም ፡ ሳሚ ፡ የሚበል ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ከሳ አል ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ወጣ ፡ እየሄደም ፡ ይረግመው ፡ ነበር ። ፮ ፡ ዳዊትና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ በሪያ ፡ ምችም ፡ ድንጋይ ፡ ይወረውሩ ፡ ነበር ፤ በንጉሡም ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉና ፡ ኃያላኑ ፡ ሁሉ ፡ ነበሩ ። ፯ ሳሚም ፡ ሲረግም ፡ — ሂድ ፡ አንተ ፡ የደም ፡ ሰው ፡ ፰ ፡ ሰው ፡ ምናምንቴ ፡ ሂድ ። በፋንታው ፡ ነግሠህ ፡ ሃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሳኦልን ፡ ቤት ፡ ደም ፡ ሁሉ ፡ መለሰብህ ፤ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥ ትን ፡ ለልጅህ ፡ ለአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፤ እነሆም ፡ አንተ ፡ የደም ፡ ሰው ፡ ነህና ፡ በመከራ ፡ ተይዘሃል ፡ አለ ።

፱ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ አቢሳ ፡ ንጉሡን ፡ — ይህ ፡ የሞተ ፡ ውሻ ፡ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይረግማል ? ልሂድና ፡ ራሱን ፡ ልቍረጠው ፡ አለው ። ፲ ንጉሡም ፡ — እናንተ ፡ የጽሩያ ፡ ልጆች ፡ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለኝ ? እግዚአብሔር ፡ ዳዊትን ፡ ስደበው ፡ ብሎ ፡ እዝዘ ታልና ፡ ይርገመኝ ፤ ለምንስ ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋለህ ? የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ? አለ ። ፲፩ ዳዊትም ፡ አቢሳንና ፡ ባሪያዎቹን ፡ ሁሉ ፡ — እነሆ ፡ ከወገቤ ፡ የወጣው ፡ ልጄ ፡ ነፍሴን ፡ ይሻል ፤ ይል ቁንስ ፡ ይህ ፡ የብንያም ፡ ልጅ ፡ እንዴት ፡ ነዋ ? እግዚአብሔር ፡ እዝዘታልና ፡ ተዉት ፡ ይርገመኝ ፡ ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ መከራዬን ፡ ፲፪ አይቶ ፡ ስለ ፡ እርግማኑ ፡ መልክም ፡ ይመልስልኛል ፡ አላቸው ። ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ በመንገድ ፡ ፲፫ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፤ ሳሚም ፡ በተራራው ፡ አጠገብ ፡ በእርሱ ፡ ትይዩ ፡ እየሄደ ፡ ይራገም ፡ ድንጋ ይም ፡ ይወረውር ፡ ትቢያም ፡ ይበትን ፡ ነበር ። ፲፬ ንጉሡና ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደከመው ፡ ነበር ፡ በዚያም ፡ ዐረፉ ።

፲፭ አቤሴሎምና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ አኪጦፌልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ። ፲፮ የዳዊትም ፡ ወዳጅ ፡ አርካዊው ፡ ኩሲ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ኩሲ ፡ — ሺህ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥህ ፡ አለው ። ፲፯ አቤሴሎምም ፡ ኩሲን ፡ — ስለ ፡ ወዳጅህ ፡ ያደረግኸው ፡ ቸርነት ፡ ይህ ፡ ነውን ? ከወዳጅህ ፡ ጋር ፡ ያልሄድህ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ኩሲም ፡ አቤሴሎ ፲፰ ምን ፡ — እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለተመረጠው ፡ ለእርሱ ፡ እሆናለሁ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እቀመጣለሁ ። ፲፱ ለሁለተኛም ፡ የማገለግል ፡ ለማን ፡ ነው ? በንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ አይደለ ምን ? በአባትህ ፡ ፊት ፡ እንዳገለገልሁ ፡ እንዲሁ ፡ በእንተ ፡ ፈት ፡ እሆናለሁ ፡ አለው ።

፳ አቤሴሎምም ፡ አኪጦፌልን ፡ — ምክሩ ፡ ምን ፡ እናድርግ ? አለው ። ፳፩ አኪጦፌል ፡

አቤሴሎምን ፦— ቤት ፡ ሊጠብቁ ፡ ወደ ፡ ተዋ
ቸው ፡ ወደ ፡ አባትህ ፡ ቁበቶች ፡ ግፀ ፡ እስራ
ልም ፡ ሁሉ ፡ አባትህን ፡ እንዳሳፈርኸው ፡ ይሰ
ማሉ ፤ ከእንተም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ እጃቸው ፡
፭ ይበረታል ፡ አለው ። ለአቤሴሎምም ፡ በሰገነት ፡
ላይ ፡ ድንኳን ፡ ተከሉለት ፡ አቤሴሎምም ፡ በእ
ስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ቁበቶች ፡
፮ ገፀ ። በዚያም ፡ ወራት ፡ የመከራት ፡ የአኪጦ
ፌል ፡ ምክር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡
መጠየቅ ፡ ነበረች ፤ የአኪጦፌልም ፡ ምክር ፡
ሁሉ ፡ ከዳዊትና ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡
ነበረች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩ አኪጦፌልም ፡ አቤሴሎምን ፦— አሥራ ፡
ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ልምረጥና ፡ በዚህች ፡
፪ ሌሊት ፡ ተነሥቼ ፡ ዳዊትን ፡ ላሳድድ ። ደክሞና ፡
እጁ ፡ ዝሎ ፡ ሳለ ፡ እወድቅበታለሁ ፡ አስፈራ
ውማለሁ ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ይሸሻል ። ንጉሡንም ፡ ብቻውን ፡ እመ
፫ ታዋለሁ ፤ ሙሽራ ፡ ወደ ፡ ባልዋ ፡ እንደምትመ
ለስ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እመልሰዋ
ለሁ ። ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ደኅና ፡ ይሆናል ፤ የምት
፬ ፈልገው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገሩም ፡
አቤሴሎምንና ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎች ፡
ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ።

፭ አቤሴሎምም ፦— አርካዊውን ፡ ኩሲን ፡ ጥሩ ፡
ደግሞም ፡ እርሱ ፡ የሚለውን ፡ እንስማ ፡ አለ ።
፮ ኩሲም ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አቤ
ሴሎም ፦— አኪጦፌል ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፤
ነገሩን ፡ እናደርገው ፡ ዘንድ ፡ ይገባልን ? ባይሆን ፡
፯ ግን ፡ አንተ ፡ ንገረን ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። ኩሲም ፡
አቤሴሎምን ፦— አኪጦፌል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
የመከራት ፡ ምክር ፡ መልካም ፡ አይደለችም ፡
፰ አለው ። ኩሲ ፡ ደግሞ ፡ አለ ፦— ግልገሎችዋ ፡
በዱር ፡ በተነጠቁ ፡ ጊዜ ፡ ድብ ፡ መራራ ፡ እንደ ፡
ሆነች ፡ በልባቸው ፡ መራሮች ፡ እጅግም ፡ ኃያ
ላን ፡ መሆናቸውን ፡ አባትህንና ፡ ሰዎቹን ፡ ታው
ቃለህ ፤ አባትህ ፡ አርበኛ ፡ ነው ፡ ከሕዝብም ፡
፱ ጋር ፡ አያድርም ። አሁንም ፡ ምናልባት ፡ በአ
ንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡
ተሸሽጎ ፡ ይሆናል ፤ በመጀመሪያም ፡ ከእነርሱ ፡
አያሌዎች ፡ ቢወድቁ ፡ የሚሰማው ፡ ሁሉ ፦—
አቤሴሎምን ፡ የተከተለው ፡ ሕዝብ ፡ ተመታ ፡
፲ ይላል ። እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ አባትህ ፡ ኃያል ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡
ሰዎች ፡ ጽኑዓን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያውቃልና ፡
ጽኑዕ ፡ ልቡም ፡ እንደ ፡ እንበሳ ፡ ልብ ፡ የሆነው ፡
፲፩ ፈጽሞ ፡ ይቀልጣል ። ነገር ፡ ግን ፡ የምመክርህ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ያለ ፡ እስ
ራኤል ፡ ሁሉ ፡ በብዛቱ ፡ እንደ ፡ በሕር ፡ አሸዋ ፡
ሆኖ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይሰብሰብ ፤ አንተም ፡ በመ
፲፪ ከከላቸው ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ውጣ ። እርሱንም ፡
ወደምናገኝበት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ እንደር
ስበታለን ፤ ጠልም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደሚ
ወድቅ ፡ እንወርድበታለን ፤ እርሱና ፡ ከእርሱም ፡
ጋር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አና
ስቀርም ። ወደ ፡ ከተማም ፡ ቢገባ ፡ እስራኤል ፡ ፲፫
ሁሉ ፡ ወደዚያች ፡ ከተማ ፡ ገመድ ፡ ይወስዳል ፤
እኛም ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ እንኳ ፡ እስከማይገኝ
በት ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ እንስበታ
ለን ። አቤሴሎምና ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ፲፬
ሁሉ ፦— የአርካዊው ፡ የኩሲ ፡ ምክር ፡ ከአኪ
ጦፌል ፡ ምክር ፡ ይሻላል ፡ አሉ ። እግዚአብ
ሔርም ፡ በአቤሴሎም ፡ ላይ ፡ ክፋ ፡ ያመጣ ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልካሚቱን ፡ የአኪጦ
ፌልን ፡ ምክር ፡ እንዲበትን ፡ አዘዘ ።

ኩሲም ፡ ለካህናቲ ፡ ለሳዶቅና ፡ ለአብያታር ፦— ፲፭
አኪጦፌል ፡ ለአቤሴሎምና ፡ ለእስራኤል ፡ ሽማ
ግሌዎች ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ መክሮአል ፤ እኔ
ግን ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ መከሬአለሁ ። አሁን ፡ ፲፮
እንግዲህ ፡ ንጉሡና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡
ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይዋጡ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ሰ
ዎችዘንይ ፡ ተሻገር ፡ እንጂ ፡ በዚህች ፡ ሌሊት ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ መሻገሪያ ፡ አትደር ፡ ብላችሁ ፡
ለዳዊት ፡ ንገሩት ፡ አላቸው ። ዮናታንና ፡ አኪ ፲፯
ማአስ ፡ ተገልጠው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ይገቡ ፡
ዘንድ ፡ አልቻሉም ፡ ነበርና ፡ በዓይንሮጌል ፡ ተቀ
ምጠው ፡ ነበር ፤ አንዲትም ፡ ባሪያ ፡ ሄዳ ፡ ትነግ
ራቸው ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ሄደው ፡ ለንጉሡ ፡
ለዳዊት ፡ ይነግሩት ፡ ነበር ። አንድ ፡ ብላቴናም ፡ ፲፰
አይቶ ፡ ለአቤሴሎም ፡ ነገረው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡
ፈጥነው ፡ ሄዱ ፤ ወደ ፡ ብራቂምም ፡ ወደ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ መጡ ፤ በግቢውም ፡
ውስጥ ፡ ጕድጓድ ፡ ነበረ ፥ ወደዚያም ፡ ውስጥ ፡
ወረዱ ። ሴቲቱም ፡ በጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ፲፱
ዳውጃ ፡ ዘረጋችበት ፥ የተከከ ፡ እህልም ፡ በላዩ ፡
አሰጣችበት ፤ ነገሩም ፡ እንዲህ ፡ ተሰወረ ።
የአቤሴሎም ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ ወደ ፡ ፳
ቤት ፡ መጥተው ፦— አኪማአስና ፡ ዮናታን ፡ የት ፡
አሉ ? አሉ ፡ ሴቲቲቱም ፦— ፈፋውን ፡ ተሻግረው ፡
ሄዱ ፡ አለቻቸው ። እነርሱም ፡ ፈልገው ፡ በላገ
ኙአቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

ከሄዱም ፡ በኋላ ፡ እነርሱ ፡ ከጕድጓዱ ፡ ወጥ ፳፩
ተው ፡ ሄዱ ፥ ለንጉሡም ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፥
ዳዊትንም ፦— አኪጦፌል ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ እን
ዲህ ፡ መክሮአልና ፡ ተነሡ ፥ ፈጥናችሁም ፡ ውኃ
ውን ፡ ተሻገሩ ፡ አሉት ። ዳዊትና ፡ ከእርሱም ፡ ፳፪
ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ተነሥተው ፡ ዮርዳኖ
ስን ፡ ተሻገሩ ፤ እስኪነጋም ፡ ድረስ ፡ ዮርዳኖ
ስን ፡ ሳይሻገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አል
ቀረም ።

አኪጦፌልም ፡ ምክሩን ፡ እንዳልተከተሉ ፡ ፳፫
በየ ፡ ጊዜ ፡ አዘያውን ፡ ጫነ ፥ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ሄደ ፤ ቤቱንም ፡ አደራ
ጅቶ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ታንቆ ፡ ሞተ ፡ በአባቱም ፡
መቃብር ፡ ተቀበረ ።

ዳዊትም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ መጣ ፡ አቤሴ ፳፬

ሎምም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡
፳፭ ሁሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ። አቤሴሎምም ፡
በጭፍራው ፡ ላይ ፡ በኢዮአብ ፡ ስፍራ ፡ አሜሳ
ያን ፡ ሾመ ፤ አሜሳይም ፡ ያይስማኤላዊ ፡ ሰው ፡
የዬቴር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ እርሱም ፡ የኢዮአብን ፡
እናት ፡ የጽሩያን ፡ እኅት ፡ የናያስን ፡ ልጅ ፡ አቢ
፳፮ ግያን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ። እስራኤልና ፡ አቤሴ
ሎምም ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ሰፈሩ ።

፳፯ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
በአሞን ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ በረባት ፡ የነበረ ፡ የና
ያስ ፡ ልጅ ፡ ኤሌስቢ ፡ የሎዶባርም ፡ ሰው ፡ የዓ
ሚኤል ፡ ልጅ ፡ ማኪር ፡ የሮግሊምም ፡ ሰው ፡
፳፰፡፳፱ ገለዓዳዊው ፡ ቤርዜሊ ፦— ሕዝቡ ፡ በምድረ ፡
በዳ ፡ ተርቦአል ፡ ደክሞአል ፡ ተጠምቶአል ፡
ብለው ፡ ምንጣፍ ፡ ዳስ ፡ የሸክላም ፡ ዕቃ ፡ ይበ
ሉም ፡ ዘንድ ፡ ስንዴ ፡ ገብስ ፡ ዱቄት ፡ የተጠበሰ ፡
እሸት ፡ በቁላ ፡ ምስር ፡ የተቁላ ፡ ሽንብራ ፡ ማር ፡
ቅቤ ፡ በጎች ፡ የላምም ፡ እርጎ ፡ ለዳዊትና ፡ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ አመጡላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ ዳዊትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡
ቈጠረ ፡ ሻለቆችንና ፡ የመቶ ፡ አለቆችንም ፡
፪ ሾመላቸው ። ዳዊትም ፡ ሕዝቡን ፡ ከኢዮአብ ፡
እጅ ፡ በታች ፡ ሚሶውን ፡ ከኢዮአብም ፡ ወን
ድም ፡ ከጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ከአቢሳ ፡ እጅ ፡ በታች ፡
ሚሶውን ፡ ከጌት ፡ ሰውም ፡ ከኢታይ ፡ እጅ ፡
በታች ፡ ሚሶውን ፡ ሰደደ ። ንጉሡም ፡ ሕዝ
ቡን ፦— እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እወጣ
፫ ለሁ ፡ አላቸው ። ሕዝቡ ፡ ግን ፦— አትወጣም ፡
ብንሸሽ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አያስቡም ፡ ከእኛም ፡ እኩ
ሌታው ፡ ቢሞት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አያስቡም ፡ አንተ ፡
ግን ፡ ለብቻህ ፡ ከእኛ ፡ ከአሥሩ ፡ ሺህ ፡ ይልቅ ፡
ትበልጣለህ ፡ አሁንም ፡ በከተማ ፡ ተቀምጠህ ፡
ብትረዳን ፡ ይሻላል ፡ አሉ ። ንጉሡም ፦— መል
ካም ፡ የሚመስላችሁን ፡ አደርጋለሁ ፡ አላቸው ።
፭ ንጉሡም ፡ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ፤ ሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ሺህ ፡ በሺህ ፡ እየሆኑ ፡
፮ ወጡ ። ንጉሡም ፡ ኢዮአብንና ፡ አቢሳን ፡ ኢታ
ይንም ፦— ለብላቴናው ፡ ለአቤሴሎም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
ራሩለት ፡ ብሎ ፡ እዘዛቸው ። ንጉሡም ፡ ስለ ፡
አቤሴሎም ፡ አለቆቹን ፡ ሁሉ ፡ ሲያዝዝ ፡ ሕዝቡ ፡
፯ ሁሉ ፡ ሰማ ።

ሕዝቡም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡
፰ ወጣ ፡ ሰልፉም ፡ በኤፍሬም ፡ ዱር ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ።
፱ በዚያም ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ በዳዊት ፡ ባሪ
ያዎች ፡ ፊት ፡ ተመቱ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡
ውጊያ ፡ በዚያ ፡ ሆነ ፡ በያ ፡ ሺህ ፡ ሰውም ፡ ሞተ ።
፲ ከዚያም ፡ ሰልፉ ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡
ተበትኖ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰይፍ ፡ ከዋጠው ፡
ሕዝብ ፡ ይልቅ ፡ ዱር ፡ ብዙ ፡ ዋጠ ።

፲፩ አቤሴሎም ፡ ከዳዊት ፡ ባሪያዎች ፡ ጋር ፡ በድ
፲፪ ንገት ፡ ተገናኘ ፤ አቤሴሎምም ፡ በበቅሎ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ ነበር ፡ በቅሎውም ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፍ ፡
ባለው ፡ በታላቅ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ገባ ፡ ራሱም ፡
በዛፉ ፡ ተያዘ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡
ተንጠለጠለ ፡ ተቀምጦበትም ፡ የነበረ ፡ በቅሎ ፡
አለፈ ። አንድ ፡ ሰውም ፡ አይቶ ፦— እነሆ ፡ ፲፩
አቤሴሎም ፡ በትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠ
ልጥሎ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ለኢዮአብ ፡ ነገረው ።
፲፪ ኢዮአብም ፡ ለነገረው ፡ ሰው ፦— እነሆ ፡ ከየ
ኸው ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አልመታኸውም ?
አሥር ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ ድግ ፡ እሰጥህ ፡ ነበር ፡
አለው ። ሰውዮውም ፡ ኢዮአብን ፦— እኛ ፡ ስን ፲፫
ሰማ ፡ ንጉሡ ፡ እንትንና ፡ አቢሳን ፡ ኢታይ
ንም ፦— ብላቴናውን ፡ አቤሴሎምን ፡ ማንም ፡
እንዳይነካው ፡ ተጠንቀቁ ፡ ብሎ ፡ አዝዞአልና ፡
ሸህ ፡ ብር ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ብትመዝን ፡ እጁን ፡
በንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ በልዘረጋሁም ፡ ነበር ፡
እኔ ፡ ቅሉ ፡ በነፍሱ ፡ ላይ ፡ ብወነጅል ፡ ኖሮ ፡ ፲፫
ይህ ፡ ከንጉሥ ፡ ባልተሰወረም ፡ አንተም ፡ በተ
ነሣህብኝ ፡ ነበር ፡ አለው ። ኢዮአብም ፦— እኔ ፡ ፲፬
ከአንተ ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡ እዘገይ ፡ ዘንድ ፡ አልች
ልም ፡ ብሎ ፡ ሦስት ፡ ጦሮች ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ፡
አቤሴሎምም ፡ ገና ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡
ሕያው ፡ ሳለ ፡ በልቡ ፡ ላይ ፡ ተክላቸው ። አሥ ፲፭
ሩም ፡ የኢዮአብ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬዎች ፡ ከበቡት ፡
አቤሴሎምንም ፡ መትተው ፡ገደሉት ።

ኢዮአብም ፡ ሕዝቡን ፡ ከልከሎ ፡ ነበርና ፡ ፲፮
ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ፡ ሕዝቡም ፡ እስራኤልን ፡
ከማሰደድ ፡ ተመለሰ ። አቤሴሎምንም ፡ ወስ ፲፯
ደው ፡ በዱር ፡ በለ ፡ በታላቅ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡
ጣሉት ፡ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የድንጋይ ፡
ክምር ፡ ከመሩበት ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ እያን
ዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ። አቤሴሎምም ፡ ፲፰
ሕያው ፡ ሳለ ፦— ለስሜ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡
ልጅ ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ሐውልት ፡ ወስዶ ፡ በን
ጉሥ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ለራሱ ፡ አቁሞ ፡ ነበር ፡
ሐውልቱንም ፡ በስሙ ፡ ጠርቶት ፡ ነበር ። እስከ ፡
ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የአቤሴሎም ፡ መታሰቢያ ፡
ተብሎ ፡ ይጠራል ።

የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማአስ ፡ ግን ፦— እግዚአ ፲፱
ብሔር ፡ ጠላቶቹን ፡ እንደ ፡ ተበቀለለት ፡ ሮጬ ፡
ለንጉሥ ፡ የምስራች ፡ ልንገር ፡ አለ ። ኢዮአ ፳
ብም ፦— በሌላ ፡ ቀን ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ ወሬ ፡ አት
ናገርም ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሞቶአልና ፡ ዛሬ ፡
ወሬ ፡ አትናገርም ፡ አለው ። ኢዮአብም ፡ ፳፩
ኩሲን ፦— ሂድ ፡ ያየኸውንም ፡ ለንጉሡ ፡ ንገር ፡
አለው ። ኩሲም ፡ ለኢዮአብ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡
ሮጠ ። ዳግመኛም ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማአስ ፡ ፳፪
ኢዮአብን ፦— የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ኩሲን ፡ ተከትዬ ፡
እባክህ ፡ ልሩጥ ፡ አለው ። ኢዮአብም ፦— ልጄ ፡
ሆይ ፡ መልካም ፡ ወሬ ፡ የምትወስድ ፡ አይደለ
ህምና ፡ ትሮጥ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ትወድዳለህ ?
አለ ። እርሱም ፦— እኔ ፡ ብሮጥ ፡ ምን ፡ ይገድ ፳፫
ዳል ? አለ ። እርሱም ፦— ሩጥ ፡ አለው ። አኪማ
አስም ፡ በሜዳው ፡ መንገድ ፡ በኩል ፡ ሮጠ ፡
ኩሲንም ፡ ቀደመው ።

ዳዊትም በሁለት በር መከከል ተቀምጦ ነበር ። ዘበኛውም በቅጥሩ ላይ ወዳለው ወደ በሩ ሰገነት ወጣ ፥ ዓይኑንም አቅንቶ ብቻውን የሚሮጥ ሰው አየ ። ዘበኛውም ለንጉሡ ሊነግረው ጮኸ ። ንጉሡም — ብቻውን እንደ ሆነ በአፉ ወሬ ይኖራል አለ ። እርሱም ፈጥኖ ቀረበ ። ዘበኛውም ሌላ ሰው ሲሮጥ አየ ። ዘበኛውም ለደጅ ጠባቂው ጮኸ — እነሆ ብቻውን የሚሮጥ ሌላ ሰው አየሁ አለ ። ንጉሡም — እርሱ ደግሞ ወሬ ይዞ ይሆናል አለ ። ዘበኛውም — የፊተኛው ሩጫ እንደ ሳዶቅ ልጅ እንደ አኪማአስ ሩጫ ይመስላል አለ ። ንጉሡም — እርሱ መልካም ሰው ነው ። መልካምም ወሬ ያመጣል አለ ።

አኪማአስም ጮኸ ። ንጉሡን — ሁሉ ደኅና ሆኖአል አለው ። በንጉሡም ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ተደፍቶ — በንጉሡ በጌታዬ ላይ ኣጃቸውን ያነሡትን ሰዎች አሳልፎ የሰጠ እምላክህ እግዚአብሔር ይመስገን አለ ። ንጉሡም — ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና ነውን ? አለ ። አኪማአስም — ኢዮአብ እኔን ባሪያህንና የንጉሡን ባሪያ በላከ ጊዜ ትልቅ ሽብር አይቻለሁ ። ምን እንደ ሆነ ግን አላወቅሁም ብሎ መለሰለት ። ንጉሡም — ፈቀቅ ብለህ ቁም አለ ። እርሱም ፈቀቅ ብሎ ቆመ ።

እነሆም ኩሲ መጣ ። ኩሲም — እግዚአብሔር በላይህ የተነሡትን ሁሉ ዛሬ እንደ ተበቀለለህ ለጌታዬ ለንጉሡ ወሬ አምጥቻለሁ አለ ። ንጉሡም ኩሲን — ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና ነውን ? አለው ። ኩሲም — የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶች በክፉም የተነሡብህ ሁሉ እንደዚያ ብላቴና ይሁኑ ብሎ መለሰለት ። ንጉሡም እጅግ አዘነ ። በበሩም ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ ። ሲሄድም — ልጄ አቤሴሎም ሆይ ልጄ ልጄ አቤሴሎም ሆይ በአንተ ፋንታ ሞቼ ኖሮ ቢሆን ልጄ አቤሴሎም ልጄ ሆይ ይል ነበር ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

ኢዮአብም ንጉሡ ስለ አቤሴሎም እንዳለቀሰና ዋይ ዋይ እንዳለ ሰማ ። በዚያም ቀን — ንጉሡ ስለ ልጁ አዘነ ሲባል ሕዝቡ ሰምቶአልና የዚያ ቀን ድል በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ወደ ኀዘን ተለወጠ ። ሕዝቡም ከሰልፍ የሸሸ ሕዝብ አፍሮ ወደ ኋላው እንዲል በዚያ ቀን ወደ ከተማ ተሰርቆ ገባ ። ንጉሡም ፊቱን ሸፈነ ። ንጉሡም በታላቅ ድምፅ — ልጄ አቤሴሎም ሆይ ልጄ አቤሴሎም ልጄ ሆይ እያለ ይጮኽ ነበር ። ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ወደ ቤት ገብቶ እንዲህ አለ — ዛሬ ነፍስህንና የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ነፍስ የሚስቶችህንና የቁባቶችህን ነፍስ ያዳኑትን የባሪያዎችህን ሁሉ ፊት ዛሬ አሳፍረሃል ። አንተ የሚጠሉህን ትወድዳለህ ። መሰፍንና ባሪያዎችህን እንዳታስብ ዛሬ ገልጠሃል ። ዛሬ ሁላችን ሞተን ቢሆን ኖሮ አቤሴሎምም ድኖ ቢሆን ኖሮ ደስ ይሰኝህ ነበረ ። እንደ ነበረ ዛሬ አያለሁ ። አሁን እንግዲህ ተነሥተህ ውጣ ። ለባሪያዎችህም የሚያጽናናቸውን ነገር ተናገራቸው ። ያልወጣህ እንደ ሆነ ግን አንድ ሰው ከእንተ ጋር በዚህች ሴሊት እንዳይቀር በእግዚአብሔር እምላለሁ ። ይህም ከብላቴናነትህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ካገኘህ ክፉ ነገር ሁሉ ይልቅ ታላቅ መከራ ይሆንብሃል ። ንጉሡም ተነሥቶ በበሩ ተቀመጠ ። ሕዝቡም ሁሉ ንጉሡ በበሩ እንደ ተቀመጠ ሰማ ። ሕዝቡም ሁሉ ወደ ንጉሡ ፊት መጣ ።

እስራኤልም እያንዳንዱ ወደ ድንኳኑ ሸሽቶ ነበር ። ሕዝቡም ሁሉ በእስራኤል ነገድ ሁሉ መካከል — ንጉሡ ከጠላቶቻችን እጅ ታድኖናል ። ከፍልስጥኤማውያንም እጅ አድኖናል ። አሁንም ስለ አቤሴሎም ከአገር ሸሽቶአል ። በላያችን እንዲሆን የቀባነው አቤሴሎም በሰልፍ ሞቶአል ። አሁንም እንግዲህ ንጉሡን ለመመለስ ስለ ምን ዝም ትላላችሁ ? እያለ እርስ በርሱ ይከራከር ነበር ።

ንጉሡም ዳዊት ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር ልከ እንዲህ አላቸው — ለይሁዳ ሽማግሌዎች እንዲህ ብላችሁ ተናገሩአቸው — የእስራኤል ሁሉ ነገር ወደ ንጉሡ ደርሶአልና ። ንጉሡን ወደ ቤቱ ከመመለስ ስለ ምን ዘገያችሁ ? እናንተ ወንድሞቼ ፥ የአጥንቴ ፍላሜና የሥጋዬ ቀሥራሜ ናችሁ ! እናንተ ንጉሡን ከመመለስ ስለ ምን ዘገያችሁ ? ለአሜሳይም — አንተ የአጥንቴ ፍላሜና የሥጋዬ ቀሥራሜ አይደለህምን ? በዘመንህም ሁሉ በኢዮአብ ፋንታ በፊቴ የሠራዊት አለቃ ሳትሆን ብትቀር እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ይህንም ይጨምርብኝ በሉት ። የይሁዳንም ሰዎች ሁሉ ልብ እንደ አንድ ሰው ልብ አድርጎ እዘነበለ ወደ ንጉሡም ልከው — አንተ ከባሪያዎችህ ሁሉ ጋር ተመለስ አሉት ።

ንጉሡም ተመልሶ እስከ ዮርዳኖስ ድረስ መጣ ። የይሁዳ ሰዎች ንጉሡን ሊቀበሉ ንጉሡንም ዮርዳኖስን ሊያሻግሩ ወደ ጌልገላ መጡ ። ከብራቂም አገር የነበረው ብንያማዊው የጌራ ልጅ ሳሚ ከያሁዳ ሰዎች ጋር ዳዊትን ሊቀበል ፈጥኖ ወረደ ። ከእርሱም ጋር ብንያማውያን የሆኑ ሺህ ሰዎች ነበሩ ። የሳኦልም ቤት በሪያ ሲባ ከእርሱም ጋር አሥራ አምስቱ ልጆችና ሃያው ባሪያዎች ነበሩ ። በንጉሡም ፊት ፈጥነው ዮርዳኖስን ተሻገሩ ። ታንኳውም የንጉሥን ቤተ ሰብ ያሻግር ዘንድ ንጉሡም ደስ ያሰኘውን ያደርግ ዘንድ ይሸጋገር ነበር ። ንጉሡም ዮርዳኖስን ከተሻገረ በኋላ የጌራ ልጅ ሳሚ በፊቱ ተደፋ ። ንጉሡንም — ጌታዬ ሆይ ኃጢአቴን ኦትቀጣብኝ ፣ ጌታዬ ንጉሡ ከኢየሩሳሌም በወጣህ ቀን ባሪያህ የበደልሁህን አታስብብኝ ፣ ንጉሡም በልቡ አያኑረው ። ባሪያህ በደልኖ እንደ ሠንሁ አውቄአለሁና ። እነሆ ከዮሴፍ ቤት ሁሉ አስቀድሜ ዛሬ መጣሁ ÷ ጌታዬንም ንጉሡን ልቀበል ወረድሁ አለው ። የጽሩያ ልጅ አቢሳ ግን — ሳሚ እግዚአብሔር የቀባውን ሰድቦአልና ሞት የተገባው አይደለምን ? አለ ። ዳዊትም — እናንተ የጽሩያ ልጆች አኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ ? ዛሬ ስለ ምን ጠላቶች ትሆኑብኛላችሁ ? ዛሬስ በእስራኤል ዘንድ ሰው ሊሞት ይገባልን ? ዛሬስ በእስራኤል ላይ እንደ ነገሥሁ አላወቅሁምን ? አለ ። ንጉሡም ሳሚን — አትሞትም አለው ። ንጉሡም ማለለት ።

የሳኦልም ልጅ ሜምፊቦስቴ ንጉሡን ሊቀበል ወረደ ። ንጉሡም ከሄደ ጀምሮ በደኅና እስከ ተመለሰበት ቀን ድረስ እግሩን አልጠነከም ÷ ጢሙንም አልቈረጠም ÷ ልብሱንም አላጠበም ነበር ። ንጉሡንም ሊቀበለው ከኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ንጉሡ — ሜምፊቦስቴ ሆይ ÷ ከእኔ ጋር ስለ ምን አልወጣህም ? አለው ። እርሱም መልሶ አለ — ጌታዬ ንጉሥ ሆይ ÷ ባሪያዬ አታሎኛል ። እኔ ባሪያህ እንከሳ ነኝና — ከንጉሥ ጋር እሄድ ዘንድ የምቀመጥበትን አህያ ልጫን አልሁት ። እርሱም እኔን ባሪያህን ለጌታዬ ለንጉሡ አማ ። አንተ ጌታዬ ንጉሥ ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነህ ÷ ደስም ያሰኘህን አድርግ ። የአባቴ ቤት ሁሉ በጌታዬ በንጉሡ ዘንድ ሞት የሚገባቸው ነበሩ ። አንተ ግን እኔን ባሪያህን በገበታህ በሚበሉ መካከል አስቀመጥኸኝ ። ለንጉሥ ደግሞ ለመናገር ምን መብት አለኝ ? ንጉሡም — ነገርህን ለምን ታበዛለህ ? አንተና ሲባ እርሻውን ትከፈሉ ዘንድ — ብያለሁ አለው ። ሜምፊቦስቴም ንጉሡን — ጌታዬ ንጉሡ በደኅና ወደ ቤቱ ከተመለሰ እርሱ ሁሉን ይውሰደው አለው ።

ገለዓዳዊውም ቤርዜሊ ከሮግሊም ወረደ ። ሊሸኘውም ከንጉሡ ጋር ዮርዳኖስን ተሻገረ ። ቤርዜሊም እጅግ ያረጀ የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነበረ ። እጅግም ትልቅ ሰው ነበረና ንጉሡ በመሃናይም ሳለ ይቀልበው ነበር ። ንጉሡም ቤርዜሊን በኢየሩሳሌም አቀልብህ ዘንድ ከእኔ ጋር አለፍ አለው ። ቤርዜሊም ንጉሡን አለው — ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እወጣ ዘንድ ከሕያውቴ ዘመን ምን ያህል ቀረኝ ? ዛሬ የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነኝ ። መልካሙንና ክፉውን መለየት እችላለሁን ? እኔ ባሪያህ የምበላውንና የምጠጣውን ጣዕሙን መለየት እችላለሁን ? የወንዱንና የሴቲቱን ዘፋን መስማት እችላለሁን ? እኔ ባሪያህ በጌታዬ በንጉሡ ላይ ለምን እስ ብደብሃለሁ ? እኔ ባሪያህ ዮርዳኖስን ተሻግሬ ከንጉሡ ጋር ጥቂት ልሄድ ነበር ። ንጉሡ እንዲህ ያለ ወረታ ለምን ይመልስልኛል ? እኔ ባሪያህ ተመልሼ በከተማዬ በእባቴና በእናቴ መቃብር አጠገብ እበከህ ልሙት ። ነገር ግን ባሪያህን ከመሰ ምን እያ እርሱ ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር ይለፍ ። ደስ የሚያሰኝህንም ለእርሱ እድርግ ። ንጉሡም — ከመሰም ከእኔ ጋር ይለፍ ÷ ደስ የሚያሰኝህንም አደርግለታለሁ ። አንተም ከእኔ የምትሻውን ሁሉ አደርግልሃለሁ አለው ። ሕዝቡም ሁሉ ዮርዳኖስን ተሻገረ ÷ ንጉሡም ተሻገረ ። ንጉሡም ቤርዜሊን ሳመው ÷ መረቀውም ። ወደ ስፍራውም ተመለሰ ።

ንጉሡም ወደ ጌልገላ ተሻገረ ÷ ከመሰም ከእርሱ ጋር ሄደ ። የይሁዳም ሕዝብ ሁሉ ደግሞም ። የእስራኤል ሕዝብ እኩሌታ ንጉሡን አሻገረው ። እነሆም ÷ የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ወደ ንጉሥ መጡ ÷ ንጉሡንም — ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች ለምን ሰረቁህ ? ንጉሡንም ቤተ ሰቡንም ከእርሱም ጋር የዳዊትን ሰዎች ሁሉ ዮርዳኖስን አሻገሩ ? አሉት ። የይሁዳም ሰዎች ሁሉ ለእስራኤል ሰዎች መልሰው — ንጉሡ ለእኛ ቅርብኞች ነው ። ስለ ምን በዚህ ነገር ትቈጣላችሁ ? በውኑ ከንጉሡ አንዳች በልተናልን ? ወይስ እርሱ በረከት ሰጥቶናልን ? አሉ ። የእስራኤልም ሰዎች ለይሁዳ ሰዎች መልሰው — በንጉሡ ዘንድ ለእኛ አሥር ክፍል አለን ÷ በዳዊትም ዘንድ ደግሞ ከእናንተ ይልቅ መብት አለን ፣ ስለ ምን ናቃችሁን ? ስለ ምንስ ንጉሣችንን ለመመለስ ቀድሞ ምክር አልጠየቃችሁንም ? አሉ ። የይሁዳም ሰዎች ቃል ከእስራኤል ሰዎች ቃል ይልቅ ጠነከረ ።

ምዕራፍ ፳ ፰

፩ እንዲህም ሆነ፥ አንድ ብንያማዊ የቢክሪ ልጅ ስሙ ሳቤኤ የሚባል ምናምንቴ ሰው ነበረ፤ እርሱም ፦ ከዳዊት ዘንድ እድል ፈንታ የለንም ÷ ከእሴይም ልጅ ዘንድ ርስት የለንም ፤ እስራኤል ሆይ ÷ እያንዳንዳ ችሁ ወደ ድንኳንህ ተመለስ ብሎ ቀንደ መለከት ነፋ ። ፪ የእስራኤልም ሰዎች ሁሉ ከዳዊት ተለይተው የቢክሪን ልጅ ሳቤኤን ተከተሉ ፤ የይሁዳ ሰዎች ግን ከዮርዳኖስ ጀምረው ኢየሩሳሌም እስኪደርሱ ንጉሣቸውን ተከተሉ ።

፫ ዳዊትም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ቤቱ መጣ ፤ ንጉሡም ቤቱን ሊጠብቁ የተዋቸውን አሥሩን ቁባቶች ወስዶ ለጠባቂ ሰጣቸው ÷ ቀለብም ሰጣቸው ÷ ነገር ግን ወደ እነርሱ አልገባም ፤ በቤት ተዘግተው እስኪሞቱም ድረስ ፣ ባልቴቶች ሆነው ተቀመጡ ።

፬ ንጉሡም አሜሳይን ፦ የይሁዳን ሰዎች ሁሉ በሦስት ቀን ውስጥ ጥራልኝ ÷ አንተም አብረህ በዚህ ቁን አለው ። ፭ አሜሳይም የይሁዳን ሰዎች ሁሉ ይጠራ ዘንድ ሄደ ፤ ነገር ግን እርሱ የተቀጠረውን ቀን አሳልፎ ዘገየ ። ፮ ዳዊትም አቢሳን ፦ አሁን ከአቤሴሎም ይልቅ የሚጐዳን የቢክሪ ልጅ ሳቤኤ ነው ፤ እርሱ የተመሸጉትን ከተሞች አግኝቶ ከዓይናችን እንዳያመልጥ ÷ አንተ የጌታህን ባሪያዎች ወስደህ አሳድደው ፤ አለው ። ፯ አቢሳንም ተከትለው የኢዮአብ ሰዎች ፣ ከሊታውያንም ፈሊታውያንም ፣ ኃያላንም ሁሉ ፤ ሄዱ ። የቢክሪንም ልጅ ሳቤኤን ለማሳደድ ከኢየሩሳሌም ወጡ ። ፰ በገባዖንም ወዳለው ወደ ታላቁ ድንጋይ በደረሱ ጊዜ ፣ አሜሳይ ሊገናኛቸው መጣ ፤ ኢዮአብም የሰልፍ ልብስ ለብሶ ፣ በላዩም መታጠቂያ ነበረ ÷ በወገቡም ላይ ሰገባ ያለው ሰይፍ ፣ ታጥቆ ነበር ፤ እርሱም ሲራመድ ሰይፉ ወደቀ ። ፱ ኢዮአብም አሜሳይን ፦ ወንድሟ ሆይ ÷ ደኅና ነህን ? አለው ። ኢዮአብም አሜሳይን የሚስም መስሎ በቀኝ እጁ ጢሙን ያዘው ። ፲ አሜሳይ ግን በኢዮአብ እጅ ከነበረው ሰይፍ አልተጠነቀቀም ፤ ነበር ፤ ኢዮአብም ሆዱን ወጋው ÷ አንጀቱንም በምድር ላይ ፣ ዘረገፈው ፤ ሁለተኛም ፣ አልወጋውም ÷ ሞተም ።

ኢዮአብና ወንድሙ አቢሳ የቢክሪን ልጅ ሳቤኤን አሳደዱ ። ፲፩ ከኢዮአብም ብላቴኖች አንዱ በአሜሳይ ሬሳ አጠገብ ቆሞ ፦ ለኢዮአብ ወዳጅ የሚሆን ለዳዊትም የሆነ ሁሉ ኢዮአብን ይከተል ይል ነበር ። ፲፪ አሜሳይም በመንገድ መካከል ወድቆ ፣ በደሙ ላይ ይንከባለል ነበር ፤ ያም ሰው ወደ እርሱ የሚመጣ ሁሉ ሲቆም ፣ አይቶአልና ፣ ሕዝቡ ሁሉ እንደ ቆመ ፣ በየ ጊዜ አሜሳይን ከመንገድ ላይ ወደ እርሻ ውስጥ ፈቀቅ አደረገው ÷ በአብስም ከደነው ። ፲፫ ከመንገድ ራቅ ባለ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ የቢክሪን ልጅ ሳቤኤን ለማሳደድ ኢዮአብን ተከትሎ ያልፍ ነበር ።

፲፬ እርሱ ግን ከእስራኤል ነገድ ሁሉ ወደ አቤል ÷ ወደ ቤትመዓካ ÷ ወደ ቤሪም ሁሉ አለፈ ፤ ሰዎችም ደግሞ ተሰብስበው ተከተሉት ። ፲፭ በቤትመዓካ ባለ በአቤልም መጥተው ከበቡት ÷ በከተማይቱም ላይ እስከ ቅጥርዋ ድረስ የአፈርን ድልድል ደለደሉ ፤ ቅጥሩንም ያፈርሱ ዘንድ ከኢዮአብ ጋር የነበሩ ሕዝብ ሁሉ ይደበድቡ ነበር ። ፲፮ ከከተማይቱም አንዲት ብልሃተኛ ሴት ፦ ስሙ ÷ ስሙ ፤ ኢዮአብንም ፦ እነግርህ ዘንድ ወደዚህ ቅረብ በሉት ስትል ጮኸች ። ፲፯ ወደ እርስዋም ቀረበ ፤ ሴቲቱም ፦ ኢዮአብ አንት አንተ ነህን ? አለች ። እርሱም ፦ እኔ ነኝ ብሎ መለሰላት ። እርስዋም ፦ የባሪያህን ቃል ስማ አለችው ። እርሱም ፦ እሰማለሁ አላት ። ፲፰ እርስዋም ፦ ቀድሞ ፦ የሚጠይቅ በአቤል ዘንድ ይጠይቅ ይባል ነበር ፤ እንዲሁም ነገሩ ይፈጸም ነበር ። ፲፱ በእስራኤል ዘንድ ሰላምንና እውነትን ከሚወድዱ እኔ ነኝ ፤ አንተ በእስራኤል ያለችውን ከተማና እናት ለማፍረስ ትሻለህ ፤ ስለ ምንስ የእግዚአብሔርን ርስት ትውጣለህ ? ብላ ተናገረች ። ፳ ኢዮአብም ፦ መልስ ፦ ይህ መዋጥና ማጥፋት ከእኔ ይራቅ ፤ ነገሩ እንዲህ አይደለም ፤ ከተራራማው ከኤፍሬም ፣ አገር የሚሆን የቢክሪ ልጅ ሳቤኤ የሚባል አንድ ሰው ግን በንጉሡ ፣ በዳዊት ላይ እጁን አነሣ ፤ እርሱን ብቻውን ስጡኝ ÷ እኔም ከከተማይቱ እርቃለሁ አላት ። ሴቲቱም ፦ ኢዮአብን ፦ እነሆ ÷ ራሱ ከቅጥር ላይ ይጣልልሃል አለችው ። ሴቲቱም በብልሃትዋ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ሄደች ፤ እነርሱም የቢክሪን ልጅ የሳቤኤን ራስ ቈርጠው ወደ ኢዮአብ ጣሉት ። እርሱም ቀንደ መለከቱን ነፋ ÷ ሰውም ሁሉ ከከተማይቱ ርቆ እያንዳንዱ ወደ ድንኳኑ ሄደ ። ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ።

፳፫ ኢዮአብም በእስራኤል ሠራዊት ሁሉ ላይ አለቃ ነበረ ፤ የዮዳሄም ልጅ በናያስ በከሊታውያንና በፈሊታውያን ላይ ነበረ ፤ አዶንራምም ግብር አስገባሪ ነበረ ፤ የአሒሉድም ልጅ ኢዮሣፍጥ ታሪክ ጸሐፊ ነበረ ፤ ሱሳም ጸሐፊ ነበረ ፤ ሳዶቅና አብያታርም ከህናት ነበሩ ፤ የኢያዕር ሰውም ዒራስ ለዳዊት አማካሪ ነበረ ።

ምዕራፍ ፳፩ ፡

፩ በዳዊትም ዘመን ፣ ሦስት ዓመት ያህል ቀጥሎ ቀጥሎ ራብ ሆነ ፤ ዳዊትም የእግዚአብሔርን ፊት ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፦ የገባዖንን ሰዎች ስለ ገደለ በሳኦልና በቤቱ ላይ ደም አለበት አለ ። ፪ ንጉሡም የገባዖንን ሰዎች ጠራ ፤ የገባዖን ሰዎችም ከአሞራውያን የተረፉ ነበሩ ፤ እንጂ ከእስራኤል ልጆች ፣ ወገን አልነበሩም ፤ የእስራኤልም ልጆች ፣ ምለውላቸው ነበር ፤ ሳኦል ግን ለእስራኤል ልጆችና ለይሁዳ ስለ ቀና ፣ ሊገድላቸው ወደደ ። ነበር ። ፫ ዳዊትም የገባዖንን ሰዎች ፦ የእግዚአብሔርን ርስት ትባርኩ ዘንድ ፣ ምን ላድርግላችሁ ? ማስተስረያውስ ፣ ምንድር ነው ? አላቸው ። ፬ የገባዖን ሰዎችም ፦ በእኛና በሳኦል ወይም በእኛና በቤቱ መካከል ያለው ፣ የብርና የወርቅ ነገር አይደለም ፤ ከእስራኤልም ወገን እኛ ፣ የምንገድለው የለም ፤ አሉት ። እርሱም ፣ የምትናገሩትን ፣ አደርግላችኋለሁ አለ ። ንጉሡንም ፦ እኛን ከጠፋ ÷ በእስራኤል ዳርቻ ሁሉ እንዳንቀመጥ ፣ መፍረሳችንን ከሰበው ፣ ሰው ፣ ልጆች ፣ ሰባት ፣ ሰዎች ፣ አሳልፈህ ስጠንና ፣ ከእግዚአብሔር በተመረጠው ፣ በሳኦል አገር ፣ በጊብዓ ለእግዚአብሔር እንሰቅላቸዋለን ፣ አሉት ። ንጉሡም ፦ እሰጣችኋለሁ ፣ አለ ።

፯ ንጉሡም ፣ በሳኦል ልጅ ፣ በዮናታንና ፣ በዳዊት ፣ መካከል ፣ ስለ ነበረው ፣ ስለ እግዚአብሔር ፣ መሐላ ፣ የሳኦልን ፣ ልጅ ፣ የዮናታንን ፣ ልጅ ፣ ሜምፊቦስቴን ፣ አዳነ ። ፰ ንጉሡም ፣ ለሳኦል ፣ የወለደቻቸውን ፣ የኢዮኤል ልጅ ፣ የሪጽፋን ፣ ሁለቱን ፣ ልጆች ፣ ሄርሞንንና ፣ ሚምፊቦስቴን ፣ ለመሐላታዊውም ፣ ለቤርዜሊ ፣ ልጅ ፣ ለኢስድሪኤል ፣ የወለደቻቸውን ፣ የሳኦልን ፣ ልጅ ፣ የሜሮብን ፣ አምስቱን ፣ ልጆች ፣ ወሰደ ÷ ለገባዖንም ፣ ሰዎች ፣ እጅ ፣ አሳልፎ ፣ ሰጣቸው ፣ በእግዚአብሔርም ፣ ፊት ፣ በተራራው ፣ ላይ ፣ ሰቀሉአቸው ፤ ሰባቱም ፣ በአንድነት ፣ ወደቁ ፤ እነዚህም ፣ በሚታጨዱበት ፣ ወራት ፣ በገብስ ፣ መከር ፣ መጀመሪያ ፣ ተገደሉ ።

፲ የኢዮኤል ልጅ ፣ ረጽፋ ፣ ማቅ ፣ ወስዳ ፣ ከመከር ፣ ወራት ፣ ጀምሮ ፣ ዝናብ ፣ ከሰማይ ፣ እስኪዘንብ ፣ ድረስ ፣ በድንጋይ ፣ ላይ ፣ ዘረጋችው ፣ በቀንም ፣ ወፎች ፣ በሌሊትም ፣ አራዊት ፣ ያርፉባቸው ፣ ዘንድ ፣ አልተወችም ። ፲፩ የሳኦልም ፣ ቁባት ፣ የኢዮኤል ፣ ልጅ ፣ ረጽፋ ፣ ያደረገች ው ፣ ለዳዊት ፣ ነገሩት ። ፲፪ ዳዊትም ፣ ሄደ ÷ ሳኦልንም ፣ በጊልቦዓ ፣ በገደሉ ፣ ጊዜ ፣ ፍልስጥኤማውያን ፣ ከሰቀሉአቸው ፣ ስፍራ ፣ ከቤትሳን ፣ አደባባይ ፣ ከሰረቁት ፣ ከኢያቢስ ፣ ገለዓድ ፣ ሰዎች ፣ የሳኦልንና ፣ የልጁን ፣ የዮናታንን ፣ አጥንት ፣ ወሰደ ፣ ከዚያም ፣ የሳኦልንና ፣ የልጁን ፣ የዮናታንን ፣ አጥንት ፣ ይዞ ፣ መጣ ፣ የተሰቀሉ ትንም ፣ ሰዎች ፣ አጥንት ፣ ሰበሰበ ። ፲፫ የሳኦልንና ፣ የልጁን ፣ የዮናታንን ፣ አጥንት ፣ በብንያም ፣ አገር ፣ በጹላ ፣ በአባቱ ፣ በቂስ ፣ መቃብር ፣ ቀበሩት ፣ ንጉሡም ፣ ያዘዘውን ፣ ሁሉ ፣ አደረጉ ። ከዚያም ፣ በኋላ ፣ እግዚአብሔር ፣ ስለ ፣ አገሩ ፣ የተለመነውን ፣ ሰማ ።

፲፬ በዮናስጥኤማውያንና ፣ በእስራኤል ፣ መካከል ፣ ደግሞ ፣ ሰልፍ ፣ ነበረ ፣ ዳዊትም ፣ ከእርሱም ፣ ጋር ፣ ባሪያዎቹ ፣ ወረዱ ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፣ ጋር ፣ ተዋጉ ፣ ዳዊትም ፣ ደከመ ። ፲፭ ከራፋይም ፣ ወገን ፣ የነበረው ፣ ይሽቢ-ብናብ ፣ ዳዊትን ፣ ይገድል ፣ ዘንድ ፣ አሰበ ፤ የመሩም ፣ ሚዛን ፣ ክብደት ፣ ሦስት ፣ መቶ ፣ ሰቅል ፣ ናስ ፣ ነበረ ፤ አዲስም ፣ የመሣሪያ ፣ ታጥቆ ፣ ነበር ። ፲፮ የጽሩያም ፣ ልጅ ፣ አቢሳ ፣ እኛነው ÷ ፍልስጥኤማውያንም ፣ መትቶ ፣ ገደለው ። ያንጊዜም ፣ የዳዊት ፣ ሰዎች ፦ አንተ ፣ የእስራኤልን ፣ መብራት ፣ እንዳታጠፋ ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ከኢኖር ፣ ጋር ፣ ለሰልፍ ፣ አትወጣም ፣ ብለው ፣ ማሉለት ።

፲፯ ከዚህም ፣ በኋላ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ በጎብ ፣ ላይ ፣ ከፍልስጥኤማውያን ፣ ጋር ፣ ሰልፍ ፣ ሆነ ÷ ኩሳታዊውም ፣ ሴቦካይ ፣ ከራፋይም ፣ ወገን ፣ የነበረውን ፣ ሳፍን ፣ ገደለ ። ደግሞም ፣ በጎብ ፣ ላይ ፣ ፲፰ ከፍልስጥኤማውያን ፣ ጋር ፣ ሰልፍ ፣ ነበረ ፣ የቤተ ልሔማዊውም ፣ የየዓሬአርጊም ፣ ልጅ ፣ ኤልያናን ፣ የጦሩ ፣ የዐ ፣ እንደ ፣ ሸማኔ ፣ መጠቅለያ ፣ የነበረውን ፣ የጌት ፣ ሰው ፣ ጎልያድን ፣ ገደለ ። ደግሞም ፣ በጌት ፣ ላይ ፣ ሰልፍ ፣ ሆነ ፣ ፲፱ በዚያም ፣ በእጁና ፣ በእግሩ ፣ ስድስት ፣ ስድስት ፣ ሁሉም ፣ ሀያ ፣ አራት ፣ ጣቶች ፣ የነበሩት ፣ አንድ ፣ ረጅም ፣ ሰው ፣ ነበረ ፣ እርሱ ፣ ደግሞ ፣ ከራፋይም ፣ የተወለደ ፣ ነበረ ። ፳ እስራኤልንም ፣ በተገዳደረ ፣ ጊዜ ፣ የዳዊት ፣ ወንድም ፣ የሚማ ፣ ልጅ ፣ ዮናታን ፣ ገደለው ። ፳፩ እነዚያም ፣ አራቱ ፣ በጌት ፣ ውስጥ ፣ ከራፋይም ፣ የተወለዱ ፣ ነበሩ ፣ በዳዊትም ፣ እጅ ፣ በባሪያዎቹም ፣ እጅ ፣ ወደቁ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ዳዊትም ፣ እግዚአብሔር ፣ ከሳኦል ፣ እጅና ፣ ከጠላቶቹ ፣ እጅ ፣ ሁሉ ፣ ባዳነው ፣ ቀን ፣ የዚህን ፣ ቅኔ ፣ ቃል ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ተናገረ ። ፪ እንዲህም ፣ አለ ፦

እግዚአብሔር ፣ ዓለቴ ፣ አምባዬ ፣ መድኃኒቴ ፣ ነው ፣

፫ እግዚአብሔር ፣ ጠባቂዬ ፣ ነው ÷ በእርሱም ፣ እታመናለሁ ፣

ጋሻዬና ፣ የረድኤቴ ፣ ቀንድ ÷ መጠጊያዬና ፣ መሸሸጊያዬ ፣

መድኃኒቴ ፣ ሆይ ፣ ከግፍ ፣ ሥራ ፣ ታድነኛለህ ።

፬ ምስጋና ፣ የሚገባውን ፣ እግዚአብሔርን ፣ እጠራለሁ ፣

ከጠላቶቼም ፣ እድናለሁ ።

፩ የሞት ፡ ጣር ፡ ያዘኝ ፤
የዓመፅ ፡ ፈሳሽም ፡ አስፈራኝ ፤
፭ የሲኦል ፡ ጣር ፡ ከበበኝ ፤
የሞት ፡ ወጥመድ ፡ ደረሰብኝ ።
፯ በጨነቀኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራ
ሁት ÷
ወደ ፡ አምላኬም ፡ ጮኽሁ ፤
ከመቅደሱም ፡ ቃሌን ፡ ሰማኝ ÷
ጩኸቴም ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ጆሮው ፡ ገባ ።
፰ ምድርም ፡ ተንቀጠቀጠች ÷ ተናወጠችም ÷
የሰማዮችም ፡ መሠረቶች ፡ ተነቃነቁ ፤
እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቶአልና ፡ ተንቀ
ጠቀጡ ።
፱ ከቍጣው ፡ ጢስ ፡ ወጣ ÷
ከአፉም ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፤
ፍምም ፡ ከእርሱ ፡ በራ ።
፲ ሰማዮችን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ ÷ ወረደም ፤
ጨለማም ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ነበረ ።
፲፩ በኪሩብም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በረረ ፤
በነፋስም ፡ ክንፍ ፡ ሆኖ ፡ ታየ ፤
፲፪ መሰወርያውን ፡ ጨለማ ÷
በዙሪያውም ፡ የነበረውን ፡ ድንኳን ÷
በደመና ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ የጨለማ ፡ ውኃ ፡
አደረገ ።
፲፫ በፊቱም ፡ ካለው ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ፍም ፡
ተቃጠለ ።
፲፬ እግዚአብሔርም ፡ ከሰማያት ፡ አንጐደ
ጕደ ÷
ልዑልም ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፤
፲፭ ፍላጻውን ፡ ላከ ÷ በተናቸውም ፤
መብረቆችን ፡ ላከ ÷ አወከቸውም ።
፲፮ ከእግዚአብሔር ፡ ዘለፋ ÷
ከመዓቱም ፡ መንፈስ ፡ አስትንፋስ ፡ የተነሣ ÷
የባሕር ፡ ፈሳሾች ፡ ታዩ ÷
የዓለም ፡ መሠረቶችም ፡ ተገለጡ ።
፲፯ ከላይ ፡ ሰደደ ÷ ወሰደኝም ፤
ከብዙ ፡ ውኖችም ፡ አወጣኝ ።
፲፰ ከብርቱዎች ፡ ጠላቶቼ ÷
ከሚጠሉኝም ፡ አዳነኝ ፤ በርትተውብኝ ፡
ነበርና ።
፲፱ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ደረሱብኝ ፤
እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ደገፋዬ ፡ ሆነ ።
፳ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ስፍራም ፡ አወጣኝ ፤
ወድዶኛልና ፡ አዳነኝ ።
፳፩ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ፡ ይከፍለኛል ፡
እንደ ፡ እጄ ፡ ንጽሕና ፡ ይመልስልኛል ፤
፳፪ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ጠብቄአለ
ሁና ÷
በአምላኬም ፡ አላመፅሁምና ።
፳፫ ፍርዱ ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ ነበረና ፤
ከሥርዓቱም ፡ አልራቅሁምና ።
፳፬ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቅን ፡ ነበርሁ ÷
ከኃጢአቴም ፡ ተጠበቅሁ ።
፳፭ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ÷
እንደ ፡ እጄም ፡ ንጽሕና ፡ በዓይኖቹ ፡ ፊት ፡
መለሰልኝ ።
፳፮ ከቸር ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ቸር ፡ ሆነህ ፡ ትገኛለህ ፤
ከቅን ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ቅን ፡ ሆነህ ፡ ትገኛለህ ፤
፳፯ ከንጹሕ ፡ ጋር ፡ ንጹሕ ፡ ሆነህ ፡ ትገኛለህ ፤
ከጠማማም ፡ ጋር ፡ ጠማማ ፡ ሆነህ ፡ ትገ
ኛለህ ።
፳፰ አንተ ፡ የተጠቃውን ፡ ሕዝብ ፡ ታድናለህና ፤
የትዕቢተኞችን ፡ ዓይን ፡ ግን ፡ ታዋርዳለህ ።
፳፱ አቤቱ ፡ አንተ ፡ መብራቴ ፡ ነህና ፤
እግዚአብሔርም ፡ ጨለማዬን ፡ ያበራል ።
፴ በአንተ ፡ ኃይል ፡ በሮፍራ ፡ ላይ ፡ እሮጣ
ለሁና ፤
፴፩ በአምላኬም ፡ ቅዥራን ፡ እዘልላለሁና ።
የአምላክ ፡ መንገድ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የነጠረ ፡ ነው ፤
በእርሱ ፡ ለሚታመኑት ፡ ሁሉ ፡ ጋሻ ፡ ነው ።
፴፪ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ ማን ፡
ነው ?
ከአምላካችንስ ፡ በቀር ፡ አምባ ፡ ማን ፡ ነው ?
፴፫ ኃይልን ፡ የሚያስታጥቀኝ ÷ መንገዴንም ፡
የሚያቃና ÷
፴፬ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ብሆር ፡ እግሮች ፡ የሚ
ያረታ ÷
በከረብቶችም ፡ የሚያቆመኝ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ነው ።
፴፭ እጆቼን ፡ ሰልፍ ፡ ያስተምራል ፤
በክንዴም ፡ የናስ ፡ ቀስት ፡ እገትራለሁ ።
፴፮ የማዳንህንም ፡ ጋሻ ፡ ሰጠኸኝ ፤
ተግሣጽህም ፡ አሳደገኝ ።
አረማመዴን ፡ በበታቼ ፡ አሰፋህ ÷
፴፯ እግሮቼም ፡ አልተንሸራተቱም ።
ጠላቶቼን ፡ አሳድጄባቸዋለሁ ÷ አጠፋቸው
ማለሁ ፤
፴፰ እስከጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ አልመለስም ።
አስጨንቃቸዋለሁ ፡ መቆምም ፡ አይች
ሉም ÷
ከእግሬም ፡ በታች ፡ ይወድቃሉ ።
፴፱ ለሰልፍም ፡ ኃይልን ፡ ታስታጥቀኛለህ ፤
በላዬ ፡ የቆሙትን ፡ በበታቼ ፡ ታስገዛቸ
ዋለህ ።
፵ የጠላቶቼን ፡ ጀርባ ፡ ሰጠኸኝ ÷
የሚጠሉኝንም ፡ አጠፋሃቸው ።
፵፩ ጮኹ ÷ የሚረዳቸውም ፡ አልነበረም ፤
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ÷ አልሰማቸ
ውምም ።
፵፪ እንደ ፡ ምድር ፡ ትቢያ ፡ ፈጨኋቸው ፤
እንደ ፡ አደባባይም ፡ ጭቃ ፡ ረገጥኋቸው ÷
ደቀደቅኋቸውም ።
፵፫ ከሕዝብ ፡ ክርክር ፡ ታድነኛለህ ፤
የአሕዛብም ፡ ራስ ፡ አድርገህ ፡ ትሾመኛለህ ፤
የማላውቀው ፡ ሕዝብም ፡ ይገዛልኛል ።
፵፬ የበዕድ ፡ ልጆች ፡ ደለሉኝ ፤
በጆሮ ፡ ሰምተው ፡ ተገዙልኝ ።

፵፭ የበዕድ ፡ ልጆች ፡ እየጠፉ ፡ ይሄዳሉ ፤
ከተዘጉ ፡ ስፍሮች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ይወ
ጣሉ ።
፵፯ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ÷ ጠባቂዬም ፡
ቡሩክ ፡ ነው ፤
የመድኃኒቴ ፡ ጠባቂ ፡ አምላኬ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ይበል ፤
፵፰ በቀሌን ፡ የሚመልስልኝ ፡ አምላክ ÷
አሕዛብን ፡ በበታቼ ፡ የሚያስገዛ ÷
፵፱ ከጠላቶቼ ፡ የሚያወጣኝ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡
በእኔም ፡ ላይ ፡ ከቆሙ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ታደ
ርገኛለህ ፤
ከግፈኛ ፡ ሰው ፡ ታድነኛለህ ።
፶ አቤቱ ÷ ስለዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አመሰ
ግንሃለሁ ÷
ለስምህም ፡ አዘምራለሁ ።
፶፩ የንጉሡን ፡ መድኃኒት ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋል ፤
ቸርነቱንም ፡ ለቀባው ÷ ለዳዊትና ፡ ለዘሩ ÷
ለዘላለም ፡ ይሰጣል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩ የዳዊትም ፡ የመጨረሻ ፡ ቃሉ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ከፍ ፡ ከፍ ፡ የተደረገው ÷ በያዕቆብም ፡ አም
ላክ ፡ የተቀባው ÷
በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ በለ ፡ ቅኔ ፡
የሆነ ÷
የእሴይ ፡ ልጅ ፡ የዳዊት ፡ ንግግር ፤
፪ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ተናገረ ፤
ቃሉም ፡ በአንደበቴ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።
፫ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ተናገረኝ ፤
የእስራኤል ፡ ጠበቂ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦
በሰው ፡ ላይ ፡ በጽድቅ ፡ የሚሠለጥን ÷
፬ በእግዚአብሔርም ፡ ፍርሃት ፡ የሚነግሥ ÷
እርሱ ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡
ፀሐይ ፡ አወጣጥ ÷
በጥዋትም ፡ ያለ ፡ ደመና ፡ እንደሚደምቅ ÷
ከዝናብ ፡ በኋላ ፡ ከምድር ፡ እንደሚበቅል ፡
ልምላሜ ፡ ይሆናል ።
፭ በውኑ ፡ ቤቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
እንዲሁ ፡ አይደለምን ?
ከእኔም ፡ ጋር ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡ ቅንና ፡ ጽኑ ፡
የሆነውን ፡
የዘላለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጎአል ፤
መድኃኒቴንና ፡ ፈቃዴን ፡ ሁሉ ፡ ያበቅላል ።
፮ ዓመፀኞች ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ እን
ደማይዘው ÷
እንደ ፡ ተጣለ ፡ እሾህ ፡ ናቸው ።
፯ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይነክው ፡ ዘንድ ፡ ቢ
ድድ ÷
በእጁ ፡ ብረትና ፡ የጦሩን ፡ የበ ፡ ይይዛል ፤
በሥራቸውም ፡ በእሳት ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃጠ
ላሉ ።
፰ የዳዊት ፡ ኃያላን ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። የአለ
ቆች ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ ከነዓናዊው ፡ ኢያቡስቴ ፡
ነበረ ፤ እርሱም ፡ ጦሩን ፡ አንሥቶ ፡ ስምንት ፡
መቶ ፡ ያህል ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ገደለ ።
ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ የአሆሃዊው ፡ የዱዲ ፡
ልጅ ፡ ኤልያናን ፡ ነበረ ፤ ለሰልፍ ፡ የተሰበሰቡ
ትን ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ በተገዳደሩ ፡ ጊዜ ፡
ከዳዊት ፡ ጋር ፡ ከሦስቱ ፡ ኃያላን ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡
ነበረ ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ። እርሱ ፡
ግን ፡ ተነሥቶ ፡ እጁ ፡ እስኪደክምና ፡ ከሰይፉ ፡
ጋር ፡ እስኪጣበቅ ፡ ድረስ ፡ ፍልስጥኤማውያ
ንን ፡ መታ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡
ታላቅ ፡ መድኃኒት ፡ አደረገ ፤ ሕዝቡም ፡ ከእ
ርሱ ፡ በኋላ ፡ ምርኮ ፡ ለመግፈፍ ፡ ብቻ ፡ ተመ
ለሰ ።
ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ የአሮዳዊው ፡ የኤሌ ፡ ልጅ ፡
ሣማ ፡ ነበረ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ምስር ፡
በሞላበት ፡ እርሻ ፡ በአንድነት ፡ ሆነው ፡ ተከማ
ችተው ፡ ነበር ፡ ሕዝቡም ፡ ከፍልስጥኤማው
ያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ። እርሱ ፡ ግን ፡ በእርሻው ፡
መካከል ፡ ቆሞ ፡ ጠበቀ ÷ ፍልስጥኤማው ያን
ንም ፡ ገደለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ታላቅ ፡ መድ
ኃኒት ፡ አደረገ ።
፲፩ ከሠላሳውም ፡ አለቆች ፡ ሦስቱ ፡ ወርደው ፡
በመከር ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ዓዶላም ፡
ዋሻ ፡ መጡ ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡
በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፍሮ ፡ ነበር ። በዚያ ፡
ጊዜም ፡ ዳዊት ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ÷ የፍ
ልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡
በቤተ ፡ ልሔም ፡ ነበረ ። ዳዊትም ፡ — በበሩ ፡
አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡
ውኃ ፡ ባጠጣኝ ? ብሎ ፡ ተመኘ ። ሦስቱም ፡
ኃያላን ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ሠራዊት ፡ ቀድ
ደው ፡ ሄዱ ÷ በበሩም ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡
ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡ ውኃ ፡ ቀዱ ÷ ይዘ
ውም ፡ ለዳዊት ፡ አመጡለት ፤ እርሱ ፡ ግን ፡
ሊጠጣ ፡ አልወደደም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ አፍስሶ ፦ አቤቱ ÷ ይህን ፡ አደርግ ፡
ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ፤ በነፍሳቸው ፡ ደፍረው ፡
የሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ አይደለምን ? ብሎ ፡
ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ። ሦስቱ ፡ ኃያላን ፡
ያደረጉት ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብ ፡ ወንድም ፡
አቢሳ ፡ የሠላሳው ፡ አለቃ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡
ጦሩን ፡ በሦስቱ ፡ መቶ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ ገደላ
ቸው ፡ ስሙም ፡ እንደ ፡ ሦስቱ ፡ ተጠርቶ ፡ ነበር ።
እርሱ ፡ በሠላሳው ፡ መካከል ፡ የከበረ ፡ አልነበ
ረምን ? ስለዚህም ፡ አለቃቸው ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ።
፳፩ በቀብጽኤል ፡ የነበረው ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ያደ
ረገው ፡ የጽኑዕ ፡ ሰው ፡ የዮዳሄ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡
የሞዓባዊውን ፡ የቀብስኤልን ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡
ገደለ ፡ በአመዳዩም ፡ ወራት ፡ ወርዶ ፡ በጉድ
ጓድ ፡ ውስጥ ፡ አንበሳ ፡ ገደለ ። ፳፪ ደግሞም ፡
ግብጻዊ ፡ ሰው ፡ ገደለ ፤ ግብጻዊው ፡ በእጁ ፡
ጦር ፡ ነበረው ፡ በናያስ ፡ ግን ፡ በትር ፡ ይዞ ፡

ወደ ፡ እርሱ ፡ ወረደ ÷ ከግብጻዊውም ፡ እጅ ፡
፳፪ ጦሩን ፡ ነቅሎ ፡ በገዛ ፡ ጦሩ ፡ ገደለው ። የዮ
ዳሄ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡ ነው ፡
ስሙም ፡ እንደ ፡ ሦስቱ ፡ ኃያላን ፡ ተጠርቶ ፡
፳፫ ነበር ። ከሠላሳውም ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ÷
ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ። ዳዊ
ትም ፡ በክብር ፡ ዘበኞቹ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።
፳፬ የኢዮአብም ፡ ወንድም ፡ አሣሄል ፡ በሠላሳው ፡
መካከል ፡ ነበረ ÷ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ሰው ፡ የዱዲ ፡
፳፭ ልጅ ፡ ኤልያናን ÷ አሮዳዊው ፡ ሣማ ÷ ሐሮዳ
፳፮ ዊው ፡ ኤሊቃ ÷ ፈልጣዊው ፡ ሴሌስ ÷ የቴቁሐ
፳፯ ዊው ፡ የሚስካ ፡ ልጅ ፡ ዒራስ ÷ ዓናቶታዊው ፡
፳፰ አቢዔዜር ÷ ኩሳታዊው ፡ ምቡናይ ÷ አሆሃ
፳፱ ዊው ፡ ጸልሞን ÷ ነጦፋዊው ፡ ኖኤራ ÷ የነጦ
ፋዊው ፡ የበዓና ፡ ልጅ ፡ ሔሌብ ÷ ከብንያም ፡
፴ ፡ ወገን ፡ ከጊብዓ ፡ የሪባይ ፡ ልጅ ፡ ኢታይ ÷ ጲር
ዓቶናዊው ፡ በናያስ ÷ የጣዓስ ፡ ወንዝ ፡ ሰው ፡
፴፩ ሂዳይ ÷ ዓረባዊው ፡ አቢዓልበን ÷ በርሑማ
፴፪ ዊው ፡ ዓዝሞት ÷ ሸዓልበናዊው ፡ ኤሊያሕባ ÷
፴፫ የአሳን ፡ ልጆች ÷ ዮናታን ÷ አሮዳዊው ፡ ሣማ ÷
፴፬ የአሮዳዊው ፡ የአራር ፡ ልጅ ፡ አምናን ÷ የማዕ
ካታዊው ፡ ልጅ ፡ የአሐስባይ ፡ ልጅ ፡ ኤሌፋላት ÷
የጊሎናዊው ፡ የአኪጦፌል ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ÷
፴፮ ቀርሜሎሳዊው ፡ ሐጽሮ ÷ አርባዊው ፡ ፈንራይ ÷
፴፯ የሱባ ፡ ሰው ፡ የናታን ፡ ልጅ ፡ ይግባል ÷ ጋዳ
፴፰ ዊው ፡ በኒ ÷ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብ ፡ ጋሻ ፡
ጃግሬዎች ፡ አሞናዊው ፡ ኤሌቅ ÷ ብኤሮታዊው ፡
፴፱ ነሃራይ ÷ ይትራዊው ፡ ዒራስ ÷ ይትራዊው ፡
፵ ጋሬብ ÷ ኬጢያዊው ፡ አርዮ ፡ ሁሉ ፡ በሁሉ ፡
ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩ ደግሞም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ ዳዊትንም ፡ — ሂድ ÷ እስራ
ኤልንና ፡ ይሁዳን ፡ ቍጠር ፡ ብሎ ፡ በላያቸው ፡
፪ አስነሣው ። ንጉሡም ፡ ኢዮአብንና ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ የነበሩትን ፡ የሠራዊት ፡ አለቆች ፡ — የሕ
ዝቡን ፡ ድምር ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከዳን ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ድረስ ፡ ተመላለሱ ÷ ሕዝቡ
፫ ንም ፡ ቍጠሩአቸው ፡ አላቸው ። ኢዮአብም ፡
ንጉሡን ፡ — የጌታዬ ፡ የንጉሡ ፡ ዓይን ፡ እያየ ፡
አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ከለው ፡ ሕዝብ ፡
መጠን ፡ በላይ ፡ መቶ ፡ እጥፍ ፡ ይጨምርበት ፡
ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ይወ
፬ ድዳል ? አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ የንጉሡ ፡ ቃል ፡
በኢዮአብና ፡ በሠራዊቱ ፡ አለቆች ፡ ላይ ፡ አሸ
ነፈ ። ኢዮአብና ፡ የሠራዊቱ ፡ አለቆችም ፡ የእስ
ራኤልን ፡ ሕዝብ ፡ ይቈጥሩ ፡ ዘንድ ፡ ከንጉሥ ፡
፭ ዘንድ ፡ ወጡ ። ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገሩ ፡ በጋድ ፡
ሸለቆ ፡ መካከል ፡ ባለችው ፡ በኢያዜር ፡ ከተማ ፡
፮ ቀኝ ፡ በኩል ፡ በአሮዔር ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ። ወደ ፡
ገለዓድም ፡ ወደ ፡ ተባሶን ፡ አዳሰይ ፡ አገር ፡ መጡ ፡
ወደ ፡ ዳንየዓንም ፡ ደረሱ ÷ ወደ ፡ ሲዶናም ፡
፯ ዞሩ ÷ ወደ ፡ ጢሮስም ፡ ምሽግ ፡ ወደ ፡ ኤዊያው
ያንና ፡ ወደ ፡ ከነዓናውያንም ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡
መጡ ፡ በይሁዳም ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ በቤርሳ
፰ ቤህ ፡ ወጡ ። በአገሪቱም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተመላ
ልሰው ፡ ከዘጠኝ ፡ ወርና ፡ ከሀያ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡
፱ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ። ኢዮአብም ፡ የሕ
ዝቡን ፡ ቍጥር ፡ ድምር ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጠ ፡ በእ
ስራኤልም ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዝዙ ፡ ስምንት ፡
መቶ ፡ ሺህ ፡ ጽኑዓን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ የይሁ
ዳም ፡ ሰዎች ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ።
፲ ሕዝቡንም ፡ ከቈጠረ ፡ በኋላ ፡ ዳዊትን ፡ ልቡ ፡
መታው ፡ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ — በደረ
ግሁት ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ በድያለሁ ፡ አሁን ፡ ግን ÷
አቤቱ ÷ ታላቅ ፡ ስንፍና ፡ አድርጌአለሁና ፡ የባ
ሪያህን ፡ ኃጢአት ፡ ታርቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንህ
፲፩ ለሁ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ማልዶ ፡ በተነሣ ፡
ጊዜ ÷ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ባለ ፡
ራእይ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ጋድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
፲፪ መጣ ፡ — ሂድ ፡ ለዳዊት ፡ — እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፡ — ሦስት ፡ ነገሮች ፡ በፊትህ ፡ እሰ
ራለሁ ፡ አደርግብህ ፡ ዘንድ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱን ፡
፲፫ ምረጥ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ አለው ። ጋድም ፡
ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥቶ ፡ — የሦስት ፡ ዓመት ፡ ራብ ፡
በአገርህ ፡ ላይ ፡ ይምጣብህን ? ወይስ ፡ ጠላቶ
ችህ ፡ እያሳደዱህ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከእነርሱ ፡ ትሸ
ሽን ? ወይስ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ቸነፈር ፡ በአገርህ ፡
ላይ ፡ ይሁን ? አሁንም ፡ ለላከኝ ፡ ምን ፡ መልስ ፡
እንደምሰጥ ፡ አስብና ፡ መርምር ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።
፲፬ ዳዊትም ፡ ጋድን ፡ — እጅግ ፡ ተጨንቄአለሁ ፡
ምሕረቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡
እንውደቅ ፤ በሰው ፡ እጅ ፡ ግን ፡ አልውደቅ ፡
አለው ።
፲፭ ዳዊትም ፡ ቸነፈሩን ፡ መረጠ ፡ የስንዴም ፡
መከር ፡ ወራት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቸነፈሩ ፡ በሕዝቡ ፡
መካከል ፡ ጀመረ ፡ ከሕዝቡም ፡ ሰባ ፡ ሺህ ፡
ሰው ፡ ሞተ ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡
፲፮ ኢየሩሳሌምን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ እጁን ፡ በዘ
ረጋ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ክፉው ፡ ነገር ፡
አዘነ ÷ ሕዝቡንም ፡ የሚያጠፋውን ፡ መልአክ ፡ —
እንግዲህ ፡ በቃህ ፡ እጅህን ፡ መልስ ፡ አለው ።
የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያቡሳዊው ፡
በአርና ፡ አውድማ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። ዳዊትም ፡
፲፯ ሕዝቡን ፡ የሚመታውን ፡ መልአክ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
እግዚአብሔርን ፡ — እነሆ ÷ እኔ ፡ በድያለሁ ፡
ጠማማም ፡ ሥራ ፡ እኔ ፡ አድርጌአለሁ ፡ እነዚህ ፡
በጎች ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ? እጅህ ፡
በእኔና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እንድትሆን ፡ አለ
ምንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።
፲፰ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጋድ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥቶ ፡ —
ውጣ ÷ በኢያቡሳዊው ፡ በአርና ፡ አውድማ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሥራ ፡ አለው ።
ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደ ፡
፲፱ ጋድ ፡ ነገር ፡ ወጣ ። አርናም ፡ ሲመጡ ፡ አየ ፡
አርናም ፡ ወጥቶ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ በምድር ፡
፳ ላይ ፡ በግምባሩ ፡ ተደፋ ። አርናም ፡ — ጌታ
ዬን ፡ ንጉሡን ፡ ወደ ፡ ባሪያው ፡ ያመጣው ፡ ምክ
ንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። ዳዊትም ፡ — መቅ
ሠፍቱ ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ይከለከል ፡ ዘንድ ፡ አው
፳፩ ድግውን ፡ ከእንተ ፡ ገዝቼ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
መሠዊያ ፡ ልሠራ ፡ ነው ፡ አለው ። አርናም ፡
ዳዊትን ፡ — ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡
ወስዶ ፡ ያቅርብ ፡ እነሆ ÷ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕ
ት ፡ በሬዎች ÷ ለሚቃጠልም ፡ እንጨት ፡ የአ
፳፪ ውድግ ፡ ዕቃና ፡ የበሬ ፡ ቀንበር ፡ አለ ። ንጉሥ ፡
ሆይ ÷ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አርና ፡ ለንጉሡ ፡ ይሰጣል ፡
አለው ፡ አርናም ፡ ንጉሡን ፡ — አምላክህ ፡ እግ
፳፫ ዚአብሔር ፡ ይቀበልህ ፡ አለው ። ንጉሡም ፡
አርናን ፡ — እንዲህ ፡ አይደለም ÷ ነገር ፡ ግን ፡
በዋጋ ፡ ከእንተ ፡ እገዛለሁ ፡ ለእምላኬም ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያለ ፡
ዋጋ ፡ አላቀርብም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አውድ
ማውንና ፡ በሬዎቹን ፡ በእምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡
፳፬ ገዛ ። በዚያም ፡ ዳዊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠ
ዊያ ፡ ሠራ ÷ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነትንም ፡
መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡
አገሪቱ ፡ የተለመነውን ፡ ሰማ ÷ መቅሠፍቱም ፡
ከእስራኤል ፡ ተከለከለ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ።

(እርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ሣልስ ፡ ነው ።)

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ሸመገለ ፡ ዕድሜውም ፡
በዛ ፡ ልብስም ፡ ያረቡለት ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አያሞ
፪ ቀውም ፡ ነበር ። ባሪያዎቹም ፡ — ለጌታችን ፡ ለን
ጉሡ ፡ ድንግል ፡ ትፈለጋለች ፡ በንጉሡም ፡ ፊት ፡
ቆማ ፡ ታገልግለው ÷ በጌታችንም ፡ በንጉሡ ፡
፫ ብብት ፡ ተኝታ ፡ ታሙቀው ፡ አሉት ። በእስራ
ኤልም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የተዋበች ፡ ቈንጆ ፡ ፈለጉ ፡
ሱነማይቱን ፡ አቢሳንም ፡ አገኙ ÷ ወደ ፡ ንጉ
፬ ሡም ፡ ይዘዋት ፡ መጡ ። ቈንጆይቱም ፡ እጅግ ፡
ውብ ፡ ነበረች ፡ ንጉሡንም ፡ ትረዳውና ፡ ታገ
ለግለው ፡ ነበር ÷ ንጉሡ ፡ ግን ፡ አያውቃትም ፡
ነበር ።
፭ የአጒትም ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፡ — ንጉሥ ፡ እሆና
ለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፡ ሰረገሎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፡
በፊቱም ፡ የሚሮጡ ፡ አምሳ ፡ ሰዎች ፡ አዘጋጀ ።
፮ አባቱም ፡ ከቶ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ — እንዲህ ፡
ለምን ፡ ታደርጋለህ ? ብሎ ፡ አልተቈጣውም ፡
ነበር ። እርሱ ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሰው ፡
ነበረ ፡ ከአቤሴሎምም ፡ በኋላ ፡ ተወልዶ ፡ ነበር ።
፯ ሩራውም ፡ ከጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮአብና ፡ ከካ
ህኑ ፡ ከአብያታር ፡ ጋር ፡ ነበረ ÷ እነርሱም ፡ አዶ
፰ ንያስን ፡ ተከትለው ፡ ይረዱት ፡ ነበር ። ነገር ፡
ግን ፡ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ የዮዳሄ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡
ነቢዩም ፡ ናታን ፡ ሳሚም ፡ ሬስይ ፡ የዳዊትም ፡
፱ ኃያላን ፡ ከአዶንያስ ፡ ጋር ፡ አልነበሩም ። አዶ
ንያስም ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ፍሪዳዎችንም ፡
በዓይንሮጌል ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በዞሔሌት ፡
፲ ድንጋይ ፡ ዘንድ ፡ ሠዋ ፡ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡
ወንድሞቹን ፡ ሁሉ ÷ የንጉሡንም ፡ ባሪያዎች ÷
የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ። ነገር ፡ ግን ፡
፲፩ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡ በናያስንም ÷ ኃያላኑንም ÷
ወንድሙንም ፡ ሰሎሞንን ፡ አልጠራም ።
፲፪ ናታንም ፡ የሰሎሞንን ፡ እናት ፡ ቤርሳቤህን ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራት ፡ — ጌታችን ፡ ዳዊት ፡
ሰያውቅ ፡ የአጒት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፡ እንደ ፡
ነገሠ ፡ አልሰማሽምን ? አሁንም ፡ ነፍ ፡ የል
፲፫ ጅሽን ፡ የሰሎሞንን ፡ ነፍስና ፡ የአንቺን ፡ ነፍስ ፡
እንድታድኝ ፡ እመክርሻለሁ ። ሂደሽ ፡ ወደ ፡
፲፬ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ግቢና ፡ — ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡
ሆይ ÷ ለእኔ ፡ ለባሪያህ ፡ — ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡
ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ÷ በዙፋኔም ፡ ይቀመ
ጣል ፡ ብለህ ፡ አልማልህልኝምን ? ስለ ፡ ምንስ ፡
አዶንያስ ፡ ይነግሣል ? በዩ ። እነሆ ÷ እንቺ ፡
፲፭ በዚያ ፡ ለንጉሥ ፡ ስትነግሪ ፡ እኔ ፡ ከአንቺ ፡ በኋላ ፡
እገባለሁ ÷ ቃልሽንም ፡ አጸናለሁ ።
፲፮ ቤርሳቤህም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡
ገባች ፡ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ሸምግሎ ፡ ነበር ÷ ሱነ
፲፯ ማይቱም ፡ አቢሳ ፡ ታገለግለው ፡ ነበር ። ቤርሳ
ቤህም ፡ አጐንብሳ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣች ፡
ንጉሡም ፡ — ምን ፡ ትፈልጊያለሽ ? አለ ። እር
፲፰ ስዋም ፡ አለችው ፡ — ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ ለባ
ሪያህ ፡ — ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነ
ግሣል ÷ በዙፋኔም ፡ ይቀመጣል ፡ ብለህ ፡ በአ
ምላክህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለህልኛል ፡ አሁ
፲፱ ንም ፡ እነሆ ÷ አዶንያስ ፡ መንገሡ ፡ ነው ፡ አን
ተም ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ አታውቅም ፡
እርሱም ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፡ በጎ
፳ ችንም ፡ ሠውቶልኛ ÷ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ÷ ካህኑንም ፡ አብያታርን ÷ የሠራዊቱንም ፡
አለቃ ፡ ኢዮአብን ፡ ጠርቶአል ፡ ባሪያህን ፡ ስሎ
ሞንን ፡ ግን ፡ አልጠራውም ። አሁንም ÷ ጌታዬ ፡
፳፩ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ከእንተ ፡ በጌታዬ ፡ በን
ጉሥ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ ትነግራ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ይመ
ለከትሃል ። ይህ ፡ ባይሆን ÷ ጌታዬ ፡ ከአባቶ
፳፪ ችህ ፡ ጋር ፡ በንቀላፋህ ፡ ጊዜ ፡ እኔና ፡ ልጄ ፡
ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ኃጢአተኞች ፡ እንቈጠራለን ።
፳፫ እነሆም ÷ ለንጉሡ ፡ ስትናገር ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡
ገባ ። ለንጉሡም ፡ — እነሆ ÷ ነቢዩ ፡ ናታን ፡
፳፬ መጥቶአል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡

ንጉሡ ፡ ፊት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በግምባሩ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣ ። ፵፬፡ ናታንም ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡— ከእኔ ፡ በኋላ ፡ አዶንያስ ፡ ይነግሣል ፡ በዙፋኔም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል ፡ ብለሃልን ? ፵፭፡ እርሱ ፡ ዛሬ ፡ ወርዶ ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፡ በጎችንም ፡ ሠውቶአል ፡ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ የሠራዊትንም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብን ፡ ካህኑንም ፡ አብያታርን ፡ ጠርቶአል ፡ እነሆም ፡ በፊቱ ፡ እየበሉና ፡ እየጠጡ ፡— አዶንያስ ፡ ሺህ ፡ ፵፮፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ ይላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ካህኑንም ፡ ሳዶቅን ፡ የዮዳሄንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ባሪያህንም ፡ ሰሎሞንን ፡ አልጠራም ። ፵፯፡ በውኑ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ የተደረገ ፡ ነውን ? ለባሪያህም ፡ ከእንተ ፡ በኋላ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ አልነገርህምን ?

፵፰፡ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡— ቤርሳቤህን ፡ ጥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገባች ፡ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆመች ። ፵፱፡ ንጉሡም ፡— ነፍሴን ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ ያዳነኝ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በእውነት ፡— ፶፡ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፡ በእኔም ፡ ፋንታ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል ፡ ብዬ ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማልሁልሽ ፡ እንዲሁ ፡ ዛሬ ፡ በእውነት ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ፶፩፡ ቤርሳቤህም ፡ በግምባርዋ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍታ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣችና ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ለዘላለም ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ፡ አለች ። ፶፪፡ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡— ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡ የዮዳሄንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ጥሩልኝ ፡ አለ ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ፊት ፡ ገቡ ። ፶፫፡ ንጉሡም ፡ አላቸው ፡— የጌታችሁን ፡ ባሪያዎች ፡ ይዛችሁ ፡ ሂዱ ፡ ልጄንም ፡ ሰሎሞንን ፡ በበቅሎዬ ፡ ላይ ፡ አስቀምጡት ፡ ወደ ፡ ግዮንም ፡ አውርዱት ፡ በዚያም ፡ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ይቅቡት ፡ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ ነፍተው ፡ ንጉሥ ፡ አዶንያስ ፡ ይንግሣል ፡ በሉ ። ፶፬፡ በኋላ ውም ፡ ተከትላችሁ ፡ ውጡ ፡ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፡ በእኔም ፡ ፋንታ ፡ ይነግሥ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አዝዣለሁ ። የዮዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ መልሶ ፡ ለንጉሡ ፡ አለ ፡— ያበጅ ፡ ያድርግ ፡ የጌታዬም ፡ የንጉሥ ፡ አምላክ ፡ ይሁን ፡ ፶፭፡ ይናገር ። እግዚአብሔር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ ከሰሎሞን ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ ዙፋኑንም ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ።

፶፮፡ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታንም ፡ የዮዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ከሊታውያንና ፡ ፈሊታውያንም ፡ ወረዱ ፡ ሰሎሞንንም ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ ወደ ፡ ግዮን ፡ አመጡት ። ፶፯፡ ካህኑም ፡ ሳዶቅ ፡ ከድንኳኑ ፡ የቅብዓቱን ፡ ቀንድ ፡ ወስዶ ፡ ሰሎሞንን ፡ ቀባ ፡ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ ነፋ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡— ሰሎሞን ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ አሉ ። ሕዝቡም ፡ ፶፰፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ፡ ሕዝቡም ፡ ዘፈን ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር ፡ በታላቅም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ከጩኸታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ።

፶፱፡ አዶንያስና ፡ እርሱም ፡ የጠራቸው ፡ ሁሉ ፡ መብሉና ፡ መጠጡ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሳለ ፡ ሰሙ ፡ ኢዮአብም ፡ የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡— ይህ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የሽብር ፡ ድምፅ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። ፷፡ እርሱም ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ የካህኑ ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ መጣ ፡ አዶንያስም ፡— አንተ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነህና ፡ መልካም ፡ ታመራልናለህና ፡ ግባ ፡ አለ ። ፷፩፡ ዮናታንም ፡ ለአዶንያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡— በእውነት ፡ ጌታችን ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞንን ፡ አነገሠው ። ፷፪፡ ንጉሡም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡ የዮዳሄንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ከሊታውያንንና ፡ ፈሊታውያንንም ፡ ሰደደ ። በንጉሡም ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ። ፷፫፡ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በግዮን ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ቀቡት ፤ ከዚያም ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ወጡ ፡ ከተማይቱም ፡ አስተጋባች ፤ የሰማችውትም ፡ ድምፅ ፡ ይህ ፡ ነው ። ፷፬፡ ደግሞም ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦአል ። የንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ ገብተው ፡— እግዚአብሔር ፡ የሰሎሞንን ፡ ስም ፡ ከስምህ ፡ ዙፋኑንም ፡ ከዙፋንህ ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ፡ ብለው ፡ ጌታችንን ፡ ንጉሡን ፡ ዳዊትን ፡ ባረኩ ፡ ንጉሡም ፡ በአልጋው ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሰገደ ። ፷፭፡ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡— ዓይኔ ፡ እያየ ፡ ዛሬ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ የሰጠኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

፷፮፡ አዶንያስም ፡ የጠራቸው ፡ ሁሉ ፡ ፈሩ ፡ ተነሡም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየመንገዳቸው ፡ ሄዱ ። ፩፡ አዶንያስም ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈራ ፡ ተነሥቶም ፡ ሄደ ፡ የመሠዊያውንም ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ። ፪፡ ለሰሎሞንም ፡— እነሆ ፡ አዶንያስ ፡ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈርቶ ፡— ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በሰይፍ ፡ እንዳይገድለኝ ፡ ዛሬ ፡ ይማልልኝ ፡ ብሎ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ይዞአል ፡ አሉት ። ፫፡ ሰሎሞንም ፡— እርሱ ፡ አካሄዱን ፡ ያሳመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከእርሱ ፡ አንዲት ፡ ጠጕር ፡ እንኳ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክፋት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሞታል ፡ አለ ። ፬፡ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ላከ ፡ ከመሠዊያውም ፡ አወረዱት ፡ መጥቶም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅ ፡ ነሣ ፡ ሰሎሞንም ፡— ወደ ፡ ቤትህ ፡ ሂድ ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፡ ዳዊትም ፡ የሚሞትበት ፡ ቀን ፡ ቀረበ ፡ ልጁንም ፡ ሰሎሞንን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ፡— ፪፡ እኔ ፡ የምድሩን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ እሄዳለሁ ፡ በርታ ፡ ሰውም ፡ ሁን ፤ የምታደርገውንና ፡ የምትሄድበትን ፡ ሁሉ ፡ ታስተውን ፡ ዘንድ ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሥርዓቱንና ፡ ትእዛዛቱን ፡ ፍርዱንና ፡ ምስክሩንም ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዱም ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ የአምላክህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ። ፬፡ ይኸውም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኔ ፡— ልጆችህ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፡ በፊቴም ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ በእውነት ፡ በፊቴ ፡ ቢሄዱ ፡ ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ሰው ፡ አይቈረጥ ብህም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ፭፡ አንተም ፡ ደግሞ ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ ሁለቱን ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራ ፡ አለቆች ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፡ የዬቴርንም ፡ ልጅ ፡ አሜሳይን ፡ ገድሎ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ታውቃለህ ፡ የሰልፋንም ፡ ደም ፡ በሰላም ፡ አፈሰሰ ፡ በወገቡም ፡ ባለው ፡ ድግና ፡ በእግሩ ፡ ባለው ፡ ጫማ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አኖረ ። ፮፡ አንተም ፡ እንደ ፡ ጥበብህ ፡ አድርግ ፡ ሽበቱንም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አታውርደው ። ከወንድምህ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ፊት ፡ በሸሸህ ፡ ጊዜ ፡ ቀርበውኛልና ፡ ለገለዓዳዊው ፡ ለቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ መልካም ፡ ቸርነት ፡ አድርግላቸው ፤ በማዕድህም ፡ ከሚበሉት ፡ መካከል ፡ ይሁኑ ። ፰፡ እኔም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ በሄድሁ ፡ ጊዜ ፡ ብርቱ ፡ እርግማን ፡ የረገመኝ ፡ የብራቂም ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የብንያማዊው ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፡ እነሆ ፡ በእንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገርሁ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበለኝ ፡ ወረደ ፤ እኔም ፡— በሰይፍ ፡ አልገድልህም ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምዩለታለሁ ። አንተ ፡ ግን ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ነህና ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ አትተወው ፡ የምታደርግበትንም ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ ሽበቱንም ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አውርደው ።

፲፡ ዳዊትም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ። ፲፩፡ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ። በኬብሮን ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። ፲፪፡ ሰሎሞንም ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ፡ መንግሥቱም ፡ እጅግ ፡ ጸና ።

፲፫፡ የአጒት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ እናት ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤህ ፡ መጣ ፡ እርስዋም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መምጣትህ ፡ በሰላም ፡ ነውን ? አለች ፡ እርሱም ፡— በሰላም ፡ ነው ፡ አለ ። ፲፬፡ ደግሞም ፡— ከአንቺ ፡ ጋር ፡ ጕዳይ ፡ አለኝ ፡ አለ ፡ እርስዋም ፡— ተናገር ፡ አለች ። ፲፭፡ እርሱም ፡— መንግሥቱ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንቺ ፡ ታውቂ ፡ ያለሽ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ሆኖ ፡ ለታላቁ ፡ መንግሥቴ ፡ ከእኔ ፡ አልፎ ፡ ለወንድሜ ፡ ሆኖአል ። ፲፮፡ አሁንም ፡ አንዲት ፡ ልመና ፡ እለምንሻለሁ ፡ አታሳፍረኝ ፡ አለ ። እርስዋም ፡— ተናገር ፡ አለችው ። ፲፯፡ እርሱም ፡— አያሳፍርሽ ፡ ምና ፡ ሱነማይቱን ፡ አቢሳን ፡ ይድርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንድትነግሪው ፡ አለም ፡ ንሻለሁ ፡ አለ ። ቤርሳቤህም ፡— መልካም ፡ ነው ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ለንጉሡ ፡ እነግረዋለሁ ፡ አለች ።

፲፱፡ ቤርሳቤህም ፡ የአዶንያስን ፡ ነገር ፡ ትነግረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ገባች ፡ ንጉሡም ፡ ሊቀበላት ፡ ተነሣ ፡ ሳማትም ፡ በዙፋኑም ፡ ተቀመጠ ፤ ለንጉሡም ፡ እናት ፡ ወንበር ፡ አስመጣላት ፡ በቀኙም ፡ ተቀመጠች ። ፳፡ እርስዋም ፡— አንዲት ፡ ታናሽ ፡ ልመና ፡ እለምንሃለሁ ፡ አታሳፍረኝ ፡ አለች ። ንጉሡም ፡— እናቴ ፡ ሆይ ፡ አላሳፍርሽምና ፡ ለምኚ ፡ አላት ። ፳፩፡ እርስዋም ፡— ሱነማይቱ ፡ አቢሳ ፡ ለወንድምህ ፡ ለአዶንያስ ፡ ትዳርለት ፡ አለች ። ፳፪፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ መልሶ ፡— ሱነማይቱን ፡ አቢሳን ፡ ለአዶንያስ ፡ ለምን ፡ ትለምኝለታለሽ ? ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ ነውና ፡ መንግሥትን ፡ ደግሞ ፡ ለምኚለት ፡ ካህኑም ፡ አብያታርና ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ ደግሞ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ናቸው ፡ አላት ። ፳፫፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡— አዶንያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ አለመናገሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፡ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ። ፳፬፡ አሁንም ፡ ያጸናኝ ፡ በአባቴም ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀመጠኝ ፡ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ ቤትን ፡ የሠራልኝ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ዛሬ ፡ አዶንያስ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደላል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማለ ። ፳፭፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ላከ ፡ እርሱም ፡ ወድቆ ፡ ሞተም ።

፳፮፡ ንጉሡም ፡ ካህኑን ፡ አብያታርን ፡— አንተ ፡ ዛሬ ፡ የሞት ፡ ሰው ፡ ነበርህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአምላክን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ተሸከምህ ፡ አባቴም ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ ተቀበልህ ፡ አልገደልህምና ፡ በዓናቶት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ እርሻህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ፳፯፡ በሴሎም ፡ በዔሊ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሰሎሞን ፡ አብያታርን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ አወጣው ።

፳፰፡ ለኢዮአብም ፡ ወሬ ፡ ደረሰለት ፡ ኢዮአብም ፡ አቤሴሎምን ፡ አልተከተለም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አዶንያስን ፡ ተከትሎ ፡ ነበር ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሽቶ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ። ፳፱፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ኢዮአብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሽቶ ፡ መሠዊያውን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ሰማ ፡ ሰሎሞንም ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡— ሂድ ፡ ውደቅበት ፡

፴፥ ብሎ ፡ አዘዘው ። በናያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ድንኳን ፡ መጥቶ ፡— ንጉሡ ፡— ውጣ ፡
ይልሃል ፡ አለው ፡ እርሱም ፡— በዚህ ፡ እሞታ
ለሁ ፡ እንጂ ፡ አልወጣም ፡ አለ ። በናያስም ፡—
ኢዮአብ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ የመለሰልኝም ፡
እንዲህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወሬ ፡
፴፩ አመጣ ። ንጉሡም ፡ አለው ፡— እንደ ፡ ነገረህ ፡
አድርግ ፡ ኢዮአብም ፡ በከንቱ ፡ ያፈሰሰውን ፡
ደም ፡ ከእኔና ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ታርቅ ፡ ዘንድ ፡
፴፪ ገድለህ ፡ ቀቢረው ። አባቴ ፡ ዳዊት ፡ ሳያውቅ ፡
ከእርሱ ፡ የሚሻሉትን ፡ ሁለቱን ፡ ጻድቃን ፡
ሰዎች ፡ የእስራኤልን ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ የኔ
ርን ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፡ የይሁዳንም ፡ ሠራዊት ፡
አለቃ ፡ የዬቴርን ፡ ልጅ ፡ አሜሳይን ፡ በሰይፍ ፡
ገድሎአልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ደሙን ፡ በራሱ ፡
፴፫ ላይ ፡ ይመልሰው ። ደማቸውም ፡ በእኢዮአብ ፡
ራስና ፡ በዘሩ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ለዘላለም ፡ ይመለስ ፡
ለዳዊት ፡ ግን ፡ ለዘሩና ፡ ለቤቱ ፡ ለዙፋኑም ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ለዘላለም ፡ ይሁን ።
፴፬ የዮዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደቀበት ፡
ገደለውም ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ ባለው ፡ በቤቱ ፡
፴፭ ተቀበረ ። ንጉሡም ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ የዮዳ
ሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ የሠራዊቱ ፡ አለቃ ፡
አደረገ ፡ በአብያታርም ፡ ፋንታ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶ
ቅን ፡ አደረገ ።
፴፮ ንጉሡም ፡ ልከ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራውና ፡—
በኢየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ ሠርተህ ፡ ተቀመጥ ፡
፴፯ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ አትውጣ ። በወጣህበትም ፡
ቀን ፡ የቄድሮንንም ፡ ፈፋ ፡ በተሻገርህበት ፡
ቀን ፡ ፈጽመህ ፡ እንድትሞት ፡ እወቅ ፡ ደምህ ፡
፴፰ በራስህ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፡ አለው ። ሳሚም ፡
ንጉሡን ፡— ነገሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡
ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ባሪያህ ፡ እንዲሁ ፡
ያደርጋል ፡ አለው ፡ ሳሚም ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ።
፴፱ ከሦስት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ከሳሚ ፡ ባሪያዎች ፡
ሁለቱ ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ መዓካ ፡
ልጅ ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ ኰበለሉ ፡ ሳሚንም ፡—
እነሆ ፡ ባሪያዎችህ ፡ በጌት ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡
፵ ነገሩት ። ሳሚም ፡ ተነሣ ፡ አህያውንም ፡ ጭኖ ፡
ባሪያዎቹን ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ወደ ፡
አንኩስ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ፡ ሳሚም ፡ ሄዶ ፡ ባሪያዎ
፵፩ ቹን ፡ ከጌት ፡ አመጣ ። ሰሎሞንም ፡ ሳሚ ፡ ከኢ
የሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ሄዶ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡
፵፪ ሰማ ። ንጉሡም ፡ ልከ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራና ፡—
ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ለመሄድ ፡ በወጣህ ፡ ቀን ፡
ፈጽመህ ፡ እንድትሞት ፡ እወቅ ፡ ብዬ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ አላስማልሁህምን ? ወይስ ፡ አላስመ
ሰክርሁብህምን ? አንተም ፡— ቃሉ ፡ መልካም ፡
፵፫ ነው ፡ ሰምቻለሁ ፡ አልኸኝ ። የእግዚአብሔርን ፡
መሐላ ፡ እኔስ ፡ ያዘዝሁህን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡
፵፬ ምን ፡ አልጠበቅህም ? አለው ። ንጉሡም ፡
ደግሞ ፡ ሳሚን ፡— አንተ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡
ላይ ፡ የሠራኸውን ፡ ልብህም ፡ ያሰበውን ፡ ክፋት ፡
ሁሉ ፡ ታውቃለህ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ክፋት ፡
ሀን ፡ በራስህ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ። ንጉሡ ፡ ፵፭
ሰሎሞን ፡ ግን ፡ የተባረከ ፡ ይሆናል ፡ የዳዊትም ፡
ዙፋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘላለም ፡ ይጸ
ናል ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ ፵፮
በናያስን ፡ አዘዘው ፡ ወጥቶም ፡ ወደቀበት ፡
ሞተም ። መንግሥትም ፡ በሰሎሞን ፡ እጅ ፡
ጸና ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ሰሎሞንም ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ፩
አማች ፡ ሆነ ፡ የፈርዖንን ፡ ልጅ ፡ አገባ ፡ ቤቱ
ንና ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌ
ም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ ቅጥር ፡ ሠርቶ ፡ እስኪ
ፈጽም ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከተማ ፡ አመ
ጣት ። እስከዚያም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብ ፪
ሔር ፡ ስም ፡ መቅደስ ፡ አልተሠራም ፡ ነበርና ፡
ሕዝቡ ፡ በኮረብታ ፡ ላይ ፡ በሱት ፡ መስገጃዎች ፡
ይሠዋ ፡ ነበር ። ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፫
ይወድድ ፡ ነበር ፡ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ሥር
ዓት ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ ብቻ ፡ በኮረብታ ፡ መስገጃ ፡
ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።
ገባዖን ፡ ዋና ፡ የኮረብታ ፡ መስገጃ ፡ ነበረችና ፡ ፬
ንጉሡ ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ሄደ ፡ ሰሎ
ሞንም ፡ በዚያ ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡
የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። እግዚአ ፭
ብሔርም ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ በሌሊት ፡ በሕ
ልም ፡ ተገለጠለት ፡ እግዚአብሔርም ፡— ምን ፡
እንድሰጥህ ፡ ለምን ፡ አለ ። ሰሎሞንም ፡ አለ ፡— ፮
እርሱ ፡ በፊትህ ፡ በእውነትና ፡ በጽድቅ ፡ በል
ብም ፡ ቅንነት ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡
ከባሪያህ ፡ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋር ፡ ታላቅ ፡ ቸር
ነት ፡ አድርገህለታል ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ በዙ
ፋኑ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ ልጅ ፡ ሰጥተህ ፡ ታላ
ቁን ፡ ቸርነትህን ፡ አቆይተህለታል ። አሁንም ፡ ፯
አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ባሪያህን ፡ በአ
ባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ እንግሠዝኸው ፡ እኔም ፡
መውጫንና ፡ መግቢያን ፡ የማላውቅ ፡ ታናሽ ፡
ብላቴና ፡ ነኝ ። ባሪያህም ፡ ያለው ፡ አንተ ፡ በመ ፰
ረጥኸው ፡ ሕዝብህ ፡ ስለ ፡ ብዛቱም ፡ ይቁጠርና ፡
ይመጠን ፡ ዘንድ ፡ በማይቻል ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡
መካከል ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በሕዝብህ ፡ ላይ ፡ ፱
መፍረድ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ መልካሙንና ፡ ክፉ
ውንም ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያህ ፡ አስተዋይ ፡
ልቡና ፡ ስጠው ፡ አለዚያማ ፡ በዚህ ፡ በታላቅ ፡
ሕዝብህ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ?
ሰሎሞንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ለመነ ፡ ነገሩ ፡ ፲
እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሰኘው ። እግዚአብ ፲፩
ሔርም ፡ አለው ፡— ፍርድን ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡
ለራስህ ፡ ማስተዋልን ፡ ለመንህ ፡ እንጂ ፡ ለራ
ስህ ፡ ብዙ ፡ ዘመናትን ፡ ባለጠግነትንም ፡ የጠላቶ
ችህንም ፡ ነፍስ ፡ ሳትለምን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለም
ነሃልና ፡ እነሆ ፡ አኔ ፡ እንደ ፡ ቃልህ ፡ አድርጌ ፲፪
ልሃለሁ ፡ እነሆ ፡ ማንም ፡ የሚመስልህ ፡ ከአ

ንተ ፡ በፊት ፡ እንደሌለ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡
እንዳይነሣ ፡ አድርጌ ፡ ጥበበኛና ፡ አስተዋይ ፡
፲፫ ልቡና ፡ ሰጥቼሃለሁ ። ደግሞም ፡ ከነገሥታት ፡
የሚመስልህ ፡ ማንም ፡ እንዳይኖር ፡ ያልለመን
ኸውን ፡ ባለጠግነትና ፡ ክብር ፡ ሰጥቼሃለሁ ።
፲፬ አባትህም ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ሥርዓቴንና ፡
ትእዛዜን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ የሄ
ድህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕድሜህን ፡ አረዝመዋለሁ ።
፲፭ ሰሎሞንም ፡ ነቃ ፡ እነሆም ፡ ሕልም ፡ ነበረ ፡
ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጥቶ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ቆመ ፡ የሚ
ቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረገ ፡ የደኅንነ
ትንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፡ ለባሪያዎቹም ፡
ሁሉ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ።
፲፮ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሁለት ፡ ጋለሞቶች ፡ ሴቶች ፡
፲፯ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ። አንደ
ኛይቱም ፡ ሴት ፡ አለች ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔና ፡
ይህች ፡ ሴት ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ እንኖራለን ፡
እኔም ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ በቤት ፡ ሳለሁ ፡ ወለ
፲፰ ድሁ ። እኔ ፡ ከወለድሁ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡
ይህች ፡ ሴት ፡ ደግሞ ፡ ወለደች ፡ እኛ ፡ በቤት ፡
ውስጥ ፡ አብረን ፡ ነበርን ፡ ከሁለታችንም ፡ በቀር ፡
፲፱ ማንም ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ። እርስ
ዋም ፡ በላዩ ፡ ስለ ፡ ተኛችበት ፡ የዚህች ፡ ሴት ፡
፳ ልጅ ፡ በሌሊት ፡ ሞተ ። እርስዋም ፡ በእኩለ
ሌሊት ፡ ተነሥታ ፡ እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡
ልጄን ፡ ከእጠጌ ፡ ወሰደች ፡ በብብትዋም ፡
አደረገችው ፡ የሞተውንም ፡ ልጅዋን ፡ በእኔ ፳፩
ብብት ፡ አደረገች ። ልጄንም ፡ አጠባ ፡ ዘንድ ፡
በማለዳ ፡ ብነሣ ፡ እነሆ ፡ ሞቶ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ብርሃን ፡ በነቡ ፡ ጊዜ ፡ ተመለከትሁት ፡
፳፪ እነሆም ፡ የወለድሁት ፡ ልጄ ፡ አልነበረም ። ሁለ
ተኛይቱም ፡ ሴት ፡— ደኅንኖው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡
ነው ፡ የሞተውም ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
አንቺ ፡ እንደምትዪው ፡ አይደለም ፡ አለች ።
ይህችም ፡— የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡
ደኅንኖውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አለች ፡ እን
ዲህም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።
፳፫ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡— ይህች ፡— ደኅ
ንኛው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሞተውም ፡ የአ
ንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፡ ያችኛይቱም ፡—
አይደለም ፡ የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡
ደኅንኛውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፡ አለ ።
፳፬ ንጉሡም ፡— ሰይፍ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፡ ሰይፍም ፡
፳፭ ይዘው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ መጡ ። ንጉ
ሡም ፡— ደኅንኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለሁለት ፡ ከፍላ
ችሁ ፡ ለአንዲቱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ለሁለተኛ
፳፮ ይቱም ፡ ሁለተኛውን ፡ ክፍል ፡ ስጡ ፡ አለ ። ደኅ
ንኛውም ፡ የነበራት ፡ ሴት ፡ አንጀትዋ ፡ ስለ ፡
ልጅዋ ፡ ናፍቆአልና ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ደኅንኛ
ውን ፡ ለእርስዋ ፡ ስጣት ፡ እንጂ ፡ አትግደል ፡
ብላ ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገረች ። ያችኛይቱ ፡ ግን ፡—
ይከፈል ፡ እንጂ ፡ ለእኔም ፡ ለእንቺም ፡ አይ
፳፯ ሁን ፡ አለች ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፡— ይህችኛ
ይቱ ፡ እናቱ ፡ ናትና ፡ ደኅንኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለእ
ርስዋ ፡ ስጡአት ፡ እንጂ ፡ አትግደሉት ፡ አለ ።
፳፰ ንጉሡም ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ሰሙ ፡ ፍርድን ፡ ለማድረግ ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ አይተዋልና ፡ ንጉሡን ፡ ፈሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፩
ላይ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ። የነበሩትም ፡ አለቆች ፡ እነ ፪
ዚህ ፡ ናቸው ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ካህኑ ፡ ዓዛርያስ ፡
፫ ጸሐፊዎቹም ፡ የሴባ ፡ ልጆች ፡ ኤልያፍናና ፡
አኪያ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊም ፡ የአሒሉድ ፡ ልጅ ፡
ኢዮሣፍጥ ፡ የዮዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ የሠራ ፬
ዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፡ ሳዶቅና ፡ አብያታርም ፡
ካህናት ፡ ነበሩ ፡ የናታንም ፡ ልጅ ፡ ዓዛርያስ ፡ ፭
የሹሞች ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፡ የናታንም ፡ ልጅ ፡
ዛቡድ ፡ የንጉሡ ፡ ኤማክሪና ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፡
አሒሳርም ፡ የቤት ፡ አዛዣ ፡ የዓብዳም ፡ ልጅ ፡ ፮
አዶኒራም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ።
ለንጉሡና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ቀለብ ፡ የሚ ፯
ሰጡ ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
ሹሞች ፡ ለሰሎሞን ፡ ነበሩት ። ከነሱም ፡ አንዱን ፡
ወር ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ይቀልቡ ፡ ነበር ።
፰ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡
በኤፍሬም ፡ የሑር ፡ ልጅ ፡ በማቃጽና ፡ በሸ ፱
ዓልቢም ፡ በቤትሳሚስና ፡ በኤሎንቤትሐናን ፡
የዴቀር ፡ ልጅ ፡ በአሩቦት ፡ የሑሴድ ፡ ልጅ ፡ ፲
ለእርሱም ፡ ሰኰትና ፡ የአፌር ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡
ነበረ ። ቦዶር ፡ አገር ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ የአሚ ፲፩
ናዳብ ፡ ልጅ ፡ እርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡
ማፈኑን ፡ አገባቸው ። ነበር ። ከቤትሳን ፡ ጀምሮ ፡ ፲፪
እስከ ፡ አቤልምሖላና ፡ እስከ ፡ ዮቅምዓም ፡ ማዶ ፡
ድረስ ፡ በታዕናክና ፡ በመጊዶ ፡ በጸርታንም ፡
አጠገብ ፡ በኢይዝራኤል ፡ በታች ፡ ባለው ፡ በቤ
ትሳን ፡ ሁሉ ፡ የአሒሉድ ፡ ልጅ ፡ በሜና ፡ ነበረ ፡
በራማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የጌበር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡ ለእ ፲፫
ርሱም ፡ በገለዓድ ፡ ያሉት ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የኢ
ያዕር ፡ መንደሮች ፡ ነበሩ ፡ ለእርሱም ፡ ደግሞ ፡
በባሳን ፡ በአርጎብ ፡ ዳርቻ ፡ ያሉት ፡ ቅጥርና ፡
የናስ ፡ መወርወሪያዎች ፡ የነበረባቸው ፡ ስድሳ ፡
ታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ነበሩበት ። በመሃናይም ፡ ፲፬
የሚ ፡ ልጅ ፡ አሒናዳብ ፡ በንፍታሌም ፡ አኪ ፲፭
ማአስ ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡
ባስማትን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ። በአሴርና ፡ በበዓ ፲፮
ሎት ፡ የኩሲ ፡ ልጅ ፡ በዓና ፡ በይሳኮር ፡ የፋሩዋ ፲፯
ልጅ ፡ ኢዮሣፍጥ ። በብንያም ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ፲፰
ሳሚ ፡ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎንና ፡ በባ ፲፱
ሳን ፡ ንጉሥ ፡ በዐግ ፡ አገር ፡ በገለዓድ ፡ አገር ፡
የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ጌበር ፡ ነበረ ፡ በዚያችም ፡ ምድር ፡
ላይ ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ ሹም ፡ ነበረ ።
ይሁዳና ፡ እስራኤልም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ፳
ብዛት ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ። በልተውም ፡ ጠጥተውም ፡
ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ነበር ። ሰሎሞንም ፡ ከወ ፳፩

ንዙ ፥ ጀምሮ ፥ እስከ ፥ ግብጽ ፥ ዳርቻ ፥ እስከ ፥ ፍል
ስጥኤም ፥ ድረስ ፥ በመንግሥታት ፥ ሁሉ ፥ ላይ ፥
ነግሦ ፥ ነበር ፥ ግብርም ፥ ያመጡለት ፥ ነበር ÷
በዕድሜውም ፡ ሙሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይገዙ ፡
፭ ፡ ነበር ። ለሰሎሞንም ፥ ለቀን ፥ ለቀኑ ፥ ቀለብ ፥
የሚሆን ፥ ሠላሳ ፡ ኮር ፡ መልካም ፡ ዱቄትና ፥
፮ ፡ ስድሳ ፡ ኮር ፡ መናኛ ፡ ዱቄት ÷ ከዋላና ፥ ከሚ
ዳቂ ፥ ከበረሀ ፥ ፍየልና ፥ ከሰቡ ፥ ወፎች ፥ በቀር ፡
አሥር ፡ ፍሪዳዎች ፥ ሀያም ፥ የተሰማሩ ፥ በራ
፯ ፡ ዎች ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ በጎች ፡ ነበረ ። ከወንዙ ፡
ወዲህ ፥ በሉት ፥ ነገሥታት ፥ ሁሉ ፥ ከወንዙም ፡
ወዲህ ፥ ባለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከተፍሳ ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጋዛ ፡ ድረስ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ፡ በዙ
ሪያውም ፡ ባለው ፡ በሁሉ ፡ ወገን ፡ ሰላም ፡ ሠኖ
፰ ፡ ለት ፡ ነበር ። በሰሎሞንም ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ይሁ
ዳና ፡ እስራኤል ፡ ከዳን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳ
ቤህ ፡ ድረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡
፱ ፡ በታች ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ። ለሰሎሞ
ንም ፡ በእርባ ፡ ሺህ ፡ ጋጥ ፡ የሚገቡ ፡ የሰረገላ ፡
ፈረሶች ፡ አሥራ ፡ ሁለትም ፡ ሺህ ፡ ፈረሰኞች ፡
፲ ፡ ነበሩት ። እነዚያም ፡ ሹሞች ፡ እያንዳንዱ ፡
በየወሩ ፥ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንንና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡
ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ማዕድ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ሁሉ ፡
ይቀልቡ ፡ ነበር ፡ ምንም ፡ አያጐድሉም ፡ ነበር ።
፲፩ ፡ እያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ለፈረሶቹና ፡ ለሰ
ጋር ፡ በቅሎች ፡ ገብስና ፡ ጭድ ፡ ወደ ፡ ስፍራ
ቸው ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።
፲፪ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡
ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ በባሕርም ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡
፲፫ ፡ አሸዋ ፡ የልብ ፡ ስፋት ፡ ሰጠው ። የሰሎሞንም ፡
ጥበብ ፡ በምሥራቅ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጥበ
፲፬ ፡ ብና ፡ ከግብጽ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ በለጠ ። ከሰውም ፡
ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ከኢይዝራኤላዊው ፡ ከኤታንና ፡
ከማሖል ፡ ልጆች ፡ ከሄማንና ፡ ከከልቀይ ፡ ከደ
ራልም ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኛ ፡ ነበረ ። በዙሪያውም ፡
፲፭ ፡ በሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዝናው ፡ ወጣ ። እርሱም ፡
ሦስት ፡ ሺህ ፡ ምሳሌዎች ፡ ተናገረ ፡ መኃልዩም ፡
፲፮ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ ነበረ ። ስለ ፡ ዛፍም ፡ ከሊባኖስ ፡
ገዝቶ ፡ ጀምሮ ፡ በቅጥር ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ እስከሚ
በቅለው ፡ እስከ ፡ ሂሶጵ ፡ ድረስ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፡
ደግሞም ፡ ስለ ፡ አውሬዎችና ፡ ስለ ፡ ወፎች ፡
ስለ ፡ ተንቀሳቃሾችና ፡ ስለ ፡ ዓሣዎች ፡ ይናገር ፡
፲፯ ፡ ነበር ። ከአሕዛብም ፡ ሁሉ ÷ ጥበቡንም ፡ ሰም
ተው ፡ ከነበሩ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡
የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ሰዎች ፡
ይመጡ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ የጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ለዳዊት ፡ በዘመኑ ፡
ሁሉ ፡ ወዳጁ ፡ ስለ ፡ ነበረ ÷ ሰሎሞን ፡ በአባቱ ፡
ፋንታ ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡
ሰምቶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ሰደደ ።
፪ ፡ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ኪራም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፫ ፡ ላከ ፦— እግዚአብሔር ፡ ከአባቴ ፡ በታች ፡ እስ
ኪዋልለት ፡ ድረስ ፡ በዙሪያው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡
ሰልፍ ፡ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ የአምላኩን ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ እንዳልቻለ ፡ አንተ ፡
ታውቃለህ ። ፬ አሁንም ፡ አምላኬ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በዙሪያዬ ፡ ካሉት ፡ ዐረፍት ፡ ሰጥቶኛል ፡
ጠላትም ፡ ክፉም ፡ ነገር ፡ የለብኝም ። እነሆም ÷ ፭
እግዚአብሔር ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡— በአንተ ፡
ፋንታ ፡ በዙፋንህ ፡ ላይ ፡ የማስቀምጠው ፡
ልጅህ ፡ እርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ ብሎ ፡
እንደ ፡ ነገረው ፡ ለአምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ ቤት ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ አስባለሁ ። አሁንም ፡ ፮
ከወገኔ ፡ እንደ ፡ ሲዶናውያን ፡ እንጨት ፡ መቁ
ረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ እንደሌለ ፡ ታውቃለህና ፡
የገባህ ፡ ዛፍ ፡ ከሊባኖስ ፡ ይቈርጡልኝ ፡ ዘንድ ፡
ባሪያዎችህን ፡ እዘዝ ፡ ባሪያዎቼም ፡ ከባሪያዎ
ችህ ፡ ጋር ፡ ይሁኑ ፡ የባሪያዎችህንም ፡ ዋጋ ፡
እንደ ፡ ተናገርኸው ፡ ሁሉ ፡ እሰጥሃለሁ ።
፯ ፡ ኪራምም ፡ የሰሎሞንን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡
እጅግ ፡ ደስ ፡ አለውና ፡— በዚህ ፡ በታላቅ ፡
ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጥበበኛ ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠ ፡
እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ይመስገን ፡ አለ ። ፰ ኪራ
ምም ፡— የላከህብኝን ፡ ሁሉ ፡ ሰማሁ ፡ ስለ ፡
ዝግባውና ፡ ስለ ፡ ጥዱ ፡ እንጨት ፡ ፈቃድህን ፡
ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ። ፱ ባሪያዎቼ ፡ ከሊባኖስ ፡ ፱
ወደ ፡ ባሕር ፡ ይጕትቱታል ፡ እኔም ፡ በታንኳ ፡
አድርጌ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እያንሳፈፍሁ ፡ አንተ ፡
እስከ ፡ ወሰንኸው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ አደርሰልሃ
ለሁ ÷ በዚያም ፡ እፈታዋለሁ ÷ አንተም ፡ ከዚያ ፡
ታስወስደዋለህ ። አንተም ፡ ፈቃዴን ፡ ታደር
ጋለህ ÷ ለቤተሙ ፡ ቀለብ ፡ የሚሆኑትን ፡ ትሰጠ
ኛለህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ላከ ። ፲ እንዲሁም ፡
ኪራም ፡ የዝግባውንና ፡ የጥዱን ፡ እንጨት ፡
እንደሚሻው ፡ ያህል ፡ ሁሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይሰ
ጠው ፡ ነበር ። ፲፩ ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ ስለ ፡
ቤቱ ፡ ቀለብ ፡ ሀያ ፡ ሺህ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡
ስንዴ ፡ ሀያ ፡ ኮርም ፡ ጥሩ ፡ ዘይት ፡ ይሰጠው ፡
ነበር ። ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ በየዓመቱ ፡
ይህን ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ። ፲፪ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡
ነገረው ፡ ለሰሎሞን ፡ ጥበብን ፡ ሰጠው ፡ በኪራ
ምና ፡ በሰሎሞንም ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ነበረ ፡
ሁለቱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋቡ ።
፲፫ ፡ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ገበሮቹን ፡
መርጦ ፡ አወጣ ፡ የገበሮቹም ፡ ቍጥር ፡ ሠላሳ ፡
ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ነበረ ። ፲፬ በየወሩም ፡ እያከታተለ ፡
ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ይሰድድ ፡
ነበር ፡ አንድ ፡ ወርም ፡ በሊባኖስ ፡ ሁለት ፡
ወርም ፡ በቤታቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። አዶ
ኒራምም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ። ፲፭ ሰሎሞንም ፡ ሰባ ፡
ሺህ ፡ ተሸካሚዎች ÷ ሰማንያ ፡ ሺህም ፡ በተራ
ራው ፡ ላይ ፡ የሚጠርቡ ፡ ጠራቢዎች ፡ ነበሩት ።
፲፮ ፡ ይኸውም ፡ በሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከተሾ
ሙት ፡ ከሦስት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡
ሌላ ፡ ነው ። ፲፯ ንጉሡም ፡ ታላላቅ ፡ ምርጥ ፡
ምርጥ ፡ ድንጋዮችን ፡ ይቈፍሩና ፡ ይጠርቡ ፡

እንጨት ፡ ከደነው ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድ ፲፯፡
ስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ኋለኛውን ፡ ሀያ
ውን ፡ ክንድ ፡ በገግባ ፡ እንጨት ፡ ጋረደው ።
በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ ያለውም ፡ መቅ ፲፱፡
ደስ ፡ ርዝመቱ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ። የቤቱ ፲፰፡
ንም ፡ ውስጥ ፡ በተጐበጐበና ፡ በፈንዛ ፡ አበባ ፡
በተቀረጸ ፡ ገግባ ፡ ለበጠው ፡ ሁሉም ፡ ገግባ ፡
ነበረ ፡ ድንጋዩም ፡ አልታየም ፡ ነበር ። በዚያም ፡ ፲፱፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡
ያኖር ፡ ዘንድ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱ
ሳኑን ፡ አበጀ ። የቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ርዝ ፳፡
መት ፡ ሀያ ፡ ክንድ ÷ ስፋቱም ፡ ሀያ ፡ ክንድ ÷
ቁመቱም ፡ ሀያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ በጥሩ ፡ ወር
ቅም ፡ ለበጠው ። በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ ፳፩፡
ከገግባ ፡ የተሠራ ፡ መሠዊያ ፡ አደረገ ፡ በጥሩ ፡
ወርቅም ፡ ለበጠው ። ቤቱንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ፳፪፡
በወርቅ ፡ ለበጠው ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡
ፊት ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡
ለበጠው ።
በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ውስጥ ፡ ቁመታቸው ፡ ፳፫፡
አሥር ፡ ክንድ ፡ የሆነ ፡ ከወይራ ፡ እንጨት ፡
ሁለት ፡ ኪሩብም ፡ ሠራ ። የኪሩብም ፡ እንደ ፳፬፡
ኖው ፡ ክንፍ ፡ አምስት ፡ ክንድ ÷ የኪሩብም ፡
ሁለተኛው ፡ ክንፍ ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፡
ከአንደኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ሁለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ አሥር ፡
ክንድ ፡ ነበረ ። ፳፭ ሁለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ አሥር ፡ ፳፮፡
ክንድ ፡ ነበረ ፡ ሁለቱም ፡ ኪሩቤል ፡ እንድ ፡
ልክና ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ ነበረ ። የአንዱ ፡ ፳፯፡
ኪሩብ ፡ ቁመት ፡ አሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ÷ የሁ
ለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ። ፳፰ ኪሩ ፳፱፡
ቤልንም ፡ በውስጠኛው ፡ ቤት ፡ አኖራቸው ፡
የኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸው ፡ ተዘርግተው ፡
ነበር ፡ የአንዱም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ አንደኛውን ፡
ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ÷ ዳሁለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡
ክንፍ ፡ ሁለተኛውን ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፡ የሁ
ለቱም ፡ ክንፎች ፡ በቤቱ ፡ መካከል ፡ እርስ ፡ በር ፴፡
ሳቸው ፡ ይነካኩ ፡ ነበር ። ኪሩቤልንም ፡ በወ ፴፩፡
ርቅ ፡ ለበጣቸው ።
በቤቱም ፡ ግንብ ፡ ሁሉ ፡ ዙሪያ ፡ በውስጥና ፡ ፴፪፡
በውጭ ፡ የኪሩቤልና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነ
ዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸ ። የቤቱንም ፡ ፴፫፡
ወለል ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ፡
ለቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ መግቢያ ፡ ከወይራ ፡ ፴፬፡
እንጨት ፡ ደጆች ፡ ሠራ ፡ መድረኩንና ፡ መቃ
ኖቹን ፡ ደፉንም ፡ አምስት ፡ ማዕዘን ፡ አደረገ ።
ሁለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከወይራ ፡ እንጨት ፡ ሠራ ፡ ፴፭፡
የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡
ምስል ፡ ቀረጸባቸው ÷ በወርቅም ፡ ለጠጣቸው ፡
ኪሩቤልንና ፡ የዘንባባውን ፡ ዛፍ ፡ በወርቅ ፡ ለበ
ጣቸው ። እንዲሁም ፡ ለመቅደሱ ፡ መግቢያ ፡ ፴፮፡
ከወይራ ፡ እንጨት ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ መቃን ፡
አደረገ ። ፴፯ ሁለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከጥድ ፡ እንጨት ፡ ፴፰፡
ሠራ ፡ አንዱ ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከሁ

ለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደረገ ÷ ሁለተኛውም ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከሁለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደ
፴፫ ረገ ። የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈንዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸባቸው ። በተቀረጸውም ፡
፴፬ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ። የውስጠኛውንም ፡ አደባባይ ፡ ቅጥር ፡ ሦስቱን ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ÷ አንዱንም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ሠራው ።
፴፮ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ዚፍ ፡ በሚባል ፡ ወር ፡
፴፰ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተመሠረተ ። በአሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ዓመት ፡ ቡል ፡ በሚባል ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ክፍሎቹና ፡ እንደ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ ተጨረሰ ። በሰባትም ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሠራው ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ ሰሎሞንም ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ በአሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሠራ ÷ የቤቱንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጨረሰ ። የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ ቤት ፡ የሚባል ፡ ቤትን ፡ ሠራ ፡ ርዝመቱንም ፡ መቶ ፡ ክንድ ÷ ስፋቱንም ፡ አምሳ ፡ ክንድ ÷ ቁመቱንም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ አደረገ ፤ የዝግባም ፡ እንጨት ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ በተሠሩ ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የዝግባ ፡ እንጨት ፡ አግዳሚ ፡ ሰረገሎች ፡ ነበሩ ። በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ በነበሩ ፡ አግዳሚዎች ፡ ቤቱ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ፤ አዕማዱም ፡ በአንዱ ፡ ተራ ፡ አሥራ ፡ አምስት ÷ በአንዱ ፡ ተራ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ እየሆኑ ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ነበሩ ። መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ነበሩ ÷ መስኮቶቹም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያዩ ፡ ነበር ። ደጆቹና ፡ መስኮቶቹም ፡ ሁሉ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ነበሩ ፤ መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ሆነው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያዩ ፡ ነበር ። አዕማዱም ፡ ያሉበትን ፡ ቤት ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱም ፡ አምሳ ፡ ክንድ ÷ ስፋቱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በእርሱም ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ አዕማድና ፡ መድረክ ፡ ያሉበት ፡ ወለል ፡ ነበረ ። ደግሞም ፡ የሚፈርድበት ፡ ዙፋን ፡ ያለበትን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አደረገ ። ከወለሉም ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡ ድረስ ፡ በዝግባ ፡ እንጨት ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ። ከፍርድ ፡ ሰቀላ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ÷ በሌላውም ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡ ሠራ ። እንደዚሁም ፡ ያለ ፡ ቤት ፡ ሰሎሞን ፡ ላገባት ፡ ለፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ቤት ፡ ሠራ ።

፱ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከመሠረቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጕልላቱ ፡ ድረስ ፡ በጥሩ ፡ በተጠረበና ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በልክ ፡ በተከረከመ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርተው ፡ ነበር ፤ በውጭውም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ። መሠረቱም ፡ አሥር ፡ ወይም ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ በሆነ ፡ በጥሩና ፡ በታላቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።
፲፩ በላዩም ፡ ልክ ፡ ሆኖ ፡ የተከረከመ ፡ ጥሩ ፡ ድንጋይና ፡ የዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ነበረ ። በታላቁም ፡ አደባባይ ፡ ዙሪያ ፡ የነበረው ፡ ቅጥር ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ቅጥርና ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወለል ፡ ሥስቱ ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ አንዱም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።
፲፫ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ልከ ፡ ኪራምን ፡ ከጢ
፲፫ ሮስ ፡ አስመጣ ። እርሱም ፡ ከንፍታሌም ፡ ወገን ፡ የነበረች ፡ የባል ፡ አልባ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ÷ አባቱም ፡ የጢሮስ ፡ ሰው ፡ ናስ ፡ ሠራተኛ ፡ ነበረ ፤ የናስንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ በብልሃትም ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጥቶ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ሠራ ። ሁለቱን ፡
፲፯ የናስ ፡ አዕማድ ፡ አደረገ ፤ የአንዱም ፡ ዓምድ ፡ ቁመት ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ÷ የዙሪያውም ፡ መጠን ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ የዓምዱም ፡ ውፍረት ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ÷ ውስጠ ፡ ክፍትም ፡ ነበረ ። ሁለተኛውም ፡ ዓምድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ። በሁለቱም ፡
፲፱ አዕማድ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ከፈሰሰ ፡ ናስ ፡ ሁለት ፡ ጕልላት ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ አምስት ፡ ክንድ ÷ የሁለተኛውም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።
፳ በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ እንደ ፡ መርበብ ፡ ሥራ ፡ አደረገ ፤ አንዱም ፡ መርበብ ፡ ለአንዱ ፡ ጕልላት ፡ ሁለተኛውም ፡ መርበብ ፡ ለሁለተኛው ፡ ጕልላት ፡ ነበረ ። ሮማኖችንም ፡ ሠራ ፤ በአንድ ፡ ጕልላት ፡ ዙሪያ ፡ በተራ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ÷ በአንድም ፡ መርበብ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ተራ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ ለሁለተኛው ፡ ጕልላት ፡ አደረገ ። በወለሉም ፡ አዕማድ ፡ በነበሩት ፡ ጕልላቶች ፡ ላይ ፡ በመርበቡ ፡ ሥራ ፡ አጠገብ ፡ ሮማኖቹን ፡ አደረገ ። አዕማዱንም ፡ በመቅደሱ ፡ ወለል ፡ አጠገብ ፡ አቆማቸው ። የቀኙንም ፡ ዓምድ ፡ አቁሞ ፡ ያቁም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፡ የግራውንም ፡ ዓምድ ፡ አቁሞ ፡ በለገ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ ሥራ ፡ ነበረ ። እንዲሁም ፡ የአዕማዱ ፡ ሥራ ፡ ተጨረሰ ።
፳፪ ከፈሰሰም ፡ ናስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አሥር ፡ ክንድ ÷ ቁመቱም ፡ አምስት ፡ ክንድ ÷ በዙሪያውም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የሆነ ፡ ክብ ፡ ሠራ ። ከከንፈሩም ፡ በታች ፡ ለአንድ ፡ ክንድ ፡ አሥር ፡ ለአንድ ፡ ክንድም ፡ አሥር ፡ ጉብጉቦች ፡ አዞረበት ፤ እርሱም ፡ በቀለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጉብጉቦቹ ፡ በሁለት ፡ ተራ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ቀልጠው ፡ ነበር ። ሸራውም ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ፡ ምስል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ከእነርሱም ፡ ሦስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ÷ ሦስቱም ፡ ወደ ፡

ምዕራብ ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ÷ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። ሸራውም ፡ በላያቸው ፡ ነበረ ÷ የሁሉም ፡ ጀርባቸው ፡ በስተ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ። ውፍረቱም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ፤ ከንፈሩም ፡ እንደ ፡ ጽዋ ፡ ከንፈር ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ አንደ ፡ ሱፍ ፡ አበባም ፡ ሆኖ ፡ ተከርክሞ ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ሺህም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ።
፳፯ አሥርም ፡ የናስ ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ መቀመጫ ፡ ርዝመት ፡ አራት ፡ ክንድ ÷ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ÷ ቁመቱም ፡ ሦስት ፡
፳፰ ክንድ ፡ ነበረ ። የመቀመጫውም ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፤ በክፈፎችም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡
፳፱ ሰንበር ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በክፈፎቹም ፡ መካከል ፡ በነበሩ ፡ ሰንበሮች ፡ ላይ ፡ አንበሳዎችና ፡ በሬዎች ፡ ኪሩቤልም ፡ ነበሩ ፡ እንዲሁም ፡ በክፈፎቹ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ ከአንበሳዎቹና ፡ ከበሬዎቹ ፡ በታች ፡ ሽኩራ ፡ የሚመስል ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር ። በየመቀመጫዎቹም ፡ ሁሉ ፡ አራት ፡ የናስ ፡ መንኰራኵሮች ፡ ነበሩባቸው ፡ መንኰራኵሮቹም ፡ የሚዘሩበትን ፡ የናስ ፡ ወስከምት ፡ ሠሩ ። ከመታጠቢያውም ፡ ሰን ፡ በታች ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ በምስል ፡ የፈሰሱ ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ። በክፈፉም ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ አንገት ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፡ አንገቱም ፡ ድቡልቡል ፡ ነበረ ÷ ቁመቱም ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ። በአንገቱም ፡ ላይ ፡ ቅርጽ ፡ ነበረበት ፡ ከፈፉ ፡ ግን ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ድቡልቡል ፡ አልነበረም ። አራቱም ፡ መንኰራኵሮች ፡ ከሰንበሮቹ ፡ በታች ፡ ነበሩ ፡ የመንኰራኵሮቹም ፡ ወስከምት ፡ በመቀመጫው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ፡ የመንኰራኵሩም ፡ ቁመት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ። የመንኰራኵሮቹም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሰረገላ ፡ መንኰራኵር ፡ ነበረ ÷ ወስከምቶቹና ፡ የመንኰራኵሮቹ ፡ ክፈፍ ፡ ቅትርቶቹም ፡ ወስ ከምቱም ፡ የሚገባበት ፡ ቢያዊ ፡ ሁሉ ፡ በምስል ፡ የፈሰሰ ፡ ነበር ። በእያንዳንዱም ፡ መቀመጫ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ደገፋዎች ፡ ነበሩ ፡ ደገፋዎቹም ፡ ከመቀመጫው ፡ ጋር ፡ ተገጥመው ፡ ነበር ። በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ ስንዝር ፡ የሚሆን ፡ ድቡልቡል ፡ ነገር ፡ ነበረ ፤ በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ መያዣዎችና ፡ ሰንበሮች ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይጋጠሙ ፡ ነበር ። በመያዣውና ፡ በሰንበሮቹ ፡ ላይ ፡ ኪሩቤልንና ፡ አንበሳዎችን ፡ የዘንባባውንም ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ መጠናቸው ፡ ቀረጸ ÷ በዙሪያውም ፡ ሽኩራ ፡ አደረገ ። እንዲሁ ፡ አሥሩን ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፡ ሁሉም ፡ በምስልና ፡ በመጠን ፡ በንድፍም ፡ ትክክሎች ፡ ነበሩ ።
፴፱ አሥሩንም ፡ የናስ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ሠራ ፡ አንዱ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አርባ ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ያኅሣ ፡ ነበር ፤ እያንዳንዱም ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በአሥሩም ፡ መቀመጫዎች ፡ ላይ ፡ በእያንዳንዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ። አምስቱንም ፡ መቀመጫዎች ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ÷ አምስቱንም ፡ በቤቱ ፡ ግራ ፡ አኖራቸው ፡ ነገሩንም ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

ኪራምም ፡ ምንቸቶችንና ፡ መጫሪያዎችን ፡ ድስቶችንም ፡ ሠራ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጨረሰ ። ሁለቱም ፡ አዕማድ ÷ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኩብ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጕልላቶች ÷ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ሁለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ የሚሸፍኑ ፡ ሁለት ፡ መርበቦች ÷ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ሁለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ መርበብ ፡ በሁለት ፡ በሁለት ፡ ተራ ፡ አድርጎ ፡ ለሁለቱ ፡ መርበቦች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ። አሥሩንም ፡ መቀመጫዎች ÷ በመቀመጫዎችም ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ አሥሩን ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ÷ አንዱንም ፡ ሁለ ÷ ከሁሉውም ፡ በታች ፡ የሚሆኑትን ፡ አሥሩ ፡ ሁለቱን ፡ በሬዎች ÷ ምንቸቶቹንም ÷ መጫሪያዎቹንም ÷ ድስቶቹንም ፡ አደረገ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ ነበረ ። በዮርዳኖስ ፡ ሜዳ ፡ በሱኮትና ፡ በጸርታን ፡ መካከል ፡ በለው ፡ በወፍራሙ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ አስፈሰሰው ። ሰሎሞንም ፡ ዕቃውን ፡ ሁሉ ፡ ሳያስመዝን ፡ አኖረ ፤ የናሱም ፡ ሚዛን ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።
፵፰ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረ ፡ ዘንጋ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ አሠራ ፤ የወርቁን ፡ መሠዊያ ፡ የገጹም ፡ ኅብስት ፡ የነበረበትን ፡ የወርቅ ፡ ገበታ ÷ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ አምስቱ ፡ በቀኝ ፡ አምስቱም ፡ በግራ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የተሠሩትንም ፡ መቅረዞች ÷ የወርቁንም ፡ አበባዎችና ፡ ቀንዲሎች ፡ መኰስ ተሪያዎችም ÷ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ ጽዋዎችና ፡ ጕጠቶች ÷ ድስቶቹንና ፡ ጭልፋዎቹንም ÷ ማንደጃዎቹንም ÷ ለውስጠኛውም ፡ ቤት ፡ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደጆች ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ደጆች ፡ የሚሆኑትን ፡ የወርቅ ፡ ማጠፊያዎች ፡ አሠራ ።
፶፩ እንዲሁ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጸመ ። አባቱም ፡ ዳዊት ፡ የቀደሰውን ÷ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ዕቃም ÷ ሰሎሞን ፡ አገባ ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በነበሩ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ አኖረው ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከጽዮን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የነገድ ፡ አለቆችን ፡ ሁሉ ÷ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የአ

በቶቻቸውን ፡ ቤቶች ፡ መሰፍንት ÷ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበ
፪ ሰብቸው ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኤታኒም ፡ በሚባል ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ተከማቹ ።
፫ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ መጡ ፡
፬ ካህናቱም ፡ ታቦቱን ፡ አነሡ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ÷ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ÷ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ አመጡ ፡ እነዚህንም ፡ ሁሉ ፡
፭ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ አመጡ ። ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የተሰበሰቡ ፡ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ሆነው ÷ ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ የማይቈጠሩትንና ፡ የማይመጠኑትን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡
፮ ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ። ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በቤቱ ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ ከኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ በታች ፡ ወደ ፡
፯ ነበረው ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ አመጡት ። ኪሩቤልም ፡ በታቦቱ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ነበር ፡ ኪሩቤልም ፡ ታቦቱንና ፡ መሎጊያዎቹን ፡ በስተ ፡ ላይ ፡ በኩል ፡ ሸፍነው ፡
፰ ነበር ። መሎጊያዎቹም ፡ ረጃጅሞች ፡ ነበሩ ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ፊት ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ሣይሾሩአቸው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፡ በውጭ ፡ ያለ ፡ ግን ፡ አያያቸውም ፡ ነበር ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡
፱ በዚያ ፡ አሉ ። በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ÷ እግዚአብሔርም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ÷ ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ከሁለቱ ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡
፲ አልነበረበትም ። ካህናቱም ፡ ከመቅደሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ደመናው ፡ የእግዚአብሔርን ፡
፲፩ ቤት ፡ ሞላው ። የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶ ፡ ነበርና ፡ ካህናቱ ፡ ከደመናው ፡ የተነሣ ፡ ለማገልገል ፡ ይቆሙ ፡
፲፪ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።
፲፫ ሰሎሞንም ፡ — እግዚአብሔር ፡ — በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎአል ፡ እኔም ፡ ለዘላለም ፡ የምትኖርበት ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ በእውነት ፡
፲፬ ሠራውልህ ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ መረቀ ፡ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።
፲፭፡፲፮ እርሱም ፡ አለ ፡— ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣሁበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ÷ በእርስዋም ፡ ቤት ፡ ይሠራልኝ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ አልመረጥሁም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ መርጫለሁ ÷ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ መርጫለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ በአፉ ፡ የተናገረ ፡ በእጁም ፡ የፈጸመ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
፲፯ ይመስገን ። አባቴም ፡ ዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡
፲፰ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ አሰበ ። እግዚአብሔርም ፡ አባቴን ፡ ዳዊትን ፡— ለስሜ ፡ ቤት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልብህ ፡ አስበሃልና ፡ ይህን ፡ በልብህ ፡ ማሰብህ ፡ መልካም ፡ አደረግህ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከወገብህ ፡
፲፱ የሚወጣው ፡ ልጅህ ፡ እርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አጸና ፡ እግዚአብሔርም ፡
፳ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ ተነሣሁ ÷ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥሁ ÷ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ሠራሁ ። ከግብጽም ፡
፳፩ ምድር ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላለበት ፡ ታቦት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ አደረግሁለት ።
፳፪ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ እያዩ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ። እንዲህም ፡
፳፫ አለ ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ÷ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ አምላክ ፡ የለም ፡ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ በፊትህ ፡ ለሚሄዱ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ÷ ለባሪያህ ፡
፳፬ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸውን ፡ ተስፋ ፡ የጠበቅህ ፡ በአፍህ ፡ ተናገርህ ÷ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀንም ፡ በእጅህ ፡ ፈጸምኸው ። አሁንም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡— አንተ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ሄድህ ፡ ልጆችህ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ አታጣም ፡ ብለህ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠኸውን ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ ጠብቅ ። አሁንም ÷ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ÷ ለባሪያህ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የተናገርኸው ፡ ቃል ÷ እባክህ ÷ ይጽና ።
፳፮ በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖራልን ? እነሆ ÷ ሰማይ ፡ ከሰማያትም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ሰማይ ፡ ይይዝህ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ ይልቁንስ ፡ እኔ ፡ የሠራሁት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ያንስ ! ነገር ፡ ግን ÷ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ባሪያህ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ተመልከት ÷ ዛሬም ፡ ባሪያህ ፡ በፊትህ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎትና ፡ ጥሪውን ፡ ስማ ፡ ባሪያህ ፡ ወደ ፡ ዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡— በዚያ ፡ ስሜ ፡ ይሆናል ፡ ወዳልኸው ፡ ስፍራ ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዓይኖችህ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የተገለጡ ፡ ይሁኑ ። ባሪያህና ፡ ሕዝብህ ፡ እስራኤል ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ልመና ፡ ስማ ፡ በማደሪያህ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፡ ሰምተህም ፡ ይቅር ፡ በል ።
፴ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢበድል ÷ በላዩም ፡ መሐላ ፡ ቢጫን ÷ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በመሠዊያህ ፡ ፊት ፡ ቢምል ÷ በሰማይ ፡ ስማ ፡ አድርግም ፡ በባሪያዎችህም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ሁን ፡ በበደለኛውም ፡ ላይ ፡ ፍረድ ÷ መንገዱ ፡

ንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መልስበት ፡ ንጹሑን ፡ አጽድቀው ÷ እንደ ፡ ጽድቁም ፡ ክፈለው ።
፴፩ ሕዝብህ ፡ እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ድል ፡ በተመቱ ፡ ጊዜ ÷ ወደ ፡ አንተ ፡ ቢመለሱ ÷ ስምህንም ፡ ቢያከብሩ ÷
፴፪ በዚህም ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩና ፡ ቢለምኑህ ÷ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፡ የሕዝብህንም ፡ የእስራኤልን ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደ ፡ ሰጠሃት ፡ ምድር ፡ መልሰኸው ።
፴፫ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰማይ ፡ በተዘጋ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብም ፡ ባልዘነበ ፡ ጊዜ ÷ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቢጸልዩ ÷ ስምህንም ፡ ቢያከብሩ ÷ ስለመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ቢመለሱ ÷
፴፬ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፡ የሚጸሩበትንም ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ በማሳየት ፡ የባሪያዎችህንና ፡ የሕዝብህን ፡ የእስራኤልን ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ለሕዝብህም ፡ ርስት ፡ አድርገህ ፡ ለሰጠሃት ፡ ምድር ፡ ዝናብ ፡ ስጥ ።
፴፭ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ÷ ወይም ፡ ቸንፈር ÷ ወይም ፡ ዋግ ÷ ወይም ፡ አረማሞ ÷ ወይም ፡ አንበጣ ÷ ወይም ፡ ኩብኩባ ፡ ቢሆን ÷ የሕዝብህም ፡ ጠላት ፡ የአገሩን ፡ ቀበሌዎች ፡ ከብበ ፡ ቢያስጨንቃቸው ÷ መቅሠፍትና ፡ ደዌ ፡ ሁሉ ፡ ቢሆን ÷
፴፮ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የልቡን ፡ ሕመም ፡ እውቆ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ቢጸልይ ÷ እጆቹንም ፡ ወደ ፡ ዚህ ፡ ቤት ፡ ቢዘረጋ ÷ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠሃት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩህ ፡ ዘንድ ፡ በማደሪያህ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ÷ ይቅርም ፡ በል ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ ታውቃለህና ፡ ለሥራው ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ ስጠው ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡ መጠን ፡ ክፈለውና ፡ ስጠው ።
፴፰ ከሕዝብህም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ያልሆነ ፡ እንግዳ ፡ ታላቁን ፡ ስምህን ÷ ብርቱይቱንም ፡ እጅህን ÷ የተዘረጋውንም ፡ ክንድህን ፡ ሰምቶ ፡ ስለ ፡ ስምህ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ÷ መጥቶም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ÷ አንተ ፡ በማደሪያህ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፡ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ስምህን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕዝብህም ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ይፈሩህ ፡ ዘንድ ÷ በዚህም ፡ በሠራሁት ፡ ቤት ፡ ስምህ ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ÷ እንግዳው ፡ የሚለምንህን ፡ ሁሉ ፡ አድርግ ።
፴፱ ሕዝብህም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመውጋት ፡ አንተ ፡ በምትልካቸው ፡ መንገድ ፡ ቢወጡ ÷ አንተም ፡ ወደ ፡ መረጥሃት ፡ ከተማ ፡ እኔም ፡ ለስምህ ፡ ወደ ፡ ሠራሁት ፡ ቤት ፡ ለእግዚአብሔር ፡
፵ ቢጸልዩ ÷ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በሰማይ ፡ ስማ ÷ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ።
፵፩ የማይበድልም ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንተን ፡ ቢበድሉ ÷ ተቈጥተህም ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ አሳልፈህ ፡ ብትሰጣቸው ፡ ሩቅ ፡ ወይም ፡ ቅርብ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ጠላቶች ፡ አገር ፡ ቢማረኩም ÷
፵፪ በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ሆነው ፡ በልባቸው ፡ ንስሐ ፡ ቢገቡ ÷ በማረኩዎቹም ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ተመልሰው ፡— ኃጢአት ፡ ሠርተናል ። በድለንማል ÷ ክፋንም ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ ቢለምኑህ ÷ በማረኩአቸው ፡ በጠላቶቻቸው ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ቢመለሱ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደ ፡ ሰጠሃት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ወደ ፡ መረጥሃትም ፡ ከተማ ፡ ለስምህም ፡ ወደ ፡ ሠራሁት ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩ ÷ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በማደሪያህ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ÷ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ለሕዝብህ ፡ ኃጢአት ፡ ለበደሉህም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ለሚራሩላቸውም ፡ በፊት ፡ ይራሩላቸው ፡ ዘንድ ፡ በማረኩአቸው ፡ ፊት ፡ ምሕረት ፡ ስጣቸው ። ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከብረት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ያወጣሃቸው ፡ ሕዝብህና ፡ ርስትህ ፡ ናቸውና ። በጠሩህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ትሰማቸው ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያህና ፡ ለሕዝብህ ፡ ለእስራኤል ፡ ልመና ፡ ዓይኖችህ ፡ የተገለጡ ፡ ይሁኑ ። ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ አባቶቻችንን ፡ ከግብጽ ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ በባሪያህ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፡ ርስት ፡ ይሆኑህ ፡ ዘንድ ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ለይተሃቸዋልና ።
፵፫ ሰሎሞንም ፡ ይህችን ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸልዮ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ÷ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ እጁንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርግቶ ፡ ነበርና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ተነሣ ። ቆሞም ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲመርቅ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እንደ ፡ ተናገረው ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ዕረፍትን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ በባሪያው ፡ በሙሴ ፡ ከሰጠው ፡ ከመልካም ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አልወደቀም ። እምላክችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አይተወን ÷ አይጣለንም ፡ በመንገዱም ፡ ሁሉ ፡ እንሄድ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችንም ፡ ያዘዛትን ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡ ትእዛዙንም ፡ እንጠብቅ ፡ ዘንድ ÷ ልባችንን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ያዘንብል ፡ ዘንድ ። ለባሪያውና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ፍርድን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የለመንኋት ፡ ቃል ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀረበች ፡ ትሁን ፡ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ከእርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ። እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀን ፡ በፈቃዱ ፡ ትሄዱ ፡ ዘንድ ÷ ትእዛዙንም ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ÷ ከእምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ልባችሁ ፡ ፍጹም ፡ ይሁን ።
፷ ንጉሡም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

፰፫፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ በሬዎችና ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ሺህ ፡ በጎች ፡ አቀረበ ። ንጉሡና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ እን
፰፬፡ ዲሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀደሱ ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ የናሱ ፡ መሠዊያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእህሉን ፡ቁርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በዚያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእህሉን ፡ ቁርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ ቀደሰ ።
፰፭፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ሰሎሞን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ በእምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓሉን ፡ አደረጉ ። በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናበተ ፡ እነርሱም ፡ ንጉሡን ፡ መረቁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለባሪያው ፡ ለዳዊትና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ሁሉ ፡ በልባቸው ፡ ተደስተው ፡ ሐሤትም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ኄዱ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩፡ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የንጉሡን ፡ ቤትና ፡ ሰሎሞን ፡ የወደደውን ፡ የልቡን ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
፪፡ እግዚአብሔር ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡
፫፡ ተገለጠለት ፡ ዳግመኛ ፡ ተገለጠለት ። እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦— በፊቴ ፡ የጸለይኸውን ፡ ጸሎትህንና ፡ ልመናህን ፡ ሰምቻለሁ ፡ ለዘላለምም ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የሠራኸውን ፡ ቤት ፡ ቀድሻለሁ ፡ ዓይኖቼና ፡ ልቤም ፡
፬፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ይሆናሉ ። ዳዊትም ፡ አባትህ ፡ በየዋህ ፡ ልብና ፡ በቅንነት ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ በፊቴ ፡ ብትሄድ ፡ ያዘዝሁህንም ፡ ሁሉ ፡ ብታደርግ ፡ ሥርዓቴንም ፡ ፍርዴንም ፡ ብትጠብቅ ፡ እኔ ፡— ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ከዘርህ ፡ ሰው ፡ አታጣም ፡ ብዬ ፡ ለአባትህ ፡ ለዳዊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ የመንግሥትህን ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘላለም ፡
፮፡ አጸናለሁ ። እናንተና ፡ ልጆቻችሁ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ብትመለሱ ፡ የሰጠኋችሁንም ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዓቴን ፡ ባትጠብቁ ፡ ሄዳችሁም ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፡ ብትሰግዱ ፡
፯፡ ላቸውም ፡ እስራኤልን ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ለስሜም ፡ የቀደስሁትን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ከፊቴ ፡ እጥለዋለሁ ፡ እስራኤልም ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ ይሆ
፰፡ ናሉ ። ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውም ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ባድማ ፡ ይሆናል ፡ በዚያም ፡ የሚያልፍ ፡ ሁሉ ፡ እያፍዋጨ ፡— እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ አገርና ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ? ብሎ ፡ ይደነቃል ። መልሰውም ፡— ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አበቶቻቸውን ፡ ያወጣውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፡ ስለ ፡ ሰገዱላቸውም ፡ ስለ ፡ አመለኩአቸውም ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አመጣባቸው ፡ ይሉሉ ።

፲፡ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ሁለቱን ፡ ቤቶች ፡ የሠራበት ፡
፲፩፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በገሊላ ፡ ምድር ፡ ያሉትን ፡ ሀያ ፡ ከተሞች ፡ ለኪራም ፡ ሰጠው ። የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ የሚሻውን ፡ ያህል ፡ የዝግባና ፡ የጥድ ፡ እንጨት ፡ የሚሻውንም ፡ ያህል ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ።
፲፪፡ ኪራምም ፡ ሰሎሞን ፡ የሰጠውን ፡ ከተሞች ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከጢሮስ ፡ ወጣ ፡ ደስም ፡ አላሰኙትም ።
፲፫፡ እርሱም ፡— ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ የሰጠኸኝ ፡ እነዚህ ፡ ከተሞች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ? አለ ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የክቡል ፡ አገር ፡ ተብለው ፡ ተጠሩ ።
፲፬፡ ኪራምም ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ለንጉሡ ፡ ላከ ።

፲፭፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ ሚሎንም ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ ሐጾርንም ፡ መጊዶንም ፡ ጌዝርንም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ገባሮችን ፡ መልምሎ ፡ ነበር ።
፲፮፡ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ወጥቶ ፡ ጌዝርን ፡ ይዞ ፡ ነበር ፡ በእሳትም ፡ አቃጥሎ ፡ በከተማም ፡ የኖሩትን ፡ ከነዓናውያን ፡ ገድሎ ፡ ነበር ፡ ለልጁም ፡ ለሰሎሞን ፡ ሚስት ፡ ትሎት ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቶአት ፡ ነበር ።
፲፯፡ ሰሎሞንም ፡ ጌዝርን ፡ ፡ የታችኛውንም ፡ ቤት ፡ ሖሮን ፡ ፡ በዕላትንም ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ አገር ፡
፲፰፡ ያለችውን ፡ ተድሞርን ፡ ለሰሎሞንም ፡ የነበሩትን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ የሰረገላ ውንም ፡ ከተሞች ፡ የፈረሰኞችንም ፡ ከተሞች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሊባኖስም ፡ በመንግሥቱም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ሰሎሞን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የወደደውን ፡ ሁሉ ፡ ሠራ ።
፲፱፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ያልነበሩትን ፡ ከአሞራውያንና ፡ ከኬጠያውያን ፡ ከፈሬዛውያን ፡ ከኤዊያውያንና ፡ ከኢያቡሳውያን ፡ የቀሩትን ፡
፳፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያጠፉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልቻሉትን ፡ በኋላቸው ፡ የቀሩትን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገባሮች ፡ አድርጎ ፡ መለመላቸው ።
፳፩፡ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ በሬያ ፡ አላደረገም ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ሰልፈኞች ፡ ሎሌዎችም ፡ መሳፍንትም ፡ አለቆችም ፡ የሰረገሎችና ፡ የፈረሶች ፡ ባለደራሶች ፡ ነበሩ ።

፳፪፡ ሰሎሞንም ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሠራ ፡ ተኛውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያዝዙ ፡ አለቆች ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ነበሩ ።
፳፫፡ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ሰሎ

ሞን ፡ ወደ ፡ ሠራላት ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ወጣች ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሚሎን ፡ ሠራ ።
፳፬፡ ሰሎሞንም ፡ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የሚቃጠለውንና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሰጣን ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ። ቤቱንም ፡ ጨረሰ ።
፳፮፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በኤሎት ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በጽዮንጋብር ፡ መርከቦችን ፡ ሠራ ።
፳፯፡ ኪራምም ፡ በእነዚያ ፡ መርከቦች ፡ ከሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ጋር ፡ የባሕሩን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁ ፡
፳፰፡ መርከበኞች ፡ ባሪያዎቹን ፡ ሰደደ ። ወደ ፡ አፌርም ፡ መጡ ፡ ከዘኢያም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ መክሊተ ፡ ወርቅ ፡ ወሰዱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ይዘው ፡ መጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩፡ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ዝና ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡
፪፡ በእንቆቅልሽ ፡ ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ። በግመሎችም ፡ ላይ ፡ ሽቱና ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ አስጭና ፡ ከታላቅ ፡ ኀይል ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባች ፣ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ በልብዋ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ አጫወተችው ። ሰሎሞንም ፡
፫፡ የጠየቀችውን ፡ ሁሉ ፡ ፈታላት ፡ ሊፈታላት ፡ ያልቻለውና ፡ ከንጉሡ ፡ የተሰወረ ፡ ነገር ፡
፬፡ አልነበረም ። የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶትም ፡ የነበረውን ፡ ቤት ፡
፭፡ የማዕዱንም ፡ መብል ፡ የብላቴኖቹንም ፡ አቀማመጥ ፡ የሎሌዎቹንም ፡ አሠራር ፡ አለባበሳቸውንም ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊዎቹንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚያሳርገውን ፡ መሥዋዕት ፡
፮፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ አልቀረላትም ። ንጉሡንም ፡ አለችው ፦— ስለ ፡ ነገርህና ፡ ስለ ፡ ጥበብህ ፡
፯፡ በአገሬ ፡ ሳለሁ ፡ የሰማሁት ፡ ዝና ፡ እውነት ፡ ነው ። እኔም ፡ መጥቼ ፡ በዓይኔ ፡ እስካይ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንሁም ፡ ነበር ፡ እነሆም ፡ እኩሌታውን ፡ አልነገሩኝም ፡ ነበር ፡ ጥበብህና ፡ ሥራህ ፡
፰፡ ከሰማሁት ፡ ዝና ፡ ይበልጣል ። በፊትህ ፡ ሁል ጊዜ ፡ የሚቆሙ ፡ ጥበብህንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎችህና ፡ እነዚህ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።
፱፡ አንተን ፡ የወደደ ፡ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመጠህ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለዘላለም ፡ ወድዶታልና ፡ ስለዚህ ፡ ፍትህና ፡ ፍርድ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ አስነሣህ ። ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ ሰጠችው ። የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠችው ፡ ያለ ፡ የሽቱ ፡ ብዛት ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አልመጣም ፡ ነበር ።

፲፩፡ ከአፌርም ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ የኪራም ፡ መርከቦች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሰንደል ፡ እንጨትና ፡
፲፪፡ የከበረ ፡ ዕንቍ ፡ ከአፌር ፡ አመጡ ። ንጉሡም ፡ ከሰንደሉ ፡ እንጨት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ለንጉሡ ፡ ቤት ፡ መከታ ፡ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡ በገና ፡ አደረገ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የሰንደል ፡ እንጨት ፡ ከቶ ፡ አልመጣም ፡ አልታየምም ።
፲፫፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ከሰጣት ፡ ሌላ ፡ የወደደችውን ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱም ፡ የለመነችውን ፡ ሁሉ ፡ ለሰባ ፡ ንግሥት ፡ ሰጣት ። እርስዋም ፡ ተመልሳ ፡ ከባሪያዎችዋ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ምድርዋ ፡ ሄደች ።

፲፬፡ ግብርም ፡ የሚያስገብሩ ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎችም ፡ የዓረብም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ የምድርም ፡ ሹማምት ፡ ከሚያወጡት ፡ ሌላ ፡ በየዓመቱ ፡ ለሰሎሞን ፡ የሚመጣለት ፡ የወርቅ ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡
፲፭፡ ነበረ ። ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፡ በአንዱም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።
፲፮፡ ከጥፍጥፍም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፡ በአንዱም ፡ ጋሻ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ምናን ፡ ነበረ ፤ ንጉሡም ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።
፲፯፡ ንጉሡም ፡ ዳግሞ ፡ ከዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ታላቅ ፡ ዙፋን ፡ አሠራ ፡ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።
፲፰፡ ወደ ፡ ዙፋንም ፡ የሚያስሄዱ ፡ ስድስት ፡ እርከኖች ፡ ነበሩ ፡ በስተ ፡ ኋላውም ፡ ያለው ፡ የዙፋኑ ፡ ራስ ፡ ክብ ፡ ነበረ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ በመቀመጫው ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ የክንድ ፡ መደገፊያዎች ፡ ነበሩበት ፡ በመደገፊያዎቹም ፡ አጠገብ ፡
፲፱፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ ቆመው ፡ ነበር ። በስድስቱም ፡ እርከኖች ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተሠራም ። ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የሚጠጣበት ፡
፳፩፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ የተባለውም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ እንጂ ፡ ብር ፡ አልነበረም ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብር ፡ ከቶ ፡ አያቄጠርም ፡ ነበር ። ለንጉሡም ፡
፳፪፡ ከኪራም ፡ መርከቦች ፡ ጋር ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ፡ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ዓመትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ዝሆንም ፡ ጥርስ ፡ ዝንጀሮና ፡ ዝንጉርጉር ፡ ወፍ ፡ ይዘው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

፳፫፡ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በባለጠግነትና ፡ በጥበብ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በልጦ ፡ ነበር ።
፳፬፡ ምድርም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ያኖረለትን ፡ ጥበቡን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ የሰሎሞንን ፡
፳፭፡ ፊት ፡ ይመኝ ፡ ነበር ። ከእነርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ በዓመት ፡ በዓመቱ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ልብስና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡

ሽቱም ÷ ፈረሶችና ፡ በቅሎች ፡ እየያዘ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ።

፲፩ ሰሎሞንም ፡ ለረዣሎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሰበሰበ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰረገሎች ÷ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህም ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ፡ በሰረገሎችም ፡ ከተሞች ፡ ከንጉሡም ፡ ጋር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ። ንጉሡም ፡ ብሩን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፡ የዝግባም ፡ እንጨት ፡ ብዛት ፡ በቁላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ ሆነ ። ሰሎሞንም ፡ ፈረሶችን ፡ ከግብጽና ፡ ከቀዌ ፡ አገር ፡ አስመጣ ፡ የንጉሡም ፡ ነጋዴዎች ፡ በገንዘብ ፡ እየገዙ ፡ ከቀዌ ፡ ያመጡአቸው ፡ ነበር ። አንዱም ፡ ሰረገላ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፡ አንዱም ፡ ፈረስ ፡ በመቶ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ከግብጽ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ለኬጢያውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በእጃቸው ፡ ያመጡላቸው ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ሌላ ፡ በሞዓብያውያንና ፡ በአሞናውያን ፡ በኤዶማውያን ፡ በሲዶናውያንና ፡ በኬጢያውያን ፡ ሴቶች ፡ በብዙ ፡ እንግዶች ፡ ፍቅር ፡ ተነደፈ ።

፪ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ — አምላክነቶቻቸውን ፡ ትከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ልባችሁን ፡ በእውነት ፡ ያዘነብላሉና ፡ ወደ ፡ እናርሱ ፡ አትግቡ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይግቡ ፡ ካላቸው ፡ ብእሕዛብ ፡ ከእነዚህ ፡ ጋር ፡ ሰሎሞን ፡ በፍቅር ፡ ተጣበቀ ። ለእርሱም ፡ ወይዛዝር ፡ የሆኑ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሚስቶች ፡ ሦስት ፡ መቶም ፡ ቁባቶች ፡ ነበሩት ፡ ሚስቶቹም ፡ ልቡን ፡ አዘነበሉት ።

፬ ሰሎሞንም ፡ ሲሸመግል ፡ ሚስቶቹ ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አዘነበሉት ፡ የአባቱ ፡ የዳዊት ፡ ልብ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሰሎሞን ፡ ልቡ ፡ እንዲሁ ፡ አልነበረም ።

፮ ሰሎሞንም ፡ የሲዶናውያንን ፡ አምላክ ፡ አስታሮትን ÷ የአሞናውያንንም ፡ ርኵሰት ፡ ሚልኮምን ፡ ተከተለ ። ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፋ ፡ ነገርን ፡ አደረገ ÷ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመከተል ፡ ፍጹም ፡ አልሆነም ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ ለሞዓብ ፡ ርኵሰት ፡ ለከሞሽ ÷ ለአሞንም ፡ ልጆች ፡ ርኵሰት ፡ ለራት ፡ በሉ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መስገጃ ፡ ሠራ ። ለአማልክቶቻቸው ፡ ዕጣን ፡ ለሚያጥኑ ፡ መሥዋዕትም ፡ ለሚሠዉ ፡ ለአንግዶች ፡ ሚስቶቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

፱፡፲ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ከተገለጠለት ÷ ሌሎችንም ፡ አማልክት ፡ እንዳይከተል ፡ ከዘዘው ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ አርቆአልና ÷ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ አልጠበቀምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰሎሞንን ፡ ተቈጣ ።

፲፩ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፡ አለው ፡ — ይህን ፡ ሠርተሃልና ÷ ያዘዝሁብህንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንና ፡ ሥርዓቴን ፡ አልጠበቅህምና ፡ መንግሥትህን ፡ ከአንተ ፡ ቀዳጅ ፡ ለባሪያህ ፡ አሰጠዋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከልጅህ ፡ እጅ ፡ አቀድደዋለሁ ፡ እንጂ ፡ ሰለ ፡ አባትህ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ በዘመንህ ፡ አላደርግም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊትና ፡ ስለ ፡ መረጥኋት ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለልጅህ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ አሰጣለሁ ፡ እንጂ ፡ መንግሥቱን ፡ ሁሉ ፡ አልቀድድም ።

፲፬ እግዚአብሔርም ፡ ከኤዶምያስ ፡ ንጉሥነት ፡ ዘር ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰው ፡ ሃዳድን ፡ ጠላት ፡ አድርጎ ፡ በሰሎሞን ፡ ላይ ፡ አስነሣው ። ኤዶምያውያን ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የኤዶምያስን ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ እስኪገድሉ ፡ ድረስ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበርና ፡ ዳዊት ፡ በኤዶምያስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሠራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ ተወጣተው ፡ የሞቱትን ፡ ሊቀብር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የኤዶምያስንም ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፡ ሃዳድ ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ ሃያ ፡ ድና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ የአባቱ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኰብልለው ፡ ነበር ። ከምድያምም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ፋራን ፡ መጡ ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ከፋራን ፡ ሰዎች ፡ ወሰዱ ። ወደ ፡ ግብጽም ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፡ እርሱም ፡ ቤት ፡ ሰጥቶ ፡ ቀለብ ፡ ዳረገው ፡ ምድርም ፡ ሰጠው ። የሚስቱንም ፡ የአቲፔፍቱን ፡ የቴቁምናስን ፡ እኅት ፡ እስኪያጋባው ፡ ድረስ ፡ ሃዳድ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ባለም ዋል ። ዘነ ። የቴቁምናስ ፡ እኅት ፡ ጌንባትን ፡ ወለደችለት ፡ ቴቁምናስም ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ አሳደገችው ፡ ጌንባትም ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ በፈርዖን ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ነበረ ። ሃዳድም ፡ በግብጽ ፡ ሳለ ፡ ዳዊት ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ እንዳንቀላፋ ፡ የሠራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ÷ ሃዳድ ፡ ፈርዖንን ፡ — ወደ ፡ አገሬ ፡ እሄድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብተኝ ፡ አለው ። ፈርዖንም ፡ — እነሆ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አገርህ ፡ መሄድ ፡ የፈለግህ ፡ ምን ፡ አጥተህ ፡ ነው ? አለው ። እርሱም ፡ — አንዳች ፡ አላጣሁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ሃዳድም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። ሃዳድም ፡ ያደረገው ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እስራኤልን ፡ አስጨነቀ ፡ በኤዶምያስም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

፲፫ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከጌታው ፡ ከሱባ ፡ ንጉሥ ፡ ከአድርአዛር ፡ የኰበለለውን ፡ የኤልያዳን ፡ ልጅ ፡ ሬዞንን ፡ ጠላት ፡ አድርጎ ፡ አስነሣበት ። ዳዊትም ፡ የሱባን ፡ ሰዎች ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፡ ሬዞን ፡ ሰዎችን ፡ ሰብስቦ ፡ የሞኖሩ ፡ አለቃ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ደማስቆም ፡ ሄዱ ÷ በዚያም ፡ ተቀመጡ ፡ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ አነገሡት ። ሃዳድም ፡ ከደረገው ፡ ክፋት ፡ ሌላ ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤል ፡ ጠላት ፡ ነበረ ።

ከሳረራ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያ ፡ የኤፍሬማዊው ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ በመፅ ፡ እናቱም ፡ ጽሩፋ ፡ የተባለች ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ ነበረች ። በንጉሡም ፡ ያመፀበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሰሎሞን ፡ ሚሎን ፡ ሠራ ÷ የአባቱንም ፡ የዳዊትን ፡ ከተማ ፡ ሰባራውን ፡ ጠገነ ። ኢዮርብዓምም ፡ ጽኑዕ ፡ ኃያል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ሰሎሞንም ፡ ጕልማሳው ፡ በሥራ ፡ የተመሰገነ ፡ መሆኑን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ በዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።

፳፪ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሴሎናዊው ፡ ነቢይ ፡ አኪያ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተገናኘው ፡ አኪያም ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፡ ሁለቱም ፡ በሜዳው ፡ ለብቻቸው ፡ ነበሩ ። አኪያም ፡ የለበሰውን ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ ይዞ ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ቁራጭ ፡ ጠው ። ኢዮርብዓምንም ፡ አለው ፡— አሥር ፡ ቍራጭ ፡ ውሰድ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— እነሆ ÷ ከሶሎሞን ፡ እጅ ፡ መንግሥቱን ፡ እቀድዳለሁ ÷ አሥሩንም ፡ ነገዶች ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ስለ ፡ መረጥኋት ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ እንድ ፡ ነገድ ፡ ይቀርለታል ። ጥለውኛልና ÷ ለሲዶና ውያንም ፡ አምላክ ፡ ለአስታሮት ÷ ለሞዓብም ፡ አምላክ ፡ ለካሞሽ ÷ ለአሞንም ፡ ልጆች ፡ አምላክ ፡ ለሚልኮም ፡ ሰግደዋልና ÷ አብቱም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፡ በፊቴ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ ሥርዓቴንና ፡ ፍርዴንም ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ አልሄዱምና ። መን ግሥቱንም ፡ ሁሉ ፡ ከእጁ ፡ አልወስድም ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዓቴን ፡ ስለ ፡ ጠበቀው ፡ ስለ ፡ መረጥሁት ፡ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ በዕድሜው ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ አደርገዋለሁ ። መንግሥቱንም ፡ ከልጁ ፡ እጅ ፡ እወስዳለሁ ÷ ለእነ ፡ ተም ፡ አሥሩን ፡ ነገድ ፡ እሰጥሃለሁ ። ስሜንም ፡ በኖርዩባት ፡ በዚያች ፡ በመረጥኋት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ በፊቴ ፡ ሁልጊዜ ፡ መብራት ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ ለልጁ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ እሰጠዋለሁ ። እንተንም ፡ እወስድሃለሁ ÷ ነፍስህም ፡ በወደደችው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ትነግሣለች ÷ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትሆናለህ ። ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ÷ ያዘዝሁህን ፡ ሁሉ ፡ ብትሰማ ፡ በመንገዴም ፡ ብትሄድ ÷ በፊቴም ፡ የቀናውን ፡ ብታደርግ ÷ ሥርዓቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ብትጠብቅ ÷ ከእንተ ፡ ጋር ፡ እሆናለሁ ÷ ለዳዊትም ፡ እንደ ፡ ሠራሁለት ፡ ጽኑ ፡ ቤት ፡ እሠራልሃለሁ ÷ እስራኤልንም ፡ ለእንተ ፡ እሰጥሃለሁ ። ስለዚህም ፡ የዳዊትን ፡ ዘር ፡ አስጨንቃለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዘመን ፡ ሁሉ ፡ አይደለም ። ሰሎሞንም ፡ ኢዮርብዓምን ፡ ሊገድለው ፡ ወደደ ፡ ኢዮርብዓምም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኰበለለ ÷ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሺሻቅ ፡ መጣ ÷ ሰሎሞንም ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ በግብጽ ፡ ተቀመጠ ።

የቀረውም ፡ የሰሎሞን ፡ ነገር ÷ ያደረገውም ፡ ሁሉ ÷ ጥበቡም ÷ እነሆ ÷ በሰሎሞን ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎአል ። ሰሎሞንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ። ሰሎሞንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፡ ልጁም ፡ ሮብዓም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ ሮብዓም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ሄደ ። እንዲህም ፡ ሆነ ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ÷ እርሱም ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ፊት ፡ ኰብልሎ ፡ በግብጽ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ÷ በግብጽም ፡ ሳለ ፡ ልከው ፡ ጠርተውት ፡ ነበርና ፡ ኢዮርብዓምና ፡ የእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ መጥተው ፡ ለሮብዓም ፡— አባትህ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ አንተ ፡ ጽኑውን ፡ የአባትህን ፡ አገዛዝ ÷ በላያችንም ፡ የጫነውን ፡ የከበደውን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልልን ፡ እኛም ፡ እንገዛልሃለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ። እርሱም ፡— ሂዱ ÷ በሦስት ፡ ተኛውም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ሄዱ ።

፭ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡— ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብሎ ፡ አባቱ ፡ ሰሎሞን ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ተማከረ ። እነርሱም ፡— ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አሁን ፡ ባሪያ ፡ ብትሆን ፡ ብትገዛላቸውም ÷ መልሰህም ፡ በገርነት ፡ ብትናገራቸው ÷ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ባሪያዎች ፡ ይሆኑልሃል ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ። እርሱ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ካደጉትና ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ብላቴኖች ፡ ጋር ፡ ተማከረ ። እርሱም ፡— አባትህ ፡ የጫነብንን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልን ፡ ለሚሉት ፡ ሕዝብ ፡ እመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የም ትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አላቸው ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያደጉት ፡ ብላቴኖች ፡— አባትህ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብናል ÷ አንተ ፡ ግን ፡ አቅልልልን ፡ ለሚሉህ ፡ ሕዝብ ፡— ታናሺቴ ፡ ጣቴ ፡ ከአባቴ ፡ ወገብ ፡ ትወፍራለች ። አሁንም ፡ አባቴ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ጭኖባችኋል ÷ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችሁ ፡ ላይ ፡ እጨምራለሁ ፡ አባቴ ፡ በአለንጋ ፡ ገርፎአችኋል ÷ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለሁ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

፲፪ ንጉሡም ፡— በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ መጡ ። ንጉሡም ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጽኑ ፡ ምላሽ ፡ መለሰላቸው ። እንደ ፡ ብላቴኖችም ፡

ምክር ፡— አባቴ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶባችሁ ፡ ነበር ÷ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችሁ ፡ ላይ ፡ እጨ ምራለሁ ፡ አባቴ ፡ በአለንጋ ፡ ገርፎአችሁ ፡ ነበር ÷ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለሁ ፡ ፲፫፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። እግዚአብሔርም ፡ በሴ ሎንያው ፡ በአኪያ ፡ አድርጎ ፡ ለናባጥ ፡ ልጅ ፡ ለኢዮርብዓም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲያ ጸና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተመድቦ ፡ ነበ ርና ፡ ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ አልሰማም ።

፲፮፡ አስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳልሰማ ቸው ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ለንጉሡ ፡— በዳ ዊት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡ አለን ? በእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ። አስራኤል ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ድንኳኖቻችሁ ፡ ተመለሱ ፡ ዳዊት ፡ ሆይ ÷ አሁን ፡ ቤትህን ፡ ተመልከት ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። አስራኤልም ፡ ወደ ፡ ድንኳኖቻ ፲፯፡ ቸው ፡ ሄዱ ። በይሁዳ ፡ ከተሞች ፡ በተቀመ ጡት ፡ በአስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሮብ ፲፰፡ ዓም ፡ ነገሠበት ። ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ አስ ገበረውን ፡ አዶኒራምን ፡ ሰደደ ፡ አስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ በድንጋይ ፡ ደብደቡት ÷ ሞተም ። ንጉ ሡም ፡ ሮብዓም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ሰረገላው ፡ ፲፱፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሸሸ ። አስራኤ ልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ፳፡ ሸፈተ ። አስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ኢዮርብዓም ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልከው ፡ ወደ ፡ ሸንጉአቸው ፡ ጠሩት ÷ በአስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አነገሡት ። ከብቻው ፡ ከይሁዳ ፡ ነገደ ፡ በቀር ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ የተከተለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

፳፩፡ ሮብዓምም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ÷ የአ ስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ወግተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ሁሉና ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የተመረጡትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺህ ፡ ፳፪፡ ሰልፈኞች ፡ ሰዎች ፡ ሰበሰበ ። የእግዚአብሔ ርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፳፫፡ ሳማያ ፡— ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ለሮብዓምና ፡ ለይሁዳ ፡ ለብንያምም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ፳፬፡ ለቀረውም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ይህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ አትውጡ ፡ የአስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ አትውጉ ፡ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ ሲል ፡ መጣ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ሰሙ ÷ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ተመልሰው ፡ ሄዱ ። ፳፭፡ ኢዮርብዓምም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሴኬምን ፡ ሠርቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ፡ ደግሞም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ጵኑኤልን ፡ ሠራ ። ፳፮፡ ኢዮርብዓምም ፡ በልቡ ፡— አሁን ፡ መንግሥቱ ፳፯፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ቤት ፡ ይመለሳል ። ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሥዋዕትን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቢወጣ ÷ የዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመለሳል ÷ እኔንም ፡ ይገድሉኛል ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ ተማክሮ ፡ ሁለ ፳፰፡ ት ም ፡ የወርቅ ፡ ጥጆች ፡ አድርጎ ፡— እስራኤል ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጡ ፡ ዘንድ ፡ ይበ ዛባችኋል ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጡህን ፡ አማል ክቶችህን ፡ እዩ ፡ አላቸው ። ፳፱፡ አንዱን ፡ በቤቴል ፡ ሁለተኛውንም ፡ በዳን ፡ አኖረ ። ፴፡ ለአንዱ ፡ ጥጃ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ሄዱ ። ፴፩፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ ኃጢአት ፡ ሆነ ። በኮ ረብቶቹም ፡ ላይ ፡ መስገጃዎች ፡ ሠራ ÷ ከሌሎ ፡ ልጆች ፡ ከይደሉ ፡ ከሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ። ፴፪፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አም ስተኛውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ እንደሚደረግ ፡ በዓል ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ አደረገ ÷ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፡ ለሠራቸውም ፡ ጥጆች ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ በቤቴል ፡ አደረገ ፡ ለከረብታ ፡ መስገጃዎችም ፡ የመረጣቸውን ፡ ካህናት ፡ በቤ ቴል ፡ አኖራቸው ። ፴፫፡ በስምንተኛውም ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ በልቡ ፡ ባሰ በው ፡ ቀን ፡ በቤቴል ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፡ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በዓል ፡ አደ ረገላቸው ፡ በመሠዊያውም ፡ ሠዋ ÷ ዕጣንም ፡ ዐጠነ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

እነሆም ÷ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በእ ፩፡ ግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጣ ፡ ኢዮርብዓምም ፡ ዕጣን ፡ እያጠነ ፡ በመ ሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። ፪፡ በመሠዊ ያውም ፡ ላይ ፡— መሠዊያ ፡ ሆይ ÷ መሠዊያ ፡ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ ስሙ ፡ ኢዮስያስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ ቤት ፡ ይወለዳል ። ዕጣንም ፡ የሚያጥኑብን ፡ የከረብታ ፡ መስገጃዎቹን ፡ ካህናት ፡ ይሠዋብ ሃል ÷ የሰዎቹንም ፡ አጥንት ፡ ያቃጥልብሃል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጮኸ ። ፫፡ በዚያም ፡ ቀን ፡— እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እነሆ ÷ መሠዊያው ፡ ይሰነጠቃል ÷ በላዩም ፡ ያለው ፡ አመድ ፡ ይፈስሳል ፡ ብሎ ፡ ምል ክት ፡ ሰጠ ። ፬፡ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የጮኸውን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮርብዓም ፡ እጁን ፡ ከመ ሠዊያው ፡ አንሥቶ ፡— ያዙት ፡ አለ ። በእር ሱም ፡ ላይ ፡ የዘረጋት ፡ እጅ ፡ ደረቀች ÷ ወደ ፡ እርሱም ፡ ይመልሳት ፡ ዘንድ ፡ አልተቻለውም ። ፭፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ምልክት ፡ መሠዊያው ፡ ተሰነጠቀ ÷ አመዱም ፡ ከመሠዊያው ፡ ፈሰሰ ። ፮፡ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡— አሁን ፡ የአምላክህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለምን ÷ እጂም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ጸልይ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ ለመን ÷ የንጉሡም ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተመለሰች ÷ እንደ ፡ ቀድሞም ፡ ሆነች ። ፯፡ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡— ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ና ፡ እንጀራም ፡ ብላ ÷ በረከ ፰፡ ትም ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ። ፰፡ የእግዚአብሔ ርም ፡ ሰው ፡ ንጉሡን ፡— የቤትህን ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ብትሰጠኝ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ አልገባም ÷ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ÷ ውኃም ፡ ፱፡ አልጠጣም ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ÷ ውኃም ፡ አት ጠጣ ÷ በመጣህበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አዝዞኛልና ። ፲፡ አለው ። በሌላም ፡ መንገድ ፡ ሄደ ÷ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ልም ፡ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ አልተመለሰም ። ፲፩፡ በቤቴልም ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነቢይ ፡ ይቀ መጥ ፡ ነበር ። ልጆቹም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥ ተው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ያደረገውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ነገሩት ፡ ደግሞም ፡ ለንጉሡ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፲፪፡ ለአባታቸው ፡ ነገሩት ። አባታቸውም ፡— በማ ናቸው ፡ መንገድ ፡ ሄደ ? አላቸው ። ልጆቹም ፡ ከይሁዳ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ፲፫፡ የሄደበትን ፡ መንገድ ፡ አመለከቱት ። ልጆቹ ንም ፡— አህያውን ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፡ አህ ያውንም ፡ በጫኑለት ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠበት ። ፲፬፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ ሄደ ፡ በእድ በርም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘውና ፡— ከይሁዳ ፡ የመጣህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነህን ? አለው ። እርሱም ፡— እኔ ፡ ነኝ ፡ ፲፭፡ አለ ። እርሱም ፡— ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ፲፮፡ ና ÷ እንጀራም ፡ ብላ ፡ አለው ። እርሱም ፡— ከእንተ ፡ ጋር ፡ እመለስና ፡ አገባ ፡ ዘንድ ፡ አይቻ ለኝም ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ እን ፲፯፡ ጀራ ፡ አልበላም ÷ ውኃም ፡ አልጠጣም ፡ በዚያ ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ÷ ውኃም ፡ አትጠጣ ÷ በመጣ ህበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግ ፲፰፡ ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተብሎልኛልና ፡ አለ ። እር ሱም ፡— እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነቢይ ፡ ነኝ ፡ መልአክም ፡— እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ውኃም ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ መልሰው ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተናገረኝ ፡ አለው ። ዋሸቶም ፡ ተናገረው ። ፲፱፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ተመለሰ ÷ በቤቱም ፡ እንጀራ ፡ በላ ÷ ውኃም ፡ ጠጣ ።

፳፡ በማዕድም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ መለሰው ፡ ነቢይ ፡ መጣ ፡ ፳፩፡ ከይሁዳም ፡ ወደ ፡ መጣው ፡ ወደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ሰው ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ዐምፀ ሃልና ÷ አምላክህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘህን ፳፪፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅህምና ÷ ተመልሰህም ፡— እንጀራ ፡ አትብላ ÷ ውኃም ፡ አትጠጣ ፡ በለህ ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ በልተሃልና ÷ ውኃም ፡ ጠጥተሃልና ፡ ሬሳህ ፡ ወደ ፡ አባቶችህ ፡ መቃ ፳፫፡ ብር ፡ አይደርስም ፡ ብሎ ፡ ሠኘ ። እንጀራም ፡ ከበላ ፡ ውኃም ፡ ከጠጣ ፡ በኋላ ፡ አህያውን ፳፬፡ ጫነለት ። ተመልሶም ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በመን

ገዱ ፡ ላይ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ፡ ሬሳ ውም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ነበር ÷ አህ ያውም ፡ በእርሱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። አን በሳውም ፡ ደግሞ ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ፳፭፡ ነበር ። እነሆም ÷ መንገድ ፡ አላፊ ፡ ሰዎች ፡ ሬሳው ፡ በመንገዱ ፡ ወድቆ ፡ አንበሳውም ፡ በሬ ሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ አዩ ፡ መጥተውም ፡ ሽማግሌው ፡ ነቢይ ፡ ተቀምጦበት ፡ በነበረው ፡ ከተማ ፡ አወሩ ።

፳፮፡ ያም ፡ ከመንገድ ፡ የመለሰው ፡ ነቢይ ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡— በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ያመፀ ፡ ያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እግ ዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ቃል ÷ እግዚ አብሔር ፡ ለአንበሳ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፡ ሰብሮም ፡ ገድሎታል ፡ አለ ። ፳፯፡ ልጆቹንም ፡— አህያ ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ ጫኑ ፡ ለት ። ፳፰፡ ሄደም ÷ ሬሳው ፡ በመንገድ ፡ ወድቆ ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ አህያውና ፡ አንበሳው ፡ ቆመው ÷ አንበሳው ፡ ሬሳውን ፡ ሳይበላው ፡ አህያውንም ፡ ሳይሰብረው ፡ አገኘ ። ፳፱፡ ነቢዩም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ አነሣ ፡ በአህ ያውም ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ መለሰው ፡ ያለቅስለትና ፡ ይቀብረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ ከተማው ፡ ይዘት ፡ መጣ ። ሬሳውንም ፡ በገዛ ፡ መቃብሩ ፡ አኖረው ። ፴፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ አለቀ ሱለት ። ፴፩፡ ከቀበረውም ፡ በኋላ ፡ ልጆቹን ፡ እን ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡— በሞትሁ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በተቀበረበት ፡ መቃብር ፡ ቀበሩኝ ፡ አጥንቶቹንም ፡ በአጥንቶቹ ፡ አጠ ገብ ፡ አኑሩ ፡ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ፴፪፡ በሰማርያም ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ ከከረብታ ዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የጮኸው ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ይደርሳልና ።

፴፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከክፉ ፡ መን ገድ ፡ አልተመለሰም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ለከረብታ ዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ አብልጦ ፡ ከሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ፡ የሚወድዳውንም ፡ ሁሉ ፡ ይቀ ድስ ፡ ነበር ÷ እርሱም ፡ ለከረብታዎቹ ፡ መስገጃ ዎች ፡ ካህን ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ፴፬፡ አስከፈርክም ፡ ከምድርም ፡ አስከጠፋ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ኃጢአት ፡ ሆነ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

በዚያም ፡ ወራት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ፩፡ አብያ ፡ ታመመ ። ፪፡ ኢዮርብዓምም ፡ ሚስቱን ፡— ፫፡ ተነሺ ፡ የኢዮርብዓም ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ሆንሽ ፡ እንዳትታወቂ ፡ ልብስሽን ፡ ለውጠሽና ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ሂጂ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እን ድነግሥ ፡ የነገረኝ ፡ ነቢዩ ፡ አኪያ ፡ በዚያ ፡ አለ ። በእጅሽም ፡ አሥር ፡ እንጀራና ፡ አንጉቻዎች ፡ ፫፡ አንድም ፡ ምንቸት ፡ ማር ፡ ይዘሽ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሂጂ ፡ በልጁም ፡ የሚሆነውን ፡ ይነግርሻል ፡ አላት ። ፬፡ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ እንዲሁ ፡ አደ ረገች ÷ ተነሥታም ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ሄደች ፡ ወደ ፡

አከ፡ያም ፡ ቤት ፡ መጣች ። አከ፡ያም ፡ ስለ ፡ መሸ
ምገሉ ፡ ዓይኖቹ ፡ ፈዝዘው ፡ ነበርና ፡ ማየት ፡ አል
፭ ፡ ቻለም ። እግዚአብሔርም ፡ አከ፡ያን ፡— እነሆ ፡ ሚ
ስለ ፡ ታመመው ፡ ልጅዋ ፡ ትጠይቅህ ፡ ዘንድ ፡
የኢ፡ዮርብዓም ፡ ሚስት ፡ ትመጣለች ፡ ሌላ ፡
ሴትም ፡ መስላ ፡ ተሰውራለችና ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡
እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ በላት ፡ አለው ።
፮ ፡ አርስዋም ፡ በደጅ ፡ ስትገባ ፡ አከ፡ያ ፡ የእግር
ዋን ፡ ኩቴ ፡ ሰማ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡— የኢ፡ዮር
ብዓም ፡ ሚስት ፡ ሆይ ፡ ግቢ ፡ ስለ ፡ ምንስ ፡ ሌላ ፡
ሴት ፡ መሰልሽ ? እኔም ፡ ብርቱ ፡ ወሬ ፡ ይገር
፯ ፡ ተልኬልኻለሁ ። ሂጂ ፡ ለኢ፡ዮርብዓምም ፡ እን
ዲህ ፡ በዪው ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ከሕዝብ ፡ መካከል ፡
ለይቼ ፡ ከፍ ፡ አድርጌህ ፡ ነበር ፡ በሕዝቤም ፡
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጌህ ፡ ነበር ፡
፰ ፡ ከዳዊትም ፡ ቤት ፡ መንግሥቱን ፡ ቀድጄ ፡ ሰጥ
ቼህ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡
ተከተለኝ ፡ በፊቴም ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንዳ
ደረገ ፡ ትእዛዜንም ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ እንደ ፡ በሪ
፱ ፡ ያዬ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ አልሆንህም ። ከአንተም ፡
አስቀድመው ፡ ከነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡
ሠራህ ፡ ታስቈጣኝም ፡ ዘንድ ፡ ሄደህ ፡ ሌሎችን ፡
አማልክትና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎች ፡
፲ ፡ አደረግህ ፡ ወደ ፡ ኋላህም ፡ ጣልኸኝ ። ስለዚህ ፡
እነሆ ፡ በኢ፡ዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ መከራ ፡
አመጣለሁ ፡ ከኢ፡ዮርብዓምም ፡ በእስራኤል ፡
ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡
ሁሉ ፡ አቈርጣለሁ ፡ ሰውም ፡ ፋንድያን ፡ እስኪ
ጠፋ ፡ ድረስ ፡ እንደሚጠርግ ፡ እሴ ፡ የኢ፡ዮርብ
፲፩ ፡ ዓምን ፡ ቤት ፡ ፈጽሜ ፡ እጠርጋለሁ ። ከኢ፡ዮ
ርብዓምም ፡ ወገን ፡ በከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞ
ተውን ፡ ውሾች ፡ ይበሉታል ፡ በሜዳውም ፡
የሞተውን ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ፡
፲፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሮአልና ። እንግዲህ ፡ ተነ
ሥተሽ ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ሂጂ ፡ እግርሽም ፡ ወደ ፡
፲፫ ፡ ከተማ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ይሞታል ። እስራ
ኤልም ፡ ሁሉ ፡ ያለቅሱለታል ፡ ይቀብሩትማል ፡
በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
በኢ፡ዮርብዓም ፡ ቤት ፡ በዘሀ ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡
ነገር ፡ ተገኝቶበታልና ፡ ከኢ፡ዮርብዓም ፡ እርሱ ፡
፲፬ ፡ ብቻ ፡ ይቀበራል ። እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ያስነሣል ፡ እርሱም ፡
በዚያ ፡ ዘመን ፡ የኢ፡ዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ያጠፋል ።
፲፭ ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሸምበቆ ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ እን
ደሚንቀሳቀስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ እስ
ራኤልን ፡ ይመታል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያስ
ቈጡ ፡ ዘንድ ፡ የማምለኪያ ፡ ዐፀድ ፡ ተክለዋ
ልና ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ከሰጣቸው ፡ ከዚች ፡ ከመ
ልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እስራኤልን ፡ ይነቅላል ፡
፲፮ ፡ በወንዙም ፡ ማዶ ፡ ይበትናቸዋል ። ስለ ፡ በደ
ለውሩ ፡ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ ስለ ፡ ኢ፡ዮ
ርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ እስራኤልን ፡ ይጥላል ።
፲፯ ፡ የኢ፡ዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ ተነሥታ ፡ ሄደች ፡
ወደ ፡ ቴርሳ ፡ መጣች ። ወደ ፡ ቤቱም ፡ መድ
ረክ ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ሞተ ። በባሪያውም ፡ ፲፰ ፡
በነቢዩ ፡ በአከ፡ያ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ እንደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ቀበሩት ፡
አለቀሱለትም ።
የቀረውም ፡ የኢ፡ዮርብዓም ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ፲፱ ፡
እንደ ፡ ተዋጋ ፡ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡
እነሆ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ተጽፎአል ። ኢ፡ዮርብዓምም ፡ የነገሠ ፳ ፡
በት ፡ ዘመን ፡ ዐያ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፡ ከአባ
ቶቹም ፡ ጋር ፡ እንቀላፋ ፡ ልጁም ፡ ናዳብ ፡ በፋ
ንታው ፡ ነገሠ ።
የሰሎሞንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓም ፡ በይሁዳ ፡ ነገሠ ፡ ፳፩ ፡
ሮብዓምም ፡ ንጉሥ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡
አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ስሙን ፡ ያኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡
ነገድ ፡ ሁሉ ፡ በመረጣት ፡ ከተማ ፡ በኢ፡የሩሳ
ሌም ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ የእና
ቱም ፡ ስም ፡ ናዕማ ፡ ነበረ ፡ አሞናዊም ፡ አሞና
ዊት ፡ ነበረች ። ይሁዳም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፳፪
ፊት ፡ ክፉ ፡ ሠራ ። አባቶቻቸውም ፡ ከሠሩት ፡
ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አብዝተው ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡
አስቈጡት ። እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ፳፫
ኮረብታ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቅጠሉ ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍ ፡
ሁሉ ፡ በታች ፡ መስገጃዎችንና ፡ ሐውልቶችን ፡
የማምለኪያ ፡ ዐፀዶችንም ፡ ለራሳቸው ፡ ሠሩ ።
በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ሰዶማውያን ፡ ነበሩ ፡ ከአ ፳፬
ስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰ
ደዳቸውን ፡ የአሕዛብን ፡ ርኵሰት ፡ ሁሉ ፡ ያደ
ርጉ ፡ ነበር ።
ሮብዓምም ፡ በነገሠ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ፳፭
የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅ ፡ በኢ፡የሩሳሌም ፡ ላይ ፡
መጣ ። የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፳፮
ንና ፡ የንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብትን ፡ ወሰደ ፡
ሁሉንም ፡ ወሰደ ፡ ሰሎሞንም ፡ የሠራውን ፡
የወርቁን ፡ ጋሻ ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ። ንጉሥም ፡ ሮብ ፳፯
ዓም ፡ በፋንታው ፡ የናስ ፡ ጋሻዎችን ፡ ሠራ ፡ የን
ጉሥንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ በሚጠብቁ ፡ በዘበኞች ፡
አለቆች ፡ እጅ ፡ አኖራቸው ። ንጉሡም ፡ ዘወ ፳፰
ትር ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ ዘበ
ኞች ፡ ይሸከሙአቸው ፡ ነበር ፡ መልሰውም ፡
በዘበኞች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሩአቸው ፡ ነበር ።
የቀረውም ፡ የሮብዓም ፡ ነገር ፡ ያደረገውም ፡ ፳፱
ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡
የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ በር ፴
ብዓምና ፡ በኢ፡ዮርብዓም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡
ነበረ ። ሮብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ ፴፩
በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ።
ልጁም ፡ አብያም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢ፡ዮርብዓም ፡ በነገሠ ፡ በአ ፩
ሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ አብያም ፡ በይ
ሁዳ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። በኢ፡የሩሳሌምም ፡ ፪

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተ
፫ ፡ ባለች ፡ የአቢሴሎም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ከእርሱ ፡
አስቀድሞ ፡ በደረገው ፡ በአባቱ ፡ ኃጢአት ፡
ሁሉ ፡ ሄደ ፡ ልቡም ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡
ዳዊት ፡ ልብ ፡ ከእምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
፬ ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጁን ፡
ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፡ ኢ፡የሩሳሌ
ምንም ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ አምላኩ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ በኢ፡የሩሳሌም ፡ መብራት ፡
፭ ፡ ሰጠው ። ዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፡
ከዘዘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፡ ነበ
፮ ፡ ርና ። በኢ፡ዮርብዓምና ፡ በሮብዓም ፡ ልጅ ፡ በአ
ብያም ፡ መካከል ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ጠብ ፡ ነበረ ።
፯ ፡ የቀረውም ፡ የአብያም ፡ ነገር ፡ ያደረገውም ፡
ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡
የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በአብያምና ፡ በኢ፡ዮር
፰ ፡ ብዓምም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ። አብያምም ፡
ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ እንቀላፋ ፡ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡
ቀበሩት ። ልጁም ፡ አሳ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።
፱ ፡ በአስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢ፡ዮርብዓም ፡ በሀ
ያኛው ፡ ዓመት ፡ አሳ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።
፲ ፡ በኢ፡የሩሳሌም ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡
እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተባለች ፡ የአቢሴሎም ፡
፲፩ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። አሳ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡
ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡
፲፪ ፡ አደረገ ። ከአገሩም ፡ ሰዶማውያንን ፡ አስወገደ ፡
አባቶቹም ፡ ያደረጉትን ፡ ጣዖታትን ፡ ሁሉ ፡
፲፫ ፡ አራቀ ። በማምለኪያ ፡ ዐፀድ ፡ ጣዖት ፡ ስላ
ሠራች ፡ እናቱን ፡ መዓካን ፡ እቴጌ ፡ እንዳት
ሆን ፡ ሻራት ፡ ጣዖትዋንም ፡ ሰበረው ፡ በቂድ
፲፬ ፡ ሮንም ፡ ፈፋ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ። ነገር ፡
ግን ፡ በኮረብቶች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡
አላራቀም ፡ የአሳ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
፲፭ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ። አባቱ ፡
የቀደሰውንና ፡ እርሱም ፡ የቀደሰውን ፡ ወርቅና ፡
ብር ፡ ዕቃውንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
አገባው ።
፲፮ ፡ በአሳና ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በባአስ ፡
መካከል ፡ በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።
፲፯ ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባአስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡
ወጣ ፡ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከአሳ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡
እንዳይወጣ ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ማንም ፡ እንዳይ
፲፰ ፡ ገባ ፡ አድርጎ ፡ ራማን ፡ ሠራ ። አሳም ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡
የቀረውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ ወስዶ ፡ በባ
ሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ ሰጣቸው ። ንጉሡም ፡ አሳ ፡ በደ
ማስቆ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለአዜን ፡ ልጅ ፡ ለጠ
ብረሞን ፡ ልጅ ፡ ለሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ለወልደ ፡
፲፱ ፡ አዩር ፡— በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ በአባ
ቴና ፡ በአባትህም ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ጸንቶአል ፡ እነሆ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ገጸ ፡ በረ
ከት ፡ ሰድጄልሃለሁ ፡ እርሱ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡
እንዲርቅ ፡ ሄደህ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባ
አስ ፡ ጋር ፡ ያለህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርስ ፡
ብሎ ፡ ሰደደ ። ወልደ ፡ አዩርም ፡ ለንጉሡ ፡ ፳፡
ለአሳ ፡ እሺ ፡ አለው ፡ የሠራዊቱንም ፡ አለቆች ፡
በእስራኤል ፡ ከተሞች ፡ ላይ ፡ ሰድዶ ፡ ዒዮንን ፡
ንና ፡ ዳንን ፡ አቤልቤትመዓካንና ፡ ኪኔሬትን ፡
ሁሉ ፡ የንፍታሌምንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ መታ ።
፳፩ ፡ በአስም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ራማን ፡ መሥ ፳፪፡
ራት ፡ ትቶ ፡ በቴርሳ ፡ ተቀመጠ ። ንጉሡም ፡ ፳፪፡
አሳ ፡ በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፡
ማንም ፡ ነጻ ፡ አልነበረም ፡ በአስም ፡ የሠራበ
ትን ፡ የራማን ፡ ድንጋይና ፡ እንጨት ፡ ወሰዳ ፡
ንጉሡም ፡ አሳ ፡ የብንያምን ፡ ጌባንና ፡ ምጽጳን ፡
ሠራበት ።
የቀረውም ፡ የአሳ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጭከናውም ፡ ፳፫፡
ሁሉ ፡ ያደረገውም ፡ ሁሉ ፡ የሠራቸው ፡ ከተ
ሞች ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡
የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ነገር ፡ ግን ፡ በሸመገለ ፡
ጊዜ ፡ እግሮቹ ፡ ታመሙ ። አሳም ፡ ከአባቶቹ ፡ ፳፬፡
ጋር ፡ እንቀላፋ ፡ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡
ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ። ልጁም ፡ ኢ፡ዮሣ
ፍጥ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።
በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሳ ፡ በሁለተኛው ፡ ፳፭፡
ዓመት ፡ የኢ፡ዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ናዳብ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፡ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ፳፮፡
አደረገ ፡ በአባቱም ፡ መንገድ ፡ እስራኤልንም ፡
ባሳተበት ፡ ኃጢአት ፡ ሄደ ። ከይሳኮርም ፡ ቤት ፡ ፳፯፡
የሆነ ፡ የአከ፡ያ ፡ ልጅ ፡ ባአስ ፡ ተማማለበት ፡
ናዳብና ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ገባቶንን ፡ ከብ
በው ፡ ነበርና ፡ ባአስ ፡ በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡
ባለው ፡ በገባቶን ፡ ገደለው ። በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ፳፰፡
በአሳ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ባአስ ፡ ናዳብን ፡
ገደለው ፡ በፋንታውም ፡ ነገሠ ። ንጉሥም ፡ ፳፱፡ ፴፡
በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የኢ፡ዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡
መታ ፡ ኢ፡ዮርብዓምም ፡ ስለ ፡ ሠራው ፡ ኃጢ
አት ፡ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ የአስራኤ
ልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስላስቈጣ
በት ፡ ማስቈጫ ፡ በባሪያው ፡ በሴሎናዊው ፡ በአ
ኪ፡ያ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ቃል ፡ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከኢ፡ዮ
ርብዓም ፡ አንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ያለው ፡ አላስቀረም ።
የቀረውም ፡ የናዳብ ፡ ነገርና ፡ ያደረገው ፡ ፴፩፡
ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽ (፴፪)
ሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ?
በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሳ ፡ በሦስተኛው ፡ ፴፫፡
ዓመት ፡ የአከ፡ያ ፡ ልጅ ፡ ባአስ ፡ በእስራኤል ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ በቴርሳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ ዐያ ፡ አራት ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ፴፬፡
አደረገ ፡ በኢ፡ዮርብዓምም ፡ መንገድ ፡ እስራኤ
ልንም ፡ ባሳተበት ፡ ኃጢአት ፡ ሄደ ።

ምዕራፍ ፲፯

፩ የእግዚአብሔርም ቃል በባአስ ላይ እን
ዲህ ብሎ ወደ አናኒ ልጅ ወደ ኢዩ
፪ መጣ እኔ ከመሬት አስነሥቼ በሕዝቤ
በእስራኤል ላይ አለቃ አድርጌሃለሁ አንተ
ግን በኢዮርብዓም መንገድ ሄደሃል ፥ በኃ
ጢአታቸውም ያስቈጡኝ ዘንድ ሕዝቤን
፫ እስራኤልን አስተሃቸዋል ። ስለዚህም ፥ እነሆ
ባአስንና ቤቱን ፈጽሜ እጠርጋለሁ ቤት
ህንም እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም
፬ ቤት አደርጋለሁ ። ከባአስም ወገን በከተ
ማይቱ ውስጥ የሚሞተውን ውሾች ይበ
ሉታል ፤ በሜዳውም የሚሞተውን የሰማይ
ወፎች ይበሉታል ።

፭ የቀረውም የባአስ ነገር ፥ ሥራውና ጭከ
ናው ፥ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽ
፮ ሐፍ የተጻፈ አይደለምን ? ባአስም ከአባ
ቶቹ ጋር አንቀላፋ ፥ በቴርሳም ተቀበረ ፤
፯ ልጁም ኤላ በፋንታው ነገሠ ። በእጁም
ሥራ ያስቈጣው ዘንድ ፥ እንደ ኢዮርብ
ዓም ቤት በእግዚአብሔር ፊት ስላደረ
ገው ክፋት ሁሉ እርሱንም ስለ ገደለው
የእግዚአብሔር ቃል በባአስና በቤቱ ላይ ፥
ወደ አናኒ ልጅ ወደ ነቢዩ ወደ ኢዩ
መጣ ።

፰ በይሁዳም ንጉሥ በአሳ በሀያ ስድስተ
ኛው ዓመት የባአስ ልጅ ኤላ በእስራ
ኤል ላይ በቴርሳ ሁለት ዓመት ነገሠ ።
፱ የእኩሌቶቹም ሰረገሎች አለቃ ዘምሪ ተማ
ማለበት ኤላም በቴርሳ ነበረ ፥ በቴርሳም
በነበረው በቤት አሽከርች አለቃ በአሳ
፲ ቤት ይሰክር ነበር ። በይሁዳም ንጉሥ
በአሳ በሀያ ሰባተኛው ዓመት ዘምሪ
ገብቶ መታው ገደለውም ፥ በፋንታውም
፲፩ ነገሠ ። ንጉሥም በሆነ ጊዜ ፥ በዙፋኑም
በተቀመጠ ጊዜ ፥ የባአስን ቤት ሁሉ
መታ ከዘመዶችና ከወዳጆች ሁሉ አንድ
፲፪ ወንድ እንኳ አልቀረም ። በአስና ልጁ
ኤላ ስለ ሠሩት ኃጢአት ሁሉ ፥ በምናም
ንቱም ሥራቸው የእስራኤልን አምላክ
እግዚአብሔርን ያስቈጡት ዘንድ ፥ እስራኤ
ልን ስለ አሳቱበት ኃጢአት ፥ በነቢዩ
በኢዩ በእጅ በባአስ ላይ እንደ ተናገረው
፲፫ እንደ እግዚአብሔር ቃል ዘምሪ የባአስን
ቤት ሁሉ እንዲሁ አጠፋ ። የቀረውም ፥
የኤላ ነገር ያደረገውም ሁሉ ፥ በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ የተጻፈ አይ
ደለምን ?

፲፬ በይሁዳ ንጉሥ በአሳ በሀያ ሰባተኛው
ዓመት ዘምሪ በቴርሳ ሰባት ቀን ነገሠ ።
ሕዝቡም በፍልስጥኤም አገር የነበረው
፲፭ ገባቶንን ከብበው ነበር ። ከተማያቱንም ከብ
በው የነበሩ ሕዝብ ዘምሪ እንደ ዐመፀ ፥
ንጉሡንም እንደ ገደለ ሰሙ ፤ እስራኤልም
ሁሉ በዚያ ቀን በሰፈሩ ውስጥ የሠራዊ
ቱን አለቃ ዘንበሪን አነገሡ ። ዘንበሪም ፥ ከእር
ሱም ጋር እስራኤል ሁሉ ከገባቶን ወጥ
፲፮ ተው ቴርሳን ከበቡ ። ዘምሪም ፥ ከተማያቱ፡
እንደ ተያዘች በየ ጊዜ ወደ ንጉሡ ቤት ፥
ግንብ ውስጥ ገባ ፥ የንጉሡንም ቤት በራሱ
፲፯ ላይ በእሳት አቃጠለ ፤ ስላደረገውም ኃጢ
አት ፥ እስራኤልንም ስላሳተበት ፥ ኃጢአት ፥
በእግዚአብሔር ፊት ክፋ አድርጎአልና ፥
በኢዮርብዓምም መንገድ ሄዶአልና ሞተ ።
፲፰ የቀረውም የዘምሪ ነገር ፥ ያደረገውም ፥
ዐመፅ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽ
ሐፍ የተጻፈ አይደለምን ?

፲፱ በዚያም ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በሁ
ለት ተከፈለ ፤ የሕዝቡም እኩሌታ የጎናትን
ልጅ ታምኒን ያነግሡት ዘንድ ተከተሉት
እኩሌታውም ዘንበሪን ተከተለ ። ዘንበሪንም፡
፳ የተከተለ ሕዝብ የጎናትን ልጅ ታምኒን
በተከተለ ሕዝብ ላይ በረታ ፤ ታምኒም
ሞተ ፥ ዘንበሪም ነገሠ ። በይሁዳ ንጉሥ
፳፩ በአሳ በሠላሳ አንደኛው ዓመት ዘንበሪ
በእስራኤል ላይ አሥራ ሁለት ዓመት
ነገሠ ። በቴርሳም ስድስት ዓመት ነገሠ ።
፳፪ ከሳምርም በሁለት መክሊት ብር የሰማር
ያን ተራራ ገዛ ፤ በተራራውም ላይ ሠራ ፥
የሠራውንም ከተማ በተራራው ባለቤት
በሳምር ስም ሰማርያ ብሎ ጠራው ። ዘን
፳፫ በረም በእግዚአብሔር ፊት ክፋ አደረገ ፥
ከእርሱም አስቀድሞ ከነበሩት ይልቅ ፡
፳፬ እጅግ ከፋ ። በናባጥም ልጅ በኢዮርብ
ዓም መንገድ ሁሉ በምናምንቴም ነገራ
ቸው የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔ
ርን ያስቈጡት ዘንድ እስራኤልን ባሳተ
በት ኃጢአት ሄደ ። የቀረውም ዘንበረ
፳፭ ያደረገው ነገር ፥ የሠራውም ጭከና ፥ በእስ
ራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ የተ
፳፮ ጻፈ አይደለምን ? ዘንበረም ፡ ከአባቶቹ
ጋር አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ተቀበረ ፤ ልጁም፡
አክዓብ በፋንታው ነገሠ ።

፳፱ በይሁዳም ንጉሥ በአሳ በሠላሳ ስምን
ተኛው ዓመት የዘንበረ ልጅ አክዓብ በእ
ስራኤል ላይ ነገሠ ፤ የዘንበረም ልጅ አክ
ዓብ በእስራኤል ላይ በሰማርያ ሀያ ሁለት
ዓመት ነገሠ ። የዘንበረም ልጅ አክዓብ ፡
፴ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ፡
፴፩ በእግዚአብሔር ፊት ክፋ አደረገ ። በናባ
ጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ፡
ታናሽ ነገር መሰለው ፥ የሲዶናውያንንም ፡
ንጉሥ የኤትበኣልን ልጅ ኤልዛቤልን ፡
አገባ ፥ ሄዶም በኣልን አመለከ ሰገደለትም ።
፴፪ በሰማርያም በሠራው በበኣል ቤት ውስጥ ፡
፴፫ ለበኣል መሠዊያ አቆመ ። አክዓብም የማ
ምለክያ ዐፀድ ተከለ ፡ አክዓብም ከእርሱ ፡

በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን ፡
አምላክ እግዚአብሔርን የሚያስቈጣውን ፡
፴፬ ነገር አበዛ ። በእርሱም ዘመን የቤቴል ፡
ሰው አኪኤል ኢያሪኮን ሠራ ። በኑዌም ፡
ልጅ በኢያሱ እጅ እንደ ተነገረው እንደ ፡
እግዚአብሔር ቃል ፥ በበኵር ልጁ በአቢ
ሮን መሠረተዋን አደረገ ፥ በታናሹ ልጁም ፡
በሠንብ በር ሾመ ።

ምዕራፍ ፲፰

፩ በገለዓድ ቴስቢ የነበረው ቴስብያዊው ፡
ኤልያስ አክዓብን ፦ በፊቱ የቆምሁት የእ
ስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን !
ከእሬ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ፡
ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው ። የእግዚ
አብሔርም ቃል እንዲህ ሲል ለእርሱ ፡
፫ መጣለት ፦ ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥ
ራቅ ሂድ ፥ በዮርዳኖስም ትይዩ በለው ፡
፬ በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ ። ከወንዙም
ትጠጣለህ ፥ ቍራዎችም በዚያ ይመግቡህ
፭ ዘንድ እዝዝሃለሁ ። ሄደም ፥ እንደ እግዚአ
ብሔር ቃልም አደረገ ። ሄዶም በዮርዳኖስ ፡
ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ ተቀ
፮ መጠ ። ቍራዎቹም በየጥዋትና በየማታው ፡
እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር ፥ ከወን
፯ ዙም ይጠጣ ነበር ። ከብዙ ቀንም በኋላ ፡
በምድር ላይ ዝናብ አልነበረምና ወንዙ ፡
፰ ደረቀ ።

፱ ተነሥተህም በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ፡
ወደ ሰራፕታ ሂድ ፥ በዚያም ተቀመጥ ፤
እነሆም ፥ ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባል
፲ ቴት አዝዣለሁ የሚል የእግዚአብሔር ፡
፲፩ ቃል መጣለት ። ተነሥቶም ወደ ሰራፕታ ፡
ሄደ ወደ ከተማይቱም በር በደረሰ ጊዜ ፡
አንዲት ባልቴት በዚያ እንጨት ትለቅም ፡
፲፪ ነበር ፡ እርሱም ጠርቶ ፦ የምጠጣው ጥቂት ፡
ውኃ በጽዋ ታመጪልኝ ዘንድ አለምንሽ
፲፫ ለሁ አላት ። ውኃም ልታመጣለት በሄደች ፡
ጊዜ ወደ እርስዋ ጠርቶ ፦ ቍራሽ እን
፲፬ ጀራ በእጅሽ ይዘሽ ትመጭ ዘንድ እለ
ምንሽለሁ አላት ። እርስዋም ፦ አምላክህ ፡
ሕያው እግዚአብሔርን ! በግድጋ ከለው ፡
ከእፍኝ ዱቄት ፥ በማሰርም ከለው ፡ ከጥቂት ፡
፲፭ ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም ፤ እነሆም ፥
ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ ፡ በልተ
ነውም እንሞት ዘንድ ጥቂት እንጨት እሰ
በስበሰለሁ አለች ። ኤልያስም አላት ፦ አት
፲፮ ፍሪ ይልቅስ ሄደሽ እንዳልሽው አድርጊ ፡
አስቀድመሽ ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እን
ጐቻ አድርገሽ አምጭልኝ ፥ ከዚያም በኋላ ፡
፲፯ ለአንቺና ለልጅሽ አድርጊ ። የእስራኤል ፡
አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና ፦
በምድር ላይ እግዚአብሔር ዝናብ እስከ
፲፰ ሚሰጥበት ቀን ድረስ ፥ ዱቄቱ ከማድጋ ፡
አይጨረስም ፥ ዘይቱም ከማሰሮው አይጐ
ድልም ። እርስዋም ሄዳ እንደ ኤልያስ ፡ ፲፱
ቃል አደረገች ፡ እርስዋና እርሱ ቤትዋም ፡
ብዙ ቀን በሉ ። በኤልያስም እጅ እንደ ፡ ፳
ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ዱቄቱ ፡
ከማድጋው አልተጨረሰም ፥ ዘይቱም ከማሰ
ሮው አልጐደለም ።

ከዚያም በኋላ የባለቤቲቱ ልጅ ታመመ ፡ ፳፩
ትንፋሹም እስኪታጣ ድረስ ደዌው እጅግ፡
ከባድ ነበረ ። እርስዋም ኤልያስን ፦ የእግ ፳፪
ዚአብሔር ሰው ሆይ ፥ ከእንተ ጋር ምን፡
አለኝ ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ፥ ልጄ
ንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃ
ልን ? አለችው ። ኤልያስም ፦ ልጅሽን ፡ ፳፫
ስጪኝ ፡ አላት ። ከብብትዋም ወስዶ ፡ ተቀ
ምጦበት ወደ ነበረው ሰገነት አወጣው ፡
በአልጋውም ላይ አጋደመው ። ወደ እግ ፳፬
ዚአብሔርም ፦ አቤቱ አምላኬ ሆይ ፥ ልጅ
ዋን በመግደልህ ይህችን ትቀልበኝ ፡ የነበ
ረቺቱን በልቴት እንዲህ ደግሞ አስጨነ
ቅኻትን ? ብሎ ጮኸ ። በብላቴናውም ላይ ፡ ፳፭
ሦስት ጊዜ ተዘረጋበት ፥ ወደ እግዚአብሔ
ርም ፦ አቤቱ አምላኬ ሆይ ፥ የዚህ ብላ
ቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ ፡
አሰምንሃለሁ ብሎ ጮኸ ። እግዚአብሔርም ፡ ፳፮
የኤልያስን ቃል ሰማ ፡ የብላቴናው ነፍስ ፡
ወደ እርሱ ተመለሰች ፥ እርሱም ዳነ ።
ኤልያስም ፡ ብላቴናውን ፡ ይዞ ከሰገነቱ ወደ ፡ ፳፫
ቤት አወረደው ፥ ኤልያስም ፦ እነሆ ፥ ልጅሽ፡
በሕይወት ይኖራል ፡ ብሎ ለእናቱ ሰጣት ።
ሴቲቱም ፡ ኤልያስን ፦ የእግዚአብሔር ሰው ፡ ፳፬
አንደ ሆንህ ፥ የእግዚአብሔርም ቃል በአ
ፍህ እውነት እንደ ሆነ አሁን አወቅሁ ፡
አለችው ።

ምዕራፍ ፲፰

ከብዙ ቀንም በኋላ በሦስተኛው ዓመት ፦ ፩
ሂድ ፥ ለአክዓብ ተገለጥ ፥ በምድር ላይም ፡
ዝናብ እሰጣለሁ ፡ የሚል የእግዚአብሔር ፡
ቃል ወደ ኤልያስ መጣ ። ኤልያስም ፡ ለአ ፪
ክዓብ ይገለጥ ዘንድ ሄደ ፤ በሰማርያም ፡
ራብ ጸንቶ ነበር ። አክዓብም የቤቱን ፡ ፫
አዛዥ አብድዩን ጠራ ፤ ጓብድዩ እግዚአብ
ሔርን እጅግ ይፈራ ነበር ። ኤልዛቤልም ፡ ፬
የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለች ጊዜ ፡
እርሱ መቶውን ነቢያት ወስዶ እምሳ ፡
አምሳውን በዋሻ ውስጥ ሸሽጎ እንጀራና ፡
ውኃ ይመግባቸው ነበር ። አክዓብም አብ ፭
ድዩን ፦ በአገሩ መካከል ወደ ውኃው ፡
ምንጭ ሁሉና ወደ ወንዝ ሁሉ ሂድ ፡
እንስሶችም ሁሉ እንዳይጠፉ ፈረሶችንና ፡
በቅሎችን የምናድንበት ሣር ምናልባት ፡
እናገኛለን አለው ። ሁለቱም የሚመለሱበ ፮
ትን አገር ተካፈሉ ፡ አክዓብም ለብቻው ፡

በአንድ፡መንገድ÷አብድዩም፡ለብቻው፡በሌላ፡መንገድ፡ሄዱ ።

፯ አብድዩም ፡በመንገድ ፡ሲሄድ ÷እነሆ ÷ኤል
ያስ ፡ተገናኘው ፡አብድዩም ፡አወቀው ÷ በግ
ምባሩም ፡ተደፍቶ ፡— ጌታዬ ፡ሆይ ÷ኤልያስ፡
፰ አንተ ፡ነህን ? አለ ። ኤልያስም ፡— እኔ ፡ነኝ ፡
ሂደህ ፡ለጌታህ ፡— ኤልያስ ፡ተገኝቶአል ፡በል ፡
፱ አለው ። አብድዩም ፡አለ ፡— እኔን ፡በረያህን ፡እን
ዲገድል ፡በአክዓብ ፡እጅ ፡አሳልፈህ ፡ትሰጠኝ ፡
፲ ዘንድ ፡ምን ፡ኃጢአት ፡አድርጌአለሁ ? አም
ላክህ ፡ሕያው ፡እግዚአብሔርን ! ጌታዬ ፡ይፈ
ልግህ ፡ዘንድ ፡ያልላከበት ፡ሕዝብ ፡ወይም ፡
መንግሥት ፡የለም ፡ሁሉም ፡— በዚህ ፡የለም ፡
፲፩ ባሉ ፡ጊዜ ፡አንተን ፡እንዳላገኙ ፡መንግሥቱ
ንና ፡ሕዝቡን ፡አምሎአቸው ፡ነበር ። አሁ
ንም ÷እነሆ ፡— ሂድ ÷ኤልያስ ፡ተገኝ ፡ብለህ ፡
፲፪ ለጌታህ ፡ንገር ፡ትለኛለህ ። እኔም ፡ከአንተ ፡
ጥቂት ፡ራቅ ፡ስል ፡የእግዚአብሔር ፡መንፈስ፡
አንሥቶ ፡ወደማላውቀው ፡ስፍራ ፡ይወስድ
ሃል ፡እኔም ፡ገብቼ ፡ለአክዓብ ፡ስነገር ÷ ባያ
ገኘህ ፡ይገድለኛል ፡እኔም ፡ባሪያህ ፡ከትንሽ
ነቴ ፡ጀምሬ ፡እግዚአብሔርን ፡እፈራ ፡ነበር ።
፲፫ ኤልዛቤል ፡የእግዚአብሔርን ፡ነቢያት ፡በስን
ደለች ፡ጊዜ ÷ መቶውን ፡የእግዚአብሔር ፡ነቢ
ያት ፡ወስጀ ÷ አምሳ ፡አምሳውንም ፡በዋሻ ፡
ውስጥ ፡ሸሽጌ ÷ እንጀራና ፡ውኃ ፡የመገብኋ
ቸው ÷ ይህ ፡ያደረግሁት ፡ነገር ፡በውኑ ፡ለጌ
፲፬ ታዬ ፡አልታወቀህምን ? አሁንም ፡— ሂደህ ፡
ኤልያስ ፡ተገኝ ፡ብለህ ፡ለጌታህ ፡ንገር ፡ትላ
፲፭ ለህ ፡እርሱም ፡ይገድለኛል ። ኤልያስም ፡—
በፊቱ ፡የቆምሁት ፡የሠራዊት ፡ጌታ ፡ሕያው ፡
እግዚአብሔርን ! እኔ ፡ዛሬ ፡ለእርሱ ፡እገለጣ
ለሁ ፡አለ ።

፲፮ አብድዩም ፡አክዓብን ፡ሊገናኘው ፡ሂዶ ÷ነገ
ረውም ፡አክዓብም ፡ኤልያስን ፡ሊገናኘው ፡
፲፯ መጣ ። አክዓብም ፡ኤልያስን ፡በየው ፡ጊዜ ፡—
እስራኤልን ፡የምትገለብጥ ፡አንተ ፡ነህን ?
፲፰ አለው ። ኤልያስም ፡— እስራኤልን ፡የምትገ
ለብጠው ÷ የእግዚአብሔርን ፡ትእዛዝ ፡ትታ
ችሁ ፡በአሊምን ፡የተከተላችሁ ÷ አንተና ፡የአ
ባትህ ፡ቤት ፡ናችሁ ፡እንጂ ፡እኔ ፡አይደለሁም ።
፲፱ አሁንም ፡ልከህ ፡እስራኤልን ፡ሁሉ ÷በኤልዛ
ቤልም ፡ማዕድ ፡የሚበሉትን ፡አራት ፡መቶ ፡
አምሳ ፡የበአልን ፡ነቢያት ÷ አራት ፡መቶም ፡
የማምለኪያ ፡ዐፀድን ፡ነቢያት ፡ወደ ፡እኔ ፡
ወደ ፡ቀርሜሎስ ፡ተራራ ፡ሰብስብ ፡አለ ።

፳ አክዓብም ፡ወደ ፡እስራኤል ፡ልጆች ፡ሁሉ ፡
ልኮ ፡ነቢያቱን ፡ሁሉ ፡ወደ ፡ቀርሜሎስ ፡ተራራ ፡
፳፩ ሰበሰበ ። ኤልያስም ፡ወደ ፡ሕዝቡ ፡ሁሉ ፡
ቀርቦ ፡— እስከ ፡መቼ ፡ድረስ ፡በሁለት ፡አሳብ ፡
ታነክሳላችሁ ? እግዚአብሔር ፡አምላክ ፡ቢሆን ፡
እርሱን ፡ተከተሉ ፡በአል ፡ግን ፡አምላክ ፡
ቢሆን ፡እርሱን ፡ተከተሉ ፡አለ ። ሕዝቡም ፡
፳፪ አንዲት ፡ቃል ፡አልመለሱለትም ። ኤልያስም ፡
ሐ ፡ሠ ፡ነ ፡አለ ፡— ከእግዚአብሔር ፡ነቢያት ፡
እኔ ፡ብቻ ፡ቀርቻለሁ ፡የበአል ፡ነቢያት ፡ግን ፡
አራት ፡መቶ ፡አምሳ ፡ሰዎች ፡ናቸው ። ሁለት ፡ ፳፫
ወይፈኖች ፡ይሰጡን ፡እነርሱም ፡አንድ ፡ወይ
ፈን ፡ይምረጡ ÷ እየብልቱም ፡ይቀ ፡ረጡት ÷
በእንጨትም ፡ላይ ፡እሳት ፡ያኑሩት ÷ በበታቹም ፡
እሳት ፡አይጨምሩ ፡እኔም ፡ሁለተኛውን ፡ወይ
ፈን ፡አዘጋጃለሁ ÷ በእንጨቱም ፡ላይ ፡አኖረ
ዋለሁ ÷ በበታቹም ፡እሳት ፡አልጨምርም ። ፳፬
እናንተም ፡የአምላካቸሁን ፡ስም ፡ጥሩ ÷እኔም ፡
የእግዚአብሔርን ፡ስም ፡እጠራለሁ ፡ሰምቶም ፡
በእሳት ፡የሚመልስ ፡አምላክ ÷ እርሱ ፡አም
ላክ ፡ይሁን ። ሕዝቡም ፡ሁሉ ፡— ይህ ፡ነገር ፡
መልካም ፡ነው ፡ብለው ፡መለሱ ።

ኤልያስም ፡የበአልን ፡ነቢያት ፡— እናንተ ፡ ፳፭
ብዙዎች ፡ናችሁና ፡አስቀድማችሁ ፡አንድ ፡
ወይፈን ፡ምረጡና ፡አዘጋጁ ፡የአምላካችሁ
ንም ፡ስም ፡ጥሩ ÷ በበታቹም ፡እሳት ፡አትጨ
ምሩ ፡አላቸው ። ወይፈኑንም ፡ወስደው ፡አዘ ፳፮
ጋጁ ÷ ከጥዋትም ፡እስከ ፡ቀትር ፡ድረስ ፡—
በአል ፡ሆይ ÷ስማን ፡እያሉ ፡የበአልን ፡ስም ፡
ጠሩ ። ድምፅም ፡አልነበረም ÷የሚመልስም ፡
አልነበረም ፡በሠሩትም ፡መሠዊያ ፡ዙሪያ ፡እያ
ነከሱ ፡ያሸበሽቡ ፡ነበር ። በቀትርም ፡ጊዜ ፡ ፳፯
ኤልያስ ፡— አምላክ ፡ነውና ፡በታላቅ ፡ቃል ፡
ጩኹ ፡ምናልባት ፡አሳብ ፡ይዘታል ÷ወይም ፡
ፈቀቅ ፡ብሎአል ÷ወይም ፡ወደ ፡መንገድ ፡ሄዶ
አል÷ ወይም ፡ተኝቶ ፡እንደ ፡ሆነ ፡መቀስቀስ ፡
ያስፈልገዋል ፡እያለ ፡አላገጠባቸው ። በታላ ፳፰
ቅም ፡ቃል ፡ይጮኹ ÷እንደ ፡ልማዳቸውም ፡
ደማቸው ፡እስኪፈስስ ፡ድረስ ፡ገላቸውን ፡በካ
ራና ፡በቀጭኔ ፡ይብዋጭሩ ፡ነበር ። ቀትርም ፡ ፳፱
ከለፈ ፡በኋላ ፡መሥዋዕት ፡ሠርክ ፡እስኪደ
ርስ ፡ትንቢት ፡ይናገሩ ፡ነበር ፡ድምፅም ፡አል
ነበረም ÷ የሚመልስና ፡የሚያደምጥም ፡አልነ
በረም ።

ኤልያስም ፡ሕዝቡን ፡ሁሉ ፡— ወደ ፡እኔ ፡ ፴
ቅረቡ ፡አላቸው ። ሕዝቡም ፡ሁሉ ፡ወደ ፡እርሱ ፡
ቀረቡ ። ፈርሶ ፡የነበረውንም ፡የእግዚአሔ
ርን ፡መሠዊያ ፡አበጀ ። ኤልያስም ፡— ስምህ ፡ ፴፩
እስራኤል ፡ይሆናል ፡የሚል ፡የእግዚአሔር
ቃል ፡እንደ ፡ደረሰለት ፡እንደ ፡ያዕቆብ ፡ልጆች ፡
ነገድ ፡ቍጥር ፡አሥራ ፡ሁለቱን ፡ድንጋዮች ፡
ወሰደ ። ከድንጋዮችም ፡ለእግዚአብሔር ፡ስም ፡ ፴፪
መሠዊያ ፡ሠራ ። በመሠዊያውም ፡ዙሪያ ፡
ሁለት ፡መስፈሪያ ፡እህል ፡የሚያዝ ፡ጕድ
ጓድ ፡ቈፈረ ። እንጨቱንም ፡በተርታ ፡አደ ፴፫
ረገ ÷ወይፈኑንም ፡በብልት ፡በብልቱ ፡ቈረጠ ÷
በእንጨቱም ፡ላይ ፡አኖረና ፡— አራት ፡ጋን ፡
ውኃ ፡ሙሉ ፡በሚቃጠለው ፡መሥዋዕትና ፡ ፴፬
በእንጨቱ ፡ላይ ፡አፍስሱ ፡አለ ። ደግሞም ፡—
ድገሙ ፡አለ ፡እነርሱም ፡ደገሙ ። እርሱም ፡—
ሦስተኛ ፡አድርጉ ፡አለ ፡ሦስተኛም ፡አደረጉ ።
ውኃውም ፡በመሠዊያው ፡ዙሪያ ፡ፈሰሰ ፡ደግ ፡ ፴፭

ሞም ፡ጕድጓዱን ፡በውኃ ፡ሞላው ። መሥ
ዋዕተ ፡ሠርክ ፡በሚቀርብበት ፡ጊዜ ፡ነቢዩ ፡
ኤልያስ ፡ቀርቦ ፡— አቤቱ ፡የአብርሃምና ፡የይስ
ሐቅ ፡የእስራኤልም ፡አምላክ ፡ሆይ ÷ አንተ ፡
በእስራኤል ፡ላይ ፡አምላክ ፡እንደ ፡ሆንህ ÷
እኔም ፡ባሪያህ ፡እንደ ፡ሆንሁ ÷ ይህንም ፡ሁሉ ፡
፴፮ በቃልህ ፡እንዳደረግሁ ፡ዛሬ ፡ይገለጥ ። አንተ ÷
አቤቱ ÷ አምላክ ፡እንደ ፡ሆንህ ÷ ልባቸው
ንም ፡ደግሞ ፡እንደ ፡መለስህ ፡ይህ ፡ሕዝብ ፡
፴፯ ያውቅ ፡ዘንድ ፡ስማኝ ÷ አቤቱ ÷ስማኝ ፡አለ ።
፴፰ የእግዚአብሔርም ፡እሳት ፡ወደቀች ÷የሚቃ
ጠለውን ፡መሥዋዕቱንም ፡እንጨቱንም ፡ድን
ጋዮቹንም ፡አፈሩንም ፡በላች ÷ በጕድጓዱም ፡
፴፱ ውስጥ ፡ያለውን ፡ውኃ ፡ላሰች ። ሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ያንን ፡በዩ ፡ጊዜ ፡በግምባራቸው ፡ተደ
ፍተው ፡— እግዚአብሔር ፡እርሱ ፡አምላክ ፡
ነው ÷ እግዚአብሔር ፡እርሱ ፡አምላክ ፡ነው ፡
፵ አሉ ። ኤልያስም ፡— ከበአል ፡ነቢያት ፡አንድ፡
ሰው ፡እንዳያመልጥ ፡ያዙ ፡አላቸው ። ያዙአቸ
ውም ፡ኤልያስም ፡ወደ ፡ቂሶን ፡ወንዝ ፡ወስዶ ፡
በዚያ ፡አሳረዳቸው ።

፵፩ ኤልያስም ፡አክዓብን ፡— የገነናቡ ፡ውሽን
ፍር ፡እጅግ ፡ነውና ፡ተነሥተህ ፡ውጣ ÷ብላም ÷
፵፪ ጠጣም ፡አለው ። አክዓብም ፡ሊበላና ፡ሊጠጣ ፡
ወጣ ፡ኤልያስም ፡ወደ ፡ቀርሜሎስ ፡አናት ፡
ወጣ ፡ፊቱንም ፡በጕልበቱ ፡መካከል ፡አድ
፵፫ ርጎ ፡በግምባሩ ፡ተደፋ ። ብላቴናውንም ፡—
ወጥተህ ፡ወደ ፡ባሕሩ ፡ተመልከት ፡አለው ።
ወጥቶም ፡ተመልክቶም ፡— ምንም ፡የለም ፡
አለ ። እርሱም ፡— ሰባት ፡ጊዜ ፡ተመላለስ ፡
አለው ። ብላቴናውም ፡ሰባት ፡ጊዜ ፡ተመላ
፵፬ ለሰ ። በሰባተኛውም ፡ጊዜ ፡— እነሆ ÷የሰው ፡
እጅ ፡የምታህል ፡ታናሽ ፡ደመና ፡ከባሕር ፡
ወጣች ፡አለ ። እርሱም ፡— ወጥተህ ፡አክዓ
ብን ፡— ዝናብ ፡እንዳይከለክልህ ፡ሰረገላን ፡
፵፭ ጭነህ ፡ውረድ ፡በለው ፡አለ ። ከጥቂትም ፡
ጊዜ ፡በኋላ ፡ሰማዩ ፡ከደመናውና ፡ከነፋሱ ፡
የተነሣ ፡ጨለመ ÷ብዙም ፡ዝናብ ፡ሆነ ፡አክዓ
ብም ፡በሰረገላው ፡ተቀምጦ ፡ወደ ፡ኢይዝራ
፵፮ ኤል ፡ሄደ ። የእግዚአብሔርም ፡እጅ ፡በኤ
ልያስ ፡ላይ ፡ነበረች ፡ወገቡንም ፡አሸንፍጦ ፡
ወደ ፡ኢይዝራኤል ፡እስኪገባ ፡ድረስ ፡በአክ
ዓብ ፡ፊት ፡ይሮጥ ፡ነበር ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ አክዓብም ፡ኤልያስ ፡ይህን ፡ሁሉ ፡እንዳደ
ረገ ÷ ነቢያትንም ፡ሁሉ ፡በሰይፍ ፡እንደ ፡
፪ ገደለ ፡ለኤልዛቤል ፡ነገራት ። ኤልዛቤልም ፡—
ነገ ፡በዚህ ፡ጊዜ ፡ነፍስህን ፡ከእነዚህ ፡እንደ ፡
፫ አንዲቱ ፡ነፍስ ፡በላደርጋት ÷ አማልክት ፡
ይህን ፡ያድርጉብኝ ፡ይህንም ፡ይጨምሩብኝ ፡
ብላ ፡ወደ ፡ኤልያስ ፡መልእክተኛ ፡ላከች ።
፬ ኤልያስም ፡ፈርቶ ፡ተነሣ ÷ ነፍሱንም ፡ሊያ
ድን ፡ሄደ ÷ በይሁዳም ፡ወዳለው ፡ወደ ፡ቤር
ሳቤህ ፡መጥቶ ፡ብላቴናውን ፡በዚያ ፡ተው ።
፭ እርሱም ፡እንድ ፡ቀን ፡የሚያህል ፡መንገድ ፡ ፱
በምድረ ፡በዳ ፡ሄደ ፡መጥቶም ፡ከክትክታ ፡
ዛፍ ፡በታች ፡ተቀመጠና ፡— ይበቃኛል ፡
አሁንም ÷ አቤቴ ÷ እኔ ፡ከአባቶቼ ፡አልበ
ልጥምና ፡ነፍሴን ፡ውሰድ ፡ብሎ ፡እንዲ
ሞት ፡ለመነ ። በክትክታውም ፡ዛፍ ፡በታች ፡ ፭
ተጋደመ ፡እንቅልፍም ፡እንቀላፋ ፡እነሆም ÷
መልአክ ፡ዳሰሰውና ፡— ተነሥተህ ፡ብላ ፡
አለው ። ሲመለከትም ÷ እነሆ ፡በራሱ ፡አጠ ፮
ገብ ፡የተጋገረ ፡እንጉቻና ፡በማሰሮ ፡ውኃ ፡
አገኘ ። በላም ፡ጠጣም ÷ ተመልሶም ፡ተኛ ።
፯ የእግዚአሔር ፡መልአክ ፡ደግሞ ፡ሁለተኛ ፡
ጊዜ ፡መጥቶ ፡ዳሰሰውና ፡— የምትሄድበት ፡
መንገድ ፡ሩቅ ፡ነውና ፡ተነሥተህ ፡ብላ ፡አለው ።
፰ ተነሥቶም ፡በላ ፡ጠጣም ፡በዚያም ፡ምግብ ፡ ፲
ኃይል ፡አስከ ፡እግዚአሔር ፡ተራራ ፡አስከ ፡
ከሬብ ፡ድረስ ፡አርባ ፡ቀንና ፡አርባ ፡ሌሊት ፡
ሄደ ።

፱ እዚያም ፡ወዳለ ፡ዋሻ ፡መጣ ÷ በዚያም ፡ ፲፩
አደረ ፡እነሆም ፡— ኤልያስ ፡ሆይ ፡በዚህ ፡
ምን ፡ታደርጋለህ ? የሚል ፡የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ወደ ፡እርሱ ፡መጣ ። እርሱም ፡— ለሠ
ራዊት ፡አምላክ ፡ለእግዚአብሔር ፡እጅግ ፡
ቀንቻለሁ ፡የእስራኤል ፡ልጆች ፡ቃል ፡ኪዳ
ንህን ፡ትተዋልና ÷ መሠዊያዎችህንም ፡አፍር
ሰዋልና ÷ ነቢያትህንም ፡በሰይፍ ፡ገድለዋልና ፡
እኔም ፡ብቻዬን ፡ቀርቻለሁ ፡ነፍሴንም ፡ሊወ
ስዱአት ፡ይሻሉ ፡አለ ። እርሱም ፡— ውጣ ÷ ፲፪
በተራራውም ፡ላይ ፡በእግዚአሔር ፡ፊት ፡
ቁም ፡አለ ። እነሆም ÷እግዚአሔር ፡አለፈ ÷
በእግዚአሔርም ፡ፊት ፡ትልቅና ፡ብርቱ ፡
ነፋስ ፡ተራሮቹን ፡ሰንጠቀ ፡ዓለቶቹንም ፡
ሰባበረ ÷ እግዚአሔር ፡ግን ፡በነፋሱ ፡ውስጥ ፡
አልነበረም ። ከነፋሱም ፡በኋላ ፡የምድር ፡መና
ወጥ ፡ሆነ ÷ እግዚአሔር ፡ግን ፡በምድር ፡
መናወጥ ፡ውስጥ ፡አልነበረም ። ከምድር ፡መና ፲፫
ወጥ ፡በኋላ ፡እሳት ፡ሆነ ÷ እግዚአሔር ፡
ግን ፡በእሳቱ ፡ውስጥ ፡አልነበረም ። ከእሳ
ቱም ፡በኋላ ፡ትንሽ ፡የዝምታ ፡ድምፅ ፡
ሆነ ። ኤልያስም ፡ያን ፡በሰማ ፡ጊዜ ፡ፊቱን ፡
በመጐናጸፊያው ፡ሸፈነ ÷ ወጥቶም ፡በዋሻው ፡
ደጃፍ ፡ቆመ ። እነሆ ፡— ኤልያስ ፡ሆይ ÷ በዚህ ፡
ምን ፡ታደርጋለህ ? የሚል ፡ድምፅ ፡ወደ ፡
እርሱ ፡መጣ ። እርሱም ፡— ለሠራዊት ፡አም ፲፬
ላክ ፡ለእግዚአሔር ፡እጅግ ፡ቀንቻለሁ ፡የእ
ስራኤል ፡ልጆች ፡ቃል ፡ኪዳንህን ፡ትተዋልና ÷
መሠዊያዎችህንም ፡አፍርሰዋልና ÷ ነቢያትህ
ንም ፡በሰይፍ ፡ገድለዋልና ፡እኔም ፡ብቻዬን ፡
ቀርቻለሁ ፡ነፍሴንም ፡ሊወስዱአት ፡ይሻሉ ፡
አለ ።

እግዚአሔርም ፡አለው ፡— ሂድ ÷ በመጣ ፲፭
ህበትም ፡መንገድ ፡በምድረ ፡በዳ ፡ወደ ፡ደማ
ስቆ ፡ተመለስ ፡ከዚያም ፡በደረስህ ፡ጊዜ ፡በሶ

ርያ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አዛሄልን ፡
፲፮፡ ቅባው ፡ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ የናሚሲን ፡ ልጅ ፡ ኢዩን ፡ ቅባው ፡ በፋ
ንታህም ፡ ነቢይ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የአቤልመሖ
ላን ፡ ሰው ፡ የሣፋጥን ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕን ፡ ቅባው ፡
፲፯፡ ከአዛኤልም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጠውን ፡ ሁሉ ። ኢ
ዩ ፡ ይገድለዋል ፡ ከኢዩም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለ
፲፰፡ ጠውን ፡ ሁሉ ፡ ኤልሳዕ ፡ ይገድለዋል ። እኔም ፡
ከእስራኤል ፡ ጕልበታቸውን ፡ ለበኣል ፡ ያላንበ
ረከኩትን ፡ ሁሉ ፡ በአፋቸውም ፡ ያልሳሙትን ፡
ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ለእኔ ፡ አስቀራለሁ ።
፲፱፡ ከዚያም ፡ ሄደ ፡ የሣፋጥንም ፡ ልጅ ፡ ኤልሳ
ዕን ፡ በእሥራ ፡ ሁለት ፡ ጥማድ ፡ በሬዎች ፡ ሲያ
ርስ ፡ አርሶም ፡ ከእሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ጋር ፡
ሆኖ ፡ አገኘው ። ኤልያስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
፳፡ አልፎ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ ጣለበት ። በሬዎቹ
ንም ፡ ተወ ፡ ከኤልያስም ፡ በኋላ ፡ ሮጠ ፡— አባ
ቴንና ፡ እናቴን ፡ እስማቸው ፡ ዘንድ ፡ እባክህ ፡
ተወኝ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እከተልሃለሁ ፡ አለው ።
አርሶም ፡— ሂድና ፡ ተመለስ ፤ ምን ፡ አድርጌ
፳፩፡ ልሃለሁ ? አለው ። ከአርሶም ፡ ዘንድ ፡ ተመ
ለሰ ፡ ሁለቱን ፡ በሬዎች ፡ ወስዶ ፡ አረዳቸው ፡
ሥጋቸውንም ፡ በበሬዎቹ ፡ ዕቃ ፡ ቀቀለው ፡
ለሕዝቡም ፡ ሰጣቸው ፡ በሉም ፤ አርሶም ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ኤልያስን ፡ ተከትሎ ፡ ገሄደ ፡ ያገለግለ
ውም ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩፡ ለኢይዝራኤላዊውም ፡ ለናቡቴ ፡ በሰማርያ ፡
ንጉሥ ፡ በአክዓብ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የወይን ፡
፪፡ በታ ፡ ነበረው ። አክዓብም ፡ ናቡቴን ፡— በቤቴ ፡
አቅራቢያ ፡ ነውና ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ አደር
ገው ፡ ዘንድ ፡ የወይን ፡ ቦታህን ፡ ስጠኝ ፤ ስለ ፡
እርሱም ፡ ከእርሱ ፡ የተሻለ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡
እሰጥሃለሁ ፤ ወይም ፡ ብትወድድ ፡ ግምቱን ፡ ገን
፫፡ ዘብ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። ናቡቴም ፡
አክዓብን ፡— የአባቶቼን ፡ርስት ፡ እሰጥህ ፡ ዘንድ ፡
፬፡ እግዚአብሔር ፡ ያርቅልኝ ፡ አለው ። ኢይዝራ
ኤላዊውም ፡ ናቡቴ ፡— የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ አል
ሰጥህም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተናገረው ፡ አክዓብ ፡ ተቆ
ጥቶና ፡ ተናድዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። በአልጋ
ውም ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ፊቱን ፡ ተሸፋፈነ ፡ እን
፭፡ ጀራም ፡ አልበላም ።
ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥታ ፡—
ልብህ ፡ የሚያዝን ፡ እንጀራስ ፡ የማትበላ ፡ ስለ ፡
፮፡ ምንድር ፡ ነው ? አለችው ። እርሱም ፡—ኢይዝ
ራኤላዊውን ፡ ናቡቴን ፡— የወይንህን ፡ ቦታ ፡ በገ
ንዘብ ፡ ስጠኝ ፤ ወይም ፡ ብትወድድ ፡ በፋንታው ፡
ሌላ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ተናገ
ርሁት ፤ እርሱ ፡ ግን ፡— የወይን ፡ ቦታዬን ፡ አል
ሰጥህም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ መለሰልኝ ፡ ነው ፡ አላት ።
፯፡ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡— አንተ ፡ አሁን ፡ የእስ
ራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ትገዛለህን ? ተነሣ ፡ እንጀ
ራም ፡ ብላ ፡ ልብህም ፡ ደስ ፡ ይበላት ፤ የኢይ
ዝራኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰ
፰፡ ጥሃለሁ ፡ አለችው ። በአክዓብም ፡ ስም ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ጻፈች ። በማኅተሙም ፡ አተመችው ፡
በከተማው ፡ ወደ ፡ ነበሩትና ፡ ከናቡቴም ፡ ጋር ፡
፱፡ ወደ ፡ ተቀመጡት ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከበርቴ
ዎች ፡ ደብዳቤውን ፡ ላከች ። በደብዳቤውም ፡—
፲፡ ለስ ፡ ጾም ፡ አዋጅ ፡ ንገሩ ፡ ናቡቴንም ፡ በሕ
ዝቡ ፡ ፊት ፡ አስቀምጡት ፡ ሁለትም ፡ ምናም
ንቴ ፡ ሰዎች ፡ በፊቴ ፡ አስቀምጡና ፡— እግዚአ
ብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድበሐል ፡ ብለው ፡ የመ
ስክሩበት ፡ አውጥታችሁም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡
ውገሩት ፡ ብላ ፡ ጻፈች ።
፲፩፡ በከተማውም ፡ የተቀመጡት ፡ የከተማው ፡
ሰዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከበርቴዎችም ፡ ኤልዛ
ቤል ፡ እንዳዘዘቻቸውና ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ በተላ
ከው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።
፲፪፡ የጾም ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ፡ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡
፲፫፡ ፊት ፡ አስቀመጡት ። ሁለቱም ፡ ምናምንቴ ፡
ሰዎች ፡ ገብተው ፡ በፊቱ ፡ ተቀመጡ ፤ ምናም
ንቴዎቹ ፡ ሰዎችም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡— ናቡቴ ፡
እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድቦአል ፡ ብለው ፡
በናቡቴ ፡ ላይ ፡ መሰከሩ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከከ
ተማ ፡ አውጥተው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ወገ
፲፬፡ ሩት ። ወደ ፡ ኤልዛቤልም ፡— ናቡቴ ፡ ተወ
፲፭፡ ግሮ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ላኩ ። ኤልዛቤልም ፡
ናቡቴ ፡ ተወግሮ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡
ኤልዛቤል ፡ አክዓብን ፡— ናቡቴ ፡ ሞቶአል ፡
እንጂ ፡ በሕይወት ፡ አይደለምና ፡ በገንዘብ ፡
ይሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ያለውን ፡ የኢይዝራ
ኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ተነሥ
፲፮፡ ተህ ፡ ውረስ ፡ አለችው ። አክዓብም ፡ ናቡቴ ፡
እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ኢይዝራኤላዊው ፡ ወደ ፡ ናቡቴ ፡ ወይን ፡
ቦታ ፡ ሊወርድ ፡ ተነሣ ።
፲፯፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያ
ዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡—
፲፰፡ ተነሥተህ ፡ በሰማርያ ፡ የሚኖረውን ፡ የአስራ
ኤልን ፡ ንጉሥ ፡ አክዓብን ፡ ትገናኘ ፡ ዘንድ ፡
ውረድ ፤ እነሆ ፡ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡ በወረደ
በት ፡ በናቡቴ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አለ ።
፲፱፡ አንተም ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ገድለህ ፡ ወረስኸውን ? ብለህ ፡ ንገረው ። ደግ
ሞም ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ውሾች ፡ የናቡቴን ፡ ደም ፡ በላሱበት ፡ ስፍራ ፡
የአንተን ፡ ደም ፡ ይላሱ ፡ ይልሱታል ፡
ብለህ ፡ ንገረው ። አክዓብም ፡ ኤልያስን ፡—
፳፡ ጠላቴ ፡ ሆይ ፡ አገኘኸኝን ? አለው ። እርሱም ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡— አግኝቼሃለሁ ፤
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ ራስ
፳፩፡ ህን ፡ ሽጠሃልና ። እነሆ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣ
ብሃለሁ ፡ ፈጽሞም ፡ እጠርግሃለሁ ፤ ከአክዓ
ብም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተ
ለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ አጠፋለሁ ፤ በሥራ
፳፪፡ ሀም ፡ አስቴዋተኸኖልና ፡ አስራኤልንም ፡ አስ

ተሃልና ፡ ቤትህን ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡
ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አኪያም ፡ ልጅ ፡
፳፪፡ እንደ ፡ ባአስ ፡ ቤት ፡ አደርገዋለሁ ። ደግሞ ፡
እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤልዛቤል ፡— በኢይዝ
ራኤል ፡ ቅጥር ፡ አጠገብ ፡ ኤልዛቤልን ፡ ውሾች ፡
፳፬፡ ይበሉአታል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ከአክዓብም ፡
ወገኝ ፡ በከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞተውን ፡
ውሾች ፡ ይበሉታል ፤ በሚዳውም ፡ የሞተውን ፡
፳፭፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ። በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ክፋት ፡ ለመሥራት ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡
ሸጠ ፡ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ እንደ ፡ ነዳችው ፡
፳፮፡ እንደ ፡ አክዓብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። እግ
ዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ያጠ
ፋቸው ፡ አሞራውያን ፡ እንደ ፡ ሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ጣዖታትን ፡ በመከተል ፡ እጅግ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡
ሠራ ።
፳፯፡ አክዓብም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብ
ሱን ፡ ቀድዶ ፡ ገላውን ፡ ማቅ ፡ አለበሰ ፤ ጾመም ፡
በማቅ ፡ ላይም ፡ ተኛ ፡ ቀስስ ፡ ብሎም ፡ ሄደ ።
፳፰፡ ፳፱፡ ደግሞም ፡— አክዓብ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ተዋረደ ፡
አየህን ? በፊቴ ፡ የተዋረደ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በልጁ ፡
ዘመን ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣለሁ ፡
እንጂ ፡ በእርሱ ፡ ዘመን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላመ
፳፩፡ ጣም ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡
ቴስብያዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩፡ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሞኖራ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሠላሳ ፡
፪፡ ሁለት ፡ ነገሥት ፡ ነበሩ ፡ ፈረሰችና ፡ ሰረገሎችም ፡
ነበሩ ፡ ወጥቶም ፡ ሰማርያን ፡ ከበበ ። ወጋትም ።
፫፡ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አክዓብ ፡—
፬፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ብርህና ፡
ወርቅህ ፡ ለእኔ ፡ ነው ፡ ሴቶችህና ፡ መልክከሞ
ቹም ፡ ልጆችህ ፡ ለእኔ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
፭፡ ከተማይቱ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ። የእስራኤ
ልም ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፡— ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡
አንተ ፡ እንዳልህ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ለእኔም ፡ የሆ
፮፡ ነው ፡ ሁሉ ፡ የአንተ ፡ ነው ፡ አለ ። ደግሞም ፡
መልእክተኞች ፡ ተመልሰው ፡— ወልደ ፡ አዴር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— ቀድሞ ፡ ብርህንና ፡ ወርቅ
ህን ፡ ሴቶችህንና ፡ ልጆችህንም ፡ ትሰጠኛለህ ፡
፯፡ ብዬ ፡ ልኬብህ ፡ ነበር ፡ ነገም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ባሪያዎቼን ፡ እልክብሃለሁ ፡ ቤትህንም ፡ የባሪያ
ዎችህንም ፡ ቤቶች ፡ ይበረብራሉ ፡ ደስ ፡ የሚ
ያሰኛቸውንም ፡ ሁሉ ፡ በእጃቸው ፡ አድርገው ፡
ይወስዳሉ ፡ አለ ።
፰፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የአገሩን ፡ ሽማግሌ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ጠርቶ ፡— ተመልከቱ ፡ ይህም ፡
ሰው ፡ ክፋ ፡ እንዲሻ ፡ እዩ ፡ ስለ ፡ ሴቶቼ ፡ ስለ ፡
ልጆቼ ፡ ስለ ፡ ብሬና ፡ ወርቄም ፡ ላከብኝ ፡ እን
፱፡ ቢም ፡ አላልሁም ፡ አለ ። ሽማግሌዎችም ፡ ሁሉ ፡
ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡— አትስማው ፡ እሺም ፡ አት
፲፡ በለው ፡ አሉት ። ለወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክ
ተኞች ፡— ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡— ለእኔ ፡ ለባ
ሪያህ ፡ በመጀመሪያ ፡ የላክህብኝን ፡ ሁሉ ፡ አደ
ርጋለሁ ፡ ይህን ፡ ግን ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፡ አይ
ቻለችም ፡ በሉት ፡ አላቸው ። መልእክተኞችም ፡
ተመልሰው ፡ ይህን ፡ አወሩለት ። ወልደ ፡ አዴ
፲፩፡ ርም ፡— ለሚከተለኝ ፡ ሕዝብ ፡ የሰማርያ ፡ ትቢያ ፡
ሞልብኝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ከእስራኤልም ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ጦሩን ፡ እንደሚያወልቅ ፡ አይመክ ፡ አለው ።
፲፪፡ ወልደ ፡ አዴርም ፡ ያን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከነ
ገሥታቱ ፡ ጋር ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ይጠጣ ፡
ነበር ። ባሪያዎቹንም ፡— ተሰለፉ ፡ አላቸው ፡
እነርሱም ፡ በከተማይቱ ፡ ትይዩ ፡ ተሰለፉ ።
፲፫፡ እነሆም ፡ ነቢይ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡
ወደ ፡ አክዓብ ፡ ቀርቦ ፡— እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፡— ይህን ፡ ብዙ ፡ ሞኖራ ፡ ሁሉ ፡
ታያለህን ? እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በእጅህ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጠዋለሁ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ ታውቃለህ ፡ አለ ። አክዓብም ፡— በማን ?
፲፬፡ አለ ፡ አርሶም ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— በአውራጆቹ ፡ አለቆች ፡ ጕልማ
ሶች ፡ አለ ፡ አርሶም ፡— ሰልፉን ፡ ማን ፡ ይጀም
ራል ? አለ ፡ አርሶም ፡— አንተ ፡ አለው ። የአው
፲፭፡ ራጆቹንም ፡ አለቆች ፡ ጕልማሶች ፡ ቈጠረ ፡
ሁለት ፡ መቶም ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ነበሩ ፤ ከእነ
ርሱም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ቈጠረ ፡ ሰባትም ፡ ሺህ ፡
ነበሩ ።
፲፮፡ ቀትርም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወጡ ፤ ወልደ ፡
አዴር ፡ ረዳቶቹም ፡ ሠላሳ ፡ ሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡
እየጠጡ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሰክሩ ፡ ነበር ።
፲፯፡ የአውራጆቹም ፡ አለቆች ፡ ጕልማሶች ፡ አስ
ቀድመው ፡ ወጡ ፡ ወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክተ
ኞችን ፡ ላከ ፡ እነርሱም ፡ ሰዎች ፡ ከሰማርያ ፡
፲፰፡ ወጥተዋል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። እርሱም ፡—
ለሰላቸው ፡ ወይም ፡ ለሰልፍ ፡ መጥተው ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ በሕይወታቸው ፡ ያዙአቸው ፡ አለ ። እነ
፲፱፡ ዚህም ፡ የአውራጆች ፡ አለቆች ፡ ጕልማሶች ፡
ከከተማይቱ ፡ ወጡ ፡ ሠራዊትም ፡ ተከተላ
ቸው ። ሁሉም ፡ በእያንዳንዱ ፡ በፊቱ ፡ የነ
፳፡ በረውን ፡ ሰው ፡ ገደለ ። ሶርያውያንም ፡ ሸሹ ፡
እስራኤልም ፡ አሳደዱአቸው ፡ የሶርያም ፡
ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ በፈረሱ ፡ አመለጠ ።
፳፩፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥም ፡ ወጥቶ ፡ ፈረሶቹንና ፡
ሰረገሎቹን ፡ ያዘ ፡ ሶርያውያንንም ፡ በታላቅ ፡
ውጊት ፡ ገደላቸው ።
፳፪፡ ነቢዩም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ቀርቦ ፡—
የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይመ
ጣብሃልና ፡ ሂድ ፡ በርታ ፡ የምታደርገውንም ፡
ተመልከትና ፡ እወቅ ፡ አለው ። የሶርያም ፡
፳፫፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡— አምላ
ካቸው ፡ የተራሮች ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡

በርትተውብን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሚዳ ፡ ላይ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ብንዋጋ ፡ በእርግጥ ፡ እን
፰፬ በረታባቸዋለን ። ይህንም ፡ አድርግ ፤ ከጭፍሮችህ ፡ ነገሥታቱን ፡ አርቅ ፡ በፋንታቸውም ፡
፰፭ አለቆችን ፡ ሹም ። አንተም ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ጠፋብህ ፡ ሠራዊት ፡ ፈረሱን ፡ በፈረስ ፡ ፋንታ ፡
ሰረገላውንም ፡ በሰረገላ ፡ ፋንታ ፡ ሠራዊትን ፡ ቍጠር ፡ በሚዳም ፡ ላይ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እን
ዋጋለን ፡ በእርግጥም ፡ እንበረታባቸዋለን ። ምክራቸውንም ፡ ሰማ ፡ እንዲሁም ፡ አደረገ ።
፰፮ በሚመጣውም ፡ ዓመት ፡ ወልደ ፡ አዼር ፡ ሶርያውያንን ፡ አሰለፈ ፡ ከእስራኤልም ፡ ጋር ፡
፰፯ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ወጣ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተሰለፉ ፡ ሊገጥሙአቸውም ፡
ወጡ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ትናንሽች ፡ የፍየል ፡ መንጋዎች ፡ ሆነው ፡ በፊ
ታቸው ፡ ሰፈሩ ፡ ሶርያውያን ፡ ግን ፡ ምድሩን ፡
፰፰ ሞልተው ፡ ነበር ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ሶርያውያን ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የተራሮች ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሸለቆ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ ብለዋልና ፡ ይህን ፡
ታላቅ ፡ ጭፍራ ፡ ሁሉ ፡ በእጅህ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠ
ዋለሁ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡
፰፱ ታው ቃላችሁ ፡ አለው ። እነዚህም ፡ በእነዚያ ፡ ትይዩ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ሰፈሩ ፡ በሰባተኛውም ፡
ቀን ፡ ተጋጠሙ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከሶር
ያውያን ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ እግረኛ ፡
፱ ገደሉ ። የቀሩትም ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ወደ ፡ ከተ ማይቱ ፡ ውስጥ ፡ ሸሹ ፤ ቅጥሩም ፡ በቀሩት ፡ በዘጠ ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።
ወልደ ፡ አዼርም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ወደ ፡ አልፍኙ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።
፴፩ ባሪያዎቹም ፡ — እነሆ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ነገሥታት ፡ መሐሪዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ሰምተ
ናል ፡ በወገባችን ፡ ማቅ ፡ እንታጠቅ ፡ በራሳች
ንም ፡ ገመድ ፡ እንጠምጥም ፡ ወደ ፡ እስራኤ
ልም ፡ ንጉሥ ፡ እንውጣ ፤ ምናልባት ፡ ነፍስህን ፡
፴፪ ይምራታል ፡ አሉት ። ወገባቸውንም ፡ በማቅ ፡ ታጠቁ ፡ በራሳቸውም ፡ ገመድ ፡ ጠመጠሙ ፡ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መጥተው ፡ — ባሪ
ያህ ፡ ወልደ ፡ አዼር ፡ — ነፍሴን ፡ ትምራት ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ ብሎአል ፡ አሉት ። እር
ሱም ፡ — ገና ፡ በሕይወቱ ፡ አለን ? ወንድሜ ፡
፴፫ ነው ፡ አለ ። ሰዎቹም ፡ የደግ ፡ ምልክት ፡ አደረ
ጉትና ፡ ቃሉን ፡ ከአፋ ፡ ተቀብለው ፡ — ወንድ
ምህ ፡ ወልደ ፡ አዼር ፡ አለ ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — ሂዱ ፡ አምጡት ፡ አለ ። ወልደ ፡ አዼርም ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ ወጣ ፡ በሰረገላውም ፡ ላይ ፡ አስ
፴፬ ቀመጠው ። ወልደ ፡ አዼርም ፡ — አባቴ ፡ ከአ
ባትህ ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከተሞች ፡ እመልስልሃ
ለሁ ፤ አባቴ ፡ በሰማርያ ፡ እንዳደረገ ፡ አንተ ፡ በደማስቆ ፡ ገበያ ፡ ታደርጋለህ ፡ አለው ። እኅ
ዓብም ፡ — እኔም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አሰድ
ድሃለሁ ፡ አለ ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጎ ፡ ሰደደው ።
፴፭ ከነቢያትም ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፡ ባልንጀራውን ፡ — ምታኝ ፡ አለው ። ሰውዮውም ፡ ይመታው ፡ ዘንድ ፡
፴፮ አንቢ ፡ አለ ። እርሱም ፡ — የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማህምና ፡ እነሆ ፡ ከእኔ ፡ በራቅህ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ ይገድልሃል ፡ አለው ። ከእርሱም ፡ በራቀ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ።
፴፯ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አግኝቶ ፡ — ምታኝ ፡ አለው ። ሰውዮውም ፡ መታው ፡ በመምታቱም ፡
አቈሰለው ። ነቢዩም ፡ ሄዶ ፡ በመንገድ ፡ አጠ
፴፰ ገብ ፡ ንጉሡን ፡ ቆየው ፡ ዓይኖቹንም ፡ ብቀጻላው ፡ ሸፍኖ ፡ ተሸሸገ ። ንጉሡም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጮኸ ፡ — ባሪያህ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ መካ
ከል ፡ ወጣ ፤ እነሆም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አመጣና ፡ —
ይህን ፡ ሰው ፡ ጠብቅ ፡ ቢኰበልልም ፡ ነፍስህ ፡ በነፍሱ ፡ ፋንታ ፡ ትሆናለች ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ትከፍላለህ ፡ አለኝ ። ፴፱ ባሪያ
ህም ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ሲመለከት ፡ ጠፋ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ — ፍርድህ ፡ እንዲሁ ፡ ይሆናል ፤ አንተ ፡ ፈርደኽዋል ፡
አለው ። ፈጥኖም ፡ ቀጸላውን ፡ ከዓይኑ ፡ አነሣ ፡
፵ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀው ። እርሱም ፡ — እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — አኔ ፡ እርም ፡ ያልሁትን ፡
ሰው ፡ ከእጅህ ፡ አውጥተሃልና ፡ ነፍስህ ፡ በነ
ፍሱ ፡ ፋንታ ፡ ሕዝብህም ፡ በሕዝቡ ፡ ፋንታ ፡ ይሆናሉ ፡ አለው ። ፵፩ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ እየ
ተቈጣና ፡ እየተናደደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፡ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

ሶርያና ፡ እስራኤልም ፡ ሳያዋጉ ፡ ሦስት ፡ ፩ ዓመት ፡ ተቀመጡ ። ፪ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡
የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወረደ ። ፫ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪ
ያዎቹን ፡ — ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የእኛ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እኛም ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ሳንወ
ስዳት ፡ ዝም ፡ እንዳልን ፡ ታውቃላችሁን ? አላ
ቸው ። ፬ ኢዮሣፍጥንም ፡ — በሬማት ፡ ዘገለ
ዓድ ፡ እንዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትመጣለ
ህን ? አለው ። አዮሣፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ — እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡
ሕዝብህ ፡ ፈረሶቼም ፡ እንደ ፡ ፈረሶችህ ፡ ናቸው ፡ አለው ።
፭ ኢዮሣፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ — የእ
ግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አስቀድመህ ፡ ትጠይቅ ፡
፮ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነቢያቶቹን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ የሚያህሉ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፡ — ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ ልሂድን ? ወይስ ፡ ልቅር ? አላቸው ።
እነርሱም ፡ — እግዚአብሔር ፡ በንጉሥ ፡ እጅ ፡
፯ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፡ ውጣ ፡ አሉት ። ኢዮ
ሣፍጥ ፡ ግን ፡ — እንጠይቀው ፡ ዘንድ ፡ ሌላ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ?
፰ አለ ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሣፍጥን ፡ — እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ የይምላ ፡
ልጅ ፡ ሚክያስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡
አይናገርልኝምና ፡ እጠላዋለሁ ፡ አለው ። ኢዮ
ሣፍጥም ፡ — ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አይበል ፡ አለ ።
፱ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አንዱን ፡ ጃንደረባ ፡
ጠርቶ ፡ — የይምላን ፡ ልጅ ፡ ሚክያስን ፡ ፈጥ
፲ ነህ ፡ አምጣ ፡ አለው ። የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ ልብሰ ፡ መንግ
ሥት ፡ ለብሰው ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡
አጠገብ ፡ በአደባባይ ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ ላይ ፡
ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ነቢያቶቹም ፡ ሁሉ ፡ በፊ
፲፩ ታቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ። የክን
ዓና ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስም ፡ የብረት ፡ ቀንዶች ፡
ሠርቶ ፡ — እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ —
፲፪ እስከ ፡ ጠፋ ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ሶርያውያንን ፡
ትወጋለህ ፡ አለ ። ነቢያትም ፡ ሁሉ ፡ — እግዚ
አብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታ
ልና ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ሂድና ፡ ተከና
ወን ፡ እያሉ ፡ እንዲህ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።
፲፫ ሚክያስንም ፡ ሊጠራ ፡ የሄደ ፡ መልእክ
ተኛ ፡ — እነሆ ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ አፍ ፡
ሆነው ፡ ለንጉሡ ፡ መልካምን ፡ ይናገራሉ ፡ ቃል
ህም ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ እንዲሆን ፡ መልካም ፡
፲፬ እንድትናገር ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለው ። ሚክያ
ስም ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! እግዚአብ
ሔር ፡ የሚነግረኝን ፡ እርሱን ፡ እናገራለሁ ፡
፲፭ አለ ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ —
ሚክያስ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰ
ልፍ ፡ እንሂድን ? ወይስ ፡ እንቅር ? አለው ፡ እር
ሱም ፡ — ውጣና ፡ ተከናወን ፤ እግዚአብሔርም ፡
በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታል ፡ ብሎ ፡ መለ
፲፮ ሰለት ። ንጉሡም ፡ — ከእውነት ፡ በቀር ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንዳትነግረኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡
፲፯ አምልሃለሁ ? አለው ። እርሱም ፡ — እስራኤል ፡
ሁሉ ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ በተራሮች ፡
ላይ ፡ ተበትነው ፡ አየሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ —
ለእነዚህ ፡ ጌታ ፡ የላቸውም ፡ እያንዳንዱም ፡
በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡
፲፰ ተናገረ ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሣፍ
ጥን ፡ — ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ እንደማይናገ
፲፱ ርልኝ ፡ አላልሁህምን ? አለው ። ሚክያስም ፡
አለ ፡ — እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ የሰ
ማይም ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡
፳ ቆመው ፡ አየሁ ። እግዚአብሔርም ፡ — ወዋቶ ፡
በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይወድቅ ፡ ዘንድ ፡ አክዓ
ብን ፡ የሚያሳስት ፡ ማን ፡ ነው ? አለ ። አንዱም ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሌላውም ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡
፳፩ ነገር ፡ ተናገረ ። መንፈስም ፡ ወጣ ፡ በእግዚአ

ብሔርም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ — እኔ ፡ አሳስተዋለሁ ፡
አለ ። እግዚአብሔርም ፡ — በምን ? አለው ። ፳፪
እርሱም ፡ — ወጥቼ ፡ በነቢያቶቹ ፡ ሁሉ ፡ አፍ ፡
ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ እሆናለሁ ፡ አለ ። እግዚአ
ብሔርም ፡ — ማሳሳትስ ፡ ታሳስተዋለህ ፡ ይሆን
ልሃልም ፡ ውጣ ፡ እንዲሁም ፡ አድርግ ፡ አለ ።
፳፫ አሁንም ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡
በነቢያትህ ፡ ሁሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡
አድርጎአል ፡ እግዚአብሔርም ፡ በላይህ ፡ ክፉ ፡
ተናግሮብሃል ።
፳፬ የክንዓናም ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ቀረበ ፡ ሚክያ
ስንም ፡ ጕንጩን ፡ በጥፊ ፡ መታውና ፡ — አንተን ፡
ሊናገር ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በምን ፡
መንገድ ፡ ከእኔ ፡ አለፈ ? አለ ። ፳፭ ሚክያስም ፡ —
እነሆ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ልትሸሸግ ፡ ወደ ፡ እልፍ
ኝህ ፡ በሄድህ ፡ ጊዜ ፡ ታያለህ ፡ አለ ። ፳፮ የእስራኤ
ልም ፡ ንጉሥ ፡ — ሚክያስን ፡ ውሰዱ ፡ ወደ ፡
ከተማይቱም ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ወደ ፡ ንጉ
ሡም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአስ ፡ መልሳችሁ ፡ —
፳፯ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — በደኅና ፡ እስከመ
ለስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ አኑሩት ፡
የመከራም ፡ እንጀራ ፡ መግቡት ፡ የመከራም ፡
ውኃ ፡ አጠጡት ፡ በሉ ፡ አለ ። ፳፰ ሚክያስም ፡ —
በደኅና ፡ ብትመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ የተ
ናገረ ፡ አይደለም ፡ አለ ። ደግሞም ፡ — አሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ ሆይ ፡ ስሙኝ ፡ አለ ።
፳፱ የእስራኤልም ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ኢዮሣፍጥ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ወጡ ።
፴ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሣፍጥን ፡ — ልብ
ሴን ፡ ለውፋው ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እገባለሁ ፡ አንተ ፡
ግን ፡ ልብስህን ፡ ልበስ ፡ አለው ። የእስራኤ
ልም ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ ለውጦ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡
ገባ ። ፴፩ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለቱን ፡ የሰ
ረገሎች ፡ አለቆች ፡ — ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡
በቀር ፡ ታናሽ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ዝማና
ቸው ፡ ጋር ፡ አትግጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዝዞ ፡ ነበር ።
፴፪ የሰረገሎች ፡ አለቆችም ፡ ኢዮሣፍጥን ፡ በዩ ፡
ጊዜ ፡ — በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡
አሉ ፡ ይገጥሙትም ፡ ዘንድ ፡ ከበቡት ፤ ኢዮሣ
ፍጥም ፡ ጮኸ ። ፴፫ የሰረገሎች ፡ አለቆችም ፡ የእ
ስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንዳልሆነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እር
ሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሱ ። ፴፬ አንድ ፡ ሰውም ፡
ቀስቱን ፡ ድንገት ፡ ገትሮ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡
በጥሩሩ ፡ ልብስ ፡ መጋጠሚያ ፡ በኩል ፡ ወጋው ፤
ሰረገለኛውንም ፡ — መልሰህ ፡ ጎዳ ፡ ተወግቻለ
ሁና ፡ ከሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ በረታ ፤ ንጉሡም ፡ በሰ ፴፭
ርያውያን ፡ ፊት ፡ በሰረገላው ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፤
ነበር ፡ ማታም ፡ ሞተ ፤ የቍስሉም ፡ ደም ፡ በሰ
ረገላው ፡ ውስጥ ፡ ፈሰሰ ። ፴፮ በሠራዊቱም ፡ መካ
ከል ፡ ፀሐይ ፡ ስትገባ ፡ — ንጉሡ ፡ ሞቶአልና ፡
እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ እያንዳንዱም ፡
ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሂድ ፡ የሚል ፡ ጩኸት ፡ ሆነ ።
፴፯ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጡ ፡ ንጉሡንም ፡ በሰ

ማርያ ፡ ቀበሩት ። አመንዝሮች ፡ በታጠቡበት ፡ በሰማርያ ፡ ሁሬ ፡ ሰረገላውን ፡ አጠቡት ÷ እግዚ አብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ቃል ፡ ውሾች ፡ ደሙን ፡ ላሱት ። የቀረውም ፡ የአክዓብ ፡ ነገር ÷ ያደረገውም ፡ ሁሉ ÷ ከዝሆን ፡ ጥርስም ፡ የሠራው ፡ ቤት ÷ የሠራቸውም ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? አክዓብም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።

አክዓብም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሳ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ። ኢዮሣፍጥ ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነበገሠ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዓዙባ ፡ የተባለች ፡ የሺልሒ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። በአባቱም ፡ በአሳ ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ሄደ ÷ ከእርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ በከረብቶች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አላራቀም ፡ ሕዝቡ ፡ ገና ፡ በከረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ። ኢዮሣፍጥም ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ታረቀ ።

የቀረውም ፡ የኢዮሣፍጥ ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ኀይከና ÷ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ ተወጋ ÷ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ከአባቱ ፡ ከአሳ ፡ ዘመን ፡ የተረፋትን ፡ ሰዶማውያን ፡ ከምድር ፡ አጠፋ ። በኤዶምያ ስም ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፡ ሹመም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ። ኢዮሣፍጥም ፡ ወደ ፡ አፈር ፡ ሄደው ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ የተርሴስን ፡ መርከቦች ፡ ሠራ ። ነገር ፡ ግን ፡ መርከቦቹ ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ ተሰበሩ ፡ እንጂ ፡ አልሄዱም ። የአክዓብም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ኢዮሣፍጥን ፡ — ባሪያዎቼ ፡ ከባሪያዎችህ ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡ ይሂዱ ፡ አለው ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ ግን ፡ አልወደደም ። ኢዮሣፍጥም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ፡ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ ኢዮራም ፡ ነገሠ ።

በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሣፍጥ ፡ በአሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የአክዓብ ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፡ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ከፋ ፡ አደረገ ÷ በአባቱና ፡ በእናቱም ፡ መንገድ ÷ እስራኤልንም ፡ ባሳተው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ሄደ ። በአልንም ፡ አመለከ ፡ ሰገደለትም ፡ አባቱም ፡ እንዳደረገ ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ።

(እርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ራብዕ ፡ ነው ።)

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ አክዓብም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሞዓብ ፡ በእስራ ፪ ኤል ፡ ላይ ፡ ሀመፀ ። አካዝያስም ፡ በሰማርያ ፡ በሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ከነይኑ ፡ ርግቡ ፡ ወድቆ ፡ ታመመ ። እርሱም ፡ — ሂዱ ፡ ከዚህም ፡ ደዌ ፡ እድን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፫ ላከ ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ቴስብያዊውን ፡ ኤልያስን ፡ — ተነሣ ÷ የሰማርያን ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተኞች ፡ ለመገናኘት ፡ ውጣና ፡ — የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ የምትሄዱት ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፬ አምላክ ፡ ስለሌለ ፡ ነውን ? ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል — ትሞታለህ ፡ እንጂ ፡ ከወጣህበት ፡ አልጋ ፡ አትወርድም ፡ በላቸው ። ኤልያስም ፡ ሄደ ።

መልእክተኞችም ፡ ወደ ፡ አካዝያስ ፡ ተመለሱ ÷ እርሱም ፡ — ለምን ፡ ተመለሳችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፡ — አንድ ፡ ሰው ፡ ሊገናኘን ፡ መጣና ፡ — ሂዱ ፡ ወደ ፡ ላካችሁም ፡ ንጉሥ ፡ ተመልሳችሁ ፡ — እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል — የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ የላክህ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አምላክ ፡ ስለሌለ ፡ ነውን ? ስለዚህ ፡ ትሞታለህ ፡ እንጂ ፡ ከወጣህበት ፡ አልጋ ፡ አትወርድም ፡ በሉት ፡ አለን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — ሊገናኛችሁ ፡ የወጣው ÷ ይህንስ ፡ ቃል ፡ የነገራችሁ ፡ ሰው ፡ መልኩ ፡ ምን ፡ ይመስላል ? አላቸው ። እነርሱም ፡ — ሰውዮው ፡ ጠጕራም ፡ ነው ÷ በወገቡም ፡ ጠፍር ፡ ታጥቆ ፡ ነበር ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — ቴስብያዊው ፡ ኤልያስ ፡ ነው ፡ አለ ።

ንጉሡም ፡ የአምሳ ፡ አለቃውን ፡ ከአምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሰደደ ÷ ወደ ፡ እርሱም ፡ ወጣ ፡ እነሆም ÷ በተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ÷ ንጉሡ ፡ — ውረድ ፡ ይልሃል ፡ አለው ። ኤልያስም ፡ መልሶ ፡ የአምሳ ፡ አለቃውን ፡ — እኔስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድ ÷ አንተንም ÷ አምሳውንም ፡ ሰዎችህን ፡ ትብላ ፡ አለው ። እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ እርሱንና ፡ አምሳውን ፡ ሰዎቹን ፡ በላች ። ደግሞም ፡ ሌላ ፡ የአምሳ ፡ አለቃ ፡ ከአምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ላከበት ፡ እርሱም ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ÷ ንጉሡ ፡ — ፈጥነህ ፡ ውረድ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ኤልያስም ፡ — እኔስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድ ÷ አንተንም ፡ አምሳውንም ፡ ሰዎችህን ፡ ትብላ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ እርሱንና ፡ አምሳውን ፡ ሰዎቹን ፡ በላች ። ደግሞም ፡ ሦስተኛ ፡ የአምሳ ፡ አለቃ ፡ ከአምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሰደደ ፡ ሦስተኛውም ፡ የአምሳ ፡ አለቃ ፡ ወጥቶ ፡ በኤልያስ ፡ ፊት ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበረከከና ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ÷ ነፍሴና ፡ የእነዚህ ፡ የአምሳው ፡ ባሪያዎችህ ፡ ነፍስ ፡ በፊትህ ፡ የከበረች ፡ ትሁን ። እነሆ ÷ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ የፊተኞቹን ፡ ሁለቱን ፡ የአምሳ ፡ አለቆችና ፡ አምሳ ፡ አምሳውን ፡ ሰዎቻቸውን ፡ በላች ። አሁን ፡ ግን ፡ ነፍሴ ፡ በፊትህ ፡ የከበረች ፡ ትሁን ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ኤልያስን ፡ — ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ውረድ ÷ አትፍራውም ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወረደ ። ኤልያስም ፡ — እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል — የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ልከሃልና ፡ ትሞታለህ ፡ እንጂ ፡ ከወጣህበት ፡ አልጋ ፡ አትወርድም ፡ አለው ።

ኤልያስም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሞተ ። ልጅም ፡ አልነበረውምና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሣፍጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወንድሙ ፡ ኢዮራም ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። አካዝያስ ፡ ያደረገው ፡ የቀረው ፡ ነገር ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ?

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኤልያስን ፡ በወሰሎ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሊያወጣው ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ ከኤልሳዕ ፡ ጋር ፡ ከጊ ፪ ልገላ ፡ ተነሣ ። ኤልያስም ፡ ኤልሳዕን ፡ — እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ልኮኛልና ፡ በዚህ ፡ ቆይ ፡ አለው ። ኤልሳዕም ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በሕያው ፡ ነፍስህም ፡ እምላለሁ ÷ አልለይህም ፡ አለ ። ወደ ፡ ቤቴልም ፡ ወረዱ ። በቤቴልም ፡ የነበሩ ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ወጥተው ፡ — እግዚአብሔር ፡ ጌታህን ፡ ከራስህ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ እንዲወስደው ፡ አውቀህልን ? አሉት ። እርሱም ፡ — አዎን ÷ አውቄአለሁ ፤ ዝም ፡ በሉ ፡ አላቸው ። ኤልያስም ፡ — ኤልሳዕ ፡ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ልኮኛልና ፡ እባክህ ÷ በዚህ ፡ ቆይ ፡ አለው ። እርሱም ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በሕያው ፡ ነፍስህም ፡ እምላለሁ ÷ አልለይህም ፡ አለ ። ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጡ ። በኢያሪኮም ፡ የነበሩ ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ቀርበው ፡ — እግዚአብሔር ፡ ጌታህን ፡ ከራስህ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ እንዲወስደው ፡ አውቀሃልን ? አሉት ። እርሱም ፡ — አዎን ÷ አውቄአለሁ ፤ ዝም ፡ በሉ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ኤልያስም ፡ — እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ልኮኛልና ፡ እባክህ ÷ በዚህ ፡ ቆይ ፡ አለው ። እርሱም ፡ — ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በሕያው ፡ ነፍስህም ፡ እምላለሁ ÷ አልለይህም ፡ አለ ። ሁለቱም ፡ ሄዱ ።

ከነቢያትም ፡ ልጆች ፡ አምሳ ፡ ሰዎች ፡ ሄዱ ÷ ፯ በፈታቸውም ፡ ርቀው ፡ ቆሙ ፤ እነዚህም ፡ ሁለቱ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዳር ፡ ቆመው ፡ ነበር ። ኤልያስም ፡ መጐናጸፊያውን ፡ ወስዶ ፡ ጠቀለለው ÷ ውኃውንም ፡ መታ ÷ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ ተከፈለ ። ሁለቱም ፡ በደረቅ ፡ ተሻገሩ ። ከተሻገሩም ፡ በኋላ ፡ ኤልያስ ፡ ኤልሳዕን ፡ — ፱ ከአንተ ፡ ሳልወሰድ ፡ አደርግልህ ፡ ዘንድ ፡ የምትሻውን ፡ አለው ፡ ኤልሳዕም ፡ — መንፈስህ ፡ በእጥፍ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለ ። እርሱም ፡ — አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ለምነሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእንተ ፡ ዘንድ ፡ በተወሰድሁ ፡ ጊዜ ፡ ብታየኝ ፡ ይሆንልህ ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ አይሆንልህም ፡ አለ ። ሲሄዱም ÷ እያዘገሙም ፡ ሲጫወቱ ÷ እነሆ ፡ ፲፩ የእሳት ፡ ሰረገላና ፡ የእሳት ፡ ፈረሶች ፡ በመካከላቸው ፡ ገብተው ፡ ከፈሉአቸው ፤ ኤልያስም ፡ በወሙሉ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።

ኤልሳዕም ፡ አይቶ ፡ — አባቴ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ÷ ፲፪ የእስራኤል ፡ ሰረገላና ፡ ፈረሰኞች ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ አላየውም ፡ ልብሱንም ፡ ይዞ ፡ ከሁለት ፡ ተረተረው ። ከኤልያስም ፡ የወደቀውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ አነሣ ÷ ተመልሶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዳር ፡ ቆመ ። ከኤልያስም ፡ ፲፫ የወደቀውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ወስዶ ፡ ውኃውን ፡ መታና ፡ — የኤልያስ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ ነው ? አለ ፤ ውኃውንም ፡ በመታ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ተከፈለ ፤ ኤልሳዕም ፡ ተሻገረ ።

ከኢያሪኮም ፡ መጥተው ፡ በአንጻሩ ፡ የነበሩት ፡ ፲፭ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ — የኤልያስ ፡ መንፈስ ፡ በኤልሳዕ ፡ ላይ ፡ ዐርፎአል ፡ አሉ ። ሊገናኙትም ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተደፉ ። እነርሱም ፡ — እነሆ ÷ ከባሪያዎችህ ፡ ፲፮ ጋር ፡ አምሳ ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ተራራ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሸለቆ ፡ ጥሎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ሄደው ፡ ጌታህን ፡ ይፈልጉት ፡ ዘንድ ፡ እንለምንሃለን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — አትስደዱ ፡ አላቸው ። እስኪያፍርም ፡ ድረስ ፲፯ ግድ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ — ስደዱ ፡ አለ ፤ አምሳም ፡ ሰዎች ፡ ሰደዱ ፤ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ፈልገው ፡ አላገኙትም ። በኢያሪኮም ፡ ተቀምጠው ፲፰ ሳለ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተመለሱ ፤ እርሱም ፡ — አትሂዱ ፡ አላልኋችሁምን ? አላቸው ።

የከተማይቱም ፡ ሰዎች ፡ ኤልሳዕን ፡ — እነሆ ÷ ፲፱ ጌታችን ፡ እንደምታይ ፡ የዚች ፡ ከተማ ፡ ኑር ፡ መልክም ፡ ነው ፤ ውኃው ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነው ÷ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ትጨነግፋለች ፡ አሉት ።

፰ እርሱም ፡— አዲስ ፡ ማሰሮ ፡ አምጡልኝ ፡ ፡ ፡

በሕፃኑ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ አኖረው ። ነገር ፡ ግን ፡ ድምፅ ፡ ወይም ፡ መስማት ፡ አልነበረም ፡ እርሱንም ፡ ሊገናኘው ፡ ተመልሶ ፡— ሕፃኑ ፡ አልነቃም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

፴፬፡ ኤልሳዕም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሕፃኑ ፡ ሞቶ ፡ በአልጋው ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡

፴፫፡ ነበር ። ገብቶም ፡ በሩን ፡ ከሁለቱ ፡ በኋላ ፡ ዘጋ ፡

፴፬፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየ ። መጥቶም ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፡ አፉንም ፡ በአፉ ፡ ዓይኑንም ፡ በዓይኑ ፡ እጁንም ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ተጋደመበት ፡ የሕፃኑም ፡ ገላ ፡ ሞቀ ። ተመልሶም ፡

፴፭፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ተመላለሰ ፡ ደግሞም ፡ ወጥቶ ፡ ሰበት ፡ ጊዜ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ፡ ሕፃኑም ፡ ዓይኖቹን ፡

፴፮፡ ከፈተ ። ግያዝንም ፡ ጠርቶ ፡— ይህችን ፡ ሱነማዊት ፡ ጥራ ፡ አለው ። ጠራትም ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡— ልጅሽን ፡ አንሥተሽ ፡

፴፯፡ ውሰጂ ፡ አላት ። ገብታም ፡ በእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ወደቀች ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ተደፋች ፡ ልጅዋንም ፡ አንሥታ ፡ ወጣች ።

፴፰፡ ኤልሳዕም ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ መጣ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ነበረ ፡ የነቢያትም ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ሎሌውንም ፡— ታላቁን ፡ ምንቸት ፡ ጣጅ ፡ ለነቢያት ፡

፴፱፡ ልጆችም ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ አለው ። አንዱም ፡ ቅጠላቅጠል ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ። የምድረ ፡ በዳውንም ፡ ሐረግ ፡ አገኘ ፡ ከዚያም ፡ የበረዘ ፡ ቅል ፡ ሰበሰበ ። ልብሱንም ፡ ሞልቶ ፡ ተመለሰ ። መትሮም ፡ በወጡ ፡ ምንቸት ፡ ውስጥ ፡ ጨመረው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

፵፡ ግን ፡ አላወቁም ። ሰምቼም ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ቀዱ ፡ ወጡንም ፡ በቀመሱ ፡ ጊዜ ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ በምንቸቱ ፡ ውስጥ ፡ ሞት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ጮኹ ፡ ይብሉም ፡ ዘንድ ፡

፵፩፡ አልቻሉም ። እርሱም ፡— ዱቄት ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፡ በምንቸቱም ፡ ውስጥ ፡ ጥሎ ፡— ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ቅዱ ፡ አለ ። በምንቸቱም ፡ ውስጥ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልተገኘም ።

፵፪፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ከበኣልሻሊሻ ፡ የበኩራቱን ፡ እንጀራ ፡ ሀያ ፡ የገብስ ፡ እንጀራ ፡ የእህልም ፡ እሸት ፡ በአቁማዳ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መጣ ። እርሱም ፡— ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስጣቸው ፡ አለ ። ሎሌውም ፡— ይህን ፡

፵፫፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ለመቶ ፡ ሰው ፡ እሰጣለሁ ? አለ ። እርሱም ፡— ይበላሉ ፡ ያተርፋሉም ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሮአልና ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡

፵፬፡ ለሕዝቡ ፡ ስጣቸው ፡ አለ ። እንዲሁም ፡ በፊታቸው ፡ አኖረው ። እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በሉ ፡ አተረፉም ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ንዕማን ፡ እግዚአብሔር ፡ በእርሱ ፡ እጅ ፡ ለሶርያ ፡ ደኅንነትን ፡ ስለ ፡ ሰጠ ፡ በጌታው ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ከቡር ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ደግሞም ፡ ጽኑዕ ፡ ኃያል ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለምጻም ፡ ነበረ ። ከሶርያውያንም ፡ አገር ፡ አደጋ ፡ ጣሪች ፡ ወጥተው ፡ ነበር ። ከእስራኤልም ፡ ምድር ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ ሴት ፡ ማርከው ፡ ነበር ፤ የንዕማንንም ፡ ሚስት ፡ ታገለግል ፡ ነበር ። እመቤትዋንም ፡— ጌታዬ ፡ በሰማርያ ፡ ካለው ፡ ከነቢዩ ፡ ፊት ፡ ቢያርስ ፡ ኖሮ ፡ ከለምጹ ፡ በፈወሰው ፡ ነበር ፡ አለቻት ። ንዕማንም ፡ ገብቶ ፡ ለጌታው ፡— ከእስራኤል ፡ አገር ፡ የሆነች ፡ አንዲት ፡ ብላቴና ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ብላለች ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ንዕማንን ፡— ሂድ ፡ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ እልክለሁ ፡ አለው ። እርሱም ፡ ሄደ ፡ አሥርም ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ስድስት ፡ ሺህም ፡ ወርቅ ፡ አሥርም ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ። ለእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡— ይህች ፡ ደብዳቤ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ስትደርስ ፡ ባሪያዬን ፡ ንዕማንን ፡ ከለምጹ ፡ ትፈውሰው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰደድሁልህ ፡ እወቅ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ወሰደ ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤውን ፡ በነበበ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡— ሰውን ፡ ከለምጹ ፡ እፈውስ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መስደዱ ፡ እኔ ፡ በውኑ ፡ ለመግደልና ፡ ለማዳን ፡ የምችል ፡ አምላክ ፡ ሆኜ ፡ ነውን ? ተመልከቱ ፡ የጠብ ፡ ምክንያትም ፡ እንደሚፈልግብኝ ፡ እዩ ፡ አለ ።

፰ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ኤልሳዕ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ እንደ ፡ ቀደደ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡— ልብስህን ፡ ለምን ፡ ቀደድህ ? ወደ ፡ እኔ ፡ ይምጣ ፡ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ነቢይ ፡ እንዳለ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ላከ ።

፱ ንዕማንም ፡ በፈረሱና ፡ በሰረገላው ፡ መጣ ፡ በኤልሳዕም ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ውጭ ፡ ቆመ ። ኤልሳዕም ፡— ሂድ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ታጠብ ! ሥጋህም ፡ ይፈወሰል ፡ አንተም ፡ ንጹሕ ፡ ትሆናለህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መልእክተኛ ፡ ላከ ። ንዕማን ፡ ግን ፡ ተቈጥቶ ፡ ሄደ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡— እነሆ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚመጣ ፡ ቆሞም ፡ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ የለምጹንም ፡ ስፍራ ፡ በእጁ ፡ ዳስሶ ፡ የሚፈውሰኝ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ። የደማስቆ ፡ ወንዞች ፡ አባናና ፡ ፋርፋር ፡ ከእስራኤል ፡ ውኆች ፡ ሁሉ ፡ አይሻሉምን ? በእነርሱስ ፡ ውስጥ ፡ መታጠብና ፡ መንጻት ፡ አይቻለኝም ፡ ኖሮአልን ? ዘወርም ፡ ብሎ ፡ ተቈጥቶ ፡ ሄደ ። በሪያዎቹም ፡ ቀርበው ፡— አባት ፡ ሆይ ፡ ነቢዩ ፡ ታላቅ ፡ ነገርስ ፡ እንኳ ፡ ቢነግርህ ፡ ኖሮ ፡ በደረግኸው ፡ ነበር ፤ ይልቁንስ ፡— ታጠብና ፡ ንጹሕ ፡ ሁን ፡ ቢልህ ፡ እንዴት ፡ ነዋ ! ብለው ፡ ተናገሩት ። ወረደም ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ አለ ፤ ሥጋውም ፡ እንደ ፡ ጨና ፡ እንደ ፡ ትንሽ ፡ ብላቴና ፡ ሥጋ ፡ ሆኖ ፡ ተመለሰ ። ንጹሕም ፡ ሆነ ።

እርሱም ፡ ከሰፍራው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ተመለሰ ። መጥቶም ፡ በፊቱ ፡ ቆመና ፡— እነሆ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ አወቅሁ ፡ አሁንም ፡ ከባሪያህ ፡ በረከት ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለ ። እርሱም ፡— በፊቱ ፡ የቆምሁት ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! አልቀበልም ፡ አለ ። ይቀበለውም ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ አለው ። እርሱ ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ አለ ። ንዕማንም ፡— እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ለሌሎች ፡ አማልክት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ አላቀርብምና ፡ ሁለት ፡ የበቅሎ ፡ ሸክም ፡ አፈር ፡ እንድወስድ ፡ እሺ ፡ ትለኝ ፡ ዘንድ ፡ አለምንህለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ ለአኔ ፡ ለባሪያህ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ፡ ጌታዬ ፡ በዚያ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ እጁን ፡ ተደግፎ ፡ ወደ ፡ ሬምን ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ በሬምን ፡ ቤት ፡ በሰገድሁ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ፡ አለ ። እርሱም ፡— በደኅና ፡ ሂድ ፡ አለው ። አንድ ፡ አማድመትም ፡ ያህል ፡ ከእርሱ ፡ ራቀ ።

፲ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ሎሌ ፡ ግያዝ ፡— ጌታዬ ፡ ሶርያዊውን ፡ ይህን ፡ ንዕማንን ፡ ማረው ፡ ከመጣለትም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ አልተቀበለም ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! በስተ ፡ ኋላው ፡ እሮጣለሁ ፡ ከእርሱም ፡ አንዳች ፡ እወስዳለሁ ፡ አለ ።

፲፩ ግያዝም ፡ ንዕማንን ፡ ተከተለው ። ንዕማንም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሲሮጥ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ሊገናኘው ፡ ከሰረገላው ፡ ወርዶ ፡— ሁሉ ፡ ደኅና ፡ ነውን ? አለው ። እርሱም ፡— ደኅና ፡ ነው ፡— አሁን ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ የሆኑት ፡ ሁለት ፡ ጕልማሶች ፡ ከተራራማው ፡ ከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተዋል ፤ አንድ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ ሁለት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ አለም ፡ ንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ላከኝ ፡ አለ ። ንዕማንም ፡— ሁለት ፡ መክሊት ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ ይፈቅድልህ ፡ አለ ፤ ግድ ፡ አለውም ፡ ሁለቱንም ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ በሁለት ፡ ከረጢት ፡ ውስጥ ፡ አሰረና ፡ ከሁለት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ጋር ፡ ለሁለት ፡ ሎሌዎቹ ፡ አስያዘ ፤ እነርሱም ፡ ተሸክመው ፡ በፊቱ ፡ ሄዱ ። ወደ ፡ ከረብታውም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ ወስዶ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ፡ ሰዎቹንም ፡ አሰናበተ ፡ እነርሱም ፡ ሄዱ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ገብቶ ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ ቆመ ። ኤልሳዕም ፡— ግያዝ ፡ ሆይ ፡ ከወዴት ፡ መጣህ ? አለው ። እርሱም ፡— እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ወዴትም ፡ አልሄድሁም ፡ አለ ።

፲፪ እርሱም ፡— ያ ፡ ሰው ፡ ከሰረገላው ፡ ወርዶ ፡ ሊቀበልህ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ልቤ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ አልሄደምን ? ብሩንና ፡ ልብሱን ፡ የወይራውንና ፡ የወይኑን ፡ ቦታ ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ባሪያዎች ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ጊዜው ፡ ነውን ? እንግዲህስ ፡ የንዕማን ፡ ለምጽ ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ ለዘላለምም ፡ በዘርህ ፡ ላይ ፡ ይጣበቃል ፡ አለው ። እንደ ፡ በረዶም ፡ ለምጻም ፡ ሆኖ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ የነቢያትም ፡ ልጆች ፡ ኤልሳዕን ፡— እነሆ ፡ በፊትህ ፡ የምንቀመጥበት ፡ ስፍራ ፡ ጠብቦናል ።

፪ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ እንሂድ ፡ ከእኛም ፡ እያንዳንዱ ፡ ከዚያ ፡ ምሰሶ ፡ ያምጣ ፡ የምንቀመጥበትንም ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ እንሥራ ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡— ሂዱ ፡ አለ ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡—

፫ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ ከባሪያዎችህ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ ፍቀድ ፡ አለ ። እርሱም ፡— እሄዳለሁ ፡ አለ ። ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እንጨት ፡ ቈረጡ ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ምሰሶውን ፡ ሲቈርጥ ፡ የምሰሩ ፡ ብረት ፡ ወደ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ። እርሱም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ወየው ! ወየው ! የተዋሰሁት ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡— የወደቀው ፡ ወዴት ፡ ነው ? አለ ፡ ስፍራውንም ፡ አሳየው ። እንጨትም ፡ ቈርጦ ፡ በዚያ ፡ ጣለው ፡ ብረቱም ፡ ተንሳፈፈ ። እርሱም ፡— ውሰደው ፡ አለ ፡ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ወሰደው ።

፰ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፡ ከባሪያዎቹም ፡ ጋር ፡ ተማክሮ ፡— በዚህ ፡ ተደብቀን ፡ እንሰፍራለን ፡ አለ ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡— ሶርያውያን ፡ በዚያ ፡ ተደብቀዋልና ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ እንዳታልፍ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ነገረው ፡ ስፍራ ፡ ሰደደ ፡ እንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳይሆን ፡ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ሳይሆን ፡ በዚያ ፡ ራሱን ፡ አዳነ ። የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ልብ ፡ ስለዚህ ፡ እጅግ ፡ ታወከ ፡ ባሪያዎቹንም ፡ ጠርቶ ፡— ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ የተወዳጀ ፡ እንዳለ ፡ አትነግሩኝምን ? አላቸው ። ከባሪያዎቹም ፡ አንዱ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንዲህ ፡ እኮ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእልፍኝህ ፡ ውስጥ ፡ ሆነህ ፡ የምትናገረውን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ኤልሳዕ ፡ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ይነግረዋል ፡ አለ ። እርሱም ፡— ልኬ ፡ አስይዘው ፡ ዘንድ ፡ ሄዳችሁ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እዩ ፡ አለ ። እርሱም ፡— እነሆ ፡ በዶታይን ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

፲፫ ወደዚያም ፡ ፈረሶችንና ፡ ሰረገሎችን ፡ እጅግም ፡ ጭፍራ ፡ ሰደደ ፡ በሌሊትም ፡ መጥተው ፡ ከተማይቱን ፡ ከበቡ ። የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሎሌ ፡ ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ በከተማይቱ ፡ ዙሪያ ፡ ጭፍራና ፡ ፈረሶች ፡ ሰረገሎችም ፡ ነበሩ ። ሎሌውም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ወዮ ! ምን ፡ እናደርጋለን ? አለው ። እርሱም ፡— ከእኛ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ካሉት ፡ ይበልጣሉና ፡ አትፍራ ፡ አለው ። ኤልሳዕም ፡—

አቤቱ÷ያይ፡ዘንድ፡ዓይኖቹን÷እበክህ÷ግለጥ፡
ብሎ፡ጸለየ ። እግዚአብሔርም፡የብላቴናውን፡
ዓይኖች ፡ገለጠ÷አየም ፡እነሆም ÷በኤልሳዕ ፡
ዙሪያ ፡ያሉት ፡የእሳት ፡ፈረሰችና፡ሰረገሎች ፡
፲፯፡ ተራራውን ፡ሞልተውት ፡ነበር ። ወደ ፡እር
ሱም፡በወረዱ ፡ጊዜ ፡ኤልሳዕ ፡— ይህን፡ሕዝብ፡
ዕውር፡ታደርገው ፡ዘንድ ፡እለምንሃለሁ ፡ብሎ፡
ወደ ፡እግዚአብሔር፡ጸለየ ። ኤልሳዕም፡እንደ፡
፲፱፡ ተናገረው ፡ቃል ፡ዕውር፡አደረጋቸው ። ኤል
ሳዕም ፡— መንገዱ፡በዚህ፡አይደለም ÷ከተማ
ይቱም ፡ይህች ፡አይደለችም ፡የምትሹትን ፡
ሰው ፡አሳያችሁ፡ዘንድ፡ተከተሉኝ፡አላቸው፡
ወደ ፡ሰማርያም ፡መራቸው ።

፳፡ ወደ ፡ሰማርያም ፡በገቡ ፡ጊዜ ፡ኤልሳዕ ፡—
አቤቱ÷ያዩ፡ዘንድ፡የእነዚህን፡ሰዎች፡ዓይኖች፡
ግለጥ ፡አለ፤እግዚአብሔርም ፡ዓይኖቻቸውን ፡
ገለጠ ÷እነርሱም ፡አዩ ። እነሆም ፡በሰማርያ ፡
፳፩፡ መካከል ፡ነበሩ ። የእስራኤልም ፡ንጉሥ ፡ባያ
ቸው ፡ጊዜ ፡ኤልሳዕን ፡— አባቴ ፡ሆይ ÷ልግደ
፳፪፡ ላቸውን ? ልግደላቸውን ? አለው ።እርሱም ፡—
አትግደላቸው ፤በሰይፍህና፡በቀስትህ፡የማረ
ክኸውን ፡ትገድል ፡ዘንድ፡ይገባሃልን ? እንጀ
ራና ፡ውኃ ፡በፊታቸው ፡አኑርላቸው ÷በልተ
ውና ፡ጠጥተውም ፡ወደ ፡ጌታቸው ፡ይሂዱ ፡
፳፫፡ አለው ። ብዙም ፡መብል ፡አዘጋጀላቸው ፤በበ
ሉና ፡በጠጡ ፡ጊዜም ፡አሰናበታቸው ÷እነር
ሱም ፡ወደ ፡ጌታቸው ፡ሄዱ ። ከዚያም ፡በኋላ፡
የሶርያ ፡አደጋ፡ጣዮች፡ወደ፡እስራኤል፡አገር፡
አልመጡም ።

፳፬፡ ከዚያም ፡በኋላ ፡የሶርያ ፡ንጉሥ ፡ወልደ ፡
አዴር ፡ሠራዊቱን ፡ሁሉ ፡ሰበሰበ ÷ወጥቶም ፡
፳፭፡ ሰማርያን ፡ከበባት ። በሰማርያም ፡ታላቅ ፡ራብ ፡
ሆኖ ፡ነበር ፤እነሆም ÷የአሀያ ፡ራስ ፡በአምሳ ፡
ብር ÷የርግብም ፡ዙስ ፡የጎሞር ፡ስምንተኛ ፡
የሚሆን ፡በአምስት ፡ብር ፡እስኪሸጥ ፡ድረስ ፡
፳፮፡ ከበቡአት ። የእስራኤልም ፡ንጉሥ ፡በቅጥር ፡
ላይ ፡በተመላለሰ ፡ጊዜ ፡አንዲት ፡ሴት ፡—
ጌታዬ ፡ንጉሥ ፡ሆይ ÷እርዳኝ ፡ብላ ፡ወደ ፡
፳፯፡ እርሱ ፡ጮኸች ። እርሱም ፡— እግዚአብሔር፡
ያልረዳሽን፡እኔ ፡እንዴት ፡እረዳሻለሁ ? ከአ
ውድማው ፡ወይስ ፡ከመጥመቂያው ፡ነውን ?
፳፰፡ አለ ። ንጉሡም ፡— ምን ፡ሆነሽል ? አላት ፤
እርስዋም ፡— ይህች ፡ሴት ፡— ዛሬ ፡እንድን
በላው ፡ልጅሽን ፡አምጪ ፤ነገም ፡ልጄን ፡
፳፱፡ እንበላለን ፡አለችኝ ። ልጄንም ፡ቀቅለን ፡በላ
ነው ፤በማግሥቱም ፡— እንድንበላው ፡ልጅ
ሽን ፡አምጪ ፡አልኋት ፡ልጅዋንም ፡ሸሸገ
፴፡ ችው ፡ብላ ፡መለሰችለት ። ንጉሡም ፡የሴቲ
ቱን ፡ቃል ፡ሰምቶ ፡ልብሱን ፡ቀደደ ፤በቅጥ
ርም ፡ይመላለስ ፡ነበር ፤ሕዝቡም ፡በስተ፡
ውስጥ ፡በሥጋው ፡ላይ ፡ለብሶት ፡የነበረውን ፡
፴፩፡ ማቅ ፡አዩ ። ንጉሡም ፡— የሣፋጥ ፡ልጅ ፡የኤ
ልሳዕ ፡ራስ ፡ዛሬ ፡በላዩ ፡ያደረ ፡እንደ ፡ሆነ ፡
እግዚአብሔር ፡ይህን፡ያድርግብኝ÷ይህንም፡
ይጨምርብኝ ፡አለ ።

ኤልሳዕ ፡ግን ፡በቤቱ ፡ተቀምጦ ፡ነበር ÷ሽማ ፴፪፡
ግሌዎችም ፡ከእርሱ ፡ጋር ፡ተቀምጠው ፡ነበር ፡
ንጉሡ ፡ሰው ፡ላከ ። መልእክተኛውም ፡ገና ፡
ሳይደርስ ፡ለሽማግሌዎች ፡— ይህ ፡የነፍሰ ፡
ገዳይ ፡ልጅ ፡ራሴን ፡ይቈርጥ ፡ዘንድ ፡እንደ ፡
ላከ ፡እዩ ፡መልእክተኛውም ፡በመጣ ፡ጊዜ ፡
ደጁን ፡ዘግታችሁ ፡ከልክሉት ፡የጌታው ፡የእ
ግሩ ፡ኮቴ ፡በኋላው ፡ነው ፡አላቸው ። ሲናገ ፴፫፡
ራቸውም ፡መልእክተኛው ፡ወደ ፡እርሱ ፡
ደረሰ ፡እርሱም ፡— እነሆ ÷ይህ ፡ክፉ ፡ነገር ፡
ከእግዚአብሔር ፡ዘንድ ፡ነው ÷እግዚአብሔ
ርን ፡ገና ፡እጠብቅ ፡ዘንድ፡ምንድር ፡ነኝ ? አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ኤልሳዕም ፡— የእግዚአብሔርን ፡ቃል ፡ ፩፡
ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡እንዲህ ፡ይላል ፡—
ነገ፡በዚህ፡ጊዜ ፡በሰማርያ ፡በር ፡አንድ ፡መስ
ፈሪያ ፡መልካም ፡ዱቄት ፡በአንድ ፡ሰቅል ÷
ሁለትም ፡መስፈሪያ ፡ገብስ ፡በአንድ ፡ሰቅል ፡
ይሸመታል ፡አለ ። ንጉሡም ፡በእጁ ፡ተደግፎ ፡ ፪፡
የነበረ፡አለቃ፡ለእግዚአብሔር፡ሰው፡መልሶ፡—
እነሆ ÷እግዚአብሔር ፡በሰማይ ፡መስኮቶች ፡
ቢያደርግ ፡ይህ ፡ነገር ፡ይሆናልን ? አለው ።
እርሱም ፡— እነሆ ÷በዓይኖችህ ፡ታየዋለህ ÷
ከዚያም ፡አትቀምስም ፡አለ ።

በበሩም ፡መግቢያ ፡አራት ፡ለምጻም ፡ሰዎች ፡ ፫፡
ነበሩ ፡እርስ ፡በርሳቸውም ፡— እስከንሞት ፡
ድረስ ፡በዚህ ፡ለምን ፡እንቀመጣለን ? ወደ ፡ ፬፡
ከተማ ፡እንገባ ፡ዘንድ ፡ብንወድድ ፡ራብ ፡በከ
ተማ ፡አለ ÷በዚያም ፡እንሞታለን ፤በዚህም ፡
ብንቀመጥ ፡እንሞታለን ። እንግዲህ ፡ኑ ÷ወደ ፡
ሶርያውያን ፡ሰፈር፡እንሸሽ ፤በሕይወት ፡ቢያኖ
ሩን ፡እንኖራለን ፡ቢገድሉንም ፡እንሞታለን ፡
ተባባሉ ። ጨለምለም ፡ባለ ፡ጊዜ ፡ወደ ፡ሶር ፭፡
ያውያን ፡ሰፈር ፡ይሄዱ ፡ዘንድ ፡ተነሡ ፡ወደ ፡
ሶርያውያንም ፡ሰፈር ፡መጀመሪያ ፡ዳርቻ ፡
በመጡ ፡ጊዜ ÷እነሆ ÷ማንም ፡አልነበረም ።
እግዚአብሔር ፡ለሶርያውያን ፡የሰረገላና ፡የፈ ፮፡
ረስ ፡የብዙም ፡ጭፍራ ፡ድምፅ ፡አሰምቶ ፡
ነበር ፤እርስ ፡በርሳቸውም ፡—እነሆ ÷የእስራ
ኤል ፡ንጉሥ ፡የኬጢያውያንንና ፡የግብጻውያ
ንን ፡ነገሥት ፡ቀጥሮ ፡አምጥቶብናል ፡ይበባሉ ፡
ነበር ። ስለዚህም ፡ተነሥተው ፡በጨለማ ፡ ፯፡
ሸሹ ፡ድንኳኖቻቸውንና ፡ፈረሶቻቸውን ፡አህ
ዮቻቸውንና ፡ሰፈሩን ፡እንዳለ ፡ትተው ፡ነፍ
ሳቸውን ፡ያድኑ ፡ዘንድ ፡ሸሹ ። እነዚህም ፡ ፰፡
ለምጻሞች ፡ወደ ፡ሰፈሩ ፡መጀመሪያ ፡ዳርቻ ፡
በመጡ ፡ጊዜ ፡ወደ ፡አንድ ፡ድንኳን ፡ገብተው ፡
በሉ ፡ጠጡም ÷ከዚያም ፡ወርቅና ፡ብር ፡ልብ
ስም ፡ወሰዱ ÷ሄደውም ፡ሸሸጉት ፤ ተመልሰ
ውም ፡ወደ ፡ሌላ ፡ድንኳን ፡ገቡ ÷ከዚያም ፡
ደግሞ ፡ወስደው ፡ሸሸጉ ።

ከዚያም ፡ወዲያ ፡እርስ ፡በርሳቸው ፡— መል ፱፡

ካም ፡አላደረግንም ፡ዛሬ ፡የመልካም ፡ምስራች ፡
ቀን ፡ነው ÷እኛም ፡ዝም ፡ብለናል ፤ እስኪ
ጋም ፡ድረስ ፡ብንቆይ ፡በደለኞች፡እንሆናለን፡
ኑ ÷እንሂድ ፡ለንጉሥ ፡ቤተ ፡ሰብ፡እንነገር ፡
፲፡ ተባበሉ ። መጥተውም ፡— ወደ ፡ሶርያውያን ፡
ሰፈር ፡መጣን ÷እነሆም ፡ፈረሶችና ፡አህዮች ፡
ታስረው ፡ድንኳኖችም ፡ተተክለው ፡ነበር ፡
እንጂ ፡ሰው ፡አልነበረም ÷የሰውም ፡ድምፅ ፡
አልነበረም ፡ብለው ፡ወደ ፡ከተማይቱ ፡ደጅ ፡
፲፩፡ ጠባቂ ፡ጮኹ ። የደጁም ፡ጠባቂዎች ፡ጠሩ ÷
፲፪፡ ለንጉሡም ፡ቤት ፡ውስጥ ፡አወሩ ። ንጉሡም ፡
በሌሊት ፡ተነሥቶ ፡ባሪያዎቹን ፡— ሶርያውያን ፡
ያደረጉብንን ፡እነግራችኋለሁ ፤ እንደ ፡ተራ
ብን ፡ያውቃሉ ፡ስለዚህ ፡— ከከተማይቱ ፡
በወጡ ፡ጊዜ ፡በሕይወታቸው፡እንይዛቸዋለን ÷
ወደ ፡ከተማም ፡እንገባለን ፡ብለው ፡በሚዳ ፡
ይሸሸጉ ፡ዘንድ ፡ከሰፈሩ ፡ወጥተዋል ፡አላ
ቸው ። ከባሪያዎቹም ፡አንዱ ፡መልሶ ፡— በከ ፲፫፡
ተማ ፡ከቀሩት ፡ፈረሶች ፡እምስት ፡ይውሰዱ ፡
እነሆ ÷እንደ ፡ቀሩት ፡እንደ ፡እስራኤል ፡ወገን ፡
ሁሉ ፡ናቸው ፡እነሆ ÷እንዳለቁ ፡እንደ ፡እስራ
፲፬፡ ኤል ፡ወገን ፡ሁሉ ፡ናቸው ፤ እንስደድም ÷
እንይም ፡አለ ። ሁለትም ፡ሰረገሎች ፡ከፈረ
ሶች ፡ጋር ፡ወሰዱ ፤ ንጉሡም ፡— ሄዳችሁ ፡
እዩ ፡ብሎ ፡ከሶርያውያን ፡ሠራዊት ፡በኋላ ፡
፲፭፡ ላከ ። በኋላቸው ፡እስከ ፡ዮርዳኖስ ፡ድረስ ፡
ሄዱ ፡እነሆም ÷ሶርያውያን ፡ሲሸሹ ፡የጣሉት ፡
ልብስና ፡ዕቃ ፡መንገዱን ፡ሁሉ ፡ሞልቶ ፡
ነበር።መልእክተኞችም ፡ተመልሰው፡ለንጉሡ፡
ነገሩት ።

፲፮፡ ሕዝቡም ፡ወጥቶ ፡የሶርያውያንን ፡ሰፈር ፡
በዘበዘ ፤እንደ ፡እግዚአብሔርም ፡ቃል ፡እንድ፡
መስፈሪያ ፡መልካም ፡ዱቄት፡በአንድ፡ሰቅል ÷
ሁለትም ፡መስፈሪያ ፡ገብስ ፡በአንድ ፡ሰቅል ፡
ተሸመተ ። ንጉሡም ፡ያን ፡አዥን ፡ይደግፈው ፡
የነበረውን ፡አለቃ ፡በሩን ፡ይጠብቅ ፡ዘንድ ፡
አቆመው ። ሕዝቡም ፡በበሩ ፡ረገጠው ÷ንጉ
ሡም ፡ወደ ፡እርሱ ፡በወረደ ፡ጊዜ ፡የእግዚ
አብሔር ፡ሰው ፡እንደ ፡ተናገረው ፡ሞተ ። ፲፯፡
የእግዚአብሔርም ፡ሰው ፡ለንጉሡ ፡— ነገ ፡
በዚህ ፡ጊዜ ፡በሰማርያ ፡በር ፡ሁለት ፡መስፈሪያ ፡
ገብስ ፡በአንድ ፡ሰቅል ፡አንድም ፡መስፈሪያ ፡
መልካም ፡ዱቄት፡በአንድ፡ሰቅል፡ይሸመታል፡
ብሎ ፡እንደ ፡ተናገረው ፡ነገር ፡እንዲሁ ፡ሆነ ። ፲፰፡
ያም ፡አለቃ ፡ለእግዚአብሔር ፡ሰው ፡መልሶ ፡—
እነሆ ፡እግዚአብሔር ፡በሰማይ ፡መስኮቶች ፡
ቢያደርግ ፡ይህ ፡ነገር ፡ይሆናልን ? ብሎ ፡ነበር ፡
እርሱም ፡— እነሆ ÷በዓይኖችህ ፡ታየዋለህ ፡
ከዚያም ፡አትቀምስም ፡ብሎት ፡ነበር ። እን ፲፱፡
ዲሁም ፡ደረሰበት ። ሕዝቡም ፡በበሩ ፡ረገጠ ፲፡
ውና ፡ሞተ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

ኤልሳዕም ፡ልጅዋን ፡ያስነሣላትን ፡ሴት ፡— ፩፡
አንቺ ፡ከቤተ ፡ሰብሽ ፡ጋር ፡ተነሥተሽ ፡ሂጂ ÷
በምታገኚውም ፡ስፍራ ፡ተቀመጪ ። እግዚአ
ብሔር ፡ራብ ፡ጠርቶአል ፡ሰባት ፡ዓመትም ፡
በምድር ፡ላይ ፡ይመጣል ፡ብሎ ፡ተናገራት ። ፪፡
ሴቲቱም ፡ተነሥታ ፡እንደ ፡እግዚአብሔር ፡
ሰው ፡ቃል ፡አደረገች ፤ከቤተ ፡ሰብዋም ፡ጋር ፡
ሄዳ ፡በፍልስጥኤም ፡አገር ፡ሰባት ፡ዓመት ፡
ተቀመጠች ። ሰባትም ፡ዓመት ፡በተፈጸመ ፡ ፫፡
ጊዜ ፡ሴቲቱ ፡ከፍልስጥኤም ፡አገር ፡ተመለ
ሰች ፡ስለ ፡ቤትዋና ፡ስለ ፡መሬትዋ ፡ልት
ጮኽ ፡ወደ ፡ንጉሡ ፡ወጣች ። ንጉሡም ፡ ፬፡
ከእግዚአብሔር ፡ሰው ፡ሎሌ ፡ካግያዝ ፡ጋር ፡—
ኤልሳዕ ፡ያደረገውን ፡ተአምራት ፡ሁሉ ፡ንገ
ረኝ ፡እያለ ፡ይጫወት ፡ነበር ። እርሱም ፡ ፭፡
የሞተውን ፡እንደ ፡አስነሣ ፡ለንጉሡ ፡ሲና
ገር ÷እነሆ ÷ልጅዋን ፡ያስነሣላት ፡ሴት ፡
ስለ ፡ቤትዋና ፡ስለ ፡መሬትዋ ፡ወደ ፡ንጉሡ ፡
ጮኸች ፡ግያዝም ፡— ጌታዬ ፡ንጉሥ ፡ሆይ ÷
ሴቲቱ ፡ይህች ፡ናት ÷ኤልሳዕም ፡ያስነሣው ፡
ልጅዋ ፡ይህ ፡ነው ፡አለ ። ንጉሡም ፡ሴቲቱን ፡ ፮፡
ጠየቀ ÷ነገረችውም ። ንጉሡም ፡— የነበረ
ትን ፡ሁሉ ÷መሬትዋንም ፡ከተወች ፡ጀምሬ ፡
እስከ ፡ዛሬ ፡ድረስ ፡ያለውን ፡የእርሻዋን ፡ፍሬ ፡
ሁሉ ፡መልስላት ፡ብሎ ፡ስለ ፡እርስዋ ፡ጃንደ
ረባውን ፡አዘዘ ።

ኤልሳዕም ፡ወደ ፡ደማስቆ ፡መጣ ፡የሶርያም ፡ ፯፡
ንጉሥ ፡ወልደ ፡አዴር ፡ታምሞ ፡ነበር ፡ወሬ
ኞችም ፡— የእግዚአብሔር ፡ሰው ፡ወደዚህ ፡
መጥቶአል ፡ብለው ፡ነገሩት ። ንጉሡም ፡አዛ ፰፡
ኤልን ፡— ገጸ ፡በረከት ፡በእጅህ ፡ወስደህ ፡የእ
ግዚአብሔርን ፡ሰው ፡ልትገናኘው ፡ሂድ ፡በእር
ሱም ፡አፍ ፡— ከዚህ ፡በሽታ ፡እድናለሁን ?
ብለህ ፡እግዚአብሔርን ፡ጠይቅ ፡አለው ። አዛ ፱፡
ኤልም ፡ሊገናኘው ፡ሄደ ÷ከእርሱም ፡ጋር ፡
ከደማስቆ ፡መልካሙን ፡ነገር ፡ሁሉ ፡የአርባ ፡
ግመል ፡ሞነት ፡ገጸ ፡በረከት ፡ወሰደ ፤መጥ
ቶም ፡በፊቱ ፡ቆመና ፡— ልጅህ ፡የሶርያ ፡
ንጉሥ ፡ወልደ ፡አዴር ፡— ከዚህ ፡በሽታ ፡እድ
ናለሁን? ሲል ፡ወደ ፡አንተ ፡ልኮኛል ፡አለ ። ፲፡
ኤልሳዕም ፡— ሂድ ፡— መዳንስ ፡ትድናለህ ፡ ፲፩፡
በለው ፡ነገር ፡ግን ፡እንዲሞት ፡እግዚአብሔር ፡
አሳይቶኛል ፡አለው ። እስኪያፍርም ፡ድረስ ፡ ፲፪፡
ትኵር፡ብሎ፡ተመለከተው፡የእግዚአብሔርም፡
ሰው ፡አነባ ። አዛኤልም ፡— ጌታዬ ፡ለምን ፡ ፲፫፡
ያነባል?አለ ።እርሱም ፡— በእስራኤል፡ልጆች፡
ላይ ፡የምታደርገውን ፡ክፋት ፡ስለማውቅ ፡
ነው ፡ምሽጎቻቸውን ፡በእሳት ፡ታቃጥላለህ ÷
ጕልማሶቻቸውንም ፡በሰይፍ ፡ትገድላለህ ÷

ሕፃናቶቻቸውንም ፡ ትፈጠፍጣለህ ፥ እርጉዞቻ
፲፫፡ ቸውንም ፡ ትቀድዳለህ ፡ አለው ። አዛኤልም ፡— ይህን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ውሻ ፡ ባሪያህ ፡ ምንድር ፡ ነኝ ? አለ ። ኤልሳዕም ፡— አንተ ፡ በሶርያ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንድ ትሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳይቶኛል ፡ አለው ።
፲፬፡ ከኤልሳዕም ፡ ርቆ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መጣ ፤ እር ሱም ፡— ኤልሳዕ ፡ ምን ፡ አለህ ? አለው ። እር
፲፭፡ ሱም ፡— እንድትፈወስ ፡ ነገረኝ ፡ አለው ። በነ ጋውም ፡ ለሐፍ ፡ ወስዶ ፡ በውኃ ፡ ነከረው ፡ በፊ ቱም ፡ ላይ ፡ ሸፈነው ። ሞተም ። አዛኤልም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።
፲፮፡ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በአክዓብ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮሣፍጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮራም ፡ ነገሠ ።
፲፯፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡
፲፰፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። የአክዓብንም ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ነበርና ፡ የአክዓብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ሄደ ፤ በእ
፲፱፡ ግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለእርሱና ፡ ለልጆቹ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ መብራት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ስለ ፡ ባሪያው ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ይሁዳን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።
፳፡ በእርሱም ፡ ዘመን ፡ ኤዶምያስ ፡ ለይሁዳ ፡ እንዳይገብር ፡ ሸፈተ ፥ በላያቸውም ፡ ንጉሥ ፡
፳፩፡ አነገሡ ። ኢዮራምም ፡ ከሰረገሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጻኢር ፡ አለፈ ፤ በሌሊትም ፡ ተነ ሥቶ ፡ እርሱንና ፡ የሰረገሎቹን ፡ አለቆች ፡ ከብ በው ፡ የነበሩትን ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ መታ ፤
፳፪፡ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ። ኤዶም ያስ ፡ ግን ፡ ለይሁዳ ፡ እንዳይገብር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሸፈተ ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡
፳፫፡ ልብና ፡ ሸፈተ ። የተረፈውም ፡ የኢዮራም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ሁሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥ ታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለ
፳፬፡ ምን ? ኢዮራምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀ ላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ፤ በፋንታውም ፡ ልጁ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።
፳፭፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በአክዓብ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡
፳፮፡ ነገሠ ። መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ አካዝያስ ፡ የሀያ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢ የሩሳሌምም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ጎቶልያ ፡ የተባለች ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዘ
፳፯፡ ንበሪ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። በአክዓብም ፡ ቤት ፡ መን ገድ ፡ ሄደ ፡ እንደ ፡ አክዓብም ፡ ቤት ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ ለአክዓብ ፡ ቤት ፡
፳፰፡ አማች ፡ ነበረና ። ከአክዓብም ፡ ልጅ ፡ ከኢዮ ራም ፡ ጋር ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ አዛኤልን ፡ በሬ ማት ፡ ዘገባዳዩ ፡ ሊጋጠም ፡ ሄደ ፤ ሶርያውያ
፳፱፡ ንም ፡ ኢዮራምን ፡ አቈሰሉት ። ንጉሡም ፡ ኢዮራም ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛኤል ፡ ጋር ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ በራማት ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቍስል ፡ እንዲፈወስ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመለሰ ። የአክዓብም ፡ ልጅ ፡ ኢዮራም ፡ ታምሞ ፡ ነበርና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ሊያየው ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወረደ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

ነቢዩም ፡ ኤልሳዕ ፡ ከነቢያት ፡ ልጆች ፡ አን
፩፡ ዱን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— ወገብህን ፡ ታጥ ቀህ ፡ ይህን ፡ የዘይት ፡ ማሰሮ ፡ በእጅህ ፡ ያዝ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድም ፡ ሂድ ። በዚያም ፡
፪፡ በደረስህ ፡ ጊዜ ፡ የናሜሲን ፡ ልጅ ፡ የኢዮሣፍ ጥን ፡ ልጅ ፡ ኢዩን ፡ ታገኘዋለህ ፤ ገብተህም ፡ ከወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ አስነሣው ፥ ወደ ፡ ጓዳም ፡ አግባው ። የዘይቱንም ፡ ማሰሮ ፡ ይዘህ ፡
፫፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፍስሰውና ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀባሁህ ፡ በለው ፤ በሩንም ፡ ከፍ ተህ ፡ ሽሽ ፥ አትዘግይም ። እንዲሁም ፡ ጕልማ
፬፡ ሳው ፡ ነቢይ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ሄደ ።
፭፡ በገባም ፡ ጊዜ ፥ እነሆ ፥ የሠራዊት ፡ አለቆች ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡— አለቃ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ አለ ። ኢዩም ፡— ከማንኛችን ፡ ጋር ፡ ነው ? አለ ። እርሱም ፡—
፮፡ አለቃ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ አለ ። ተነ ሥቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፡ ዘይቱንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፍስሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
፯፡ ንጉሥ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀባሁህ ። የባሪያዎቼን ፡ የነቢያትን ፡ ደም ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ባሪያ ዎች ፡ ሁሉ ፡ ደም ፡ ከኤልዛቤል ፡ እጅ ፡ እበቀል ፡ ዘንድ ፡ የጌታህን ፡ የአክዓብን ፡ ቤት ፡ ትመታ ለህ ። የአክዓብም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ። በእ
፰፡ስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተለቀቀ ውን ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ ከአክዓብ ፡ አጠፋለሁ ።
፱፡ የአክዓብንም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አኪያም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ባአስ ፡ ቤት ፡ አደርገዋለሁ ። አልዛቤ
፲፡ ንም ፡ በኢይዝራኤል ፡ እርሻ ፡ ውሾች ፡ ይበሉ አታል ፡ የሚቀብራትም ፡ አታገኝም ። በሩንም ፡ ከፍቶ ፡ ሸሸ ።
፲፩፡ ኢዩም ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ ባሪያዎች ፡ ወጣ ፡ እነ ርሱም ፡— ደኅና ፡ ነውን ? ይህ ፡ እብድ ፡ ለምን ፡ መጣብህ ? አሉት ። እርሱም ፡— ሰውዮውንና ፡
፲፪፡ ነገሩን ፡ ታውቃላችሁ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡— ሐሰት ፡ ነው ፡ ንገረን ፡ አሉት ፤ እርሱም ፡— እግ ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀባሁህ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነገረኝ ፡ አላቸው ። ሁሉም ፡
፲፫፡ ፈጥነው ፡ ልብሳቸውን ፡ ወሰዱ ፥ በሰገነቱ ፡ መሰ ላል ፡ እርከን ፡ ላይ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አነጠ

ፉት ፥ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ እየነፉ ፡— ኢዩ ፡ ነግ ሦአል ፡ አሉ ።
፲፬፡ እንዲሁም ፡ የናሜሲ ፡ ልጅ ፡ የኢዮሣፍጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዩ ፡ በኢዮራም ፡ ላይ ፡ ተማማለ ። ኢዮ ራምና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛኤል ፡ የተነሣ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድን ፡
፲፭፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። ንጉሡ ፡ ኢዮራም ፡ ግን ፡ ከሰ ርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛኤል ፡ ጋር ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቍስል ፡ ይታከም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመልሶ ፡ ነበር ። ኢዩም ፡— ልባችሁስ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ከሆነ ፡ በኢይዝራኤል ፡ እንዳያወራ ፡ ማንም ፡ ከከተማ ፡
፲፮፡ ኩብልሎ ፡ አይውጣ ፡ አለ ። ኢዮራምም ፡ በዚያ ፡ ታምሞ ፡ ተኝቶ ፡ ነበርና ፡ ኢዩ ፡ በሰረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ሄደ ። የይ ሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ ኢዮራምን ፡ ለማ የት ፡ ወርዶ ፡ ነበር ።
፲፯፡ በኢይዝራኤልም ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ የቆመው ፡ ሰላይ ፡ የኢዩ ፡ ጭፍራ ፡ ሲመጣ ፡ አይቶ ፡— ጭፍራ ፡ አያለሁ ፡ አለ ። ኢዮራምም ፡— የሚ ገናኘው ፡ ፈረሰኛ ፡ ላክ ፥ እርሱም ፡— ሰላም ፡
፲፰፡ ነውን ? ይበለው ፡ አለ ። ፈረሰኛውም ፡ ሊገና ኘው ፡ ሄዶ ፡— ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ሰላም ፡ ነውን ? አለ ። ኢዩም ፡— አንተ ፡ ከሰ
፲፱፡ላም ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለህ ? ወደ ፡ ኋላዬ ፡ አልፈህ ፡ ተከተለኝ ፡ አለ ። ሰላዩም ፡— ደረሰባቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፡ አልተመለሰም ፡ በሚል ፡ ወደ ፡ እነርሱም ፡ ደርሶ ፡— ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
፳፡ ሰላም ፡ ነውን ? አለ ። ኢዩም ፡— አንተ ፡ ከሰ ላም ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለህ ? ወደ ፡ ኋላዬ ፡ አልፈህ ፡ ተከተለኝ ፡ አለ ። ሰላዩም ፡— ደረሰባቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፡ አልተመለሰም ፡ በችኰላ ፡ ይሄዳልና ፡ አካሄዱ ፡ እንደ ፡ ናሜሲ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኢዩ ፡ አካሄድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።
፳፩፡ ኢዮራምም ፡— ሰረገላ ፡ አዘጋጁ ፡ አለ ፡ ሰረገ ላውንም ፡ አዘጋጁለት ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮራም ፡ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ በሰ ረገሎቻቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ወጡ ፡ ኢዩንም ፡ ሊገናኙት ፡ ሄዱ ፡ በኢይዝራኤላዊው ፡ በና
፳፪፡ቡቴ ፡ እርሻ ፡ ውስጥ ፡ አገኙት ። ኢዮራምም ፡ ኢዩን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡— ኢዩ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ነውን ? አለ ። እርሱም ፡— የእናትህ ፡ የኤልዛቤል ፡ ግል ሙትናዋና ፡ መተትዋ ፡ ሲበዛ ፡ ምን ፡ ሰላም ፡
፳፫፡ አለ ? ብሎ ፡ መለሰ ። ኢዮራምም ፡ መልሶ ፡ እጁን ፡ መልሶ ፡ አካዝያስንም ፡— አካዝያስ ፡ ሆይ ፥
፳፬፡ ክህደት ፡ ነው ፡ አለው ። ኢዩም ፡ በእጁ ፡ ቀስ ቱን ፡ ለጠጠ ፥ ኢዮራምንም ፡ በጫንቃው ፡ መካ ከል ፡ ወጋው ፡ ፍላጻውም ፡ በልቡ ፡ አለፈ ፥ ወደ ፡ ሰረገላውም ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ። ኢዩም ፡ አለቃ
፳፭፡ ውን ፡ ቢድቃርን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— አንሥ ተህ ፡ በኢይዝራኤላዊው ፡ በናቡቴ ፡ እርሻ ፡ ጣለው ፥ አንተና ፡ እኔ ፡ ጕን ፡ ለጕን ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጠን ፡ አባቱን ፡ አክዓብን ፡ በተከተልን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተናገረበት ፡ አስብ ፡— በእው
፳፮፡ነት ፡ የናቡቴንና ፡ የልጆቹን ፡ ደም ፡ ትናንትና ፡ አይቻለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚህም ፡ እርሻ ፡ አመልስብሃለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ቃል ፡ ወስደህ ፡ በእርሻው ፡ ውስጥ ፡ ጣለው ።
፳፯፡ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ ያንን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በአትክልት ፡ ቤት ፡ መንገድ ፡ ሸሸ ። ኢዩም ፡— ይህን ፡ ደግሞ ፡ በሰረገላው ፡ ላይ ፡ ውጉት ፡ እያለ ፡ ተከተለው ፡ በይብለዓምም ፡ አቅ ራቢያ ፡ በሰችው ፡ በጉር ፡ ዐቀበት ፡ ላይ ፡ ወጉት ።
፳፰፡ ወደ ፡ መጊዶም ፡ ሸሽ ፡ በዚያም ፡ ሞተ ። በሪያ ዎቹም ፡ በሰረገላው ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ ሌም ፡ ወሰዱት ፡ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ በመቃ ብሩ ፡ ከአበቶቹ ፡ ጋር ፡ ቀበሩት ።
፳፱፡ በአክዓብም ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ አካዝያስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።
፴፡ ኢዩም ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ መጣ ፡ ኤልዛ ቤልም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ዓይንዋን ፡ ተኳለች ፡ ራስዋንም ፡ አስጌጠች ፡ በመስኮትም ፡ ዘልቃ
፴፩፡ ትመለከት ፡ ነበር ። ኢዩም ፡ በበሩ ፡ ሲገባ ፡— ጌታውን ፡ የገደለ ፡ ዘምሪ ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ነውን ?
፴፪፡ አለችው ። ፊቱንም ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ አን ሥቶ ፡— ከእኔ ፡ ጋር ፡ ማን ፡ ነው ? አለ ። ሁለት ፡ ሦስትም ፡ ጃንደረቦች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተመለከቱ ።
፴፫፡ እርሱም ፡— ወደ ፡ ታች ፡ ወርውሩአት ፡ አለ ፡ ወረወሩአትም ፡ ደምዋም ፡ በግንቡና ፡ በፈረ
፴፬፡ሶቹ ፡ ላይ ፡ ተረጨ ። ረገጡአትም ። በገባም ፡ ጊዜ ፡ በላ ፡ ጠጣም ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡— ይህ ችን ፡ የተረገመች ፡ እዩ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ናትና ፡ ቀበሩአት ፡ አለ ። ሊቀብሩአትም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡
፴፭፡ ከእናትዋና ፡ ከእግርዋ ፡ ከመዳፍም ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላገኙም ። ተመልሰውም ፡ ነገሩት ፡
፴፮፡ እርሱም ፡— በባሪያው ፡ በቴስብያዊ ፡ ኤልያስ ፡— በእይዝራኤል ፡ እርሻ ፡ የኤልዛቤልን ፡ ሥጋ ፡ ውሾች ፡ ይበላሉ ፡ የኤልዛቤልም ፡ ሬሳ ፡ በኢ ይዝራኤል ፡ እርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፍግ ፡ ይሆናልና ፡ ማንም ፡— ይህች ፡ ኤልዛቤል ፡ ናት ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ለአክዓብም ፡ በሰማርያ ፡ ሰባ ፡ ልጆች ፡ ነበ
፩፡ ሩት ። ኢዩም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ፡ የአክዓብን ፡ ልጆች ፡ ለሚያሳድጉ ፡ ለሰማርያ ፡ ታላላቆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡— ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ አሁን ፡ በደረሳ
፪፡ችሁ ፡ ጊዜ ፡ የጌታችሁ ፡ ልጆች ፡ ሰረገሎችና ፡ ፈረሶችም ፡ የተመሸገች ፡ ከተማ ፡ መሣሪያዎ
፫፡ችም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አሉና ፥ ከጌታችሁ ፡ ልጆች ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛችሁንና ፡ የሚሻላች ሁን ፡ ምረጡ ፥ በአባቱም ፡ ዙፋን ፡ አስቀም ጡት ፥ ስለ ፡ ጌታችሁም ፡ ቤት ፡ ተዋጉ ፡ ብሎ ፡

፩ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ሰደደ ። እነርሱ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፈርተው ፡— እነሆ ÷ ሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፡ እኛስ ፡ እንዴት ፡ ፪ እንቆማለን ? አሉ ። የቤቱ ፡ አለቃ ÷ የከተማይቱም ፡ አለቃ ÷ ሽማግሌዎችና ፡ ልጆቹን ፡ የሚያሳድጉ ፡— እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ነን ÷ ያዘዝኸንን ፡ ሁሉ ፡ እናደርጋለን ፡ ንጉሥም ፡ በላያችን ፡ እናነግሥም ፤ የምትወድደውን ፡ አድ ፫ ርግ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ ላኩ ። ሁለተኛም ፡— ወገኖቼስ ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ÷ ነገሬንም ፡ ከሰማችሁ ÷ የጌታችሁን ፡ ልጆች ፡ ራስ ፡ ቀረጡ ÷ ነገም ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይዛችሁ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈላቸው ። የንጉሡም ፡ ልጆች ፡ ሰብዐ ፡ ሰዎች ፡ በሚያሳድጓቸው ፡ በከተማይቱ ፡ ታላላቆች ፡ ፬ ዘንድ ፡ ነበሩ ። ደብዳቤውም ፡ በደረሳቸው ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ሰብዐውን ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ገደሉአቸው ፤ ራሳቸውንም ፡ በቅርጫት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ኢይዝ ፭ ራኤል ፡ ላኩ ። መልእክተኛም ፡ መጥቶ ፡— የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። እርሱም ፡— እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ በበሩ ፡ አደባበይ ፡ ሁለት ፡ ክምር ፡ አድርጋ ፮ ችሁ ፡ አኑሩአቸው ፡ አለ ። በነጋውም ፡ ወጥቶ ፡ ቆመ ÷ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡— እናንተ ፡ ንጹሐን ፡ ናችሁ ፤ እነሆ ÷ ጌታዬን ፡ የወጋጀልሁ ፡ የገደልሁትም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እነዚህንስ ፡ ሁሉ ፡ የገደለ ፯ ማን ፡ ነው ? እግዚአብሔር ፡ በእክዓብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ከተናገረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በም ድር ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ እንዳይወድቅ ፡ አሁን ፡ እወቁ ። እግዚአብሔር ፡ በባሪያው ፡ በኤልያስ ፰ የተናገረውን ፡ አድርጎአል ፡ አላቸው ። ኢዩም ፡ ከእክዓብ ፡ ቤት ፡ የቀረውን ፡ ሁሉ ÷ ታላላቆቹንም ፡ ሁሉ ÷ ወዳጆቹንና ፡ ካህናቱን ፡ ማንም ፡ ሳይቀር ፡ በኢይዝራኤል ፡ ገደላቸው ።

፱ ፲ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ሄደ ፤ በመንገድም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ በግ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቤት ፲ ፩ በደረሰ ፡ ጊዜ ÷ ኢዩ ፡ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከአካዝያስ ፡ ወንድሞች ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡— እናንተ ፡ እነማን ፡ ናችሁ ? አለ ። እነርሱም ፡— እኛ ፡ የአካዝያስ ፡ ወንድሞች ፡ ነን ፤ የንጉሡንና ፡ የእቴጌይቱን ፡ ልጆች ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠየቅ ፡ እንወ ፲ ፪ ርዳለን ፡ አሉት ። እርሱም ፡— በሕይወታቸው ፡ ያዙአቸው ፡ አለ ። ያዙአቸውም ÷ በበግ ፡ ጠባቂዎችም ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ጕድጓድ ፡ አርባ ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ገደሉአቸው ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ።

፲ ፫ ከዚያም ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የሬካብን ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብን ፡ ተገናኘው ፤ ደኅንነቱንም ፡ ጠይቆ ፡— ልቤ ፡ ከልብህ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያህል ፡ ልብህ ፡ ከልቤ ፡ ጋር ፡ በቅንነት ፡ ነውን ? አለው ፤ ኢዮናዳብም ፡— እንዲሁ ፡ ነው ፡ አለው ። ኢዩም ፡— እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ሆነስ ፡ እጅህን ፡ ስጠኝ ፡ አለ ። እጁንም ፡ ሰጠው ፤ ወደ ፡ ሰረገላውም ፡ አውጥቶ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስቀመጠው ። ፲ ፮ ፡— ከእኔ ፡ ጋር ፡ ና ÷ ለእግዚአብሔርም ፡ መቅናቴን ፡ እይ ፡ አለው ። በሰረገላውም ፡ አስ ፲ ፯ ቀመጠው ። ወደ ፡ ሰማርያም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ለኤልያስ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከአክዓብ ፡ በሰማርያ ፡ የቀረውን ፡ ሁሉ ፡ ገደለ ።

፲ ፰ ኢዩም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡— አክዓብ ፡ በኣልን ፡ በጥቂቱ ፡ አመለከው ፡ ኢዩ ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ያመልከዋል ። አሁንም ፡ የበኣልን ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ÷ አገልጋዮቹንም ፡ ሁሉ ÷ ካህናቱንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ጥሩ ፡ ማንም ፡ አይቅር ፤ ለበኣል ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርባለሁ ÷ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ በሕይወት ፡ አይኖርም ፡ አላቸው ። ኢዩም ፡ የበኣልን ፡ አገልጋዮች ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በተንኰል ፡ ይህን ፡ አደረገ ። ፲ ፱ ኢዩም ፡— ለበኣል ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ ቀድሱ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ አወጁ ። ፲ ፳ ኢዩም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ላከ ÷ የበኣልም ፡ አገልጋዮች ፡ ሁሉ ፡ መጡ ፤ ሰይመጣ ፡ የቀረ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልነበረም ። ወደ ፡ በኣልም ፡ ቤት ፡ ገቡ ÷ የበኣልም ፡ ቤት ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ። ፲ ፳፩ ዕቃ ፡ ቤቱንም ፡— ለበኣል ፡ አገልጋዮች ፡ ሁሉ ፡ ልብስ ፡ አውጣ ፡ አለው ። ልብሱንም ፡ አወጣላቸው ። ፲ ፳፪ ኢዩም ፡ የሬካብም ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ወደ ፡ በኣል ፡ ቤት ፡ ገቡ ። የበኣልንም ፡ አገልጋዮች ፡— መርምሩ ÷ ከበኦል ፡ አገልጋዮች ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ወገን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ እንዳይኖር ፡ ተመልከቱ ፡ አላቸው ። ፲ ፳፫ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕትም ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፤ ኢዩም ፡— በእጃችሁ ፡ አሳልፌ ፡ ከምሰጣችሁ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያመለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነፍሱ ፡ በዚያ ፡ ነፍስ ፡ ፋንታ ፡ ትሆናለች ፡ ብሎ ፡ በውጪ ፡ ሰማንያ ፡ ሰዎችን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ።

፲ ፳፬ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርበው ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ኢዩ ፡ ዘበኞቹንና ፡ አለቆቹን ፡— ግቡና ፡ ግደሉአቸው ፤ አንድም ፡ አይውጣ ፡ አላቸው ። በሰይፍም ፡ ስለት ፡ ገደሉአቸው ፤ ዘበኞችና ፡ አለቆችም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሉአቸው ÷ ወደ ፡ በኣልም ፡ ቤት ፡ ከተማ ፡ ሄዱ ። ፲ ፳፭ ከዘበኣልም ፡ ቤት ፡ ሐውልቶቹን ፡ አወጡ ፡ አቃጠሉአቸውም ። የበኣልን ፡ ሐውልት ፡ ቀጠቀጡ ÷ የበኣልንም ፡ ቤት ፡ አፈረሱ ÷ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የውኃቂ ፡ መጣያ ፡ አደረጉት ።

፲ ፳፮ እንዲሁም ፡ ኢዩ ፡ በኣልን ፡ ከእስራኤል ፡ አጠፋ ። ፲ ፳፯ ነገር ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናቦዋ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ÷ በቤቴልና ፡ በዳን ፡ ከነበሩት ፡ ከወርቁ ፡ እምቦሶች ÷ ኢዩ ፡ አልራቀም ። ፲ ፳፰ እግዚአብሔርም ፡ ኢዩን ፡— በፊቴ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አድርገሃልና ÷ በልቤም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በአክዓብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አድርገሃልና ፡ ልጆችህ ፡ እስከ ፡ አራት ፡

ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፡ አለው ። ፲ ፴ ኢዩ ፡ ግን ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ አልተጠነቀቀም ፤ እስራኤልንም ፡ ካሳተው ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ አልራቀም ።

፲ ፴፩ በዚያም ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ይከፋፍላቸው ፡ ዘንድ ፡ ጀመረ ፤ አዛሄልም ፡ በእስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ መታቸው ። ፲ ፴፪ በዮርዳኖስ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ የገለዓድን ፡ አገር ፡ ሁሉ ÷ በአርኖን ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከአሮዔር ፡ ጀምሮ ፡ የጋድንና ፡ የሮቤልን ፡ የምናሴንም ፡ አገር ÷ ገለዓድንና ፡ ባሳንን ፡ መታ ። ፲ ፴፫ የቀረውም ፡ የኢዩ ፡ ነገር ÷ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ÷ ጭከናውም ፡ ሁሉ ÷ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ኢዩም ፡ ከእባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በሰማርያም ፡ ቀበሩት ። በፋንታውም ፡ ልጁ ፡ ኢዮአካዝ ፡ ነገሠ ። ፲ ፴፬ ኢዩም ፡ በሰማርያ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ሀያ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ የአካዝያስም ፡ እናት ፡ ጎቶልያ ፡ ልጅዋ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በየች ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ የመንግ ፪ ሥትን ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ አጠፋች ። የንጉሡ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ የአካዝያስ ፡ እኅት ፡ ዮሳቤት ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአስን ፡ ወስዳ ፡ ከተገደሉት ፡ ከንጉሥ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ሰረቀችው ፡ እርሱንና ፡ ሞግዚቱንም ፡ ወደ ፡ አልፍኝ ፡ ወሰደች ÷ እንዳይገደልም ፡ ከጎቶልያ ፫ ፡ ሸሸገችው ። በእርስዋም ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተቀመጠ ። ፬ ጎቶልያም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነገሠች ። በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ዮዳሄ ፡ ልከ ፡ በካራውያንና ፡ በዘበኞች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የመቶ ፡ አለቆች ፡ ወሰደ ÷ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገባቸው ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አማላቸው ÷ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አሳያቸው ። ፭ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡— እንዲህ ፡ አድርጉ ፤ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከምትገቡት ፡ ከእናንተ ፡ ከሦስት ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ዘብ ፮ ጠብቁ ፤ ከእናንተ ፡ ከሦስት ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ በሱር ፡ በር ፡ ሁኑ ፤ አንዱም ፡ እጅ ፡ ከዘበኞች ፡ ቤት ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ በር ፡ ሁኑ ፡ ቤቱንም ፡ ጠብቁ ÷ ከልክሉም ፤ ከእናንተም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የምትወጡት ፡ ሁለቱ ፡ እጅ ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ ሆናችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ጠብቁ ። ፰ ንጉሡንም ፡ በዙሪያው ፡ ከበቡት ÷ የጦር ፡ ዕቃችሁም ፡ በእጃችሁ ፡ ይሁን ፤ በሰልፋችሁም ፡ መከከል ፡ የሚገባ ፡ ይገደል ፤ ንጉሡም ፡ በወጣና ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሁኑ ። ፱ መቶ ፡ አለቆችም ፡ ካህኑ ፡ ዮዳሄ ፡ ያዘዘውን ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ ፤ ከእነርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ በሰንበት ፡ ይገቡ ፡ የነበሩትን ÷ በሰንበቱም ፡ ይወጡ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ ዮዳሄ ፡ መጡ ። ፲ ካህኑም ፡ በእግ ፤ ዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡን ፡ የዳዊትን ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ለመቶ ፡ አለቆች ፡ ሰጣቸው ። ፲፩ ዘበኞቹም ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የጦር ፡ ዕቃቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ ከቤቱ ፡ ቀኝ ፡ እስከ ፡ ቤቱ ፡ ግራ ፡ ድረስ ፡ በመሠዊያውና ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ። ፲፪ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አውጥቶ ፡ ዘውዱን ፡ ጫነ ፡ በት ÷ ምስክሩንም ፡ ሰጠው ፤ ቀብተውም ፡ ንጉሥ ፡ አደረጉትና ፡— ንጉሡ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ እያሉ ፡ እጃቸውን ፡ አጨበጨቡ ።

፲፫ ጎቶልያም ፡ የሠራዊቱንና ፡ የሕዝቡን ፡ ድምፅ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መጣች ። ፲፬ እነሆም ÷ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ በዓምዱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ÷ ከንጉሡም ፡ ጋር ፡ አለቆችና ፡ መለከተኞች ፡ ቆመው ፡ እየች ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይነፋ ፡ ነበር ። ጎቶልያም ፡ ልብስዋን ፡ ቀድዳ ፡— ዓመፅ ፡ ነው ÷ ዓመፅ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ጮኸች ። ፲፭ ካህኑም ፡ ዮዳሄ ፡ በሞፍራው ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ የመቶ ፡ አለቆች ፡— ወደ ፡ ሰልፉ ፡ መካከል ፡ አውጡአት ፤ የሚከተላትንም ፡ በሰይፍ ፡ ግደሉት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ካህኑ ፡— በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አትገደል ፡ ብሎአልና ። ፲፮ እጃቸውንም ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ÷ በፈረሱም ፡ መግቢያ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወሰዱአት ፤ በዚያም ፡ ገደሉአት ።

፲፯ ዮዳሄም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በንጉሡ ፡ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፤ ደግሞም ፡ በንጉሡና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ። ፲፰ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ በኣል ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ አፈረሱት ፤ መሠዊያዎቹንና ፡ ምስሎቹን ፡ አደቀቁ ÷ የበኣልንም ፡ ካህን ፡ ማታንን ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ገደሉት ። ካህኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ ሾመ ። መቶ ፡ አለቆቹንና ፡ ከራውያንንም ÷ ፲፱ ዘበኞችንና ፡ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ፤ ንጉሡንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አወረዱት ÷ በዘበኞችም ፡ በር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቤት ፡ አመጡት ፤ በነገሥታቱም ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ። ፳ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ÷ ከተማይቱም ፡ ጸጥ ፡ አለች ። ንቶልያንም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉአት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ኢዮአስም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ፪ በኢዩ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ኢዮአስ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ÷ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ እናቱም ፡

ሳብያ ፡ የተባለች ፡ የቤርሳቤህ ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ፫ ፩ ከሀኑ ፡ ዮዳሄም ፡ ያስተምረው ፡ በነበረ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ኢዮአስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ፬ ፪ ነገር ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ በኮረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፡ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኮረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

፭ ፫ ኢዮአስም ፡ ካህናቱን ፡— ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚገባውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ÷ ስለ ፡ ነፍሱም ፡ ዋጋ ፡ የሚቀርበውን ፡ ገንዘብ ÷ በልባቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚያመጡትን ፡ ገንዘብ ፡ ፮ ፬ ሁሉ ÷ ካህናቱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከሚያመጣው ፡ ይውሰዱ ፡ በመቅደስም ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ይጠግኑበት ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ፯ ፭ ግን ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ኢዮአስ ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ካህናቱ ፡ አልጠገኑትም ፡ ፰ ፮ ነበር ። ኢዮአስም ፡ ካህኑን ፡ ዮዳሄንና ፡ ካህናቱን ፡ ጠርቶ ፡— በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ስፍራዎች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትጠግኑአቸውም ? ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ገንዘቡ ፡ ለቤቱ ፡ መጠገኛ ፡ ይሰጥ ፡ እንጂ ፡ ከሚያመጡት ፡ ሰዎች ፡ ፱ ፯ አትቀበሉ ፡ አላቸው ። ካህናቱም ፡— ከሕዝቡ ፡ ገንዘቡን ፡ እንወስድም ÷ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ እንጠግንም ፡ ብለው ፡ እሺ ፡ አሉ ። ፲ ፰ ካህኑ ፡ ዮዳሄ ፡ ግን ፡ ሣጥን ፡ ወስዶ ፡ መክደኛውን ፡ ነደለው ÷ በመሠዊያውም ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሚገቡበት ፡ መግቢያ ፡ በስተ ፡ ቀኝ ፡ አኖረው ። ደጆንም ፡ የሚጠብቁ ፡ ካህናት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ያኖሩበት ፡ ነበር ። ፲፩ ፱ በሣጥንም ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ መኖሩን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ጸሐፊና ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ ቁጥረው ፡ በከረጢት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሩት ፡ ነበር ። ፲፪ ፲ የተመዘነውንም ፡ ገንዘብ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ በተሾሙት ፡ ፲፫ ፲፩ እጅ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። የተናደውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመጠገን ፡ መክፈል ፡ ለሚያሻው ፡ ሁሉ ፡ ድንጋይና ፡ እንጨት ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለሚሠሩ ፡ አናጢዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ ፲፬ ፲፪ ገንዘቡን ፡ ሰጡ ። ያገለገሉትም ፡ ድንጋይ ፡ ወቃሪዎች ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከሚመጣው ፡ ገንዘብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚሆኑ ፡ የብር ፡ ጽዋዎችና ፡ ጕጠቶች ፡ ድስቶችም ፡ መለከቶችም ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃዎችም ፡ አልተሠሩም ፡ ነበር ። ፲፭ ፲፫ ነገር ፡ ግን ፡ ለሚሠሩት ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ጠገኑበት ። ፲፮ ፲፬ ለሠራተኞችም ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚወስዱትን ፡ ሰዎች ፡ አይቈጣጠሩ ፡ እቸውም ፡ ነበር ፤ በታማኝነት ፡ ይሠሩ ፡ ነበርና ። ፲፯ ፲፭ ስለ ፡ በደልና ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የቀረበውም ፡ ገንዘብ ፡ ለካህናት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አያገቡትም ፡ ነበር ።

፲፰ ፲፮ በዚያም ፡ ወራት ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ አዛኤል ፡ ወጥቶ ፡ ጌትን ፡ ወጋ ÷ ያዘውም ፤ አዛኤልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመውጣት ፡ ፊቱን ፡ አቀና ። ፲፱ ፲፯ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ አባቶቹ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ኢዮሣፍጥና ፡ ኢዮራም ፡ አካዝያስም ፡ የቀደሱትን ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ÷ እርሱም ፡ የቀደሰውን ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዝግብት ፡ የተገኘውን ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ÷ ወደ ፡ ሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አዛኤል ፡ ላከው ። እርሱም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሰ ።

፳ ፲፰ የቀረውም ፡ የኢዮአስ ፡ ነገር ÷ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ÷ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ፳፩ ፲፱ ባሪያዎቹም ፡ ተነሡበት ÷ ወደ ፡ ሲላ ፡ በሚወርደውም ፡ መንገድ ፡ በሚሎ ፡ ቤት ፡ ገደሉት ። ፳፪ ፳ ባሪያዎቹም ፡ የሰምዓት ፡ ልጅ ፡ ዮዘካርና ፡ የሾሜር ፡ ልጅ ፡ ዮዛባት ፡ መቱት ÷ ሞተም ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አሜስያስ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ፩ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአካዝያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአስ ፡ በሀያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዩ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአካዝ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ነገሠ ፤ ፪ ፪ አሥራ ፡ ሰባትም ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ÷ እስራኤልን ፡ ያሳተውን ፡ የናባጥን ፡ ልጅ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ኃጢአት ፡ ተከተለ ፤ ከእርስዋም ፡ አልራቀም ። ፫ ፫ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ በሶርያው ፡ ንጉሥ ፡ በአዛኤል ፡ እጅ ፡ በአዛኤልም ፡ ልጅ ፡ በወልደ ፡ አደር ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ። ፬ ፬ ኢዮአካዝም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤልን ፡ ያስጨነቀበትን ፡ ጭንቀት ፡ አይቶአልና ፡ ሰማው ። ፭ ፭ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ታዳጊ ፡ ሰጠ ÷ ከሶርያውያንም ፡ እጅ ፡ ዳኑ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ በድንኳኖቹ ፡ ተቀመጡ ። ፮ ፮ ነገር ፡ ግን ፡ በእርስዋ ፡ ቤቶ ፡ እንጂ ፡ እስራኤልን ፡ ካሰተው ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ኃጢአት ፡ አልራቁም ፤ ደግሞም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐፀድ ፡ በሰማርያ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ። ፯ ፯ ለኢዮአካዝም ፡ ከአምሳ ፡ ፈረሰኞች ÷ ከአሥርም ፡ ሰረገሎች ÷ ከአሥር ፡ ሺህም ፡ እግረኞች ፡ በቀር ፡ ሕዝብ ፡ አልቀረለትም ፤ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ አጥፍቶአቸዋልና ÷ በአውድማም ፡ እንዳለ ፡ ዕብቅ ፡ አድቅቆአቸዋልና ። ፰ ፰ የቀረውም ፡ የኢዮአካዝ ፡ ነገር ÷ ያደረገውም ፡ ሁሉ ÷ ጭከናውም ÷ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ፱ ፱ ኢዮአካዝም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በሰማር ፡ ያም ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ዮአስ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

፲ ፲ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአስ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ነገሠ ፤ አሥራ ፲፩ ፲፩ ስድስትም ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ባሳተው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ሄደ ፡ እንጂ ፡ ከእርስዋ ፡ አልራቀም ። ፲፪ ፲፪ የቀረውም ፡ የዮአስ ፡ ነገር ÷ ያደረገውም ፡ ሁሉ ÷ ከይሁዳም ፡ ከአሜስያስ ፡ ጋር ፡ የተዋጋበት ፡ ጭከና ÷ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ፲፫ ፲፫ ዮአስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ ኢዮርብዓምም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፤ ዮአስም ፡ በሰማርያ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ።

፲፬ ፲፬ ኤልሳዕም ፡ በሚሞትበት ፡ በሽታ ፡ ታመመ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ወርዶ ፡ በፊቱ ፡ አለቀሰና ፡— አባቴ ፡ ሆይ ÷ አባቴ ፡ ሆይ ÷ የእስራኤል ፡ ሰረገላና ፡ ፈረሰኞቹ ፡ አለ ። ፲፭ ፲፭ ኤልሳዕም ፡— ቀስትና ፡ ፍላጻዎች ፡ ውሰድ ፡ አለው ፤ ቀስቱንና ፡ ፍላጻዎችንም ፡ ወሰደ ። ፲፮ ፲፮ የእስራኤልንም ፡ ንጉሥ ፡— እጅህን ፡ በቀስቱ ፡ ላይ ፡ ጫን ፡ አለው ። እጁንም ፡ ጫነ ፡ በት ፤ ኤልሳዕም ፡ እጁን ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡— የምሥራቁን ፡ መስኮት ፡ ክፈት ፡ አለ ፤ ከፈተውም ። ኤልሳዕም ፡— ወርውር ፡ አለ ፤ ወረወረውም ። እርሱም ፡— የእግዚአብሔር ፡ መድኃኒት ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ በሶርያ ፡ ላይ ፡ የመድኃኒት ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ እስከ ፡ ታጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ሶርያውያንን ፡ በአፌቅ ፡ ትመታለህ ፡ አለ ። ፲፯ ፲፯ ደግሞም ፡— ፍላጻዎቹን ፡ ውሰድ ፡ አለው ፤ ወሰዳቸውም ። የእስራኤልንም ፡ ንጉሥ ፡— ምድሩን ፡ ምታው ፡ አለው ። ሦስት ፡ ጊዜም ፡ መትቶ ፡ ቆመ ። ፲፰ ፲፰ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ተቈጥቶ ፡— አምስት ፡ ወይም ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ መትተኸው ፡ ኖሮ ፡ ሶርያን ፡ እስከ ፡ ታጠፋው ፡ ድረስ ፡ በመታኸው ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሶርያን ፡ ትመታለህ ፡ አለ ።

፳ ፳ ኤልሳዕም ፡ ሞተ ÷ ቀበሩትም ። ከሞዓብም ፡ አደጋ ፡ ጣሪች ፡ በየዓመቱ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይገቡ ፡ ነበር ። ፳፩ ፳፩ ሰዎችም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲቀብሩ ፡ አደጋ ፡ ጣሪዎችን ፡ አዩ ÷ ሬሳውንም ፡ በኤልሳዕ ፡ መቃብር ፡ ጣሉት ፤ የኤልሳዕንም ፡ አጥንት ፡ በነካ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ድኖ ፡ በእግሩ ፡ ቆመ ።

፳፪ ፳፪ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ አዛኤል ፡ በኢዮአካዝ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እስራኤልን ፡ አስጨነቀ ። ፳፫ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ራራላቸው ÷ ማራቸውም ÷ ከአብርሃምና ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብም ፡ ጋር ፡ ስላደረገው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አነርሱን ፡ ተመለከተ ፤ ሊያጠፋቸውም ፡ አልወደደም ÷ ፈጽሞም ፡ ከፊቱ ፡ አልጣላቸውም ። ፳፬ ፳፬ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ አዛኤል ፡ ሞተ ፤ ልጁም ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ። ፳፭ ፳፭ አዛኤልም ፡ ከአባቱ ፡ ከኢዮአካዝ ፡ እጅ ፡ በሰልፍ ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከተሞች ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ከአዛዜል ፡ ልጅ ፡ ከወልደ ፡ አዴር ፡ እጅ ፡ ወሰደ ። ዮአስም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መታው ÷ የእስራኤልንም ፡ ከተሞች ፡ መለሰ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ ፩ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ በዮአስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ አሜስያስ ፡ ነገሠ ። ፪ ፪ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሀያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዮዓዳን ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ፫ ፫ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ ኢዮአስ ፡ እንዳደረገ ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ አላደረገም ። ፬ ፬ ነገር ፡ ግን ፡ በኮረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኮረብቶች ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ። ፭ ፭ መንግሥቱም ፡ በጸናለት ፡ ጊዜ ፡ አባቱን ፡ የገደሉትን ፡ ባሪያዎች ፡ ገደለ ። ፮ ፮ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ÷ እግዚአብሔርም ፡— ሁሉ ፡ በኃጢአቱ ፡ ይሙት ፡ እንጂ ፡ አባቶች ፡ በልጆች ፡ አይሙቱ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮቹን ፡ ልጆች ፡ አልገደለም ። ፯ ፯ አቤም ፡ በጨው ፡ ሸለቆ ፡ ከኤዶምያስ ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ገደለ ፤ ሴላን ፡ በሰልፍ ፡ ወስዶ ፡ ስምዋን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዮቅትኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራት ።

፰ ፰ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አሜስያስ ፡— ና ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንተያይ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮአስ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ። ፱ ፱ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡— የሊባኖስ ፡ ሱርንችት ፡— ልጅህን ፡ ለልጄ ፡ ሚስት ፡ አድርገህ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ላከ ፤ የሊባኖስም ፡ አውሬ ፡ አልፎ ፡ ሱርንችቱን ፡ ረገጠ ። ፲ ፲ ኤዶምያስን ፡ በእውነት ፡ መታህ ÷ ልብህንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግህ ፤ በዚያ ፡ ተመካ ÷ በቤትህም ፡ ተቀመጥ ፤ አንተ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋር ፡ ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ትሻለህ ? ብሎ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሜስያስ ፡ ላከ ።

፲፩ ፲፩ አሜስያስ ፡ ግን ፡ አልሰማም ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ ወጣ ÷ እርሱና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስም ፡ በይሁዳ ፡ ባለች ፡ በቤትሳሚስ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ። ፲፪ ፲፪ ይሁዳም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ተመታ ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ። ፲፫ ፲፫ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአስን ፡ ልጅ ፡ አሜስያስን ፡ በቤትሳሚስ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ ከኤፍሬም ፡ በር ፡ ጀምሮ ፡

እስከ ፡ ማዕዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አፈረሰ ። ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የነበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ በመ ያዣም ፡ የተያዙትን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ተመለሰ ።

፲፫ የቀረውም ፡ ያደረገው ፡ የዮአስ ፡ ነገር ፡ ጭከ ናውም ፡ ከይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ከአሜስያስ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ?

፲፬ ዮአስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ በሰማ ርያም ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ተቀ በረ ፤ ልጁም ፡ ኢዮርብዓም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

፲፭ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ አሜ ስያስ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ከዮአስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ አሥራ ፡ አም ስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ። የቀረውም ፡ የአሜስያስ ፡ ነገር ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በኢየሩሳሌምም ፡ የዓመፅ ፡ መሐላ ፡ አደረጉበት ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ኰበለለ ፤ በኋላውም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላኩ ፡ በዚያም ፡ ገደሉት ። በፈረስም ፡ ጭነው ፡ አመጡት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ። የይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የአሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ የነበረ ውን ፡ ዓዛርያስን ፡ ወስዶ ፡ በአባቱ ፡ በአሜስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠው ። ንጉሡም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ካንቀላፋ ፡ በኋላ ፡ ኤላትን ፡ ሠርቶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ መለሳት ።

፲፫ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ በአሜ ስያስ ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእስ ራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዮአስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፤ አርባ ፡ አንድ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳታቸው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ አልራቀም ። የጋትሔፈር ፡ በነበረው ፡ በአማቴ ፡ ልጅ ፡ በባሪያው ፡ በነቢዩ ፡ በዮናስ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ እምላክ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የእስራኤልን ፡ ድንበር ፡ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዓረባ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ መለሰ ። የታሰረውና ፡ የተለቀቀውም ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ እስራኤልንም ፡ የሚረዳ ፡ እንዳልነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ የመረረውን ፡ የእስራኤልን ፡ ጭንቀት ፡ አየ ።

፲፬ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ስም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ይደመስስ ፡ ዘንድ ፡ አልተናገረም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዮአስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ።

፲፭ የቀረውም ፡ የኢዮርብዓም ፡ ነገር ፡ ያደረገውም ፡ ሁሉ ፡ ጭከናውም ፡ እንደ ፡ ተዋጋም ፡ የይሁዳ ፡ የነበረውን ፡ ደማስቆንና ፡ ሐማትን ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ኢዮርብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ። ልጁም ፡ ዘካርያ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮርብዓም ፡ በሀያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የአሜ ስያስ ፡ ልጅ ፡ ዓዛርያስ ፡ ነገሠ ። መንገሥም ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የአሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ይኮልያ ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ። አባቱ ፡ አሜ ስያስ ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ በከፍ ፩ ብቶች ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፡ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በከረብቶች ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡ ንጉሡን ፡ ቀሠፈው ፡ እስከ ፪ ሚሞትበትም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለምጻም ፡ ሆነ ፡ በተለየ ፡ ቤትም ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ የንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ሠልጥኖ ፡ ለአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ። የቀረ ፫ ውም ፡ የዓዛርያስ ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ዓዛርያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

፭ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓዛርያስ ፡ በሠላሳ ፡ ስምን ተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ዘከርያ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ። አባቶቹም ፡ እንዳደረጉት ፡ በእግዚአ ፮ ብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳታቸው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ አልራቀም ። የአሴሊቤስ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ተማማለበት ፡ በይብላዓም ፡ መትቶ ፡ ገደለው ፡ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። የቀረውም ፡ የዘከርያ ፡ ነገር ፡ እነሆ ፡ በእስራ ፲፩ ኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ አል ። ለኢዩ ፦ ልጆችህ ፡ እስከ ፡ አራት ፲፪ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ ሆነ ።

፲፫ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ዓመት ፡ የኢያቤስ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ነገሠ ፤ በሰማርያም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ነገሠ ። የጋዲም ፡ ልጅ ፡ ምናሔም ፡ ከቴርሳ ፡ ወጥቶ ፲፬ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ መጣ ፡ በሰማርያም ፡ የኢያቤስን ፡ ልጅ ፡ ሰሎምን ፡ መታ ፡ ገደለውም ፤ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። የቀረውም ፡ የሰሎም ፡ ነገር ፡ የተማማለውም ፡ ዓመፅ ፡ እነሆ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎአል ። ፲፭ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ምናሔም ፡ ከቴርሳ ፡ ወጥቶ ፡ ቲፍሳን ፡ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ ዳርቻዋንም ፡ መታ ፡ ይከፍቱለትም ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና ፡ መታት ፡ በእርስዋም ፡ የነበሩትን ፡ እርጉዞች ፡ ሁሉ ፡ ቀደዳቸው ።

፲፯ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓዛርያስ ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ዓመት ፡ የጋዲ ፡ ልጅ ፡ ምናሔም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፤ በሰማርያም ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢአት ፡ አልራቀም ። በዘመኑም ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ፎሐ ፡ በምድሪቱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ ምናሔምም ፡ መንግሥቱን ፡ በእጁ ፡ ያጸናለት ፡ ዘንድ ፡ የፎሐ ፡ እጅ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንዲሆን ፡ አንድ ፡ ሺህ ፳ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ሰጠው ። ምናሔምም ፡ ብሩን ፡ ለአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡ ባለ ፡ ጠጎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ላይ ፡ አምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ አስገብሮ ፡ አወጣ ። የአሦር ፳፩ ንጉሥ ፡ ተመለሰ ፡ በአገሪቱም ፡ አልተ ቀመጠም ። የቀረውም ፡ የምናሔም ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥ ፳፪ ታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ፳፫ ምናሔም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ ልጁም ፡ ፋቁስያስ ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

፳፫ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በዓዛርያስ ፡ በአምሳ ፳፬ ኛው ፡ ዓመት ፡ የምናሔም ፡ ልጅ ፡ ፋቁስያስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፤ ፳፭ ሁለት ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳ ተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢ አት ፡ አልራቀም ። የሠራዊቱም ፡ አለቃ ፡ የሮ ሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ተማማለበት ፡ በሰማ ርያም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ከአር ጎብና ፡ ከአርያ ፡ ጋር ፡ መታው ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አምሳ ፡ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ገደለ ፳፮ ውም ፡ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። የቀረውም ፡ የፋቁስያስ ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ፳፯ እነሆ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ተጽፎአል ።

፳፰ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓዛርያስ ፡ በአምሳ ፡ ሁለ ተኛው ፡ ዓመት ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ በእ ስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፤ ፳፱ ሀያ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳ ተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኃጢ አት ፡ አልራቀም ።

፴ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በፋቁሔ ፡ ዘመን ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ መጥቶ ፡ ኢዮንና ፡ አቤልቤትመዓካን ፡ ያኖዋንም ፡ ቃዴ ስንና ፡ አሶርንም ፡ ገለዓድንና ፡ ገሊላንም ፡ የንፍ ታሌምን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ፤ ወደ ፡ አሦርም ፡ አፈለሳቸው ። በ፫ዝያንም ፡ ልጅ ፡ በኢዮአ ታም ፡ በሀያኛው ፡ ዓመት ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ሆሴዕ ፡ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ ላይ ፡ ተማማለ ፡ መትቶም ፡ ገደለው ፡ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

፴፩ የቀረውም ፡ የፋቁሔ ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እነሆ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎአል ።

፴፪ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የዖዝያን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡ ነገሠ ። ፴፫ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ኢየሩሳ ፴፬ ነበረች ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ አባቱ ፡ ዖዝያን ፡ እንዳደረገ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ በከረብቶች ፴፭ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፡ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በከረብቶች ፡ ላይ ፡ በሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የላይኛውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ በር ፡ ሠራ ። የቀረውም ፡ የኢዮአታም ፡ ነገር ፡ የሠ ፴፮ ራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በዚ ፴፯ ያም ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶንንና ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔን ፡ በይ ሁዳ ፡ ላይ ፡ መስደድ ፡ ጀመረ ። ፴፰ ኢዮአታም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፡ በአባቱም ፡ በዳ ዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አካዝ ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ በአሥራ ፡ ሰባ ተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአ ታም ፡ ልጅ ፡ አካዝ ፡ ነገሠ ። ፪ አካዝ ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በአም ላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አላ ደረገም ። ፫ ነገር ፡ ግን ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ሄደ ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእ ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳሳደዳቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ ልጁን ፡ በእሳት ፡ አሳ ለፈው ። በመስገጃዎችና ፡ በከረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ፬ በለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ በታች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

፭ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶንና ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ሊዋጉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ፤ አካዝንም ፡ ከበቡት ፡ ሊያሸንፉት ፡ ግን ፡ አልቻሉም ። ፮ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶን ፡ ኤላትን ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ መለሰ ፡ አይሁድንም ፡ ከኤላት ፡ አሳደደ ፤ ኤዶማውያንም ፡ ወደ ፡ ኤላት ፡ መጥተው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእር ስዋ ፡ ተቀምጠዋል ።

፯ አካዝም ፦ እኔ ፡ ባሪያህና ፡ ልጅህ ፡ ነኝ ፤ መጥተህ ፡ ከተነሡብን ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥና ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አሦር ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡

ፍ፣ መልእክተኞችን ላከ ። አካዝም ፣ በእግዚአ
ብሔር ቤትና ፣ በንጉሡ ቤት ፣ መዛግብት ፣
የተገኘውን ፣ ብርና ፣ ወርቅ ፣ ወስዶ ፣ ወደ ፣
አሦር ፣ ንጉሥ ፣ ገጸ ፣ በረከት ፣ አድርጎ ፣ ሰደ
ደው ። የአሦርም ፣ ንጉሥ ፣ ሰማው ፣ የአሦርም ፣
ንጉሥ ፣ በደማስቆ ፣ ላይ ፣ ወጣበት ፣ ወሰዳትም ÷
ሕዝብዋንም ፣ ወደ ፣ ቂር ፣ አፈለሰባቸው ÷ ረአሶ
ንንም ፣ ገደለ ።

፲ ። ንጉሡም ፣ አካዝ ፣ የአሦርን ፣ ንጉሥ ፣ ቴል
ጌልቴልፌልሶርን ፣ ሊገናኘው ፣ ወደ ፣ ደማስቆ ፣
ሄደ ፣ በደማስቆ ፣ የነበረውን ፣ መሠዊያ ፣ አየ ፣
ንጉሡም ፣ አካዝ ፣ የመሠዊያውን ፣ ምሳሌና ፣
የአሠራሩን ፣ መልክ ፣ ወደ ፣ ካህኑ ፣ ወደ ፣ አርያ ፣
፲፩ ። ላከው ። ካህኑም ፣ አርያ ፣ መሠዊያ ፣ ሠራ ፣
ንጉሡ ፣ አካዝ ፣ ከደማስቆ ፣ ልኮ ፣ እንዳዘዘው ፣
ሁሉ ፣ እንዲሁ ፣ ካህኑ ፣ አርያ ፣ ንጉሡ ፣ አካዝ ፣
፲፪ ። ከደማስቆ ፣ እስኪመጣ ፣ ድረስ ፣ ሠራው ። ንጉ
ሡም ፣ ከደማስቆ ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ መሠዊያውን ፣
አየ ፣ ንጉሡም ፣ ወደ ፣ መሠዊያው ፣ ቀርቦ ፣ በእ
፲፫ ። ርሱ ፣ ላይ ፣ ወጣ ። በመሠዊያውም ፣ ላይ ፣ የሚ
ቃጠለውን ፣ መሥዋዕትና ፣ የእህሉን ፣ ቍርባን ፣
አሳረገ ÷ የመጠጡንም ፣ ቍርባን ፣ አፈሰሰ ÷
፲፬ ። የደኅንነቱንም ፣ መሥዋዕት ፣ ደም ፣ ረጨ ። በእ
ግዚአብሔርም ፣ ፊት ፣ የነበረውን ፣ የናሱን ፣
መሠዊያ ፣ ከመቅደሱ ፣ ፊት ፣ ከመሠዊያውና ፣
ከእግዚአብሔር ፣ ቤት ፣ መካከል ፣ ፈቀቅ ፣ አድ
ርጎ ፣ በመሠዊያው ፣ አጠገብ ፣ በሰሜን ፣ በኩል ፣
፲፭ ። አኖረው ። ንጉሡም ፣ አካዝ ፣ — የሚቃጠለ
ውን ፣ የጥዋት ፣ መሥዋዕት ÷ የማታውንም ፣
የእህሉን ፣ ቍርባን ÷ የንጉሡንም ፣ የሚቃጠለ
ውን ፣ መሥዋዕትና ፣ የእህሉን ፣ ቍርባን ÷ ለአ
ገሩም ፣ ሕዝብ ፣ የሚሆን ፣ የሚቃጠለውን ፣ መሥ
ዋዕትና ፣ የእህሉን ፣ የመጠጡንም ፣ ቍርባን ፣
በታላቁ ፣ መሠዊያ ፣ ላይ ፣ አቅርብ ፣ የሚቃጠለ
ውንም ፣ መሥዋዕት ፣ ደም ፣ ሁሉ ፣ የሌላ ፣ መሥዋ
ዕቱንም ፣ ደም ፣ ሁሉ ፣ ርጭበት ፣ የናሱ ፣ መሠ
ዊያ ፣ ግን ፣ እኔ ፣ እጠይቅበት ፣ ዘንድ ፣ ይሁን ፣
፲፮ ። ብሎ ፣ ካህኑን ፣ አርያን ፣ አዘዘው ። ካህኑ ፣ አርያ ፣
ንጉሡ ፣ አካዝ ፣ እንዳዘዘው ፣ ሁሉ ፣ እንዲሁ ፣
አደረገ ።

፲፯ ። ንጉሡም ፣ አካዝ ፣ የመቀመኣዎችን ፣ ክፈፍ ፣
ቊረጠ ÷ ከእነርሱም ፣ የመታጠቢያውን ፣ ሰኖች ፣
ወሰደ ፣ ኵሬውንም ፣ ከበታቹ ፣ ከነበሩት ፣ ከናሱ ፣
በሬዎች ፣ አወረደው ÷ በጠፍጣፋውም ፣ ድን
፲፰ ። ጋይ ፣ ላይ ፣ አኖረው ። በእግዚአብሔርም ፣ ቤት ፣
የዙፋኑን ፣ መሠረት ፣ ሠራ ÷ ስለ ፣ አሦርም ፣
ንጉሥ ፣ በውጭ ፣ ያለውን ፣ የንጉሡን ፣ መን
ገድ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ቤት ፣ አዞረው ።
፲፱ ። የቀረውም ፣ አካዝ ፣ ያደረገው ፣ ነገር ፣ በይሁዳ ፣
ነገሥታት ፣ ታሪክ ፣ መጽሐፍ ፣ የተጻፈ ፣ አይደ
ም ? ለምን ? አካዝም ፣ ከአባቶቹ ፣ ጋር ፣ አንቀላፋ ÷
በዳዊትም ፣ ከተማ ፣ ከአባቶቹ ፣ ጋር ፣ ተቀበረ ፣
ልጁም ፣ ሕዝቅያስ ፣ በእርሱ ፣ ፋንታ ፣ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፣ ፲፯ ።

፩ ። በይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ በአካዝ ፣ በአሥራ ፣ ሁለ
ተኛው ፣ ዓመት ፣ የኤላ ፣ ልጅ ፣ ሆሴዕ ፣ በእስራ
ኤል ፣ ላይ ፣ በሰማርያ ፣ ንጉሥ ፣ ሆነ ፣ ዘጠኝ ፣
፪ ። ዓመትም ፣ ነገሠ ። በእግዚአብሔርም ፣ ፊት ፣
ክፉ ፣ ነገር ፣ አደረገ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ከእርሱ ፣ አስ
ቀድሞ ፣ እንደ ፣ ነበሩት ፣ እንደ ፣ እስራኤል ፣
፫ ። ነገሥታት ፣ አይደለም ። የአሦርም ፣ ንጉሥ ፣
ስልምናሶር ፣ በእርሱ ፣ ላይ ፣ ወጣ ፣ ሆሴዕም ፣
፬ ። ተገዛለት ÷ ግብርም ፣ አመጣለት ። የአሦርም ፣
ንጉሥ ፣ በሆሴዕ ፣ ላይ ፣ ዓመፅ ፣ አገኘ ፣ መልእክ
ተኞችን ፣ ወደ ፣ ግብጽ ፣ ንጉሥ ፣ ወደ ፣ ሶኅር ፣
ልኮ ፣ ነበርና ፣ እንደ ፣ ልማዱም ፣ በየዓመቱ ፣ ለአ
ሦር ፣ ንጉሥ ፣ ግብር ፣ አልሰጠምና ፣ ስለዚህ ፣
የአሦር ፣ ንጉሥ ፣ ይዞ ፣ በወህኒ ፣ ቤት ፣ አሰረው ።
፭ ። የአሦርም ፣ ንጉሥ ፣ በምድር ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣
ወጣ ፣ ወደ ፣ ሰማርያም ፣ ወጥቶ ፣ ሦስት ፣ ዓመት ፣
፮ ። ከበባት ። በሆሴዕ ፣ በዘጠኝኛው ፣ ዓመት ፣ የአ
ሦር ፣ ንጉሥ ፣ ሰማርያን ፣ ወሰደ ÷ እስራኤል
ንም ፣ ወደ ፣ አሦር ፣ አፈለሰ ÷ በእላሔና ፣ በአ
ቦር ፣ በጎዛንም ፣ ወንዝ ፣ በሚዶንም ፣ ከተሞች ፣
አኖራቸው ።

፯ ። የእስራኤልም ፣ ልጆች ፣ ከግብጽ ፣ ንጉሥ ፣
ከፈርዖን ፣ እጅ ÷ ከግብጽ ፣ ምድር ፣ ያወጣቸ
ውን ፣ አምላካቸውን ፣ እግዚአብሔርን ፣ በድ
ለው ፣ ነበርና ÷ ሌሎችንም ፣ አማልክት ፣ አም
ልከው ፣ ነበርና ÷ እግዚአብሔርም ፣ ከእስራ
ኤል ፣ ልጆች ፣ ፊት ፣ ባሳደዳቸው ፣ በአሕዛብ ፣
፰ ። ሥርዓት ÷ የእስራኤልም ፣ ነገሥታት ፣ በደረ
ጓት ፣ ሥርዓት ፣ ሄደው ፣ ነበርና ፣ እንደዚህ ፣
፱ ። ሆነ ። የእስራኤልም ፣ ልጆች ፣ በአምላካቸው ፣
በእግዚአብሔር ፣ ላይ ፣ ቅን ፣ ያልሆነን ፣ ነገር ፣
በስውር ፣ አደረጉ ፣ በከተሞቻቸውም ፣ ሁሉ ፣
ከዘበኞች ፣ ግንብ ፣ ጀምሮ ፣ እስከ ፣ ተመሸገች ፣
ከተማ ፣ ድረስ ፣ በከፍታ ሞቹ ፣ ላይ ፣ መስገጃዎ
፲ ። ችን ፣ ሠሩ ። በረጃጅሙ ፣ ኮረብታ ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣
በለመለመውም ፣ ዛፍ ፣ ሁሉ ፣ ታች ፣ ሐውልቶ
ችንና ፣ የማምለኪያ ፣ ዐፀዶችን ፣ ተከሉ ። እግ
፲፩ ። ዚአብሔርም ፣ ከፊታቸው ፣ ያወጣቸው ፣ አሕ
ዛብ ፣ እንዳደረጉት ÷ በኮረብቶቹ ፣ መስገጃዎች
ሁሉ ፣ ላይ ፣ ያጥኑ ፣ ነበር ። እግዚአብሔርንም ፣
፲፪ ። ያስቈጡ ፣ ዘንድ ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ አደረጉ ። እግዚ
አብሔርም ፣ የከለከላቸውን ፣ ጣዖቶች ፣ አመ
፲፫ ። ለኩ ። እግዚአብሔርም ፣ — ከክፉ ፣ መንገዳ
ችሁ ፣ ተመለሱ ፣ ለአብቶቻችሁም ፣ እንዳዘዝ
ሁት ÷ በነቢያዎቼ ፣ በነቢያት ፣ የላክሁላችሁን ፣
ትእዛዜንና ፣ ሥርዓቴን ፣ ሕጌንም ፣ ሁሉ ፣ ጠብቁ ፣
ብሎ ፣ በነቢዩ ፣ ሁሉና ፣ በባለ ፣ ራእዩ ፣ አፍ ፣
ሁሉ ፣ በእስራኤልና ፣ በይሁዳ ፣ መሰከረ ።
፲፬ ። ነገር ግን ፣ አምላካቸውን ፣ እግዚአብሔርን ፣ አን
ዳላመኑ ፣ እንደ ፣ አባቶቻቸው ፣ አንገት ፣ አንገ
ታቸውን ፣ እደነደኑ ፣ እንጂ ፣ አልሰሙም ።

፲፭ ። ሥርዓቱንም ፣ ከአባቶቻቸውም ፣ ጋር ፣ ያደረገ
ውን ፣ ቃል ፣ ኪዳን ÷ ያጸናላቸውንም ፣ ምስክ
ራን ፣ ናቁ ፣ ከንቱ ፣ ነገርንም ፣ ተከተሉ ÷ ምና
ምንቴዎችም ፣ ሆኑ ÷ እግዚአብሔርም ፣ እንደ
፲፮ ። እነርሱ ፣ እንዳይሠሩ ፣ ያዘዛቸውን ፣ በዙሪያ
ቸው ፣ ያሉትን ፣ አሕዛብን ፣ ተከተሉ ። የአም
ላካቸውንም ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ትእዛዝ ፣ ሁሉ ፣
ተዉ ÷ ቀልጠው ፣ የተሠሩትንም ፣ የሁለቱን ፣
እምቦሶች ፣ ምስሎች ፣ አደረጉ ÷ የማምለኪያ ፣
ዐፀድንም ፣ ተከሉ ÷ ለሰማይም ፣ ሠራዊት ፣
፲፯ ። ሁሉ ፣ ሰገዱ ÷ በኣልንም ፣ አመለኩ ። ወንዶ
ችና ፣ ሴቶች ፣ ልጆቻቸውን ፣ በእሳት ፣ አሳለፉ
አቸው ÷ ምዋርተኞችና ፣ አስማተኞችም ፣
ሆኑ ÷ ያስቈጡትም ፣ ዘንድ ፣ በእግዚአብሔር ፣
፲፰ ። ፊት ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ ለማድረግ ፣ ራሳቸውን ፣
ሸጡ ። ስለዚህም ፣ እግዚአብሔር ፣ በእስራኤል ፣
ላይ ፣ እጅግ ፣ ተቈጣ ÷ ከፊቱም ፣ ጣላቸው ፣
ከይሁዳም ፣ ነገድ ፣ ብቻ ፣ በቀር ፣ ማንም ፣ አል
፲፱ ። ቀረም ።

ይሁዳም ፣ ደግሞ ፣ እስራኤል ፣ በደረጋት ፣
ሥርዓት ፣ ሄደ ፣ እንጂ ፣ የአምላኩን ፣ የእግዚአ
ብሔርን ፣ ትእዛዝ ፣ አልጠበቀም ። እግዚአብ
ሔርም ፣ የእስራኤልን ፣ ዘር ፣ ሁሉ ፣ ጠላ ÷ አስ
ጨነቃቸውም ÷ ከፊቱም ፣ እስኪጥላቸው ፣
ድረስ ፣ በበዝባዦች ፣ እጅ ፣ አሳልፎ ፣ ሰጣቸው ።
፳ ። እስራኤልንም ፣ ከዳዊት ፣ ቤት ፣ ለየ ፣ የናባጥ
ንም ፣ ልጅ ፣ ኢዮርብዓምን ፣ አነገሡ ፣ ኢዮርብ
ዓምም ፣ እግዚአብሔርን ፣ ከመከተል ፣ እስራኤ
ልን ፣ መለሰ ÷ ታላቅም ፣ ኃጢአት ፣ አሠራቸው ።
፳፩ ። የእስራኤልም ፣ ልጆች ፣ ኢዮርብዓም ፣ በደረ
ገው ፣ ኃጢአት ፣ ሁሉ ፣ ሄዱ ፣ እግዚአብሔርም ፣
በባሪያዎቹ ፣ በነቢያቱ ፣ ሁሉ ፣ አፍ ፣ እንደ ፣
ተናገረው ፣ እስራኤልን ፣ ከፊቱ ፣ እስኪያወጣ ፣
ድረስ ፣ ከእርስዋ ፣ አልራቁም ። እስራኤልም ፣
እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ ከምድሩ ፣ ወደ ፣ አሦር ፣
፳፫ ። ፈለሰ ።

፳፬ ። የአሦርም ፣ ንጉሥ ፣ ከባቢሎንና ፣ ከኩታ ፣
ከአዋና ፣ ከሐማት ፣ ከሰፈርዋይም ፣ ሰዎችን ፣
አመጣ ÷ በእስራኤልም ፣ ልጆች ፣ ፋንታ ፣ በሰማ
ርያ ፣ ከተሞች ፣ አኖራቸው ፣ ሰማርያንም ፣ ወረ
ሱአት ፣ በከተሞችዋም ፣ ተቀመጡ ። በዚያም ፣
መቀመጥ ፣ በጀመሩ ፣ ጊዜ ፣ እግዚአብሔርን ፣
፳፭ ። አይፈሩትም ፣ ነበር ። እግዚአብሔርም ፣ አን
ሶች ፣ ሰደደባቸው ÷ ይገድሉአቸውም ፣ ነበር ።
፳፮ ። ስለዚህም ፣ ለአሦር ፣ ንጉሥ ፣ — ያፈለስኻቸው ÷
በሰማርያም ፣ ከተሞች ፣ ያኖርኻቸው ፣ የአገ
ሩን ፣ አምላክ ፣ ወግ ፣ አላወቁም ፣ የአገሩን ፣
አምላክ ፣ ወግ ፣ አላወቁምና ፣ አንበሶችን ፣ ሰድ
ዶባቸዋል ÷ እነሆም ፣ ገደሉአቸው ፣ ብለው ፣
፳፯ ። ተናገሩት ።

፳፰ ። የአሦርም ፣ ንጉሥ ፣ — ከዚያ ፣ ከመጣችኋ
ቸው ፣ ካህናት ፣ አንዱን ፣ ውሰዱ ፣ ሄዶም ፣
በዚያ ፣ ይቀመጥ ÷ የአገሩንም ፣ አምላክ ፣ ወግ ፣
ያስተምራቸው ፣ ብሎ ፣ አዘዘ ። ከሰማርያም ፣
ከፈለሱአቸው ፣ ካህናት ፣ አንዱ ፣ መጥቶ ፣ በቤ
ቴል ፣ ተቀመጠ ÷ እግዚአብሔርንም ፣ እንዴት ፣
እንዲፈሩት ፣ ያስተምራቸው ፣ ነበር ። በየሕዝ ፳፱ ።
ባቸውም ፣ አምላክነቸውን ፣ አደረጉ ÷ ሰምራው
ያንም ፣ በሠሩት ፣ በኮረብታው ፣ መስገጃዎች ፣
ሕዝቡ ፣ ሁሉ ፣ በሚኖሩበት ፣ ከተሞቻቸው ፣ አኖ
ሩአቸው ። የባቢሎንም ፣ ሰዎች ፣ ሱኮትበኖ ፴ ።
ትን ፣ ሠሩ ፣ የኩታም ፣ ሰዎች ፣ ኤርጌልን ፣ ሠሩ ፣
የሐማትም ፣ ሰዎች ፣ አሲማትን ፣ ሠሩ ፣ አዋው
ያንም ፣ ኤልባዝርንና ፣ ተርታቅን ፣ ሠሩ ፣ የሴፈ ፴፩ ።
ርዋይም ፣ ሰዎችም ፣ ለሴፈርዋይም ፣ እሳልክት ፣
ለአድራሜሌክና ፣ ለአኒሜሌክ ፣ ልጆቻቸውን ፣
በእሳት ፣ ያቃጥሉ ፣ ነበር ። እግዚአብሔርንም ፴፪ ።
ይፈሩ ፣ ነበር ÷ ከመካከላቸውም ፣ ለኮረብታው
መስገጃዎች ፣ ካህናት ፣ አደረጉ ÷ በኮረብታ
ውም ፣ መስገጃዎች ፣ ይሠዉ ፣ ነበር ። እግዚአ ፴፫ ።
ብሔርንም ፣ ሲፈሩ ፣ ከመካከላቸው ፣ እንደ ፣
ፈለሱት ፣ እንደ ፣ አሕዛብ ፣ ልማድ ፣ እምላካቸ
ውን ፣ ያመልኩ ፣ ነበር ።

፴፬ ። እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ እንደ ፣ ቀደመው ፣ ልማድ ፣
ያደርጋሉ ። እግዚአብሔርንም ፣ አይፈሩም ÷
እግዚአብሔርም ፣ እስራኤል ፣ ብሎ ፣ የጠራ
ውን ፣ የያዕቆብን ፣ ልጆች ፣ እንዳዘዛቸው ፣
ሥርዓትና ፣ ፍርድ ፣ ሕግና ፣ ትእዛዝም ፣ አያደ
ርጉም ። እግዚአብሔርም ፣ ከእነርሱ ፣ ጋር ፣ ፴፭ ።
ቃል ፣ ኪዳን ፣ አደረገ ÷ እንዲህም ፣ ብሎ ፣ አዘዛ
ቸው ፣ — ሌሎችን ፣ አማልክት ፣ አትፍሩ ÷ አት
ስገዱላቸው ÷ አታምልኩአቸው ÷ አትሠዉ
ላቸው ፣ ነገር ፣ ግን ፣ በታላቅ ፣ ኃይል ፣ በተዘረጋ ፴፮ ።
ችም ፣ ክንድ ፣ ከግብጽ ፣ ምድር ፣ ያወጣችሁን ፣
እግዚአብሔር ፣ እርሱን ፣ ፍሩ ÷ ለእርሱም ፣
ስገዱ ÷ ለእርሱም ፣ ሠዉ ፣ የጻፈላችሁንም ፣ ፴፯ ።
ሥርዓትና ፣ ፍርድ ፣ ሕግና ፣ ትእዛዝም ፣ ለዘላ
ለም ፣ ታደርጉ ፣ ዘንድ ፣ ጠብቁ ፣ ሌሎችንም ፣
አማልክት ፣ አትፍሩ ። ከእናንተም ፣ ጋር ፣ ያደ ፴፰ ።
ረግሁትን ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ አትርሱ ፣ ሌሎችንም ፣
አማልክት ፣ አትፍሩ ። አምላካችሁን ፣ እግዚ ፴፱ ።
አብሔርን ፣ ፍሩ ፣ እርሱም ፣ ከጠላቶቻችሁ ፣
ሁሉ ፣ እጅ ፣ ያድናችኋል ። ነገር ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ፵ ።
ቀደመው ፣ ልማዳቸው ፣ አደረጉ ፣ እንጂ ፣ አል
ሰሙም ። እነዚህም ፣ አሕዛብ ፣ እግዚአብሔ ፵፩ ።
ርን ፣ ይፈሩ ፣ ነበር ፣ ደግሞም ፣ የተቀረጹ ፣ ምስ
ሎቻቸውን ፣ ያመልኩ ፣ ነበር ፣ ልጆቻቸውም ፣
የልጅ ፣ ልጆቻቸውም ፣ አባቶቻቸው ፣ እንዳደ
ረጉ ፣ እንዲሁ ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ ያደርጋሉ ።

ምዕራፍ ፣ ፲፰ ።

፩ ። እንዲህም ፣ ሆነ ፣ በእስራኤል ፣ ንጉሥ ፣ በኤላ ፣
ልጅ ፣ በሆሴዕ ፣ በሦስተኛው ፣ ዓመት ፣ የይሁዳ ፣
፪ ። ንጉሥ ፣ የአካዝ ፣ ልጅ ፣ ሕዝቅያስ ፣ ነገሠ ። መን
ግሥ ፣ በጀመረ ፣ ጊዜ ፣ የሠያ ፣ አምስት ፣ ዓመት ፣
ጒልማሳ ፣ ነበረ ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ ሠያ ፣ ዘጠኝ ፣
፫ ። ዓመት ፣ ነገሠ ፤ እናቱም ፣ የዘካርያስ ፣ ልጅ ፣
አቡ ፣ ነበረች ። እርሱም ፣ አባቱ ፣ ዳዊት ፣ እን ፫ ።

ዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡
፬ ፡ ነገርን ፡ አደረገ ። በኮረብታም ፡ ያሉትን ፡ መስ
ገጃዎች ፡ አስወገደ ፡ ሐውልቶችንም ፡ ቀለጣ
ጠመ ፡ የማምለኪያ ፡ ዐፀዶቹንም ፡ ቈረጠ ፡ የእ
ስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡
ያጥኑለት ፡ ነበርና ፡ ሙሴ ፡ የሠራውን ፡ የናሱን ፡
እባብ ፡ ሰባበረ ፡ ስሙንም ፡ ነሑሽታን ፡ ብሎ ፡
፭ ፡ ጠራው ። በእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ታመነ ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ከእርሱም ፡
በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ከይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡
፮ ፡ እርሱን ፡ የሚመስል ፡ አልነበረም ። ከእግዚአ
ብሔርም ፡ ጋር ፡ ተጣበቀ ፡ እርሱንም ፡ ከመከ
ተል ፡ አልራቀም ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡
፯ ፡ ያዘዘውን ፡ ትእዛዛቱን ፡ ጠበቀ ። እግዚአብሔ
ርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ የሚሄድበትም ፡
መንገድ ፡ ተከናወነለት ፡ በአሦርም ፡ ንጉሥ ፡
፰ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፡ አልገበረለትም ። ፍልስጥኤማ
ውያንንም ፡ እስከ ፡ ጋዛና ፡ እስከ ፡ ዳርቻዋ ፡
ድረስ ፡ ከዘበኞች ፡ ግንብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ምሽጉ ፡ ከተማ ፡ ድረስ ፡ መታ ።

፱ ፡ በንጉሡ ፡ በሕዝቅያስ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡
በአስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኤላ ፡ ልጅ ፡ በሆሴዕ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ሰል
ምናሶር ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ወጣ ፡ ከበባትም ።
፲ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ ወሰዳት ፡ በሕዝቅ
ያስ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ በእስራኤል ፡
ንጉሥ ፡ በሆሴዕ ፡ በዘጠኝኛው ፡ ዓመት ፡ ሰማ
፲፩ ፡ ርያ ፡ ተያዘች ። የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ አስራኤልን ፡
ወደ ፡ አሦር ፡ አፈለሰ ፡ በአላሔና ፡ በአቦር ፡
በጎዛንም ፡ ወንዝ ፡ በሜዶንም ፡ ከተሞች ፡ አኖ
፲፪ ፡ ራቸው ፡ የእምላክቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ አልሰሙምና ፡ ቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ አፍ
ርሰዋልና ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡
ያዘዘውን ፡ ሁሉ ፡ አልሰሙምና ። አላደረጉምና ።
፲፫ ፡ በንጉሡም ፡ በሕዝቅያስ ፡ በአሥራ ፡ አራተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡
ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ ተመሸጉት ፡ ከተሞች ፡
፲፬ ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ፡ ወሰዳቸውም ። የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡
ሕዝቅያስ ፡ — በድያለሁ ፡ ከእኔ ፡ ተመለስ ፡ የም
ትጭንብኝን ፡ ሁሉ ፡ እሸከማለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
አሦር ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላከ ። የአሦርም ፡
ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ላይ ፡
ሦስት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ ሠላሳ ፡ መክ
፲፭ ፡ ሊት ፡ ወርቅ ፡ ሚነበት ። ሕዝቅያስም ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግ
፲፮ ፡ ብት ፡ የተገኘውን ፡ ብር ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ። በዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መቅ
ደስ ፡ ደጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡
ከለበጣቸው ፡ መቃኖች ፡ ወርቁን ፡ ቈረጠ ። ለአ
፲፯ ፡ ሦርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰጠው ።

፲፯ ፡ የአሦርም ፡ ንጉሥ ፡ ተርታንንና ፡ ራፋስን ፡
ራፋስቂስንም ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ከለኪሶ ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ላከ ። ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
መጡ ። በመጡም ፡ ጊዜ ፡ በአጣቢው ፡ እርሻ ፡
መንገድ ፡ በለችው ፡ በላይኛይቱ ፡ ኵሬ ፡ መስኖ ፡
አጠገብ ፡ ቆሙ ። ንጉሡንም ፡ ጠሩ ፡ የቤቱም ፡ ፲፰
አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሐፊ
ውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊውም ፡ የአሳፍ ፡
ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወጡ ።

ራፋስቂስም ፡ አላቸው ፡ — ለሕዝቅያስ ፡ እን ፲፱
ዲህ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩት ፡ — ታላቁ ፡ የአሦር ፡
ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ይህ ፡ የምትታ
መንበት ፡ መተማመኛ ፡ ምንድር ፡ ነው ? የከን
፳ ፡ ፈር ፡ ቃል ፡ ለሰልፍ ፡ ምክርና ፡ ኃይል ፡ እንደ
ሚሆን ፡ ትናገራለህ ፤ አሁንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡
ያመፅኸው ፡ በማን ፡ ተማምነህ ፡ ነው ? እነሆ ፡ ፳፩
በዚህ ፡ በተቀጠቀጠ ፡ በሸምበቆ ፡ በትር ፡ በግ
ብጽ ፡ ትታመናለህ ፤ ሰው ፡ ቢመረኰዘው ፡ ተሰ
ብሮ ፡ በእጁ ፡ ይገባል ፡ ያቄስለውማል ፡ የግብጽ ፡
ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ለሚታመኑበት ፡ ሁሉ ፡ እን
ዲህ ፡ ነው ። እናንተም ፡ — በአምላካችን ፡ በእ ፳፪
ግዚአብሔር ፡ እንታመናለን ፡ ብትሉኝ ፡ ሕዝቅ
ያስ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ — በኢየሩሳ
ሌም ፡ ባለው ፡ በዚህ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ስገዱ ፡
ብሎ ፡ የነበረ ፡ መስገጃዎቹንና ፡ መሠዊያዎ
ቹን ፡ ያስፈረሰ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ? እሁን ፡ እንግ ፳፫
ዲህ ፡ ከጌታዬ ፡ ከአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተወራ
ረድ ፡ የሚቀመጡባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ማግ
ኘት ፡ ቢቻልህ ፡ እኔ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ፈረሶች ፡
እሰጥሃለሁ ። ስለ ፡ ሰረገሎችና ፡ ስለ ፡ ፈረሰ ፳፬
ኞች ፡ በግብጽ ፡ ስትታመን ፡ ከጌታዬ ፡ ባሪያ
ዎች ፡ የሚያንሰውን ፡ የአንዱ ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡
ትቃወም ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻልሃል ? አሁን ፡ ፳፭
በውኑ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡
ስፍራ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቻለሁን ? እግዚአ
ብሔር ፡ — ወደዚች ፡ አገር ፡ ወጥተህ ፡ አጥፋት ፡
አለኝ ።

የኬልቅያስም ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ሳምናስም ፡ ፳፮
ዮአስም ፡ ራፋስቂስን ፡ — እኛ ፡ እንለማለንና ፡
እባክህ ፡ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡ ለባሪያዎችህ ፡ ተና
ገር ፤ በቅጥርም ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ ጆሮ ፡
በእይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ አትናገረን ፡ አሉት ። ራፋ ፳፯
ስቂስ ፡ ግን ፡ — ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እናገር ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንተና ፡ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ልኮኛ
ልን ? ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ሆሳቸውን ፡ ይበሉ ፡
ዘንድ ፡ ሽንታቸውንም ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ በቅ
ጥር ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ አይደ
ለምን ? አላቸው ። ራፋስቂስም ፡ ቆሞ ፡ በታ ፳፰
ላቅ ፡ ድምፅ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ጮኸ ፡ — የታላቁን ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ቃል ፡
ስሙ ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ከእጁ ፡ ፳፱
ያድናችሁ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ሕዝቅያስ ፡
አያታልላችሁ ። ሕዝቅያስም ፡ — እግዚአብ ፴
ሔር ፡ በእርግጥ ፡ ያድነናል ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡
በአሦር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ እንድትታመኑ ፡ አያድርጋችሁ ።
ሕዝቅያስንም ፡ አትስሙ ፤ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ፴፩

እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ከእኔ ፡ ጋር ፡ ታረቁ ፡ ወደ ፡
እኔም ፡ ውጡ ፡ እያንዳንዳችሁም ፡ ከወይናች
ሁና ፡ ከበለሳችሁ ፡ ብሉ ፡ ከጕድጓዳችሁም ፡
ውኃ ፡ ጠጡ ፤ ይህም ፡ መጥቼ ፡ ምድራችሁን ፡
ወደምትመስለው ፡ ምድር ፡ እስልና ፡ የወይን ፡
ጠጅ ፡ እንጀራና ፡ ወይን ፡ ወይራና ፡ ማር ፡ ወዳ
ለበት ፡ ምድር ፡ እስካፈልሳችሁ ፡ ድረስ ፡ በሕ
ይወት ፡ እንድትኖሩ ፡ እንጂ ፡ እንዳትሞቱም ፡ ነው ።
ሕዝቅያስም ፡ — እግዚአብሔር ፡ ያድነናል ፡ ፴፪
ብሎ ፡ ቢያታልላችሁ ፡ አትስሙት ። በውኑ ፡
የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አገሮቻቸውን ፡ ከአሦር ፡
ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነዋቸዋልን ? የሐማትና ፡ ፴፫
የአርፋድ ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ? የሴፈር
ዋይምና ፡ የሄና ፡ የዒዋም ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ ፴፬
አሉ ? ሰማርያን ፡ ከእጄ ፡ አድነዋታልን ? እግ
ዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡
ዘንድ ፡ ከአገሮቹ ፡ አማልክት ፡ ሁሉ ፡ አገሩን ፡
ከእጄ ፡ ያዳነ ፡ ማን ፡ ነው ?

ሕዝቡም ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ አንዳችም ፡ አልመ ፴፮
ለሱለትም ፡ ንጉሡ ፡ እንዳይመልሱለት ፡ አዝዞ ፴፯
ነበርና ። የቤቱ ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡
ኤልያቄም ፡ ጸሐፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐ
ፊም ፡ የአሳፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀድ
ደው ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጡ ፡ የራፋስቂስ
ንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፩
ልብሱን ፡ ቀደደ ፡ ማቅም ፡ ለበሰ ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔርም ፡ ቤት ፡ ገባ ። የቤቱንም ፡ አዛዥ ፡ ፪
ኤልያቄምን ፡ ጸሐፊውንም ፡ ሳምናስን ፡ የካህና
ቱንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡
ነቢዩ ፡ ወደ ፡ አሞጽ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡
ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ። እነርሱም ፡ — ሕዝ ፫
ቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ይህ ፡ ቀን ፡ የመከ
ራና ፡ የተግሣጽ ፡ የዘለፋም ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ልጆች ፡
የሚወለዱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሰአል ፡ ለመውለ
ድም ፡ ኃይል ፡ የለም ። ምናልባት ፡ በሕያው ፡ ፬
አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ የአ
ሦር ፡ ንጉሥ ፡ የላከውን ፡ የራፋስቂስን ፡ ቃል ፡
ሁሉ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ሰማው ፡
ቃል ፡ ይገሥጸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ለቀ ፮
ረው ፡ ቅሬታ ፡ ጸልይ ፡ አሉት ። እንዲሁ ፡ የን
ጉሡ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢሳይ
ያስ ፡ መጡ ። ኢሳይያስም ፡ — ለጌታችሁ ፡ — ፯
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — የአሦር ፡
ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ ስለ ፡ ሰደቡኝ ፡ ስለ ፡ ሰማ
ኸው ፡ ቃል ፡ አትፍራ ። እነሆ ፡ በላዩ ፡ መን ፰
ፈስን ፡ አሰድዳለሁ ፡ ወሬንም ፡ ይሰማል ፡ ወደ ፡
ምድሩም ፡ ይመለሳል ፤ በምድሩም ፡ በሰይፍ ፡
እንዲወድቅ ፡ አደርገዋለሁ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።
የአሦርም ፡ ንጉሥ ፡ ከለኪሶ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ፱
ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ ራፋስቂስ ፡ ተመልሶ ፡ በልብና ፡
ሲዋጋ ፡ አገኘው ። እርሱም ፡ — የኢትዮጵያ ፡
ንጉሥ ፡ ቲርሐቅ ፡ ሊዋጋህ ፡ መጥቶአል ፡ የሚል ፡
ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡
መልእክተኞችን ፡ ላከ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ — ለይ ፲
ሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡
ንገሩት ፡ — ኢየሩሳሌም ፡ በአሦር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡
አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ የምትታመንበት ፡ አምላክህ ፡
አያታልልህ ። እነሆ ፡ የአሦር ፡ ነገሥታት ፡ በም ፲፩
ድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ እንዲትስ ፡ እን
ዳጠፋአቸው ፡ ሰምተሃል ፤ አንተስ ፡ ትድና
ለህን ? አባቶቼ ፡ ያጠፋአቸውን ፡ ጎዛንን ፡ ፲፪
ካራንን ፡ ራፊስን ፡ በተላሳር ፡ የነበሩትንም ፡
የዒድንን ፡ ልጆች ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡
አዳኑአቸውን ? የሐማት ፡ ንጉሥ ፡ የአርፋድ ፡
ንጉሥ ፡ የሴፈርዋይም ፡ ከተማ ፡ ንጉሥ ፡ የሄ
ናና ፡ የዒዋ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ አሉ ?

ሕዝቅያስም ፡ ደብዳቤውን ፡ ከመልእክተ ፲፬
ኞች ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ አነበበው ፤ ሕዝቅያስም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ፊት ፡ ዘረጋው ። ሕዝቅያስም ፡ ወደ ፲፭
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡ — በኪ
ሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ የእስራኤል ፡ አም
ላክ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ብቻህን ፡ የምድር ፡ ነገሥ
ታት ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ ሰማይንና ፡ ምድ
ርን ፡ ፈጥረሃል ። አቤቱ ፡ ጆሮህን ፡ አዘንብ ፲፮
ልና ፡ ስማ ፤ አቤቱ ፡ ዓይንህን ፡ ክፈትና ፡ እይ ፤
በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡
የላከውን ፡ የሰናክሬምን ፡ ቃል ፡ ስማ ። አቤቱ ፡ ፲፯
በእውነት ፡ የአሦር ፡ ነገሥታት ፡ አሕዛብንና ፡
ምድራቸውን ፡ አፍርሰዋል ፡ አማልክቶቻቸ ፲፰
ውንም ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጥለዋል ፤ የእንጨ
ትና ፡ የድንጋይ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ነበሩ ፡
እንጂ ፡ አማልክት ፡ አልነበሩምና ፤ ስለዚህ ፡
አጥፍተዋቸዋል ። እንግዲህም ፡ አምላካችን ፡ ፲፱
አቤቱ ፡ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡
ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡
ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁ ፡ እንድታድነን ፡ አለም
ንሃለሁ ።

የአሞጽም ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፳
ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላከ ፡ — የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ስለ ፡ አሦር ፡
ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የለመንኸ
ውን ፡ ሰምቻለሁ ። እግዚአብሔር ፡ በእርሱ ፡ ፳፩
ላይ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ — ድን
ግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ቀላል ፡ አድርጋሃለች ፡
በንቀትም ፡ ስቃብሃለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡
በላይህ ፡ ራስዋን ፡ ነቅንቃብሃለች ። የተገዳደ ፳፪
ርኸው ፡ የሰደብኸውስ ፡ ማን ፡ ነው ? ቃልህንስ ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኸው ፡ ዓይንህንም ፡ ወደ ፡
ላይ ፡ ያነሣኸው ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ነው ? በእስራ
ኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ነው ። አንተስ ፡ — በሰረ ፳፫
ገላዩ ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ተራሮች ፡ ከፍታ ፡ ወደ ፡
ሊባኖስ ፡ ጥግ ፡ ላይ ፡ ወጥቻለሁ ፡ ረጃጅሞቹንም ፡
ዝግባዎች ፡ የተመረጡትንም ፡ ጥዶች ፡ አቈር

ጣለው ÷ ወደ ፡ አገሩም ፡ ዳር፫ና ፡ ወደ ፡ ቀርሜ
፳፩፡ ሎስ ፡ ዳር ፡ እገባለሁ ። ቈፈርሁም ÷ እንግዳ
ውንም ፡ ውኃ ፡ ጠጣሁ ፤ የተገደበውንም ፡
ውኃ ፡ ሁሉ ፡ በእግሬ ፡ ጫማ ፡ አደር፫ቅለሁ ፡
ብለህ ፡ በመልእክተኞችህ ፡ እጅ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ላይ ፡ ተገዳደርህ ።
፳፪፡ እኔ ፡ ዋንቴን ፡ እንደ ፡ ሠራሁት ÷ ቀድሞ
ውንም ፡ እንዳደረግሁት ፡ አልሰማህምን ? አሁ
ንም ፡ የተመሸገ፡ትን ፡ ከተሞች ፡ የፍርስራሽ ፡
ክምር ፡ እስክሆኑ ፡ ድረስ ፡ እንድታፈርስ ፡ አደረ
፳፭፡ ግሁህ ። ስለዚህም ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ሰዎች ፡
እጃቸው ፡ ዝሎአል ÷ ደንግጠውም ፡ ታውከ
ዋል ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሣር ፡ እንደ ፡ ለም
ለምም ፡ ቡቃያ ÷ በሰገነትም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡
ሣር ÷ ሰይሽ ፡ ቀማ ፡ እንደ ፡ መታውም ፡ እህል ፡
፳፮፡ ሆነዋል ። እኔ ፡ ግን ፡ መቀመጫህንና ፡ መው
ጫህንም ፡ መግቢያህንም ÷ በእኔም ፡ ላይ ፡ የተ
፳፯፡ ቈጣኸውን ፡ ቍጣ ፡ አውቄአለሁ ። ቍጣህና ፡
ትዕቢትህ ፡ ወደ ፡ ጆሮዬ ፡ ደርሶአልና ፡ ስለዚህ ፡
ስናጋዥን ፡ በአፍንጫህ ÷ ልጓሜንም ፡ በከንፈ
ርህ ፡ አደርጋለሁ ÷ በመጣህበትም ፡ መንገድ ፡
እመልስሃለሁ ።
፳፰፡ ይህም ፡ ምልክት ፡ ይሆንሃል ፤ በዚህ ፡ ዓመት ፡
የገበውን ÷ በሁለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከገበው ፡
የበቀለውን ፡ ትበላላችሁ ፤ በሦስተኛውም ፡
ዓመት ፡ ትዘራላችሁ ÷ ታጭዱማላችሁ ÷ ወይን
ንም ፡ ትተክላላችሁ ÷ ፍሬውንም ፡ ትበላላችሁ ።
፳፱፡ ያመለጠው ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ሥሩን ፡
ወደ ፡ ታች ፡ ይሰድዳል ÷ ወደ ፡ ላይም ፡ ያፈ
፴፩፡ራል ። ከኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ ከጽዮንም ፡
ተራራ ፡ ያመለጡት ፡ ይወጣሉና ፤ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅንዓት ፡ ይህን ፡ ያደር
፴፪፡ጋል ። ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አሦር ፡
ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደዚች ፡ ከተማ ፡
አይመጣም ÷ ፍላጻንም ፡ አይወረውርበትም ÷
በጋሻም ፡ አይመጣባትም ÷ የአፈርንም ፡ ድል
፴፫፡ድል ፡ አይደለድልባትም ። በመጣበት ፡ መን
ገድ ፡ በዚያው ፡ ይመለሳል ÷ ወደዚህችም ፡
ከተማ ፡ አይመጣም ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፴፬፡ስለ ፡ እኔም ÷ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡
ይህችን ፡ ከተማ ፡ አድናት ፡ ዘንድ ፡ እጋርዳታ
ለሁ ።
፴፭፡ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡
መልአክ ፡ ወጣ ÷ ከአሦራውያንም ፡ ሰፈር ፡
መቶ ፡ ሰማንያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ገደለ ፤ ማለ
ዳም ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ÷ እነሆ ÷ ሁሉ ፡ በድኖች ፡
፴፮፡ነበሩ ። የአሦርም ፡ ንጉሥ ፡ ስናክሬም ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ሄደ ÷ ተመልሶም ፡ በነነዌ ፡ ተቀመጠ ።
፴፯፡ በአምላኩም ፡ በናሰራክ ፡ ቤት ፡ ሲሰግድ ፡
ልጆቹ ፡ አደራሜሌክና ፡ ሳራ-ሶር ፡ በሰይፍ ፡ ገደ
ሉት ፡ ወደ ፡ አራራትም ፡ አገር ፡ ኰበለሉ ።
ልጁም ፡ አስራዶን ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡
ድረስ ፡ ታመመ ። ነቢዩም ፡ የአሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳ
ይያስ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥቶ ፡ — እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ትሞታለህ ፡ እንጂ ፡ በሕይ
ወት ፡ አትኖርምና ፡ ቤትህን ፡ አስተካክል ፡
አለው ። ፪ፋቱንም ፡ ወደ ፡ ግድግዳው ፡ መልሶ ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፡ —
፫አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ በእውነትና ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡
እንደ ፡ ሄድሁ ÷ ደስ ፡ የሚያሰኝህንም ፡ እን
ዳደረግሁ ፡ ታስብ ፡ ዘንድ ፡ አለምንሃለሁ ። ሕዝ
ቅያስም ፡ እጅግ ፡ አደር፫ኃ ፡ አለቀሰ ። ፬ኢሳይያ
ስም ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡ ከተማ ፡ አደባባይ ፡
ሳይደርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ መጣለት ፦ ፭ተመልሰህ ፡ የሕዝቤን ፡
አለቃ ፡ ሕዝቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የአባ
ትህ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፦ ጸሎትህን ፡ ሰምቻለሁ ÷ እን
ባህንም ፡ አይቻለሁ ፤ እነሆ ÷ እፈውስሃለሁ ፡
በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ትወጣለህ ። ፮በዕድሜህም ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡
አምስት ፡ ዓመት ፡ እጨምራለሁ ፡ አንተንና ፡
ይህችን ፡ ከተማ ፡ ከአሦር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ እታ
ደጋለሁ ፡ ስለ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡
ዳዊት ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ እጋርዳታለሁ ። ፯ኢሳ
ይያስም ፦ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አምጡልኝ ፡
አለ ፡ አምጥተውም ፡ በእብጩ ፡ ላይ ፡ አደረጉ
ለት ÷ እርሱም ፡ ተፈወሰ ።
፰ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያስን ፦ እግዚአብሔር ፡
እንዲፈውሰኝ ፡ እኔስ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንድወጣ ፡ ምልክቱ ፡
ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ኢሳይያስም ፦ እግ
፱ዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽ
መው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡
ይህንልህ ፡ ጥላው ፡ አሥር ፡ ደረጃ ፡
ወደ ፡ ፊት ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ አሥር ፡
ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ትወድዳ
ለህን ? አለ ። ፲ሕዝቅያስም ፦ ጥላው ፡ አሥር ፡
ደረጃ ፡ ቢጨምር ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡
አይሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥላው ፡ አሥር ፡ ደረጃ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ይመለስ ፡ አለው ። ፲፩ነቢዩም ፡ ኢሳ
ይያስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ፤ ጥላው
ንም ፡ በአካዝ ፡ የጥላ ፡ ስፍራ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ በወ
ረደበት ፡ መንገድ ፡ አሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
መለሰው ።
፲፪በዚያም ፡ ወራት ፡ የበቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የባል
ዳን ፡ ልጅ ፡ መሮዳክ ፡ ባልዳን ፡ ሕዝቅያስ ፡ እንደ ፡
ታመመ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ ደብዳቤና ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላከ ። ፲፫ሕዝቅያስም ፡
ደስ ፡ አለው ÷ ግምጃ ፡ ቤቱንም ፡ ሁሉ ÷ ብሩ
ንና ፡ ወርቁንም ÷ ቅመሙንና ፡ የከበረውንም ፡

ዘይት ÷ መሣሪያም ፡ ያለበትን ፡ ቤት ÷ በቤተ ፡
መዛግብቱም ፡ የተገኘውን ፡ ሁሉ ፡ አሳያቸው ፤
በቤቱና ፡ በግዛቱ ፡ ሁሉ ፡ ካለው ፡ ሕዝቅያስ ፡
፲፬፡ያላሳያቸው ፡ የለም ። ነቢዩም ፡ ኢሳይያስ ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጥቶ ፡ —
እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ አሉ ? ከወዴትስ ፡
መጡልህ ? አለው ። ሕዝቅያስም ፡ — ከሩቅ ፡
፲፭፡አገር ፡ ከባቢሎን ፡ መጡ ፡ አለው ። እርሱም ፡ —
ቤቴ፡ን ፡ ያዩት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ፤ ሕዝ
ቅያስም ፡ — በቤቴ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ አይተዋል ፤
በቤተ ፡ መዛግብቴ ፡ ካለው ፡ ያላሳየኋቸው ፡
የለም ፡ አለው ።
፲፮ኢሳይያስም ፡ ሕዝቅያስን ፡ — የእግዚአብሔ
፲፯ርን ፡ ቃል ፡ ስማ ። እነሆ ÷ በቤትህ ፡ ያለው ፡
ሁሉ ÷ አባቶችህም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያከ
ማቹት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ በቢሎን ፡ የሚፈልስበት ፡
ወራት ፡ ይመጣል ፤ ምንም ፡ አይቀርም ÷ ይላል ፡
፲፰እግዚአብሔር ። ከአንተም ፡ ከሚወጡት ፡ ከም
ትወልዳቸው ፡ ልጆችህ ፡ ማርከው ፡ ይወስዳሉ ፤
በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጃንደረ
፲፱ባቦች ፡ ይሆናሉ ፡ አለው ። ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያ
ስን ፦ የተናገርኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
መልካም ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞም ፦ በዘ
መኔ ፡ ሰላምና ፡ እውነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
፳መልካም ፡ አይደለምን ? አለ ። የቀረውም ፡
የሕዝቅያስ ፡ ነገር ÷ ጭከናውም ፡ ሁሉ ÷ ኩሬ
ውንና ፡ መስኖውንም ፡ እንደ ፡ ሠራ ÷ ውኃው
ንም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ እንዳመጣ ÷ በይሁዳ ፡
ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደ
፳፩ለምን ? ሕዝቅያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀ
ላፋ ፤ ልጁም ፡ ምናሴ ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩፡ ምናሴም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የአ
ሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳ
ሌምም ፡ አምሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ የእ
፪ናቱ ፡ ስም ፡ ሐፍሲባ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔርም ፡
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳወጣቸው ፡
እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡
፫ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ። ፫አባቱም ፡ ሕዝቅ
ያስ ፡ ያፈረሰቸውን ፡ የከረብታውን ፡ መስገጃ
ዎች ፡ መልሶ ፡ ሠራ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡
አክዓብ ፡ እንዳደረገው ፡ ለበኣል ፡ መሠዊያ ፡
ሠራ ÷ የማምለክያ ፡ ዐፀድንም ፡ ተከለ ÷ ለሰ
ማይም ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ሰገደ ፡ አመለካቸ
፬ውም ። ፬እግዚአብሔርም ፦ ስሜን ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ አኖራለሁ ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡
፭ቤት ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ። ፭በእግዚአብሔ
ርም ፡ ቤት ፡ በሁለቱ ፡ ወለሎች ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡
፮ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ። ፮ልጁ
ንም ፡ በእሳት ፡ አሳለፈ ÷ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ ሆነ ÷
አስማትም ፡ አደረገ ÷ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡
ጠንቋዮችንም ፡ ሰበሰበ ፤ ያስቈጣውም ፡ ዘንድ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደ
ረገ ። ፯እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጁ ፡ ለሰ
፯ሎሞን ፦ በዚህ ፡ ቤት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡
ሁሉ ፡ በመረጥኋት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስሜን ፡
ለዘላለም ፡ እኖራለሁ ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ሁሉ ÷
፰ባሪያዬም ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛቸውን ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡
ቢያደርጉ ፡ ቢጠብቁም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ከሰ
ጠኋት ፡ ምድር ፡ የእስራኤልን ፡ እግር ፡ እንደ ፡
ገና ፡ አላቅበዘብዝም ፡ ባለው ፡ ቤት ፡ የሠራ
ውን ፡ የማምለክያ ፡ በፀድን ፡ የተቀረጸውን ፡
ምስል ፡ አቆመ ። ፱ነገር ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፤ እግ
፱ዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡
ከጠፋቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ይሠሩ ፡
ዘንድ ፡ ምናሴ ፡ አሳታቸው ።
፲እግዚአብሔርም ፡ በባሪያዎቹ ፡ በነቢያት ፡
፲፩እጅ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፦ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ምናሴ ፡ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ አድርጎአልና ÷ ከፊ
ቱም ፡ የነበሩ ፡ አሞራውያን ፡ ከሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶአልና ÷ ይሁዳንም ፡
ደግሞ ፡ በጣዖታቱ ፡ አስቶአልና ፡ ስለዚህ ፡ የእ
፲፪ስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ እነሆ ÷ የሚሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ሁለቱ ፡
ጆሮቹ ፡ ጭው ፡ የሚያደርግ፡ክፉ ፡ ነገርን ፡ በኢየ
፲፫ሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ አመጣለሁ ። የሰማር ፡
ያንም ፡ገመድ ፡የአክዓብንም ፡ቤት ፡ቱንቢ ፡በኢ
የሩሳሌም ፡ ላይ ፡ እዘረጋለሁ ፡ ሰውም ፡ ወጭ
ቱን ፡ እንዲወለውል ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ወልውዬ ፡
እገለብጣታለሁ ። የርስቴንም ፡ ቅሬታ ፡ እጥላ
፲፬ለሁ ÷ በጠላቶቻቸውም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸ
ዋለሁ ÷ ለጠላቶቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ምርኮና ፡ ብዝ
በዛ ፡ ይሆናሉ ፤ አባቶቻቸው ፡ ከግብጽ ፡ ከወጡ ፡
፲፭ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ሠር
ተዋልና ÷ አስቈጥተውኝማልና ።
፲፮ደግሞም ፡ ምናሴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ክፉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳን ፡ ከሳተበት ፡ ኃጢ
አት ፡ ሌላ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡
እስኪሞላት ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ንጹሕ ፡
ደም ፡ አፈሰሰ ። ፲፯የምናሴም ፡ የቀረው ፡ ነገርና ፡
የሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ÷ ያደረገውም ፡ ኃጢ
አት ÷ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡
የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ምናሴም ፡ ከአባቶቹ ፡
፲፰ጋር ፡ አንቀላፋ ÷ በቤቱም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡
በዖዛ ፡ አትክልት ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አሞጽ ፡
በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።
፲፱አሞጽም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌ
ምም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዮ
ጥባ ፡ ሰው ፡ የሐሩስ ፡ ልጅ ፡ ሜሰላሜ ፡ ነበረች ።
፳አባቱም ፡ ምናሴ ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ክፉ ፡ ሠራ ። ፳፩አባቱም ፡ በሄደበት ፡ መን
፳፪ገድ ፡ ሁሉ ፡ ሄደ ÷ አባቱም ፡ ያመለካቸውን ፡
ጣዖታት ፡ አመለከ ፡ ሰገደላቸውም ። ፳፪የአባቶ
ቹንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተወ ÷ በእ
ግዚአብሔርም ፡ መንገድ ፡ አልሄደም ። ፳፫የአሞ
፳፫ጽም ፡ባሪያዎች ፡አሴሩበት ፡ንጉሡንም ፡በቤቱ ፡

፳፪ ውስጥ ፣ ገደሉት ÷ የአገሩ ፣ ሕዝብ ፣ ግን ፣ በን
ጉሡ ፣ በአሞጽ ፡ ላይ ፡ ያሴሩበትን ፡ ሁሉ ፣ ገደሉ ፤
የአገሩም ፣ ሕዝብ ፣ ልጁን ፣ ኢዮስያስን ፣ በአ
፳፫ ርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ። የአሞጽም ፡ የቀረው ፡
ነገርና ፡ የሠራው ፡ ሥራ ÷ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡
፳፬ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በያ
ዛም ፡ አትክልት ፡ ባለው ፡ በመቃብሩ ፡ ተቀበረ ፤
ልጁም ፡ ኢዮስያስ ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ ኢዮስያስም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የስ
ምንት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፣ በኢየሩሳሌምም ፡
ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ክባ
ሱሮት ፡ የሆነ ፣ የአዳያ ፡ ልጅ ፡ ይዲዳ ፡ ነበረች ።
፪ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቀን ፡ ነገርን ፡ ሕዶ
ረገ ÷ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡
ሄደ ÷ ቀኝም ፡ ግራም ፡ አላለም ።
፫ በንጉሡም ፡ በኢዮስያስ ፡ በአሥራ ፡ ስምን
ተኛው ፡ ዓመት ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፣ ንጉሡ ፡
ጸሐፊው ፣ የሜሰላሚን ፡ ልጅ ፡ የኤዚልያስን ፡
ልጅ ፡ ሳፋንን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
፬ ላከው ÷ እንዲህም ፡ አለው ፡— የመቅደሱ ፡
በረኞች ፡ ከሕዝቡ ፡ የሰበሰቡትን ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ቤት ፡ የገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ይደምር ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ኬልቅያስ ፡
፭ ሂድ ። በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ላሉት ፡ ሠራ
ተኞች ፡ አለቆች ፡ ይስጡት ፤ እነርሱም ፡ የተ
ናደውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለሚጠግ
፮ ኑት ፡ ሠራተኞች ÷ ለአናጢዎችና ፡ ለጠራቢ
ዎች ÷ ለድንጋይም ፡ ወቃሪዎች ÷ መቅደሱ
ንም ፡ ለመጠገን ፡ እንጨትንና ፡ የተወቀረውን ፡
፯ ድንጋይ ፡ ለሚገዙ ፡ ይክፈሉት ። ነገር ፡ ግን ፡
እነርሱ ፡ የታመኑ ፡ ነበሩና ፡ በእጃቸው ፡ ስለ ፡
ተሰጠ ፡ አያቈጣጠሩአቸውም ፡ ነበር ።
፰ ካህኑም ፡ ኬልቅያስ ፡ ጸሐፊውን ፡ ሳፋንን ፡—
የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
አግኝቻለሁ ፡ አለው ፡ ኬልቅያስም ፡ መጽሐፉን ፡
ለሳፋን ፡ ሰጠው ÷ እርሱም ፡ አነበበው ።
፱ ጸሐፊውም ፡ ሳፋን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ ÷
ለንጉሡም ፡— በመቅደሱ ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡
ባሪያዎችህ ፡ አፈሰሱት ÷ በእግዚአብሔርም ፡
ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ለተሾሙት ፡ አለቆች ፡
፲ ሰጡት ፡ ብሎ ፡ አወራለት ። ጸሐፊውም ፡
ሳፋን ፡ ለንጉሡ ፡ ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ሰጥቶኛል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሳፋንም ፡
፲፩ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አነበበው ። ንጉሡም ፡ የሕጉን ፡
መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ።
፲፪ ንጉሡም ፡ ካህኑን ፡ ኬልቅያስን ፡ የሳፋንንም ፡
ልጅ ፡ አኪቃምን ÷ የሚክያስንም ፡ ልጅ ፡ ዓክ
በርን ÷ ጸሐፊውንም ፡ ሳፋንን ÷ የንጉሡንም ፡
፲፫ ብላቴና ፡ ዓሳያን ፡— አባቶቻችን ፡ በእርስዋ ፡
የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ የዚህችን ፡
መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ስላልሰሙ ፡ በላያችን ፡ የነ
ደደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፡
ሄዳችሁ ፡ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ይሁ
ዳም ፡ ሁሉ ፡ የዚህችን ፡ የተገኘችውን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡
አዘዛቸው ።
፲፬ እንዲሁም ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስና ፡ አኪቃም ፡
ዓክቦርም ፡ ሳፋንና ፡ ዓሳያም ፡ ወደ ፡ ልብስ ፡
ጠባቂው ፡ ወደ ፡ ሐስራ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቲቁዋ ፡
ልጅ ፡ ወደ ፡ ሴሌም ፡ ሚስት ፡ ወደ ፡ ነቢይቱ ፡
ወደ ፡ ሕልዳና ፡ ሄዱ ፤ እርስዋም ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ፤ ከእር
ስዋም ፡ ጋር ፡ ተነጋገሩ ። እርስዋም ፡ አለቻ
፲፭ ቸው ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— ወደ ፡ እኔ ፡ ለላካችሁ ፡ ሰው ፡
እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩት ፡— እግዚአብሔር ፡
፲፮ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
እንዳነበበው ፡ እንደ ፡ መጽሐፉ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡
በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ አመጣለሁ ። በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ትተውኛልና ÷ ለሌሎችም ፡
አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፡ ቍጣዬ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡
ላይ ፡ ይነድዳል ÷ አይጠፋምም ። እግዚአብ
፲፰ ሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ለላካችሁ ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ግን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ስለ ፡ ሰማ
ኸው ፡ ቃል ÷ ልብህ ፡ ገር ፡ ሆኖአልና ÷ እነር
፲፱ ሱም ፡ ለድንቅና ፡ ለመርገም ፡ እንዲሆኑ ፡ በዚህ ፡
ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ የተናገርሁትን ፡
ሰምተህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተዋርደሃልና ÷
ልብስህን ፡ ቀድደሃልና ÷ በፊቴም ፡ አልቅሰሃ
ልና ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሰምቼሃለሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብ
፳ ሔር ። ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አባቶችህ ፡
እሰበስብሃለሁ ÷ በሰላም ፡ ወደ ፡ መቃብርህ ፡
ትሰበሰባለህ ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የማመ
ጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ዓይኖችህ ፡ አያዩም ።
ይህንም ፡ ለንጉሡ ፡ አወሩለት ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩ ንጉሡም ፡ ላከ ፤ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌም
ንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰባቸው ። ንጉ
፪ ሡም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጣ ፤ ከእ
ርሱም ፡ ጋር ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ÷ በኢየሩ
ሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ካህናቱና ፡ ነቢያ
ቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ከታናሽ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡
ድረስ ፡ ወጡ ፤ በእግዚአብ
ሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡
መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በጆሮአቸው ፡ አነበበ ።
፫ ንጉሡም ፡ በዓምዱ ፡ ወርቁ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ተከትሎ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ÷
ትእዛዙንና ፡ ምስክሩንም ፡ ሥርዓቱንም ፡ በፍ
ጹም ፡ ልቡና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሱ ፡ ይጠብቅ ፡
ዘንድ ÷ በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡
የቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፤ ሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገቡ ።

፬ ንጉሡም ፡ የካህናቱን ፡ አለቃ ፡ ኬልቅያስን ፡
በሁለተኛውም ፡ መዣርግ ፡ ያሉትን ፡ ካህናትን ፡
በረኞቹንም ፡ ለበኣልና ፡ ለማምለኪያ ፡ ሀፀድ ፡
ለሰማያትም ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ የተሠሩትን ፡ ሰቃ
ዮች ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ያወጡ ፡
ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ውጭ ፡
በቄድሮን ፡ ሜዳ ፡ አቃጠላቸው ÷ አመዱንም ፡
፭ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወሰደው ። የይሁዳ ፡ ነገሥታ
ትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተሞች ፡ በነበሩት ፡ በከረብ
ታው ፡ መስገጃዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡
ባሉ ፡ መስገጃዎች ፡ ያጥኑ ፡ ዘንድ ፡ ያሾሩአቸ
ውን ፡ የጣዖቱን ፡ ካህናት ÷ ለበኣልና ፡ ለፀሐይ ፡
ለጨረቃና ፡ ለነዋክብት ፡ ለሰማያም ፡ ሠራዊት ፡
፮ ሁሉ ፡ ያጥኑ ፡ የነበሩትንም ፡ አስወገደ ። የማም
ለኪያ ፡ ሀፀድንም ፡ ጣዖት ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ወደ ፡ ቄድ
ሮን ፡ ፈፋ ፡ አወጣው ፡ በቄድሮንም ፡ ፈፋ ፡ አጠ
ገብ ፡ አቃጠለው ÷ አድቅቆም ፡ ትቢያ ፡ አደረ
ገው ÷ ትቢያውንም ፡ በሕዝብ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡
፯ ጣለው ። ሴቶቹም ፡ ለማምለኪያ ፡ ሀፀድ ፡ መጋ
ረጃ ፡ ይፈትሉባቸው ፡ የነበሩትን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የሰዶማውያንን ፡
፰ ቤቶች ፡ አፈረሰ ። ካህናቱንም ፡ ሁሉ ፡ ከይ
ሁዳ ፡ ከተሞች ፡ አወጣቸው ፡ ከጌባም ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ድረስ ፡ ከህናት ፡ ያጥኑበት ፡
የነበረውን ፡ የኮረብታ ፡ መስገጃ ፡ ሁሉ ፡ ርኵስ ፡
አደረገው ።በከተማይቱም ፡ በር ፡ በግራ ፡ በኩል ፡
በነበረው ፡ በከተማይቱ ፡ ሹም ፡ በኢያሱ ፡ በር ፡
መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ የነበሩትን ፡ የበሮቹን ፡ መስ
፱ ገጃዎች ፡ አፈረሰ ። የኮረብታው ፡ መስገጃዎች ፡
ካህናት ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ አይመጡም ፡ ነበር ፡
ብቻ ፡ በወንድሞቻቸው ፡ መካከል ፡ ቂጣ ፡ እን
፲ ጀራ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ። ማንም ፡ ሰው ፡ ወንድ ፡
ልጁን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ለሞሎክ ፡ በእ
ሳት ፡ እንዳያሳልፍ ፡ በሄኖም ፡ ልጆች ፡ ሸለቆ ፡
፲፩ የነበረውን ፡ ቶፌትን ፡ ርኩስ ፡ አደረገው ። የይ
ሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ በከተማው ፡ አቅራቢያ ፡
በአዜርሙሬሌክ ፡ ብኔንደረበው ፡ በናታንሜሌክ ፡ መኖ
ሪያ ፡ አጠገብ ፡ ለፀሐይ ፡ የሰጡትን ፡ ፈረሶች ፡
አስወገዱ ፤ የፀሐይንም ፡ ሰረገሎች ፡ በእሳት ፡
፲፪ አቃጠለ ። የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩትን ፡
በአካዝ ፡ ቤት ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መሠ
ዊያዎች ÷ ምናሴም ፡ ያሠራውን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቤት ፡ ብሁለቱ ፡ መለሎች ፡ ላይ ፡ የነበሩ
ትን ፡ መሠዊያዎች ፡ ንጉሡ ፡ አስፈረሳቸው ÷
አደቀቃቸውም ÷ ትቢያቸውንም ፡ በቄድሮን ፡
፲፫ ፈፋ ፡ ጣለ ። በኢየሩሳሌምም ፡ ፊት ፡ ሰፊት ፡
በርኵሰት ፡ ተራራ ፡ ቀኝ ፡ የነበሩትን ÷ የእስራ
፲፬ ኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ለሲዶናውያን ፡ ርኵ
ሰት ፡ ለአስታሮት ፡ ለሞዓብም ፡ ርኵሰት ፡ ለካ
ሞሽ ፡ ለአሞንም ፡ ልጆች ፡ ርኵሰት ፡ ያሠሣል
ከም ፡ ያሠራቸውን ፡ መስገጃዎች ፡ ንጉሡ ፡
ርኩስ ፡ አደረገ ። ሐውልቶቹንም ፡ ሁሉ ፡ አደ
፲፭ ቀቀ ÷ የማምለኪያ ፡ ዐፀዶቹንም ፡ ቈረጠ ÷ በስ
ፍራቸውም ፡ የሙታንን ፡ አጥንት ፡ ሞላበት ።
ደግሞም ፡ በቤቴል ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ÷
፲፮ እስራኤልንም ፡ ያሳተ ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮር
ብዓም ፡ ያሠራውን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃ ÷
ይህን ፡ መሠዊያና ፡ መስገጃ ፡ አፈረሰ ፡ ድንጋ
ዮቹንም ፡ ሰባበረ ÷ አድቅቆም ፡ ትቢያ ፡ አደረ
ገው ÷ የማምለኪያ ፡ ዐፀዱንም ፡ አቃጠለው ።
፲፯ ኢዮስያስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በተራራው ፡ የነበ
ሩትን ፡ መቃብሮች ፡ አየ ፡ ኢዮርብዓምም ፡ በበ
ዓል ፡ ጊዜ ፡ በመሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ሲቆም ፡ እን
ዲህን ፡ ነገሮች ፡ የተነበ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ሰው ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ቃል ፡ ያከ ፡ ከመቃብሮቹ ፡ አጥንቶቹን ፡
አስወጣ ÷ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አቃጠላቸው ፡
አረከሰውም ። ዘወርም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ተናገ
ረው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መቃብር ፡
ዓይናቸውን ፡ አቅንቶ ፡— ያ ፡ የማየው ፡ የመታሰ
፲፰ ቢያ ፡ ምልክት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። የዘያ
ችም ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡— ከይሁዳ ፡ ወጥቶ ፡ በቤ
ቴል ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያደረገውን ፡
ነገር ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡
መቃብር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። እርሱም ፡—
፲፱ ተዉት ÷ ማንም ፡ አጥንቱን ፡ አያንቀሳቅሰው ፡
አለ ፤ እነርሱም ፡ ከሰማርያ ፡ ከወጣው ፡ ከነቢዩ ፡
አጥንት ፡ ጋር ፡ አጥንቱን ፡ ተዉ ። ፱በሰማርያም ፡
ከተሞች ፡ የነበሩትን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስቈ
ጡት ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ የሠሩ
ትን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ኢዮስያስ ፡
አስወገዳቸው ÷ በቤቴልም ፡ እንዳደረገው ፡ ነገር ፡
፳ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገባቸው ። ፹በዚያም ፡ የነበ
ሩትን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ካህናት ፡
ሁሉ ፡ በመሠዊያዎቹ ፡ ላይ ፡ ገደላቸው ÷ የሰዎ
ቹንም ፡ አጥንት ፡ በመሠዊያዎቹ ፡ ላይ ፡ አቃ
፳፩ ጠለ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተመለሰ ።
ንጉሡም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡— በዚህ ፡ በቃል ፡
፳፪ ኪዳን ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ለአምላካ
ችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡
አዘዘቸው ። ፰እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ በእስ
፳፫ ራኤል ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ከነበሩ ፡ ከመሳፍንት ፡
ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥ
ታት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ አልተፈጸመም ። ነገር ፡
፳፬ ግን ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ በአሥራ ፡
ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ፋሲካ ፡ በኢየሩሳ
ሌም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተፈጸመ ። ፰
ደግሞም ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ በእግዚአብ
፳፭ ሔር ፡ ቤት ፡ ባገኘው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡
የሕጉን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ÷ መናፍስት ፡ ጠሪ
ዎቹንና ፡ ጠንቋዮቹን ፡ ተራፊምንና ፡ ጣዖታት
ንም ፡ በይሁዳ ፡ አገርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተገ
ኘውን ፡ ርኵሰት ፡ ሁሉ ፡ ኢዮስያስ ፡ አስወገደ ።
ሕንደ ፡ ሙሴም ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡
፳፮ በፍጹምም ፡ ነፍሱ ፡ በፍጹምም ፡ ኀይሉ ፡ ወደ ፡

እግዚአብሔርም ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ከእርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ አልነበረም ፤ እንደ ፡ እርሱም ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ አልተነሣም ።

፳፭ ነገር ፡ ግን ፡ ምናሴ ፡ ስላስቈጣው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ከነደደው ፡ ከታ
፳፮ ላቱ ፡ ቍጣው ፡ ትኵሳት ፡ አልተመለሰም ። እግዚአብሔርም ፡— አስራኤል ፡ እንዳራቅሁት ፡ ይሁዳን ፡ ከፊቴ ፡ አርቀዋለሁ ፤ ይህችንም ፡ የመረጥኋትን ፡ ከተማ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡— ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይሆናል ፡ ያልሁትን ፡ ቤት ፡ እጥላለሁ ፡ አለ ።

፳፯ የቀረውም ፡ የኢዮስያስ ፡ ነገር ፡ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽ
፳፰ ሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? በእርሱም ፡ ዘመን ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ኒካው ፡ ከአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ሊጋጠም ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ወጣ ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮስያስ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሊጋጠም ፡ ወጣ ፤ ፈርዖንም ፡ በተገ
፳፱ ናኘው ፡ ጊዜ ፡ በመጊዶ ፡ ገደለው ። ከሞተም ፡ በኋላ ፡ ባሪያዎቹ ፡ በሰረገላው ፡ አድርገው ፡ ከመጊዶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አመጡት ÷ በመቃብሩም ፡ ቀበሩት ። የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክስን ፡ ወሰዱት ÷ ቀብተውም ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ።

፴ኛ፩ ኢዮአክስም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ አሚጣል ፡ ትባል ፡ ነበር ÷ እርስዋም ፡ የልብና ፡ ሰው
፴፪ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። አባቶቹም ፡ እንዳደረጉ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።
፴፫ በኢየሩሳሌምም ፡ እንዳይገሥሥ ፡ ፈርዖን ፡ ኒካው ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በሪብላ ፡ አሰረው ፤ በምድሩም ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ፈሰሴ
፴፬ ፡ ጣለበት ። ፈርዖን ፡ ኒካውም ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄምን ፡ በእባቱ ፡ በኢዮስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠ ÷ ስሙንም ፡ ኢዮአቄም ፡ ብሎ ፡ ለወጠው ። ኢዮአክስንም ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አፈለሰው ፤ በዚያም ፡ ሞተ ። ኢዮአቄምም ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ ለፈርዖን ፡ ሰጠው ፤ እንደ ፡ ፈርዖንም ፡ ትእዛዝ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ምድሩን ፡ አስገበረ ፤ ለፈርዖን ፡ ኒካው ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ግምጋሜው ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አስከፈለ ።

፴፮ ኢዮአቄምም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ዘቢዳ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ እርስዋም ፡
፴፯ የሩማ ፡ ሰው ፡ የፈዳያ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። አባቶቹም ፡ እንዳደረጉ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

በእርሱም ፡ ዘመን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡ ፩ ከደነፆር ፡ ወጣ ÷ ኢዮአቄምም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተገዛለት ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ ዐመፀበት ። እግዚአብሔርም ፡ የከለዳውያንንና ፪ ፡ የሶርያውያንን ፡ የሞዓብያንንም ፡ የአሞንንም ፡ ልጆች ፡ አደጋ ፡ ጣሮች ፡ ሰደደበት ፤ በባሪያዎቹ ፡ በነቢያት ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ በይ
ሁዳ ፡ ላይ ፡ ሰደዳቸው ። ምናሴ ፡ ስላደረገው ፡ ፫ ፡ ፬ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ስላፈሰሰውም ፡ ንጹሕ ፡ ደም ÷ ኢየሩሳሌምንም ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ስለ ፡ ሞላ ፡ ጌታ ፡ ያስወግዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሆነ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይራራ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

፭ የቀረውም ፡ የኢዮአቄም ፡ ነገር ÷ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ÷ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ኢዮአቄ ፮ ምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋር ፡ አንቀላፋ ፤ ልጁም ፡ ዮአኪን ፤ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። የባቢሎ ፯ ንም ፡ ንጉሥ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ወስዶ ፡ ነበርና ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ከአገሩ ፡ አልወጣም ።

፰ ዮአኪን ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የአ ሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢ የሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ኔስታ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ እርስዋም ፡ የኢየሩሳ ሌም ፡ ሰው ፡ የኤልናታን ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። አባቱም ፡ እንዳደረገ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፩ ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

፲ በዚያም ፡ ወራት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡ ፩ ከደነፆር ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ÷ ከተማይቱም ፡ ተከበበች ። ፲፩ ባሪያዎቹም ፡ በከበቡ ፲፪ አት ፡ ጊዜ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ወጣ ። የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪንና ፡ እናቱ ÷ ባሪያዎቹም ÷ አለቆቹም ÷ ጃንደረቦቹም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወጡ ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ያዘው ። የእግዚብሔርም ፡ ቤት ፡ መዛ ፲፫ ግብትን ፡ ሁሉ ፡ የንጉሡም ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ ከዚያ ፡ አወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ የሠራውን ፡ የወር ቁን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ሰባበረ ። ፲፬ ኢየሩሳሌምንም ፡ ሁሉ ÷ አለቆቹንም ፡ ሁሉ ÷ ጽኑዓን ፡ ኃያላኑንም ፡ ሁሉ ÷ ጠራቢዎቹንም ፡ ሁሉ ÷ ብረት ፡ ሠራተኞቹን ፡ ሁሉ ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ምርኮኞች ፡ አፈለሰ ፤ ከድሆች ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አልቀረም ። ፲፭ ዮአኪንንም ፡ ወደ ፡ ባቢ

ሎን ፡ አፈለሰ ፤ የንጉሡንም ፡ እናት ÷ የንጉሡ ፡ ሚስቶች ÷ ጃንደረቦቹንም ÷ የአገሩንም ፡ ታላላቆች ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ፲፮ ማረከ ። የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ብርቱዎቹንና ፡ ሰልፍ ፡ የሚችሉትን ፡ ሁሉ ÷ ኃያላኑን ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ያህል ÷ ጠራቢዎችና ፡ ብረት ፡ ሠራተኞችም ፡ አንድ ፡ ሺህ ÷ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ፲፯ ማረከ ። የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የዮአኪንን ፡ አጎት ፡ ማታንያን ፡ በእርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠ ÷ ስሙንም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ብሎ ፡ ለወጠው ። ፲፰ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ አሚጣል ፡ የተባለች ፡ የልብና ፡ ሰው ፡ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ኢዮአቄምም ፡ እንዳደረገ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ። ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ፡ ፵፫ ፡ ፵፬ ፡ ፵፭ ፡ ፵፮ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ፡ ፵፱ ፡ ፶ ፡ ፶፩ ፡ ፶፪ ፡ ፶፫ ፡ ፶፬ ፡ ፶፭ ፡ ፶፮ ፡ ፶፯ ፡ ፶፰ ፡ ፶፱ ፡ ፷ ፡ ፷፩ ፡ ፷፪ ፡ ፷፫ ፡ ፷፬ ፡ ፷፭ ፡ ፷፮ ፡ ፷፯ ፡ ፷፰ ፡ ፷፱ ፡ ፸ ፡ ፸፩ ፡ ፸፪ ፡ ፸፫ ፡ ፸፬ ፡ ፸፭ ፡ ፸፮ ፡ ፸፯ ፡ ፸፰ ፡ ፸፱ ፡ ፹ ፡ ፹፩ ፡ ፹፪ ፡ ፹፫ ፡ ፹፬ ፡ ፹፭ ፡ ፹፮ ፡ ፹፯ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ፺ ፡ ፺፩ ፡ ፺፪ ፡ ፺፫ ፡ ፺፬ ፡ ፺፭ ፡ ፺፮ ፡ ፺፯ ፡ ፺፰ ፡ ፺፱ ፡ ፻ ፡ ፻፩ ፡ ፻፪ ፡ ፻፫ ፡ ፻፬ ፡ ፻፭ ፡ ፻፮ ፡ ፻፯ ፡ ፻፰ ፡ ፻፱ ፡ ፻፲ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፲፪ ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፲፬ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፲፮ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፳ ፡ ፻፳፩ ፡ ፻፳፪ ፡ ፻፳፫ ፡ ፻፳፬ ፡ ፻፳፭ ፡ ፻፳፮ ፡ ፻፳፯ ፡ ፻፳፰ ፡ ፻፳፱ ፡ ፻፴ ፡ ፻፴፩ ፡ ፻፴፪ ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፬ ፡ ፻፴፭ ፡ ፻፴፮ ፡ ፻፴፯ ፡ ፻፴፰ ፡ ፻፴፱ ፡ ፻፵ ፡ ፻፵፩ ፡ ፻፵፪ ፡ ፻፵፫ ፡ ፻፵፬ ፡ ፻፵፭ ፡ ፻፵፮ ፡ ፻፵፯ ፡ ፻፵፰ ፡ ፻፵፱ ፡ ፻፶ ፡ ፻፶፩ ፡ ፻፶፪ ፡ ፻፶፫ ፡ ፻፶፬ ፡ ፻፶፭ ፡ ፻፶፮ ፡ ፻፶፯ ፡ ፻፶፰ ፡ ፻፶፱ ፡ ፻፷ ፡ ፻፷፩ ፡ ፻፷፪ ፡ ፻፷፫ ፡ ፻፷፬ ፡ ፻፷፭ ፡ ፻፷፮ ፡ ፻፷፯ ፡ ፻፷፰ ፡ ፻፷፱ ፡ ፻፸ ፡ ፻፸፩ ፡ ፻፸፪ ፡ ፻፸፫ ፡ ፻፸፬ ፡ ፻፸፭ ፡ ፻፸፮ ፡ ፻፸፯ ፡ ፻፸፰ ፡ ፻፸፱ ፡ ፻፹ ፡ ፻፹፩ ፡ ፻፹፪ ፡ ፻፹፫ ፡ ፻፹፬ ፡ ፻፹፭ ፡ ፻፹፮ ፡ ፻፹፯ ፡ ፻፹፰ ፡ ፻፹፱ ፡ ፻፺ ፡ ፻፺፩ ፡ ፻፺፪ ፡ ፻፺፫ ፡ ፻፺፬ ፡ ፻፺፭ ፡ ፻፺፮ ፡ ፻፺፯ ፡ ፻፺፰ ፡ ፻፺፱ ፡ ፪፻ ፡ ፪፻፩ ፡ ፪፻፪ ፡ ፪፻፫ ፡ ፪፻፬ ፡ ፪፻፭ ፡ ፪፻፮ ፡ ፪፻፯ ፡ ፪፻፰ ፡ ፪፻፱ ፡ ፪፻፲ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ፪፻፲፪ ፡ ፪፻፲፫ ፡ ፪፻፲፬ ፡ ፪፻፲፭ ፡ ፪፻፲፮ ፡ ፪፻፲፯ ፡ ፪፻፲፰ ፡ ፪፻፲፱ ፡ ፪፻፳ ፡ ፪፻፳፩ ፡ ፪፻፳፪ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ፪፻፳፬ ፡ ፪፻፳፭ ፡ ፪፻፳፮ ፡ ፪፻፳፯ ፡ ፪፻፳፰ ፡ ፪፻፳፱ ፡ ፪፻፴ ፡ ፪፻፴፩ ፡ ፪፻፴፪ ፡ ፪፻፴፫ ፡ ፪፻፴፬ ፡ ፪፻፴፭ ፡ ፪፻፴፮ ፡ ፪፻፴፯ ፡ ፪፻፴፰ ፡ ፪፻፴፱ ፡ ፪፻፵ ፡ ፪፻፵፩ ፡ ፪፻፵፪ ፡ ፪፻፵፫ ፡ ፪፻፵፬ ፡ ፪፻፵፭ ፡ ፪፻፵፮ ፡ ፪፻፵፯ ፡ ፪፻፵፰ ፡ ፪፻፵፱ ፡ ፪፻፶ ፡ ፪፻፶፩ ፡ ፪፻፶፪ ፡ ፪፻፶፫ ፡ ፪፻፶፬ ፡ ፪፻፶፭ ፡ ፪፻፶፮ ፡ ፪፻፶፯ ፡ ፪፻፶፰ ፡ ፪፻፶፱ ፡ ፪፻፷ ፡ ፪፻፷፩ ፡ ፪፻፷፪ ፡ ፪፻፷፫ ፡ ፪፻፷፬ ፡ ፪፻፷፭ ፡ ፪፻፷፮ ፡ ፪፻፷፯ ፡ ፪፻፷፰ ፡ ፪፻፷፱ ፡ ፪፻፸ ፡ ፪፻፸፩ ፡ ፪፻፸፪ ፡ ፪፻፸፫ ፡ ፪፻፸፬ ፡ ፪፻፸፭ ፡ ፪፻፸፮ ፡ ፪፻፸፯ ፡ ፪፻፸፰ ፡ ፪፻፸፱ ፡ ፪፻፹ ፡ ፪፻፹፩ ፡ ፪፻፹፪ ፡ ፪፻፹፫ ፡ ፪፻፹፬ ፡ ፪፻፹፭ ፡ ፪፻፹፮ ፡ ፪፻፹፯ ፡ ፪፻፹፰ ፡ ፪፻፹፱ ፡ ፪፻፺ ፡ ፪፻፺፩ ፡ ፪፻፺፪ ፡ ፪፻፺፫ ፡ ፪፻፺፬ ፡ ፪፻፺፭ ፡ ፪፻፺፮ ፡ ፪፻፺፯ ፡ ፪፻፺፰ ፡ ፪፻፺፱ ፡ ፫፻ ፡ ፫፻፩ ፡ ፫፻፪ ፡ ፫፻፫ ፡ ፫፻፬ ፡ ፫፻፭ ፡ ፫፻፮ ፡ ፫፻፯ ፡ ፫፻፰ ፡ ፫፻፱ ፡ ፫፻፲ ፡ ፫፻፲፩ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ፫፻፲፫ ፡ ፫፻፲፬ ፡ ፫፻፲፭ ፡ ፫፻፲፮ ፡ ፫፻፲፯ ፡ ፫፻፲፰ ፡ ፫፻፲፱ ፡ ፫፻፳ ፡ ፫፻፳፩ ፡ ፫፻፳፪ ፡ ፫፻፳፫ ፡ ፫፻፳፬ ፡ ፫፻፳፭ ፡ ፫፻፳፮ ፡ ፫፻፳፯ ፡ ፫፻፳፰ ፡ ፫፻፳፱ ፡ ፫፻፴ ፡ ፫፻፴፩ ፡ ፫፻፴፪ ፡ ፫፻፴፫ ፡ ፫፻፴፬ ፡ ፫፻፴፭ ፡ ፫፻፴፮ ፡ ፫፻፴፯ ፡ ፫፻፴፰ ፡ ፫፻፴፱ ፡ ፫፻፵ ፡ ፫፻፵፩ ፡ ፫፻፵፪ ፡ ፫፻፵፫ ፡ ፫፻፵፬ ፡ ፫፻፵፭ ፡ ፫፻፵፮ ፡ ፫፻፵፯ ፡ ፫፻፵፰ ፡ ፫፻፵፱ ፡ ፫፻፶ ፡ ፫፻፶፩ ፡ ፫፻፶፪ ፡ ፫፻፶፫ ፡ ፫፻፶፬ ፡ ፫፻፶፭ ፡ ፫፻፶፮ ፡ ፫፻፶፯ ፡ ፫፻፶፰ ፡ ፫፻፶፱ ፡ ፫፻፷ ፡ ፫፻፷፩ ፡ ፫፻፷፪ ፡ ፫፻፷፫ ፡ ፫፻፷፬ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ፫፻፷፮ ፡ ፫፻፷፯ ፡ ፫፻፷፰ ፡ ፫፻፷፱ ፡ ፫፻፸ ፡ ፫፻፸፩ ፡ ፫፻፸፪ ፡ ፫፻፸፫ ፡ ፫፻፸፬ ፡ ፫፻፸፭ ፡ ፫፻፸፮ ፡ ፫፻፸፯ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ፫፻፸፱ ፡ ፫፻፹ ፡ ፫፻፹፩ ፡ ፫፻፹፪ ፡ ፫፻፹፫ ፡ ፫፻፹፬ ፡ ፫፻፹፭ ፡ ፫፻፹፮ ፡ ፫፻፹፯ ፡ ፫፻፹፰ ፡ ፫፻፹፱ ፡ ፫፻፺ ፡ ፫፻፺፩ ፡ ፫፻፺፪ ፡ ፫፻፺፫ ፡ ፫፻፺፬ ፡ ፫፻፺፭ ፡ ፫፻፺፮ ፡ ፫፻፺፯ ፡ ፫፻፺፰ ፡ ፫፻፺፱ ፡ ፬፻ ፡ ፬፻፩ ፡ ፬፻፪ ፡ ፬፻፫ ፡ ፬፻፬ ፡ ፬፻፭ ፡ ፬፻፮ ፡ ፬፻፯ ፡ ፬፻፰ ፡ ፬፻፱ ፡ ፬፻፲ ፡ ፬፻፲፩ ፡ ፬፻፲፪ ፡ ፬፻፲፫ ፡ ፬፻፲፬ ፡ ፬፻፲፭ ፡ ፬፻፲፮ ፡ ፬፻፲፯ ፡ ፬፻፲፰ ፡ ፬፻፲፱ ፡ ፬፻፳ ፡ ፬፻፳፩ ፡ ፬፻፳፪ ፡ ፬፻፳፫ ፡ ፬፻፳፬ ፡ ፬፻፳፭ ፡ ፬፻፳፮ ፡ ፬፻፳፯ ፡ ፬፻፳፰ ፡ ፬፻፳፱ ፡ ፬፻፴ ፡ ፬፻፴፩ ፡ ፬፻፴፪ ፡ ፬፻፴፫ ፡ ፬፻፴፬ ፡ ፬፻፴፭ ፡ ፬፻፴፮ ፡ ፬፻፴፯ ፡ ፬፻፴፰ ፡ ፬፻፴፱ ፡ ፬፻፵ ፡ ፬፻፵፩ ፡ ፬፻፵፪ ፡ ፬፻፵፫ ፡ ፬፻፵፬ ፡ ፬፻፵፭ ፡ ፬፻፵፮ ፡ ፬፻፵፯ ፡ ፬፻፵፰ ፡ ፬፻፵፱ ፡ ፬፻፶ ፡ ፬፻፶፩ ፡ ፬፻፶፪ ፡ ፬፻፶፫ ፡ ፬፻፶፬ ፡ ፬፻፶፭ ፡ ፬፻፶፮ ፡ ፬፻፶፯ ፡ ፬፻፶፰ ፡ ፬፻፶፱ ፡ ፬፻፷ ፡ ፬፻፷፩ ፡ ፬፻፷፪ ፡ ፬፻፷፫ ፡ ፬፻፷፬ ፡ ፬፻፷፭ ፡ ፬፻፷፮ ፡ ፬፻፷፯ ፡ ፬፻፷፰ ፡ ፬፻፷፱ ፡ ፬፻፸ ፡ ፬፻፸፩ ፡ ፬፻፸፪ ፡ ፬፻፸፫ ፡ ፬፻፸፬ ፡ ፬፻፸፭ ፡ ፬፻፸፮ ፡ ፬፻፸፯ ፡ ፬፻፸፰ ፡ ፬፻፸፱ ፡ ፬፻፹ ፡ ፬፻፹፩ ፡ ፬፻፹፪ ፡ ፬፻፹፫ ፡ ፬፻፹፬ ፡ ፬፻፹፭ ፡ ፬፻፹፮ ፡ ፬፻፹፯ ፡ ፬፻፹፰ ፡ ፬፻፹፱ ፡ ፬፻፺ ፡ ፬፻፺፩ ፡ ፬፻፺፪ ፡ ፬፻፺፫ ፡ ፬፻፺፬ ፡ ፬፻፺፭ ፡ ፬፻፺፮ ፡ ፬፻፺፯ ፡ ፬፻፺፰ ፡ ፬፻፺፱ ፡ ፭፻ ፡ ፭፻፩ ፡ ፭፻፪ ፡ ፭፻፫ ፡ ፭፻፬ ፡ ፭፻፭ ፡ ፭፻፮ ፡ ፭፻፯ ፡ ፭፻፰ ፡ ፭፻፱ ፡ ፭፻፲ ፡ ፭፻፲፩ ፡ ፭፻፲፪ ፡ ፭፻፲፫ ፡ ፭፻፲፬ ፡ ፭፻፲፭ ፡ ፭፻፲፮ ፡ ፭፻፲፯ ፡ ፭፻፲፰ ፡ ፭፻፲፱ ፡ ፭፻፳ ፡ ፭፻፳፩ ፡ ፭፻፳፪ ፡ ፭፻፳፫ ፡ ፭፻፳፬ ፡ ፭፻፳፭ ፡ ፭፻፳፮ ፡ ፭፻፳፯ ፡ ፭፻፳፰ ፡ ፭፻፳፱ ፡ ፭፻፴ ፡ ፭፻፴፩ ፡ ፭፻፴፪ ፡ ፭፻፴፫ ፡ ፭፻፴፬ ፡ ፭፻፴፭ ፡ ፭፻፴፮ ፡ ፭፻፴፯ ፡ ፭፻፴፰ ፡ ፭፻፴፱ ፡ ፭፻፵ ፡ ፭፻፵፩ ፡ ፭፻፵፪ ፡ ፭፻፵፫ ፡ ፭፻፵፬ ፡ ፭፻፵፭ ፡ ፭፻፵፮ ፡ ፭፻፵፯ ፡ ፭፻፵፰ ፡ ፭፻፵፱ ፡ ፭፻፶ ፡ ፭፻፶፩ ፡ ፭፻፶፪ ፡ ፭፻፶፫ ፡ ፭፻፶፬ ፡ ፭፻፶፭ ፡ ፭፻፶፮ ፡ ፭፻፶፯ ፡ ፭፻፶፰ ፡ ፭፻፶፱ ፡ ፭፻፷ ፡ ፭፻፷፩ ፡ ፭፻፷፪ ፡ ፭፻፷፫ ፡ ፭፻፷፬ ፡ ፭፻፷፭ ፡ ፭፻፷፮ ፡ ፭፻፷፯ ፡ ፭፻፷፰ ፡ ፭፻፷፱ ፡ ፭፻፸ ፡ ፭፻፸፩ ፡ ፭፻፸፪ ፡ ፭፻፸፫ ፡ ፭፻፸፬ ፡ ፭፻፸፭ ፡ ፭፻፸፮ ፡ ፭፻፸፯ ፡ ፭፻፸፰ ፡ ፭፻፸፱ ፡ ፭፻፹ ፡ ፭፻፹፩ ፡ ፭፻፹፪ ፡ ፭፻፹፫ ፡ ፭፻፹፬ ፡ ፭፻፹፭ ፡ ፭፻፹፮ ፡ ፭፻፹፯ ፡ ፭፻፹፰ ፡ ፭፻፹፱ ፡ ፭፻፺ ፡ ፭፻፺፩ ፡ ፭፻፺፪ ፡ ፭፻፺፫ ፡ ፭፻፺፬ ፡ ፭፻፺፭ ፡ ፭፻፺፮ ፡ ፭፻፺፯ ፡ ፭፻፺፰ ፡ ፭፻፺፱ ፡ ፮፻ ፡ ፮፻፩ ፡ ፮፻፪ ፡ ፮፻፫ ፡ ፮፻፬ ፡ ፮፻፭ ፡ ፮፻፮ ፡ ፮፻፯ ፡ ፮፻፰ ፡ ፮፻፱ ፡ ፮፻፲ ፡ ፮፻፲፩ ፡ ፮፻፲፪ ፡ ፮፻፲፫ ፡ ፮፻፲፬ ፡ ፮፻፲፭ ፡ ፮፻፲፮ ፡ ፮፻፲፯ ፡ ፮፻፲፰ ፡ ፮፻፲፱ ፡ ፮፻፳ ፡ ፮፻፳፩ ፡ ፮፻፳፪ ፡ ፮፻፳፫ ፡ ፮፻፳፬ ፡ ፮፻፳፭ ፡ ፮፻፳፮ ፡ ፮፻፳፯ ፡ ፮፻፳፰ ፡ ፮፻፳፱ ፡ ፮፻፴ ፡ ፮፻፴፩ ፡ ፮፻፴፪ ፡ ፮፻፴፫ ፡ ፮፻፴፬ ፡ ፮፻፴፭ ፡ ፮፻፴፮ ፡ ፮፻፴፯ ፡ ፮፻፴፰ ፡ ፮፻፴፱ ፡ ፮፻፵ ፡ ፮፻፵፩ ፡ ፮፻፵፪ ፡ ፮፻፵፫ ፡ ፮፻፵፬ ፡ ፮፻፵፭ ፡ ፮፻፵፮ ፡ ፮፻፵፯ ፡ ፮፻፵፰ ፡ ፮፻፵፱ ፡ ፮፻፶ ፡ ፮፻፶፩ ፡ ፮፻፶፪ ፡ ፮፻፶፫ ፡ ፮፻፶፬ ፡ ፮፻፶፭ ፡ ፮፻፶፮ ፡ ፮፻፶፯ ፡ ፮፻፶፰ ፡ ፮፻፶፱ ፡ ፮፻፷ ፡ ፮፻፷፩ ፡ ፮፻፷፪ ፡ ፮፻፷፫ ፡ ፮፻፷፬ ፡ ፮፻፷፭ ፡ ፮፻፷፮ ፡ ፮፻፷፯ ፡ ፮፻፷፰ ፡ ፮፻፷፱ ፡ ፮፻፸ ፡ ፮፻፸፩ ፡ ፮፻፸፪ ፡ ፮፻፸፫ ፡ ፮፻፸፬ ፡ ፮፻፸፭ ፡ ፮፻፸፮ ፡ ፮፻፸፯ ፡ ፮፻፸፰ ፡ ፮፻፸፱ ፡ ፮፻፹ ፡ ፮፻፹፩ ፡ ፮፻፹፪ ፡ ፮፻፹፫ ፡ ፮፻፹፬ ፡ ፮፻፹፭ ፡ ፮፻፹፮ ፡ ፮፻፹፯ ፡ ፮፻፹፰ ፡ ፮፻፹፱ ፡ ፮፻፺ ፡ ፮፻፺፩ ፡ ፮፻፺፪ ፡ ፮፻፺፫ ፡ ፮፻፺፬ ፡ ፮፻፺፭ ፡ ፮፻፺፮ ፡ ፮፻፺፯ ፡ ፮፻፺፰ ፡ ፮፻፺፱ ፡ ፯፻ ፡ ፯፻፩ ፡ ፯፻፪ ፡ ፯፻፫ ፡ ፯፻፬ ፡ ፯፻፭ ፡ ፯፻፮ ፡ ፯፻፯ ፡ ፯፻፰ ፡ ፯፻፱ ፡ ፯፻፲ ፡ ፯፻፲፩ ፡ ፯፻፲፪ ፡ ፯፻፲፫ ፡ ፯፻፲፬ ፡ ፯፻፲፭ ፡ ፯፻፲፮ ፡ ፯፻፲፯ ፡ ፯፻፲፰ ፡ ፯፻፲፱ ፡ ፯፻፳ ፡ ፯፻፳፩ ፡ ፯፻፳፪ ፡ ፯፻፳፫ ፡ ፯፻፳፬ ፡ ፯፻፳፭ ፡ ፯፻፳፮ ፡ ፯፻፳፯ ፡ ፯፻፳፰ ፡ ፯፻፳፱ ፡ ፯፻፴ ፡ ፯፻፴፩ ፡ ፯፻፴፪ ፡ ፯፻፴፫ ፡ ፯፻፴፬ ፡ ፯፻፴፭ ፡ ፯፻፴፮ ፡ ፯፻፴፯ ፡ ፯፻፴፰ ፡ ፯፻፴፱ ፡ ፯፻፵ ፡ ፯፻፵፩ ፡ ፯፻፵፪ ፡ ፯፻፵፫ ፡ ፯፻፵፬ ፡ ፯፻፵፭ ፡ ፯፻፵፮ ፡ ፯፻፵፯ ፡ ፯፻፵፰ ፡ ፯፻፵፱ ፡ ፯፻፶ ፡ ፯፻፶፩ ፡ ፯፻፶፪ ፡ ፯፻፶፫ ፡ ፯፻፶፬ ፡ ፯፻፶፭ ፡ ፯፻፶፮ ፡ ፯፻፶፯ ፡ ፯፻፶፰ ፡ ፯፻፶፱ ፡ ፯፻፷ ፡ ፯፻፷፩ ፡ ፯፻፷፪ ፡ ፯፻፷፫ ፡ ፯፻፷፬ ፡ ፯፻፷፭ ፡ ፯፻፷፮ ፡ ፯፻፷፯ ፡ ፯፻፷፰ ፡ ፯፻፷፱ ፡ ፯፻፸ ፡ ፯፻፸፩ ፡ ፯፻፸፪ ፡ ፯፻፸፫ ፡ ፯፻፸፬ ፡ ፯፻፸፭ ፡ ፯፻፸፮ ፡ ፯፻፸፯ ፡ ፯፻፸፰ ፡ ፯፻፸፱ ፡ ፯፻፹ ፡ ፯፻፹፩ ፡ ፯፻፹፪ ፡ ፯፻፹፫ ፡ ፯፻፹፬ ፡ ፯፻፹፭ ፡ ፯፻፹፮ ፡ ፯፻፹፯ ፡ ፯፻፹፰ ፡ ፯፻፹፱ ፡ ፯፻፺ ፡ ፯፻፺፩ ፡ ፯፻፺፪ ፡ ፯፻፺፫ ፡ ፯፻፺፬ ፡ ፯፻፺፭ ፡ ፯፻፺፮ ፡ ፯፻፺፯ ፡ ፯፻፺፰ ፡ ፯፻፺፱ ፡ ፰፻ ፡ ፰፻፩ ፡ ፰፻፪ ፡ ፰፻፫ ፡ ፰፻፬ ፡ ፰፻፭ ፡ ፰፻፮ ፡ ፰፻፯ ፡ ፰፻፰ ፡ ፰፻፱ ፡ ፰፻፲ ፡ ፰፻፲

ተቀመጡ ÷ ለባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ÷ መልካምም ፡ ይሆንላችኋል ፡ ብሎ ፡ ለእነርሱና ፡
፳፭፡ ለሰዎቻቸው ፡ ማለላቸው ። በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ግን ፡ የመንግሥት ፡ ዘር ፡ የነበረ ፡ የኤሊሳማ ፡ ልጅ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ንዶልያስንና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በምጽጳ ፡ የነበሩትን ፡ አይሁድንና ፡ ከለዳውያንን ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ መቱ
፳፮፡ አቸው ። ከለዳውያንንም ፡ ፈርተው ፡ ነበርና ፡ ከታናሹ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የጭፍሮቹም ፡ አለቆች ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መጡ ።
፳፯፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በአ
ሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሀያ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ዮርማሮ
ዴቅ ፡ በነገሠ ፡ በእንደኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪንን ፡ ከወህኒ ፡ አወጣው ፤ በፍ ፳፰፡
ቅርም ፡ ተናገረው ÷ ዙፋኑንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በባቢሎን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ በላይ ፡
አደረገለት ። በወህኒም ፡ ውስጥ ፡ ለብሶት ፡ የነ ፳፱፡
በረውን ፡ ልብስ ፡ ለወጠለት ፡ ዮአኪንም ፡ በሕ
ይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ እን ፴፡
ጀራ ፡ ይበላ ፡ ነበር ። ንጉሡም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የዘወትር ፡ ቀለብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፡፩፡ አዳም ÷ ሴት ÷ ሄኖስ ÷ ቃይናን ÷ መላል
፪፡ ኤል ÷ ያሬድ ÷ ሄኖክ ÷ ማቱሳላ ÷ ላሜሕ ÷
፬፡ ኖኅ ÷ ሴም ÷ ካም ÷ ያፌት ።
፭፡ የያፌት ፡ ልጆች ፡ ጋሜር ÷ ማጎግ ÷ ማዲ ÷
፮፡ ያዋን ÷ ቶቤል ÷ ሞሳሕ ÷ ቴራስ ። የጋሜርም ፡
፯፡ ልጆች ፡ አስከናዝ ÷ ሪፋት ÷ ቴርጋማ ። የያ
ዋንም ፡ ልጆች ፡ ኤሊሳ ÷ ተርሴስ ÷ ኪቲም ÷
ዶዶኢ ።
፰፡ የካምም ፡ ልጆች ፡ ኩሽ ÷ ምጽራይም ÷ ፉጥ ÷
፱፡ ከነዓን ። የኩሽም ፡ ልጆች ፡ ሳባ ÷ ኤውላጥ ÷
ሰብታ ÷ ራዕማ ÷ ሰብቃታ ። የራዕማም ፡ ልጆች ፡
፲፡ ሳባ ÷ ድዳን ። ኩሽም ፡ ናምሩድን ፡ ወለደ ፤
እርሱም ፡ በምድር ፡ ኃያል ፡ መሆንን ፡ ጀመረ ።
፲፩፡ ምጽራይምም ፡ ሉዲምን ÷ ዐናሚምን ÷ ላህ
፲፪፡ ቢምን ÷ ነፍተሂምን ÷ ፈትሩሲምን ÷ ፍልስጥ
ኤማውያን ፡ የወጡበትን ፡ ከስሉሂምን ÷ ከፍ
፲፫፡ ቶፊምን ፡ ወለደ ። ከነዓንም ፡ የበኵር ፡ ልጁን ፡
፲፬፡ ሲዶንን ÷ ኬጢን ÷ ኢያቡሳዊውን ÷ አሞራዊ
፲፭፡ ውን ÷ ጌርጌሳዊውን ÷ ኢዊያዊውን ÷ ዐርከዊ
፲፮፡ ውን ÷ ሲንያዊውን ÷ ሐራደዎንን ÷ ዕማራም
ንን ÷ አማቲን ፡ ወለደ ።
፲፯፡ የሴም ፡ ልጆች ፡ ኤላም ÷ አሦር ÷ አርፋክ
ስድ ÷ ሉድ ÷ አራም ÷ ዑፅ ፡ ሁል ÷ ጌቴር ÷
፲፰፡ ሞሳሕ ። አርፋክስድም ፡ ቃይንምን ፡ ወለደ ፤
ቃይንምም ፡ ሳላን ፡ ወለደ ፤ ሳላም ፡ ዔቦርን ፡
፲፱፡ ወለደ ። ለዔቦርም ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ተወለዱ
ለት ፤ በዘመኑ ፡ ምድር ፡ ተከፍላለችና ፡ የእን
ደኛው ፡ ስም ፡ ፋሌቅ ፡ ተባለ ፤ የወንድሙም ፡
፳፡ ስም ፡ ዮቅጣን ፡ ነበረ ። ዮቅጣንም ፡ አልሞዳ
፳፩፡ ድን ÷ ሣሌፍን ÷ ሐሰረሞትን ÷ ያራሕን ÷ ሀዶራ
፳፪፡ ምን ÷ አውዛልን ÷ ደቅላን ÷ ዖባልን ÷ አቢማ
፳፫፡ ኤልን ÷ ሳባን ÷ አፊርን ÷ ኤውላጥን ÷ ዮባብን ፡
ወለደ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፡
ነበሩ ።
፳፬፡ ሴም ÷ አርፋክስድ ÷ ሳላ ÷ ዔቦር ÷ ፋሌቅ ÷ ፳፭፡፳፮፡
ራግው ÷ ሴሮሕ ÷ ናኮር ÷ ታራ ÷ አብርሃም ፡ የተ ፳፯፡
ባለ ፡ አብራም ።
የአብርሃምም ፡ ልጆች ፡ ይስሐቅ ÷ እስማ ፳፰፡
ኤል ። ትውልዳቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ፳፱፡
የእስማኤል ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ነባዮት ፤ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ቄዳር ÷ ነብዳኤል ÷ መብሳም ÷ ማስ ፴፡
ማዕ ÷ ዱማ ÷ ማሣ ÷ ኩዳን ÷ ቴማን ÷ ኢጡር ÷ ፴፩፡
ናፈስ ÷ ቄድማ ። እነዚህ ፡ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡
ናቸው ።
የአብርሃምም ፡ ገረድ ፡ የኬጡራ ፡ ልጆች ፡ ፴፪፡
ዘምራን ÷ ዮቅሳን ÷ ሜዳን ÷ ምድያም ÷ የስ
ቦቅ ÷ ስዌሕ ። የዮቅሳንም ፡ ልጆች ፡ ሳባ ÷
ድዳን ። የምድያምም ፡ ልጆች ፡ ጌፌር ÷ ዔፌር ÷ ፴፫፡
ሄኖኅ ÷ አቢዳዕ ÷ ኤልዳኅ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡
የኬጡራ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።
አብርሃምም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ። የይስሐ ፴፬፡
ቅም ፡ ልጆች ፡ ዔሳውና ፡ እስራኤል ፡ ነበሩ ።
የዔሳው ፡ ልጆች ፡ ኤልፋዝ ÷ ራጉኤል ÷ ፴፭፡
የውስ ÷ የዕላም ÷ ቆሬ ። የኤልፋዝ ፡ ልጆች ፡ ፴፮፡
ቴማን ÷ አማር ÷ ስፎ ÷ ጎቶም ÷ ቄኔዝ ፡ ቲም
ናዕ ÷ አማሌቅ ። የራጉኤል ፡ ልጆች ፡ ናሖት ÷ ፴፯፡
ዛራ ÷ ሻማ ÷ ሚዛህ ።
የሴይርም ፡ ልጆች ፡ ሎጣን ÷ ሦባል ÷ ጽብ ፴፰፡
ዖን ÷ ዓና ÷ ዲሶን ÷ ኤጽር ÷ ዲሳን ። የሎጣ
ንም ፡ ልጆች ፡ ሖሪ ÷ ሄማም ፡ ቲምናዕ ፡ የሎጣን ፡
እኅት ፡ ነበረች ። የሦባል ፡ ልጆች ፡ ዓልዋን ÷ ማኔ ፴፱፡
ሐት ÷ ዔባል ÷ ስፎ ÷ አውናም ። የጽብዖንም ፡
ልጆች ፡ አያ ÷ ዓና ። የዓና ፡ ልጅ ፡ ዲሶን ። የዲሶ
ንም ፡ ልጆች ፡ ሔምዳን ÷ ኤስባን ÷ ይትራን ÷
ክራን ። የኤጽር ፡ ልጆች ፡ ቢልሐን ÷ ዛዕዋን ÷ ፵፪፡
ዓቃን ። የዲሳን ፡ ልጆች ፡ ዑዶ ÷ አራን ።
በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ንጉሥ ፡ ፵፫፡
ሳይነግሥ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ የነገሡ ፡ ነገ
ሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የብዖር ፡ ልጅ ፡
ባላቅ ፡ የከተማይቱም ፡ ስም ፡ ዲንሃባ ፡ ነበረ ።

፵፱፡ ባላቅም ፡ ሞተ ÷ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ የባሰራ ፡
፶፡ ሰው ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ኢዮባብ ፡ ነገሠ ። ኢዮባ
ብም ፡ ሞተ ÷ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ የቴማን ፡
፶፩፡ አገር ፡ ሰው ፡ ሑሳም ፡ ነገሠ ። ሑሳምም ፡ ሞተ ÷
በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ምድያ
ምን ፡ የመታው ፡ የባዳድ ፡ ልጅ ፡ ሃዳድ ፡ ነገሠ ፤
፶፪፡ የከተማይቱም ፡ ስም ፡ ዓዊት ፡ ነበረ ። ሃዳድም ፡
ሞተ ÷ በእርሱም ፡ ፋንታ ፡ የመሥፈታ ፡ ሰው ፡
፶፫፡ ሣምላ ፡ ነገሠ ። ሣምላም ፡ ሞተ ÷ በእርሱም ፡
ፋንታ ፡ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ያለችው ፡ የረሆቦት ፡
፶፬፡ ሰው ፡ ሳኡል ፡ ነገሠ ። ሳኡልም ፡ ሞተ ÷ በእ
ርሱም ፡ ፋንታ ፡ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ በኣልሐናን ፡
፶፭፡ ነገሠ ። በኣልሐናንም ፡ ሞተ ÷ በእርሱም ፡
ፋንታ ፡ ሃዳድ ፡ ነገሠ ፤ የከተማይቱም ፡ ስም ፡
ፋው ፡ ነበረ ፤ ሚስቱም ፡ የሜዛሃብ ፡ ልጅ ፡ የመ
ጥሬድ ፡ ልጅ ፡ መሄጣብኤል ፡ ነበረች ፤ ሃዳድም ፡
ሞተ ።
፶፩፡ የኤዶምያስም ፡ አለቆች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤
ቲምናዕ ፡ አለቃ ÷ ዓልዋ ፡ አለቃ ÷ የቴት ፡ አለቃ ÷
፶፪፡ አሀሊባማ ፡ አለቃ ÷ ኤላ ፡ አለቃ ÷ ፊኖን ፡
፶፫፡ አለቃ ÷ ቄኔዝ ፡ አለቃ ÷ ቴማን ፡ አለቃ ÷ ሚብ
፶፬፡ ሳር ፡ አለቃ ÷ መግዲኤል ፡ አለቃ ÷ ዒራም ፡
አለቃ ፤ እነዚህ ፡ የኤዶምያስ ፡ አለቆች ፡ ነበሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡
ሮቤል ÷ ስምዖን ÷ ሌዊ ÷ ይሁዳ ÷ ይሳኮር ÷ ዛብ
፪፡ ሎን ÷ ዳን ÷ ዮሴፍ ÷ ብንያም ÷ ንፍታሌም ÷
ጋድ ÷ አሴር ።
፫፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዔር ÷ አውናን ÷ ሴሎም ፤
እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ከከነዓናዊቱ ፡ ከሱዋ ፡ ልጅ ፡
ተወለዱለት ። የይሁዳም ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ዔር ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፤ ገደለውም ።
፬፡ ምራቱም ፡ ትዕማር ፡ ፋሬስንና ፡ ዛራን ፡ ወለደ
፭፡ ችለት ። የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አምስት ፡
ነበሩ ።
፮፡ የፋሬስ ፡ ልጆች ፡ ኤስሮም ÷ ሐሙል ።
፯፡ የዛራም ፡ ልጆች ፡ ዘምሪ ÷ ኤታን ÷ ሄማን ÷
፰፡ ከልኮል ÷ ዳራ ፡ ሁሉም ፡ አምስት ፡ ነበሩ ። የከ
ርሚም ፡ ልጅ ፡ አስራሌልን ፡ የስጨነቀ ÷ እር
ሙንም ፡ ሰርቆ ፡ የበደለ ፡ አካን ፡ ነበረ ። የኤታ
ንም ፡ ልጅ ፡ አዛርያ ፡ ነበረ ።
፱፡ ለኤስሮም ፡ የተወለዱለት ፡ ልጆች ፡ ይረሕም
፲፡ ኤል ÷ አራም ÷ ካልብ ፡ ነበሩ ። አራምም ፡ አሚ
ናዳብን ፡ ወለደ ፤ አሚናዳብም ፡ የይሁዳን ፡
፲፩፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ፤ ነአሶንም ፡
ሰልሞንን ፡ ወለደ ፤ ሰልሞንም ፡ ቦዔዝን ፡ ወለደ ፤
፲፪፡ ቦዔዝም ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ፤ ኢዮቤድም ፡
፲፫፡ እሴይን ፡ ወለደ ። እሴይም ፡ የበኵር ፡ ልጁን ፡
ኤልያብን ÷ ሁለተኛውንም ፡ አሚናዳብን ÷ ሦስ
፲፬፡ ተኛውንም ፡ ነታንኤልን ÷ አራተኛውንም ፡ ናትናኤ
፲፭፡ ልን ÷ አምስተኛውንም ፡ ራዳይን ÷ ስድስተኛ
ውንም ፡ አሳምን ÷ ሰባተኛውንም ፡ ዳዊትን ፡
፲፮፡ ወለደ ፤ እኅቶቻቸውም ፡ ጽሩያና ፡ አቢግያ ፡
ነበሩ ። የጽሩያም ፡ ልጆች ፡ አቢሳ ÷ ኢዮአብ ÷
አሣሄል ፡ ሦስቱ ፡ ነበሩ ። አቢግያም ፡ አሜሳ ፲፯፡
ይን ፡ ወለደች ፤ የአሜሳይም ፡ አባት ፡ እስማኤ
ላዊው ፡ ዬቴር ፡ ነበረ ።
፲፰፡ የኤስሮምም ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ ከሚስቱ ፡ ከዓ ፲፱፡
ዙባ ፡ ከይሪዖትም ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፤ ልጆች
፲፱፡ ዋም ፡ ያሰር ÷ ሶባብ ÷ አርዶን ፡ ነበሩ ። ዓዙ
ባም ፡ ሞተች ÷ ካሌብም ፡ ኤፍራታን ፡ አገባ ፤
እርስዋም ፡ ሆርን ፡ ወለደችለት ። ሆርም ፡ ኡሪን ፡ ፳፡
ወለደ ÷ ኡሪም ፡ ባስልኤልን ፡ ወለደ ።
፳፩፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ኤስሮም ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ ፳፪፡
በሆነው ፡ ጊዜ ፡ ወዳገባት ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ አባት ፡
ወደ ፡ ማኪር ፡ ልጅ ፡ ገባ ፤ ሠጉብንም ፡ ወለደ
ችለት ። ሠጉብም ፡ ኢያዕርን ፡ ወለደ ፤ ለእር ፳፫፡
ሱም ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ሀያ ፡ ሦስት ፡ ከተሞች ፡
ነበሩት ። ጌሹርና ፡ አራምም ፡ የኢያዕርን ፡ ከተ
ሞች ፡ ከቄናትና ፡ ከመንደሮችዋ ፡ ጋር ፡ ስድሳ
ውን ፡ ከተሞች ፡ ወሰዱባቸው ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡
የገለዓድ ፡ አባት ፡ የማኪር ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።
፳፬፡ ኤስሮምም ፡ በካሌብ ፡ ኤፍራታ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
የኤስሮም ፡ ሚስት ፡ አቢያ ፡ የቴቁሔን ፡ አባት ፡
አሹሑርን ፡ ወለደችለት ።
፳፭፡ የኤስሮምም ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ የይረሕምኤል ፡
ልጆች ፡ በኵሩ ፡ ራም ÷ ቡናህ ÷ አሬን ÷ አጼም ÷
አኪያ ፡ ነበሩ ። ለይረሕምኤልም ፡ ዓጣራ ፡ የተ ፳፮፡
ባለች ፡ ሌላ ፡ ሚስት ፡ ነበረችው ፤ እርስዋም ፡
የአናም ፡ እናት ፡ ነበረች ። የይረሕምኤል ፡ የበ ፳፯፡
ኵሩ ፡ የራም ፡ ልጆች ፡ መዓዝ ÷ ያሚን ÷ ዔቄር ፡
ነበሩ ። የአናምም ፡ ልጆች ፡ ሾማይና ፡ ያዳ ፡ ፳፰፡
ነበሩ ። የሾማይ ፡ ልጆች ፡ ናዳብና ፡ አቢሱር ፡
ነበሩ ። የአቢሱርም ፡ ሚስት ፡ አቢካኢል ፡ ነበ ፳፱፡
ረች ፤ አሕባንንና ፡ ሞሊድን ፡ ወለደችለት ። የና ፴፡
ዳብም ፡ ልጆች ፡ ሴሌድና ፡ አፋይም ፡ ነበሩ ፤
ሴሌድም ፡ ያለ ፡ ልጆች ፡ ሞተ ። የአፋይምም ፡ ፴፩፡
ልጅ ፡ ይሽዒ ። የይሽዒም ፡ ልጅ ፡ ሶሳን ÷ የሶሳ
ንም ፡ ልጅ ፡ አሕላይ ፡ ነበረ ። የሾማይም ፡ ወን ፴፪፡
ድም ፡ የያዳ ፡ ልጆች ፡ ዬቴርና ፡ ዮናታን ፡ ነበሩ ፤
ዬቴርም ፡ ያለ ፡ ልጆች ፡ ሞተ ። የዮናታንም ፡ ፴፫፡
ልጆች ፡ ፈሌትና ፡ ዛዛ ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ የይረ
ሕምኤል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ። ለሶሳንም ፡ ሴቶች ፡ ፴፬፡
ልጆች ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩ
ትም ፤ ለሶሳንም ፡ ኢዮዬል ፡ የተባለ ፡ ግብጻዊ ፡
አገልጋይ ፡ ነበረው ። ሶሳንም ፡ ለአገልጋዩ ፴፭፡
ለኢዮዬል ፡ ልጁን ፡ አጋበት ÷ እርስዋም ፡ ዓታ
ይን ፡ ወለደችለት ። ዓታይም ፡ ናታንን ፡ ወለደ ፤ ፴፮፡
ናታንም ፡ ዛባድን ፡ ወለደ ፤ ዛባድም ፡ ኤፍላ ፴፯፡
ልን ፡ ወለደ ፤ ኤፍላልም ፡ ዖቤድን ፡ ወለደ ፤
ዖቤድም ፡ ኢዩን ፡ ወለደ ፤ ኢዩም ፡ ዓዛርያስን ፡ ፴፰፡
ወለደ ፤ ዓዛርያስም ፡ ኬሌስን ፡ ወለደ ፤ ኬሌስም ፡ ፴፱፡
ኤልዓሣን ፡ ወለደ ፤ ኤልዓሣም ፡ ሲስማይን ፡ ፵፡
ወለደ ፤ ሲስማይም ፡ ሰሎምን ፡ ወለደ ፤ ሰሎ ፵፩፡
ምም ፡ የቃምያን ፡ ወለደ ፤ የቃምያም ፡ ኤሊሳ
ማን ፡ ወለደ ።
የይረሕምኤልም ፡ ወንድም ፡ የካሌብ ፡ ልጆች ፡ ፵፪፡